# Contents


ክፍል ስድስት ........ 4

የፍትህ አስተዳደር ........ 4

ሀ/ ፍርድ ቤቶች ........ 4

ስለፍርድ ቤቶች የዳኝነት ገንዘብ አከፋፈል የወጣ የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ........ 4

ቁጥር 177/1945 ዓ.ም ........ 4

አዋጅ ቁጥር 25/1988 ........ 31

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ........ 31

አዋጅ ቁጥር 188/1992 ........ 47

የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን አቋም ለማጠናከር የወጣ አዋጅ ........ 47

አዋጅ ቁጥር 322/1995 ........ 56

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትን በተወሰኑ ክልሎች ለማደራጀት የወጣ አዋጅ ........ 56

አዋጅ ቁጥር 684/2002 ........ 57

የተሻሻለው የፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ማቋቋሚያ አዋጅ ........ 57

ለ/ ልዩ የስነስርዓት ህጎች እና የወንጀል ምስክሮች ........ 65

አዋጅ ቁጥር 434/1997 ........ 65

የተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ........ 65

አዋጅ ቁጥር 699/2003 ........ 91

የወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ አዋጅ ........ 91

ደንብ ቁጥር 371/2008 ........ 107

ስለወንጀል ምስክሮች የውሎ አበልና የጉዞ ወጪ አከፋፈል የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 107

ደንብ ቁጥር 306/2006 ዓ.ም ........ 112

የሽብርተኛ ሀብት የሚታገድበት ሥነ-ሥርዓት ለመወሰን ወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 112

ሐ/ ታራሚዎች .......... 130

ደንብ ቁጥር 138/1999 .......... 135

ስለፌዴራል ታራሚዎች አያያዝ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ .......... 135

አዋጅ ቁጥር 840/2006 ዓ.ም .......... 149

የይቅርታ አሰጣጥና አፈጻፀም ሥነ-ሥርዓት አዋጅ .......... 149

መ/ ጥብቅና .......... 160

ደንብ ቁጥር 57/1992 .......... 160

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች የሥነ ምግባር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ .......... 160

አዋጅ ቁጥር 199/1992 .......... 180

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች ፈቃድ አሰጣጥና ምዝገባ አዋጅ .......... 180

ደንብ ቁጥር 65/1992 .......... 194

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የጥብቅና ፈቃድ፣ የፈተና መመዝገቢያ እና የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ድርጅት መመዝገቢያ ክፍያ መወሰኛ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ .......... 194

ሠ/ ሙስናን መከላከል .......... 195

ደንብ ቁጥር 144/2000 .......... 195

የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች አሠራርን ለመወሰን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ .......... 195

አዋጅ ቁጥር 668/2002 .......... 206

የሀብት ማሳወቂያና ማስመዝገቢያ አዋጅ .......... 206

ክፍል ሰባት .......... 216

በተለይ የወጡ የወንጀል ህጎች .......... 216

አዋጅ ቁጥር 384/1996 ዓ.ም .......... 216

አደገኛ ቦዘኔነትን ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ .......... 216

አዋጅ ቁጥር 652/2001 ዓ.ም .......... 222

ስለፀረ ሽብርተኝነት የወጣ አዋጅ .......... 222

**አዋጅ ቁጥር 780/2005 ዓ.ም** ....................................................................................244

**በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ**................244

**አዋጅ ቁጥር 881/2007** ..........................................................................................286

**የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ** ...................................................................286

**አዋጅ 909/2007** .....................................................................................................311

**ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ** ......................................................................311

**አዋጅ ቁጥር 958/2008** ..........................................................................................336

**የኮምፒዩተር ወንጀልን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ** ..............................................................336

## ክፍል ስድስት

## የፍትህ አስተዳደር

### ሀ/ ፍርድ ቤቶች

### ስለፍርድ ቤቶች የዳኝነት ገንዘብ አከፋፈል የወጣ የሕግ ክፍል ማስታወቂያ

### ቁጥር 177/1945 ዓ.ም

### የዳኝነት ሥራ አካሄድ አዋጅ ቁጥር 2/1934 ዓ.ም

### በአዋጁ በአንቀጽ 20 መሠረት የወጣ ደንብ

1. ይህ ደንብ ስለፍርድ ቤቶች የዳኝነት ገንዘብ አከፋፈል የወጣ የ1945 ዓ.ም ደንብ ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል፡፡ የሚሠራበትም በከፍተኛው ፍርድ ቤትና የማዕረግ ደረጃቸው ከርሱ በታች በሆኑት ፍርድ ቤቶች ሁሉ ነው፡፡
2. ሀ/ ክስ ቀርቦ በመዝገብ ሲገባ የሚከፈለው የዳኝነቱ ገንዘብ ክስ የቀረበበት ገንዘብ ወይም የነገሩ ግምት ከዜሮ እስከ አንድ መቶ ብር ሲሆን በየአሥሩ ብር ወይም በከፊሉ ላይ ሀምሳ የብር ሳንቲም ታስቦ ይከፈልበታል፡፡

   ገንዘቡ፤ ወይም የነገሩ ግምት ከ 1 መቶ ብር በላይ ከ1ሺህ ብር በታች ሲሆን ከመቶ ብር በላይ በሆነው በየሃምሳው ብር፤ ወይም በከፊሉ ሁለት ብር ከሃምሳ ሳንቲም ይከፈላል፡፡

   ገንዘቡ፤ ወይም የነገሩ ግምት ከ1ሺህ ብር በላይ ከ10ሺህ በታች ሲሆን ከ1ሺህ ብር በላይ በሆነው በየመቶ ብር፤ ወይም በከፊሉ ላይ አራት ብር ታስቦ ይከፈላል፡፡

   ገንዘቡ፤ ወይም የነገሩ ግምት ከ10 ሺህ ብር በላይ ከአምሳ ሺህ ብር በታች ሲሆን

   ከ10 ሺህ ብር በላይ በሆነው በየሁለት መቶ ሃምሳው ብር፤ ወይም በከፊሉ ላይ ዘጠኝ ብር ታስቦ ይከፈላል፡

   ገንዘቡ፤ ወይም ግምቱ ከሀምሳ ሺህ ብር በላይ ከመቶ ሺህ ብር በታች ሲሆን፤ ከሀምሳ ሺህ ብር በላይ በሆነው በየአምስት መቶው ብር፤ ወይም በከፊሉ ላይ አሥራ አምስት ብር ታስቦ ይከፈላል፡፡

   **ማሳሰቢያ**፡- የዚህ ደንብ ሠንጠዥ ከዚህ በላይ የተመለከተውን የዳኝነት ገንዘብ አከፋፈል ዘርዝሮ ያመለክታል፡፡

ከአንድ መቶ ሺህ እስከ ሁለት መቶ ሺህ ብር ለሆነው ነገር በአንድ መቶ ሺህ ብር የሚከፈለው ከተከፈለ በኋላ ከመቶ ሺህ ብር በላይ ባለው በእያንዳንዱ መቶ ብር ላይ አንድ ብር ከሃምሳ ሳንቲም እየተጨመረ ይከፈላል፡፡ ለምሳሌ፤ ስለ 140 ሺህ ብር ክስ የቀረበ እንደሆነ 3,950 ብር ዳኝነት ይከፈላል፡፡

ከሁለት መቶ ሺህ ብር በላይ ለሆነው ነገር ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ለሁለት መቶ ሺህ ብር የሚከፈለው ገንዘብ ከተከፈለ በኋላ ከ200 ሺህ ብር በላይ ባለው በእያንዳንዱ መቶ ብር ላይ አንድ ብር እየተጨመረ ይከፈላል፡፡ ለምሳሌ ስለ ሁለት መቶ ሰማንያ ሺህ ብር ክስ የቀረበ እንደሆነ 5 ሺህ 650 ብር ዳኝነት ይከፈላል፡፡

<u>ማሳሰቢያ</u>፡-

ክሱ በመዝገብ ገብቶ የጥሪው ማዘዣ በተሰጠ ቁጥር በእያንዳንዱ የጥሪ ማዘዣ የኢትዮጵያ ብር ሃምሳ ሳንቲም ታስቦ ተጨማሪ ሆኖ ከዳኝነቱ ገንዘብ በላይ ይከፈላል፡፡

ለ/ የተፈረመ የፍርድ ማስታወቂያ ትክክል ግልባጭ ሲሰጥ ሁለቱ ባላጋራዎች ቀርበው የተፈረደ ፍርድ ቢሆንና ወይም ከባላጋራዎቹ አንዱ በሌለበት የተፈረደ ፍርድ ቢሆን እንደሚከተለው ይከፈላል፡፡

የነገሩ ግምት መቶ ብር ወይም ከመቶ ብር በታች የሆነ እንደሆነ፤....... 1 ብር

የነገሩ ግምት ከመቶ ብር በላይ የሆነ እንደሆነ.................................. 3 ብር

ሐ/ ተከሳሹ መከላከያ አለማቅረቡን ወይም ተረችው ይግባኝ አለማቅረቡን ለማረጋገጥ ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው የተፈረመ ወረቀት ሲሰጥ እንደሚከተለው ይከፈላል፡፡

የነገሩ ግምት መቶ ብር ወይም ከመቶ ብር በታች የሆነ እንደሆነ......... 1 ብር

የነገሩ ግምት ከመቶ ብር በላይ የሆነ እንደሆነ፤.............................. 3 ብር

መ/ የፍርድ ግልባጭ ወይም ማናቸውም ትክክል ግልባጭ ሲሰጥ ገጹ በሙሉ ወይም በከፊል ቢጻፍ የሚከፈል፤................................................... 50 ሣንቲም

ሠ/ ፍርድን በአስገዳጅነት ማስፈጸም፡፡

በሚንቀሳቀስ ወይም በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ፍርዱ በአስገዳጅነት ይፈጸምልኝ ብሎ አንድ ሰው ጥያቄውን ሲያቀረብ እንደሚከተለው ይከፈላል፡፡

ግምቱ መቶ ብር ወይም ከመቶ ብር በታች በሆነ ነገር፤....................... 1 ብር

ግምቱ ከመቶ ብር በላይ በሆነው ነገር.............................................. 3 ብር

ግምቱ ከአምስት መቶ ብር በላይ በሆነው ነገር...................................5 ብር

ግምቱ ከአንድ ሺህ ብር በላይ በሆነው ነገር.....................................10 ብር

ግምቱ ከአሥር ሺህ ብር በላይ በሆነው ነገር .................................. 25 ብር

ከዚህ በቀር ፍርዱን ሲያስፈጽሙ የሚያመጣውን ማናቸውንም ሌላ ኪሣራ ማስከፈል ያስፈልጋል፡፡

ረ/ ፍርዱን ለማስፈጸም የሚሠራው የአስገዳጅነት ሥራ ከተፈጸመ በኋላ ገንዘቡ ባለ መብቃቱን ፍርዱ በሙሉ ሳይፈጸም መቅረቱን የሚያስረዳ የምስክር ወረቀት ሲሰጥ እንደሚከተለው ይከፍላል፡፡

የነገሩ ግምት መቶ ብር፤ ወይም ከመቶ ብር በታች የሆነ እንደሆነ ......... 1 ብር

የነገሩ ግምት ከመቶ ብር በላይ የሆነ እንደሆነ .................................. 3 ብር

ሰ/ ነፍሰ ገዳይ የደም ዋጋ ከፍሎ ከባለደሞቹ ጋራ ታርቆ እርቁ በመዝገብ ሲጻፍ የሚከፈል[1]............................................................................... 20 ብር

ቀ/ የውርስ ወይም የስጦታ ነገር በመዝገብ ሲጻፍ ...................................10 ብር

በ/ በሽምግልና ያለቀ ነገር በመዝገብ ሲጻፍ (ሁለቱም ወገኖች እኩል በኩል የሚከፍሉት)፡፡.................................................................... 2 ብር

ተ/ የባልና የሚስት ፍች በመዝገብ ሲጻፍ (ሁለቱም ወገኖች እኩል በኩል የሚከፍሉት) ........................................................... 10 ብር

ኀ/ የምስክር ማቅረቢያ ማዘዣ ሲጻፍ ................................................... 50 ሣ

ነ/ ከዚህ በላይ ያልተመለከተ ማናቸውም በጽሕፈት የሆነ ቃል ከፍርድ ቤቱ ሲሰጥ ...................................................................... 25 ሣንቲም

## ጠቅላላ ደንብ

3. ማናቸውም ነገር ግምቱ ተለውጦ ሲያድግ የዳኝነቱም ገንዘብ ከዚህ በላይ በተጻፈው የዳኝነት ገንዘብ አከፋፈል መሠረት እየተጨመረ ይከፈላል፡፡
4. ተከሳሹ በከሳሹ ላይ ክስ ያቀረበ እንደሆነ የዳኝነቱን ገንዘብ ከዚህ በላይ በተጻፈው ልክ ይከፍላል፡፡

[1] ይህ አይነት ስምምነት በአሁኑ ግዜ በተግባር እየተመዘገበ አይደለም፡፡

5. ግምቱ ባልተወሰነ ነገር ክስ የቀረበ እንደሆነ፤ የዳኝነቱ ገንዘብ በሚከተለው ዓይነት ይከፈላል፡፡

**ክሱ የቀረበው**[2]

በከፍተኛው ፍርድ ቤት ሲሆን .......................................... 90 ብር

በጠቅላይ ግዛት ፍርድ ቤት ሲሆን፤ ..................................... 25 ብር

በአውራጃ ግዛት ፍርድ ቤትና ከርሱ በታች በሆኑት ፍርድ ቤቶች ሲሆን፤ ........................10 ብር

ነገር ግን ለወደፊት ግምቱ ሲታወቅ በማናቸውም ጊዜ ፍርድ ቤቱ ይህን የዳኝነት ገንዘብ ሊጨምርበት፡ ወይም ሊያሳንሰው ይችላል፡፡

6. ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት ከባለነገርተኞቹ አንዱ አንድ ነገር እንዲደረግ፡ ወይም እንዳይደረግ ማዘዣ ይሰጠኝ ብሎ የጠየቀ እንደሆነ ስለዚሁ ማዘዣ 10 ብር ይከፍላል፡፡

7. በሌለበት የተፈረደበት ሰው በፍርዱ ላይ ተቃዋሚ መሆኑን እየገለጸ እንደ ገና ለመነጋገር አቤቱታውን ያቀረበ እንደሆነ፤ በተፈረደው ነገር ላይ የተከፈለው የዳኝነት ገንዘብ አስቀድሞ ይከፈላል፤ ከዚህም በላይ ስለ መቀጫ 10 ብር መክፈል አለበት፡፡ ያልከፈለ እንደሆነ ግን አቤቱታውን ፍርድ ቤቱ አይቀበለውም፡፡

8. በይግባኝ እንዲታይ ስለሚቀርበው ነገር የሚከፈለው ገንዘብ በመጀመሪያ ከፍርድ ቤት ቀርቦ ሲታይ የተከፈለው ገንዘብ ልክ ታይቶ ግማሹ ይከፈላል፡፡ ነገር ግን ይግባኙ የቀረበው በጭፍጫፊ ነገር በትእዛዝ ላይ የሆነ እንደሆነ፤ ይግባኝ በተባለ ቁጥር በሚከተለው ዓይነት ይከፈላል፡፡[3]

**ይግባኙ የቀረበው**

ለጠቅላይ ንጉሠ ነገሥቱ ፍርድ ቤት ሲሆን፤ ...................... 30 ብር

ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ሲሆን፤........................................ 20 ብር

ለጠቅላይ ግዛት ፍርድ ቤት ሲሆን፤.................................... 15 ብር

---

[2] የቀድሞው የፍርድ ቤት አደረጃጀት በአዋጅ ቁጥር 25/1988 መሰረት በመቀየሩ አሁን ያለው አደረጃጀት የፌዴራል ክፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ናቸው።

[3] የፍትሐ ብሔር ስነስርዓት ህግ ቁጥር 320 በእንደዚህ አይነት ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ ማለትን ስለሚከለክል ይህ ድንጋጌ ተፈፃሚ አይሆንም።

ለአውራጃ ፍርድ ቤት፤ ወይም ከርሱ በታች ለሆኑት ፍርድ ቤቶች ሲሆን፤ …………….. 10 ብር

9. የዳኝነቱን ገንዘብ በሙሉ ከሳሹ ይከፍላል፡፡
ነገሩ አልቆ ፍርዱ ከተሰጠ በኋላ ግን ረችው ስለፍርዱ የከፈለውን ማናቸውንም ገንዘብ ዝርዝሩን የደረሰኙን ጭምር ለፍርድ ቤቱ በጽሕፈት ቤት አቅርቦ ጽሕፈት ቤቱ መርምሮ ይህ ገንዘብ አስቀድሞ ለዳኝነት ከተከፈለው ገንዘብ ጋራ ተጨምሮ ድምሩን በሙሉ ተረችው ይከፍለዋል፡፡

10. ተከሳሹ የተፈረደበት እንደሆነና ገንዘብ አጥቶ የተፈረደበትን ለመፈጸም ያልቻለ እንደሆነ በዚህ ምክንያት ከሳሹ ለዳኝነት የከፈልሁት ገንዘብ ይመለስልኝ ብሎ ፍርድ ቤቱን ለመጠየቅ አይችልም፡፡

11. አንድ ክስ ቀርቦ ችሎት ሳይጀመር ከሳሹ ክሴን ትቼዋለሁ ብሎ ያስታወቀ እንደሆነ ለዳኝነቱ ከተከፈለው ገንዘብ በኪሣራ ስም ለፍርድ ቤቱ ገቢ የሚሆነው ገንዘብ ከዚህ ቀጥሎ በተጻፈው አኳኋን ይቀነሣል ቀሪውንም ገንዘብ የፍርድ ቤቱ የጽሕፈት ቤት ሹም ጽፎ ፈርሞ ባስታወቀው ልክ የገንዘብ ሚኒስቴር ግምጃ ቤት ለተከሳሹ ይመልስለታል፡፡ ለዳኝነቱ የተከፈለው ገንዘብ ከ30 ብር በታች እንደሆነ 4ኛው እጅ (ሩቡ) ይቀነሳል፡፡ ከ30 ብር በላይ ከመቶ ሀምሳ ብር በታች እንደሆነ 5ኛው እጅ ይቀነሳል፡፡ ከመቶ ሃምሳ ብር በላይ ከስድስት መቶ ብር በታች የሆነ እንደሆነ 6ኛው እጅ ይቀነሳል፡፡ ከ600 ብር በላይ የሆነ 10ኛው እጅ ይቀነሳል፡፡

12. አንድ ፍርድ ቤት በዚህ ደንብ ያልተመለከተ ሌላ ሥራ የሠራ እንደሆነ ስለዚሁ ሥራ ሊከፈል የሚገባውን የዳኝነት ገንዘብ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ከፍርድ ሚኒስትር[4] አስፈቅዶ ሊቆርጠው ይችላል፡፡

13. ይህ ደንብ ከኅዳር 30 ቀን 1946 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡ በ1936 ዓ.ም በቁጥር 34 ታትሞ የወጣው የ1935 ዓ.ም የዳኝነት ገንዘብ አከፋፈል ደንብ ቀሪ ሆኖ ይህ ተተክቶበታል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ 21 ቀን 1945 ዓ.ም**

**ሔንሪ እስቲድ ሮበርትስ**

**የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት**

[4] በአዋጅ ቁጥር 943/2008 መሰረት ፌዴራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ ሆኗል፡፡

**ተፈቅዷል**

**ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ወ.ዮ.**

**የፍርድ ሚኒስትር**

**ሠንጠረዥ**

**በደንቡ በአንቀጽ 2 በተመለከተው መሠረት የዳኝነቱን ገንዘብ**

**አከፋፈል ዝርዝር መግለጫ**

| ገንዘቡ | ወይም | ግምቱ | | | | ብር ሳ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ከዜሮ | እስከ | 10ብር | | | | 0.50 |
| ከ | 10 | በላይ | ከ | 20 | በታች | 1.00 |
| “ | 20 | “ | “ | 30 | “ | 1.50 |
| “ | 30 | “ | “ | 40 | “ | 2.00 |
| “ | 40 | “ | “ | 50 | “ | 2.50 |
| “ | 50 | “ | “ | 60 | “ | 3.00 |
| “ | 60 | “ | “ | 70 | “ | 3.50 |
| “ | 70 | “ | “ | 80 | “ | 4.00 |
| “ | 80 | “ | “ | 90 | “ | 4.50 |
| “ | 90 | “ | “ | 100 | “ | 5.00 |
| “ | 100 | “ | “ | 150 | “ | 7.50 |
| “ | 150 | “ | “ | 200 | “ | 10.00 |
| “ | 200 | “ | “ | 250 | “ | 12.50 |
| “ | 250 | “ | “ | 300 | “ | 15.00 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| “ | 300 | “ | “ | 350 | “ | 17.50 |
| “ | 350 | “ | “ | 400 | “ | 20.00 |
| “ | 400 | “ | “ | 450 | “ | 22.50 |
| “ | 450 | “ | “ | 500 | “ | 25.00 |
| “ | 500 | “ | “ | 550 | “ | 27.50 |
| “ | 550 | “ | “ | 600 | “ | 30.00 |
| “ | 600 | “ | “ | 650 | “ | 32.50 |
| “ | 650 | “ | “ | 700 | “ | 35.00 |
| “ | 700 | “ | “ | 750 | “ | 37.50 |
| “ | 750 | “ | “ | 800 | “ | 40.00 |
| “ | 800 | “ | “ | 850 | “ | 42.50 |
| “ | 850 | “ | “ | 900 | “ | 45.00 |
| “ | 900 | “ | “ | 950 | “ | 47.50 |
| “ | 950 | “ | “ | 1,000 | “ | 50.00 |
| “ | 1,000 | “ | “ | 1,100 | “ | 54.00 |
| “ | 1,100 | “ | “ | 1,200 | “ | 58.00 |
| “ | 1,200 | “ | “ | 1,300 | “ | 62.00 |
| “ | 1,300 | “ | “ | 1,400 | “ | 66.00 |
| “ | 1,400 | “ | “ | 1,500 | “ | 70.00 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| “ | 1,500 | “ | “ | 1,600 | “ | 74.00 |
| “ | 1,600 | “ | “ | 1,700 | “ | 78.00 |
| “ | 1,700 | “ | “ | 1,800 | “ | 82.00 |
| “ | 1,800 | “ | “ | 1,900 | “ | 86.00 |
| “ | 1,900 | “ | “ | 2,000 | “ | 90.00 |
| “ | 2,000 | “ | “ | 2,100 | “ | 94.00 |
| “ | 2,100 | “ | “ | 2,200 | “ | 98.00 |
| “ | 2,200 | “ | “ | 2,300 | “ | 102.00 |
| “ | 2,300 | “ | “ | 2,400 | “ | 106.00 |
| “ | 2,400 | “ | “ | 2,500 | “ | 110.00 |
| “ | 2,500 | “ | “ | 2,600 | “ | 114.00 |
| “ | 2,600 | “ | “ | 2,700 | “ | 118.00 |
| “ | 2,700 | “ | “ | 2,800 | “ | 122.00 |
| “ | 2,800 | “ | “ | 2,900 | “ | 126.00 |
| “ | 2,900 | “ | “ | 3,000 | “ | 130.00 |
| “ | 3,000 | “ | “ | 3,100 | “ | 134.00 |
| “ | 3,100 | “ | “ | 3,200 | “ | 138.00 |
| “ | 3,200 | “ | “ | 3,300 | “ | 142.00 |
| “ | 3,300 | “ | “ | 3,400 | “ | 146.00 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | **ገንዘቡ ወይም ግምቱ** | | | | |
| | | | | **የዳኘነት ገንዘብ** | | |
| | | | | | | **ብር ሣ** |
| **ከ** | **3,400** | **በላይ** | **ከ** | **3,500** | **በታች** | **150.00** |
| “ | 3,500 | “ | “ | 3,600 | “ | 154.00 |
| “ | 3,600 | “ | “ | 3,700 | “ | 158.00 |
| “ | 3,700 | “ | “ | 3,800 | “ | 162.00 |
| “ | 3,800 | “ | “ | 3,900 | “ | 166.00 |
| “ | 3,900 | “ | “ | 4,000 | “ | 170.00 |
| “ | 4,000 | “ | “ | 4,100 | “ | 174.00 |
| “ | 4,100 | “ | “ | 4,200 | “ | 178.00 |
| “ | 4,200 | “ | “ | 4,300 | “ | 182.00 |
| “ | 4,300 | “ | “ | 4,400 | “ | 186.00 |
| “ | 4,400 | “ | “ | 4,500 | “ | 190.00 |
| “ | 4,500 | “ | “ | 4,600 | “ | 194.00 |
| “ | 4,600 | “ | “ | 4,700 | “ | 198.00 |
| “ | 4,700 | “ | “ | 4,800 | “ | 202.00 |
| “ | 4,800 | “ | “ | 4,900 | “ | 206.00 |
| “ | 4,900 | “ | “ | 5,000 | “ | 210.00 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| " | 5,000 | " | " | 5,100 | " | 214.00 |
| " | 5,100 | " | " | 5,200 | " | 218.00 |
| " | 5,200 | " | " | 5,300 | " | 222.00 |
| " | 5,300 | " | " | 5,400 | " | 226.00 |
| " | 5,400 | " | " | 5,500 | " | 230.00 |
| " | 5,500 | " | " | 5,600 | " | 234.00 |
| " | 5,600 | " | " | 5,700 | " | 238.00 |
| " | 5,700 | " | " | 5,800 | " | 242.00 |
| " | 5,800 | " | " | 5,900 | " | 246.00 |
| " | 5,900 | " | " | 6,000 | " | 250.00 |
| " | 6,000 | " | " | 6,100 | " | 254.00 |
| " | 6,100 | " | " | 6,200 | " | 258.00 |
| " | 6,200 | " | " | 6,300 | " | 262.00 |
| " | 6,300 | " | " | 6,400 | " | 266.00 |
| " | 6,400 | " | " | 6,500 | " | 270.00 |
| " | 6,500 | " | " | 6,600 | " | 274.00 |
| " | 6,600 | " | " | 6,700 | " | 278.00 |
| " | 6,700 | " | " | 6,800 | " | 282.00 |
| " | 6,800 | " | " | 6,900 | " | 286.00 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| “ | 6,900 | “ | “ | 7,000 | “ | 290.00 |
| “ | 7,000 | “ | “ | 7,100 | “ | 294.00 |
| “ | 7,100 | “ | “ | 7,200 | “ | 298.00 |
| “ | 7,200 | “ | “ | 7,300 | “ | 302.00 |
| “ | 7,300 | “ | “ | 7,400 | “ | 306.00 |
| “ | 7,400 | “ | “ | 7,500 | “ | 310.00 |
| “ | 7,500 | “ | “ | 7,600 | “ | 314.00 |
| “ | 7,600 | “ | “ | 7,700 | “ | 318.00 |
| “ | 7,700 | “ | “ | 7,800 | “ | 322.00 |
| “ | 7,800 | “ | “ | 7,900 | “ | 326.00 |
| “ | 7,900 | “ | “ | 8,000 | “ | 330.00 |
| “ | 8,000 | “ | “ | 8,100 | “ | 334.00 |
| “ | 8,100 | “ | “ | 8,200 | “ | 338.00 |
| “ | 8,200 | “ | “ | 8,300 | “ | 342.00 |
| “ | 8,300 | “ | “ | 8,400 | “ | 346.00 |
| “ | 8,400 | “ | “ | 8,500 | “ | 350.00 |
| “ | 8,500 | “ | “ | 8,600 | “ | 354.00 |
| | | **ገንዘቡ ወይም ግምቱ** | | | | |
| | | | | **የዳኝነት ገንዘብ** | | |

| | | | | | ብር ሣ | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ከ | 8,600 | በላይ | ከ | 8,700 | በታች | 358.00 |
| “ | 8,700 | “ | “ | 8,800 | “ | 362.00 |
| “ | 8,800 | “ | “ | 8,900 | “ | 366.00 |
| “ | 8,900 | “ | “ | 9,000 | “ | 370.00 |
| “ | 9,000 | “ | “ | 9,100 | “ | 374.00 |
| “ | 9,100 | “ | “ | 9,200 | “ | 378.00 |
| “ | 9,200 | “ | “ | 9,300 | “ | 382.00 |
| “ | 9,300 | “ | “ | 9,400 | “ | 386.00 |
| “ | 9,400 | “ | “ | 9,500 | “ | 390.00 |
| “ | 9,500 | “ | “ | 9,600 | “ | 394.00 |
| “ | 9,600 | “ | “ | 9,700 | “ | 398.00 |
| “ | 9,700 | “ | “ | 9,800 | “ | 402.00 |
| “ | 9,800 | “ | “ | 9,900 | “ | 406.00 |
| “ | 9,900 | “ | “ | 10,000 | “ | 410.00 |
| “ | 10,000 | “ | “ | 10,250 | “ | 419.00 |
| “ | 10,250 | “ | “ | 10,500 | “ | 428.00 |
| “ | 10,500 | “ | “ | 10,750 | “ | 437.00 |
| “ | 10,750 | “ | “ | 11,000 | “ | 446.00 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| “ | 11,000 | “ | “ | 11,250 | “ | 455.00 |
| “ | 11,250 | “ | “ | 11,500 | “ | 464.00 |
| “ | 11,500 | “ | “ | 11,750 | “ | 473.00 |
| “ | 11,750 | “ | “ | 12,000 | “ | 482.00 |
| “ | 12,000 | “ | “ | 12,250 | “ | 491.00 |
| “ | 12,250 | “ | “ | 12,500 | “ | 500.00 |
| “ | 12,500 | “ | “ | 12,750 | “ | 509.00 |
| “ | 12,750 | “ | “ | 13,000 | “ | 518.00 |
| “ | 13,000 | “ | “ | 13,250 | “ | 527.00 |
| “ | 13,250 | “ | “ | 13,500 | “ | 536.00 |
| “ | 13,500 | “ | “ | 13,750 | “ | 545.00 |
| “ | 13,750 | “ | “ | 14,000 | “ | 554.00 |
| “ | 14,000 | “ | “ | 14,250 | “ | 563.00 |
| “ | 14,250 | “ | “ | 14,500 | “ | 572.00 |
| “ | 14,500 | “ | “ | 14,750 | “ | 581.00 |
| “ | 14,750 | “ | “ | 15,000 | “ | 590.00 |
| “ | 15,000 | “ | “ | 15,250 | “ | 599.00 |
| “ | 15,250 | “ | “ | 15,500 | “ | 608.00 |
| “ | 15,500 | “ | “ | 15,750 | “ | 617.00 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| “ | 15,750 | “ | “ | 16,000 | “ | 626.00 |
| “ | 16,000 | “ | “ | 16,250 | “ | 635.00 |
| “ | 16,250 | “ | “ | 16,500 | “ | 644.00 |
| “ | 16,500 | “ | “ | 16,750 | “ | 653.00 |
| “ | 16,750 | “ | “ | 17,000 | “ | 662.00 |
| “ | 17,000 | “ | “ | 17,250 | “ | 671.00 |
| “ | 17,250 | “ | “ | 17,500 | “ | 680.00 |
| “ | 17,500 | “ | “ | 17,750 | “ | 689.00 |
| “ | 17,750 | “ | “ | 18,000 | “ | 698.00 |
| “ | 18,000 | “ | “ | 18,250 | “ | 707.00 |
| “ | 18,250 | “ | “ | 18,500 | “ | 716.00 |
| “ | 18,500 | “ | “ | 18,750 | “ | 725.00 |
| “ | 18,750 | “ | “ | 19,000 | “ | 734.00 |
| “ | 19,000 | “ | “ | 19,250 | “ | 743.00 |
| “ | 19,250 | “ | “ | 19,500 | “ | 752.00 |
| | | **ገንዘቡ ወይም ግምቱ** | | | | |
| | | | | | **የዳኝነት** | **ገንዘብ** |
| | | | | | | **ብር ሣ** |
| **ከ** | 19,500 | **በላይ** | **ከ** | 19,750 | **በታች** | 761.00 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| “ | 19,750 | “ | “ | 20,000 | “ | 770.00 |
| “ | 20,000 | “ | “ | 20,250 | “ | 779.00 |
| “ | 20,250 | “ | “ | 20,500 | “ | 788.00 |
| “ | 20,500 | “ | “ | 20,750 | “ | 797.00 |
| “ | 20,750 | “ | “ | 21,000 | “ | 806.00 |
| “ | 21,000 | “ | “ | 21,250 | “ | 815.00 |
| “ | 21,250 | “ | “ | 21,500 | “ | 824.00 |
| “ | 21,500 | “ | “ | 21,750 | “ | 833.00 |
| “ | 21,750 | “ | “ | 22,000 | “ | 842.00 |
| “ | 22,000 | “ | “ | 22,250 | “ | 851.00 |
| “ | 22,250 | “ | “ | 22,500 | “ | 860.00 |
| “ | 22,500 | “ | “ | 22,750 | “ | 869.00 |
| “ | 22,750 | “ | “ | 23,000 | “ | 878.00 |
| “ | 23,000 | “ | “ | 23,250 | “ | 886.00 |
| “ | 23,250 | “ | “ | 23,500 | “ | 896.00 |
| “ | 23,500 | “ | “ | 23,750 | “ | 905.00 |
| “ | 23,750 | “ | “ | 24.000 | “ | 914.00 |
| “ | 24.000 | “ | “ | 24,250 | “ | 923.00 |
| “ | 24,250 | “ | “ | 24,500 | “ | 932.00 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| " | 24,500 | " | " | 24,750 | " | 941.00 |
| " | 24,750 | " | " | 25,000 | " | 950.00 |
| " | 25,000 | " | " | 25,250 | " | 959.00 |
| " | 25,250 | " | " | 25,500 | " | 968.00 |
| " | 25,500 | " | " | 25,750 | " | 977.00 |
| " | 25,750 | " | " | 26,000 | " | 986.00 |
| " | 26,000 | " | " | 26,250 | " | 995.00 |
| " | 26,250 | " | " | 26,500 | " | 1,004.00 |
| " | 26,500 | " | " | 26,750 | " | 1,013.00 |
| " | 26,750 | " | " | 27,000 | " | 1,022.00 |
| " | 27,000 | " | " | 27,250 | " | 1,031.00 |
| " | 27,250 | " | " | 27,500 | " | 1,040.00 |
| " | 27,500 | " | " | 27,750 | " | 1,049.00 |
| " | 27,750 | " | " | 28,000 | " | 1,058.00 |
| " | 28,000 | " | " | 28,250 | " | 1,067.00 |
| " | 28,250 | " | " | 28,500 | " | 1,076.00 |
| " | 28,500 | " | " | 28,750 | " | 1,085.00 |
| " | 28,750 | " | " | 29,000 | " | 1,094.00 |
| " | 29,000 | " | " | 29,250 | " | 1,103.00 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| “ | 29,250 | “ | “ | 29,500 | “ | 1,112.00 |
| “ | 29,500 | “ | “ | 29,750 | “ | 1,121.00 |
| “ | 29,750 | “ | “ | 30,000 | “ | 1,130.00 |
| “ | 30,000 | “ | “ | 30,250 | “ | 1,139.00 |
| “ | 30,250 | “ | “ | 30,500 | “ | 1,148.00 |
| “ | 30,500 | “ | “ | 30,750 | “ | 1,157.00 |
| “ | 30,750 | “ | “ | 31,000 | “ | 1,166.00 |
| “ | 31,000 | “ | “ | 31,250 | “ | 1,175.00 |
| “ | 31,250 | “ | “ | 31,500 | “ | 1,184.00 |
| “ | 31,500 | “ | “ | 31,750 | “ | 1,193.00 |
| “ | 31,750 | “ | “ | 32,000 | “ | 1,202.00 |
| “ | 32,000 | “ | “ | 32,250 | “ | 1,211.00 |
| | 32,250 | | | 32,500 | “ | 1,220.00 |
| | | **ገንዘቡ ወይም ግምቱ** | | | | |
| | | | | | **የዳኝነት** | **ገንዘብ** |
| | | | | | | **ብር ሣ** |
| **ከ** | **32,500** | **በላይ** | **ከ** | **32,750** | **በታች** | **1,229.00** |
| “ | 32,750 | “ | “ | 33,000 | “ | 1,238.00 |
| “ | 33,000 | “ | “ | 33,250 | “ | 1,247.00 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| “ | 33,250 | “ | “ | 33,500 | “ | 1,256.00 |
| “ | 33,500 | “ | “ | 33,750 | “ | 1,265.00 |
| “ | 33,750 | “ | “ | 34,000 | “ | 1,274.00 |
| “ | 34,000 | “ | “ | 34,250 | “ | 1,283.00 |
| “ | 34,250 | “ | “ | 34,500 | “ | 1,292.00 |
| “ | 34,500 | “ | “ | 34,750 | “ | 1,301.00 |
| “ | 34,750 | “ | “ | 35,000 | “ | 1,310.00 |
| “ | 35,000 | “ | “ | 35,250 | “ | 1,319.00 |
| “ | 35,250 | “ | “ | 35,500 | “ | 1,328.00 |
| “ | 35,500 | “ | “ | 35,750 | “ | 1,337.00 |
| “ | 35,750 | “ | “ | 36,000 | “ | 1,346.00 |
| “ | 36,000 | “ | “ | 36,250 | “ | 1,355.00 |
| “ | 36,250 | “ | “ | 36,500 | “ | 1,364.00 |
| “ | 36,500 | “ | “ | 36,750 | “ | 1,373.25 |
| “ | 36,750 | “ | “ | 37,000 | “ | 1,382.00 |
| “ | 37,000 | “ | “ | 37,250 | “ | 1,391.75 |
| “ | 37,250 | “ | “ | 37,500 | “ | 1,400.50 |
| “ | 37,500 | “ | “ | 37,750 | “ | 1,409.25 |
| “ | 37,750 | “ | “ | 38,000 | “ | 1,418.00 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| “ | 38,000 | “ | “ | 38,250 | “ | 1,427.71 |
| “ | 38,250 | “ | “ | 38,500 | “ | 1,436.50 |
| “ | 38,500 | “ | “ | 38,750 | “ | 1,445.25 |
| “ | 38,750 | “ | “ | 39,000 | “ | 1,454.00 |
| “ | 39,000 | “ | “ | 39,250 | “ | 1,463.75 |
| “ | 39,250 | “ | “ | 39,500 | “ | 1,472.50 |
| “ | 39,500 | “ | “ | 39,750 | “ | 1,481.25 |
| “ | 39,750 | “ | “ | 40,000 | “ | 1,490.00 |
| “ | 40,000 | “ | “ | 40,250 | “ | 1,499.75 |
| “ | 40,250 | “ | “ | 40,500 | “ | 1,508.50 |
| “ | 40,500 | “ | “ | 40,750 | “ | 1,517.25 |
| “ | 40,750 | “ | “ | 41,000 | “ | 1,526.00 |
| “ | 41,000 | “ | “ | 41,250 | “ | 1,535.75 |
| “ | 41,250 | “ | “ | 41,500 | “ | 1,544.50 |
| “ | 41,500 | “ | “ | 41,750 | “ | 1,553.25 |
| “ | 41,750 | “ | “ | 42,000 | “ | 1,562.00 |
| “ | 42,000 | “ | “ | 42,250 | “ | 1,571.75 |
| “ | 42,250 | “ | “ | 42,500 | “ | 1,580.50 |
| “ | 42,500 | “ | “ | 42,750 | “ | 1,589.25 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| “ | 42,750 | “ | “ | 43,000 | “ | 1,598.00 |
| “ | 43,000 | “ | “ | 43,250 | “ | 1,607.75 |
| “ | 43,250 | “ | “ | 43,500 | “ | 1,616.50 |
| “ | 43,500 | “ | “ | 43,750 | “ | 1,625.25 |
| “ | 43,750 | “ | “ | 44,000 | “ | 1,634.00 |
| “ | 44,000 | “ | “ | 44,250 | “ | 1,643.75 |
| “ | 44,250 | “ | “ | 44,500 | “ | 1,652.50 |
| “ | 44,500 | “ | “ | 44,750 | “ | 1,661.25 |
| “ | 44,750 | “ | “ | 45,000 | “ | 1,670.00 |
| “ | 45,000 | “ | “ | 45,250 | “ | 1,679.75 |
| “ | 45,250 | “ | “ | 45,500 | “ | 1,688.50 |
| | | | | **ገንዘብ** | **ወይም** | **ግምቱ** |
| | | | | | **የዳኝነት** | **ገንዘብ** |
| | | | | | | **ብር ሣ** |
| **ከ** | **45,500** | **በላይ** | **ከ** | **45,750** | **በታች** | **1,697.25** |
| “ | 45,750 | “ | “ | 46,000 | “ | 1,706.00 |
| “ | 46,000 | “ | “ | 46,250 | “ | 1,715.75 |
| “ | 46,250 | “ | “ | 46,500 | “ | 1,724.50 |
| “ | 46,500 | “ | “ | 46,750 | “ | 1,733.25 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| “ | 46,750 | “ | “ | 47,000 | “ | 1,742.00 |
| “ | 47,000 | “ | “ | 47,250 | “ | 1,751.75 |
| “ | 47,250 | “ | “ | 47,500 | “ | 1,760.50 |
| “ | 47,500 | “ | “ | 47,750 | “ | 1,769.25 |
| “ | 47,750 | “ | “ | 48,000 | “ | 1,778.00 |
| “ | 48,000 | “ | “ | 48,250 | “ | 1,787.75 |
| “ | 48,250 | “ | “ | 48,500 | “ | 1,796.50 |
| “ | 48,500 | “ | “ | 48,750 | “ | 1,805.25 |
| “ | 48,750 | “ | “ | 49,000 | “ | 1,814.00 |
| “ | 49,000 | “ | “ | 49,250 | “ | 1,823.75 |
| “ | 49,250 | “ | “ | 49,500 | “ | 1,832.50 |
| “ | 49,500 | “ | “ | 49,750 | “ | 1,841.25 |
| “ | 49,750 | “ | “ | 50,000 | “ | 1,850.00 |
| “ | 50,000 | “ | “ | 50,500 | “ | 1,865.00 |
| “ | 50,500 | “ | “ | 51,000 | “ | 1,880.00 |
| “ | 51,000 | “ | “ | 51,500 | “ | 1,895.00 |
| “ | 51,500 | “ | “ | 52,000 | “ | 1,910.00 |
| “ | 52,000 | “ | “ | 52,500 | “ | 1,925.00 |
| “ | 52,500 | “ | “ | 53,000 | “ | 1,940.00 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| “ | 53,000 | “ | “ | 53,500 | “ | 1,955.00 |
| “ | 53,500 | “ | “ | 54,000 | “ | 1,970.00 |
| “ | 54,000 | “ | “ | 54,500 | “ | 1,985.00 |
| “ | 54,500 | “ | “ | 55,000 | “ | 2,000.00 |
| “ | 55,000 | “ | “ | 55,500 | “ | 2,015.00 |
| “ | 55,500 | “ | “ | 56,000 | “ | 2,030.00 |
| “ | 56,000 | “ | “ | 56,500 | “ | 2,045.00 |
| “ | 56,500 | “ | “ | 57,000 | “ | 2,060.00 |
| “ | 57,000 | “ | “ | 57,500 | “ | 2,075.00 |
| “ | 57,500 | “ | “ | 58,000 | “ | 2,090.00 |
| “ | 58,000 | “ | “ | 58,500 | “ | 2,105.00 |
| “ | 58,500 | “ | “ | 59,000 | “ | 2,120.00 |
| “ | 59,000 | “ | “ | 59,500 | “ | 2,135.00 |
| “ | 59,500 | “ | “ | 60,000 | “ | 2,150.00 |
| “ | 60,000 | “ | “ | 60,500 | “ | 2,165.00 |
| “ | 60,500 | “ | “ | 61,000 | “ | 2,180.00 |
| “ | 61,000 | “ | “ | 61,500 | “ | 2,195.00 |
| “ | 61,500 | “ | “ | 62,000 | “ | 2,210.00 |
| “ | 62,000 | “ | “ | 62,500 | “ | 2,225.00 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| “ | 62,500 | “ | “ | 63,000 | “ | 2,240.00 |
| “ | 63,000 | “ | “ | 63,500 | “ | 2,255.00 |
| “ | 63,500 | “ | “ | 64,000 | “ | 2,270.00 |
| “ | 64,000 | “ | “ | 64,500 | “ | 2,285.00 |
| “ | 64,500 | “ | “ | 65,000 | “ | 2,300.00 |
| “ | 65,000 | “ | “ | 65,500 | “ | 2,315.00 |
| “ | 65,500 | “ | “ | 66,000 | “ | 2,330.00 |
| “ | 66,000 | “ | “ | 66,500 | “ | 2,345.00 |
| “ | 66,500 | “ | “ | 67,000 | “ | 2,360.00 |
| | | | | | **የዳኝነት** | **ገንዘብ** |
| | | | | | | **ብር ሣ** |
| **ከ** | **67,000** | **በላይ** | **ከ** | **67,500** | **በታች** | **2,375.00** |
| “ | 67,500 | “ | “ | 68,000 | “ | 2,390.00 |
| “ | 68,000 | “ | “ | 68,500 | “ | 2,405.00 |
| “ | 68,500 | “ | “ | 69,000 | “ | 2,420.00 |
| “ | 69,000 | “ | “ | 69,500 | “ | 2,435.00 |
| “ | 69,500 | “ | “ | 70,000 | “ | 2,450.00 |
| “ | 70,000 | “ | “ | 70,500 | “ | 2,465.00 |
| “ | 70,500 | “ | “ | 71,000 | “ | 2,480.00 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| “ | 71,000 | “ | “ | 71,500 | “ | 2,495.00 |
| “ | 71,500 | “ | “ | 72,000 | “ | 2,510.00 |
| “ | 72,000 | “ | “ | 72,500 | “ | 2,525.00 |
| “ | 72,500 | “ | “ | 73,000 | “ | 2,540.00 |
| “ | 73,000 | “ | “ | 73,500 | “ | 2,555.00 |
| “ | 73,500 | “ | “ | 74,000 | “ | 2,570.00 |
| “ | 74,000 | “ | “ | 74,500 | “ | 2,585.00 |
| “ | 74,500 | “ | “ | 75,000 | “ | 2,600.00 |
| “ | 75,000 | “ | “ | 75,500 | “ | 2,615.00 |
| “ | 75,500 | “ | “ | 76,000 | “ | 2,630.00 |
| “ | 76,000 | “ | “ | 76,500 | “ | 2,645.00 |
| “ | 76,500 | “ | “ | 77,000 | “ | 2,660.00 |
| “ | 77,000 | “ | “ | 77,500 | “ | 2,675.00 |
| “ | 77,500 | “ | “ | 78,000 | “ | 2,690.00 |
| “ | 78,000 | “ | “ | 78,500 | “ | 2,705.00 |
| “ | 78,500 | “ | “ | 79,000 | “ | 2,720.00 |
| “ | 79,000 | “ | “ | 79,500 | “ | 2,735.00 |
| “ | 79,500 | “ | “ | 80,000 | “ | 2,750.00 |
| “ | 80,000 | “ | “ | 80,500 | “ | 2,765.00 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| “ | 80,500 | “ | “ | 81,000 | “ | 2,780.00 |
| “ | 81,000 | “ | “ | 81,500 | “ | 2,795.00 |
| “ | 81,500 | “ | “ | 82,000 | “ | 2,810.00 |
| “ | 82,000 | “ | “ | 82,500 | “ | 2,825.00 |
| “ | 82,500 | “ | “ | 83,000 | “ | 2,840.00 |
| “ | 83,000 | “ | “ | 83,500 | “ | 2,855.00 |
| “ | 83,500 | “ | “ | 84,000 | “ | 2,870.00 |
| “ | 84,000 | “ | “ | 84,500 | “ | 2,885.00 |
| “ | 84,500 | “ | “ | 85,000 | “ | 2,900.00 |
| “ | 85,000 | “ | “ | 85,500 | “ | 2,915.00 |
| “ | 85,500 | “ | “ | 86,000 | “ | 2,930.00 |
| “ | 86,000 | “ | “ | 86,500 | “ | 2,945.00 |
| “ | 86,500 | “ | “ | 87,000 | “ | 2,960.00 |
| “ | 87,000 | “ | “ | 87,500 | “ | 2,975.00 |
| “ | 87,500 | “ | “ | 88,000 | “ | 2,990.00 |
| “ | 88,000 | “ | “ | 88,500 | “ | 3,005.00 |
| “ | 88,500 | “ | “ | 89,000 | “ | 3,020.00 |
| “ | 89,000 | “ | “ | 89,500 | “ | 3,035.00 |
| “ | 89,500 | “ | “ | 90,000 | “ | 3,050.00 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| “ | 90,000 | “ | “ | 90,500 | “ | 3,065.00 |
| “ | 90,500 | “ | “ | 91,000 | “ | 3,080.00 |
| “ | 91,000 | “ | “ | 91,500 | “ | 3,095.00 |
| “ | 91,500 | “ | “ | 92,000 | “ | 3,110.00 |
| “ | 92,000 | “ | “ | 92,500 | “ | 3,125.00 |
| “ | 92,500 | “ | “ | 93,000 | “ | 3,140.00 |
| | | | | | **የዳኝነት** | **ገንዘብ** |
| | | | | | | **ብር ሣ** |
| **ከ** | **93,000** | **በላይ** | **ከ** | **93,500** | **በታች** | **3,155.00** |
| “ | 93,500 | “ | “ | 94,000 | “ | 3,170.00 |
| “ | 94,000 | “ | “ | 94,500 | “ | 3,185.00 |
| “ | 94,500 | “ | “ | 95,000 | “ | 3,200.00 |
| “ | 95,000 | “ | “ | 95,500 | “ | 3,215.00 |
| “ | 95,500 | “ | “ | 96,000 | “ | 3,230.00 |
| “ | 96,000 | “ | “ | 96,500 | “ | 3,245.00 |
| “ | 96,500 | “ | “ | 97,000 | “ | 3,260.00 |
| “ | 97,000 | “ | “ | 97,500 | “ | 3,275.00 |
| “ | 97,500 | “ | “ | 98,000 | “ | 3,290.00 |
| “ | 98,000 | “ | “ | 98,500 | “ | 3,305.00 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| “ | 98,500 | “ | “ | 99,000 | “ | 3,320.00 |
| “ | 99,000 | “ | “ | 99,500 | “ | 3,335.00 |
| “ | 99,500 | “ | “ | 100,000 | “ | 3,350.00 |

## አዋጅ ቁጥር 25/1988

## የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የዳኝነት ሥልጣን በፌዴራል መንግሥቱና በክልሎች የተከፋፈለ በመሆኑ፤

ሕገ መንግሥቱን መሠረት በማድረግ የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን ሥልጣን መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

   1. "የፌዴራል መንግሥት ባለሥልጣኖች" ማለት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባሎች፣ ከሚኒስትር ደረጃ በላይ የሆኑ የፌዴራል መንግሥቱ ባለሥልጣኖች፣ ሚኒስትሮች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች እና በተመሣሣይ ደረጃ ላይ የሚገኙ የፌዴራሉ መንግሥት ባለሥልጣኖች ናቸው፤
   2. "የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች" ማለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ውስጥ ከተጠቀሱት ውጭ ያሉ በፌዴራል መንግሥት ሥራ ላይ የተሰማሩ ሠራተኞችን ሁሉ ያጠቃልላል፤
   3. "የፌዴራል መንግሥት ሕጎች" ማለት ሕገ መንግሥቱን የማይቃረኑና በሕገ መንግሥቱ ላይ የተጠቀሱትን በፌዴራል መንግሥቱ ሥልጣን ክልል ሥር ያሉ ጉዳዮችን የሚመለከቱ በሥራ ላይ ያሉ ነባር ሕጎችን ይጨምራል፤
   4. "ፌዴራል ፍርድ ቤቶች" ማለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ናቸው፤

5. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለ ፌዴራል ፍርድ ቤቶች የወል የዳኝነት ሥልጣን

3. **መሠረቱ**

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች፣

1. ሕገ መንግሥቱን፣ የፌዴራል መንግሥቱን ሕጎች፣ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን መሠረት በማድረግ በሚነሱ ጉዳዮች፤
2. በፌዴራል መንግሥቱ ሕግ ተገልጸው በተወሰኑ ባለጉዳዮች፤
3. በፌዴራል መንግሥቱ ሕገ መንግሥት ወይም በሕግ በተገለጹ ቦታዎች ላይ የዳኝነት ሥልጣን ይኖራቸዋል።

4. **የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን**[5]

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በሚከተሉት የወንጀል ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ሥልጣን ይኖራቸዋል፤

1. በመንግሥት ግዛት ሀገር ላይ በሚፈጸሙ ወንጀሎች፤
2. በውጭ ሀገር መንግሥት ላይ በሚፈጸሙ ወንጀሎች፤
3. በሰው ልጆች መብት ላይ በሚፈጸሙ ወንጀሎች፤
4. በፌዴራል መንግሥቱ የቀረጥና የግብር ገቢዎች፣ በጠቅላላ የገንዘብ ጥቅሞች ላይ በሚፈጸሙ ወንጀሎች፤
5. የሐሰት ገንዘብን በሚመለከቱ ወንጀሎች፤
6. በፌዴራል መንግሥት ሰነዶች ላይ የሐሰት ስራ በመሥራት በሚፈጸሙ ወንጀሎች፤
7. ከአንድ ክልል በላይ ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ አገልግሎት በሚሰጡ መገናኛዎች ፀጥታና ነጻነት ላይ በሚፈጸሙ ወንጀሎች፤
8. የበረራ ደህንነትን በሚመለከቱ ወንጀሎች፤
9. ዓለም አቀፍ የዲፕሎማቲክ ሕጎችና ልምዶች እንዲሁም ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸው ሌሎች ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ልዩ

[5] የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እና (9) በማሻሻያ አዋጅ 9/41(1995)አ.321 አንቀጽ 2(1) እስከ (3) መሰረት ነባሮቹ ተሰርዘው ተተክተዋል፡፡ እንዲሁም ንዑስ አንቀፅ (13) እና (14) አዲስ የተጨመሩ ናቸው፡፡

መብትና ጥበቃ ያላቸው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ የውጭ ሀገር ሰዎች ተበዳይ ወይም ተከሳሽ የሆኑባቸው ወንጀሎች፣ እንዲሁም የዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ (3) እና አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (3) እንደተጠበቀ ሆኖ ከ5 ዓመት ጽኑ እሥራት በላይ ሊያስቀጡ የሚችሉ የውጭ ሀገር ዜጎች ተበዳይ ወይም ተከሳሽ የሆኑባቸው ወንጀሎች፤

10. የአደገኛና አደንዛዥ ዕጾች ሕገ ወጥ ዝውውርን በሚመለከቱ ወንጀሎች፤
11. በተለያዩ ክልሎች ወይም በፌዴራልና በክልል ፍርድ ቤቶች የሥልጣን ክልል ሥር በሚወድቁና በተያያዙ ወንጀሎች፤
12. የፌዴራል መንግሥቱ ባለሥልጣኖችና ሠራተኞች በሥራቸው ወይም በኃላፊነታቸው ምክንያት ተጠያቂ በሚሆኑባቸው የወንጀል ጉዳዮች፡፡
13. በተለያዩ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦች፣ ጎሣዎች፣ በሃይማኖት ተከታዮች ወይም በፖለቲካ ቡድኖች መካከል ከተፈጠረ ግጭት ጋር የተያያዙ ወንጀሎች፤
14. በፌዴራል መንግሥቱ ንብረቶች ላይ በሚፈጸሙ እና የዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ (3) እና አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (3) እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ከ5 ዓመት ጽኑ እሥራት በላይ ሊያስቀጡ የሚችሉ ወንጀሎች

5. <u>የፍትሐ ብሔር የዳኝነት ሥልጣን</u>

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በሚከተሉት የፍትሐ ብሔር ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ሥልጣን ይኖራቸዋል፤

1. የፌዴራል መንግሥቱ አካል ተከራካሪ በሆነበት ጉዳይ፤
2. መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ በሆኑ ሰዎች መካከል በሚነሱ ክርክሮች፤
3. የፌዴራል መንግሥቱ ባለሥልጣኖችና ሠራተኞች በሥራቸው ወይም በኃላፊነታቸው ምክንያት ተጠያቂ በሚሆኑባቸው ጉዳዮች፤
4. የውጭ ሀገር ዜጋ ተከራካሪ በሆነበት ጉዳይ፤
5. ዜግነትን በሚመለከቱ፤ ጉዳዮች ላይ በሚነሱ ክርክሮች፤
6. በፌዴራል መንግሥቱ አካላት የተመዘገቡ ወይም የተቋቋሙ የንግድ ድርጅቶችና ማህበሮችን በሚመለከት በሚነሱ ክርክሮች፤
7. በሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች (ኔጎሽየብል ኢንስትሩመንትስ) ላይ በሚነሱ ክርክሮች፤

8. በፈጠራ፣ በድርሰትና ሥነ ጥበብ ባለቤትነት መብቶች ላይ በሚነሱ ክርክሮች፤
9. በኢንሹራንስ ውል ላይ በሚነሱ ክርክሮች፤
10. ተገዶ የመያዝ ሕጋዊነትን ለማጣራት በሚቀርብ አቤቱታ፡፡

6. <u>የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስለሚሠሩባቸው የፍሬ ነገር ሕጎች</u>

1. የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሥልጣን ክልላቸውን መሠረት አድርገው የሚቀርቡላቸውን ጉዳዮች ወይም ክርክሮች፤
   ሀ/ የፌዴራል መንግሥቱን ሕጎችና ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን መሠረት በማድረግ ይዳኛሉ፤
   ለ/ ጉዳዩ የክልል ሕግን የሚመለከት ሆኖ ሲገኝ በክልሉ ሕግ መሠረት ይዳኛሉ።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንጽ (1)(ለ) መሠረት ተፈጸሚ የሚሆነው የክልል ሕግ በፌዴራል መንግሥቱ ሕጎችና ከዓለም አቀፍ ስምምነቶች ጋር የሚጋጭ ከሆነ በጉዳዩ ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡
3. የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የያዙት ጉዳይ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ከመስጠታቸው በፊት ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ይልኩታል።

7. <u>የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስለሚሠሩባቸው የሥነ ሥርዓት ሕጎች</u>

ከዚህ አዋጅ ጋር የማይጋጩ በሥራ ላይ ያሉ የወንጀለኛና የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጎች እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎች በዚህ አዋጅ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>ስለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን</u>

8. <u>የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን</u>

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ ብቸኛ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፤

1. የፌዴራል መንግሥቱ ባለሥልጣኖች በሥራ ኃላፊነታቸው ምክንያት ተጠያቂ በሚሆኑባቸው የወንጀል ጉዳዮች፤

2. ዓለም አቀፍ የዲፕሎማቲክ ሕጎችና ልምዶች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የውጭ ሀገር አምባሳደሮች ቆንስላዎች እንዲሁም የዓለም አቀፍ ድርጅቶችና የውጭ መንግሥታት ወኪሎች ተጠያቂ በሚሆኑባቸው የወንጀል ጉዳዮች፣
3. በሕግ በሚወሰነው መሠረት አንድ ጉዳይ ከአንድ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወደ ሌላ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም ወደራሱ እንዲዛወር በሚቀርብ ጥያቄ፡፡

9. **የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ ሥልጣን**

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚከተሉትን ጉዳዮች በይግባኝ የማየት ሥልጣን ይኖረዋል፣

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣኑ ውሣኔ የሰጠባቸውን ጉዳዮች፣
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ ሰሚነት ሥልጣኑ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሰጠው ውሣኔ የተለየ ውሣኔ የሰጠባቸውን ጉዳዮች።

10. **የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥልጣን**[6]

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ያለባቸውን የሚከተሉትን ጉዳዮች በሰበር የማየት ሥልጣን ይኖረዋል፣

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሣኔ የሰጠባቸውን ጉዳዮች፣
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት የመጨረሻ ውሣኔ የሰጠባቸውን ጉዳዮች፣
3. የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት ወይም በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠባቸውን ጉዳዮች።
4. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ችሎት የሚሰጠው የሕግ ትርጉም በየትኛውም ደረጃ ላይ በሚገኝ የፌዴራል ወይም የክልል ፍርድ ቤት ላይ አስገዳጅነት ይኖረዋል፡፡ ሆኖም የሰበር ችሎቱ በሌላ ጊዜ በተመሳሳይ ጭብጥ የተለየ ትርጉም ሊሰጥ ይችላል፡፡

[6] የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (4) እና (5) በማሻሻያ አዋጁ 11/42(1997) አ.454 መሰረት የተጨመሩ ናቸው፡፡

5. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሰጠባቸውን ውሳኔዎች በየደረጃው ላሉ ፍ/ቤቶችና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት አሳትሞ ያሰራጫል፡፡

## ክፍል አራት

## ስለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን

### 11.የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የፍትሐ ብሔር የዳኝነት ሥልጣን

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግምታቸው ከአምስት መቶ ሺህ (500,000) ብር በላይ በሆኑ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፤

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በአንቀጽ 3 እና 5 መሠረት በሚቀርቡ የፌዴራል የፍትሐ ብሔር ጉዳዮች፤

ለ/ በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ ውስጥ በሚነሱ በሌሎች የፍትሐ ብሔር ጉዳዮች።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) ድንጋጌ ቢኖርም፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፤

ሀ/ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን (ፕራይቬት ኢንተርናሽናል ሎው) በሚመለከቱ ጉዳዮች፤

ለ/ ዜግነትን በሚመለከቱ ጉዳዮች፤

ሐ/ የውጭ ሀገርን ፍርድ ወይም ብይን ለማስፈጸም በሚቀርብ አቤቱታ፤

መ/ በሕግ በሚወሰነው መሠረት አንድን ጉዳይ ከአንድ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወደ ሌላ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወይም ወደ ራሱ እንዲዛወር በሚቀርብ ጥያቄ፡፡

**12.የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን[7]**

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፤

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (1)፣ (2)፣ (3)፣ (8)፣ (10) እና (13) በተመለከቱት የወንጀል ጉዳዮች፤
2. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ (9) የውጭ ሀገር ዜጎችን እንዲሁም አንቀፅ (14)ን[8] በሚመለከቱና በስራ ላይ ባሉት ሕጎች ለከፍተኛ ፍርድ ቤት በተሰጡት የወንጀል ጉዳዮች፤
3. በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ ከተሞች ውስጥ በሚነሱና በስራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለከፍተኛ ፍርድ ቤት በተሰጡ በሌሎች የወንጀል ጉዳዮች፡፡

**13.የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ሥልጣን**

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በይግባኝ የማየት ሥልጣን ይኖረዋል።

**14.የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የፍትሐ ብሔር የዳኝነት ሥልጣን**

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ግምታቸው እስከ ብር አምስት መቶ ሺህ (500,000 ብር) በሚደርስ ወይም ግምታቸው በገንዘብ ሊተመን በማይችል በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የፍትሐ ብሔር የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 እና አንቀጽ 11(2) ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትና ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በአንቀጽ 3 እና 5 መሠረት በሚቀርቡ የፌዴራል የፍትሐ ብሔር ጉዳዮች፤
2. በሕግ ለሌሎች አካላት የተሰጠው የዳኝነት ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተማ ውስጥ በሚነሱ በሌሎች የፍትሐ ብሔር ጉዳዮች ።

**15.የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን[9]**

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሚከተሉት የወንጀል ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፤

---

[7] ይህ አንቀፅ በማሻሻያ አዋጁ 9/41(1995)አ.321 አንቀፅ 4 መሰረት የቀድሞው ተሰርዞ ተተክቷል፡፡

[8] ንዑስ አንቀፅ 14 መሆን ነበረበት

[9] ይህ አንቀጽ በማሻሻያ አዋጁ 9/41(1995)አ.321 አንቀጽ 5 መሰረት ተሰርዞ በአዲስ ተተክቷል፡፡

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (4)፣ (5)፣ (6) እና (7) በተመለከቱት የወንጀል ጉዳዮች፤
2. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ (9) የውጪ ሀገር ዜጎችን እንዲሁም ንዑስ አንቀፅ (14)ን በሚመለከቱና በስራ ላይ ባሉት ሕጎች ለወረዳና ለአውራጃ ፍርድ ቤት በተሰጡ የወንጀል ገዳዮች፤
3. በሕግ ለሌሎች አካላት የተሰጠው የዳኝነት ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተሞች ውስጥ በሚነሱና በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለአውራጃና ለወረዳ ፍርድ ቤቶች በተሰጡ በሌሎች የወንጀል ጉዳዮች።

## ክፍል አምስት

## ስለ ፌዴራል ፍርድ ቤቶች ፕሬዚዳንቶች

### 16.የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት በሕግ መሠረት የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን ለማስተዳደር ኃላፊ ይሆናል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፤[10]

   ሀ/ ለፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የፌዴራል ፍርድ ቤት ዳኞችን ይደለድላል፣ ሥራ ይሰጣል፣ ያስተዳድራል፤

   ለ/ ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞችን ይቀጥራል፤

   ሐ/ የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ሥራ ላይ ያውላል፤ የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን የዳኝነት ሥልጣን በውክልና ለሚሰሩ የክልል ፍርድ ቤቶች የበጀት ማካካሻ ጥያቄ ሲቀርብ አስተያየቱን ይሰጣል፤

   መ/ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሕግ መጽሔት እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤

   ሠ/ ስለ ፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሥራ በስታስቲክስ የተደገፈ መግለጫ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ የክልል ፍርድ ቤቶች የፌዴራል ጉዳዮችን

---

[10] የዚህ ንዑስ አንቀፅ ፊደል (ሀ) እና (ለ) በማሻሻያ አዋጁ 5/15(1991)አ.138 አንቀጽ 2(3) መሰረት ተሰርዘው ተተክተዋል።

አስመልክቶ ስላከናወኑት ተግባር በስታትስቲክስ ተደገፈ ሪፖርት እንዲቀርብ ያደርጋል፤

ረ/ የዳኞችና የሌሎች ሠራተኞች ትምህርትና ሥልጠና የሚካሄድበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

ሰ/ በክልል ስለሚታዩ የፌዴራል ጉዳዮች የመዝገብ አያያዝና ጠቅላላ አሠራር ከክልል ፍርድ ቤት ጋር በመመካከር የሚሻሻልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

ሸ/ ስለፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥራ አካሄድ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥናታዊ ዘገባዎችን ያቀርባል፤

ቀ/ ትምህርታዊ የሆኑ የዓመቱ ፍርዶችና ውሳኔዎች ተመርጠው እንዲታተሙ ያደርጋል፤

በ/ የተከላካይ ጠበቆችን ቢሮ ያደራጃል፤

ተ/ በሕግ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፡፡

3. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው፤[11]

ሀ/ ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለፌዴራል ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንቶች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

ለ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ለ የተመለከተውን ሥልጣን በሥራ ላይ ሲያውል የፌዴራል ከፍተኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንቶችን ፍርድ ቤቶቻቸውን በሚመለከት በተናጠልም ሆነ በጋራ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

**17.<u>የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት</u>**

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት፤

1. በፕሬዚዳንት የሚመራለትን ሥራ ያከናውናል፤
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት በማይኖርበት ጊዜ ፕሬዚዳንቱን ተክቶ ይሠራል፡፡

**18.<u>ስለ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንቶች ሥልጣንና ተግባር</u>**[12]

[11] ይህ ንዐሰ አንቀጽ በማሻሻያ አዋጁ 5/15(1991)አ.138 አንቀጽ 2(4) መሰረት የተጨመረ ነው፡፡

[12] የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) በማሻሻያ አዋጁ 5/15(1991)አ.138 አንቀጽ 2(5) መሰረት ተሰርዘው ተተክተዋል፡፡

የየፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንት፤

1. ፍርድ ቤቱን ይወክላል፣ ለዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት በሚሰጠው ውክልናና መመሪያ መሠረት የፍርድ ቤቱን ዳኞች ይደለድላል፤ ሥራ ይሰጣል፣ ያስተዳድራል፤
2. በአዋጁ አንቀጽ 16(3) 'ሀ' እንደተመለከተው በሚሰጠው ውክልናና መመሪያ መሠረት የፍርድ ቤቱን ሠራተኞች ያስተዳድራል፤
3. ስለ ፍርድ ቤቱ በስታትስቲክስ የተደገፈ መግለጫ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤
4. የፍርድ ቤቱን ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፤
5. ትምህርታዊ የሆኑ የየዓመቱ ፍርዶችና ውሳኔዎች ተመርጠው ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት እንዲላኩ ያደርጋል፤
6. ስለ ሥራው እንቅስቃሴ በየጊዜው ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ሪፖርት ያቀርባል፤
7. በሕግ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>ስለ ፌዴራል ፍርድ ቤቶች አደረጃጀትና የዳኝነት ሥራ አካሄድ</u>

19.<u>**የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞችና ሌሎች ሠራተኞች**</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አንድ ፕሬዚዳንት፣ አንድ ምክትል ፕሬዚዳንት እንዲሁም ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ዳኞች ይኖሩታል፡፡
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለሥራው የሚያስፈልጉ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

20.<u>**የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ችሎቶች**</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚከተሉት ችሎቶች ይኖሩታል፤
   ሀ/ የፍትሐ ብሔር ችሎት
   ለ/ የወንጀል ችሎት፤ እና
   ሐ/ የሥራ ክርክር ችሎት፡፡
2. በእያንዳንዱ ችሎት አንድ ሰብሳቢና ሁለት ዳኞች ሆነው ያስችላሉ።
3. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት በማናቸውም ችሎት ሰብሳቢ ሆኖ ሊሠራ ይችላል፡፡

## 21. ከአምስት ያላነሱ ዳኞች ስለሚሰየሙበት ችሎት

1. የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት በራሱ አነሳሽነት ወይም በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ችሎት አሳሳቢነት ወይም ከተከራካሪ ወገኖች ባንዱ ጥያቄ ሲቀርብለት አንድን ጉዳይ ከአምስት ያላነሱ ዳኞች ተሰይመው እንዲያዩት ለማድረግ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ጉዳዮች የሚታዩት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት ይሆናል፤[13]

   ሀ/ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ችሎቶች መካከል መሠረታዊ የሆነ የትርጉም ልዩነት የተፈጠረበትን ሕግ የሚመለከቱ ጉዳዮች ሲከሰቱ፤

   ለ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 የተጠቀሱት ጉዳዮች በሰበር እንዲሰሙ ሲወሰን።

## 22.የሰበር አቤቱታ አቀራረብ ሥነ ሥርዓት

1. አንድ ውሣኔ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 መሠረት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር የሚሰማው አስቀድሞ ሦስት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች የተሰየመበት ችሎት ውሣኔው ለሰበር የሚያበቃ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት ብሎ ሲወስን ነው፡፡
2. ጉዳዩ በሰበር እንዲታይለት የሚፈልግ አቤቱታ አቅራቢ ጉዳዩ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት የሚልበትን ምክንያት በማመልከቻው ላይ በዝርዝር ጽፎ ማቅረብ አለበት፡፡
3. አቤት ባዩ ከማመልከቻው በተጨማሪ ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔና የበታች ፍርድ ቤት ውሣኔ ቅጂዎችን ማቅረብ አለበት፡፡
4. የሰበር ጥያቄ ማመልከቻ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መቅረብ የሚገባው የሰበር ጥያቄ በሚቀርብበት ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ውሣኔ በተሰጠ በዘጠና ቀን ውስጥ ይሆናል፡፡

## 23.የፌዴራል ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ችሎቶች[14]

---

[13] የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (2) ሀ በማሻሻያው አዋጅ 11/42(1997) አ.454 መሰረት ተሰርዞ ፊደል ተራ (ለ) እና (ሐ) የነበሩት እንደቅደም ተከተላቸው (ሀ) እና (ለ) ሆነው ሆነዋል።

[14] ይህ አንቀፅ በማሻሻያ አዋጁ 11/42(1997) አ.454 (አዋጅ ቁጥር 138/ 1991 አንቀጽ 2(6) እንደተሻሻለ) መሰረት ተሰርዞ ተተክቷል፡፡

1. የፌዴራል ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ለሥራቸው አስፈላጊ የሆኑ ችሎቶች ይኖሯቸዋል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ችሎቶች በአንድ ዳኛ ያስችላሉ፡፡
3. ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 2 የተደነገገው ቢኖርም፡-
   ሀ/ ከ15 ዓመት በላይ ጽኑ እሥራት የሚያስቀጡ በከፍተኛው ፍርድ ቤት የሚቀርቡ የወንጀል ክሶች ሦስት ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት ይታያሉ፡፡
   ለ/ የፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ በዚህ አዋጅ በአንድ ዳኛ እንዲታዩ የተወሰኑት ጉዳዮች በሦስት ዳኞች እንዲታዩ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡
4. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት እንዲሁም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት በየፍርድ ቤቶቻቸው በየትኛውም ችሎት ሊያስችሉ ይችላሉ፡፡

24. <u>ስለማስቻያ ሥፍራ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የማስቻያ ሥፍራ አዲስ አበባ ይሆናል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶችና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች የማስቻያ ሥፍራ በአዲስ አበባ ከተማ፣ በድሬዳዋ ከተማ እና በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 78 (2) በሚወሰነው መሠረት ይሆናል፡፡
3. በየትኛውም እርከን ላይ የሚገኝ የፌዴራል ፍርድ ቤት ቀልጣፋ ፍትሕ ለመስጠት አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ለዳኝነት ሥራ በተመደበለት ክልል ወይም አካባቢ በማንኛውም ስፍራ ተዘዋውሮ ሊያስችል ይችላል፡፡

25. <u>የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሥራ ቋንቋ</u>

1. የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የችሎት ቋንቋ አማርኛ ይሆናል፡፡
2. የአማርኛ ቋንቋ ለማይችል ባለጉዳይ ፍርድ ቤቱ አስተርጓሚ ይመደብለታል፡፡

26. <u>በግልጽ ችሎት ስለማስቻል</u>

1. ፍርድ ቤቶች ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ሁኔታ ያስችላሉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ቢኖርም ለዳኝነት አሠራር አግባብነት ያላቸው የሥነ ሥርዓት ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ በዝግ ችሎት ያስችላሉ፤
   ሀ/ ለሕዝብና ለመንግሥት ሰላምና ፀጥታ አስፈላጊ ሲሆን፣ ወይም

ለ/ ለሕዝብ መልካም ጠባይ ወይም ግብረገብነት ሲባል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፡፡

**27.<u>የዳኞች ከችሎት መነሳት</u>**

1. አንድ የፌዴራል ፍርድ ቤት ዳኛ ከዚህ ቀጥሎ ከተመለከቱት ምክንያቶች በአንዱ ከችሎት ይነሳል፤

   ሀ/ ዳኛው ከተከራካሪዎቹ ከአንደኛው ወገን ወይም ከጠበቃው ጋር የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው እንደሆነ፤

   ለ/ ዳኛው ከተከራካሪዎቹ የአንደኛው ወገን ሞግዚት፣ ነገረ ፈጅ ወይም ጠበቃ በሆነበት ጉዳይ ላይ የተነሳ ክርክር የሆነ እንደሆነ፤

   ሐ/ ዳኛው ክርክር የተነሣበትን ጉዳይ አስቀድሞ በዳኝነት ወይም በእርቅ መንገድ ያየው ወይም የሚያውቀው ሆኖ የተገኘ እንደሆነ፤

   መ/ ዳኛው ከተከራካሪዎቹ ወገኖች ከአንደኛው ወይም ከጠበቃው ጋር በፍርድ ቤት የተያዘ ክርክር ወይም ሙግት ያለው እንደሆነ፤

   ሠ/ ከዚህ በላይ ከ(ሀ) እስከ (መ) ከተመለከቱት ምክንያቶች ውጭ ትክክለኛ ፍትሕ አይሰጥም የሚያሰኝ ሌላ በቂ ምክንያት ሲኖር፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ዳኛው በችሎት ላይ ሊቀመጥ የማይገባው መሆኑን ሲያውቅ ከችሎት ተነስቶ ሌላ ዳኛ መተካት አለበት፡፡

**28.<u>ዳኛ ከችሎት እንዲነሳ ስለማመልከት</u>**

1. ከተከራካሪዎች አንደኛው በአንቀጽ 27 በተዘረዘሩት ምክንያቶች መሠረት አንድ ዳኛ ከችሎት መነሳት የሚገባው መስሎ የታየው እንደሆነ ለፍርድ ቤቱ ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል፡፡

2. ማመልከቻው የሚቀርበው ክርክሩ ከመጀመሩ በፊት ወይም ማመልከቻ ለማቅረብ ምክንያት መኖሩን አመልካቹ እንዳወቀ ወዲያውኑ መሆን አለበት፡፡

3. አንድ ዳኛ ብቻውን የሚያስችል ከሆነ ከችሎት ስለመነሳት የሚቀርብለትን ማመልከቻ ተመልክቶ ጥያቄውን የተቀበለው እንደሆነ ከችሎት ይነሳል፡፡ ጥያቄውን ያልተቀበለው እንደሆነ ግን በዚያው ፍርድ ቤት በሚገኝ ሌላ ችሎት፣ ሌላ ችሎት ከሌለ የዚህኑ ፍርድ ቤት ውሣኔ ይግባኝ በሚያየው ፍርድ ቤት እንዲወሰን ማስተላለፍ አለበት፡፡

4. ከችሎት እንዲነሳ ማመልከቻ የቀረበበት ዳኛ ከሌሎች ዳኞች ጋር በሚያስችልበት ጊዜ ከሆነ ማመልከቻ የቀረበበት ዳኛ በሌለበት በቀረው ዳኛ ወይም ዳኞች ማመልከቻው ውሣኔ ያገኛል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) መሠረት የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻና ይግባኝ የማይባልበት ይሆናል፡፡
6. የሚሰጠውን ማናቸውንም ውሣኔ ዳኛው ወዲያውኑ መፈጸም አለበት።

29.<u>ማመልከቻው ስለሚያስከትለው ኪሣራ</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 መሠረት ዳኛ ከችሎት እንዲነሣ የሚቀርበው ማመልከቻ ያስከተለው ኪሣራ ከዋናው ነገር ኪሣራ ጋር ይጠቃለላል፡፡ ነገር ግን ፍርድ ቤቱ ማመልከቻውን ተገቢ አይደለም በማለት ሳይቀበለው ከቀረ የዋናውን ነገር ውጤት ሳይመለከት ኪሣራውን የሚከፍለው ማመልከቻውን ያቀረበው ሰው ይሆናል ፡፡

30.<u>በቂ ምክንያት ሳይኖር የሚቀርብ ማመልከቻ ስለሚያስከትለው ቅጣት</u>

ከተከራካሪዎቹ አንደኛው ወገን ዳኛው ከችሎት እንዲነሣለት ያቀረበው ማመልከቻ በቂ ምክንያት ሳይኖረው የቀረ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ማመልከቻውን ውድቅ አድርጎ በአመልካቹ ላይ እስከ አምስት መቶ (500 ብር) መቀጫ ሊጥልበት ይችላል፡፡

<u>ክፍል ሰባት</u>

<u>ስለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባዔ</u>

31.<u>የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባዔ</u>

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አንድ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባዔ (ከዚህ በኋላ "ጉባዔው" እየተባለ የሚጠራ) ይኖረዋል።

32.<u>የጉባዔው አባላት</u>

1. የጉባዔው አባላት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንቶችና የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ፕሬዚዳንቶች ይሆናሉ፡፡
2. በጉባዔው ላይ የፍትሕ ሚኒስትር[15] ይሳተፋል፣ ሆኖም ድምጽ የመስጠት መብት አይኖረውም፡፡

[15] በ22/62(2008) አ. 943 መሰረት ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ተብሎ ይነበባል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ያልተጠቀሱ ዳኞች እና አግባብ ያላቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን፣ ማኅበራትን፣ ድርጅቶችን፣ የሕግ ፋክልቲዎችን እና የሳይንስ ተቋሞችን የሚወክሉ ሰዎች ወይም ሌሎች ግለሰቦች በጉባዔው እንዲሳተፉ ሊጋበዙ ይችላሉ፣ ሆኖም ድምጽ የመስጠት መብት አይኖራቸውም፡፡

33.<u>የጉባዔው ሥልጣንና ተግባር</u>

ጉባዔው ከዚህ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

1. በዳኝነት ሥራ አስተዳደር ረገድ ባጋጠሙ ችግሮች ላይ ተወያይቶ መፍትሔ መስጠት፣
2. የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት አሠራርን ለማሻሻል የሚረዱ መመሪያዎችና ውሳኔዎችን ማሳለፍ፣
3. አዳዲስ ሕጎች እንዲወጡ ወይም ነባር ሕጎች እንዲሻሻሉ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሃሣብ ማቅረብ፣
4. የዳኝነት ሥራ አካሄድን ለማቀላጠፍና ለማጠናከር የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ማከናወን፣ እና
5. ለጉባዔው ሥራ አፈፃፀም አስፈላጊውን ደንብ ማውጣት፡፡

34.<u>የጉባዔው አሠራር</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት የጉባዔው ሰብሳቢ ይሆናል፡፡
2. ጉባዔው የራሱን ፀሐፊ ይመድባል፡፡
3. ጉባዔው በዓመት አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጨማሪ ስብሰባም መጥራት ይችላል፡፡
4. ከጉባዔው አባላት ሁለት ሦስተኛው ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል። ውሣኔ በድምጽ ብልጫ ይሰጣል፤ ድምጽ እኩል ለእኩል በተከፈለ ጊዜ የጉባዔው ሰብሳቢ ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።

## <u>ክፍል ስምንት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

35.<u>የፍርድ ቤት ውሣኔዎችና ትዕዛዞች</u>

1. በማናቸውም ደረጃ የሚገኙ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚሰጧቸው ውሣኔዎችና ትዕዛዞች በክልል ፍርድ ቤቶች እንዲፈጸሙ የፌዴራሉ ፍርድ ቤቶች ማዘዝ ይችላሉ።

2. አንድን ጉዳይ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የክልል ወይም የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሥልጣናችን ነው ብለው የያዙት ወይም ሥልጣናችን አይደለም ብለው የመለሱት እንደሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተገቢውን ትዕዛዝ መስጠት ይችላል።

36.**በፍርድ ቤት በመታየት ላይ ስላሉ ጉዳዮች**

ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በማዕከላዊ ፍርድ ቤቶች እንዲሁም በክልል 14 እና በድሬዳዋ ፍርድ ቤቶች በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮች በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ሥልጣን ወዳላቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ተዛውረው ይታያሉ፡፡

37.**የተሻሩ ሕጎችና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

1. የማዕከላዊ የሽግግር መንግሥት ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 40/1985 (እንደተሻሻለ) በዚህ አዋጅ ተሽሯል።
2. ይህን አዋጅ የሚቃረን ወይም በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን የሚመለከት ማናቸውም ሕግ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

38.**መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**[16]

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሥራ ላይ የሚገኙ ሕጎችን ሳይቃረን አስፈላጊ የሆኑ የሥነ ሥርዓት መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

39.**አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከየካቲት 7 ቀን 1988 ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት 7 ቀን 1988 ዓ.ም**

**ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ**

---

[16] ይህ አንቀፅ በማሻሻያ አዋጁ 11/42(1997) አ.454 አንቀጽ 4 መሰረት አዲስ የገባ ነው። በዚህም ምክንያት የቀድሞው አንቀጽ 37 አንቀጽ 38 ሆኖ ተሸጋሽጓል።

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**አዋጅ ቁጥር 188/1992**

**የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን አቋም ለማጠናከር የወጣ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት በአንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት የጋብቻ፣ የግልና የቤተሰብ መብት ላይ የሚነሱ የሕግ ጉዳዮችን አስመልክቶ በፈቃደኝነት ላይ በተመሰረተ ሁኔታ በባህላዊና በሃይማኖት ሕጐች ለመዳኘት የሚቻል በመሆኑ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 78 ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት የባሕልና የሃይማኖት ሕጐችን መሠረት አድርገው የሚዳኙ ሃይማኖታዊና ባህላዊ የፍርድ ተቋማት በሌሉ ጊዜ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የክልል ምክር ቤቶች እነዚህን ተቋማት እንደአስፈላጊነቱ እንዲያቋቁሙ ሥልጣን የተሰጠ በመሆኑ፤

ከሕገ መንግሥቱ መጽደቅ በፊት በሥራ ላይ የነበሩና የመንግሥት ዕውቅና የነበራቸው ሃይማኖታዊና ባህላዊ የፍርድ ተቋማት ሕገ መንግሥቱ በሚሰጠው ዕውቅና መሠረት በአዲስ መልክ ሊደራጁ እንደሚችሉ በተደነገገው መሠረት፤ ቀደም ሲል ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ ተቋቁመው እንዳችም የማሻሻያ ለውጥ ሳይደረግባቸው ባሉበት ሁኔታ እንዲቆዩ የተደረጉትን የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አቋም ብቃት ባለው ሁኔታ እንዲደራጁ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55 (1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን አቋም ለማጠናከር የወጣ አዋጅ ቁጥር 188/1992" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

በዚህ አዋጅ ወስጥ፤

1. "ቃዲ" ማለት በሸሪያ ፍርድ ቤቶች ውስጥ በየትኛውም ደረጃ ተሾሞ የሚሠራ ዳኛ ነው፤
2. "ዋና ቃዲ" ማለት የፌደራል ጠቅላይ ሸሪያ ፍርድ ቤት የበላይ ወይም ሰብሳቢ ቃዲ ነው፤
3. "ተጠሪዎች" ማለት የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤትና የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ኃላፊዎች ሆነው የየፍርድ ቤቶቻቸውን ሥራ የሚመሩ ቃዲዎች ናቸው፤
4. "የፌዴሪል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች" ማለት የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ፤ የከፍተኛ ሸሪዓ እና የጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ናቸው፤
5. "የፍትሐብሄር ሥነ ሥርዓት ሕጎች" ማለት በ1957 ዓ.ም የወጣውን የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግና እርሱን ለማሻሻል በየጊዜው የወጡና ወደፊትም የሚወጡትን ይጨምራል፤
6. "የፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ" ማለት በአዋጅ ቁጥር 24/1988[17] የተቋቋመው ጉባኤ ነው።

3. **መቋቋም**

ተጠሪነታቸው ለፌዴራሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የሆኑ፤

ሀ/ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት፤

ለ/ የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት፤ እና

[17] ይህ አዋጅ በ16/41(2002) አ.684 ተሽሯል፡፡

ሐ/ የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ተቋቁመዋል።

## ክፍል ሁለት

## ስለፍርድ ቤቶች የወል የዳኝነት ሥልጣን

4. ***መሠረቱ***

1. የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ከዚህ በታች በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ የወል የዳኝነት ሥልጣን ይኖራቸዋል፡፡

   ሀ/ ማናቸውም የጋብቻ፣ የፍቺ፣ የቀለብ አወሳሰን፣ አካለ መጠን ያልደረሱ ሕፃናት ሞግዚትነት እና በቤተሰብ ተዛምዶ ላይ የሚነሱ ጉዳዮችን አስመልክቶ ሃይማኖት ሥርዓት መሠረት የተፈጸመ የሆነ እንደሆነ ወይም ባለጉዳዮቹ በእስልምና ሃይማኖት ሥርዓት ለመዳኘት ፈቅደው ከሆነ፤

   ለ/ የወቅፍ፣ የስጦታ (ሂባ) የውርስ ወይም የኑዛዜ ጉዳዮችን በተመለከተ አውራሽ ወይም ስጦታ አድራጊ ወይም ተናዛዡ ሙስሊም የሆነ እንደሆነ፤ ወይም ሟች በሞተበት ሰዓት ሙስሊም ሆኖ የሞተ እንደሆነ፤

   ሐ/ ከፍ ብሎ ከ(ሀ) እስከ (ለ) በተገለጹት ጉዳዮች በሚቀርቡ ክሶች ኪሳራ መወሰንን በተመለከተ፤

2. በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ (5) በተገለጸው መሠረት ከፍ ብሎ በተገለጹት ጉዳዮች ላይ ፍ/ቤቶቹ የዳኝነት ሥልጣን የሚኖራቸው ተከራካሪ ወገኖች በእስልምናው ሃይማኖት ሥርዓት ለመዳኘት ግልጽ በሆነ መንገድ በፈቃዳቸው መርጠው የቀረቡ ከሆነ ብቻ ይሆናል፡፡

5. ***ፈቃደኝነትን ወይም ተቃውሞን ስለመወሰን***

1. ከተከራካሪ ወገኖች አንዱ በሸሪዓ ፍ/ቤት ለመዳኘት አቤቱታ ሲያቀርብ ጉዳዩ የቀረበለት የሸሪዓ ፍርድ ቤት ሌላው ተከራካሪ ወገን በፍ/ቤቱ ለመዳኘት ፈቃደኛ መሆን አለመሆኑን ከዚህ አዋጅ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ቅጽ መሠረት ቀርቦ እንዲያረጋግጥ መጥሪያ ይልክለታል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) በተገለጸው መሠረት የፍርድ ቤቱ መጥሪያ በአግባቡ እንዲደርሰው የተደረገ ተከራካሪ ወገን ተቃውሞውን ወይም ፈቃደኛነቱን ለፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር ቀርቦ ካላረጋገጠ ተቃውሞ ለማቅረብ እንዳልፈለገ ተቆጥሮ ጉዳዩ በሌለበት ይታያል፡፡

3. በፍርድ ቤቶቹ ለመዳኘነት በተከሪካሪ ወገኖች መካከል ግልጽ በሆነ መንገድ ስምምነት በሌለ ጊዜ ጉዳዩ የቀረበለት የሸሪዓ ፍርድ ቤት ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን በመደበኛ ፍርድ ቤት እንዲያስወስኑ ጉዳዩን ሥልጣን ላለው የፌዴራል መደበኛ ፍ/ቤት ያስተላልፋል፡፡
4. በተከሪካሪ ወገኖች ፈቃድ ላይ ተመስርተው በሸሪዓ ፍርድ በመታየት ላይ የሚገኙ ጉዳዮችን በማናቸውም ምክንያት ወደ መደበኛው ፍርድ ቤት፤ ወይም በመደበኛው ፍርድ ቤት በመታየት ላይ የሚገኙ ጉዳዮችን ወደ ሸሪዓ ፍ/ቤት ተዘዋውረው እንዲታዩ ማድረግ አይቻልም።

6. **ፍርድ ቤቶቹ ስለሚሠሩባቸው ሕጐች**

1. የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የሥልጣን ክልላቸውን መሠረት አድርገው የቀረበላቸውን ጉዳዮች ሲመረምሩ የሸሪዓውን ሕግ መሠረት አድርገው ይዳኛሉ።
2. ፍርድ ቤቶቹ የያዟቸውን ጉዳዮች ሥርዓት ባለው ሁኔታ ለመምራትን እንዲያስችላቸው በሥራ ላይ ያሉትን የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጐች ተከትለው ይሠራሉ፡፡

7. **ፍርድ ቤትን ስለመድፈር**

ማንም ሰው የፍርድ ሥራ በሚከናወንበት ጊዜ በማናቸውም ዓይነት መንገድ የችሎት መድፈር ተግባር የፈጸመ ወይም ያለበቂ ምክንያት የችሎቱን ትዕዛዝ ያላከበረ እንደሆነ አንድ ወር በሚደርስ እሥራት ወይም እስከ ብር 1000 (አንድ ሺህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

**ክፍል ሦስት**

**የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን**

8. **የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን**

የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፤

1. የፌደራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣኑ ውሳኔ በሰጠባቸው ጉዳዮች፤
2. የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በይግባኝ ሰሚነት ሥልጣን በሰጠው በማናቸውም ውሳኔ የሚቀርቡ ጉዳዮች፡፡

9. **የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ግምታቸው ከብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ) በላይ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል።
2. የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የፌዴሪል የመጀመሪ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የወሰነውን ውሳኔ በይግባኝ የማየት ሥልጣን ይኖረዋል።
3. አንድን ጉዳይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ወደ ሌላ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወይም ወደ ራሱ እንዲዛወር የሚቀርብን ጉዳይ ለማየት ሥልጣን ይኖረዋል።

10.<u>የፌዴሪል መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን</u>

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ግምታቸው እስከ ብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ) የሚሆኑ ጉዳዮችን ወይም ግምታቸው በገንዘብ ሊተመን በማይችሉ ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል።

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ በታች አደረጃጀትና የዳኝነት ሥራ አካሄድ</u>

11.<u>የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ዳኞችና ሌሎች ሠራተኞች</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት አንድ ዋና ቃዲ እና አንድ ምክትል ዋና ቃዲ እንዲሁም ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ቃዲዎችና ሬጅስትራሮች ይኖሩታል።
2. የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖሩታል።

12.<u>የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤትና የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤትና የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ለየፍርድ ቤቶቹ ተጠሪ የሚሆኑ ሹሞችና ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ቃዲዎችና ሬጅስትራሮች ይኖሯቸዋል፡፡
2. ፍርድ ቤቶቹ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖሯቸዋል፡፡

13.<u>የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤት ችሎትና የማስቻያ ስፍራ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ችሎቶች በአንድ ቃዲ ያስችላሉ፡፡
2. በፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤትና በሸሪዓው ጠቅላይ ፍርድ ቤት ችሎቶች አንድ ሰብሳቢና ሁለት ቃዲዎች ተሰይመው ያስችላሉ፡፡
3. የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ማስቻያ ስፍራ አዲስ አበባ ይሆናል፡፡

4. የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችና የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የማስቻያ ስፍራ በአዲስ አበባ ከተማ፣ በድሬዳዋና በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 78 ንዑስ አንቀጽ (2) በሚወሰነው መሠረት ይሆናል፡፡

14 **<u>የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የሥራ ቋንቋ</u>**

1. የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የሥራ ቋንቋ አማርኛ ይሆናል፡፡
2. አማርኛ ቋንቋ ለማይችል ባለጉዳይ ፍርድ ቤቱ አስተርጓሚ ይመድብለታል፡፡

15.**<u>በግልጽ ችሎት ስለማስቻልና ከችሎት ስለመነሳት</u>**

1. የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ሁኔታ ያስችላሉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ቢኖርም ለዳኝነት አሠራር አግባብነት ያላቸው የፍትሕ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡
3. የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤት ቃዲ ከችሎት እንዲነሳ ከተከራካሪ ወገኖች አንዱ ለፍርድ ቤቱ ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል፡፡
4. ማመልከቻ የቀረበበት ቃዲ ከችሎት የሚነሳበትን ሁኔታ በተመለከተ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 ከአንቀጽ 27 እስከ 30 ያሉት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

16.**<u>ቃዲ ሆኖ ለመመረጥ የሚያበቁ ሁኔታዎች</u>**

የሚከተሉትን ሁኔታዎች የሚያሟላ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በፌዴራሉ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ቃዲ ሆኖ ሊሾም ይችላል፤

1. በእስልምና ትምህርት ተቋማት በሸሪዓ ሕግ የሠለጠነ ወይም በሸሪዓ ሕግ በቂ የሆነ ልምድ እና ዕውቀት ያካበተ፤
2. በታታሪነቱና በስነ-ምግባሩ መልካም ስም ያተረፈ፤
3. ቃዲ ሆኖ ለመሥራት ፈቃደኛ የሆነ፣ እና
4. ዕድሜው ከ25 ዓመት በላይ የሆነ፡፡

17.**<u>የቃዲዎች አሿሿም</u>**

1. እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ጉባዔ ከፌዴራሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ጥያቄ ሲቀርብለት የቃዲዎችን ምልመላ ያከናውናል፤
2. የእስልምና ጉባዔው ሰብሳቢ፣ በጉባዔው የተጠቆሙትንና በተለያዩ ደረጃ እንዲመደቡ የድምጽ ብልጫ ድጋፍ ያገኙትን የዕጩ ቃዲዎች አጭር የሕይወት ታሪክ መግለጫ አዘጋጅቶ ለፌዴራሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ያቀርባል፡፡

3. በየትኛውም ደረጃ የሚመደቡ ቃዲዎች ሹመት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አቅራቢነት በፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ይጸድቃል፡፡

**18.ስለዲሲፕሊን አወሳሰን**

የፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ አዋጅና የፌዴራሉ ዳኞች መተዳደሪያ ደንብ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ቃዲዎችን ለሚመለከቱ የዲሲፕሊን ጉዳዮች አወሳሰን ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

**19.በጀት**

የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የሚገኝ ይሆናል፤

ሀ/ ከፌዴራሉ መንግሥት በሚሰጥ የበጀት ድጐማ፤

ለ/ ከሌሎች ምንጮች ከሚገኝ ድጋፍ፡፡

## ክፍል አምስት

## ስለዋናው ቃዲ፤ ምክትል ዋና ቃዲ እና ተጠሪዎች

**20.የዋናው ቃዲ ሥልጣንና ተግባር**

1. ዋናው ቃዲ የፌዴራሉን ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በበላይነት ያስተዳድራል፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋናው ቃዲ፡-
   ሀ/ በየደረጃው የሚደራጁ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን መዋቅር አዘጋጅቶ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ያቀርባል፤ ሲፈቀድለትም በሥራ ላይ ያውላል።
   ለ/ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አማካኝነት የሚላኩለትን ቃዲዎች በፌዴራሉ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ውስጥ በመደልደል ያሠራል፤
   ሐ/ የፌዴራሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች እንዲቀጠሩለት ይጠይቃል፤ ሲፈቀድለትም ሠራተኞች ይቀጥራል፤ በየሥራው ደልድሎ ያሠራል።
3. የፌዴራሉ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ስላከናወኑዋቸው ሥራዎች በየስድስት ወሩ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ሪፖርት ያቀርባል፤
4. የፍርድ ቤቶቹን ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ያቀርባል፤ ሲፈቀድለትም ሥራ ላይ ያውላል፤
5. መሥሪያ ቤቱን በመወከል አስፈላጊ ቦታዎች ይገኛል፤ መግለጫዎችን ይሰጣል፤

6. በራሱ አነሳሽነት ወይም በችሎቶች አሳሳቢነት ወይም በባለጉዳዮች ጠያቂነት በፌዴራሉ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ችሎቶች መካከል መሠረታዊ የሆኑ የትርጉም ልዩነት ያለባቸው የሸሪዓውን ሕግ የሚመለከቱ ጉዳዮች ሲነሱ ጉዳዩን ከአምስት ያላነሱ ቃዲዎች ተሰይመው እንዲያዩት ለማድረግ ይችላል፡፡

21.<u>የምክትል ዋና ቃዲው ሥልጣንና ተግባር</u>

ምክትል ዋና ቃዲው፡-

1. በዋናው ቃዲ የሚመሩለትን ጉዳዮች ያከናውናል፤
2. ዋናው ቃዲ በማይኖርበት ጊዜ ዋናውን ቃዲ ተክቶ ይሠራል።

22.<u>የተጠሪዎች ሥልጣንና ተግባር</u>

የፌዴራል ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት ተጠሪዎች፤

1. ፍርድ ቤቶቻቸውን ይወክላሉ፤
2. ዋናው ቃዲ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የፍርድ ቤቱን ሥራ ይመራሉ፤ ሠራተኞች ያስተዳድራሉ፤
3. ስለተከናወኑ ሥራዎች ለዋናው ቃዲ በእስታትስቲክስ የተደገፈ መግለጫ እና እንደአስፈላጊነቱ በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባሉ፤ ስለሥራዎቻቸው እንደአስፈላጊነቱ ከዋናው ቃዲ ጋር በመመካከር ያከናውናሉ፡፡
4. ሌሎች በሕግ የሚሰጧቸውን ተግባራት ያከናውናል፡፡

<u>ክፍል ስድስት</u>

<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

23.<u>የፌዴራሉ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ውሳኔዎችና ትዕዛዞች</u>

1. በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በሥልጣን ክልላቸው በሚሸፈኑ ጉዳዮች ላይ የሚሰጣቸውን ውሳኔዎችና ትዕዛዞች አስፈጻሚ ክፍሎች እንዲፈጽሙ ለማዘዝ ይችላሉ፡፡
2. የሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ የደረሳቸው አስፈጻሚ አካላትም ሆኑ ግለሰቦች በትዕዛዙ መሠረት የመፈጸምም ሆነ የማስፈጸም ግዴታ አለባቸው።

24.<u>በፍርድ ቤት በመታየት ላይ ስላሉ ጉዳዮች</u>

ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮች በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ሥልጣን ወዳላቸው የፌዴራል ሸሪዓ ፍ/ቤቶች ተዛውረው ይታያል፡፡

## 25.<u>የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጐች</u>

1. የቃዲዎችንና የናኢባዎችን ጉባዔ ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 62/1936 በዚህ አዋጅ ተሽሯል።
2. ይህን አዋጅ የሚቃረን ወይም በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን የሚመለከት ማንኛውም ሕግ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## 26.<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከህዳር 27 ቀን 1992 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ኅዳር 27 ቀን 1992 ዓ.ም**

**ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌዴራል …………….. ሸሪዓ ፍርድ ቤት

ቀን………………………

ቁጥር……………………….

የፍትሐብሔር መዝገብ ቁጥር……………………….

<u>የማረጋገጫ ሠነድ፣</u>

የአመልካች ስም…………………………………………..

አድራሻ፡- ወረዳ…………..የቤት ቁጥር……..የስ/ቁ……………..ሥራ………………..

እኔ አመልካች በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ (5) እና በፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ማጠናከሪያ አዋጅ ቁጥር 188/1992 በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (1) በተገለጸው መሠረት በፍትሐብሔር መዝገብ ቁጥር በዚህ ፍርድ ቤት የተመሠረተውን ጉዳይ በሃይማኖቱ ሥርዓትና ደንብ መሠረት ለመዳኘትና ለመጨረስ የተስማማሁ/ያልተስማማሁ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የአመልካች ሥም…………………………………………….

ፊርማ……………………………

ከፍ ብሎ የተገለጸውን ቃል ፊቴ ቀርበው አረጋግጠዋል።

የሬጅስትራር ሥም…………………………..

ፊርማ……………………………

**ቀን.................................**

.....................................

**ማሕተም**

## **አዋጅ ቁጥር 322/1995**

## **የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትን በተወሰኑ ክልሎች ለማደራጀት የወጣ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 78(2) የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሆነ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሀገሪቱ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲደራጅ በሁለት ሦስተኛ ድምጽ ሊወስን እንደሚችል በመደንገጉ፤

በተወሰኑ ክልሎች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ማደራጀት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 78(2) እና አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማደራጃ አዋጅ ቁጥር 322/1995" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ስለማደራጀት**

   የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት 30 ቀን 1995 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ በአፋር ክልል፣ በቤንሻንጉል ክልል፣ በጋምቤላ ክልል፣ በሶማሌ ክልል እና በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች እንዲደራጁ ወስኗል፡፡

3. **በመታየት ላይ ስላለ ጉዳዮች**

1. ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 789(2) በተሰጣቸው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሥልጣን መሠረት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2 በተመለከቱት ክልሎች በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮች በተጀመሩበት ፍርድ ቤቶች ታይተው ይወሰናሉ።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮች በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲታይ ለማድረግ ይችላል፡፡

4. **<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ ከመጋቢት 30 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት 30 ቀን 1995 ዓ.ም**
**ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ**
**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## <u>አዋጅ ቁጥር 684/2002</u>

## <u>የተሻሻለው የፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ማቋቋሚያ አዋጅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ነጻ የዳኝነት አካል የተቋቋመ በመሆኑ፤

ይህ ነፃ የዳኝነት አካል ነፃነቱ የሚረጋገጠው ተቋማዊ እና ዳኝነታዊ ነፃነቱን መጠበቅ ሲቻል በመሆኑ፤ ይህንንም ለማድረግ ፍርድ ቤቶች ከማናቸውም አካል ተፅዕኖ ነፃ ሆነው ራሳቸውን ማስተዳደር መቻል ያለባቸው በመሆኑ፤

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ዳኞችን ተጠያቂነት ማስፈንና የጉባዔውን አባላት ስብጥር ማስፋት በማስፈለጉ፤

ለዚህም አስፈላጊውን መዋቅር ያሟላና ሥልጣኑ በህግ እውቅና የተሰጠው የዳኝነት አስተዳደር አካል ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

1. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "የተሻሻለው የፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 684/2002" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **<u>ትርጓሜ</u>**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "ጉባዔ" ማለት የፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ነው፣
2. "የፌዴራል ዳኛ" ማለት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ፕሬዚዳንቶችንና ምክትል ፕሬዚዳንቶችን ጨምሮ በፌዴራል ፍርድ ቤት ውስጥ በዳኝነት ተሹሞ የሚሰራ ሰው ነው፣
3. "የዲሲፕሊን ጥፋት" ማለት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ዳኞች የሥነ-ምግባር ደንብ ውስጥ የተዘረዘሩትን ማናቸውንም ድንጋጌዎች የሚጥስ ተግባር ነው፤
4. "ጉልህ የሆነ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና ማነስ" ማለት በፌዴራል ዳኞች የሥራ አፈጻጸም መመዘኛ ከተመለከተው የምዘና ውጤት በታች ማግኘት ነው፤
5. "ህገ-መንግሥት" ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት ነው፤
6. "ፕሬዚዳንት" ማለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ነው፤
7. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

3. **<u>የጾታ አገላለፅ</u>**

በዚህ አዋጅ በወንድ ጾታ የተገለፀው የሴትንም ያካትታል።

4. **<u>የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ መቋቋም</u>**

1. የፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ (ከዚህ በኋላ "ጉባዔው" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡
2. ጉባዔው የራሱ ጽሕፈት ቤት፣ ኃላፊ፣ በጀት እና አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖሩታል። የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ የጉባዔው ፀሐፊ ሆኖ ያገለግላል።
3. የጉባዔው ጽሕፈት ቤት ሕጋዊ ሰውነት አለው፡፡

5. **<u>የጉባዔው አባላት</u>**

1. ጉባዔው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

ሀ/ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት------------------- ሰብሳቢ

ለ/ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት -------አባል

ሐ/ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሦስት አባላት ---------------- "

መ/ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፍትህ ሚኒስቴር[18]----"

ሠ/ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት------------------ "

ረ/ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት------------"

ሰ/ በፌዴራል ዳኞች ጠቅላላ ስብሰባ የሚመረጥ አንድ ዳኛ---------- "

ሸ/ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የጥብቅና ፈቃድ ካላቸው ጠበቆች መካከል በጉባዔው የሚመረጥ አንድ ጠበቃ----------------------------------- "

ቀ/ እውቅና ባለው የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሕግ ከሚያስተምሩ መምህራን መካከል በጉባዔው የሚመረጥ አንድ የሕግ መምህር----------------------- "

በ/ በጉባዔው የሚመረጥ አንድ ታዋቂ ግለሰብ---------------------------- "

2. በጉባዔው አባላት ስብጥር የሴቶችን ተዋጽኦ ለማረጋገጥ ጥረት ይደረጋል፡፡
3. ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ሰብሳቢውን ተክቶ ይሰራል።

6. <u>የጉባዔው ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ጉባዔው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ በፕሬዚዳንቱ ጥያቄ ለፌዴራል ዳኝነት ቦታዎች ዕጩዎችን ለመለየት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የያዘ ማስታወቂያ እንዲወጣ ይወሰናል፣ ማስታወቂያው የትና እንዴት እንደሚሰራጭም ይወስናል፤

ለ/ በዳኝነት ሥራ ለመሰማራት ካመለከቱ ግለሰቦች መካከል በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 መሠረት ለዳኝነት ብቁ የሆኑትን እጩ ዳኞች ይለያል፤

ሐ/ ለፌዴራል ከፍተኛና መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት የሚሆኑ እጩዎችን በፕሬዚዳንቱ ከሚቀርብ ዝርዝር ውስጥ ያጫል፤

መ/ የጉባዔውን ጽሕፈት ቤት ኃላፊ፣ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሬጅስትራሮችን፣ ረዳት ዳኞችን እና ሌሎች የፍርድ ቤቱ የሥራ ኃላፊዎችን በፕሬዚዳንቱ አቅራቢነት ይሾማል፤ ደመወዛቸውን፣ አበላቸውን እና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞቻቸውን እንዲሁም ከሥራ የሚነሱበትን ሁኔታ ይወስናል፤

[18] የኢፌዴሪ ፍትህ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 943/2008 መሰረት በፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ በመተካቱ የፌዴራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ በሚል ይነበባል፡፡

ሠ/ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 81/4/ መሠረት ከክልል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔዎች በሚቀርቡለት የክልል ጠቅላይና ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ዕጩ ዳኞች ላይ አስተያየቱን ይሰጣል፤

ረ/ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ፕሬዚዳንቶችና ምክትል ፕሬዚዳንቶች እና የፌዴራል ዳኞች የሚመሩበትን የሥነ ምግባር ደንብ፣ የዲሲፕሊን ክስ ሥነ-ሥርዓት ደንብ እና የሥራ አፈጻጸም መመዘኛ መስፈርት ያወጣል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

ሰ/ ስለ ፌዴራል ዳኞች ምደባ፣ ዝውውር፣ ደመወዝ፣ አበል፣ ሕክምና እና የደረጃ ዕድገት ይወስናል፤

ሸ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 መሠረት የሚቀርቡ ጉዳዮችን ይወሰናል፣ ውሳኔው በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እስከሚፀድቅ ድረስ ዳኛውን ከሥራ ማገድ ይችላል፣ ዝርዝሩ በፌዴራል ዳኞች የዲሲፕሊን ክስ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ይወስናል፤

ቀ/ የጉባዔው ጽሕፈት ቤት የሚሰራበትን መመሪያ ያወጣል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

በ/ የፌዴራል ዳኞች የዲስፕሊን ክስን በተመለከተ ጉባዔው በመረጣቸው የጥፋት ዓይነቶች ላይ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ፕሬዚዳንቶች ውሳኔ እንዲሰጡ ስልጣን ሊሰጣቸው ይችላል፤ በዚህ ስልጣን መሠረት በፕሬዚዳንቶቹ በሚሰጥ ውሳኔ ላይ ለጉባዔው ይግባኝ ይቀርብበታል፣ ዝርዝሩ በዳኞች የዲስፕሊን ክስ ሥነ ሥርዓት ደንብ ይወሰናል፤

ተ/የፌዴራል ፍርድ ቤቶችንና የፌዴራል ዳኞችን የዳኝነት ስራ በየወቅቱ ይገመግማል።

2. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀጽ 1/መ/ በተደነገገው መሠረት በጉባዔው የሚሾሙትን ግለሰቦች በተመለከተ በዚህ አዋጅ ተለይተው ለጉባዔው ሥልጣን ከተሰጠባቸው ጉዳዮች ውጭ አግባብነት ያለው የሲቪል ሰርቪስ ሕግ ተፈጻሚ ይሆናል።

7. <u>የጉባዔው ስብሰባ</u>

1. ጉባዔው በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል።
2. ከጉባዔው አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።

3. የጉባዔው ውሳኔዎች በድምፅ ብልጫ ያልፋሉ፣ ሆኖም ድምፁ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሣኝ ድምጽ ይኖረዋል።
4. የዲሲፕሊን ክስ የቀረበበት ማንኛውም የጉባዔው አባል የሆነ ዳኛ ጉዳዩ በሚታይበት ጊዜ በጉባዔው ስብሰባ ላይ በአባልነት መቀመጥ አይችልም።
5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/፣ /2/፣ /3/ እና /4/ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ጉባዔው የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ማውጣት ይችላል።

8. <u>የጉባዔው ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባራት</u>

የጉባዔው ሰብሳቢ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የጉባዔውን ጽሕፈት ቤት በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤
2. የጉባዔውን ስብሰባ ይጠራል፤
3. የጉባዔውን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል፤
4. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6/1/ሀ/ መሠረት በወጣው ማስታወቂያ ተወዳድረው የተመረጡ ግለሰቦችን አጭር የህይወት ታሪክ መግለጫ አዘጋጅቶ ለጉባዔው ያቀርባል፣ በጉባዔው የተመረጡት እጩ ዳኞች በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲሾሙ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ያቀርባል፣
5. ክፍት ለሆኑ የፌዴራል ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች የፕሬዚዳንትነትና የምክትል ፕሬዚዳንትነት ቦታዎች የሚሆኑ እጩዎችን ለጉባዔው ያቀርባል፤ በጉባዔው የተመረጡትን እጩዎችም በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲሾሙ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ያቀርባል፤
6. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 (1) /ሐ/ እና /መ/ መሠረት የሚሾሙ ግለሰቦችን አጭር የህይወት ታሪክ መግለጫ አዘጋጅቶ ለጉባዔው ያቀርባል፤
7. ለጉባዔው የሚያስፈልገውን በጀት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፀድቅም በጀቱን ያስተዳድራል።

9. <u>የጉባዔው ጽሕፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር</u>

የጉባዔው ጽሕፈት ቤት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሥልጣንና ይኖሩታል፡-

1. የጉባዔውን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፤
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13 መሠረት በፌዴራል ዳኞች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ይቀበላል፣ በአቤቱታዎች ላይ ጉባዔው የሚሰጣቸውን ውሳኔዎች በአግባቡ ለሚመለከታቸው ሰዎችና አካላት እንዲደርስ ያደርጋል፤

3. የፌዴራል ዳኞችን የግል ማህደር ያደራጃል፣ አስፈላጊ መረጃዎች በማህደሮች መግባታቸውን ይከታተላል፤
4. የፌዴራል ዳኞችን አስተዳደራዊ ጉዳዮች አፈጻጸም ይከታተላል፤
5. የጉባዔውን የስብሰባ ቃለጉባዔዎችና ሌሎች ሰነዶች በአግባቡ ይይዛል፤
6. የፌዴራል ዳኞች የሥራ አፈጻጸም ምዘና ጉባዔው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት እንዲካሄድ ያደርጋል፣ የምዘና ውጤቶች በዳኞች የግል ማህደር እንዲገቡ ያደርጋል፤
7. ሌሎች በጉባዔው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።

10.**<u>የጉባዔው ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር</u>**

የጉባዔው ጽሕፈት ቤት ኃላፊ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በጉባዔው ስብሰባዎች ላይ በፀሐፊነት ይገኛል፣ ቃለጉባዔ ይይዛል፣ ቃለጉባዔዎች በጉባዔው አባላት መፈረማቸውን ይከታተላል፤
2. የጉባዔውን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት ለጉባዔው ሰብሳቢ ያቀርባል፤
3. ስለጉባዔው ዕቅድ አፈጻጸም በጉባዔው በተጠየቀ ጊዜ ሪፖርት ያቀርባል፤
4. በፌዴራል ዳኞች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ለጉባዔው ያቀርባል፣ የተሰጡ ውሳኔዎች መፈፀማቸውን ይከታተላል፤
5. የጽሕፈት ቤቱን ሠራተኞች ያስተዳድራል፤
6. ሌሎች በጉባዔው ሰብሳቢ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።

11.**<u>ለዳኝነት ለመሾም የሚያበቁ ሁኔታዎች</u>**

1. የሚከተሉትን ሁኔታዎች የሚያሟላ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ዳኛ ሆኖ ሊሾም ይችላል፦

ሀ/ በዳኝነት ሙያ ለመሰማራት ፈቃደኛ የሆነ፤

ለ/ ዕድሜው ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሀያ አምስት ዓመት ያላነሰ፤ ለፌዴራል ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከሰላሳ አምስት ዓመት ያላነሰ፤

ሐ/እውቅና ካለው የከፍተኛ ትምህርት ተቋም በሕግ ትምህርት ቢያንስ በመጀመሪያ ዲግሪ በከፍተኛ ውጤት የተመረቀ ሆኖ ዝርዝር አፈፃፀሙ ጉባዔው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፤

መ/ ለሕገ መንግሥቱ ታማኝ የሆነ፤ ለሕገ መንግሥቱ ታማኝ ስለመሆኑና ሕገ መንግሥቱን በሚቃረን ተግባር ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተሳትፎ እንደማያውቅ በጽሁፍ ማረጋገጫ የሚሰጥ፤

ሠ/ ጉባዔው በሚያደርግለት ቃለ መጠየቅ፣ የማጣሪያ ፈተናና ሌሎች የባህርይ ምርመራዎች በእውቀቱ፣ በታታሪነቱ፣ በሥነ-ምግባሩ፣ በፍትሃዊነቱና በሕግ አክባሪነቱ መልካም ስም ያለው ሆኖ የሚገኝ፤

ረ/ በጉባዔው ለሚወሰን ጊዜ፣ ቀድሞ ስልጠና ያልወሰደ በጉባዔው በተመረጠ የሥልጠና ቦታ የሚሰጠውን የቅድመ ዕጩነት ስልጠና በአግባቡ የሚያጠናቅቅና በሚሰጠው የማጠቃለያ ፈተናም ከአማካይ በላይ ነጥብ የሚያገኝ፤

ሰ/ በፅኑ እስራት ተቀጥቶ የማያውቅ ስለመሆኑ ማረጋገጫ የሚሰጥ።

2. ማንኛውም ሰው በመንግሥት ሕግ አውጭ ወይም አስፈጻሚ ውስጥ ወይም በማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት በአባልነት በሚያገለግልበት ጊዜ አጣምሮ የዳኝነት ሥራ ሊሰራ አይችልም፡፡

## 12.<u>የዳኞች ከሥራ መሰናበት</u>

1. ማንኛውም የፌዴራል ዳኛ ከሥራ የሚሰናበተው በሚከተሉት ምክንያቶች ይሆናል፦

ሀ/ ሥራውን ለመልቀቅ ሲፈልግ የሁለት ወር የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፤

ለ/ ዕድሜው ስድሳ (60) ዓመት ሲሞላው፤

ሐ/ በሕመም ምክንያት ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን አይችልም ተብሎ ሲወሰን፤

መ/ በፌዴራል ዳኞች ስነ ምግባር ደንብ መሠረት ከሥራ የሚያሰናብት የዲሲፕሊን ጥፋት ፈጽሞ ሲገኝ፤

ሠ/ ጉልህ የሆነ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና አንሶታል ተብሎ ሲወሰን።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጉባዔው ስራውን ለመልቀቅ ማስታወቂያ የሰጠ የፌዴራል ዳኛ ሥራውን የሚለቅበትን የመጨረሻ ቀን የማስታወቂያው ጊዜ ካበቃበት ቀን ጀምሮ ከሦስት ወራት ለማይበልጥ ተጨማሪ ጊዜ ሊያራዝመው ይችላል፡፡

3. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀጽ /2/ በተደነገገው መሠረት ጉባዔው ጊዜውን ለማራዘም ከወሰነ ይህንኑ ውሳኔውን ዳኛው የሰጠው የማስጠንቀቂያ ጊዜ ከማለቁ በፊት ለዳኛው በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት። ዳኛው የሰጠው የማስጠንቀቂያ ጊዜ ካለፈ በኋላ በጉባዔው የሚሰጥ የጊዜ ማራዘሚያ ውሳኔ በዳኛው ላይ አስገዳጅነት አይኖረውም።

4. በዲሲፕሊን ጥፋት ምክንያት ከሥራው የተሰናበተ የፌዴራል ዳኛ ከሥራ ከመሰናበት ጋር በተያያዘ ለፌዴራል ዳኞች በሕግ የተፈቀዱ ጥቅማ ጥቅሞችን አያገኝም።
5. ስለጠበቆች ፈቃድ አሰጣጥ የሚደነግጉ ሌሎች ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው ከስራው የተሰናበተ የፌዴራል ዳኛ ስራውን ካቆመበት የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ለሁለት ዓመታት አስቀድሞ ይሰራበት በነበረው የፌዴራል ፍርድ ቤት በሚገኝ ማናቸውም ችሎት ፊት በጠበቃነት ተከራካሪዎችን ወክሎ መቅረብ አይችልም።

13.<u>አቤቱታ ስለማቅረብ</u>

1. ማንኛውም ሰው የዲሲፕሊን ጥፋት ፈጽሟል በሚለው የፌዴራል ዳኛ ላይ ለጉባዔው አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ጉባዔው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አቤቱታ የቀረበባቸውን ጉዳዮች ለማጣራት ኮሚቴ ሊያቋቁም ይችላል። ኮሚቴው የሚዋቀርበት ሁኔታና የሚከተለው ሥርዓት ጉባዔው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

14.<u>ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

ጉባዔው ይህን አዋጅ ለማስፈፀም ደንብ ወይም መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

15.<u>ቃለ መሐላ</u>

ዳኞች ሥራቸውን ከመጀመራቸው በፊት የሚከተለውን ቃለ መሐላ ይፈጽማሉ፡-

“እኔ ................................ በዛሬው ዕለት ............. ፍርድ ቤት ዳኛ በመሆን ተሹሜ ስራዬን ስጀምር የተጣለብኝን ከፍተኛ ኃላፊነት በታማኝነት ለመፈፀም ቃል እገባለሁ።”

16.<u>የተሻሩ ሕጎች</u>

የፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 24/1988 በዚህ አዋጅ ተሽሯል።

17.<u>መብትና ግዴታ ስለማስተላለፍ</u>

በአዋጅ ቁጥር 24/1988 የተቋቋመው የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ መብትና ግዴታ በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ጉባዔ ተላልፏል።

18.<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ከሰኔ 22 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሐምሌ 17 ቀን 2002 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ**

**ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝደንት**

**ለ/ ልዩ የስነስርዓት ህጎች እና የወንጀል ምስክሮች**

**አዋጅ ቁጥር 434/1997**

**የተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ህግ አዋጅ**

የሙስና ወንጀል ትርጉምን፣ የክስ ሂደትና የማስረጃ ድንጋጌዎችን ከወንጀል ህጉ ጋር በተጣጣመ መልኩ ማሻሻልና መደንገግ በማስፈለጉ፣

በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው የተያዙ ወይም የተከሰሱ ሰዎች በዋስትና ስለሚለቀቁበት ሁኔታ ዝርዝር ድንጋጌ መደንገግ በማስፈለጉ፣

በሙስና ወንጀል የተጠረጠሩ ሰዎችን ንብረት ስለማገድ፣ ስለማስተዳደርና ስለመውረስ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ማሻሻል በማስፈለጉ፣

የጸረ ሙስና ልዩ ስነስርዓትና የማስረጃ ድንጋጌዎችን ከሌሎች ህጎች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ማስተካከልና ማሻሻል በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 55(1) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**ክፍል አንድ**

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ አዋጅ ቁጥር 434/1997" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**[19]

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

1. "የሙስና ወንጀል" ማለት የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 881/2007 የተሰጠው ትርጓሜ ይኖረዋል፡፡
2. "በሙስና ወንጀል የተገኘ ንብረት" ማለት በተከሳሽ ባለቤትነት ወይም ይዞታ ስር የሚገኝ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በሙስና በወንጀል የተገኘ ንብረት ወይም ገንዘብ ሲሆን ወንጀሉ ከተፈጸመ በኋላ በቀጥታም ሆነ በእጅ አዙር ከተከሳሹ በስጦታ የተሰጠ በአደራ የተቀመጠ እና የተሸሸገ፣ ማናቸውም በወንጀል የተገኘ ንብረትን ወይም ገንዘብን ይጨምራል።
3. "አግባብ ያለው አካልን" ማለት የሙስና ወንጀልን ለመመርመር እና/ወይም ለመክሰስ ሥልጣን የተሰጠው አካል ነው።
4. "የእግድ ትእዛዝ" ማለት ተከሳሽ በንብረቱ ላይ ያለውን መብት እንዳይጠቀምበት የሚከለክል ትእዛዝ ሲሆን በማናቸውም መንገድ ለሌላ ሰው ማስተላለፍን የመጠቀም መብት መስጠትንና ማስወገድን ይጨምራል።
5. "ኮሚሽነር" ማለት የስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ነው፡፡
6. "ጠቋሚ" ማለት ተፈፅሟል ወይም ሲፈፀም ነው ብሎ ያመነውን የሙስና ወንጀል የሚመለከት መረጃ አግባብ ላለው አካል ወይም ለሌላ የፍትህ አካል፣ ለመንግስት መሥሪያ ቤት፣ ለመንግስት የልማት ድርጅት ወይም ለህዝባዊ ድርጅት የበላይ ኃላፊ ወይም ወይም በመመሪያ የሙስና ወንጀል ጥቆማን እንዲቀበል ኃላፊነት ለተስጠው ሌላ አካል የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው ሲሆን፣ ለእነዚህ ለተጠቀሱት አካላት ጥቆማ ባያቀርብም የሙስና ወንጀል የተፈፀመበትን ጉዳይ ኦዲት

[19] የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) በማሻሻያ አዋጁ 21/37(2007) አ.882 አንቀፅ 2(1) እና (3) መሰረት የቀድሞው ተሰርዞ የተተካ ሲሆን በተጨማሪም አዲስ ንዑስ አንቀፅ (5)፣(6)፣(7) እና (8) ተጨምረው ነባሩ ንዑስ አንቀፅ (5) ንዑስ አንቀፅ (9) ሆኖ ተሸጋሽጓል።

የሚያደርግ ወይም በአዲት ተግባሩ ሙስና መፈፀሙን ያጋለጠ ኦዲተርን እና ጥቆማን የሚያጣራ ወይም የሚመረምር ሰውን ያካትታል፡፡

7. "የበላይ ኃላፊ" ማለት አንድን የመንግስት መሥሪያ ቤት፣ የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም የህዝባዊ ድርጅት በኃላፊነት የሚመራ ሰውን ወይም ምክትሎቹን ወይም ሚኒስትር ዴኤታዎችን ይመለከታል፡፡
8. "ህዝባዊ ድርጅት" ማለት የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 881/2007 የተሰጠውን ትርጓሜ ይኖረል፡፡
9. "ሰው" ማለት ማናቸውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

3. <u>**የአዋጁ ተፈጻሚነት ወሰን**</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራልና በክልል ሥልጣን ስር በሚወድቁ የሙስና ወንጀሎች የምርመራና የክስ ሂደት ተፈጻሚ ይሆናል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለ ዋስትና የፍርድ ቤት ስልጣን</u>

4. <u>**በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው ስለተያዙ ሰዎች በዋስትና የመፈታት መብት**</u>

1. በሙስና ወንጀል የተያዘ ሰው በዋስ እንዲለቀቅ ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል፡፡ ሆኖም የተከሰሰበት ወይም የተጠረጠረበት ወንጀል ከአሥር ዓመት በላይ በሆነ ፅኑ እሥራት ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ በዋስትና መለቀቅ አይችልም። ከአራት ዓመት በላይ እና ከአስር ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲኖሩም እየተደመሩ ከአስር አመት በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ ዋስትና ይከለከላል።[20]
2. በሙስና ወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘ ሰውን መርማሪው ከዚህ በታች በተመለከቱት ሁኔታዎች የዋስትና ወረቀት በማስፈረም ወይም መያዣ በማስያዝ ሊለቀው ይችላል፡-

   ሀ/ ተፈጸመ የተባለው ወንጀል ለመፈጸሙ የሚያጠራጥር ከሆነ፣ ወይም

   ለ/ የተያዘው ሰው ወንጀሉን ለመፈጸሙ የሚያጠራጥር ከሆነ፣ ወይም

   ሐ/ ተፈጸመ የተባለው ወንጀል በጽኑ እስራት የማያስቀጣ ከሆነ

[20] ይህ ንዑስ አንቀፅ በማሻሻያ አዋጁ 21/37(2007) አ.882 አንቀፅ 2(2) መሰረት የቀድሞው ተሰርዞ ተተክቷል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት በዋስትና ወረቀት ያልተለቀቀ ተከሳሽ በዋስትና ወረቀት እንዲለቀቅ ፍርድ ቤትን ለመጠየቅ ይችላል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በተከሳሹ ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት በተጠርጣሪው የሚቀርበውን በዋስትና ወረቀት የመለቀቅ ጥያቄን ፍርድ ቤቱ ከዚህ በታች በተመለከቱት ሁኔታዎች መፍቀድ አይችልም።

   ሀ/ ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ በዋስትና ቢለቀቅ ይጠፋል ተብሎ የሚገመት ሲሆን ወይም፣

   ለ/ ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ በዋስትና ቢለቀቅ ማስረጃዎችን ያጠፋል ወይም ሌላ ወንጀል ይፈጽማል ተብሎ ሲገመት፣

5. <u>*የዋስትና መብትን በማክበር ወይም በመከልከል በሚሰጥ ወሳኔ ላይ ስለሚቀርብ ይግባኝ*</u>

   1. በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 4 በተመለከተው መሰረት ፍርድ ቤት ዋስትናን በሚመለከት በሚሰጠው ትእዛዝ ላይ ይግባኝ ማቅረብ ይቻላል፡፡
   2. ይግባኙ የቀረበው በዋስትና መለቀቁን ወይም የዋስትና ገንዘብ መጠኑን በመቃወም ከሆነ ጉዳዩ በይግባኝ ታይቶ እስኪወሰን ድረስ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔው ሳይፈጸም ይቆያል፡፡
   3. ፍርድ ቤቱ በሙስና ወንጀል የተጠረጠረው ወይም የተከሰሰው ሰው በዋስትና እንዲለቀቅ የወሰነ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ መጠየቁ የሚያስረዳ የጽሑፍ ማስረጃ ከይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ለማምጣት አግባብ ነው ብሎ በሚወስነው ጊዜ ውስጥ መርማሪው ወይም አቃቤ ህጉ ማስረጃውን ካላመጣ በቀር አስፈላጊው ስነስርዓት ተሟልቶ ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ እንዲለቀቅ በውሳኔው ላይ መግለጽ አለበት፡፡

6. <u>*የመንቀሳቀስ መብትን ስለመገደብ*</u>

   ፍርድ ቤቱ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 4 ወይም 5 በተመለከተው መሰረት የዋስትና መብቱ በተከበረለት ሰው ላይ ከዚህ በታች ከተመለከቱት አንዱን ወይም ከአንድ በላይ ትእዛዞች ሊሰጥ ይችላል፡፡

   ሀ/ ከተወሰነ ክልል ውጭ እንዲይንቀሳቀስ፣

   ለ/ ማስረጃ ሊያጠፋ በሚችልባቸው የተወሰኑ ቦታዎች እንዳይደርስ፣

   ሐ/ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ አግባብ ላለው የምርመራ አካል ሪፖርት እንዲያደርግ፣

መ/ ወደውጭ አገር እንዳይወጣ

7. **የሙስና ወንጀሎችን የማየት ስልጣን ስላለው ፍርድ ቤት**

1. አግባብ ባለው ህግ መሠረት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን እንዲታዩ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ሌሎች በፌዴራል መንግሥት ሥር የሚወድቁ የሙስና ወንጀሎችን በሚመለከት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን አለው፣
2. አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን እንዲታዩ የተደነገጉት ክሶች እንደተጠበቁ ሆነው ሌሎች በክልል መንግሥት ሥር የሚወድቁ የሙስና ወንጀሎችን በሚመለከት የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን አለው፣
3. ከአዲስ አበባ እና ከድሬዳዋ አስተዳደሮች ጋር በተያያዘ የሚፈጸሙ የሙስና ወንጀሎችን በመጀመሪያ ደረጃ የማየት ሥልጣን እንደ ሁኔታው አግባብ ባለው የፌዴራል ፍርድ ቤት የሚካሄድ ይሆናል፣
4. ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ የሚነሱ የመያዝ፣ የብርበራ፣ የቀነ ቀጠሮ፣ በማረፊያ ቤት የማቆየት፣ የዋስትና፣ የእግድ እንዲሁም ከምርመራ ጋር የተያያዙ ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች የሚታዩት የሙስና ወንጀሉን ክስ ለማየት ሥልጣን በተሰጠው ፍርድ ቤት ይሆናል፡፡
5. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (4) የተደነገገው ቢኖርም፡-[21]

   ሀ/ እነዚህ የሥነ-ሥርዓት ገዳዮች የሙስና ወንጀሎችን የማየት ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት እንዲታዩ መደረጉ የተከሳሽን መብት የሚያጣብብ ወይም ማስረጃ እንዲጠፋ ምክንያት የሚሆን ወይም ተገቢ ላልሆነ ወጪ የሚዳርግ መሆኑን አግባብ ያለው አካል ካመነበት እንደ ሁኔታው በአቅራቢያው በሚገኝ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲታይ ሊወስን ይችላል፤

   ለ/ በዚህ ንዑስ አንቀፅ በፊደል ተራ (ሀ) በተመለከተው አግባብ ጉዳዩ በቀረበለት ፍርድ ቤት በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን አግባብነት ወደ አለው ፍርድ ቤት ይግባኝ መጠየቅ ይችላል። ይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

---

[21] ይህ አንቀፅ በማሻሻያ አዋጁ 21/37(2007) አ.882 አንቀፅ 2(2) መሰረት የቀድሞው አዲስ የተጨመረ ነው።

## ክፍል ሶስት

## ስለ እግድ

### 8. መርህ[22]

1. የአዋጁ አንቀፅ 10 እንደተጠበቀ ሆኖ ፍርድ ቤት በወንጀል የተገኘ ማንኛውም ንብረት እና በወንጀል የተገኘው ንብረት ያፈራውን ንብረት ለማገድ ይችላል፡፡
2. መርማሪ ወይም ዐቃቤ ህገ በወንጀል የተገኘ ማንኛውም ንብረት እና በወንጀል የተገኘው ንብረት ያፈራው ንብረት እንዲታገድ በቃለ መሀላ በተደገፈ መረጃ ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል፡፡
3. ለእግድ የሚቀርብ ማመልከቻ የወንጀል ክስ ከተመሰረተ በኋላ ወይም የወንጀል ክሱ ከመመስረቱ በፊት ሊቀርብ ይችላል፡፡
4. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1)፣ (2) እና (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ያለው አካል የበላይ ኃላፊ በፍርድ ቤት የእግድ ትዕዛዝ እስኪወጣ ድረስ ንብረቱ እንደሚባክን ሲያምንበት ለ48 ስዓት የሚፀና ጊዜያዊ የእግድ ትዕዛዝ መስጠት ይችላል።

### 9. ሌሎች ንብረቶች ስለሚታገዱበት ሁኔታ[23]

1. በሙስና ወንጀል የተገኘ ለመሆኑ መረጃ ባይቀርብም ምርመራ በተጀመረበት ወይም ክስ በቀረበበት የሙኳስና ወንጀል ተከሳሽ ያገኘው የማይገባ ጥቅም ወይም ያደረሰው ጉዳት ለመኖሩ በቃለ መሀላ ሲረጋገጥ በወንጀሉ ተገኘ ከተባለው የማይገባ ጥቅም ወይም ደረስ ተብሎ ከሚገመተው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ በተከሳሽ፣ በትዳር ጓደኛው ወይም ከ 18 ዓመት በታች በሆነ ልጁ ስም በባንክ የተቀመጠ ገንዘብ ወይም ንብረት ወይም በእነዚሁ ሰዎች ስም ያለ ንብረት እንዳይሸጥ፣ እንዳይለወጥ ወይም እንዳይተላለፍ ታግዶ እንዲቆይ በመርማሪ ወይም በዐቃቤ ህግ አቤቱታ ሲቀርብ ፍርድ ቤት የእግድ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

---

[22] ይህ አንቀፅ በማሻሻያ አዋጁ 21/37(2007) አ.882 አንቀፅ 2(5) መሰረት የቀድሞው ተሰርዞ ተተክቷል፡፡

[23] ይህ አንቀፅ በማሻሻያ አዋጁ 21/37(2007) አ.882 አንቀፅ 2(5) መሰረት የቀድሞው ተሰርዞ ተተክቷል፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት የሚሰጥ የአንድ ትእዛዝ ተጠርጣሪው በታገደው ንብረቱ የመጠቀም መብቱን አይነካም።
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) የተደነገገው ቢኖርም ተጠርጣሪው በባንክ በተቀመጠው ገንዘብ ወይም ንብረት የመጠቀም መብት አይኖረውም። ሆኖም ሁኔታዎች ሲያስገድዱ ፍርድ ቤቱ እንዲታገድ ከተደረገው ከዚሁ ገንዘብ ወይም ንብረት ውስጥ ተጠርጣሪው ሊጠቀምበት የሚገባ መጠን ወስኖ እንዲጠቀም ሊፈቅድለት ይችላል።
4. ተጠርጣሪው በተፈቀደለት የመጠቀም መብት ሲጠቀም በንብረቱ ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል ተብሎ ሲገመት መርማሪው ወይም ዐቃቤ ሕጉ ንብረቱን ከጉዳት ለመከላከል የሚጠቅም ትእዛዝ እንዲሰጥለት ፍርድ ቤቱን ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱ በቀረበው ጥያቄ ላይ ተገቢ የሆነውን ውሳኔ ይሰጣል፡፡

10.<u>ስለማይታገዱ ንብረቶች</u>

ለተከሳሹ የእለት ኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ንብረቶች በአንቀጽ 8 በተመለከተው መሰረት የእግድ ትእዛዝ አያርፍባቸውም፣ የእግድ ትእዛዝ ከማያርፍባቸው ውስጥ በተለይ የሚከተሉት ይገኙበታል፣

1. ለተከሳሹና ለቤተሰቡ የዕለት አገልግሎት የሚጠቅሙ ልብሶች፣ የምግብ ማብሰያ የሆኑ የቤት ቁሳቁስ፣ የመኝታ አልጋ፣ የአልጋ ልብሶችና የብርድ ልብሶች፣
2. ለራሱና ለቤተሰቡ ለዕለት ኑሮ ጠቃሚ የሚሆን ከሶስት ወር ያልበለጠ ስንቅ፣
3. የተከሳሹንና የቤተሰቡን የእለት ኑሮ ለማሟላት የሚያገለግሉ ቀላል መሳሪያዎች፣
4. ተከሳሹና ቤተሰቡ የሚተዳደሩበት ሌላ ንብረት የሌላቸው ሲሆንና የሚተዳደሩት ከታገደው ንብረት ከሚገኝ ገቢ ከሆነ መሰረታዊ ፍላጎትን ለማሟላት ለተከሳሹና ለቤተሰቡ ፍርድ ቤቱ በቂ ነው ብሎ የሚገምተውን ያህል ገቢ፣

11.<u>የማመልከቻው ይዘት</u>

1. የእግድ ትእዛዝ እንዲሰጥ የሚቀርብ በቃለ መሀላ የተደገፈ ማመልከቻ፣
   ሀ/ የወንጀሉን ፍሬ ነገርና በየደረጃው የተወሰዱትን እርምጃዎች፤ ክስ ያልተመሰረተ ከሆነ ጉዳዩ የሚገኝበትን ደረጃ የሚያሳይ መረጃ
   ለ/ የሚታገደው ንብረት ወይም ገንዘብ በሙስና ወንጀል የተገኘ ንብረት መሆኑን የሚያሳዩ ወይም ተፈጽሞአል በተባለውና ምርመራ በተጀመረበት የሙስና ወንጀል አማካይነት ተጠርጣሪው ያገኘው የማይገባ ጥቅም ወይም የደረሰ ጉዳትን በሚመለከት አሳማኝ ምክንያቶች፣

ሐ/ የንብረቶቹን ዝርዝርና አድራሻ፣

የያዘ መሆን ይኖርበታል።

2. የአገዳው ማመልከቻ እና የእግድ ትእዛዙን በመደገፍ የሚቀርቡ ጉዳዮች በተሟላና ግልጽ በሆነ ሁኔታ በቃለ መሀላው ውስጥ በዝርዝር መገለጽ ይኖርባቸዋል።

3. የእግድ ትእዛዝ ከተሰጠ በኋላ በተጨማሪ የእግድ ትእዛዝ እንዲሰጥ የሚያስገድድ ሁኔታ የተፈጠረ እንደሆነ መርማሪው ወይም ዐቃቤ ህጉ ለፍርድ ቤት ተጨማሪ የእግድ ትእዛዝ እንዲሰጥ ማመልከት ይችላል።

12.<u>የእግድ ትእዛዝ ስለመስጠት</u>

1. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 እንደተጠበቀ ሆኖ ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን ማመልከቻና ሰነዶች ከመረመረ በኋላ የእግዱን አስፈላጊነት ካመነበት የእግድ ትእዛዝ መስጠት ይችላል።

2. ተከሳሹ በሌለበት የእግድ ትእዛዝ ከተሰጠ መርማሪው ወይም ዐቃቤ ህጉ ትእዛዙንና የቃለ መሀላውን ግልባጮች ለተከሳሹና በትእዛዙ ስሙ ለተጠቀሰው ሌላ ሰው ያደርሳል፣ የእግድ ትእዛዙን ለሚመለከተው ለማናቸውም ሰው ያስታውቃል።

3. ፍርድ ቤቱ የተለየ ትእዛዝ ካልሰጠ በቀር ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠ የእግድ ትእዛዝ የጸና ይሆናል፡፡

13.<u>ንብረት ጠባቂ ስለመሾም</u>

ፍርድ ቤት የእግድ ትእዛዝ የሰጠበትን ንብረት አጠባበቅ በተመለከተ በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ 17 እስከ 21 የተመለከቱት ተፈጻሚ ይሆናሉ።

14.<u>አግባብ ያለው አካል ኃላፊነት</u>

1. አግባብ ያለው አካል፡-

ሀ/ ንብረት ጠባቂው ንብረቱን በአግባቡ ማስተዳደሩን ይከታተላል፡፡

ለ/ ንብረት ጠባቂው ንብረቱን በአግባቡ አላስተዳደረም ብሎ ካመነ ምክንያቱን በመግለጽ መግለጫ ለፍርድ ቤት ያቀርባል።

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት አግባብ ያለው አካል ያቀረበውን መግለጫ ተመልክቶ ፍርድ ቤቱ ተገቢ የመሰለውን ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

15.<u>የእግድ ትዕዛዝ ስለሚቋረጥበት ሁኔታ</u>

1. ፍርድ ቤቱ የውርስ ውሳኔ የሰጠ ከሆነ የእግድ ትእዛዙ ይቋረጣል።

2. ተከሳሹ በነጻ የተለቀቀ እንደሆነ የእግድ ትእዛዙ እንዲነሳለት ለፍርድ ቤቱ አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል።
3. በዚህ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ 2 በተመለከተው መሰረት ለቀረበው አቤቱታ ፍርድ ቤቱ አቃቤ ህግ አስተያየቱን እንዲሰጥ ይጠይቃል፡፡ አስተያየቱን ካዳመጠ በኋላ በቀረበው አቤቱታ መሰረት እግዱ እንዲነሳ ወይም እግዱ ሳይነሳ እንዲቆይ ሊወስን ይችላል።

16.<u>የእግድ ትእዛዝ ስለማንሳት ወይም ስለማሻሻል</u>

1. የእግድ ትእዛዝ የደረሰው ወይም ትእዛዙን እንዲያውቅ የተደረገ ማናቸውም ሰው የእግዱ ትእዛዝ እንዲነሳለት ወይም እንዲሻሻል ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የቀረበውን ማመልከቻና ማስረጃ ፍርድ ቤቱ ከተቀበለው ለመርማሪው ወይም ለአቃቤ ህጉ እንዲደርሰው በማድረግ ምላሽ እንዲሰጥበት ያደርጋል፡፡
3. የእግድ ትእዛዝ እንዲነሳ ወይም እንዲሻሻል የቀረበው አቤቱታ በበቂ ምክንያት ላይ የተመሰረተ ሆኖ ያገኘው እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ሰጥቶ የነበረውን የእግድ ትእዛዝ እንዲሻሻል ወይም እንዲነሳ ሊያደርግ ይችላል።
4. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 3 በተመለከተው መሰረት ለመወሰን ተጣርቶ እንዲቀርብለት ፍርድ ቤቱ ባለሙያ ሊመድብ ይችላል።

<u>**ንዑስ ክፍል ሶስት**</u>

<u>**ንብረት ጠባቂ ስለመሾም**</u>

17.<u>የንብረት ጠባቂ ስለሚሾምበት ሁኔታ</u>

1. ፍርድ ቤቱ የሚመችና ትክክለኛ መሆኑን የገመተ እንደሆነ የእግድ ትእዛዝ የተሰጠበትን ንብረት በተመለከተ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱትን ትእዛዞች ለመስጠት ይችላል፣

ሀ/ ንብረቱን ተቀብሎ የሚጠብቅ ሰው መርጦ መሾም፣

ለ/ ንብረቱን በይዞታ ወይም በአደራ አስቀማጭነት ወይም በጠባቂነት ለሌላ ሰው ሆኖ የያዘን ሰው ንብረቱን እንዲለቅ፣

ሐ/ የተለቀቀውን ንብረት ጠባቂው ተረክቦ በይዞታው ስር እንዲያደርግ እንዲጠብቅና እንዲያስተዳድር ለማዘዝ፣

መ/ ተቀባዩ የተረከበውን ንብረት ለመጠበቅ ለማስተዳደርና ለማሻሻል የሚያስችለው ሥልጣን ለመስጠት።

2. ፍርድ ቤቱ ንብረት ጠባቂው ስለተቀበለው ንብረት የመክሰስ ወይም የመከሰስ መብት እንዲኖረው እንዲሁም ከንብረቱ የሚገኝ ኪራይ ትርፍ ወይም ሌላ ማንኛውም ገቢ ለመሰብሰብና የሰበሰበውንም ገንዘብ ጠቃሚ ለሚሆን ጉዳይ ለማዋል እንዲችል ወይም ፍርድ ቤቱ ተገቢ መስሎ የታየውን ሌላ ስልጣን ሊሰጠው ይችላል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ትእዛዝ ንብረት ጠባቂውን ለመሾም የሚያስፈልገውን ወጪ ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል። አስፈላጊ ሆኖ ካገኘውም ሹመቱን ከመስጠቱ በፊት አስፈላጊው ማጣራት እንዲደረግ ማዘዝ ይችላል።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) መሰረት በንብረት ጠባቂነት የሚሾመው የተፈጥሮ ሰው የሆነ እንደሆነ ይህ ሰው መልካም ሥነ ምግባርና ችሎታ ያለው እንዲሁም ከተከሳሽ ጋር ዝምድና ወይም የጥቅም ግንኙነት የሌለው መሆን ይኖርበታል።
5. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1(ሀ) መሰረት በንብረት ጠባቂነት የሚሾመው የህግ ሰውነት ያለው ከሆነ ያለፉት ሶስት አመታት የሂሳብ አያያዙ ንጹህ መሆኑንና የጥቅም ግጭት አለመኖሩ መረጋገጥ ይኖርበታል።
6. በዚህ አንቀጽ መሰረት ንብረት ጠባቂ የሚሆኑትን ለማሾም በመርማሪው ወይም በአቃቤ ህጉ ወይም በተጠርጣሪው ሊቀርብ ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱም እንደሁኔታው የሌላኛውን ተከራካሪ ወገን አስተያየት በመጠየቅ ይወስናል፡፡

18.<u>ስለንብረት ጠባቂው አበል ክፍያ</u>

ለንብረት ጠባቂው ከተከበረው ንብረት ላይ የሚከፈለውን አበል በሚመለከት ፍርድ ቤቱ በሚሰጠው ጠቅላላ ወይም ልዩ ትእዛዝ ይወሰናል፡፡

19.<u>ንብረት ስለማረካከብ</u>

በዚህ አዋጅ መሰረት የተከበረ ንብረትን ለንብረት ጠባቂው ለማረካከብ የሚወጣው ወጪ ከተከበረው ንብረት ላይ በንብረት ጠባቂው አማካይነት ስለሚከፈልበት ሁኔታ በፍርድ ቤት ይወሰናል፡፡

20.<u>ስለንብረት ጠባቂው ግዴታዎች</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 መሰረት የሚሾም ንብረት ጠባቂ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ግዴታዎች ይኖሩታል።

1. እንዲያስተዳድር የተሾመበትን ንብረት በተመለከተ ኃላፊ ለመሆን የሚችል ዋስ ወይም መያዣ የመስጠት፣
2. ፍርድ ቤቱ በሚወስነው ጊዜና የአቀራረብ ፎርም መሰረት የሂሳብ መግለጫ እየሰራ የማቅረብ፣
3. ፍርድ ቤቱ በሚወስነው መሰረት የሚፈለግበትን ገንዘብ የመክፈል እና
4. በራሱ ከባድ ቸልተኝነት ወይም ሆን ብሎ ባደረገው ጉድለት በተረከበው ንብረት ላይ ላደረሰው ጉዳት ሀላፊ ሆኖ የመክፈል፡፡

21.<u>የንብረት ጠባቂውን ግዴታ ስለማስከበር</u>

1. ንብረት ጠባቂው በራሱ ከባድ ቸልተኝነት ወይም ሆን ብሎ በንብረቱ ላይ ጉዳት ወይም ጉድለት ያደረሰ እንደሆነ የሚፈለግበትን ገንዘብ እንዲከፍል ፍርድ ቤቱ ሊያዘው ይችላል፡፡
2. ገንዘብ እንዲከፍል ፍርድ ቤቱ ካዘዘው በኋላ ሳይፈጽም የቀረ እንደሆነ ጠባቂው ንብረቱ ተሸጦ ከሽያጩ ላይ የተገኘው ሀብት በቸልተኝነት ወይም ሆነ ብሎ ያደረሰው ጉድለት እንዲተካ ወይም ጉዳቱን ለመጠገን የሚያስፈልገውን ገንዘብ እንዲከፍል በማዘዝ ቀሪ ገንዘቡ እንዲመለስለት ለማድረግ ይችላል፡፡

## <u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለማሸግና የሀብት ዝርዝር ስለማዘጋጀት</u>

22.<u>መkርህ</u>

1. ዕግድ የተሰጠበትን ንብረት አሽጎ መጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በዚህ ክፍል የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።
2. በፍርድ ቤት ትእዛዝ የተደረገውን እሽግ ፍርድ ቤቱ እንዲነሳ ካላዘዘ በቀር ማንም ሰው እሽጉን ለመቅደድ ወይም ለመክፈት አይችልም። በጉዳዩ ያገባኛል የሚል ወገን እሽጉ እንዲነሳለት ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል፡፡

23.<u>እሽግ እንዲደረግ ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>

1. መርማሪው ወይም ዐቃቤ ህጉ ንብረቱን ማሸግ አስፈላጊ መሆኑን በቃለ መሀላ ወይም በሌላ መንገድ በተረጋገጠ ማስረጃ ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል፡፡

2. የወንጀሉ ጉዳይ ውሳኔ ከማግኘቱ በፊት ፍርድ ቤት በራሱ አስተያየት ወይም ማመልከቻ ሲቀርብለት የማሸግ ትዕዛዝ ለመስጠት ይቻላል፡፡
3. ፍርድ ቤት የማሸግ ትዕዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ ይህንን ስራ ለመፈጸም ተገቢ የሆነ ሰው ከዚህ በኋል “አሻጊ” በመባል የሚታወቅ መርጦ ይሾማል፡፡

24.<u>ስለመዝገብ</u>

1. አሻጊው በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሰረት የእሸጉ ስራ ከተፈጸመ በኋላ ከዚህ ቀጥሎ የተገለጹትን ጉዳዮች የሚያመለክት የራሱ ፊርማ ያረፈበት እሸጉ የተደረገበት ቀንና ዓመት ምህረት ያለበት መዝገብ ያዘጋጃል፡፡

   ሀ/ የፍርድ ቤቱ ትእዛዝና ትእዛዙ የተሰጠበት ቀንና ዓመት ምህረት፣

   ለ/ የታሸጉትን ነገሮች ዝርዝርና የሚገኙበትን ሥፍራ፣

   ሐ/ እንዲታሸጉ ከታዘዙት ውስጥ መገኘትና መታሸግ የሚገባቸው ሆነው ሳይገኙ የቀሩትን /የጎደሉትን/ ነገሮች ዝርዝር፣

   መ/ የታሸጉ ነገሮች ያሉበትን ቤት ወይም የሚገኙበትን ቦታ የሚጠብቀውን ወይም ለዚሁ ቤትና ስፍራ አላፊ የሆነ ሰው ካለ ስሙንና አድራሻውን፣

2. የታሸጉ ንብረቶች የሚገኙበት ቤት ወይም ቦታ ቁልፍ ያለው ሲሆን አሻጊው መክፈቻዎቹን ለፍርድ ቤቱ ሬጂስትራር ማስረከብ አለበት።

25.<u>ስለማይታሸጉ ነገሮች</u>

1. ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ንብረቶች ላይ የእሽግ ትእዛዝ አያርፍባቸውም

   ሀ/ በተፈጥሮአቸው የሚበላሹ ወይም ቶሎ የሚሻግቱና የሚበሰብሱ ሲሆኑ፣

   ለ/ በመታሸጋቸው ምክንያት የሚበላሹ ወይም ቶሎ የሚሻግቱና የሚበሰብሱ ሲሆኑ፣

   ሐ/ ለባለንብረቱ አስፈላጊ የሆኑና ፍርድ ቤቱም አስፈላጊ መሆናቸውን ተረድቶ እንዳይታሸግባቸው ያዘዘ ሲሆን፣

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሐ) በተመለከተው መሰረት ፍርድ ቤቱ እንዲይታሸጉ ትእዛዝ የሰጠባቸውን ነገሮች ዝርዝር አሻጊው አዘጋጅቶ ማቅረብ አለበት።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) መሰረት የእሽግ ትእዛዝ እንዲያርፍበት የተደረገው ንብረት በሐራጅ ተሸጦ ገንዘቡ ተቀማጭ እንዲሆን ፍርድ ቤቱ ለማዘዝ ይችላል።

26.<u>ስለኑዛዜዎችና ስለሌሎች የጽሁፍ ሰነዶች</u>

1. አሻጊው በሚያሽገው ነገር ውስጥ የጉዛዜ ጽሁፎች ወይም ቀድሞ የታሸጉ ነገሮች ወይም ሌሎች ሰነዶች ያገኘ እንደሆነ የነዚህኑ ጽሁፎች ዝርዝር አዘጋጅቶ ባንድ ላይ ጠቅልሎ በእሽጉ ውስጥ እንዲቀመጡ ካደረገ በኋላ ስለዚሁ ጉዳይ ትእዛዝ እንዲሰጥበት ያዘጋጀውን ዝርዝር ለፍርድ ቤቱ ያቀርባል።
2. ፍርድ ቤቱም እነዚህ ሰነዶች ስለሚቀመጡበት ሁኔታና ስለአያያዛቸው ተስማሚ መስሎ የታየውን ውሳኔ ይሰጣል።

27.**<u>እሽግን ስለማንሳት</u>**

1. እሽግ እንዲነሳ ማመልከቻ ሲቀርብ ወይም ፍርድ ቤቱ በራሱ አስተያየት እሽጉን ማንሳት ተገቢ መሆኑን ሲገምት ትእዛዙን በሚሰጥበት ጊዜ ለጉዳዩ አግባብ ያላቸው ወገኖች ሁሉ እንዲቀርቡ ያዛል፣ ባለጉዳዮቹም ቀርበው ያላቸውን ሀሳብ ለመግለጽ ይችላሉ፡፡
2. እሽጉ እንዲነሳ ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ከሰጠ በኋላ አሻጊው እሽጉን በማንሳት እሽጉ ሲከፈት የተገኙትን ነገሮች ዝርዝር አዘጋጅቶ ከፈረመባቸው በኋላ ቀኑንና ዓመተ ምህረቱን ጽፎ ያቀርባል፡፡

28.**<u>የንብረቶችን ዝርዝር ስለማዘጋጀት</u>**

1. ትእዛዝ የተሰጠበትን ንብረት ዝርዝር እንዲዘጋጅና እንዲታወቅ ማስፈለጉን ፍርድ ቤቱ ሲረዳው ይህንኑ ዝርዝር ለማዘጋጀት ይችላል ብሎ የሚገምተውን ሰው/ ከዚህ ቀጥሎ "መዝጋቢ" በመባል የሚታወቅ/ መርጦ የዚህኑ ንብረት ዝርዝር አዘጋጅቶ እንዲቀርብ ትእዛዝ ይሰጣል።
2. መዝጋቢው ከሁለት የማያንሱ ምስክሮች ባሉበት በፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ላይ ተለይቶ የተገለጸውን የንብረት ዝርዝር ያዘጋጃል። ዝርዝሩም ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱትን ነገሮች ይይዛል፡፡

   ሀ/ የንብረቱ ዝርዝር እንዲዘጋጅ ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ትእዛዝ እና

   ለ/ የተመዘገቡትን ንብረቶች ትክክለኛ ዝርዝር ከዋጋቸው ግምት ጋር።
3. ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ከሰጠ የንብረቶቹ ዋጋ የሚገመተው በፍትሀ ብሄር ሥነሥርአት ሕግ አንቀፅ 131 በተመለከተው መሰረት በልዩ አዋቂ /ኤክስፐርት/ አማካይነት ይሆናል፡፡ ልዩ አዋቂው ባደረገው የዋጋ ግምት ዝርዝር መግለጫ ላይ ቀኑንና ዓመተ ምሕረቱን ጽፎና ፈርሞበት ከመዝጋቢው ራፖር ጋር ይያያዛል።

4. የመዝጋቢው ራፖር የተጻፈበት ቀንና ዓመት ምህረት ተሞልቶበትና ተፈርሞበት ለፍርድ ቤት ይቀርባል፡፡ ፍርድ ቤቱም በተለይ ለዚሁ ጉዳይ በተዘጋጀው መዝገብ ውስጥ በፍርድ ቤቱ ሬጂስትራር እንዲመዘገብ ካደረገ በኋላ ጉዳዩ ከሚመለከተው መዝገብ ጋር በማያያዝ አባሪ ሆኖ እንዲቀመጥ ያደርጋል።

## ክፍል አራት

## ስለንብረት አወራረስ ሥነሥርአት

### 29.ንብረት ስለሚወረስበት ሁኔታ[24]

1. ተከሳሽ በሙስና ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ፡-

ሀ/ በሙስና ወንጀል የተገኘ ለመሆኑ የተረጋገጠ ንብረትና በወንጀሉ ከተገኘው ንብረት ያፈራው ንብረት ወይም በሙስና ወንጀሉ ከተገኘው ጥትምና በወንጀል ከተገኘው ንብረት ያፈራው ንብረት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ማናቸውም የተከሳሹ ንብረት እንዲወረስ፣ ወይም

ለ/ በወንጀሉ ምክንያት ከራሱ ያገኘው ጥቅም ባይኖርም ሌሎች ሰዎች ጥቅም ማግኘታቸው ወይም በግለሰብ፣ በመንግሥት ወይም በሕዝባዊ ድርጅት ጥቅም የደረሰ ጉዳት መኖሩ ከተረጋጋጠ ሌሎች ሰዎች ካገኙት ጥቅም ወይም ደረሰ ተብሎ ከሚገመተው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የተከሳሽ ንብረት በማካካሻነት እንዲወረስ፣ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

2. ለዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) አፈፃፀም የተከሳሹ ንብረት በሙስና ከተገኘው ጥቅም ወይም ከደረሰው ጉዳት ያነሰ እንደሆነ ወይም በተከሳሹ ስም የተመዘገበ ንብረት ያልተገኘ እንደሆነ ውሳኔው በተከሳሹ የጋራ ንብረት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።
3. ለዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) አፈፃፀም የተከሳሹ የጋራ ንብረት በተከሳሹ እና በሌላ ሰው ስም በጋራ የተያዘ ንብረት ወይም በህግ እንደ የጋራ ንብረት የሚወሰድ ንብረት ሲሆን በተከሳሹ የትዳር ጓደኛ ወይም ከ18 ዓመት በታች ዕድሜ ባለው ልጁ ወይም በእነዚህ በሁለቱ ስም በጋራ ያለ ንብረት የተከሳሹ የጋራ ንብረት እንደሆነ ይገመታል። ሆኖም የሚመለከተው ሰው ንብረቱ ከተከሳሹ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው የግል ሀብቱ መሆኑን በግልፅ የሚያስረዳ ማስረጃ ለፍርድ ቤት በማቅረብ ይህን ግምት ማፍረስ ይችላል።

[24] ይህ አንቀፅ በማሻሻያ አዋጁ 21/37(2007) አ.882 አንቀፅ 2(5) መሰረት የቀድሞው ተሰርዞ ተተክቷል፡፡

30.**<u>የመውረስ ውሳኔን ስለማዘግየት</u>**

1. ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ በወንጀል ድርጊቱ ጥቅም ማግኘት አለማግኘቱን ወይም ተመላሽ የሚሆነውን የንብረት መጠን ለመወሰን ተጨማሪ ማስረጃዎች ማግኘት አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው የጥፋተኝነት ውሳኔ ከሰጠበት ቀን አንስቶ ከስድስት ወር ላልበለጠ ጊዜ ውሳኔውን ሊያዘገየው ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የመውረስን ውሳኔ ለማዘግየት የሚቻለው በዐቃቤ ህግ ጥያቄ ወይም በፍርድ ቤቱ አነሳሽነት ሊሆን ይችላል፡፡

31.**<u>ንብረት እንዲወረስ ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>**

1. ፍርድ ቤቱ ንብረት እንዲወረስ ያልወሰነ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 29 በተመለከተው መሰረት ንብረት የመውረስ ጥያቄ በዐቃቤ ህግ አመልካችነት ሊታይ ይችላል።[25]
2. የንብረት መወረስ ጥያቄ ተከሳሹ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ በኋላ ሊቀርብ ይችላል፡፡

32.**<u>ንብረትን በፍታሐ ብሔር ክስ ስለማስመለስ</u>**[26]

1. በዚህ አዋጅ በአንቀፅ 29 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በተለያየ ምክንያት ክሱ እንዲቋረጥ በመደረጉ ወይም በማንኛውም ሌላ ምክንያት የጥፋነኝነት ውሳኔ ባይሰጥም በሙስና የተገኘ ንብረት እና በወንጀሉ በተገኘው ንብረት ያፈራው ንብረት ወይም በወንጀል ከተገኘው እና ከተፈራው ንብረት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ዋጋ እንዲወረስ ለማድረግ ወይም በወንጀሉ ለደረሰ ጉዳት ማካካሻ የሚሆን ተመጣጣኝ ዋጋን ለማስከፈል አግባብ ያለው አካል በፍትሐ ብሔር ክስ ሊመሰርት ይችላል፡፡
2. አግባብ ያለው አካል ተገቢ ሆኖ ሊያገኘው በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (5) ከተገለፀው ውጭ በማንኛውም ምክንያት በሙስና ወንጀል የተገኘ ንብረት እና በወንጀሉ በተገኘው ንብረት ያፈራው ንብረት ወይም በወንጀል ከተገኘው እና ከተፈራው ንብረት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ዋጋ እንዲወረስ ለማድረግ፣ ወይም በወንጀሉ ለደረሰ ጉዳት ማካካሻ የሚሆን ተመጣጣኝ ዋጋን ለማስከፈል በፍትሐ ብሔር ክስ ሲመሰርት ይችላል፡፡

---

[25] ይህ ንዑስ አንቀፅ በማሻሻያ አዋጁ 21/37(2007) አ.882 አንቀፅ 2(6) መሰረት የቀድሞው ተሰርዞ ተተክቷል፡፡

[26] ይህ አንቀፅ በማሻሻያ አዋጁ 21/37(2007) አ.882 አንቀፅ 2(7) መሰረት የቀድሞው ተሰርዞ ተተክቷል፡፡

3. በሙስና ወንጀል የተገኘው ንብረት የመንግስት መስሪያ ቤት፣ የመንግስት የልማት ድርጅት፣ የህዝባዊ ድርጅት ወይም የሌላ ግለሰብ ንብረት ወይም ገንዘብ ሆነ ይኸው ተቋም ወይም ግለሰብ በሙስና የተገኘው ንብረት ወይም ገንዘብ እንዲመለስ በፍትሐ ብሔር ክስ እንዲመሰርት አግባብ ያለው አካል ፈቃድ ሊሰጥ ወይም ሊወክል ይችላል። አግባብ ያለው አካል እነዚህ ተቋማት የሚመሰርቱትን ክስ በሚመለከት ውጤቱን ይከታተላል።

33.**ለፍርድ ቤት ስለሚቀርበው የማስረጃ ደረጃ**

አንድ ሰው በሙስና የወንጀል ድርጊት ሳቢያ ጥቅም ያገኘ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ወይም ተመሳሽ የሚሆነውን ገንዘብ መጠን መወሰንን አስመልክቶ የሚነሱ ክርክሮችን ለማስረዳት የሚቀርበው የማስረጃ ደረጃ በፍትሐብሄር ክርክር ጊዜ እንደሚቀርበው የማስረጃ ደረጃ ይሆናል።

34.**ተመላሽ ስለሚሆነው የንብረት ወይም የጥቅም መጠንና ንብረቱ ለመንግሥት ገቢ ስለሚሆንበት ሁኔታ**[27]

1. ተከሳሹ በሙስና ወንጀል ያገኘው ንብረትና በወንጀል ከተገኘው ንብረት ያፈራው ንብረት ወይም ተመጣጣኙ፣ ወይም በወንጀሉ ካደረሰው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው ንብረት ተመላሽ ይደረጋል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) በተመለከተው ተመላሽ የሚደረገው የንብረት መጠን ተከሳሹ ካገኘው ጥቅም ወይም ያገኛል ተብሎ ከሚገመተው ጥቅም ወይም ደረሰ ተብሎ ከሚገመተው ጉዳት በላይ መሆን ወይም መብለጥ የለበትም፡፡
3. በፍርድ እንዲወረስ ውሳኔ የተሰጠበትን ንብረት አግባብ ያለው አካል በመረከብ ለመንግስት ያስረክባል። ንብረቱ ሙሉ በሙሉ የማይወረስ ሲሆን ወይም ከሌላ ንብረት ጋር ተዳብሎ የሚገኝ ሲሆን አግባብ ያለው አካል ንብረቱ በፍርድ አፈፃፀም መሠረት እንዲሸጥ በማድረግ ገንዘቡን ለመንግስት ገቢ ያደርጋል።

**ክፍል አምስት**

**ቅድመ ክስ ዝግጅት**

35.**መርህ**

[27] ይህ አንቀፅ በማሻሻያ አዋጁ 21/37(2007) አ.882 አንቀፅ 2(8) መሰረት የቀድሞው ተሰርዞ ተተክቷል፡፡

የሙስና ወንጀል ክስ የቀረበለት ፍርድ ቤት የቀረበው ክስ ጭብጦችና የማስረጃው ዝርዝር ውስብስብ በመሆኑ ምክንያት የፍርድ ሂደቱን የሚያራዝመውና የሚያወሳስበው መስሎ ከታየውና በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 36 የተመለከቱትን አላማዎች ሊያሟላ ይችላል ብሎ ካመነ የቅድመክስ ዝግጅት እንዲከናወን ሊወስን ይችላል፡፡

## 36.<u>ቅድመ ክስ ዝግጅት ዓላማና ሂደት</u>

1. የቅድመ ክስ ዝግጅት አላማ የሚከተሉት ናቸው።

   ሀ/ ለክሱ አወሳሰን ሊረዱ የሚችሉ ጭብጦችን ለመለየት

   ለ/ ባለጉዳዮች ጭብጦቹን እንዲረዱ እገዛ ለማድረግ

   ሐ/ የክሱን ሂደት ለማፋጠን

   መ/ ፍርድ ቤት የክሱን አካሄድ ለመምራት እንዲያስችለው ለማገዝ

2. በቅድመ ክስ ሂደት ፍርድ ቤቱ፣[28]

   ሀ/ ዐቃቤ ሕግና ተከሳሽ በዚህ ክፍል የተጣለባቸውን ግዴታዎች መፈፀማቸውን ያረጋግጣል፤

   ለ/ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕጉ አንቀፅ 130 መሠረት ለሚነሱ ጉዳዮች እልባት ይሰጣል፡፡

   ሐ/ ዐቃቤ ሕግ የተከሳሽን መልስ ከተመለከተ በኋላ ክስ ማሻሻያ መኖር ያለመኖሩን በመጠየቅ ያረጋጣል፤ የሚሻሻል ሲኖርም ክሱን እንዲያሻሽል ዐቃቤ ህጉን ያዘዋል።

## 37.<u>አቃቤ ህግ ግዴታ</u>[29]

ፍርድ ቤቱ አቃቤ ህጉን፣

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 38 ሥር የተዘረዘሩትን በተመለከተ ለፍርድ ቤቱና ለተከሳሽ የጽሁፍ መግለጫ እንዲሰጥ፣
2. ለክሱ ሂደት ሊረዱ የሚችሉ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ እና ክሱን ለመረዳት የሚያስችል ማቴሪያል ፍርድ ቤቱ በሚያዘው ፎርም መሰረት እንዲያዘጋጅና ለፍርድ ቤትና ለተከሳሽ እንዲሰጥ፣

---

[28] ይህ ንዑስ አንቀፅ በማሻሻያ አዋጁ 21/37(2007) አ.882 አንቀፅ 2(9) መሰረት የቀድሞው ተሰርዞ ተተክቷል፡፡

[29] የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (4) በማሻሻያ አዋጁ 21/37(2007) አ.882 አንቀፅ 2(10) መሰረት ተሰርዟል፡፡

3. በእሱ አስተያየት ተቀባይነት ሊኖራቸው ይገባል የሚላቸውን ይዘታቸው እውነትነት ያላቸውን ሰነዶች እና ሌሎች ስምምነት ሊደረስባቸው ይችላሉ የሚላቸውን ጉዳዮች ለፍርድ ቤትና ለተከሳሽ በጽሁፍ እንዲያስታውቅ፣

38.**<u>በዐቃቤ ህግ የሚቀርብ የጽሁፍ መግለጫ</u>**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 37 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚቀርብ የጽሁፍ መግለጫ የሚከተሉትን የያዘ መሆን ይኖርበታል፤

1. ለክሱ መሰረት የሆኑትን መሰረታዊ ፍሬ ነገሮች፣
2. በአቃቤ ህግ አመልካችነት ፍርድ ቤት ሲፈቅድ የምስክሮችን ስም በምስጢር መያዝ ካላስፈለገ በስተቀር ለፍሬ ነገሩ የሚጠሩትን ምስክሮች፣
3. ለፍሬ ነገሩ አግባብነት ያላቸውን ኤግዚቢቶች እና ሌሎች የሰነድ ማስረጃዎች፣
4. ዐቃቤ ህጉ ለክሱ መሰረት ያደረገውን የህግ ድንጋጌ፣
5. ከዚህ በላይ ባሉት ንዑስ አንቀጾች ከተመለከቱት የሚመነጩ ወይም የተያያዙ ናቸው ብሎ ዐቃቤ ህግ የሚያቀርባቸው፡፡

39.**<u>የተከሳሽ ግዴታ</u>**

ዐቃቤ ህጉ በፍርድ ቤቱ ትእዛዝ መሰረት ከፈጸመ በኋላ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ፣

1. የመከላከያውን አጠቃላይ ነጥቦች ይዘት እና በመሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ሊያነሳ ያሰባቸውን ጭብጦች በተመለከተ ለፍርድ ቤቱና ለዐቃቤ ሕግ የጽሁፍ መግለጫ እንዲሰጥ፣
2. በቀረበው ክስ ላይ ያለውን ተቃውሞ ለፍርድ ቤቱና ለዐቃቤ ህግ የጽሁፍ መግለጫ እንዲሰጥ፣
3. ለመከላከያው መሰረት ያደረጋቸውን የሕግ ነጥቦችና ማስረጃዎችን በተመለከተ ለፍርድ ቤቱና ለዐቃቤ ሕጉ የጽሁፍ መግለጫ እንዲሰጥ፣
4. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 37 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ዐቃቤ ህጉ ያቀረባቸውን ሰነዶችና ሌሎች ጉዳዮች በተመለከተ ከአቃቤ ሕግ ጋር የሚስማማባቸው ነጥቦች ካሉ እንዲገልጽ፣ ያልተስማማባቸው ካሉ ምክንያቱን እንዲገልጽ፣

   ሊያዘው ይችላል።

**<u>ክፍል ስድስት</u>**

**<u>ስለ ማስረጃ</u>**

**40.ማስረጃ ስለመጠየቅ**[30]

1. አንድ መርማሪ ወይም አቃቤ አንድ ተጠርጣሪ በወንጀል ድርጊት ተጠቃሚ መሆኑን ወይም ከወንጀል ድርጊት የተገኘውን የጥቅም መጠን ወይም የሚገኝበትን ቦታ ለማወቅ አግባብ ያለው ሰነድ በእጁ ያለ ወይም የሚገኝበትን የሚያውቅ ማንኛውም ወይም አካል እንዲሰጠው ወይም እንዲያይ ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ ጥያቄው አግባብነት ያለው ሆኖ ካገኘው ጉዳዩ የሚመለከተውን ሰው መጥራት ሳያስፈልግ በእጁ የሚገኘውን ወይም ይገኛል ተብሎ የሚጠረጠረውን ማስረጃ ፍርድ ቤቱ በሚወስነው ቀን ውስጥ ሰነዱን ለመርማሪው ወይም ለዐቃቤ ህጉ እንዲሰጥ ወይም እንዲያሳይ ለማዘዝ ይችላል፡፡
3. ፍርድ ቤቱ በሶስተኛ ሰው እጅ የሚገኝ ማስረጃ ለመርማሪው ወይም ለአቃቤ ህጉ እንዲሰጥ ወይም መርማሪው ወይም አቃቤ ህጉ እንዲያየው ለማዘዝ ይችላል።

**41.ግብረ አበርን ከክስ ነጻ ስለማድረግ**

1. በሙስና ወንጀል ተካፋይ የሆነ ጉዳዩ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት ስለተፈጸመው ድርጊትና ስለተባባሪዎች ሚና ጠቃሚ ማስረጃ ከሰጠ በፌዴራል የስነ ምግባርና የጸረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ወይም አግባብ ባለው አካል የበላይ ኃላፊ ውሳኔ ከክሱ ነፃ እንዲሆን ይደረጋል፡፡
2. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "ጠቃሚ ማስረጃ" ማለት፣
   ሀ/ የቀረበው ማስረጃ ብቻውን በቀረበው የሙስና ወንጀል ክስ የጥፋተኛነት ውሳኔ ለማሰጠት በቂ ከሆነ፣ ወይም
   ለ/ ማስረጃው በመገኘቱ ሌሎች መረጃዎችንም ለማግኘት መሰረታዊ ፍንጭ ሆኖ የሚያገለግል ከሆነ፣ ወይም
   ሐ/ የተገኘው ማስረጃ ከሌሎች ማስረጃዎች ጋር በመቀናጀት የጥፋተኝነት ውሳኔ ለማሰጠት የሚያስችል ከሆነና ይኸው ማስረጃ ባለመካተቱ ወንጀሉን ለማረጋገጥ በሌላ መልኩ የተሰባሰበው ማስረጃ በቂ የማይሆን ነው ተብሎ ሲታመን፣

   ነው።

[30] ይህ አንቀፅ ቀድሞ አንቀፅ 42 የነበረ ሲሆን በማሻሻያ አዋጁ 21/37(2007) አ.882 አንቀፅ 2(11) መሰረት አንቀፅ 40 አና 41 የነበሩት ተሰርዘው ከአንቀፅ 42 እስከ 56 ያሉት ነባር አንቀጾች እንደ ቅደም ተከተላቸው ከአንቀፅ 40 እስከ 54 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

3. ተጠርጣሪው ማስረጃውን በመስጠቱ ከክስ ነጻ የሚሆን ለመሆኑ ስልጣን ያለው ባለስልጣን በጽሁፍ ማረጋገጫ ይሰጠዋል። አግባብ ያለው አካል ከተጠርጣሪው የተገኘውን ማስረጃ በሰጠው ሰው ላይ በማስረጃነት ሊያቀርብ አይችልም።
4. ተጠርጣሪው በገባው ስምምነት መሰረት ማስረጃውን ካላቀረበ ወይም ተገቢውን ምስክርነት ካልሰጠ ስምምነቱን እንዳላከበረ ተቆጥሮ ያለመከሰስ መብቱ ይነሳል።
5. ከክስ ነጻ የተደረገ በሙስና ወንጀል ተካፋይ የሆነ ሰው የሚሰጠው የምስክርነት ቃል ክብደት ማንኛውም ምስክር ከሚሰጠው ምስክርነት እኩል ዋጋ አለው፡፡
6. በዚህ አንቀጽ መሠረት ከክሱ ነፃ የሚሆን በሙስና ወንጀል ተካፋይ የሆነ ሰው በወንጀሉ ያገኘው ንብረት ተመላሽ እንዲሆን ይደረጋል።

42.**<u>ስለአስጠቂ ምስክር</u>**

1. በዐቃቤ ህግ ወይም በመከላከያ ምስክርነት የቀረበ ማንኛውም ሰው በምስክርነት በተጠራበት ጉዳይ እውነቱን ለመናገር ባለመፈለግ ቀድሞ ከሰጠው የምስክርነት ቃል የሚቃረን የምስክርነት ቃል የሰጠ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ምስክሩን ያቀረበውን ወገን መሪ ጥያቄ እንዲጠይቅ ሊፈቅድለት ይችላል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ መሪ ጥያቄ እንዲጠየቅ ከመፍቀዱ በፊት ተቃራኒ የምስክርነት ቃል የሰጠ መሆን አለመሆኑን ምስክሩን ይጠይቀዋል። ምስክሩ ተቃራኒ የምስክርነት ቃል መስጠቱን ከተቀበለ መሪ ጥያቄውን ይፈቅዳል።
3. ምስክሩ ተቃራኒ የምስክርነት ቃል መስጠቱን የካደ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ምስክሩ ተቃራኒ ቃል መስጠት አለመስጠቱን ይወስናል።

43.**<u>ስለኮምፕዩተር ሰነድ</u>**

በኮምፒዩተር በተገኘ ሰነድ ላይ የሰፈረ ጽሁፍ አንድን ፍሬ ነገር ለማረጋገጥ በማስረጃነት ተቀባይነት የማይኖረው፣

1. በኮምፒዩተር ተገቢ ያልሆነ አጠቃቀም ምክንያት በሰነዱ ላይ የሰፈረው ጽሁፍ ትክክለኛ አለመሆኑን የሚያሳምኑ በቂ ምክንያቶች መኖራቸውን ወይም
2. ኮምፒዩተሩ ስራ ላይ ባልዋለባቸው ጊዜያት በተገቢው መንገድ የማይሰራ መሆኑን ወይም ኮምፒዩተሩ በስራ ላይ ባልዋለበት ወይም ከስራ ውጭ በሆነበት ጊዜ የሰነዱን አወጣጥ ወይም ይዘት የሚያፋልስ መሆኑን፣

   ማሳየት ሲቻል ነው፡፡

## 44.ግንኙነትንና ደብዳቤን ስለመጥለፍ [31]

1. ለሙስና ወንጀል ምርመራ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በስልክ፣ በቴሌኮሚኒኬሽንና በኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች የሚደረግ ግንኙነት እንዲሁም ደብዳቤ እንዲጠለፍ አግባብ ያለው አካል የበላይ ሀላፊ ማዘዝ ይችላል።
2. ለሙስና ወንጀል ምርመራ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በካሜራ፣ ድምጽ መቅረጫ እና የመሳሰሉት የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች አማካይነት የተሰባሰቡ ማስረጃዎች እንደማንኛውም ማስረጃ የሙስና ወንጀል መፈጸሙን ለማስረዳት ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚሰጥ ትእዛዝ ለጠለፋው ምክንያት የሆነውን ወንጀል እና ጠለፋው የሚቆይበትን ጊዜ የሚጠለፈው የስልክ ግንኙነት ከሆነ ጠለፋው የሚመለከተውን የግንኙነት መስመር መግለጽ ይኖርበታል። አግባብ ያለው አካል የበላይ ሀላፊ በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በቀር ትእዛዙ የሚጸናው ከአራት ወር ላልበለጠ ጊዜ ይሆናል፡፡
4. ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ ስልክ በመደወል ተገቢ ያልሆነ ጥቅም እንዲሰጠው የጠየቀ ወይም ምስክርን፣ ጠቋሚን፣ መርማሪን፣ ዐቃቤ ህግን ወይም ዳኛን ያስፈራራ ስውን ማንነት እና አድራሻ ጉዳዩ የሚመለከተው ቴሌኮሙኒኬሽን አካል እንዲያሳውቀው አግባብ ያለው አካል የበላይ ኃላፊ ሊጠይቅ ይችላል፡፡
5. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት የደዋዩን ማንነት እና አድራሻ እንዲያሳውቅ ጥያቄ የቀረበለት ጉዳዩ የሚመለከተው አካል የሥራ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ሳይዘገይ የተሟላ መረጃ ጥያቄውን ላቀረበለት አግባብ ላለው አካል መስጠት አለበት፡፡ መረጃውን አለመስጠት ወይም መረጃውን በተሟላ መልኩ አለመስጠት አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ ድንጋጌ ያስጠይቃል፡፡

## 45.ስለመቅዳት

1. ግንኙነት መቅዳትን በተመለከተ ትዕዛዙን የሚፈጽመው አካል በእያንዳንዱ ጠለፋ የተቀዳውን እና ጠለፋው የተጀመረበትንና ያበቃበትን ሰዓት መመዝገብ ይኖርበታል።

---

[31] የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (4) እና (5) ማሻሻያ አዋጁ 21/37(2007) አ.882 አንቀፅ 2(12) መሰረት አዲስ የተጨመሩ ናቸው፡፡

2. ትእዛዙ የተላለፈለት አካል በጠለፋ ከተቀዳው ውስጥ ከወንጀሉ ጋር በተያያዘ እውነቱን ለማወቅ የሚረዳውን በጽሁፍ አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ማቅረብ ይኖርበታል።

## ክፍል ሰባት

## የሙስና ድርጊትን ስለሚጠቁሙ ሰዎች ጥበቃ

### 46.ዓላማ

የጥበቃው አላማ

1. የሙስና ወንጀል እንዲጋለጥ ለማበረታታት፤ እና
2. ጥቆማውን ያቀረበውን ሰው መብትና ጥቅም ተገቢው ግምት እንዲሰጥ ለማድረግ ነው።

### 47.ስለጥቆማ አቀራረብ

1. የሙስና ድርጊት የጠቋሚውን ስም ተገልጸ ወይም ሳይገለጽ አግባብ ላለው አካል ሊቀርብ ይችላል።
2. አንድን ጥቆማ በአግባቡ አግባብ ላለው አካል ከደረሰ ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ጥቆማውን እንደተቀበለው ይቆጠራል።

### 48.ከሃላፊነት ነጻ ስለመሆን

በሕግ በቃለ መሀላ ወይም በስምምነት ማስረጃን በሚስጥር የመጠበቅ ግዴታ ያለበት ማናቸውም ሰው ማስረጃውን አግባብ ላለው አካል በመስጠቱ ህጉን ቃለ መሐላውን ወይም ስምምነቱን እንደጣሰ አያስቆጥረውም፡፡

### 49.ጥቆማውን ስለሚቀበለው አካል

1. አግባብ ያለው አካል ከማናቸውም ሰው የሙስና ድርጊትን በተመለከተ ጥቆማ ሲደርሰው የመቀበል ግዴታ አለበት፡፡
2. አግባብ ያለው አካል ጥቆማውን እንደደረሰው በመዝገብ ውስጥ ማስፈር ይኖርበታል።
3. አግባብ ያለው አካል የደረሰውን ጥቆማ በተመለከተ፣

   ሀ/ ተጠሪ ለሆነው አካል ዓመታዊ ሪፖርት የማቅረብ

   ለ/ በስም ጥቆማ ላቀረበ ሰው በጥቆማው ላይ ስለተወሰደው እርምጃ ተገቢውን መረጃ የመስጠት ሀላፊነት አለበት፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3(ለ) መሰረት የሚሰጥ ማስረጃ ለማናቸውም ሰው ደህንነት የሚያሰጋ ወይም የወንጀሉን የምርመራ ሂደት የሚያደናቅፍ ከሆነ ማስረጃው መሰጠት የለበትም፡፡

50.**<u>በመዝገቡ ስለሚሰፍሩ ጉዳዮች</u>**

አግባብ ያለው አካል የሚደርሰውን ጥቆማ በተመለከተ ቢያንስ የሚከተሉትን ማስረጃዎች በመዝገብ ማስፈር ይኖርበታል።

ሀ/ የሚታወቅ ከሆነ የጠቋሚውን ስም

ለ/ የጥቆማውን ፍሬ ሀሳብ እና

ሐ/ ጥቆማውን አስመልክቶ ስለተወሰደው እርምጃ

51.**<u>የቂም በቀል እርምጃ ህገወጥ ስለመሆኑ</u>**

1. ማንኛውም ሰው በሌላ በማንኛውም ሰው ላይ ጥቆማ አቅርቦአል ወይም ምስክርነት ሰጥቶአል ወይም ለማቅረብ፣ ለመስጠት አስቧል በሚል ጉዳት ማድረስ ወይም ለማድረስ መሞከር ወይም ማሴር ህገወጥ ድርጊት ነው።
2. እያንዳንዱ የመንግስት መስሪያ ቤት፣ የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛውን ከቂም በቀል እርምጃ ለመከላከል የሚያስችለው ሥርዓት መዘርጋት ይኖርበታል።[32]

52.**<u>የቂም በቀል እርምጃን ስለማገድ[33]</u>**

1. የቂም በቀል እርምጃ የተወሰደበት ሰው ሰራተኛ ከሆነ በአስተዳደሩ የተወሰደበት እርምጃ እንዲታገድለት አግባብ ላለው አካል አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አቤቱታ የቀረበለት አግባብ ያለው አካል አቤቱታውን ወዲያውኑ በመቀበል የቂም በቀል እርምጃ መኖር አለመኖሩን በማጣራት ተገቢነት ያለውን ትእዛዝ መስጠት ይኖርበታል።
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) መሠረት አግባብ ያለው አካል በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ወገን እቤቱታውን በ 60 ቀናት ጊዜ ውስጥ ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል። በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ አቤቱታውን ለፍርድ ካላቀረበ ተቀባይነት እንዳገኘ ተቆጥሮ ውሳኔው የፀና ይሆናል።

---

[32] ይህ ንዑስ አንቀፅ በማሻሻያ አዋጁ 21/37(2007) አ.882 አንቀፅ 2(13)መሰረት የቀድሞው ተሰርዞ ተተክቷል፡፡

[33] ይህ አንቀፅ በማሻሻያ አዋጁ 21/37(2007) አ.882 አንቀፅ 2(14) መሰረት የቀድሞው ተሰርዞ ተተክቷል፡፡

4. አግባብ ያለው አካል የቁም በቀል እርምጃ በወሰደው ሰው ላይ አግባብ ባለው ሕግ መስረት የወንጀል ክስ የመሰረተ እንደሆነ በቀረበው ክስ ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ የእግድ ትእዛዙ እንደፀና ይቆያል።
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ለፍርድ ቤት በቀረበው አቤቱታ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ በዚሁ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ እንደፀና ይቆያል።

## <u>ክፍል ስምንት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

### 53.<u>ተፈጻሚነት ስላላቸው ህጎች</u>

የወንጀል ሥነሥርአት ህግ፣ የፍትሀብሄር ሥነሥርአት ህግ የወንጀል ህግና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ህጎች ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

### 54.<u>ስለቅጣት</u>

1. ተከሳሹ ወይም የእግድ ትእዛዙ የሚመለከተው ሌላ ሰው ፍርድ ቤት የሰጠውን የእግድ ትእዛዝ ያላከበረ እንደሆነ ተከሳሹ ወይም ትእዛዙን ያላከበረው ሰው በፍርድ ቤት መድፈር ወንጀል ከሁለት ዓመት ባልበለጠ የእስራት ቅጣት እና ከብር አስር ሺህ ባልበለጠ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡
2. በወንጀል ህግ የበለጠ ቅጣት የሚያስቀጣ ካልሆነ በቀር በዚህ አዋጅ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 1 እና አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተውን በመተላለፍ ሆን ብሎ በንብረት ላይ ጉዳት ወይም ጉድለት ያደረሰ ወይም እሽጉን የቀደደ ወይም የከፈተ ከ3 አመት በማይበልጥ እስራትና ከብር ሃያ ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

### 55.<u>የመቀጮ ቅጣት ተፈፃሚነት</u>[34]

1. በሙስና ወንጀል ጥፋተኝነቱ የተወሰነበትን ቅጣት ተከሳሹ መክፈል ካልቻለ በወንጀል ህግ ሥነ-ሥርዓት መሰረት ፍርድ ቤቱ የሚወስዳቸው እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆነው አግባብ ያለው አካል ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ፍርድ ቤቱ ያዘዋል።

[34] አንቀፅ 55፣ 56 እና 57 በማሻሻያ አዋጁ 21/37(2007) አ.882 አንቀፅ 2(15) መሰረት አዲስ የተጨመሩ ናቸው፡፡

2. ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ትእዛዝ የተሰጠው አግባብ ያለው አካል መቀጮው ለመንግሥት ገቢ መደረጉን ያረጋግጣል፤ ገቢ ያልተደረገ ሲሆን ገቢ ስለሚሆንበት ወይም የማካካሻ እርምጃ ስለሚወሰድበት ሁኔታ አጥንቶ ለፍርድ ቤቱ ያቀርባል፤ ፍርድ ቤቱ በቀረበው ጥናት ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## 56.<u>በወንጀል ያለመከሰስ መብትን ስለማንሳት</u>

ያለመከሰስ መብትን ስለማንሳት በሌሎች ህጎች የተደነገገው ቢኖርም የፌዴራል ወይም የክልል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የበላይ ኃላፊ[35] ለመመርመርና ለመክሰስ ስልጣን በተሰጠው ጉዳዮች ዙሪያ ያለመከሰስ መብት የማንሳት ጥያቄን እንደሁኔታው ጉዳዩን ለሚመለከተው የሕዝብ ተወካዮች ወይም የክልል ምክር ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

## 57.<u>በፌዴራልና በክልል የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች መካከል ስለሚኖር የሥራ ግንኙነት</u>

1. ሙስናን መሸከም የማይችል ህብረተሰብ በመፍጠር፣ እንዲሁም የሙስና ወንጀልን በመከላከል፣ በመመርመርና በመክሰስ ረገድ የፌዴራል እና የክልል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ተቋሞች በትብብርና በተደጋጋፊነት ይሠራሉ።
2. የክልል የሥነ-ምንባርና የፀረ-ሙስና ተቋሞች በኮሚሽኑ በሚሰጣቸው ውክልና መሠረት የሙስና ወንጀል ጉዳዮችን ሲመረምሩና ሲከሱ ተጠሪነታቸው ለኮሚሽኑ ይሆናል፡፡
3. የፌዴራል እና የክልል የሥነ-ምግባርና ሙስና ተቋሞች ለፀረ-ሙስና እንቅስቃሴው ስኬት፣ ሀገራዊ የፀረ-ሙስና ትግሉ አቅጣጫዎችን ለመንደፍና ለመተግበር፣ እንዲሁም በጋራ ለሚያከናውኗቸው ተግባራትና የሚያከናውኗቸውን አፈፃፀም ለመገምገም የሚወያዩበት የጋራ ጉባኤ ያቋቁማል ጉባኤው በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር የፌደራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር የጋራ ጉባኤውን ይመራል።
4. የጋራ ጉባኤው፡-

   ሀ/ የጋራ የአሠራር ውስጠ ደንብ ያወጣል፤

[35] በዚህ አንቀፅ ያለመከሰስ መብትን በተመለከተ ለፌዴራል ሰነምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር የተሰጠው ሰልጣን በአዋጅ ቁጥር 22/63(2008) አ.943 መሰረት ኮሚሽኑ የሙስና ወንጀሎችን የመክሰስ መብት የሌለው በመሆኑ ለኮሚሽነሩ የተሰጠው ግዴታ በጠቅላይ አቃቤ ህጉ የሚፈፀም ይሆናል፡፡

ለ/ ሙስናን በመከላከል፣ በመመርመር፣ በመክሰስ እና መልካም ሥነ-ምግባርን በማስፈን ረገድ የሥራ እንቅስቃሴዎችን በመገምገም የልምድ ልውውጥ ያደርጋል፤

ሐ/ የፀረ ሙስና ትግሉን የሚያጠናክሩ ጥናቶች የሚካሄዱበትን አቅጣጫ ይቀይሳል፤ በሚቀርቡ ጥናቶች ላይ ይወያያል፤ በጥናቶቹ መሰረት ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች እንዲወስኑ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል ወይም እንደሁኔታውም ይወስናል፤ በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

መ/ ሥራውን የሚያቀናጅለት ጽህፈት ቤት ይኖረዋል። ጉባኤው በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የጋራ ጉባኤው ጽህፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል፤

5. የጋራ ጉባኤው ያስተላለፋቸው ውሳኔዎች መተገበራቸውን የጉባኤው አባላት በየበኩላቸው ይከታተላሉ።
6. የኮሚሽኑ አካላትና የክልል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ተቋሞች በየአካባቢያቸው ስላለው የሙስና ወንጀል ሁኔታ እና ለተከናወነ የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ በሚመለከት ስታቲስቲካዊ መረጃ በየጊዜው ለጋራ ጉባኤው ጽህፈት ቤት ያስተላልፋሉ።

## 58.<u>መሸጋገርያ ድንጋጌ</u> [36]

ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተፈፀሙ ወንጀሎች በነባሩ የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ልዩ የስነ ስርዓትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 434/1997 መስረት ፍፃሜ ያገኛሉ።

## 59.<u>የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ህጎች</u>

1. የጸረሙስና የልዩ ሥነሥርዓትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 236/1993 እንደተሻሻለው በዚህ አዋጅ ተሸሯል፡፡
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ሌሎች ሕጎች በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

## 60.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከጥር 25 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

---

[36] ይህ አንቀፅ በማሻሻያ አዋጁ 21/37(2007) አ.882 አንቀፅ 2(16) መሰረት የቀድሞው አንቀፅ 57 ተሰርዞ የተተካ ሲሆን ነባሮቹ አንቀፅ 58 እና 59 አንደቅደም ተከተላቸው አንቀፅ 59 እና 60 ሆነው ተሸጋሽገዋል።

**ጥር 25 ቀን 1997 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## **አዋጅ ቁጥር 699/2003**

## **የወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ አዋጅ**

የወንጀል ድርጊቶች ከተፈጸሙ በኋላ ፈጻሚዎቹ ተደብቀው እንዳይቀሩና ህግ ፊት ቀርበው ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ በማድረግ የህብረተሰቡ ሰላማዊ ኑሮ የሚረጋገጥበትን ሁኔታ ማመቻቸት አስፈላጊ በመሆኑ፤

ለወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ መስጠት በኅብረተሰቡ ላይ ከፍተኛ ስጋት ሊያስከትሉ የሚችሉ ወንጀሎችን በማጋለጥ ወንጀልን ለመከላከል የሚረዳ በመሆኑ፤

የወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች በምስክርነታቸው ወይም በጠቋሚነታቸው ምክንያት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ከሚደርስባቸው አደጋና ጥቃት ለመከላከልና ደህንነታቸውን ለመጠበቅ የጥበቃ ሥርዓቶችን በሕግ መደንገግ በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግሥት አንቀጽ 55/1/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## **ክፍል አንድ**

## **ጠቅላላ**

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ “የወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 699/2003” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "ጠቋሚ ወይም ምስክር" ማለት በወንጀል ምርመራ፣ በወንጀል ክስ ወይም በወንጀል ማጣራት ሒደት መረጃ ወይም ምስክርነት የሰጠ ወይም ለመስጠት የተስማማ ሰው ነው፤
2. "የጥበቃ ተጠቃሚ" ማለት ከሚኒስቴሩ ጋር የጥበቃ ስምምነት የተፈራረመ ምስክር፣ ጠቋሚ ወይም የምስክር ወይም የጠቋሚ ቤተሰብ አባል ነው፤
3. "የመኖሪያ ስፍራን መቀየር" ማለት የጥበቃ ተጠቃሚን ከመኖሪያ ስፍራው ለጊዜው ወይም ለዘለቄታው ሚኒስቴሩ በአገር ውስጥ ወይም በውጭ አገር በሚያዘጋጅለት ቦታ ማስፈርን ወይም የጥበቃ ተጠቃሚው ነጻነትን የሚያሳጣ ቅጣት በመፈጸም ላይ ከሆነ ቅጣቱን በመፈጸም ላይ ካለበት ቦታ ወደተዘጋጀለት ሌላ የቅጣት መፈጸሚያ ቦታ ማዛወርን የሚመለከት የጥበቃ እርምጃ ነው፤
4. "ማንነትን መቀየር" ማለት የጥበቃ ተጠቃሚን ግላዊ መረጃዎች በከፊል ወይም በሙሉ ከአዲስ ሁኔታ ጋር እንዲስማማ አድርጎ ማስተካከል ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ አካላዊ ገጽታን መቀየርን የሚጨምር የጥበቃ እርምጃ ነው፤
5. "የዓይነ ቁራኛ ጥበቃ" ማለት ለጥበቃ ተጠቃሚ ስውር ጥበቃ ማድረግንና የረጅም ርቀት የመገናኛ መሣሪያ በመጠቀም በመኖሪያ ቤቱ ላይ የሚደረግ ቴክኒካዊ ቁጥጥርና ቀረጻን የሚያካትት የጥበቃ እርምጃ ነው፤
6. "ማንነትንና ባለንብረትነትን መደበቅ" ማለት የጥበቃ ተጠቃሚን ግላዊና ንብረቱን የሚመለከቱ ሰነዶችን በጊዜያዊነት መፍጠርንና መጠቀምን የሚያካትት የጥበቃ እርምጃ ነው፤
7. "ቤተሰብ" ማለት የትዳር ጓደኛን፣ ጋብቻ ሳይፈጸም እንደ ባል ወይም እንደ ሚስት አብሮ የሚኖር ሰውን፣ ልጅን፣ ወላጅን፣ እህትና ወንድምን፣ የትዳር ጓደኛ ልጅን እና ጋብቻ ሳይፈጸም እንደ ባል ወይም እንደ ሚስት አብሮ የሚኖር ሰው ልጅን ያጠቃልላል፡፡
8. "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የፍትህ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤[37]
9. "ኮሚሽን" ማለት የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ነው፤

---

[37] የኢፌዴሪ ፍትህ ሚኒስቴር  በአዋጅ ቁጥር 943/2008 መሰረት በፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ በመተካቱ ፍትህ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስቴር የሚለው እንደቅደም ተከተሉ የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ወይም ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ተብሎ ይነበባል፡፡ በአዋጁ ውስጥም በተመሳሳይ ሚኒስቴሩ የሚለው የፌዴራል ጠቅላይ አቃቤ ህጉ በሚል የሚነበብ ይሆናል፡፡

10.“ሰው“ ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

11.ማንኛውም በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴት ፆታን ያካትታል።

3. **የተፈጻሚነት ወሰን**

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የሚደረግ ጥበቃ ተፈጻሚ የሚሆነው በሕግ የተደነገገው የፅኑ እስራት መነሻ ከግምት ሳይገባ አስር ዓመትና ከዚያ በላይ በሆነ ጽኑ እስራት ወይም በሞት ሊያስቀጣ በሚችል የወንጀል ድርጊት ተጠርጣሪ ላይ የሚሰጥ ምስክርነትን ወይም ጥቆማን ወይም የሚካሄድ ምርመራን በሚመለከት ሆኖ፡-

   ሀ/ የወንጀል ድርጊቱ ያለምስክሩ ወይም ያለጠቋሚው ምስክርነት ወይም ጥቆማ በሌላ ማናቸውም መንገድ ሊረጋገጥ ወይም ሊደረስበት የማይችል ሲሆን፤ እና

   ለ/ በምስክሩ፣ በጠቋሚው ወይም በምስክሩ ወይም በጠቋሚው ቤተሰብ ህይወት፣ አካላዊ ደህንነት፣ ነጻነት ወይም ንብረት ላይ ከባድ አደጋ ይደርሳል ተብሎ ሲታመን፤

   ነው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገው ቢኖርም ሚኒስቴሩ እና ኮሚሽኑ የጥበቃ ተጠቃሚ ላልሆኑ ምስክሮችና ጠቋሚዎችም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ /1/ /ቸ/፣ /ኀ/፣ /ኘ/፣ /አ/ እና /ዘ/ የተደነገጉትን የጥበቃ እርምጃዎች ሥራ ላይ ሊያውሉ ይችላሉ፡፡

## ክፍል ሁለት

## የጥበቃ እርምጃዎች

4. **የጥበቃ እርምጃ ዓይነቶች**

1. የሚከተሉት የጥበቃ እርምጃዎች እንደሁኔታው በተናጠል ወይም በጣምራ ለጥበቃ ተጠቃሚ ተፈጻሚ ሊደረጉ ይችላሉ፡-

   ሀ/ የአካልና ንብረት ደህንነት ጥበቃ፤

   ለ/ የመኖሪያ ስፍራ መቀየርን ጨምሮ ደህንነቱ የተጠበቀ የመኖሪያ ቦታ መስጠት፤

   ሐ/ ማንነትንና ባለንብረትነትን መደበቅ፤

   መ/ ማንነትን መቀየር፤

   ሠ/ ለራስ መጠበቂያ የነፍስ ወከፍ መሳሪያ መስጠት፤

   ረ/ መረጃ በተሰጠበት የወንጀል ድርጊት ያለመከሰስ፤

ሰ/ መረጃ በሚሰጥበት የወንጀል ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊትም ሆነ በኋላ ተከሳሽ በጥበቃ ተጠቃሚው መኖሪያ ወይም የሥራ ቦታ ወይም ትምህርት ቤት አካባቢ እንዳይደርስ ማገድ፤

ሸ/ የፍርድ ሂደት ተጀምሮ ምስክርነት እስከሚሰጥ ድረስ የምስክር ማንነት እንዳይገለጽ ማድረግ፤

ቀ/ ምስክርነት በዝግ ችሎት እንዲሰጥ ማድረግ፤

በ/ ምስክርነት በአካል ሳይታይ ከመጋረጃ በስተጀርባ ሆኖ ወይም ማንነትን በመሸፈን እንዲሰጥ ማድረግ፤

ተ/ ማስረጃ በኤሌክትሮኒክስ ወይም በሌላ የተለየ ዘዴ እንዲቀርብ ማድረግ፤

ቸ/ በሚስጥር መያዝ ያለበት ካልሆነ በስተቀር ለጠቋሚ ጥቆማ ባቀረበበት ጉዳይ ላይ ወቅታዊ መረጃና ምክር መስጠት፤

ኀ/ እንዲመሰክር ለተጠራ ምስክር የጉዞና የውሎ አበል መስጠት፤

ነ/ የጥበቃ እርምጃው የመኖሪያ ስፍራን ለውጥ ካስከተለ የጓዝ ማንሻ ወጪን መሸፈን፤

ኘ/ በበቀል የተወሰደ አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲታገድ ወይም እንዲሻር ማድረግ ወይም ተመጣጣኝ የሆነ የማካካሻ እርምጃ መውሰድ፤

አ/ በበቀል እርምጃ ለደረሰ ጉዳት የህክምና አገልግሎት በመንግሥት ሆስፒታል በነጻ መስጠት፤

ከ/ በጥበቃ እርምጃው ምክንያት ለደረሰ ገቢ ማጣት ወይም በበቀል እርምጃ ለደረሰ የመሥራት ችሎታ ማጣት የመሠረታዊ ፍላጎት ማሟያ ወጪን መሸፈን፤

ኸ/ በጥበቃ ሥር እያለ ለደረሰ ሞት የቀብር ማስፈጸሚያ ወጪ መሸፈንና ለቤተሰብ የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ፤

ወ/ የጥበቃ ተጠቃሚው የሥራና የትምህርት ዕድል እንዲያገኝ መርዳት፤

ዘ/ ለምስክሩ ወይም ለጠቋሚው የምክር አገልግሎት መስጠት ወይም እንዲያገኝ ማድረግ።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌዎች ቢኖሩም ለጥበቃ ሲባል ለጥበቃ ተጠቃሚው የሌለው የሙያ ማረጋገጫ እንዳለው ተደርጎ አይሰጠውም።

5. **<u>የጥበቃ እርምጃን ዓይነት ስለመወሰን</u>**

ለጥበቃ ተጠቃሚ የሚሰጠውን የጥበቃ እርምጃ ዓይነት ለመወሰን የሚከተሉት ከግምት ውስጥ መግባት ይኖርባቸዋል፡-

1. የጥበቃ ተጠቃሚው ሊደርስበት ይችላል ተብሎ የሚገመተው የአደጋ ሁኔታ፤
2. የጥበቃ ተጠቃሚው የወንጀል ሪከርድ ያለበት ከሆነ ሊሰጥ የታሰበው ጥበቃ ሕዝብን ለአደጋ የሚያጋልጥ መሆኑ ወይም ያለመሆኑ፤
3. ሊሰጥ የታሰበው ጥበቃ በሌላ ሰው መብትና ህጋዊ ጥቅም ላይ የሚያስከትለው ጉዳት፤
4. የጥበቃ ተጠቃሚው የጤናና የኑሮ ሁኔታ፤
5. የጥበቃ ተጠቃሚው ሊሰጥ ከታሰበው ጋር ራሱን ለማላመድ ያለው ብቃት፤
6. ለጥበቃው የሚወጣው ወጪ መጠን፤
7. የጥበቃ ተጠቃሚው ከሌሎች የጥበቃ ተጠቃሚዎች ጋር ያለው ግንኙነት፤
8. በጥበቃ ተጠቃሚው ላይ በሕግ መሠረት የተጣሉ ግዴታዎችና ገደቦች፤
9. በሚኒስቴሩ የሚወጡ አግባብነት ያላቸው ሌሎች መመዘኛዎች።

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>የጥበቃ ማመልከቻና ስምምነት</u>

6. **<u>የጥበቃ ማመልከቻ</u>**

1. ለጥበቃ ተጠቃሚነት የሚቀርብ ማመልከቻ፡-

   ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 መሠረት ጥበቃ ሊደረግለት በሚገባው ሰው፤ ወይም

   ለ/ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባው ሰው መጠየቅ በማይችልበት ጊዜ እርሱን በመወከል በመርማሪው፣ በዐቃቤ ህግ ወይም በማንኛውም ጉዳዩ ያገባኛል በሚል ሰው፤ ሊቀርብ ይችላል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ለጥበቃ ተጠቃሚነት የሚቀርብ ማመልከቻ፡-

   ሀ/ ጥበቃ የሚደረግለትን ሰው ማንነትና አድራሻ የሚገልጹ መረጃዎችን፤

   ለ/ ለጥበቃው ምክንያት ከሆነው ጥቆማ፣ ምስክርነት ወይም ምርመራ ጋር የተያያዘውን የወንጀል ድርጊት፤

   ሐ/ ጥበቃ በሚደረግለት ሰው ላይ የተጋረጠው አደጋ፤

መ/ የጥበቃ ተጠቃሚ ለመሆን ከማመልከቱ በፊት የቀረበበት የወንጀል ወይም የፍትሐብሔር ክስ፣ ዕዳ ወይም ከሙብት የመሻር ፍርድ ካለ ይህንኑ፤ እና

ሠ/ ሌሎች በሚኒስቴሩ የሚጠየቁ አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን፤

መያዝ አለበት፡፡

7. **<u>በጥበቃ ማመልከቻ ላይ ስለሚሰጥ ውሳኔ</u>**

   1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 መሠረት የቀረበው ማመልከቻ በመርማሪው ወይም በዐቃቤ ህግ ባልሆነ ጊዜ ሚኒስቴሩ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት የመርማሪውን ወይም የዐቃቤ ህጉን አስተያየት መጠየቅ አለበት፡፡
   2. ሚኒስቴሩ ለጥበቃ ተጠቃሚነት በቀረበ ማመልከቻ ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 ድንጋጌዎች መሠረት በ30 ቀን ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡
   3. ሚኒስቴሩ በቀረበለት የጥበቃ ተጠቃሚነት ጥያቄ ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ በአመልካቹ ህይወት፣ አካላዊ ደህንነት ወይም ንብረት ላይ ከባድ አደጋ ይደርሳል ብሎ ካመነ የአስቸኳይ ጊዜ የጥበቃ እርምጃ ሊወሰድ ይችላል።
   4. ሚኒስቴሩ የቀረበለትን የጥበቃ ተጠቃሚነት ጥያቄ ያልተቀበለው እንደሆነ ያልተቀበለበትን ምክንያት ለጠያቂው በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

8. **<u>የጥበቃ ስምምነት</u>**

   1. ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ /1/ ከፊደል ተራ /ሀ/ እስከ /መ/ ከተመለከቱት የጥበቃ ዓይነቶች አንዱን ወይም ከአንድ በላይ ለመስጠት ከወሰነ ከጥበቃው ተጠቃሚ ጋር የጥበቃ ስምምነት መፈራረም አለበት፡፡
   2. የጥበቃ ተጠቃሚው አካለ መጠን ያልደረሰ ወይም በፍርድ የተከለከለ ሰው ከሆነ የጥበቃ ስምምነቱ ከወላጆቹ ወይም ከአሳዳሪው ጋር ይፈረማል፡፡
   3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት የተደረገ የጥበቃ ስምምነት የጥበቃ ተጠቃሚው አካለ መጠን ከደረሰ ወይም የህግ ችሎታውን መልሶ ካገኘ በኋላ የሚቀጥል ከሆነ ስምምነቱን የጥበቃ ተጠቃሚው ራሱ መፈረም አለበት፡፡

9. **<u>ልዩ የጥበቃ ስምምነት</u>**

   1. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ /2/ ቢኖርም የጥበቃ ተጠቃሚ የሆነ አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ፡-

      ሀ/ መረጃ ወይም ምስክርነት የሚሰጠው በወላጁ ወይም በአሳዳሪው ላይ ሲሆን፤

      ለ/ ወላጅ ወይም አሳዳሪ የሌለው ሲሆን፤

ሐ/ አስፈላጊው ጥረት ተደርጎ ወላጁን ወይም አሳዳሪውን ማግኘት ያልተቻለ እንደሆነ፤ ወይም

መ/ ወላጁ ወይም አሳዳሪው በቂ ባልሆነ ምክንያት ፈቃዱን ሳይሰጥ ሲቀር ወይም በማናቸውም ምክንያት ፈቃዱን መስጠት ሳይችል ሲቀር፤

ሚኒስቴሩ ከልጁ ጋር ልዩ የጥበቃ ስምምነት ሊፈራረም ይችላል።

2. አካለ መጠን ካልደረሰ ልጅ ጋር የተደረገ ልዩ የጥበቃ ስምምነት ከተፈረመበት ዕለት ጀምሮ ባሉት አስር ቀናት ውስጥ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀርቦ መጽደቅ አለበት።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚቀርብ ጥያቄ፡-

ሀ/ ጥበቃው አስፈላጊ የሆነበትን ምክንያት፤ እና

ለ/ አካለ መጠን ካላደረሰ ልጅ ጋር የተደረገውን ልዩ የጥበቃ ስምምነት፤

መያዝ አለበት፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት ጥያቄ የቀረበለት ፍርድ ቤት አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ጥቅምና ደህንነት ይበልጥ ሊረጋገጥ የሚችልበትን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት የጥበቃ ስምምነቱን መሻር፣ ማጽደቅ ወይም ማሻሻል ይችላል፡፡

5. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /4/ መሠረት ልዩ የጥበቃ ስምምነቱን የሻረው እንደሆነ ሚኒስቴሩ አካለመጠን ያላደረሰውን ልጅ ከጥበቃው ማሰናበት አለበት፡፡

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /4/ መሠረት የጸደቀ ወይም የተሻሻለ ልዩ የጥበቃ ስምምነት አስገዳጅ ስምምነት ይሆናል፡፡

10.<u>**የጥበቃ ስምምነት ሥራ ላይ ስለሚውልበት ጊዜ**</u>

የጥበቃ ስምምነት ሥራ ላይ የሚውለው በጥበቃ ተጠቃሚውና በሚኒስቴሩ መካከል ከተፈረመበት ዕለት ጀምሮ ይሆናል።

11.<u>**የጥበቃ ስምምነት ተዋዋይ ወገኖች ግዴታዎች**</u>

1. የጥበቃ ተጠቃሚው የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

ሀ/ ለጥበቃ ስምምነቱ ምክንያት ለሆነው ጉዳይ ምርመራ ወይም ክስ እውነተኛ፣ ግልጽና የተሟላ መረጃ ወይም ማስረጃ የመስጠት ወይም በፍርድ ቤት ምስክርነት የመስጠት፤

ለ/ ሚኒስቴሩ አዘጋጅቶ የሚያቀርበውን የግላዊ መረጃ መጠይቅ በትክክል የመሙላት፤

ሐ/ የጥበቃ እርምጃውን ከሚያደናቅፍ ተግባር የመቆጠብ፤

መ/ ጥበቃውን አስመልክቶ የተሰጡትን ትዕዛዞችና መመሪያዎች የመቀበልና ተግባራዊ የማድረግ፤

ሠ/ በሚኒስቴሩ ሲጠየቅ የህክምና ምርመራ በማድረግ ውጤቱን የማሳወቅ፤

ረ/ በሚኒስቴሩ ሲጠየቅ ከአደንዥ ዕፅ ወይም አልኮል ሱስ ጋር በተያያዘ ምክር የመቀበል ወይም ህክምና የማድረግና ውጤቱን የማሳወቅ፤

ሰ/ በጥበቃ ስር ባለበት ጊዜ የቀረበበትን የወንጀል ክስ ወይም ከሙብት የመሻር የፍርድ ውሳኔ ካለ ለሚኒስቴሩ የማሳወቅ፤

ሸ/ በጥበቃ እርምጃው ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር አዲስ ሁኔታ ሲከሰት ወዲያውኑ ለሚኒስቴሩ የማሳወቅ፤

ቀ/ በዓይነ ቁራኛ ለመጠበቅ የመስማማት፤

በ/ የመሠረታዊ ፍላጎት ማሟያ ወጪ ተጠቃሚ ከሆነ በኢኮኖሚ ራሱን ለመቻል ጥረት ማድረግ፤ እና

ተ/ ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን ሌሎች ግዴታዎች የመፈጸም።

2. ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

ሀ/ የጥበቃ ተጠቃሚውን መብትና ነጻነት አስፈላጊ ከሆነው መጠን በላይ ያለመገደብ፤

ለ/ የጥበቃ እርምጃውን ሊያደናቅፉ ይችላሉ ተብለው የጥበቃ ተጠቃሚው ሊቆጠብባቸው የሚገቡ ተግባሮችን አስቀድሞ የማሳወቅ፤

ሐ/ ለጥበቃ ተጠቃሚው የሚሰጠውን የመሠረታዊ ፍላጎት ማሟያ ወጪ መጠንና የቆይታ ጊዜ የማሳወቅ፤

መ/ የጥበቃ ተጠቃሚ በጥበቃ ሥር ባለበት ጊዜ አስፈላጊውን የምክር አገልግሎት እንዲያገኝ የማድረግ፤ እና

ሠ/ በጥበቃ ስምምነቱ የተመለከቱ የጥበቃ እርምጃዎችን ውጤታማነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን ሁሉ የመውሰድ።

12.<u>የጥበቃ ስምምነት ስለሚቋረጥበት ሁኔታ</u>

1. የጥበቃ ስምምነት በሚከተሉት ምክንያቶች ይቋረጣል፡-

ሀ/ በስምምነቱ የተመለከተው ስምምነቱ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ ሲያበቃ፤

ለ/ የጥበቃ ተጠቃሚው ሲሞት፤

ሐ/ የጥበቃ ተጠቃሚው የስምምነቱ ተጠቃሚ መሆንን በፈቃዱ ሲተው፤

መ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት የተፈጸመ ከሆነ ስምምነቱ እንዲቋረጥ በወላጅ ወይም በአሳዳሪ በጽሁፍ ጥያቄ ሲቀርብ፤

ሠ/ አካለ መጠን ያልደረሰ ወይም በፍርድ የተከለከለ ሰው የህግ ችሎታ ማጣቱ እንዳበቃ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ /3/ መሠረት የጥበቃ ስምምነቱ እንዲቀጥል ፈቃዱን ለመስጠት እምቢተኛ ሆኖ ሲገኝ፤

ረ/ በጥበቃ ስምምነቱ የተወሰነው ጊዜ ሳያበቃ ጥበቃውን አስፈላጊ ያደረገው ሁኔታ ሲወገድ፤

ሰ/ የጥበቃ ተጠቃሚው ባሕሪ የራሱን ወይም የሌሎች የጥበቃ ተጠቃሚዎችን የጥበቃ እርምጃ ውጤታማ እንዳይሆን የሚያደርግ ሆኖ ሲገኝ፤ ወይም

ሸ/ የጥበቃ ተጠቃሚው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገጉትን፤ ግዴታዎች ሲጥስ።

2. ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ /ረ/፣ /ሰ/ ወይም /ሸ/ መሠረት የጥበቃ ስምምነቱን ከማቋረጡ በፊት መቼና ለምን እንደሚቋረጥ በመግለጽ የጥበቃ ተጠቃሚው አስተያየቱን በጽሑፍ እንዲያቀርብ እድል መስጠት አለበት፡፡

3. ሚኒስቴሩ የጥበቃ ተጠቃሚው የሰጠው አስተያየት ተቀባይነት ያለው ሆኖ ያገኘው እንደሆነ የጥበቃ ስምምነቱ እንዲቀጥል ይወሰናል፡፡

4. የጥበቃ ተጠቃሚው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት እንዲያውቀው በተደረገ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መልስ ያልሰጠ እንደሆነ ወይም የሰጠው አስተያየት ተቀባይነት የሌለው ከሆነ ወይም በአድራሻው ተፈልጎ ያልተገኘ እንደሆነ ሚኒስቴሩ የጥበቃ ስምምነቱ እንዲቋረጥ ይወሰናል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ መሠረት የጥበቃ ስምምነት ሲቋረጥ ሚኒስቴሩ ለሚመለከታቸው አካላት ማሳወቅ አለበት፡፡

13.**የጥበቃ ስምምነትን ስለማራዘም**

1. የጥበቃ ተጠቃሚ የጥበቃ ስምምነቱ ለተጨማሪ ጊዜ እንዲራዘምለት ለሚኒስቴሩ ሊያመለከት ይችላል፡፡
2. ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ማመልከቻ ሲቀርብለት ለጥበቃው ምክንያት የሆነው የአደጋ ስጋት ያልተወገደ መሆኑን ሲያምንበት ስምምነቱን ለተጨማሪ ጊዜ ያራዝማል።
3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 መሠረት የተደረገን ልዩ የጥበቃ ስምምነት ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በራሱ ተነሳሽነት እንዲራዘም ሊወስን ይችላል።

**ክፍል አራት**

**ማንነትንና ባለንብረትነትን የመደበቅ እና ማንነትን የመቀየር የጥበቃ እርምጃዎች አፈጻጸም**

14.**ማንነትንና ባለንብረትነትን የመደበቅ እርምጃ**

1. የጥበቃ ተጠቃሚ ማንነቱንና ባለንብረትነትን ለመደበቅ የተሰጠውን ስነድ ተጠቅሞ በሶስተኛ ወገኖች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል ህጋዊ ግዴታ ውስጥ ለመግባት የሚችለው የሚኒስቴሩን ፈቃድ ሲያገኝ ነው፡፡
2. የጥበቃ ተጠቃሚው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ለሚኒስቴሩ ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ካላገኘ ሚኒስቴሩን በማሳወቅ በቀድሞ ስሙ ህጋዊ ግዴታ የሚገባለትን እንደራሴ ሊወከል ይችላል።

15.**ማንነትን የመቀየር እርምጃ**

1. ሚኒስቴሩ ማንነትን የመቀየር የጥበቃ እርምጃ ሥራ ላይ እንዲውል የሚወስነው ሌሎች የጥበቃ እርምጃ ዓይነቶች የጥበቃ ተጠቃሚን ደህንነት ለመጠበቅ የማያስችሉ መሆናቸውን ሲያረጋግጥ ብቻ ነው።
2. የጥበቃ ተጠቃሚው ማንነትን የመቀየር የጥበቃ እርምጃ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ለሶስተኛ ወገኖች የገባቸውን ህጋዊ ግዴታዎች መፈጸም አለበት።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ የተደነገገው ቢኖርም ሚኒስቴሩ የጥበቃ ተጠቃሚው ህጋዊ ግዴታውን ለመወጣት የማይችል መሆኑን ካረጋገጠ ራሱ ህጋዊ ግዴታውን በመፈጸም ማንነትን የመቀየር የጥበቃ እርምጃው በሥራ ላይ እንዲውል ሊፈቅድ ይችላል፡፡

16.<u>ከማንነት መቀየር በኋላ ስለሚቀጥሉ መብቶችና ግዴታዎች</u>

1. የጥበቃ ተጠቃሚው ከማንነት መቀየር በኋላ በሚቀጥሉ መብቶች ለመጠቀምና ግዴታዎችን ለመወጣት እንደራሴ ሊወከል ይችላል፡፡
2. የጥበቃ ተጠቃሚው ማንነቱ ከመቀየሩ በፊት ያላወቀው ህጋዊ ግዴታ የነበረበት መሆኑን ሚኒስቴሩ ከተረዳ የጥበቃ ተጠቃሚው ግዴታውን እንዲፈጽም መጠየቅ አለበት፡፡
3. የጥበቃ ተጠቃሚው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት ግዴታውን መወጣት ያልቻለ ወይም ያልፈለገ እንደሆነ ሚኒስቴሩ እንደሁኔታው የጥበቃ ተጠቃሚውን ግዴታ ይፈጽማል ወይም የጥበቃ ስምምነቱ እንዲቋረጥ ያደርጋል፡፡

17.<u>አዲስ የማንነት ሰነዶችን ስለመስጠት</u>

1. ሚኒስቴሩ የማንነት መቀየርን የጥበቃ እርምጃ ሥራ ላይ እንዲውል ከወሰነ የጥበቃ ተጠቃሚውን የቀድሞና አዲስ ግላዊ መረጃዎች በተለይ ለዚሁ ተግባር በተዘጋጁ መዛግብት አስፍሮ ይይዛል፡፡ የመዝገብ አጠባበቁም ባልተፈቀደላቸው ሰዎች ከቀድሞው መረጃዎች አዲሱን ወይም ከአዲሱ መረጃዎች የቀድሞውን የጥበቃ ተጠቃሚውን ማንነት ለመረዳት የማያስችል መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡
2. የሰነድ ማስረጃ የሚሰጡ አካላት ሚኒስቴሩ የሚሰጣቸውን መረጃ መሠረት በማድረግ በአዲሱ ማንነት አግባብ ያላቸው ሰነዶችን የማዘጋጀትና ለጥበቃ ተጠቃሚው የመስጠት ግዴታ አለባቸው።

18.<u>የጥበቃ ተጠቃሚው የግንኙነት መስመር</u>

ማንኛውም ማንነቱ የተቀየረ ወይም ማንነቱና የባለንብረትነት መረጃው የተደበቀ የጥበቃ ተጠቃሚን መብትና ግዴታ የሚመለከት ግንኙነት በጥበቃ ተጠቃሚው ፈቃድ በሚኒስቴሩ አማካይነት ይፈጸማል፡፡

19.<u>ቅድመ ጥበቃ የተፈጸመ ወንጀል</u>

1. የጥበቃ ተጠቃሚ ከመሆኑ በፊት ወንጀል የፈጸመን የጥበቃ ተጠቃሚ ክርክሩን እንዲከታተል አግባብ ያለው ፍርድ ቤት ያዘዘ እንደሆነ ሚኒስቴሩ የጥበቃ ተጠቃሚውን ፍርድ ቤት ማቅረብ አለበት።
2. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የቀረበን የጥበቃ ተጠቃሚ የጥበቃውን ዓላማ በማይጻረር ሁኔታ በክርክሩ እንዲሳተፍ ያደርጋል።

20.**ቅድመ ጥበቃ የተፈጸመ ወንጀል ምስክርነት**

የጥበቃ ስምምነት ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በተፈጸመ የወንጀል ድርጊት እንዲመሰክር የተፈለገ የጥበቃ ተጠቃሚ የፍርድ ቤቱ መጥሪያ የሚደርሰውና ፍርድ ቤት ቀርቦ የሚመሰክረው በሚኒስቴሩ አማካይነት ይሆናል።

21.**በቀድሞ ማንነት የፍትሐ ብሔር ክርክር ስለማድረግ**

1. የጥበቃ ተጠቃሚ በቀድሞ ማንነቱ የፍትሐብሔር ክርክር ማድረጉ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሚኒስቴሩ በሚሰጠው ፈቃድና መመሪያ መሠረት በክርክሩ ሊሳተፍ ይችላል፡፡
2. የጥበቃ ተጠቃሚው በቀድሞው ማንነቱ በፍትሐብሔር ክርክሩ እንዲሳተፍ ሚኒስቴሩ ያልፈቀደ እንደሆነ ክርክሩን በወኪሉ አማካይነት ሊያካሂድ ይችላል፡፡

22.**የቀድሞ ማንነትን ስለመመለስ**

1. ሚኒስቴሩ፡-
   ሀ/ በጥበቃ ስምምነት የተመለከተው የጥበቃ ጊዜ ካበቃ ወይም የጥበቃ ጊዜው ከማብቃቱ በፊት ማንነትን ከመቀየር በመለስ ባሉ ሌሎች የጥበቃ እርምጃዎች የጥበቃ ተጠቃሚውን ደህንነት ማረጋገጥ ይቻላል ብሎ ከወሰነ፤ እና
   ለ/ የማንነት መቀየር እንደ ጋብቻና አባትነት ወይም እናትነት በመሳሰሉት በሶስተኛ ወገኖች አቋም ላይ ከፍ ያለ ተጽዕኖ የማያሳድር መሆኑን ካረጋገጠ፤ የጥበቃ ተጠቃሚው የቀድሞው ማንነቱ እንዲመለስ ያደርጋል።
2. ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የቀድሞ ማንነት እንዲመለስ ከማድረጉ በፊት የጥበቃ ተጠቃሚው እንዲያውቀው በማድረግ አስተያየቱን እንዲሰጥበት ዕድል ይሰጠዋል።
3. የጥበቃ ተጠቃሚ የቀድሞው ማንነቱ ሲመለስ የአዲሱን ማንነት መታወቂያና ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው ሰነዶች ለሚኒስቴሩ መመለስ አለበት፡፡
4. የጥበቃ ተጠቃሚው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ መሠረት የአዲሱን የማንነት መታወቂያና ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸውን ሰነዶች እንደመለሰ ሚኒስቴሩ የቀድሞ ማንነት መታወቂያና ሌሎች ተዛማጅ ሰነዶች በሚመለከታቸው አካላት እንዲሰጡ ያደርጋል፡፡

5. የማንነት መታወቂያና ሊሎች ተዛማጅ ሰነዶች የሚሰጡ አካላት ሚኒስቴሩ የሚሰጣቸውን መረጃ መሠረት በማድረግ የቀድሞውን ማንነት የሚመለከቱ ተፈላጊ ሰነዶችን ለጥበቃ ተጠቃሚው የመስጠት ግዴታ አለባቸው።
6. የጥበቃ ተጠቃሚው በአዲሱ ማንነቱ ያደረጋቸው ሕጋዊ ግንኙነቶች ሕጋዊ ውጤቶች መጠበቃቸውን ሚኒስቴሩ ያረጋግጣል።

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 23.የፍትሕ አካላት ኃላፊነት

1. ጉዳዩ የሚመለከተው ፍርድ ቤት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ /1/ ከፊደል ተራ /ሰ/ እስከ /ተ/ የተደነገጉት የጥበቃ እርምጃዎች እንደ አግባቡ መወሰዳቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት ይኖርበታል።
2. ጉዳዩ የሚመለከተው ዐቃቤ ሕግ፡-

   ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ /1/ ለ/የተመለከተውን የዐቃቤ ሕግ ተግባር የማከናወን ሃላፊነት፣ እና

   ለ/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀጽ /1/ ከፊደል ተራ /ሰ/ እስከ /ተ/ እንዲሁም በፊደል ተራ /ዘ/ የተደነገጉት የጥበቃ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል፡፡
3. የሚመለከተው መርማሪ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ /1//ለ/ የተመለከተውን የመርማሪ ተግባር የማከናወን ኃላፊነት ይኖርበታል።

### 24.የሚስጥር አጠባበቅ

1. ከጥበቃ ተጠቃሚ ጋር ተያያዥነት ያላቸው መዛግብትና መረጃዎች በጥብቅ ሚስጥርነት ተፈርጀው መጠበቅ አለባቸው።
2. በሚኒስቴሩ የበላይ አመራር ካልተፈቀደ በስተቀር ሥራው ከሚመለከታቸው ሠራተኞች ውጭ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከቱትን መዛግብት መመልከት አይችልም።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገው ቢኖርም የጥበቃ ተጠቃሚ የሆነ ወይም የነበረ ሰው፣

   ሀ/ መረጃው እንዲገለጽ የተስማማ እንደሆነ፣

ለ/ መረጃውን አስቀድሞ የገለፀው እንደሆነ፣

ሐ/ የጥበቃ ተጠቃሚው አስር ዓመትና ከዚያ በላይ በሆነ ጽኑ እሥራት ወይም በሞት ሊያስቀጣ የሚችል የወንጀል ድርጊት ፈጽሟል ተብሎ የተጠረጠረ እንደሆነ የተጠረጠረበትን የወንጀል ድርጊት ለማጣራት፣ ወይም

መ/ በወንጀል ክስ ዳኝነት የሌላ ተጠርጣሪን ንፁህነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ፣

ሚኒስቴሩ መረጃውን ሊገልጽ ይችላል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ ተራ ፊደል /ሐ/ ወይም /መ/ መሠረት የጥበቃ ተጠቃሚ የሆነ ወይም የነበረ ሰው መረጃ ለመግለጽ፡-

ሀ/ የመረጃው መገለፅ የጥበቃ ተጠቃሚ በሆነው ወይም በነበረው ሰው ላይ ሊያስከትል የሚችለው አደጋ፣ እና

ለ/ የመረጃው መገለፅ በሌላ መንገድ ሊተካ አለመቻሉ፣

መገናዘብ አለበት።.

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ መሠረት መረጃው የተገለጸለት ሰው መረጃውን ለተገለጸለት ዓላማ ብቻ ማዋል አለበት።

25.<u>ቅሬታ ስለማቅረብ</u>

1. በሚመለከተው የሚኒስቴሩ ኃላፊ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ለጥበቃ ተጠቃሚነት ያመለከተ ሰው ወይም የጥበቃ ተጠቃሚ የሆነ ወይም የነበረ ሰው ቅሬታውን ውሳኔው በደረሰው 15 ቀናት ውስጥ ለሚኒስትሩ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ሚኒስትሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ቅሬታ ሲቀርብለት በአስር ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡ የሚኒስትሩ ውሳኔ ለፍርድ ቤት አቤቱታ የማይቀርብበት የመጨረሻ ውሳኔ ይሆናል፡፡

26.<u>የምስክርነት ተአማኒነት</u>

የምስክር በዚህ አዋጅ መሠረት የጥበቃ ተጠቃሚ መሆን የሚሰጠውን ምስክርነት ተአማኒነት ደረጃ ዝቅ ለማድረግ ምክንያት ሆኖ ሊቀርብ አይችልም።

27.<u>ከሌሎች አካላት ጋር ስለሚደረግ ስምምነት</u>

1. ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጥ ጥበቃን ሥራ ላይ ለማዋል ከሚመለከታቸው የፌዴራል ወይም የክልል አካላት ጋር ስምምነት ሊፈጽም ይችላል፡፡

2. ለምስክሮችና ጠቋሚዎች ተገቢውን ጥበቃ ለመስጠት እንዲቻል መንግሥት የሁለትዮሽ ወይም የባለብዙ ወገን ዓለም ዓቀፍ ስምምነት ሊፈራረም ይችላል።

28.**የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚኒስቴሩ ትብብር ሲጠየቅ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

29.**ቅጣት**

1. ማንኛውም የጥበቃ ተጠቃሚ፡-

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ /1/ /ሀ/ የተደነገገውን ከተላለፈ ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል። ሆኖም በወንጀል ጉዳይ ተከሳሽ በመስካሪው ድርጊት ምክንያት የጥፋተኛነት ውሳኔ ተላልፎበት እንደሆነ ወይም ከአሥር ዓመት ፅኑ እሥራት በላይ ተፈርዶበት እንደሆነ የተመሰከረበት ሰው በስህተት በተወሰነበት ቅጣት ልክ ሀሰተኛ መስካሪው ሊወሰንበት ይችላል፤

ለ/ በቂ ምክንያት ሳይኖረው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ /3/ በተደነገገው መሠረት የአዲስ ማንነት መታወቂያና ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸውን ሰነዶች ካልመለሰ እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራት ወይም እስከ አስር ሺ ብር በሚደርስ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፤

ሐ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 መሠረት ሚኒስቴሩ የሚያቀርብለትን የትብብር ጥያቄ ለመፈጸም እምቢተኛ የሆነ ማንኛውም ሰው ከስድስት ወር በማያንስ ቀላል እስራት ወይም ከብር አስር ሺ በማይበልጥ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፤

መ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ /1//ሐ/ የተደነገገውን በመተላለፍ ጥበቃውን የሚያደናቅፍ ተግባር የፈጸመ ማንኛውም የጥበቃ ተጠቃሚ ከአንድ ዓመት በማያንስ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ወይም ከብር 50000 (ሀምሳ ሺ) በማያንስ ከብር 500,000 (አምስት መቶ ሺ ብር) በማይበልጥ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

2. የዚህን አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች የተላለፈ ማንኛውም ሰው አግባብ ባላቸው የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች መሠረትበይቀጣል።

30.<u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

ይህ አዋጅ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተደረገ የጥበቃ ስምምነት ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር እስካልተቃረነ ድረስ በዚህ አዋጅ መሠረት እንደተደረገ ይቆጠራል።

31.<u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።
2. ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የወጡ ደንቦችን ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

32.<u>ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

33.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ የካቲት 4 ቀን 2003 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## ደንብ ቁጥር 371/2008

## ስለወንጀል ምስክሮች የውሎ አበልና የጉዞ ወጪ አከፋፈል የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና በወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 699/2003 አንቀጽ 31(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የወንጀል ምስክሮች የውሎ አበልና የጉዞ ወጪ አከፋፈል የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 371/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር  በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. "የፍትህ አካል" ማለት በሕግ ወንጀል የመመርመር፣ የወንጀል ክስ የማቅረብ ወይም ክስ በመስማት ፍርድ የመስጠት ሥልጣን ያለው ማንኛውም የፌደራል መንግሥት አካል ነው፤
   2. "የፍትህ አካል የበላይ ኃላፊ" ማለት እንደፍትህ ተቋሙ አግባብነት ዋና ኃላፊ ሲሆን ምክትሎችን ይጨምራል፤
   3. "የክፍያ መጠየቂያ ቅፅ" ማለት የወንጀል ምስክር የውሎ አበል እና የጉዞ ወጪ እንዲከፈለው የሚሞላበት ቅፅ ነው፤
   4. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

3. **የተፈፃሚነት ወሰን**

   ይህ ደንብ የደንብ መተላለፍ ጉዳዮችን ሳይጨምር በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ሥር በሚታይ የወንጀል ጉዳይ ላይ በምርመራ፣ በክስ ወይም በክስ መስማት ሂደት ማስረጃ ወይም ምስክርነት እንዲሰጥ በቀረበ ምስክር ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

## ስለውሎ አበልና የጉዞ ወጭ አከፋፈል

4. **የፍትሕ አካላት ኃላፊነት**
   1. ማንኛውም የፍትህ አካል ለጠራው የወንጀል ምስክር በዚህ ደንብ መሠረት የውሎ አበልና የጉዞ ወጪ ይሸፍናል፤
   2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ይህ ደንብ በሚከተሉት ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፦
      ሀ/ በወንጀል ሕጉ እና በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሠረት በግል አቤቱታ ክስ እንዲቀርብ በተፈቀደባቸው መዝገቦች ተጠርተው ለሚቀርቡ ምስክሮች፤
      ለ/ ፍትሕ አካል ዘንድ ለመመስከር ቀርቦ የምስክርነት ቃሉን ለመስጠት ፈቃደኛ ላልሆነ የወንጀል ምስክር፤
      ሐ/ ከሥራው ጋር በተያያዘ ኃላፊነቱን ወይም የሙያ ግዴታውን በሚወጣ የመንግስት ሠራተኛ፤
      መ/ በሐሰተኛ ምስክርነት የተጠረጠረ የወንጀል ምስክር፤ ወይም
      ሠ/ ለተከሳሽ መከላከያ ምስክር፡፡
5. **ስለ ውሎ አበል አከፋፈል**

   ለወንጀል ምስክር የሚከፈለው የውሎ አበል፦
   1. ምስክሩ በማንኛውም አሠሪ ተቀጥሮ የሚሰራ ሠራተኛ ከሆነ በወር ደመወዙ ላይ ተመሥርቶ በመንግስት ሠራተኞች የውሎ አበል አከፋፈል መመሪያ መሠረት ተሰልቶ ይከፈለዋል፤ ወይም
   2. ምስክሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ተቀጥሮ የሚሰራ ሠራተኛ ካልሆነ በመንግስት ሠራተኞች የውሎ አበል አከፋፈል መመሪያ የተመለከተው መካከለኛው የውሎ አበል መጠን ይከፈለዋል፡፡
6. **ስለ ጉዞ ወጪ አከፋፈል**
   1. ለወንጀል ምስክር የሚከፈለው የጉዞ ወጪ መጠን የሕዝብ ማመላለሻ የአንድ ጉዞ የትራንስፖርት ታሪፍ በሁለት ተባዝቶ የሚገኘው መጠን ይሆናል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ምስክሩ የሕዝብ ማመላለሻ መጠቀም የማይችል ሲሆን እና የፍትህ አካሉ የበላይ ኃላፊ የግል ተሽከርካሪ እንዲጠቀም ከፈቀደ ለነዳጅ ያወጣው ወጪ ይተካለታል፡፡
3. የወንጀል ድርጊቱ ያለምስክሩ ቃል በሌላ በማናቸውም መንገድ ሊረጋገጥ የማይችል ወይም ምስክርነቱ በአስቸኳይ ሊሰጥ የሚገባ ሲሆን እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተመለከተውን የመጓጓዣ መንገዶችን ለመጠቀም አመቺ በማይሆንበት ጊዜ በፍትህ አካሉ የበላይ ኃላፊ ፈቃድ የአየር መጓጓዣ የጉዞ ወጪ ለወንጀል ምስክሩ ይከፈላል፡፡
4. ለወንጀል ምስክር የሚከፈለው የጉዞ ወጪ የሚሰላው ለምስክሩ በተፃፈው መጥሪያ ላይ ከተገለጸው የመኖሪያ ወይም የሥራ አድራሻ አጭር ርቀት ላይ በመመስረት ይሆናል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ምስክሩ እንዲቀርብ በተጠራበት መጥሪያ ላይ የተገለፀው የመኖሪያ ወይም የሥራ አድራሻ ትክክለኛ ባለመሆኑ በጉዞ ወጭ አከፋፈል ላይ ተጽዕኖ የሚያመጣ ከሆነ ይኸው እንዲታረም ለፍትህ አካሉ ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል፡፡
6. ማንኛውም የወንጀል ምስክር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)፣ (2) ወይም (3) መሠረት ያወጣው ወጪ እንዲተካለት በፍትህ አካሉ የተዘጋጀውን የክፍያ መጠየቂያ ቅጽ ሞልቶ ወጪውን ከሚያሳይ ደረሰኝ ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(6) የተደነገገው ቢኖርም የወንጀል ምስክሩ የወጪ ደረሰኝ ማቅረብ ያልቻለበት ምክንያት አሳማኝ ሲሆን በፍትህ አካሉ የበላይ ኃላፊ ውሳኔ በመንግሥት ሠራተኞች የጉዞ ወጪ አከፋፈል ሥርዓት መሠረት እንዲከፈለው ሊፈቀድ ይችላል፤ ሆኖም የወንጀል ምስክሩ በራሱ በሆነ ጥፋት የወጪ ደረሰኝ ማቅረብ ካልቻለ ክፍያው አይፈፀምም፡፡

7. <u>ስለልዩ አዋቂ ምስክር የውሎ አበልና የጉዞ ወጪ አከፋፈል</u>

በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 (2) (ሐ) ከተመለከተው ውጭ ያለ ሌላ የልዩ አዋቂ ምስክር፦

1. ለምስክርነት በቀረበ ጊዜ በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 እና 6 መሠረት የውሎ አበልና የጉዞ ወጪ ይከፈለዋል፤
2. በሚሰጠው የምስክርነት ጉዳይ ምክንያት የተለየ ወጪ ያወጣ እንደሆነ በሚያቀርበው ደረሰኝ መሠረት ወጪው ይተካለታል፡፡

8. **ምስክርነት ሳይሰጥ የውሎ አበል እና የጉዞ ወጪ ስለመክፈል**

የወንጀል ምስክር ፍትሕ አካል ዘንድ ቀርቦ በራሱ ባልሆነ ምክንያት የምስክርነት ቃሉን ሳይሰጥ ቢቀርም የውሎ አበል እና የጉዞ ወጪ ይከፈለዋል፡፡

9. **ስለ ቅድመ ክፍያ**

1. ማንኛውም የወንጀል ምስክር ለምስክርነት በተጠራበት ጊዜ በገንዘብ እጦት ምክንያት ለመቅረብ የማይችል መሆኑ ከታመነ በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 እና 6 የተመለከቱት ክፍያዎች በቅድሚያ እንዲከፈሉት የሚመለከተው የፍትሕ አካል የበላይ ኃላፊ ሊፈቅድ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚፈቀድ የቅድሚያ ክፍያ መጠን ከጠቅላላ ክፍያ ከግማሽ መብለጥ የለበትም፤ ሆኖም እንደነገሩ ሁኔታ በፍትሕ አካሉ የበላይ ኃላፊ ሲፈቀድ ከግማሽ በላይ የሆነ ክፍያ ሊከፈል ይችላል፡፡

10. **ስለ ምስክር ረዳት**

1. በዕድሜ፣ በአካል ጉዳት ወይም በህመም ምክንያት ረዳት የሚያስፈልገውን የወንጀል ምስክር ለመርዳት አብሮ የተገኘ ረዳት ሰው በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 እና 6 የተመለከቱት ክፍያዎች ይፈጸሙለታል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርብ ረዳት ሰው ከአንድ መብለጥ የለበትም፤ ሆኖም የምስክሩ ሁኔታ ተጨማሪ ረዳት የሚጠይቅ መሆኑ በፍትህ አካል የበላይ ሃላፊ ከታመነ ተጨማሪ አንድ ሰው ሊፈቀድ ይችላል፡፡

11. **የክፍያ መጠየቂያ ቅጽን ሞልቶ ስለማቅረብ**

1. ማንኛውም የወንጀል ምስክር እንዲሞላ የሚጠየቀውን የክፍያ መጠየቂያ ቅጽ በእውነትና በትክክል የመሙላት ግዴታ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በቅጽ ላይ የተሞላው መረጃ ትክክለኛ መሆኑን የሚመለከተው የፍትህ አካል የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

12. **ሐሰተኛ የወንጀል ምስክር**

በዚህ ደንብ አንቀጽ 4(2) (መ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የወንጀል ምስክር፦

1. ሐሰተኛ ምስክርነት በመስጠት መጠርጠሩን፣ ወይም

2. ሆነ ብሎ ከፍተኛ አበል ወይም የጉዞ ወጪ ክፍያ ለማግኘት ሲል ሥራውን፣ የመኖሪያ አድራሻውን ወይም መሰል ጉዳዮችን በተመለከተ ሐሰተኛ መረጃ መስጠቱን፣

የፍትህ አካሉ ያረጋገጠ እንደሆነ የውሎ አበልና የጉዞ ወጭ ክፍያ አይፈጸምለትም፤ ተከፍሎትም እንደሆነ እንዲመልስ ይደረጋል፡፡

13. <u>የሌሎች ደንቦችና መመሪያዎች ተፈጻሚነት</u>

በዚህ ደንብ ያልተሸፈኑ የወንጀል ምስክር የውሎ አበልና የጉዞ ወጪዎች አከፋፈልን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ አግባብ ያላቸው የፌደራል ሕጎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

14. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር 27 ቀን 2008 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

# ደንብ ቁጥር 306/2006 ዓ.ም

## የሽብርተኛ ሀብት የሚታገድበት ሥነ-ሥርዓት ለመወሰን ወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 34፣ በፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 37 እና በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ቁጥር 780/2005 አንቀጽ 54(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የሽብርተኛ ሀብት የሚታገድበት ሥነ-ሥርዓት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 306/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. "አዋጅ" ማለት በወንጀል ድርጊት የተገኘ ንብረት ወይም ገንዘብ ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 780/2005 ነው፤
   2. በአዋጁ አንቀጽ 2 ሥር ለተመለከቱት ቃላት የተሰጡ ትርጓሜዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፤
   3. "ማዕከል" በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 171/2002 የተቋቋመው የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል ነው፤
   4. "ኮሚቴ" ማለት በተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔ ቁጥር 1267/1999፣ 1988/2011፣ 1989/2011 ወይም አግባብ ባለው ሌላ የተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔ መሠረት የተቋቋመ ማዕቀብ የሚወስን አካል ነው፤
   5. "ፍርድ ቤት" ማለት የፌደራል ከፍተኛ ወይም ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው፤

6. “ኃላፊነት ያለበት ሰው” ማለት ማዕከሉ በአዋጁ፣ በዚህ ደንብ ወይም በሌላ ሕግ መሠረት ሥልጣንና ተግባሩን በሚያከናውንበት ጊዜ ለዕማከሉ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ ያለበት ሰው ሲሆን የሚከተሉትን ያጠቃልላል፤

ሀ/ የፋይናንስ ተቋማትን፤

ለ/ ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ስራዎችን፤

ሐ/ ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶችንና የሃይማኖት ድርጅቶችን፤

መ/ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣንን፤

ሠ/ የበጎ አድራጎትና ማህበራት ኤጀንሲ፤ እና

ረ/ ሌሎች የማገድ ግዴታ ያለባቸው ወይም በማዕከሉ ሪፖርት እንዲያቀርቡ የተለዩ ሰዎች፡፡

7. “አግባብነት ያለው ባለስልጣን” ማለት ማዕከሉ፣ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት፣ ፖሊስ፣ ዓቃቤ ህግ ወይም የምርመራ ስራን በኃላፊነት የሚሰራ አካል፣ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ወይም የሚመለከተው ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ነው፤

8. “የተሰየመ ሰው” ማለት፡-

ሀ/ በፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 መሠረት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሰየመ ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበት፤

ለ/ በተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔ ቁጥር 1267/1999 ወይም አግባብነት ባለው ማንኛውም የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔ መሰረት ሽብርተኝነትን ለመዋጋት ተለይተው የተቀመጡ የቁጥጥር እርምጃዎች እንዲወሰዱባቸው በተመለከቱት የተወሰኑ ሰዎችና ድርጅቶች ዝርዝር ውስጥ የተካተተ፤ ወይም

ሐ/ በተባበሩት መንግስታት የጸጥታው ም/ቤት ውሳኔ ቁጥር 1373/2001 መሰረት ሥልጣን ባለው የሌላ አገር የመንግስት አካል በአሸባሪነት የተሰየመ፤

ግለሰብ፣ ቡድን ወይም ድርጅት ነው፡፡

9. “የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበት ሰው” ማለት የሽብርተኝነት ድርጊት ፈፅሞ የመጨረሻ ውሳኔ በሰጠው ፍርድ ቤት ጥፋተኛ የተባለ ሰው ነው፤

10. “ሀብት“ ማለት በአዋጁ አንቀጽ 2 እንደተተረጎመው ፈንድ፣ ገንዘብ፣ የኢኮኖሚያዊ ሀብት፣ ንብረት ወይም አገልግሎት ነው፤

11. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

12. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል።

## ክፍል ሁለት

## ስለተሰየሙ ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈባቸው ሰዎች ዝርዝርና ስያሜ ስለማሳወቅ

### 3. የተሰየሙ ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈባቸው ሰዎች ዝርዝር

1. ማዕከሉ ማንኛውንም የተሰየመን ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበትን ሰው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) በተጠቀሰው አግባብ ያለው ዝርዝር ውስጥ እንዲካተት ማድረግ አለበት፡፡
2. ማዕከሉ የተሰየሙ ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈባቸው ሰዎች ዝርዝሮችን እንደየአግባቡ "የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ዝርዝር"፣ "የተባበሩት መንግሥታት ዝርዝር"፣ "የውጭ አገር መንግሥት አካል ዝርዝር" እና "የፍርድ ቤት ዝርዝር" በሚሉ ስያሜዎች ለይቶ ይይዛል፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) መሰረት የተያዘ ዝርዝር የተሰየመን ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበትን ሰው ማንነት ለመለየት የሚያስችሉ መረጃዎችን መያዝ አለበት፡፡ እነዚህም መረጃዎች ሊታወቁ እስከቻሉ ድረስ የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

   ሀ/ የተሰየመውን ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበትን ሰው ስም፣ የቤተዘመድ ስም እና ሌሎች መጠሪያዎችና የማዕረግ ስሞች ካሉ፤

   ለ/ የተወለደበት ቦታና ቀን ወይም ተቋም ከሆነ የምዝገባ ቁጥሩን ጨምሮ የተመዘገበበትን ቦታና ቀን፤

   ሐ/ ፆታ፣ ዜግነትና አድራሻ፤

   መ/ ሙያ፣ ሥራ፣ ወይም የንግድ ሥራ ዓይነት፤

   ሠ/ ስያሜው ወይም የፍርድ ውሳኔው የተላለፈበት ቀን፤

   ረ/ በተሰየሙ ወይም የፍርድ ውሳኔ በተላለፈባቸው ሰዎች ዝርዝር ውስጥ የተካተተበት ቀን፣ እና፤

   ሰ/ የእግድ እርምጃዎችን አፈጻጸም ውጤታማ ለማድረግ አስፈላጊ ናቸው ተብለው የሚታመንባቸው ሌሎች መረጃዎች፡፡

4. **የተሰየሙ ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈባቸው ሰዎች ዝርዝሮችን ስለማሰራጨት**

   1. ማዕከሉ የተሰየመ ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበትን ሰው ዝርዝር እና የዝርዝሩን ማሻሻያዎች ለሁሉም ኃላፊነት ላለባቸው ሰዎችና ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ሳያዘገይ ማሰራጨት አለበት፣ እንደአስፈላጊነቱም ለህዝብ ግልፅ ያደርጋል፡፡
   2. ማዕከሉ ስለተሰየሙና የፍርድ ውሳኔ የተላለፈባቸውን ሰዎች በዚህ ደንብ መሠረት የሚፈለጉ መረጃዎችን ሲጠየቅ ለሚመለከተው ሰው ይሰጣል፡፡
   3. ማዕከሉ የተሰየመ ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበትን ሰው በዚህ ደንብ አንቀፅ 8 (2) መሰረት ሃብቱ እንዲታገድ ካደረገ በኋላ የተሰየሙ ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈባቸው ሰዎችን ዝርዝር ለህዝብ ይፋ ያደርጋል፡፡

5. **መሰየምን ወይም የፍርድ ውሳኔ መተላለፍን ስለማሳወቅ**

   1. ማዕከሉ የተሰየመ ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበት ሰውን ሃብት እንዲታገድ ካደረገ በኋላ ይህ ሰው የኢትዮጵያ ዜጋ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ከሆነ በተሰየሙ ወይም የፍርድ ውሳኔ በተላለፈባቸው ሰዎች ዝርዝር ውስጥ እንዲካተት የተደረገበትን ምክንያት እና ከዝርዝሩ ሊሰረዝ የሚችልበትን ሥነ-ሥርዓት በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡
   2. በመሰየሙ ወይም በፍርድ ውሳኔ በሌላ አኳኋን ካልተገለፀ በስተቀር ማዕከሉ በዚህ ደንብ አንቀፅ 12 መሰረት የታገደ ሀብት ከፊሉን መጠቀም ስለሚቻልበት ሁኔታ እና ስነ-ስርዓት ለተሰየመው ሰው በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

6. **የመሰየም ወይም የፍርድ ውሳኔ ዝርዝርን መሠረዝ ወይም ማሻሻል**

የመሰየም ወይም የፍርድ ውሳኔ እንደነገሩ ሁኔታ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ በኮሚቴው፣ ሥልጣን ባለው የውጭ አገር መንግሥት አካል ወይም በፍርድ ቤት የተሠረዘ ወይም የተሻሻለ እንደሆነ ማዕከሉ ወቅታዊነቱን በጠበቀ ሁኔታ የሚከተሉትን መፈጸም አለበት፡-

   1. የተሰየመውን ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበትን ሰው ስም ከሚመለከተው የተሰየሙ ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈባቸው ሰዎች ዝርዝር ውስጥ ማውጣት ወይም ዝርዝሩን እንደውሳኔው ማሻሻል፣

2. የመሰየም ወይም የፍርድ ውሳኔው መሰረዙን ወይም መሻሻሉን እና የሚያስከትለውን ውጤት ለተሰየመው ወይም የፍርድ ውሳኔ ለተላለፈበት ሰው በጽሑፍ ማሳወቅ፤
3. ስያሜውን እንዲያውቁት የተደረጉ ኃላፊነትያለባቸው ሰዎችና የመንግስት አካላት የመሰየም ወይም የፍርድ ውሳኔውን መሰረዝ ወይም መሻሻል እና የሚያስከትለውን ውጤት በፅሁፍ ማሳወቅ፤ እና
4. እንደአግባብነቱ በኮሚቴው ወይም ሥልጣን ባለው የውጭ አገር የመንግሥት አካል የማሻሻል ወይም የመሰረዝ ውሳኔ በተሰጠባቸውና ቀደም ሲል የሀብት ማገድን ጨምሮ በዚህ ደንብ መሰረት የተወሰዱ አስፈላጊ እርምጃዎችን ሁኔታ ለእነዚሁ አካላት በፅሁፍ የማሳወቅ፡፡

7. **<u>ከተሰየሙ ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈባቸው ሰዎች ዝርዝር ውስጥ ለመሰረዝ ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>**

1. ስሙ ከተሰየሙ ወይም የፍርድ ውሳኔ ከተላለፈባቸው ሰዎች ዝርዝር ውስጥ እንዲሰረዝለት የሚፈልግ ሰው፡-
   ሀ/ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትን ዝርዝር የሚመለከት ሲሆን ማመልከቻውን ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ማቅረብ፤
   ለ/ የፍርድ ቤትን ዝርዝር የሚመለከት ሲሆን ማመልከቻውን የመጨረሻ ውሳኔ ለሰጠው ፍርድ ቤት ማቅረብ፤
   ሐ/ የተባበሩት መንግሥታትን ዝርዝር ወይም የውጭ አገር መንግሥት አካልን ዝርዝር የሚመለከት ሲሆን ማመልከቻውን በማዕከሉ አማካይነት ለኮሚቴው ወይም ሥልጣን ላለው የውጭ አገር መንግሥት አካል፤

   ይችላል፡፡
2. ማዕከሉ አንድ የተሰየመ ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበት ሰው ከሞተ ወይም ህጋዊ ሰውነቱን ያጣ ከሆነ እና ከተሰየሙ ወይም የፍርድ ውሳኔ ከተላለፈባቸው ሰዎች ዝርዝር ውስጥ ለመሰረዝ የሚያስችል በቂ ምክንያት መኖሩን ሲያምን እንደሁኔታው የዚህን ሰው ስምና ሌሎች ዝርዝሮች ውሳኔውን ለሰጠው አካል ወይም የፍርድ ውሳኔውን ያስተላለፈውን ፍርድ ቤት ፈቃድ ጠይቆ ሲያገኝ ከዝርዝር እንዲሰረዝ ያደርጋል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የመሰየም ወይም የጥፋተኝነት ውሳኔ ውጤት

### 8. ሀብትን ስለማገድ

1. ስሙ በተሰየሙ ወይም የፍርድ ውሳኔ በተላለፈባቸው ሰዎች ዝርዝር ውስጥ በሚታይ ሰው ባለቤትነት፣ ይዞታ ወይም ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ቁጥጥር ሥር ያለ ሀብት ሳይዘገይ መታገድ አለበት፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የተሰየመ ሰው ስም በዚህ ደንብ አንቀጽ 3 መሠረት በተሰየሙ ሰዎች ዝርዝር ውስጥ እንዲካተት ማድረግን በሚመለከት በአዋጁ አንቀጽ 37 መሠረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ በተሰየመው ሰው ባለቤትነት፣ ይዞታ ወይም ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ቁጥጥር ሥር ያለ ሀብት ሳይዘገይ በማዕከሉ ውሳኔ መታገድ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበት ሰው ሀብት በማዕከሉ ከታገደ፤ ማዕከሉ ለዚህ ደንብ አንቀፅ 23 አፈፃፀም የሀብቱን መታገድ ለሚመለከተው አካል ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት በማዕከሉ ውሳኔ የታገደ ሀብት ስለመኖሩ ማዕከሉ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡
5. የዚህ ደንብ አንቀጽ 11 እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)፣ (2) እና (3) መሠረት የታገደ ሀብት በይዞታው ሥር የሚገኝ ማንኛውም ሰው የፋይናንስ አገልግሎት መስጠትን ጨምሮ የተሰየመው ወይም የፍርድ ውሳኔ የተሳለፈበት ሰው በሀብቱ እንዳይጠቀም ወይም በዚህ ሰው ስም ጥቅም ላይ እንዳይውል መከልከል አለበት፡፡
6. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) ዓላማ “መጠቀም” ማለት የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

   ሀ/ ፈንድን በሚመለከት፡-

   1) መለወጥን፣ ማንቀሳቀስን፣ ተደራሽነት እንዲኖር መፍቀድን ወይም ማዛወርን፤

2) ብዛትን፣ መጠንን፣ የመገኛ አድራሻን፣ ባለቤትነትን፣ ተጠቃሚ የሚሆን ባለቤትነትን፣ ይዞታን፣ ባህሪን ወይም መዳረሻ ቦታን መቀየር በሚችል አግባብ ማናቸውንም እርምጃ መውሰድን፤ ወይም

3) የፖርትፎሊዮ አስተዳደርን ጨምሮ በጥቅም ላይ ማዋልን የሚያስችል ማንኛውንም ሌላ ለውጥ ማድረግን፤

ለ/ ኢኮኖሚያዊ ሀብትን በሚመለከት ለግብይት ማዋል ወይም በፈንዶች፣ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች መለወጥ፡፡

7. ለዚህ አንቀጽ ዓላማ ማንኛውም ሀብት በተሰየመ ወይም የፍርድ ውሳኔ በተላለፈበት ሰው ባለቤትነት ወይም ቁጥጥር ሥር መሆን አለመሆኑን በመወሰን ረገድ የሀብቱ ማህበርተኛ በሆነ ወይም ግንኙነት ባለው ሌላ ሰው ስም መያዝ ለውጥ አያመጣም፤ የሽብርተኝነት ድርጊቱ በልዩ ሁኔታ ወይም በጠቅላላው መፈፀሙ እርምጃውን አያስቀረውም፡፡

8. ማዕከሉ፡-

ሀ/ ለትክክለኛ አስተዳደር እንዲያመች በዚህ ደንብ መሠረት የታገዱ ሀብቶችን በሙሉ በባለቤቶቹ ወይም ተጠቃሚ በሚሆኑት ባለቤቶች ስም መዝግቦ መያዝ አለበት፤

ለ/ መመሪያ በማውጣት በዚህ ደንብ መሠረት የታገዱ ሀብቶች የሚተዳደሩበትን ሥርዓት ሊወስን ይችላል፡፡

9. በዚህ አንቀፅ መሰረት የተገለጸው የስያሜ ወይም የጥፋተኝነት ውሳኔ ውጤት እንደተጠበቀ ሆኖ ስለጉዞ እና ቪዛ መስጠትን ስለመከልከልና ማገድ፣ የጦር መሳሪያ አቅርቦትና ግዥ ለመፈፀም ወይም የተሰየሙ ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈባቸው ሰዎች የውትድርና ልምምድ እንዳያደርጉ ስለሚከለክሉ እና ተያያዥነት ያላቸው ሌሎች ማንኛውም አይነት ግብይቶች እና ድርድሮችን ለመከልከል የሚያስችሉ አግባብነት ያላቸው የአገሪቱ ህጎች፣ አለም አቀፍ ስምምነቶች እና በሚመለከታቸው በተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤት የተላለፉ ውሳኔዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

9. **<u>የተሰየሙ ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈባቸው ሰዎችን ዝርዝር ስለመመልከት እና ለማዕከሉ ሪፖርት ስለማድረግ</u>**

1. ማንኛውም ኃላፊነት ያለበት ሰው ከማንኛውም ግለሰብ፣ ቡድን ወይም ድርጅት ጋር ማናቸውንም ግብይት ከመፈጸሙ ወይም ማናቸውንም ግንኙነት ከመመሥረቱ በፊት የግለሰቡ፣ የቡድኑ ወይም የድርጅቱ ስም በዝርዝሮቹ ውስጥ መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትን፣ የተባበሩት መንግስታትን እና የውጭ መንግስት አካልን እና የፍርድ ቤትን ዝርዝሮች መመልከት አለበት፡፡
2. የግለሰብ፣ የቡድን ወይም የድርጅት ስም በተሰየሙ ወይም የፍርድ ውሳኔ በተላለፈባቸው ሰዎች ስም ዝርዝር ውስጥ መኖሩ ሲረጋገጥ፣ ማንኛውም ኃላፊነት ያለበት ሰው የግለሰቡ፣ የቡድኑ ወይም የድርጅቱ ሀብት መሆኑ ወይም በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የሚቆጣጠረው መሆኑ የታወቀን ሀብት ካገደና ሂሳቡ እንዳይንቀሳቀስ ካደረገ በኋላ ሀብቱን ለማገድ የተወሰዱ ሁሉንም እርምጃዎች የሚመለከቱ መረጃዎችን ጨምሮ "ጥርጣሬ ያለበት ግብይት" በማለት ለማዕከሉ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) መሰረት ማዕከሉ ሪፖርት የቀረበለት እንደሆነ ይህንኑ በአዋጁ መሠረት የሚመለከታቸው ባለሥልጣናት ተጨማሪ እርምጃዎችን መውሰድ እንዲችሉ ማሳወቅ አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ኃላፊነት ባለበት ሰው የሚቀርብ ሪፖርት የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡-
   ሀ/ ሁኔታውን ለማወቅ ወይም ለመጠርጠር መነሻ የሆነውን መረጃ ወይም ሌላ ጉዳይ፤
   ለ/ የተባለውን ሰው ማንነት ለመለየት የሚያስችል ያለውን መረጃ፤
   ሐ/ ከስያሜው ወይም የጥፋተኝነት ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ባሉት አሥር ዓመታት ውስጥ ለተባለው ሰው ይዞት የነበረውን ሀብት ዓይነት፣ ባህሪ፣ መጠን እና ብዛት፡፡
5. ማንኛውም ኃላፊነት ያለበት ሰው በዚህ ደንብ አንቀጽ 13 መሠረት ወደ ታገደ ሂሳብ ገቢ የተደረገ ግብይትን ወዲያውኑ ለማዕከሉ ማሳወቅ አለበት፡፡ ማዕከሉም በአዋጁ መሠረት ለሚመለከታቸው ባለሥልጣናት ይህንኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

10.<u>የታገደ ሀብት ጥቅም ላይ እንዲውል ተደራሽ ስለማድረግ</u>

1. በማዕከሉ ካልተፈቀደ በስተቀር ማንኛውም ኃላፊነት ያለበት ሰው ሀብትን ለተሰየመ ወይም የፍርድ ውሳኔ ለተላለፈበት ሰው ወይም ለዚሁ ሰው ጠቀሜታ ለሚያውል ለሌላ ሰው በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ የለበትም፡፡
2. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) ዓላማ፡-

ሀ/ ሀብት ለተሰየመ ወይም የፍርድ ውሳኔ ለተላለፈበት ሰው ጠቀሜታ እንዲውል ተደራሽ ተደረገ ሊባል የሚችለው ይኸው ሰው የፋይናንስ ጥቅም ያገኘበት ወይም ሊያገኝበት የሚችል ሲሆን ነው፤

ለ/ የፋይናንስ ጥቅም ሲባልም የተሰየመው ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበት ሰው ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በኃላፊነት የሚጠየቅበትን የፋይናንስ ግዴታ መወጣትንም ይጨምራል።

11.<u>በታገደ ሀብት መጠቀምን ስለመፍቀድ</u>

1. የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበትን ሰው በተመለከተ በወንጀል ህግና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የተሰየመ ሰው መሠረታዊ ወጪዎችን ለመሸፈን የሚያስፈልግ ሀብትን የሚመለከት እግድ በማዕከሉ ሲፈቀድና እንደሁኔታው አግባብነት ባለው የተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔ ወይም አግባብ ባለው ህግ ድንጋጌዎች መሠረት ሊነሳ ይችላል፡፡ እነዚህም መሠረታዊ ወጪዎች እንደነገሩ ሁኔታ የሚከተሉትን ሊጨምሩ ይችላሉ፡-

ሀ/ የምግብ፣ የኪራይ ወይም የሞርጌጅ፣ የመድኃኒትና የሕክምና፣ የግብር፣ የኢንሹራንስ አረቦን እና ሌሎች በማዕከሉ የጸደቁ መሠረታዊ ወጪዎችን ለመሸፈን የሚፈጸሙ ክፍያዎች፤

ለ/ የሕዝባዊ አገልግሎቶች ክፍያዎች ወይም የሕግ አገልግሎት ከመስጠት ጋር የተያያዙ ተገቢ ሙያዊ ክፍያዎችንና የወጪ ተመላሾችን ለመሸፈን ብቻ የሚፈጸሙ ክፍያዎች፣ ለታገደ ሀብት መደበኛ አያያዝ ወይም እንክብካቤ ሲባል የሚፈጸሙ የባንክ ወይም የአገልግሎት ክፍያዎች፤ እና

ሐ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) እና ያልተካተቱ ሌሎች ልዩ አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚደረጉ ክፍያዎች፡፡

2. ከተለመደው በላይ ለሆኑ ወጪዎች የሚያስፈልግ ሀብትን የሚመለከት እግድ የሚነሳው ማዕከሉ ለኮሚቴው አሳውቆት ኮሚቴውም ያጸደቀው እንደሆነ ነው፡፡

12.**የታገደ ሀብት መጠቀምን የመፍቀድ ሥነ-ሥርዓት**

1. በዚህ ደንብ አንቀፅ 11 መሠረት የታገደ ሀብትን ለመጠቀም የሚቀርብ ማመልከቻ በተሰየመው ሰው ወይም የውክልና ሥልጣን በተሰጠው ወኪል አማካይነት ከደጋፊ ሰነዶች ወይም ማስረጃዎች ጋር ለማዕከሉ መቅረብ አለበት፤ ማዕከሉም በቂ ምክንያት መኖሩን ሲያረጋግጥ በታገደ ሀብት መጠቀምን ሊፈቅድ ይችላል፡፡
2. የተሰየመው ሰው በተባበሩት መንግሥታት ወይም የውጭ አገር መንግሥት አካል ዝርዝር ውስጥ የተካተተ ከሆነ ማዕከሉ የታገደን ሀብት ወይም የሀብቱን ማናቸውም ክፍል ለመጠቀም መፍቀድ ማሰቡን ለሚመለከተው ኮሚቴ ወይም የውጭ አገር መንግሥት አካል ማሳወቅ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) መሰረት በማዕከሉ ሐሳብ የቀረበለት ኮሚቴ ወይም የውጭ ሀገር የመንግሥት አካል በሐሳቡ መስማማቱን ወይም አለመስማማቱን በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ካላሳወቀ የታገደው ሀብት ማዕከሉ በፈቀደው መሠረት በጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፡፡
4. ኃላፊነት ያለበት ሰው ወይም የታገደው ሀብት ጠባቂ የሆነው ሌላ ወገን የተሰጠውን የመጠቀም ፈቃድ በሥራ ላይ እንዲያውል ፈቃዱ በተሰጠ በ48 ሰዓታት ውስጥ በጽሑፍ እንዲያውቀው መደረግ እና እርሱም ስለተወሰደው እርምጃ በጽሑፍ ለማዕከሉ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡
5. በማናቸውም የተሰየሙ ሰዎች ዝርዝር ውስጥ የተካተተ የተሰየመ ሰው ወይም ወኪሉ ማመልከቻው ተቀባይነት ማግኘቱን ወይም ውድቅ መደረጉን በሚመለከት በጽሑፍ እንዲያውቀው መደረግ አለበት፡፡

13.**ተጨማሪ ገንዘብን ወደ ታገደ ሂሳብ ገቢ ስለማስገባት**

1. የታገደ ሂሳብ የገቢ ምንጭ የሆነ ማንኛውም መጠን ያለው ገንዘብ፦
   ሀ/ ከሂሳቡ የመነጩ የወለድ ወይም ሌሎች ገቢዎችን፣
   ለ/ ሂሳቡ ከመታገዱ በፊት በተደረጉ ውሎች ወይም ስምምነቶች ወይም በተፈጠሩ ግዴታዎች መሠረት የተገኙ ክፍያዎችን፤ እና

ሐ/ ወደ ታገደው ሂሳብ የተላለፉ ገንዘቦችን፣ ጨምሮ ወደ ታገደው ሂሳብ ገቢ ተደርጎ የታገደው ፈንድ አካል ይደረጋል፣ ኃላፊነት ያለበት ሰውም እንደዚህ ያለውን ተጨማሪ ገንዘብ መቀበሉን የሚመለከት ሪፖርት ለማዕከሉ ማቅረብ አለበት፡፡

2. በዚህ ደንብ የተደነገጉ ክልከላዎችና እርምጃዎች ወደ ታገደው ሂሳብ ገቢ የተደረገውን ተጨማሪ ገንዘብ በሚመለከት ተፈጻሚ ይሆናሉ።

3. በዚህ አንቀጽ በተመለከተው መሠረት የተገኘን ፈንድ በመቀበል ገቢ የሚደረግበት ቀደም ሲል የተከፈተ ሂሳብ በሌለበት ሁኔታ መወሰድ ስላለበት አግባብ ያለው እርምጃ ማዕከሉን ማሳወቅ አለበት፡፡

4. ለዚህ አንቀጽ ዓላማ "የታገደ ሂሳብ" ማለት በዚህ ደንብ የተደነገጉ ክልከላዎችና እርምጃዎች ተፈጻሚ የሚደረጉበት ኃላፊነት ባለበት ሰው ዘንድ በሚገኝና በተሰየመ ሰው ስም በተከፈተ ወይም የተሰየመው ወይም የፍርድ ውሳኔ በተላለፈበት ሰው በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ በሚቆጣጠረው ሂሳብ የተያዘ ገንዘብ ወይም ኢኮኖሚያዊ ሀብት ነው፡፡

14.<u>በስህተት ስለታገደ ሀብት</u>

1. በስም ተመሳሳይነት በተሰየሙ ወይም የፍርድ ውሳኔ በተላለፈባቸው ሰዎች ዝርዝር ወይም ሂሳብ ውስጥ በስህተት በማካተት ወይም በሌላ ስህተት ምክንያት ሀብት የታገደ እንደሆነ ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው እገዳው እንዲነሳለት ለማዕከሉ ማመልከት ይችላል፡፡

2. ማዕከሉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማመልከቻ ከተቀበለ በኋላ ማመልከቻው፡-

ሀ/ የተባበሩት መንግስታትን ዝርዝር ወይም የውጭ አገር መንግስት አካልን ዝርዝር የሚመለከት ሆኖ ከተገኘ ማመልከቻውን ከተቀበለበት ቀን አንስቶ በ15 ቀናት ውስጥ ከሚመለከተው ኮሚቴ ወይም ሥልጣን ያለው የውጭ አገር መንግሥት አካል ጋር ተወያይቶ ውሳኔ ማስተላለፍ አለበት፣

ለ/ ስያሜው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትን ዝርዝር ወይም የፍርድ ቤትን ዝርዝር የሚመለከት ሆኖ ከተገኘ ማመልከቻውን ከተቀበለበት ቀን አንስቶ በ15 ቀናት ውስጥ ከሚመለከተው ጋር ተወያይቶ ውሳኔ ማስተላለፍ አለበት፡፡

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) መሰረት የተወሰነውን ውሳኔ ማዕከሉ እንደአግባብነቱ ለአመልካቹ፣ ለሁሉም ኃላፊነት ላለባቸው ሰዎችና ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

## ክፍል አራት

## ስለመረጃና ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ

### 15. ኃላፊነት ያለበት ሰው ሪፖርት የማድረግ ግዴታ

1. ማንኛውም ኃላፊነት ያለበት ሰው የሚመለከተው ሰው፡-

   ሀ/ የተሰየመ ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበት መሆኑን፤ ወይም

   ለ/ በአዋጁ መሰረት ወንጀል የፈጸመ መሆኑን፤

   ያወቀ ወይም የተጠራጠረ እንደሆነ ይህንኑ ለማዕከሉ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

2. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ዓላማ "የሚመለከተው ሰው" ማለት፡-

   ሀ/ ኃላፊነት ያለበት ሰው ደንበኛ፤

   ለ/ ከተስየመበት ወይም የፍርድ ውሳኔ ከተላለፈበት ቀን በፊት ባሉት አስር ዓመታት ውስጥ በማናቸውም ጊዜ ኃላፊነት ያለበት ሰው ደንበኛ የነበረ፤ ወይም

   ሐ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ለ) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ኃላፊነት ካለበት ሰው ጋር ማንኛውንም የሥራ ግንኙነ ያደረገ ሰው ነው፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርብ ሪፖርት የሚከተሉትን መግለጽ አለበት፡-

   ሀ/ ጥርጣሬው ወይም ማረጋገጫው መሠረት ያደረገውን መረጃ ወይም ሌሎች ማስረጃዎች፤

   ለ/ የሚመለከተውን ሰው ማንነት የሚገልጽ በእጁ የሚገኘውን ማንኛውንም መረጃ፤ እና

   ሐ/ ስያሜው ወይም የጥፋተኝነት ውሳኔው ከመስጠቱ በፊት ባሉት አስር ዓመታት ውስጥ ባለው ማናቸውም ጊዜ ለተሰየመው ሰው ኃላፊነት ባለበት ሰው የተያዘ ማንኛውም ሀብት ዓይነት፣ ባህሪ፣ መጠን እና ብዛት፡፡

### 16. መረጃን የመጠየቅ ስልጣን

1. ማዕከሉ የተሰየመን ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበትን ሰው ወይም ማንኛውንም ኃላፊነት ያለበት ሰው፡-

ሀ/ በተሰየመው ወይም የፍርድ ውሳኔ በተላለፈበት ሰው ወይም እርሱን በመወከል በባለቤትነት ወይም በይዞታነት የተያዘ ወይም ቁጥጥር የሚደረግበት ሀብት ስለመኖሩ፤ ወይም

ለ/ ስያሜው ወይም የጥፋተኝነት ውሳኔው ከመሰጠቱ በፊትም ሆነ በኋላ የተወገደ ማንኛውም ሀብት ስለመኖሩ፤

ሊጠይቅ ይችላል፡፡

2. ማዕከሉ ከሥራው ጋር በተያያዘ በቂ ምክንያት ያስፈልጉኛል የሚላቸውን የሚከተሉትን ወጪዎች የሚመለከት መረጃ ከተሰየመው ወይም የፍርድ ውሳኔ ከተላለፈበት ወይም ከማንኛውም ኃላፊነት ካለበት ሰው ሊጠይቅ ይችላል፦

ሀ/ በተሰየመው ወይም የፍርድ ውሳኔ በተላለፈበት ሰው ወይም ይህንኑ ሰው በመወከል የተደረጉ ወጪዎችን፤ ወይም

ለ/ ለተሰየመው ወይም የፍርድ ውሳኔ ለተላለፈበት ሰው ጥቅም ሲባል የተደረጉ ወጪዎችን፡፡

3. ማዕከሉ ከሥራው ጋር በተያያዘ በቂ ምክንያት ለሚከተሉት ዓላማዎች የሚፈልገውን መረጃ ማንኛውም በኢትዮጵያ የግዛት ክልል ውስጥ የሚገኝ ወይም ነዋሪ የሆነ ሰው እንዲሰጠው መጠየቅ ይችላል፦

ሀ/ የዚህ ደንብ ተፈፃሚነት ለማረጋገጥ፤

ለ/ በአዋጁ ላይ የተመለከተ ወንጀልን ከመፈጸም ጋር የተያያዙ ማስረጃዎችን ለማግኘት፤

ሐ/ የሚከተሉትን ለማረጋገጥ፡-

1) በተሰየመው ወይም የፍርድ ውሳኔ በተላለፈበት ሰው ወይም ይህንኑ ሰው በመወከል በባለቤትነት ወይም በይዞታነት የተያዘ ወይም ቁጥጥር የሚደረግበት ሀብት፤

2) ለተሰየመው ወይም የፍርድ ውሳኔ ለተላለፈበት ሰው ወይም ለዚሁ ሰው ጥቅም ሲባል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተደራሽ እንዲሆን የተደረገን ማንኛውም ሀብት፤

3) በተሰየመው ወይም የፍርድ ውሳኔ በተላለፈበት ሰው የተደረገን ማንኛውም የፋይናንስ ግብይት፤ዓይነት፣ ባህሪ፣ መጠን ወይም ብዛት፡፡

4. ማዕከሉ መረጃ የሚቀርብለትን አኳኋን እና ጊዜ በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ማዕከሉ በመመሪያ ጊዜውን ያልወሰነ ከሆነ የተጠየቀው መረጃ በተገቢ ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡
6. የመረጃ ጥያቄው ሁኔታዎች በተለወጡ ቁጥር ወይም ማዕከሉ በሚወስነው በመደበኛ ጊዜ መረጃዎች ለማዕከሉ እንዲደርሱ ለማድረግ የሚያስችል ቀጣይነት ያለውን ግዴታ ሊያካትት ይችላል፡፡

17.<u>ሰነድ ስለማቅረብ</u>

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 16 መሠረት የሚጠየቅ መረጃ የተወሰኑ ሰነዶች ወይም ስለተወሰነ ነገር የሚገልጹ ወይም የሚዘረዝሩ ሰነዶች እንዲቀርቡ መጠየቅን ሊጨምር ይችላል፡፡
2. ማዕከሉ ሰነድ እንዲቀርብለት ሲጠይቅ፡-

ሀ/ የሰነዱን ኮፒ ወይም የሰነዱ የተወሰነ ክፍል ለመውሰድ፤

ለ/ ሰነዱን ያቀረበው ሰው ስለሰነዱ ገለፃ እንዲያደርግለት ሊጠይቅ፤

ሐ/ ሰነዱን ያቀረበው ሰው የሕግ ሰውነት ያለው ድርጅት ከሆነ የድርጅቱ ኃላፊ የሆነ ወይም የነበረ ወይም ሰራተኛ የሆነ ሰው ይህንኑ ገለፃ እንዲያደርግለት ሊጠይቅ፤

ይችላል፡፡

3. ማዕከሉ የተሰየመው ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበት ሰው ሰነድ እንዲያቀርብ የጠየቀ እንደሆነ ይህ ሰው፡-

ሀ/ ሰነዱ አስቀድሞ በይዞታው ወይም በቁጥጥሩ ሥር የሚገኝ ካልሆነ ሰነዱን ለማግኘት ተገቢ የሆነ ጥረት፤ እና

ለ/ ለማዕከሉ ለመሰጠት ካልሆነ ወይም ማዕከሉ በሌላ ሁኔታ ካልፈቀደ በስተቀር ሰነዱን በይዞታው ወይም በቁጥጥሩ ሥር ጠብቆ ማቆየት፤

አለበት፡፡

18.<u>ስለመረጃዎች ሚስጥራዊነት</u>

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 4(1) መሠረት በማዕከሉ መረጃዎች የሰጠው ሰው ወይም እነዚህኑ መረጃዎች ያገኘ ሰው ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ካልሆነ በስተቀር መረጃዎቹን ለሌላ ሰው መግለጽ የለበትም፡፡
2. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ዓላማ መረጃ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ለሌላ ሰው ተገለጸ ሊባል የሚችለው፡-

ሀ/ በዚህ ደንብ የተደነገገን ግዴታ ለመወጣት፤ ወይም

ለ/ ማንኛውንም የክርክር ሂደት በሚመለከት የፍርድ ቤት ሥነ ሥርዓት ሕግን ለማሟላት ወይም የፍርድ ቤት ትዕዛዝን ለመፈፀም፤

ሲባልና ለዚሁ በሚያስፈልግ ደረጃ የተገለጸ እንደሆነ ነው፡፡

3. በዚህ አንቀጽ የተደነገገው ቢኖርም መረጃው ከሌላ ምንጭ አስቀድሞ ለሕዝብ ይፋ የተደረገ ከሆነ መረጃው የደረሰው ሰው መረጃውን እንዳይገልጽ አይከለከልም።

19. <u>መረጃን የመግለጽ ጠቅላላ ስልጣን</u>

ማዕከሉ በዚህ ደንብ መሠረት ሥራውን ሲያከናውን ያገኘውን ማንኛውንም መረጃ፣ የቀረበለትን ሰነድ፣ የሰነዱን ኮፒ ወይም የሰነዱን የተወሰነ ክፍል ጨምሮ ለሚከተሉት ሊገልፅ ይችላል፡-

1. ኃላፊነት ላለበት ሰው እና አግባብ ላላቸው የመንግስት አካላት፤
2. በዚህ ደንብ መሠረት የተወሰዱ እርምጃዎች ለሚመለከታቸው አግባብ ላሏቸው የውጭ አገር መንግሥት አካላት፡፡

20. <u>ከሕገ ውጪ መረጃን ስለመግለጽ</u>

1. በዚህ ደንብ መሠረት የቀረበ ወይም የተላለፈ መረጃን በሥራው አጋጣሚ ያወቀ ወይም የያዘ ሰው ይህንን ደንብ ለማስፈፀም ሲባል ካልሆነ በስተቀር መረጃውን፣ የመረጃውን ምንጭ ጨምሮ፣ በማናቸውም መንገድ መግለጽ የለበትም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ክልከላ የግለሰቡ የስራ ግንኙነት ከተቋረጠም በኋላ ቢሆን የሚቀጥል ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

21. <u>ከተባበሩት መንግስታት ጋር ስለሚደረግ የግንኙነት መስመር</u>

1. በዚህ ደንብ መሰረት ከኮሚቴው ጋር በማዕከሉ የሚደረግ ማንኛውም ግንኙነት በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር አማካኝነት መተላለፍ አለበት፡፡
2. የተባበሩት መንግስታት የጸጥታው ም/ቤት በቁጥር 1267(1999)፣ 1333(2000)፣ 1363(2001)፣ 1373(2001)፣ 1390(2002)፣ 1452(2002)፣ 1455(2003)፣ 1526(2004)፣ 1566(2004)፣ 1617(2005)፣ 1624(2005)፣ 1699(2006)፣ 1730(2006)፣ 1735(2006)፣ 1822(2008)፣ 1904(2009)፣ 1988(2011)፣

1989(2011)፣ 2082(2012) እና 2083(2012) ያሳለፋቸውን፣ ውሳኔዎች እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔዎች በኢትዮጵያ ውስጥ በማስፈጸም ሂደት የተወሰዱ እርምጃዎችን የሚመለከቱ አስፈላጊ ሪፖርቶችን በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መሪነት የፍትህ ሚኒስቴር፣[38] የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት እና ማዕከሉን በማካተት በኢትዮጵያ፣ በተባበሩት መንግሥታት እና በሌሎች አገራት ወይም ተቋማት ስምምነት ላይ በተደረሰበት የጊዜ ልዩነት ማዘጋጀትና ማቅረብ አለባቸው።

22. **ዓለም አቀፍ ትብብር**

1. ማዕከሉ በራሱ ወይም አግባብ ካላቸው ባለስልጣናት ጋር በመተባበር የተሰየመን ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበትን ሰው ሀብት ወይም የፋይናንስ ግብይት በኢትዮጵያ ወይም በሌላ ቦታ በማገድ ወይም በመመርመር ሂደት በአዋጁ መሠረት ለመተባበር ተገቢ መስሎ የታየውን እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡
2. የሽብር ተግባርን በገንዘብ መርዳትን ከመከላከልና ከመቆጣጠር አንፃር አገራት እርስ በርሳቸው ትብብር እንዲያደርጉ በሚደነግግ የተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔ መሠረት የውጭ አገር መንግስት፡-

   ሀ/ የሽብር ድርጊትን ያመቻቸ ወይም አሽባሪን ወይም አሸባሪ ድርጅትን በማቴሪያል የደገፈ ድርጅትን ጨምሮ በዚያ አገር የተሰየመ ሰው ሀብት፤

   ለ/ የተሰየመው ሰው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በባለቤትነት የያዘው ወይም የሚቆጣጠረው ድርጅት ሀብት፤

   ሐ/ የተሰየመው ሰው ወኪል በመሆን ወይም በዚሁ ሰው አመራር ሰጪነት ተግባሩን የሚያከናውን ሰው ሀብት፤

   መ/ የተሰየመው ሰው በባለቤትነት ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከሚቆጣጠረው ንብረት የተገኘ ወይም የመነጨ ፈንድ፤

   እንዲታገድ ኢትዮጵያን የጠየቀ እንደሆነ አግባብ ባለው የተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔ መሠረት የሕግ ድጋፍ የጋራ ትብብር ለማድረግ ጥያቄው ለማዕከሉ መቅረብ አለበት፡፡

[38] በአዋጅ ቁጥር 943/2008 መሰረት የፈዴራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ ሆኗል፡፡

3. የአዋጁ አንቀጽ 48 እንደተጠበቀ ሆኖ የትብብር ጥያቄው የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-
   ሀ/ ሀብቱ የሚታገድበት ሰው የሽብር ተግባር ስለመፈፀሙ ወይም ከሽብር ተግባር ጋር ግንኙነት እንዳለው የሚያስረዱ ፍሬ ነገሮችን የሚዘረዝር መግለጫ፤
   ለ/ ከማንኛውም የሽብር ድርጊት ጋር የተያያዙ ሕገወጥ እንቅስቃሴዎች ፍሬ ስለመሆኑ ወይም ለታቀዱ የሽብር ተግባራት በመሣሪያነት የሚውል ስለመሆኑ የሚያስረዱ ፍሬ ነገሮችን የሚዘረዝር መግለጫ፤
   ሐ/ እርምጃው የሚመለከተውን ሰው ማንነትና አድራሻ በበቂ ደረጃ ለመለየት የሚያስችል የተሟላ መረጃ፤
   መ/ የሚታወቅ ከሆነ በሀብቱ ላይ የይገባኛል መብት አለን የሚሉ ሰዎችን ማንነትና አድራሻ ከመብቶቻቸው ዓይነት ጭምር የሚያሳይ መግለጫ፤ እና
   ሠ/ የተሰየመውን ሰው በሚመለከት በጠያቂው አገር የተካሄደ፣ በመካሔድ ላይ ያለ ወይም ሊካሄድ የታሰበ የወንጀል ክስ ሂደቶችን ዝርዝር የሚያሳይ መግለጫ።
4. ማዕከሉ ምክንያታዊ በሆኑ መሥፈርቶች ላይ ተመሥርቶ የትብብር ድጋፉ ሲሰጥ ይገባል ብሎ ካመነ የሚመለከተው ባለሥልጣን እንዲፈጽመው በጥያቄው ላይ ያለውን ስተያየት ጨምሮ በተገቢው ጊዜ ውስጥ ያስተላልፍለታል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚደረግ የሀብት እገዳ የሚመለከታቸው ወገኖች በጋዜጣም ሆነ በማንኛቸውም መንገድ አስቀድሞ እንዲያውቁት ማድረግም ሆነ የወንጀል ምርመራ ማካሄድ ሳያስፈልግና ባለጉዳዮቹ በሌሉበት የሚፈጸም ይሆናል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት የሀብት ዕገዳ እርምጃ ከተወሰደ በኋላ ማዕከሉ እገዳውን በማረጋገጥ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ይፋ እንዲሆን ያደርጋል፤ ሆኖም ማዕከሉ እገዳውን ለማረጋገጥም ሆነ ላለማረጋገጥ በሚወስንበት ሂደት ጠያቂው አገር ጥያቄውን ለመደገፍ ያቀረባቸውን መረጃዎች ሚስጥራዊነት ለመጠበቅ አስፈላጊ የሆኑ አግባብነት ያላቸውን እርምጃዎች ሁሉ መውሰድ አለበት፡፡
7. በዚህ አንቀጽ መሠረት የዕገዳ ትዕዛዝ ተፈፃሚ ከተደረገ ጠያቂው የውጭ መንግስት አካል የሀብት እገዳ ጥያቄውን ካላነሳ ወይም ማዕከሉ የእግድ ጥያቄው

ተገቢነቱን እንደያዘ ያልቀጠለ መሆኑን ካልወሰነ በስተቀር ተፈጻሚነቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቀጥላል።

8. የሀብት እገዳ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) እና (6) መሠረት እስከተረጋገጠ ድረስ ጉዳዩ በዚህ ደንብ በተመለከተው "የተሰየመ ሰው" ሀብት የሚታገድበትን ስነ-ስርዓት በጠበቀ መልክ የሚስተናገድ ይሆናል፡፡

23.<u>ሀብትን መያዝና መውረስ</u>

የተሰየመ ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበት ሰውን ሀብት የመያዝ ወይም የመውረስ ስነ-ስርዓት አግባብነት ባላቸው ሌሎች ህጎች መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

24.<u>ሌሎች ኃላፊነት ያለባቸው አካላት</u>

ለዚህ ደንብ አፈፃፀም ሲባል የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ፣ የንግድ ሚኒስቴር፣ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴርን እና ሌሎች ኃላፊነት ያለባቸው የመንግስት ተቋማት ሪፖርት በማቅረብ ረገድ በዚህ ደንብ አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ (6) በተመለከተው "ኃላፊነት ያለበት ሰው" ትርጓሜ እንደሚሸፈን ተደርጎ ይቆጠራሉ።

25.<u>የመተባበር ግዴታ</u>

1. ማንኛውም የሚመለከተው አካል ማዕከሉ በአዋጁ እና በዚህ ደንብ መሠረት ሥልጣንና ተግባሩን በሥራ ላይ ሲያውል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡
2. ማዕከሉ በራሱ ወይም በአዋጁ መሠረት አግባብ ካለው ባለስልጣን ጋር በመተባበር በአዋጁ ወይም በዚህ ደንብ የተመለከቱ ግዴታዎች ስለመፈፀማቸው አስፈላጊውን ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

26.<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 26 ቀን 2006 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

# አዋጅ ቁጥር 1089/2010

## የምህረት አሰጣጥ እና አፈጻጸም ሥነ-ሥርዓትን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ

የማሕበረሰቡን ሰላም እና ደህንነት ለማረጋገጥ እንዲሁም የሕዝቡን ፖለቲካዊ፣ ማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለመጠበቅ ምህረት ለመስጠት የሚያስችል ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ በየወቅቱ ለሚከሰቱ ከፍተኛ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ችግሮች መፍትሔ ለመስጠት ሕግን ለተላለፉ አካላትምህረት የሚሰጥበትን ሁኔታ ማመቻቸት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ ምህረትን በተመለከተ ከሀገሪቱ የወንጀል ሕግየተደነገገውን ከሕገ-መንግሥቱ ጋርበማጣጣም ምህረት የሚሰጥበትን ሥነ-ሥርዓት በሕግ መደንገግ በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለውታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ “የምህረት አሰጣጥ እና አፈጻጸም ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1089/2010” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነበስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

   1. “ምህረት” ማለት የወንጀል ምርመራ ከመጀመሩ በፊት፣ ከተጀመረ በኋላ፣ የክስ ሂደት ላይ እያለ ወይም የወንጀል ቅጣት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በተመሳሳይ ወንጀል የተጠረጠሩ ወይም የቅጣት ውሳኔ ያገኙ ሰዎችን ያለምንም ገደብ ወይም በአንዳንድ ገደቦች ወይም ግዴታዎች ከወንጀል ተጠያቂነት ነጻ ማድረግ ነው፤
   2. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 47(1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤
   3. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግየሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
   4. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው ድንጋጌ ሴትንም ይጨምራል፡፡

3. **የተፈጻሚነት ወሰን**

   1. ይህ አዋጅ በማንኛውም የወንጀል አይነቶች ተጠርጣሪዎች፣ ተከሳሾች ወይም ፍርደኞች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ይህ አዋጅ የሰው ዘር በማጥፋት፣ ያለፍርድ የሞት ቅጣት እርምጃ መውሰድ፣ በአስገዳጅ ሰውን መሰወር እና ኢ-ሰብአዊ የድብደባ ድርጊት መፈጸም ወንጀሎች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለምህረት ቦርድ</u>

### 4. <u>የምህረት ቦርድ ስለመቋቋም</u>

1. የምህረት ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለየሚጠራ) በዚህ አዋጅ መሰረት ተቋቁሚል፡፡
2. የቦርዱ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል፡፡

### 5. <u>የቦርዱ አባላት</u>

ቦርዱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

1. የፌደራልጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ.......................................................ሰብሳቢ
2. የሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ……..…………………አባል
3. የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ ኮሚሽነር ጀነራል ………...….......................አባል
4. የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር ………………… አባል
5. ከፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚወከል አንድ ዳኛ …………………… አባል
6. በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየሙ ሁለት ሰዎች ……………………………አባላት

### 6. <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ለምህረት አሰጣጥና አፈጻጸም የሚረዱበመመሪያ መስፈርቶችን ያወጣል፤
2. የምህረት ጥያቄን ይቀበላል፤ ይመረምራል፤የውሳኔ ሀሳብ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ያቀርባል፤
3. የምህረት ጥያቄውን በተመለከተ አግባብ ያላቸው አካላት ቀርበው እንዲያስረዱ ያደርጋል፤
4. ምህረት ለተደረገላቸው ሰዎች የምስክርወረቀት እንዲሰጥ ያደርጋል፤
5. ምህረት የተደረገላቸው ሰዎች ከማህበረሰቡ ጋር ተዋህደው ወደ ሰላማዊ ህይወት እንዲመለሱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋርበመተባበር ይሠራል፤
6. የምህረት አፈጻጸምን ይከታተላል፤ ችግር ካለ አስፈላጊ ማስተካከያ እንዲወሰድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይሠራል፡፡

7. **የቦርዱ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት**

1. ቦርዱ በሰብሳቢው ጥሪ በማንኛውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡
2. ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡
3. የቦርዱ ውሳኔ በአብላጭ ድምጽ ይተላለፋል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽይኖረዋል፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ውስጠ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

8. **ስለ ቦርዱ ጽሕፈት ቤት**

1. በይቅርታ አሰጣጥና አፈጻጸም ሥነ-ሥርዓትአዋጅ ቁጥር 840/2010 አንቀጽ 13(1) መሠረት በፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ውስጥ የተደራጀው የይቅርታ ቦርድ ጽህፈት ቤት የቦርዱ ጽሕፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል፡፡
2. ጽሕፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) ለቦርዱ አባላት አስተዳደራዊ አገልግሎት ይሰጣል፤

ለ) የቦርዱን መዛግብት፣ ሰነዶችና ውሳኔ የተሰጠባቸውን ጉዳዮች በአግባቡ ይይዛል፤ ይጠብቃል፤

ሐ) የስብሰባ ጥሪ ለቦርዱ አባላት ያስተላልፋል ፤ አጀንዳዎችንና አስፈላጊ ሰነዶችን ያሰራጫል፤

መ) ለቦርዱ ስራ ስኬታማነት የሚረዱ ሌሎች ተግባራቶችን ያከናውናል፡፡

## ክፍል ሶስት

## የምህረት አሰጣጥና አፈጻጸም

9. **ምህረት የሚሰጥባቸውን ጉዳዮች ለይቶ ስለማቅረብ**

1. የሕዝብ እና የመንግስትን ጥቅም መሰረት በማድረግ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በራሱ ተነሳሽነት ወይም ከክልሎች በሚቀርብ ጥያቄ መሰረት ምህረት የሚሰጥባቸውን ወንጀሎች እና በወንጀል የተጠረጠሩ፣ የተከሰሱ ወይም የወንጀል ፍርድ የተላለፈባቸው ሰዎች ለይተው ለቦርዱ ያቀርባል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የምህረት ጥያቄ ለቦርዱ ሲቀርብ የሚከተሉትን ነጥቦች መያዝ ይኖርበታል፡-

ሀ) የወንጀሉን ዓይነት፤

ለ) ምህረት የሚደረግላቸው ቡድኖች ወይም ግለሰቦች ፤

ሐ) ምሕረት የሚሰጥበትን ምክንያት እና፤

መ) ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች፡፡

10.<u>ምሕረት ለመስጠት ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ሁኔታዎች</u>

ምሕረት ለመስጠት የሚከተሉት ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ መግባት አለባቸው፡-

1. የወንጀል ድርጊቱ በሀገር ሉአላዊነት ላይ የሚያስከትለው ወይም ያስከተለው ተፅዕኖ፤
2. ሰላም እና ደህንነት ለማረጋገጥ የተሻለ አማራጭ ስለመሆኑ፤
3. ምህረት የሚደረግላቸው ሰዎች ወደ ሰላማዊ ሕይወት ለመመለስ የሚያሳዩት ፍላጎት፡፡

11.የምሕረት ውሳኔ አሰጣጥ

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ጠቅላይ ሚኒስትሩ የቀረበለትን የምህረት የውሳኔ ሀሳብ መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል፡፡
2. ጠቅላይ ሚኒስትሩ የቦርዱን የምህረት የውሳኔ ሐሳብ ከተቀበለ በጉዳዩ ላይ ረቂቅ የምሕረት አዋጅ በፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በኩል እንዲዘጋጅ ያደርጋል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት የተዘጋጀው ረቂቅ የምሕረት አዋጅ የሚኒስትሮች ምክር ቤት መክሮበት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይቀርባል፤ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከጸደቀ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያስፈጽማል፡፡

12.<u>የምህረት ውጤት</u>

1. ምሕረት የሚከተለው ውጤት ይኖረዋል፡-

   ሀ) ማንኛውም የወንጀል ምርመራ ወይም ክስ እንዳይጀመር ወይም እንዳይቀጥል ያደርጋል፤

   ለ) ቅጣት ተወስኖ ከሆነ ቅጣቱንና ቅጣቱ የሚያስከትለውን ማናቸውንም የወንጀል ውጤቶች ያስቀራል፤

   ሐ) የጥፋተኝነት ውሳኔም እንዳልነበረ ተቆጥሮ ከወንጀለኛ መዝገብ ላይ ይሰረዛል፤

   መ) በተለየ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር ለመንግስት ሊከፈል የሚገባውና ገና ያልተከፈለ ኪሳራ ቀሪ ይሆናል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (መ) ድረስ የተደነገገው ቢኖርም ምህረት በፍትሐ ብሔር በኩል የጠፋውን እንደነበረ የመመለስና በተበዳዩ ላይ ለደረሰው ጉዳት የሚከፈለውን ካሳና ኪሳራ አያስቀርም፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

13. **የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ለምህረት አሰጣጥና አፈጻጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

14. **ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች**

ይህን አዋጅ የሚቃረን ሕግ ወይም ልማዳዊ አሠራር ወይም ውሳኔ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

15. **ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ቦርዱ ለዚህ አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

16. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ 10 ቀን 2010 ዓ.ም**

**ሙላቱ ተሾመ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## ሐ/ ታራሚዎች

### ደንብ ቁጥር 138/1999

### ስለፌዴራል ታራሚዎች አያያዝ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/1998 አንቀጽ 5 እና በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 365/1999 አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የፌዴራል ታራሚዎች አያያዝ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 138/1999" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

   1. አስተዳደር ማለት የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ነው፤
   2. ማረሚያ ቤት፣ ታራሚ እና የማረሚያ ጠባቂ የሚሉት ቃላቶች በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 365/1995 የተሰጣቸው ትርጉም ይኖራቸዋል፤
   3. ፍርድ ቤት ማለት የፌዴራል ፍርድ ቤት ወይም የፌዴራል ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን የተሰጠው ፍርድ ቤት ነው፤
   4. የሕክምና ተቋም ማለት በአስተዳደሩ ሥር የሚገኝ የሕክምና ተቋም ወይም ለማረሚያ ጥበቃ አባላትና ለታራሚዎች የሕክምና አገልግሎት የሚሰጥበት ተቋም ነው፡፡

3. ***መሠረታዊ መርሆች***

   የታራሚዎች አያያዝ በሚከተሉት መሠረታዊ መርሆዎች ላይ የተመሠረተ ይሆናል፤

   1. በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በብሔር ብሔረሰብ አባልነት፣ በማህበራዊ ደረጃ ወይም በዜግነት ምክንያት ልዩነት ያለማድረግ፤
   2. የተላለፈባቸው ቅጣት የሚጥለው ገደብ ከሌለ በቀር ሰብዓዊ ክብራቸው እንዲጠበቅ ማድረግ፤
   3. የእሥራት ቅጣቱ አፈፃፀም አስተማሪና ገንቢ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

4. <u>ታራሚዎችን ስለመቀበልና ስለመመዝገብ</u>

   1. ማንኛውም ማረሚያ ቤት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ በፍርድ ቤት ትእዛዝ የሚላኩትን ታራሚዎች ይቀበላል።
   2. ወደ ማንኛውም ማረሚያ ቤት የሚገቡ ታራሚዎች አስተዳደሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በመዝገብ ላይ እንዲመዘገቡና እያንዳንዱ ታራሚ የግል ማህደር እንዲኖረው ይደረጋል፡፡
   3. ማንኛውም ታራሚ ማረሚያ ቤት በሚገባበት እለት የጤና ምርመራ ይደረግለታል፡፡
   4. ታራሚዎች በማረሚያ ቤት ቆይታቸው ስለሚኖራቸው መብትና ግዴታ ይገለጽላቸዋል፡፡

5. <u>ታራሚዎችን ለይቶ ስለመያዝ</u>

   1. ወንድና ሴት ታራሚዎች ተለይተው መያዝ አለባቸው። በተለይም፣

      ሀ/ ለሴት ታራሚዎች የተመደበው ክፍል በጥብቅ መከለል ይኖርበታል፣

      ለ/ ሴት ታራሚዎችን የሚጠብቁና የሚቆጣጠሩት ሴት የጥበቃ አባሎችና ኃላፊዎች ብቻ ይሆናሉ፤ ሆኖም የማረሚያ ቤቱ ወንድ የጥበቃ አባላት በተለይም ሐኪሞችና መምህራን በሴቶች ክልል ሙያዊ ተግባራቸውን ማካሄድ ይችላሉ፡፡
   2. የሞት ቅጣት የተወሰነባቸው ታራሚዎች ከሌሎች ታራሚዎች ተለይተው መያዝ አለባቸው።
   3. ሁኔታዎች በፈቀዱ መጠን፣

      ሀ/ እድሜያቸው ከ18 አመት በታች የሆኑ ታራሚዎች ከአዋቂዎች ተለይተው ይያዛሉ፤

      ለ/ ያልተፈረደባቸው ታራሚዎች ከተፈረደባቸው ታራሚዎች ተለይተው ይያዛሉ፤

      ሐ/ ከባድ የወንጀል ሪከርድ ያለባቸው፣ ተደጋጋሚ የወንጀል ድርጊት የፈጸሙና ምግባረ ብልሹ ታራሚዎች ከሌሎች ታራሚዎች ተለይተው ይያዛሉ፤

      መ/ ተላላፊ በሽታና የአእምሮ ሕመም ያለባቸው ታራሚዎች ከሌሎች ታራሚዎች ተለይተው ይያዛሉ።
   4. የታራሚዎችን ማህበራዊና ተሃድሶ ሁኔታ ለማሳካት ይቻል ዘንድ በሚመሳሰሉባቸውና በሚለያዩባቸው ሁኔታዎች በመለየት ሥራ ላይ እንዲሰማሩ ይደረጋል፡፡

6. <u>የታራሚዎች ክፍሎች ማሟላት ስለሚኖርባቸው ሁኔታዎች</u>

ታራሚዎች የሚኖሩባቸውም ሆነ የሚሠሩባቸው ክፍሎች፣

1. መጽሐፍ ለማንበብ የሚያስችል በቂ ብርሃንና ለጤንነት ተስማሚ የሆነ አየር የሚያስገቡ መስኮቶች፣ እና
2. በሌሊት መጽሐፍ ለማንበብ የሚያስችል የዐይንን ጤንነት የማይጐዳ መብራት፣ ያሏቸው መሆን ይኖርባቸዋል።

7. <u>ስለልብስ</u>

1. ማንኛውም ታራሚ በማረሚያ ቤቱ የተዘጋጀውን ልብስ መልበስ አለበት፡፡
2. በጤና ምክንያት ሐኪም ካዘዘ ወይም አስተዳዳሩ ከፈቀደ ተጨማሪ ልብስ ለታራሚ ሊሰጥ ይችላል፡፡

8. <u>ስለመኝታ</u>

1. ማንኛውም ታራሚ አስፈላጊ የሆነውን መኝታና የመኝታ ልብስ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡
2. በጤና ምክንያት ሐኪም ካዘዘ ወይም አስተዳዳሩ ከፈቀደ ተጨማሪ መኝታና የመኝታ ልብስ ለታራሚ ሊሰጥ ይችላል፡፡

9. <u>ስለጽዳት</u>

ታራሚዎች በየጊዜው ንጽሕናቸውን የሚጠብቁበት በቂ ውሃና የንጽሕና መጠበቂያ ቁሳቁስ እንዲሁም የመጸዳጃ ቤት እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡

10. <u>ስለምግብ</u>

1. ማንኛውም ታራሚ ለጤንነት የሚስማማና የተመጣጠነ በቂ ምግብ በማረሚያ ቤቱ ይቀርብለታል፡፡
2. በሕመም ምክንያት ሐኪም ካዘዘ ለታራሚው ልዩ ምግብ ይቀርብለታል፡፡
3. ማንኛውም ታራሚ በቂና ንጹህ የመጠጥ ውሃ ይቀርብለታል።

11. <u>ስለህክምና</u>

1. ታራሚዎች ነፃ የህክምና አገልግሎት የማግኘት መብት አላቸው፡፡
2. ማንኛውም ማረሚያ ቤት አቅም በፈቀደ መጠን የህክምና መስጫ ጣቢያ፣ የተሟሉ የህክምና መሳሪያዎች፣ መድሃኒቶችና የህክምና ባለሙያዎች ይኖሩታል።

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ ቢኖርም፣ ማንኛውም መድሃኒት የህክምና ኃላፊ ካልፈቀደ በስተቀር ወደ ማረሚያ ቤት እንዲገባ ወይም ታራሚዎች እንዲጠቀሙበት አይደረግም።
4. ማንኛውም የህክምና ኃላፊ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ማንኛውም ታራሚ ወደ ሌላ የህክምና ተቋም ተልኮ እንዲታከም ሃሳብ ያቀርባል። ማረሚያ ቤቱም ከሃኪሙ በቀረበው ሃሳብ መሠረት ታራሚው ወደ ሌላ ህክምና ተቋም ተዛውሮ እንዲታከም ያደርጋል፡፡
5. የማረሚያ ቤቱ የንጽህና ሁኔታና የምግቡ የጥራት ደረጃ በህክምና ኃላፊ ቁጥጥር ይደረግበታል። መስተካከል የሚገባው ካለም የህክምና ኃላፊ እያጠና ለአስተዳደሩ ሃሳብ ያቀርባል፤ አፈፃፀሙንም ይከታተላል።
6. ማንኛውም የህክምና ኃላፊ የዲስፒሊን ቅጣት የተወሰነበት ታራሚ ቅጣቱ ለጤንነቱ ጎጂ መሆኑን ካረጋገጠ ቅጣቱ እንዲቀነስለት ወይም እንዲቀርለት ለማረሚያ ቤቱ ሃሳብ ያቀርባል።
7. ነፍሰ ጡር የሆነች ታራሚ የመውለጃ ቀኗ ሲደርስ በተቻለ መጠን በቂ የህክምና አገልግሎት ወደሚገኝበት ተቋም ተወስዳ እንድትወልድ ይደረጋል፡፡ ሆኖም ህፃኑ በማረሚያ ቤቱ ውስጥ የተወለደ ከሆነ ይኸው ሁኔታ በልደት የምስክር ወረቀቱ ላይ አይጠቀስም፡፡

12.<u>ስለነፍሰጡርና እመጫት ታራሚ ሴት</u>

1. ሴት ታራሚ እድሜው 18 ወር ያልበለጠው ሕፃን ይዛ ከመጣችና ለልጁ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ሕፃኑ በማረሚያ ቤቱ ውስጥ ከእናቱ ጋር እንዲቆይ ይደረጋል፡፡
2. ሕጻኑ በማረሚያ ቤት ቆይታው አስፈላጊውን ምግብ፣ ክትባት፣ ሕክምና እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡
3. ሕፃኑ በማረሚያ ቤት በመቆየቱ በአካሉ ወይም በሥነ ልቦናው ችግር የሚያመጣበት ሆኖ ሲገኝ ለቅርብ ዘመድ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡ ሆኖም የቅርብ ዘመድ የማይገኝ ከሆነ ሕጻኑ ሌላ አሳዳጊ የሚያገኝበትን ሁኔታ አስተዳደሩ ያመቻቻል።
4. ነፍሰ ጡር ወይም እመጫት የሆነች ታራሚ በሀኪም ትዕዛዝ ተጨማሪ ምግብ እንድታገኝ ይደረጋል፡፡

13.**<u>ከጎብኚዎች ጋር ስለሚደረግ ግንኙነት</u>**

1. ታራሚዎች ከትዳር ጓደኞቻቸው፣ ከቅርብ ዘመዶቻቸው፣ ጓደኞቻቸው፣ ከሐኪሞቻቸው፣ ከሕግ አማካሪዎቻቸውና ከሃይማኖት አባቶቻቸው ጋር የመገናኘት መብት ይኖራቸዋል። ዝርዝር አፈጻፀሙ አስተዳደሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡
2. የውጭ ዜጋ የሆነ ታራሚ በአገሩ ኤምባሲ ወይም ቆንሲላ እንዲጐበኝ ይፈቀድለታል፡፡

14.**<u>ጎብኚዎችን ስለመፈተሽ</u>**

1. ታራሚዎችን ለመጠየቅ ወደ ማረሚያ ቤት የሚመጣ ማንኛውም ጐብኚ መታወቂያውን በማሳየት በተመሳሳይ ፆታ በማረሚያ ጠባቂ ተፈትሾ እንዲጐበኝ ይደረጋል፡፡
2. ማንኛውም ጐብኝ እንዲፈተሽ ተጠይቆ ፈቃደኛ ካልሆነ ታራሚዎችን እንዲጐበኝ አይፈቀድለትም።
3. ማንኛውም ጐብኚ ታራሚዎችን ጐብኝቶ ሲወጣ መፈተሽ ይኖርበታል፡፡

15.**<u>ጐብኝና ታራሚዎችን ስለመቆጣጠር</u>**

1. ታራሚዎች ከጐብኝዎቻቸው ጋር በሚነጋገሩበት ጊዜ ለጥበቃ ሥራ ተቃራኒ የሆነ ተግባር እንዳይፈጸም ቁጥጥርና ክትትል ይደረጋል፡፡
2. ማንኛውም ታራሚ ከሕግ አማካሪው ወይም ከጠበቃው ወይም ማረሚያ ቤቱን ለመቆጣጠር ሥልጣን ከተሰጠው ኃላፊ ጋር ግንኙነት ሲያደርግ በማረሚያ ጠባቂዎች እይታ ሥር ሆኖ ንግግሩን በማያዳምጡበት ሁኔታ ይካሄዳል፡፡

16.**<u>ታራሚዎችን ስለሚጠይቁ ህፃናት</u>**

እድሜው ከዘጠኝ አመት በታች የሆነ ማንኛውም ሕፃን ከአዋቂ ሰው ጋር ካልሆነ በስተቀር ታራሚን እንዲጠይቅ አይፈቀድለትም።

17.**<u>ታራሚዎች በአንድ ቦታ በህብረት እንዲጎበኙ ስለማድረግ</u>**

ታራሚዎች በየክፍላቸው እንዲጐበኙ ለማድረግ አመቺ ባልሆነ ጊዜ የማረሚያ ቤቱ ኃላፊ ሲፈቅድ በአንድ ቦታ በሕብረት እንዲጐበኙ ሊደረግ ይችላል፡፡

18.**<u>ስለመጻጻፍ</u>**

ታራሚዎች ከማረሚያ ቤቱ ውጭ ካሉ ሰዎች ጋር መጻጻፍ ይፈቀድላቸዋል። ሆኖም ለጥበቃ ሥራ ተቃራኒ የሆነ ተንግር እንዳይፈጸም በጽሑፎቹ ላይ ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

19.**ስለዝውውር ጥያቄ**

ማንኛውም ታራሚ የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘ ከሆነና በሌላ ክስ የማይፈለግ ከሆነ ቤተሰቦቹ በሚኖሩበት አካባቢ ወደሚገኝ ማረሚያ ቤት እንዲዛወር ካመለከተ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡ ቤተሰቦቹም እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡

20.**ስለፖሊስ ምርመራና የፍርድ ቤት መጥሪያ**

1. የፍርድ ቤት ትእዛዝ የያዘ ማረሚያ ቤት በመግባት ታራሚን መመርመር ይችላል፡፡
2. ማንኛውም ሰው ማረሚያ ቤቱ ሲፈቅድ በሥራ ሰዓት ወደ ማረሚያ ቤት በመግባት ለታራሚ የፍርድ ቤት መጥሪያ መስጠት ይችላል፡፡

21.**የታራሚን ሞት ስለማሳወቅ**

ማረሚያ ቤቱ በሞት የተለየ ታራሚ ሲኖር፣

1. የሞተበትን ምክንያት ከነሐኪም ማስረጃው ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ያሳውቃል፡፡
2. ታራሚው መሞቱን ለቤተሰቡ ወይም ለዘመዱ ያሳውቃል፤ አስክሬኑንም ለቤተሰቡ ወይም ለዘመዱ ይሰጣል፡፡ ሆኖም የሟቹን አስከሬን የሚወስድ ቤተሰብ ወይም ዘመድ ካልተገኘ በሚመለከተው ማዘጋጃ ቤት አማካይነት እንዲቀበር ይደረጋል፡፡

22.**ስለኑዛዜ**

ማንኛውም ታራሚ ኑዛዜ ለማድረግ ሲጠይቅ ማረሚያ ቤቱ አስፈላጊው ሁኔታ እንዲመቻችለት ያደርጋል።

23.**ስለትምህርት እና ስልጠና**

1. ታራሚዎች የቀለም ትምህርትና ልዩ ልዩ የሙያ ሥልጠና እንዲከታተሉ ይደረጋል፡፡ ሆኖም ማንበብና መጻፍ የማይችሉ ታራሚዎች እንዲማሩ ቅድሚያ ይሰጣቸዋል።
2. የትምህርትና ሥልጠና አሰጣጡ ሥልጣን ባለው አካል በወጣው ሥርአተ ትምህርት መሠረት ይሆናል፡፡
3. ማንኛውንም ትምህርት ወይም ሥልጠና የሚከታተሉ ታራሚዎች ሥልጣን በተሰጠው አካል እውቅና ያለው ፈተና ተፈትነው ካለፉ የትምህርት ማስረጃ ይሰጣቸዋል።
4. ሴትና ወጣት ታራሚዎች የትምህርት እድል እንዲያገኙ ልዩ ትኩረት ይደረጋል፡፡

## 24.ስለሰውነት ማጠናከርያ ትምህርትና መዝናኛ

1. ማንኛውም ማረሚያ ቤት ታራሚዎች አስፈላጊና ተስማሚ የሆነ የሰውነት ማጠንከሪያ ትምህርትና እንቅስቃሴ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡
2. ማረሚያ ቤቱ ታራሚዎች በተለያዩ የተሃድሶና የመዝናኛ እንቅስቃሴዎች እንዲሳተፉ ለማስቻል የሚያስፈልገውን ዝግጅት ያሟላል፡፡

## 25.ስለምክር አገልግሎት

ታራሚዎች በማረሚያ ቤት የቆይታ ጊዜያቸው የባህሪ ለውጥ በማምጣት እሥራታቸውን ጨርሰው ሲወጡና ከሕብረተሰቡ ሲቀላቀሉ ሕግ አክባሪና አምራች ዜጋ እንዲሆኑ የሚያስችላቸውን የምክር አገልግሎት በባለሙያ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

## 26.ስለእምነት ነጻነት

1. ማንኛውም ታራሚ በማረሚያ ቤት የቆይታ ጊዜው የእምነት ነፃነቱ የተጠበቀ ነው፡፡
2. የአንድ ታራሚ ሃይማኖት ወደ ማረሚያ ቤት ሲገባ ያስመዘገበው ሃይማኖት ይሆናል፡፡ ሆኖም በማረሚያ ቤቱ ቆይታ ጊዜው ሃይማኖቱን ከለወጠ ይህንኑ ማስመዝገብ ይችላል፡፡
3. ማንኛውም ታራሚ መንፈሳዊ መጻሕፍቶችን፣ መጽሔቶችንና ጽሁፎችን የማግኘትና የማንበብ እንዲሁም መንፈሳዊ በዓላትን የማክበር መብት ይኖረዋል።

## 27.መረጃ የማግኘት መብት

1. ማንኛውም ታራሚ ወደ ማረሚያ ቤት በሚገባበት ጊዜ የማረሚያ ቤቱ የስነ ሥርዓት ደንቦች በቃል ወይም በጽሁፍ ይገለፅለታል፡፡
2. ታራሚው አንብቦ መረዳት የማይችል ከሆነ መረጃው በተሟላ አኳኋን በሚገባው ቋንቋ በቃል ይገለፅለታል፡፡

## 28.አቤቱታ የማቅረብ መብት

1. ማንኛውም ታራሚ በጽሁፍ ወይም በቃል ደረጃውን ጠብቆ አቤቱታ የማቅረብ መብት ይኖረዋል።
2. ታራሚው የሚያቀርበው አቤቱታ በአስቸኳይ ውሳኔ አግኝቶ ውጤቱ ለታራሚው ይነገረዋል፡፡
3. በተሰጠው ውሳኔ የማይስማማ ከሆነ ቅሬታውን ለሚመለከተው ኃላፊ የማቅረብ መብት አለው፡፡

29.<u>ስለታራሚዎች ግዴታ</u>

ታራሚዎች ስለ ጥበቃ ሥራ፣ ስለሥነ-ሥርዓት አከባበር፣ ስለጽዳት፣ ስለጤና አጠባበቅ፣ ስለማህበራዊ ግንኙነትና ስለሌሎች ጉዳዮች የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን የማክበር ግዴታ አለባቸው።

30.<u>ስለስራ አመዳደብ</u>

1. ታራሚዎች እንደየሥራ ችሎታቸው፣ ሙያቸውና ጠባያቸው እየታየ የሥራ ደረጃ ወጥቶላቸው እንዲሠሩ ይደረጋል፤ ለሚሠሩት ሥራም ክፍያ ይከፈላቸዋል፡፡
2. ታራሚው በቂ ችሎታ የሌለው ከሆነ ልምምድ እንዲያደርግና አስፈላጊ ትምህርት እንዲሠጠው ይደረጋል።

31.<u>እንዲሰሩ ስለማይገደዱ ታራሚዎች</u>

1. የዚህ ደንብ አንቀጽ 32 ድንጋጌ ቢኖርም፣

   ሀ/ የሞት ፍርድ የተፈረደባቸው ሰዎች፣

   ለ/ ሴት ታራሚዎች ከእርግዝናቸው ከ6 ወር ጀምሮ እንዲሁም ከወለዱ በኋላ እስከ 2 ወር ድረስ፣

   ሐ/ እድሜአቸው ከ60 አመት በላይ የሆኑ ወንድ ታራሚዎችና ከ50 አመት በላይ የሆኑ ሴት ታራሚዎች፣ እና

   መ/ በቀጠሮ ላይ ያሉ ሰዎች፣ እንዲሠሩ አይገደዱም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ለ)፣ (ሐ) እና (መ) የተጠቀሱት ሰዎች ለመሥራት እንደማይገደዱ ተገልጾላቸው ለመሥራት ከጠየቁ ሥራው ጤንነታቸውን የሚጐዳ ካልሆነ በስተቀር ከመስራት አይከለከሉም።

32.<u>መሟላት ስለሚገባቸው ሁኔታዎች</u>

1. ታራሚዎች ለስራ የሚሰማሩት፣

   ሀ/ የሥራው ሁኔታ ለጥበቃ አመቺ መሆኑ ሲታመን፣ እና

   ለ/ የጤና ሁኔታቸው አስተማማኝ መሆኑን የህክምና ሀላፊው ሲያረጋግጥ፣ ይሆናል።
2. ማንኛውም ታራሚ ጎጂ በሆነና ጭካኔ በተሞላበት አኳኋን እንዲሁም በቀን ከ7 ሰዓትና በሣምንት ከ6 ቀናት የበለጠ እንዲሠራ አይደረግም።

33.<u>ያለክፍያ ስለሚሰራ ስራ</u>

1. ታራሚዎች በግል ወይም በቡድን ተደራጅተው ለታራሚዎች ጥቅምና ማህበራዊ አገልግሎት የሚሰሩትን ሥራ አስተዳደሩ ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

2. ታራሚዎች በጋራ የሚገለገሉበትን ማንኛውም ሥራ ያለክፍያ የመስራት ግዴታ አለባቸው።

34.<u>ከማረሚያ ቤት ውጪ ስለመስራት</u>

1. ፍርደኛ ታራሚዎች ከማረሚያ ቤት ወጥተው እንዲሰሩ አይፈቀድላቸውም፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ቢኖርም ማረሚያ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ታራሚው ከማረሚያ ቤት ወጥቶ እንዲሠራ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡ የክፍያ አፈጻፀሙም በአካባቢው የገበያ ዋጋ ላይ ተመስርቶ ማረሚያ ቤቱ በሚያደርገው ስምምነት መሠረት ይወሰናል፡፡
3. ታራሚዎች ከማረሚያ ቤት ወጥተው በመሥራት ከሚያገኙት ገቢ ላይ ለማረሚያ ቤቱ ስለሚከፈልበት ሁኔታ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

35.<u>ገንዘብ ስለማስቀመጥ</u>

ማንኛውም ታራሚ የሚያገኘው ገንዘብ በስሙ የተመዘገበ ደረሰኝ እየተሰጠው በማረሚያ ቤቱ ወይም ለበለጠ ጥንቃቄ አመቺ በሆነ ስፍራ ሊቀመጥ ይችላል፡፡ ካስቀመጠው ገንዘብ ላይ እንዲሰጠው ሲጠይቅም ይከፈለዋል።

36.<u>የዲሲፕሊን ቅጣት አይነቶች አመዳደብ</u>

1. የዲሲፕሊን ጉድለት የፈፀመ ታራሚ እንደ ጥፋቱ ክብደት ከሚከተሉት አንዱ ሊወሰንበት ይችላል፡፡

   ሀ/ ለብቻው ወይም በታራሚዎች ፊት የቃል ማስጠንቀቂያ መስጠት፣

   ለ/ ከአንድ ወር ላልበለጠ ጊዜ በጐብኚዎች እንዳይጐበኝ ወይም ደብዳቤ እንዳይልክና እንዳይቀበል ወይም ወደ ቤተመጻሕፍት እንዳይገባ ወይም በአንድነት ከሚደረግ ዝግጅትና መዝናኛ እንዳይካፈል መከልከል፣

   ሐ/ ከስምንት ቀን ላላነሰ ከሁለት ወር ላልበለጠ ጊዜ ለብቻው ለይቶ ማሰር፣

   መ/ ከአንድ ወር ላላነሰና ከአራት ወር ላልበለጠ ጊዜ በፊደል ተራ /ለ/ ከተዘረዘሩት የቅጣት አይነቶች በአንዱ መቅጣት፣

   ሠ/ ከሁለት ወር ላላነሰ ከአራት ወር ላልበለጠ ጊዜ ለብቻው ለይቶ ማሰር፣

   ረ/ ከሚያገኘው የጉልበት ዋጋ ክፍያ አንድ ሶስተኛ ከ6 ወር ላልበለጠ ጊዜ በመቀነስ ለማረሚያ ቤቱ ገቢ እንዲሆን ማድረግ፣

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ሐ) የተዘረዘሩት ቀላል የዲሲፕሲን ቅጣቶች፣ ከፊደል ተራ (መ) እስከ (ረ) የተሠሩት ከባድ የዲሲፕሲን ቅጣቶች ተብለው ይመደባሉ።

37.<u>ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስከትሉ ጥፋቶች</u>

የሚከተሉት ጥፋቶች ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣት ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡

1. በሥራ ላይ መለገም፣
2. ስንፍና፣
3. ግዴለሽነት፣
4. ሣይታመሙ ታምሚያለሁ ብሎ መተኛት፣
5. ቸልተኝነት፣
6. እምቢተኛነት ማሳየት፣
7. በማንኛውም ሰው ላይ በአጋጣሚ ወይም በድንገት የእጅ እልፊት ተግባር መፈፀም፣
8. ከሰው ጋር እንዳይገናኝ ከተከለከለ ታራሚ ጋር ያለ ፈቃድ መገናኘት፣
9. ያለ ፈቃድ ከመኝታ ክፍል መውጣት፣
10. ያለ ፈቃድ ከሥራ ቦታ መነሳት፣
11. ያለ ፈቃድ መገኘት ከሚገባው ቦታ ሣይገኝ መቅረት፣
12. የሐሰት አቤቱታ ማቅረብ፣
13. በማንኛውም መንገድ ፀጥታ መንሳት፣
14. ቁማር መጫወት፣
15. ከተወሰነ ቦታ ውጪ መጸዳዳት፣
16. የታራሚዎችን ክፍል ወይም የማረሚያ ቤቱን ቅጥር ግቢ ማቆሸሽ፣
17. በማረሚያ ቤቱ ቅጥር ግቢም ሆነ ከማረሚያ ቤቱ ውጪ መለመን እና
18. ክብደታቸው ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ጋር የሚመጣጠን የዲሲፕሊን ጥፋቶች መፈፀም፣

38.<u>ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስከትሉ ጥፋቶች</u>

የሚከተሉት ጥፋቶች ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡

1. አድማ ማድረግ፣ ወይም አድማ እንዲደረግ ማነሳሳት፣
2. ሁከት ወይም ሽብር መፍጠር፣
3. ከማረሚያ ቤት ለማምለጥ መሞከር ወይም ማምለጥ፣

4. ተደጋጋሚ መጥፎ ፀባይ ማሳየት፣
5. ራስን የማጥፋት ሙከራ ማድረግ፣
6. የተከለከሉ ነገሮችን ወደ ማረሚያ ቤት ማስገባት ወይም መስጠት ወይም መቀበል፣
7. መደለያ መስጠት ወይም መቀበል፣
8. ስርቆት፣
9. በሀሰት መመስከር ወይም መክሰስ፣
10. ዝሙት መፈፀም፣
11. በንብረት ላይ ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ፣
12. ከባድ የሆነ የእጅ እልፊት መፈፀም፣
13. የኃይል ተግባር መፈፀም ወይም በድርጊቱ መካፈል፣
14. የአስተዳደሩን ወይም የማረሚያ ቤቱን ኃላፊዎች፣ ሠራተኞችና የጥበቃ አባሎች መስደብ፣ ዛቻ፣ በንግግር፣ በተግባር ወይም በሌላ አኳኋን ለመልካም ፀባይ ተቃራኒ የሆነ ተግባር መፈፀም እና
15. ክብደታቸው ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ጋር የሚመጣጠን የዲሲፕሊን ጥፋቶች መፈጸም፤

39. <u>ስለዲሲፕሊን ቅጣት አወሳሰን</u>

1. የዲሲፕሊን ጥፋት በፈፀሙ ታራሚዎች ላይ ማረሚያ ቤቱ በዚህ ደንብ መሠረት ተገቢውን የዲስፕሊን ቅጣት ሊወስን ይችላል፡፡
2. ማንኛውም የዲስፕሊን ቅጣት ከመወሰኑ በፊት ታራሚው ፈጸመ የተባለው ጥፋት ተገልጾለት መልስ እንዲሰጥበት እድል ይሰጠዋል።
3. የዲስፕሊን እርምጃ ለታራሚ የሚገለጸው በጽሁፍ ሆኖ የይግባኝ እድሉን ጭምር የሚያመለክት መሆን አለበት፡፡

40. <u>በታራሚ ስለሚፈጸም ወንጀል</u>

ማንኛውም ታራሚ በማረሚያ ቤት ቆይታው የወንጀል ድርጊት ቢፈጽም ወይም ከማረሚያ ቤት ቢጠፋ በወንጀል ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

41. <u>ባመለጡ ታራሚዎች ላይ ስለሚወሰድ እርምጃ</u>

1. ከማረሚያ ቤት ያመለጠ ታራሚ በፈጸመው የማምለጥ ወንጀል ጉዳዩ በፖሊስ ተጣርቶ ክስ እንዲመሠረትበት ይደረጋል፡፡

2. ታራሚው ከማምለጡ በፊት ከነበረበት የሥራ መደብ ዝቅ ባለ የሥራ ደረጃ እንዲመደብ ይደረጋል፡፡ የማምለጡ ጉዳይም በማረሚያ ቤቱ ተመዝግቦ ይያዛል፡፡
3. ታራሚው ከማረሚያ ቤት አምልጦ ውጭ የቆየበት ጊዜ ሲፈጸም ከነበረው ቅጣት ላይ ቅናሽ አይደረግለትም፡፡

42.<u>በታራሚዎች ላይ ስለሚጣሉ ቅጣቶች አፈጻጸም</u>

ማንኛውም ታራሚ የእስራት ቅጣት በመፈፀም ላይ እያለ በሌላ የወንጀል ጥፋት ምክንያት የቅጣት ውሳኔ ከተላለፈበት የተጣለበት የእስራት ቅጣት የሚፈፀመው የመጀመሪያው ቅጣት ከተፈፀመ በኋላ ነው፡፡

43.<u>ስለቅጣት መጀመሪያና መጨረሻ ጊዜ</u>

1. የእሥራት ቅጣት ጊዜ የሚጀመረውና የሚፈፀመው ቅጣቱን የወሰነው ፍርድ ቤት በሰጠው ትእዛዝ መስረት ይሆናል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ታራሚው በአመክሮ፣ በይቅርታ ወይም በምህረት ከእሥር ሊፈታ ይችላል፡፡

44.<u>ስለማረሚያ ቤቱ ግዴታ</u>

1. ማንኛውም ታራሚ የእሥራት ጊዜውን ሲጨርስ፣ ይቅርታ ወይም ምህረት ሲያገኝ ወይም ፍርድ ቤት በአመክሮ እንዲፈታ ትዕዛዝ ሲሰጥ ማረሚያ ቤቱ ታራሚውን ወዲያው የመፍታት ግዴታ አለበት፡፡
2. ታራሚዎች የእስራት ጊዜያቸውን ሲፈጽሙ መፈታት እንዲችሉ የሚመለከታቸውን ኃላፊዎች የግል ማህደሮቻቸውን በየጊዜው መመርመር አለባቸው።

45.<u>ስለእስራት ቅናሽ</u>

1. ታራሚው የእሥራት ቅናሽ ተደርጎለት እንደሆነ ቅናሹ የሚደረገው በጠቅላላው ከተፈረደበት የእሥራት ጊዜ ላይ ይሆናል፡፡
2. ታራሚው በገንዘብና በእሥራት እንዲቀጣ ሲፈረድበት ወይም ገንዘቡን መክፈል ባለመቻሉ የእሥራት ቅጣት ሲፈረድበት ቅናሽ የሚደረገው በማረሚያ ቤቱ እንዲፈጸም ከታዘዘው ቅጣት ላይ ብቻ ነው።
3. በማንኛውም የሕክምና ተቋም ገብቶ በመታከም ላይ የሚገኝ ታራሚ በማረሚያ ቤት እንዳለ ይቆጠራል።
4. ታራሚው ወደ ማረሚያ ቤት ሲገባ የእሥራት ቅናሽ ሊያገኝ የሚችልበት ሁኔታ ይገልጽለታል።

5. በማንኛውም ምክንያት የእሥራት ቅናሽ እንዲያገኝ በሚደረግበት ጊዜ አስተዳደሩ ታራሚው እንዲያውቀው ማድረግ አለበት፡፡
6. በታራሚው ላይ የተጣለበት ቅጣት፣ የተፈቀደለት ወይም የተከለከለው የእሥራት ቅናሽ እና የእሥራቱ ዘመን የሚያልቀበት ጊዜ በግል ማህደሩ ተመዝግቦ ይቀመጣል።

46.<u>አመክሮ ስለሚጠየቅላቸው ታራሚዎች</u>

ማንኛውም ታራሚ፣

1. በማረሚያ ቤት መልካም ጠባይ ካሳየ፣
2. ከተፈታ በኋላ መልካም ውጤት ሊያስገኝ ይችላል ተብሎ ከተገመተ፣
3. በፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረት የሚፈለግበትን ማንኛውንም ክፍያ አጠናቅቆ ከፈጸመ፣
4. ሁለት ሦስተኛውን የእሥራት ቅጣት ከፈጸመ ወይም የእድሜ ልክ እሥራት ተፈርዶበት ሃያ አመት ከታሠረ፣ እና
5. ለማሕበራዊ ኑሮ መልካም ዝንባሌ የሚያሳይ ከሆነ፣ አመክሮ ይጠየቅለታል።

47.<u>የአመክሮ ኮሚቴ ስለማቋቋም</u>

1. በአመክሮ ሊፈቱ የሚችሉ ታራሚዎችን ጉዳይ የሚያጠና አንድ ሰብሳቢና አራት አባላት ያሉት ኮሚቴ ይቋቋማል፡፡
2. ኮሚቴው የሚያቀርበው ሃሣብ በማረሚያ ቤቱ ዋና አስተዳዳሪ ጸድቆ ለመጨረሻ ውሣኔ አግባብ ላለው ፍርድ ቤት ይቀርባል፡፡

48.<u>ይቅርታ ስለሚጠየቅላቸው ታራሚዎች</u>

ታራሚዎች በማይድን ሕመም፣ በእድሜ መግፋት ወይም በማረሚያ ቤት ቆይታቸው በሚያሳዩት የባህሪ ለውጥ ምክንያት ይቅርታ ሊጠየቅላቸው ይችላል፡፡

49.<u>ታራሚዎች ከእስር ሲፈቱ ሊሟሉ ስለሚገባቸው ሁኔታዎች</u>

1. ማንኛውም ታራሚ በአመክሮ፣ በይቅርታ፣ በምህረት ወይም የእሥራት ጊዜውን ጨርሶ ከእሥር ሲፈታ በማረሚያ ቤት ያስቀመጠውን ገንዘብ፣ ልብስ ወይም ዕቃ ካለ ደረሰኝ ፈርሞ ይወስዳል ወይም ለሚወክለው ሰው ወይም ድርጅት ይሰጥለታል፡፡
2. ታራሚው ሲፈታ ገንዘብ የሌለው መሆኑ ከተጣራ በኋላ ወደ ቀድሞ መኖሪያ ቦታው ለመመለስ የሚያስችለው ለመጓጓዣና ለስንቅ የሚሆን ገንዘብና ልብስ ማረሚያ ቤቱ ይሰጠዋል።

3. ማንኛውም ታራሚ ከእሥር ሲፈታ ማረሚያ ቤቱ ከእሥር የተፈታ መሆኑን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል።

50. <u>**የታራሚዎች መዝገብ ስለማቋቋም**</u>

የታራሚዎች የሕይወት ታሪክና ቅጣት የሚመዘገብበት መዝገብ ይቋቋማል፡፡

51. <u>**መመሪያ ስለማዉጣት**</u>

አስተዳደሩ ይህን ደንብ በአግባቡ ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑትን መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

52. <u>**ተፈጻሚት ስለማይኖራቸው ደንቦችና መመሪያዎች**</u>

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ደንብ ወይም መመሪያ በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

53. <u>**ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ 16 ቀን 1999 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

# አዋጅ ቁጥር 840/2006 ዓ.ም

## የይቅርታ አሰጣጥና አፈጻፀም ሥነ-ሥርዓት አዋጅ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት በሕግ መሠረት ይቅርታ እንደሚያደርግ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 71(7) የተደነገገ በመሆኑ፤

የይቅርታ አሰጣጥ እና አፈፃፀም ሥነ-ሥርዓትን የበለጠ ውጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ ሲሠራበት በቆየው ሕግ አፈጻጸም ወቅት የተገኙ ልምዶችን ማካተት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 55(1) እና አንቀጽ 71(7) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የይቅርታ አሰጣጥና አፈፃፀም ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 840/2006 ተብሎ ሊጠቀሱ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

   1. "ይቅርታ" ማለት የቅጣት ፍርድ በሙሉ ወይም በከፊል ቀሪ እንዲሆን ወይም የቅጣት ፍርዱ አፈጻጸምና ዓይነት ቀለል ተደርጎ እንዲፈፀም ማድረግ ነው፣
   2. "የቅጣት ፍርድ" ማለት በወንጀል ጉዳይ ዋና ቅጣትን፣ ተጨማሪ ቅጣትን ወይም የክልከላ እና የጥበቃ ጥንቃቄ እርምጃን በተመለከተ በፍርድ ቤት የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ነው፤
   3. "ፍርድ ቤት" ማለት የፌደራል ፍርድ ቤት ሲሆን በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 78(2) መሠረት የፌደራል ጉዳዮችን የሚያስተናግድ የክልል ፍርድ ቤትን፣ የሞት ፍርድ የሰጠ የክልል ፍርድ ቤት እና ወታደራዊ ፍርድ ቤትን ይጨምራል፤
   4. "ፕሬዚዳንት" ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት ነው፤
   5. "ይቅርታ ጠያቂ" ማለት ይቅርታ የተጠየቀበት የቅጣት ፍርድ የሚመለከተው ሰው ነው፤

6. “ማረሚያ ቤት” ማለት በፌዴራል ወይም በክልል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ሥር የሚተዳደር ማረሚያ ቤት ሆኖ የወታደራዊ ማረሚያ ቤትንም ይጨምራል፤
7. “ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት እንደቅደም ተከተሉ የፍትህ ሚኒስቴር[39] ወይም ሚኒስትር ነው፡
8. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
9. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል፡፡

3. <u>**የይቅርታ ዓላማ**</u>

የይቅርታ አሰጣጥ ዋና ዓላማ የህዝብ፣ የመንግስትና የታራሚዎችን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል መንግስት የወንጀል ጥፋተኞች በጥፋታቸው የተጸጸቱና የታረሙ መሆኑን በማረጋገጥ ወደ ህብረተሰቡ ተቀላቅለው አምራች ዜጋ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡

4. <u>**የተፈፃሚነት ወሰን**</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች፣ በወታደራዊ ፍርድ ቤቶች እንዲሁም በሕገመንግስቱ አንቀፅ 78(2) መሰረት የፌደራል ጉዳዮችን የሚያስተናግዱ የክልል ፍርድ ቤቶች በሰጧቸው የመጨረሻ የወንጀል ቅጣቶችና የሞት ፍርድ የሰጠ የክልል ፍርድ ቤት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ይቅርታን የሚሰጡና የሚያስፈጽሙ አካላት</u>

5. <u>**የፕሬዚዳንቱ ሥልጣን**</u>

1. ፕሬዚዳንቱ በሕገመንግስቱ አንቀፅ 71(7) እና በዚህ አዋጅ መሰረት ይቅርታ ያደርጋል፡፡
2. ፕሬዚዳንቱ በዚህ አዋጅ የሚካተቱ ጉዳዮችን እንደአስፈላጊነቱ አግባብ ላለው የክልል መንግሥት አካል የሥልጣን ውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

6. <u>**የይቅርታ ቦርድ**</u>

1. የይቅርታ ጥያቄዎችን የሚመረምርና ለፕሬዚዳንቱ የውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብ የይቅርታ ቦርድ (ከዚህ በኋላ “ቦርድ” እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡
2. የቦርዱ ተጠሪነት ለፕሬዚዳንቱ ይሆናል፡፡

---

[39] በአዋጅ ቁጥር 943/2008 መሰረት የፌዴራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ ሆኗል፡፡ ውስጥም በተመሳሳይ “የፍትህ ሚኒስቴር” የሚለው “የፌዴራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ” እንዲሁም “የፍትህ ሚኒስትር” የሚለው “ጠቅላይ አቃቤ” ህግ ተብሎ ይነበብ፡፡

7. **የቦርዱ አባላት**

ቦርዱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል:-

1. የፍትህ ሚኒስትር ....................... ሰብሳቢ፤
2. የፍትህ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ............................ ምክትል ሰብሳቢ፤
3. የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ............................... አባል፤
4. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ…..........አባል፤
5. የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር[40] ሚኒስትር ዴኤታ........................አባል፤
6. የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር[41] ሚኒስትር ዴኤታ ..... አባል፤
7. የአገር መከላከያ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ............................ አባል፤
8. የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር ጀነራል..................አባል፤
9. የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ምክትል ዋና ዳይሬክተር ............ አባል፤
10. ለሕገ-መንግስቱ ታማኝ የሆኑና መልካም ስነምግባር ያላቸው በሚኒስትሩ አቅራቢነት አብዛኛውን የህብረተሰብ ክፍል ከሚወክሉ አደረጃጀቶች በፕሬዚዳንቱ የሚመደቡ ሁለት ሰዎች ................................................ አባላት፡፡

8. **የቦርዱ አባላት**

ማንኛውም የቦርዱ አባል፡-

1. ለቦርዱ የተሰጡትን ሃላፊነቶች ለማሳካት ተገቢውን ጥረት የማድረግ፤
2. በቦርዱ ስብሰባዎች የመገኘት፤
3. በቦርዱ የሚቀርቡ ጉዳዮችን በአግባቡ የመመርመር፤
4. ከጥቅሙ ጋር የሚጋጭ ጉዳይ ሲያጋጥመው ለቦርዱ ሰብሳቢ በማሳወቅ ጉዳዩ በሚታይባቸው የቦርዱ ስብሰባዎች ያለመሳተፍ፤
5. በሚስጥር መጠበቅ ያለባቸውን ጉዳዮች ያለመግለጽ፤

ግዴታዎች አለበት፡፡

9. **የቦርዱ ስልጣንና ተግባር**

---

[40] በአዋጅ ቁጥር 916/2008 መሰረት የፌዴራልና አርብቶ አደር ጉዳዮች ልማት ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

[41] በአዋጅ ቁጥር 916/2008 መሰረት ይህ መኒስቴር መስሪያ ቤት የሴቶችና ህፃናት ሚኒስቴር እና የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ተብሎ ለሁለት ተከፍሏል፡፡

1. የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

   ሀ/ በዚህ አዋጅ መሰረት የሚቀርብለትን የይቅርታ ጥያቄ በመመርመር በቅድመ ሁኔታ ላይ ወይም ያለቅድመ ሁኔታ ተመስርቶ ይቅርታ እንዲሰጥ የውሳኔ ሃሳብ ለፕሬዚዳንቱ የማቅረብ፤

   ለ/ ለይቅርታ አሰጣጥ አስፈላጊ የሆኑና ነባራዊ ሁኔታን ያገናዘቡ መስፈርቶችን የማውጣት፤

   ሐ/ እንደ አስፈላጊነቱ ክሱን የተከታተለው የዐቃቤ ሕግ አካል፣ ማንኛውም ባለሥልጣን ወይም ግለሰብ በአካል በመቅረብ ወይም በጽሁፍ ሀሳብ እንዲያቀርብ የማድረግ፤

2. ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለክልል የይቅርታ ቦርዶች ወይም የይቅርታ ጥያቄን እንዲመረምሩ ለተመደቡ አካላት የስልጣንና ተግባር ውክልና ሊሰጥ ያችላል፡፡

10.<u>የቦርዱ ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር</u>

የቦርዱ ሰብሳቢ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የቦርዱን ሰብሳቢዎች በሊቀመንበርነት የመምራት፤
2. በቦርዱ ጽህፈት ቤት በኩል ይቅርታ የተደረገላቸው ሰዎችን በተመለከተ ለሚመለከታቸው አካላት የመግለጽ፤
3. ስለቦርዱ የሥራ አፈፃፀም በየስድስት ወሩ ለፕሬዚዳንቱ ሪፖርት የማቅረብ፤
4. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ይቅርታን አስመልክቶ የሚሰጡ ውሳኔዎች በመገናኛ ብዙሀን እንዲገለጹ የማድረግ፤ እና
5. በፕሬዚዳንቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተዝማጅ ተግባራት የማከናወን፡፡

11.<u>የቦርዱ ምክትል ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር</u>

1. የቦርዱ ምክትል ሰብሳቢ ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፡፡
2. የቦርዱ ምክትል ሰብሳቢ በሰብሳቢው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

12.<u>የቦርዱ ስብሰባዎች</u>

1. ቦርዱ በሰብሳቢው ጥሪ በማንኛውም ጊዜ ይሰበሰባል፡፡
2. ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

3. የቦርዱ ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ ያልፋል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

13.<u>የቦርዱ ጽህፈት ቤት</u>

1. የይቅርታ ቦርድ ጽህፈት ቤት (ከዚህ በኋላ "ጽህፈት" ቤት እየተባለ የሚጠራ) በሚኒስቴሩ ውስጥ ይደራጃል፡፡
2. ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-
   ሀ/ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚቀርቡ የይቅርታ ማመልከቻዎችን ይቀበላል፤ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ለቦርዱ ውሳኔ ያቀርባል፤
   ለ/ የቦርዱን መዛግብትና ሠነዶች በአግባቡ ይይዛል፣ ይጠብቃል፤
   ሐ/ በቦርዱ የውሳኔ ሀሳብ የተሰጠባቸውን ሁሉንም ጉዳዮችና በፕሬዚዳንቱ የጸደቁትን ውሳኔዎች በአግባቡ ይይዛል፣ ይጠብቃል፣ ስታትስቲክስ ያዘጋጃል፤
   መ/ የይቅርታ ጥያቄዎችን በሚመለከት በቦርዱም ሆነ በፕሬዚዳንቱ የሚሰጡ ውሳኔዎችን ይቅርታ ጠያቂው ለሚገኝበት ማረሚያ ቤት ያሳውቃል፤ አፈፃጸሙንም ይከታተላል፤ የይቅርታ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡
   ሠ/ ስለይቅርታ ውሳኔ ዋጋ ማጣትና የቅጣት ፍርድ አፈጻጸም መቀጠል በዚህ አዋጅ አንቀጽ 23(3) መሠረት በቦርዱ የሚሰጠውን ትዕዛዝ ለሚመለከታቸው ወገኖች ያስተላልፋል፡፡
   ረ/ ይቅርታዎችን በመዝገብ ያሰፍራል፤ መዝገቡን ይጠብቃል፤ አግባብነት ባለው ህግ መሠረት መዝገቡን ለህዝብ ክፍት ያደርጋል፤
   ሰ/ ከይቅርታ ጉዳዮች ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ሌሎች ሥራዎች ያከናውናል።

14.<u>የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት</u>

የቦርዱ ጽህፈት ቤት ኃላፊ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል:-

1. የጽህፈት ቤቱን ተግባርና ኃላፊነቶች በሥራ ላይ ያውላል፤
2. ለቦርዱ አባላት የስብሰባ ጥሪ ያስተላልፋል፤ ለአባላቱ አስፈላጊ የሆኑ ሠነዶች መድረሳቸውንም ያረጋግጣል፤
3. የቦርዱ ፀሐፊ ሆኖ ያገለግላል፤
4. ከቦርዱ ሰብሳቢ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የይቅርታ አሰጣጥና አፈፃፀም

### 15.የይቅርታ ጥያቄ ስለማቅረብ

1. በሌሎች ህገዞች የተደነገጉ ክልከላዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 3 የተደነገገውን ዓላማ ለማሳካት ቦርዱ በዚህ አዋጅ መሰረት የሚቀርቡለትን የይቅርታ ማመልከቻዎች ከመንግስትና ከህዝብ ጥቅም አንፃር በማመዛዘን ያስተናግዳል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የመጨረሻ የቅጣት ፍርድ የተሰጠበት ማንኛውም ሰው የይቅርታ ጥያቄውን ራሱ ወይም በባለቤቱ፣ በቅርብ ዘመዱ፤ በወኪሉ ወይም በጠበቃው አማካይነት ማቅረብ ይችላል፡፡
3. የይቅርታ ጥያቄውን ያቀረበው ታራሚው ራሱ፣ ጠበቃው ወይም ወኪሉ ካልሆነ በስተቀር በስሙ የይቅርታ ጥያቄ የቀረበለት ታራሚ በይቅርታ ጥያቄው የሚስማማ መሆኑን በማረጋገጥ በይቅርታ መጠየቂያ ማመልከቻው ላይ መፈረም አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም ሚኒስቴሩ ወይም የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው ደንብ ወይም መመሪያ ይቅርታ ሊደረግላቸው የሚገባቸውን ሰዎች በመምረጥ የይቅርታ ጥያቄ ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል፡፡
5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (4) መሰረት የሚቀርብ የይቅርታ ጥያቄ ለቦርዱ ከመቅረቡ በፊት ይቅርታ ለተጠየቀለት ሰው መድረስ አለበት፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) እና (5) በተደነገገው መሠረት ይቅርታ እንዲደረግለት የተጠየቀለት ሰው ይቅርታውን ለመቀበል የማይፈልግ መሆኑን የይቅርታ መጠየቂያው ደብዳቤ ቅጅ በደረሰው በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ለቦርዱ ካላስታወቀ በይቅርታ ጥያቄው እንደተስማማ ይቆጠራል።
7. ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት አጋጥሞት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) የጊዜ ገደብ ውስጥ የይቅርታ ማመልከቻውን ለመቀበል የማይፈልግ መሆኑን ለማስታወቅ

ያልቻለ ሰው ያጋጠመው ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ከተወገደበት ዕለት አንስቶ ባሉት 15 የሥራ ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ማስታወቅ ይችላል፡፡

16.<u>የይቅርታ ጥያቄ ይዘት</u>

1. በግለሰብ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን የቅጣት ፍርድን በሚመለከት የሚቀርብ የይቅርታ ጥያቄ የማከተሉትን መረጃዎች አሟልቶ መያዝ ይኖርበታል፡-

   ሀ/ የይቅርታ ጠያቂው ሙሉ ስም ከነአያት፣ የእናቱ ሙሉ ስም፣ ዕድሜ፣ ፆታ፣ ዜግነት ብሔር እና ከመታሰሩ በፊት የነበረው ሥራና አድራሻ፤

   ለ/ ለቅጣት ፍርዱ ምክንያት የሆነውን ወንጀል ከፈጸመበት ቀን ጀምሮ ወደ ኋላ ለሚቆጠሩ አምስት ዓመታት ይኖርበት የነበረውን አድራሻ፤

   ሐ/ የተከሰሰበት ወንጀል፣ ጥፋተኛ የሆነበት የወንጀል ሕግና የተወሰነበት ቅጣት የፈረደውን ፍርድ ቤት፣ የቅጣት ፍርዱ አፈፃፀም የሚገኝበት ደረጃ እና የክሱ መዝገብ ቁጥር፤

   መ/ የደንብ መተላላፍን ሳይጨምር ቀድሞ ተከሶ የተፈረደበት ወንጀል ካለ የወንጀሉን ዓይነት፣ የተወሰነው ቅጣት፣ የቅጣት ፍርዱ አፈፃፀም የሚገኝበት ደረጃ እና የቅጣት ፍርዱን ያስተላለፈው ፍርድ ቤት ስም፤

   ሠ/ የቅጣት ፍርዱን በመፈጸም ላይ የሚገኝበት የማረሚያ ቤት ወይም ተቋም ስም፤

   ረ/ ይቅርታ ሊደረግለት ይገባል የሚባልበትን ምክንያት፤

   ሰ/ የሚገኝበት ማረሚያ ቤት ወይም ተቋም ሥነ-ምግባሩን አስመልክቶ የሰጠውን አስተያየት፤

   ሸ/ ከቅጣት ፍርዱ በፊት ስለነበረው ሥነ-ምግባር ሊመሰክሩለት የሚችሉና ከይቅርታ ጠያቂው ጋር ምንም ዓይነት የሥጋ፣ የጋብቻ ወይም የጥቅም ግንኙነት የሌላቸውን የሦስት ሰዎች ሙሉ ስምና አድራሻ፤

   ቀ/ በፍርድ ቤት መቀጮ፣ የጉዳት ካሣ ወይም ሁለቱንም እንዲከፍል ተወስኖበት ከሆነ ስለመክፈሉ ወይም ያልከፈለ ከሆነ ያልከፈለበትን ምክንያት፤

   በ/ ቀደም ሲል ይቅርታ ተደርጎ እንደሆነ ወይም የይቅርታ ጥያቄ ቀርቦ ውድቅ ሆኖ እንደሆነ ውሳኔው የተሰጠበት ቀንና ዓመተ ምሕረት፤

   ተ/ የይቅርታ ጥያቄው በሌላ ሰው አማካይነት የሚቀርብ ከሆነ ይህንን ለመፈጸም መብት የሚሰጠውን ሕጋዊ ምክንያት፤

ቸ/ ከይቅርታ ጥያቄው ጋር በአባሪነት የተያያዙ ደጋፊ ሰነዶች ካሉ ዝርዝራቸውን፤

ኀ/ ከይቅርታ ጥያቄው ማመልከቻ ጋር ያልተያያዙ ደጋፊ ሰነዶች ካሉ የሚገኙበትን ቦታ፤ እና

ነ/ በዚህ አዋጅ መሠረት በወጣ ደንብ የተዘረዘሩ ሌሎች መረጃዎች፡፡

2. በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካልን በሚመለከት የሚቀርብ የይቅርታ ጥያቄ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተደነገጉት ውስጥ አግባብነት ያላቸውን ዝርዝሮች መያዝ አለበት፡፡

## 17.የይቅርታ ጥያቄ የማቅረቢያ ጊዜ

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15 መሠረት የይቅርታ ጥያቄ የሚያቀርብ ሰው የይቅርታ ጥያቄውን፡-

ሀ/ የቅጣት ፍርዱ ከተሰጠ በኋላ በማናቸውም ጊዜ፤

ለ/ የይቅርታ ጥያቄ አቅርቦ ጥያቄው ውድቅ ከተደረገ ከስድስት ወር በኋላ፤ ወይም

ሐ/ ቅጣቱ በከፊል ይቅርታ ተደርጎለት የነበረ እንደሆነ የይቅርታ ውሳኔ ውሣኔ ከተሠጠ ከአንድ ዓመት በኋላ፤

ማቅረብ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ለ) እና (ሐ) የተደነገገው ቢኖርም በአፋጣኝ ታይቶ ምላሽ ማግኘት ያለበት የይቅርታ ጥያቄ ከሆነና ከቦርዱ አባላት በሶስት አራተኛ ድምፅ ከተደገፈ በማናቸውም ጊዜ ሊቀርብ ይችላል፡፡

## 18.የይቅርታ ጥያቄን ስለመመርመር

ቦርዱ የይቅርታ ጥያቄ ሲቀርብለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16 ከተመለከቱት ዝርዝር መረጃዎች በተጨማሪ እንደአስፈላጊነቱ የዐቃቤ ሕግ እና የፍርድ ቤት መዝገቦችን እና ከማንኛውም ሰው የሚቀርቡለትን ወይም ራሱ የሚያገኛቸውን የይቅርታ ጥያቄውን የሚደግፉ ወይም የሚቃወሙ ማናቸውንም ማስረጃዎች ወይም መረጃዎች መመርመር ይኖርበታል፡፡

## 19.የምስክሮችና የባለሙያዎች

የይቅርታ ጥያቄን አስመልክቶ ለቦርዱ ምስክርነት ወይም የባለሙያ አስተያየት የሚሰጥ ማንኛዉም ሰው እውነትንና ሙያዊ ብቻ መሠረት አድርጎ ምስክርነቱን ወይም አስተያየቱን መስጠት አለበት፡፡

## 20.ለይቅርታ አሰጣጥ ከግምት ውስጥ መግባት ስላለባቸው ሁኔታዎች

ለይቅርታ አሰጣጥ የሚከተሉት ከግምት ዉስጥ መግባት አለባቸው፡-

1. የይቅርታ ጠያቂው የአደገኝነት ሁኔታ፤
2. የወንጀሉ ክብደት እና የይቅርታ ጠያቂው በማረፊያ ቤትና በማረሚያ ቤት የቆየበት ጊዜ፤
3. ይቅርታ ጠያቂው አስቀድሞ ይሠራበት ከነበረበት መሥሪያ ቤት፣ ይኖርበት ከነበረበት አካባቢ ማህበረሰብ፣ ከቤተሰብ፣ ከሐኪሙ ወይም ከሌሎች አግባብነት ካላቸው አካላት የተሰባሰቡ መረጃዎች፤
4. ይቅርታ ጠያቂው ለወደፊቱ በሠላም ለመኖር የሚያሳየውን ባህሪ፤
5. ይቅርታ ጠያቂው ጥፋተኝነቱን አምኖ በመቀበል የተጸጸተ መሆኑ፣ ከተጎጂ ወይም ከተጎጂ ወገን ቤተሰብ ጋር ለመታረቅና ያደረሰውን በደል ለመካስ ያደረገው ጥረት ወይም የተወሰነበትን ካሣ ለመክፈል ያለውን አቅምና ፍላጎት፤
6. ይቅርታ ጠያቂው በማረሚያ ቤት ቆይታው ወቅት ያሳየውን መልካም ዐባይና ሥነ-ምግባር፤
7. ተጎጂውን ወይም የተጎጂውን ቤተሰቦች ለማግኘት ከተቻለ የቀረበውን የይቅርታ ጥያቄ በሚመለከት ያላቸውን አስተያየት፤
8. የይቅርታ ጠያቂው የቤተሰብና የጤንነት አቋም እና የዕድሜ ሁኔታ፡፡

21.<u>የይቅርታ ውሳኔ ስለሚሰጥበት ስነስርዓት</u>

1. ቦርዱ የሚቀርብለትን የይቅርታ ማመልከቻ ይመረምራል፡፡
2. ቦርዱ ይቅርታ ይገባዋል የሚለውን ሰው ስም ከመግለጫው ጋር ለፕሬዚዳንቱ ያቀርባል፡፡
3. ፕሬዚዳንቱ የቀረበውን ስም እና መግለጫ መሰረት በማድረግ የመጨረሻውን የይቅርታ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

22.<u>የይቅርታ ውሳኔ የሚኖረው ውጤት</u>

1. በይቅርታ ውሳኔው በግልፅ ካልተመለከተ በስተቀር የይቅርታ ውሳኔው በፍርድ ቤት ውሳኔ የተሰጡትን ቅጣቶች በሙሉ የሚያስቀር ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የይቅርታ ውሳኔ ከወንጀል ውሳኔው የሚመነጩ የፍትሐብሔር ሃላፊነቶችን የሚያስቀር አይሆንም።
3. በይቅርታ ውሳኔው በግልፅ ካልተገለጸ በስተቀር ከይቅርታ ውሳኔው በፊት የተፈጸሙ ቅጣቶች የጸኑ ይሆናሉ።

23.<u>የይቅርታ ዋጋ ማጣት</u>

1. በሃሰተኛ ወይም በተጭበረበረ ማስረጃ ላይ ተመሥርቶ የተሰጠ ይቅርታ ዋጋ አይኖረውም፡፡
2. በቅድመ ሁኔታ ላይ ተመስርቶ የተሰጠ ይቅርታ ቅድመ ሁኔታው ከተጣሰ ዋጋ ያጣል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሠረት የይቅርታ ውሳኔ ዋጋ የማይኖረው መሆኑን ቦርዱ ሲያረጋግጥ የቅጣት ፍርዱ አፈጻጸም ከይቅርታው በፊት በነበረው ይዘቱ እንዲቀጥል ትዕዛዝ እንዲሰጥ ለፕሬዚዳንቱ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የሚተላለፈው የፕሬዚዳንቱ ትዕዛዝ የቅጣት ፍርዱን ለሚያስፈጽሙ አካላትና ይቅርታው ተደርጎለት ለነበረው ሰው እንዲደርስ ይደረጋል፡፡
5. ይቅርታ ተደርጎለት የነበረ ሰው ይቅርታ ተደርጎለት ከመለቀቁ በፊት በእስር ከነበረ ወደ ማረሚያ ቤት እንዲመለስ ለማድረግ የመያዣ ትዕዛዝ እንዲሰጥ ጥያቄ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይቀርባል፡፡
6. ፍርድ ቤቱ በሚሰጠው የመያዣ ትዕዛዝ መሰረት ይቅርታ ተደርጎለት የነበረ ሰው ወደ ማረሚያ ቤት እንዲመለስ ይደረጋል፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከተው የፕሬዚዳንቱ ትዕዛዝ የደረሰው ይቅርታ ተደርጎለት የነበረ ሰው የተሰጠው ትዕዛዝ እንደገና እንዲታይለት ውሳኔው ከደረሰው ቀን ጀምሮ ባሉት 15 የሥራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል፡፡
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (7) መሠረት የቀረበው አቤቱታ በቦርዱ ወድቅ ከተደረገ ይቅርታ ተደርጎለት የነበረ ሰው ተሰጥቶት የነበረውን የይቅርታ ምስክር ወረቀት ለጽህፈት ቤቱ መመለስ አለበት፡፡

24.<u>ይቅርታን ስለማስረዳት</u>

1. ማንኛውም ይቅርታ የተደረገለት ሰው ይቅርታ የተደረገለት መሆኑን ማስረዳት የሚችለው የይቅርታ የምስክር ወረቀቱን በማቅረብ ይሆናል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የይቅርታ ምስክር ወረቀቱ የጠፋበት ሰው ይቅርታ የተደረገለት መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ጽህፈት ቤቱ ለሚመለከተው ወገን እንዲሰጥለት ሊጠይቅ ይችላል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 25.የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሰረት ለይቅርታ አሰጣጥ የሚረዳ ማስረጃ፣ መረጃ ወይም አስተያየት እንዲሰጥ ሲጠየቅ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

### 26.ስለመብትና ግዴታ መተላለፍ

በይቅርታ ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 395/1996 የተቋቋመው ቦርድ መብትና ግዴታ በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ቦርድ ተላልፏል፡፡

### 27.የተሻረ ሕግ

የይቅርታ ሥነሥርዓት አዋጅ ቁጥር 395/1996 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

### 28.ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ቦርዱ ለዚህ አዋጅና በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

### 29.አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ያሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ 15 ቀን 2006 ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

መ/ **ጥብቅና**

**ደንብ ቁጥር 57/1992**

**የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች የሥነ ምግባር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 4/1987 አንቀጽ 5 መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች የሥነ ምግባር ደንብ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 57/1992" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **የተፈጻሚነት ወሰን**

   ይህ ደንብ የፌዴራል ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ በተሰጠው በማንኛውም ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

3. **አጠቃላይ መርህ**

   ማንኛውም ጠበቃ ሕግን ለማስከበርና ፍትሕን ለማስገኘት የፍትሕ አስተዳደሩን የማገዝ ኃላፊነት አለበት፡፡ ማንኛውም ጠበቃ በተለይም ለደንበኛው፣ ለሌሎች የሕግ ሙያተኞችና ተከራካሪ ወገኖች፣ ለፍርድ ቤት፣ ለሙያው እና በአጠቃላይ ለህብረተሰቡ ያለበትን የሙያ ኃላፊነት በቅንነት፣ በታማኝነት እና በእውነተኛነት መወጣት አለበት፡፡

4. **ደንበኛን ስለመቀበል**

   ማንኛውም ጠበቃ የሕግ አገልግሎት ለማግኘት የመጣ ደንበኛን ጉዳይ ተቀብሎ የጉዳዩን ፍሬ ነገርና ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ ክርክሩ ሕጋዊ መሠረት የሌለው ከሆነ ጉዳዩን መያዝ የለበትም፡፡ ሆኖም ለሰጠው የሕግ ምክር አገልግሎት ተገቢውን ክፍያ ተቀብሎ ደንበኛውን ያሰናብታል።

5. **አገልግሎት ለመስጠት ፈቃደኛ ስላለመሆን**

   ማንኛውም ጠበቃ በአገልግሎት ጠያቂ ደንበኛው የሞራል ባህሪ፣ በተፈጸመው ወንጀል ከባድነትና አስነዋሪነት ወይም በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ነው በሚል እምነት ወይም የደንበኛውን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ ወይም የሞራል አቋሙን መሠረት በማድረግ የጥብቅና አገልግሎት አልሰጥም ማለት አይችልም።

6. <u>ከደንበኛ ጋር ስለሚደረግ ውል</u>

1. ማንኛውም ጠበቃ ከደንበኛው ጋር በጽሑፍ የሰፈረ ግልጽ የውል ስምምነት ሊፈጽም ይገባል፡፡ ውሉም የተዋዋዮችን ስም፣ አደራሻ፣ የአገልግሎቱን ዓይነት፣ የውክልና ዓይነትና መጠን የአገልግሎት ክፍያውን መጠን ክፍያው የሚወሰንበትን ሥልትና የአከፋፈሉን ሥርዓትና የመክፍያውን ጊዜ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን የያዘ ይሆናል፡፡
2. አንድ ጠበቃ ለደንበኛው የገባውን የሙያ አገልግሎት በአግባቡ ባለማበርከቱ ምክንያት የሚኖርበትን የፍትሐብሔር ኃላፊነት የሚቀንስ ወይም የሚያስቀር ስምምነት ዋጋ የለውም።

7. <u>የአገልግሎት ዓይነትና የውክልና መጠን</u>

1. ማንኛውም ጠበቃ የደንበኛውን ጉዳይ ፍሬ ነገርና ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ በሕግ መሠረት በጉዳዩ ሊገኝ የሚችለውን ውጤት ወይም አማራጭ ውጤቶች እንዲሁም ተፈላጊውን ውጤት ለማግኘት ደንበኛው ለጠበቃው ሊሰጠው የሚገባውን የውክልና ዓይነትና መጠን በማስረዳት ከተገቢው ውሳኔ ላይ እንዲደርስ የመርዳት ግዴታ አለበት፡፡
2. ደንበኛው ከጠበቃው በተሰጠው የሕግ ምክር ላይ ተመስርቶ የሚሰጠው ውሳኔ ሕግንና ይህን ደንብ የማይጥስ እስከሆነ ድረስ ጠበቃው የማክበር ግዴታ አለበት፡፡ በተለይም ጉዳዩ በግልግል እንዲያልቅ ደንበኛው ከወሰነ ጠበቃው ውሳኔውን ማክበር አለበት፡፡
3. ደንበኛው የሚፈልገው የዕርዳታ ወይም የአገልግሎት ጥያቄ ይህን የሥነ ምግባር ደንብ ወይም ሌላ ሕግ የሚጥስ ከሆነ ጠበቃው አገልግሎቱን ሊሰጥ የማይችልበትን ምክንያት ለደንበኛው ማስረዳትና ደንበኛው ምክሩን ተቀብሎ የማያስተካክል ከሆነ ማሰናበት አለበት፡፡
4. ደንበኛው በውክልናው ላይ ውሳኔ ለመስጠት በመፈለግ መረጃ በጠየቀ ጊዜ ጠበቃው ተገቢውን ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችሉትን መረጃዎች በማቅረብ ውሳኔ ላይ እንዲደርስ መርዳት አለበት፡፡

8. <u>ብቃት ያለው አገልግሎት ስለመስጠት</u>

1. ማንኛውም ጠበቃ በሚሰጠው የጥብቅና አገልግሎት ከፍትኛ የሙያ ችሎታና ብቃት ማሳየት ይጠበቅበታል፡፡
2. ጠበቃው ሕግ በሚፈቅደው መሠረት፣
   ሀ/ የደንበኛውን መብትና ጥቅም ለማስከበር ዕውቀቱና የሥራ ልምዱን በሥራ ላይ የማዋል፤
   ለ/ የደንበኛውን ጉዳይ በትጋት የመከታተልና አፋጣኝና ፍትሐዊ ውሣኔ ለማግኘት ሊወሰድ የሚገባውን እርምጃ ሁሉ በጥንቃቄና በወቅቱ የመፈጸም ሙያዊ ግዴታ አለበት፡፡

9. **<u>አስፈላጊውን መረጃ ስለመስጠት</u>**

ማንኛውም ጠበቃ ጉዳዩ የደረሰበትን ደረጃና የሚገኝበትን ሁኔታ በየጊዜው ለደንበኛው የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡ ደንበኛው መረጃ እንዲሰጠው በጠየቀ ጊዜም አፋጣኝ ምላሽ የማግኘት መብት አለው።

10. **<u>ምስጢር ስለመጠበቅ</u>**

1. ማንኛውም ጠበቃ የደንበኛውን ግላዊ ወይም ድርጅታዊ መረጃ ወይም በሙያ አገልግሎቱ ምክንያት በእጁ የገባውን ማንኛውንም ሌላ መረጃ በምስጢር የመጠበቅ ሙያዊ ግዴታ አለበት፡፡
2. ጠበቃው በውክልናው ምክንያት ከደንበኛው የተሰጠውን መረጃ እና ማንኛውንም ሌላ መረጃ ከደንበኛው ፈቃድ ሳያገኝ ሊገልጽ አይችልም።
3. የጠበቃ ምስጢር የመጠበቅ ሙያዊ ግዴታ በእርሱና በደንበኛው መካከል የነበረው የሥራ ውል በመቋረጡ ምክንያት ቀሪ ሊሆን አይችልም።

11. **<u>ምስጢር ስለሚገለጽበት ሁኔታ</u>**

የአንቀጽ 10 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ጠበቃው ተገቢ ነው ብሎ ሲያምን በሙያ ሥራው አጋጣሚ በእጁ የገባውን መረጃ በሚከተሉት ምክንያቶች እንደአስፈላጊነቱ መጠን ሊገልጽ ይችላል፣

1. ከደንበኛው ያገኘው መረጃ ለተወከለበት ሥራ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ፣
2. ከደንበኛው ጋር ክርክር በሚፈጠርበት ጊዜ ራሱን ለመከላከል ወይም መብቱን ለማስከበር፣
3. የውክልና ሥልጣኑን የተመለከተ ክርክር ሲነሳ፣ ወይም
4. ሕግ በሌላ ሁኔታ በግልጽ የጣለበትን ግዴታ ለመወጣት።

12.**የጥቅም ግጭት**

ማንኛውም ጠበቃ በራሱና በደንበኛው ወይም በዘመዶቹና ደንበኛው ወይም በሸሪኮቹና በደንበኛው ወይም በሁለት ደንበኞቹ መካከል የጥቅም ግጭት መኖሩን እያወቀ የሙያ አገልግሎት ለመስጠት መዋዋል አይችልም። የጥቅም ግጭት መኖሩ የታወቀው አገልግሎቱ ከተጀመረ በኋላ ከሆነ ይሄንኑ ለደንበኛው አስረድቶ አገልግሎቱን ማቋረጥ አለበት፡፡

13.**ከቀድሞ ደንበኛ ጋር ስለሚኖር የጥቅም ግጭት**

1. ማንኛውም ጠበቃ ከዚህ ቀደም የጥብቅና አገልግሎት ከሰጠበት ጉዳይ ወይም ከደንበኛው ጥቅም ጋር በሚጻረሩ ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ባላቸው ሌሎች ጉዳዮች ላይ ከቀድሞ ደንበኛው ጋር ተመካክሮ የጽሑፍ ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር ለአዲስ ደንበኛ የጥብቅና አገልግሎት ሊሰጥ አይችልም።
2. ማንኛውም ጠበቃ ከዚህ ቀደም ይሰራበት የነበረው የጥብቅና አገልግሎት ድርጅት የጥብቅና አገልግሎት ከሰጠው ደንበኛ ጥቅም ጋር የሚጻረር ጥቅም ላለውና ስለደንበኛውም መረጃ ባገኘበት ጉዳይ ከቀድሞ የድርጅቱ ደንበኛ ጋር ተመካክሮ የጽሑፍ ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር ለአዲሱ ደንበኛው የጥብቅና አገልግሎት ሊሰጥ አይችልም።

14.**በጠበቃና በደንበኛ መካከል የሚፈጸሙ ውሎች**

ማንኛውም ጠበቃ ከደንበኛው ጋር ማናቸውንም ውል ሊዋዋል የሚችለው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ከተሟላ ብቻ ነው፣

1. በጠበቃውና በደንበኛው መካከል የሚደረገው ውል ከወቅቱና ከሁኔታዎች አንፃር ተገቢና ምክንያታዊ ሲሆን፤
2. ጠበቃው የስምምነቶቹን መስፈርቶችና የውሉን ዓይነት ለደንበኛው በግልጽ ያስረዳው ከሆነ፤ ወይም
3. ደንበኛው በውሉ ላይ ከሌላ ሰው ጋር ተመካክሮ ስምምነቱን በጽሑፍ ያፀደቀ ሲሆን።

15.**ከደንበኛ ስለሚደረግ ስጦታና ኑዛዜ**

ማንኛውም ጠበቃ ደንበኛው በመልካም ፈቃዱ የሚያደርግለትን ኑዛዜ ወይም ከፍተኛ ዋጋ ያለውን ስጦታ ሊቀበል የሚችለው ጉዳዩ በጽሑፍ ከሆነና ድርጊቱ በሚፈጸምበት ጊዜ ደንበኛው ተገቢው የምክር አገልግሎት የተሰጠውና ስለድርጊቱም ውጤት ከገለልተኛ ጠበቃ የተረዳ መሆኑን ካረጋገጠ ብቻ ነው።

16.**በጠበቃና በደንበኛ መካከል ስለሚደረግ ብድር**

ማንኛውም ጠበቃ ከደንበኛው ገንዘብ ሊበደር ወይም ለደንበኛው ገንዘብ ሊያበድር አይችልም።

17.**ጠበቃ ሸሪክ በሆነበት የንግድ ድርጅት ስለሚሰጠው የምክር አገልግሎት**

ማንኛውም ጠበቃ ሸሪክ በሆነበት የንግድ ድርጅት ውስጥ አጠቃላይ የንግድ ድርጅቱን ወይም ሦስተኛ ወገኖችን በተመለከተ የምክር አገልግሎት ለመስጠት ይችላል፤ ሆኖም ራሱን በሚመለከት የድርጅቱ ጉዳይ ላይ የምክር አገልግሎት ለመስጠት አይችልም።

18.**የመንግሥት ሠራተኛ የነበረ ጠበቃ**

1. ማንኛውም ከዚህ ቀደም የመንግሥት ሠራተኛ ወይም ባለሥልጣን የነበረ ጠበቃ በቀጥታ በወሰነባቸው ወይም በጥልቀት በተሳተፈባቸው ጉዳዮች ላይ ከቀድሞ አሠሪው ጋር ተመካክሮ የጽሑፍ ፈቃድ ካልተሰጠው በስተቀር ለአንድ ደንበኛ የሙያ አገልግሎት መስጠት አይችልም።
2. ሕግ በግልጽ ካልፈቀደ በስተቀር የመንግሥት ሠራተኛ ወይም ባለሥልጣን በነበረበት ጊዜ አንድን ግለሰብ በተመለከተ መረጃ ያገኘ ጠበቃ መረጃው ከሚመለከተው ሰው ጥቅም ጋር የሚጻረር ጥቅም ላለው ሰው የጥብቅና አገልግሎት ሊሰጥ አይችልም።

19.**ዳኛ ወይም የሽምግልና ዳኛ ወይም አስታራቂ**

1. ማንኛውም ጠበቃ ቀደም ሲል በዳኝነት ወይም አንድን ወገን በመወከል ሳይሆን በገለልተኝነት በሽምግልና ዳኝነት የተካፈለበትን ወይም በአስታራቂነት ወይም በሕግ ጉዳይ ፀሐፊነት የተሳተፈበትን ጉዳይ በሚመለከት በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን የጥብቅና አገልግሎት ሊሰጥ አይችልም።
2. ማንኛውም ጠበቃ በዳኝነት፣ በሽምግልና ዳኝነት፣ በአስታራቂነት፣ በሕግ ጉዳይ ፀሐፊነት ወይም በተመሳሳይ ኃላፊነት በሚሠራበት ወቅት በዚሁ ጉዳይ ተካፋይ የሆነ ባለጉዳይ ወይም የሕግ ባለሙያ በሠራተኛነት እንዲቀጥረው ሊደራደር አይችልም።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተከለከለ ጠበቃ አባል የሆነበት የጥብቅና አገልግሎት ድርጅት ጠበቃው አገልግሎት እንዳይሰጥ በተከለከለበት ጉዳይ ላይ በሌላ ጠበቃ አማካኝነት አገልግሎት ሊሰጥ የሚችለው፤
   ሀ/ የተከለከለው ጠበቃ በጉዳዩ ላይ ምንም ዓይነት ተሳትፎና ከአገልግሎት ክፍያውም ድርሻ እንዳይኖረው ከተደረገ፤
   ለ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ለተመለከተው ጉዳዩን ላየው አካል ይህ ደንብ አለመጣሱን እንዲያረጋግጥ ይደረግ ዘንድ ተገቢው የጽሑፍ ማስታወሻ በወቅቱ የተላከለት ከሆነ።

20.<u>የአስታራቂነት ሥራ መሥራት</u>

1. ማንኛውም ጠበቃ ከዚህ የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በመከተል በሁለት ደንበኞች መካከል በአስታራቂነት ሊሠራ ይችላል፤
   ሀ/ ጠበቃው ሁለት ደንበኞችን ለማስታረቅ መሥራቱ የሚኖረውን አንድምታ፣ ጥቅምና ጉዳቱን ጨምሮ ካስረዳቸው በኋላ ሁለቱም ደንበኞች በጠበቃው አስታራቂነት የተስማሙ ሲሆን፤
   ለ/ በጠበቃው ሚዛናዊ ግምት ጉዳዩ ከሁለቱ ወገኖች ጥቅም ጋር በተጣጣመ ሁኔታይፈታል ብሎ ሲያምን፤ በተለይም እያንዳንዱ ደንበኛ በጉዳዩ ላይ አጥጋቢ ውሣኔ ለመስጠት ይችላል ብሎ ሲገምት፤
   ሐ/ ጉዳዩ በእርቅ ሳይፈታ ቢቀር በየትኛውም ወገን ጥቅም ላይ መሠረታዊ የሆነ ጉዳት ይደርሳል ተብሎ የማይጠበቅ ሲሆን፤ እና
   መ/ ሁለቱን ደንበኞቹን በጋራ የመወከሉን ኃላፊነት በገለልተኝነት ለመወጣት የሚችልና የትኛውም ወገን ላይ ተገቢ ያልሆነ ተጽዕኖ የማያሳድር መሆኑን ሲያረጋግጥ።
2. ማንኛውም ጠበቃ የአስታራቂነት አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ ከእያንዳንዱ ደንበኛ ጋር የሚደረስበትን ውሣኔ በመመካከር እና በጉዳዩ ላይ ውሣኔ ለመስጠት የሚረዱትን ቁም ነገሮች በሙሉ እንዲገነዘቡ በማድረግ እያንዳንዱ ደንበኛ የተሟላና አጥጋቢ ውሳኔ እንዲሰጥ መርዳት አለበት፡፡
3. ማንኛውም ጠበቃ ከደንበኞቹ አንዱ የአስታራቂነት አገልግሎቱን እንዲያቋርጥ በጠየቀ ጊዜ ወይም በንዑስ አንቀጽ (1) ከተመለከቱት ሁኔታዎች አንዱን መሟላት

ባልቻለ ጊዜ የአስታራቂነት አገልግሎቱን ያቋርጣል። ውክልናውን ከአቋረጠም በኋላ በዚያው ጉዳይ ላይ ለማንኛውም ወገን የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት አይችልም።

21. **ለድርጅት ጠበቃ ስለመሆን**

1. ለአንድ ድርጅት የጠበቃ አገልግሎት የሚሰጠው በድርጅቱ ደንብ መሠረት አግባብ ያላቸውን የድርጅቱን የሥራ ኃላፊዎች እያማከረ ይሆናል፡፡
2. ማንኛውም ጠበቃ የድርጅቱ ተወካይ ሆኖ በሚሠራበት ወቅት የድርጅቱ ባለሥልጣን፣ ተቀጣሪ ወይም ከድርጅቱ ጋር ተባባሪ ሆኖም የሚሠራ ሌላ ሰው ድርጅትን በሕገ ወጥነት ሊያስጠይቅ በሚችል ሁኔታ አንድን ድርጊት በመፈፀም ወይም ባለመፈጸም በድርጅቱ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል ብሎ በገመተ ጊዜ ጉዳቱን ለመከላከል ይቻል ዘንድ አስፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡ በጠበቃው ሊወሰዱ ከሚችሉ እርምጃዎች የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

   ሀ/ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ መጠየቅ፣

   ለ/ በጉዳዩ ላይ የተለየ አስተያየት ቀርቦበት ሥልጣን ላለው የድርጅቱ አካል እንዲቀርብ ምክር መስጠት፣ ወይም

   ሐ/ ጉዳዩን ከፍ ላለው የድርጅቱ አካል ማቅረብ ወይም ጉዳዩ አሳሳቢና ከባድ በሆነ ጊዜ ደግሞ ለድርጅቱ የመጨረሻ ውሳኔ ሰጭ አካል ማቅረብ፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው መሠረት ተገቢው ውሣኔ እንዲሰጥበት አስፈላጊው ጥረት ተደርጎ የመጨረሻ ውሳኔ ሰጭው አካል ሕግን የሚጥሰውና በድርጅቱ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትል የሚችለው እርምጃ እንዲቀጥል ከወሰነ ጠበቃው አገልግሎቱን በፈቃዱ መልቀቅ ይጠበቅበታል፡፡
4. ጠበቃው የድርጅቱን መሪ፣ ባለሥልጣን፣ ሠራተኛ፣ ባለአክሲዮን ወይም በድርጅቱ የታቀፈ ሰው ጉዳይ በሚያይበት ጊዜ የእነዚህ ሰዎች ጥቅም ከድርጅቱ ጥቅም ጋር የሚጋጭ መሆኑ ከታወቀ የሰውዬውን ማንነት ማስረዳት አለበት፡፡
5. የጥቅም ግጭትን በተመለከተ የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ አንድን ድርጅት ወክሎ የሚሠራ ጠበቃ የድርጅቱን መሪዎች፣ ባለሥልጣኖች፣ ሠራተኞች፣ ባለአክሲዮኖች ወይም ሌሎች ሰዎችን በመወከል ሊሰራ ይችላል፡፡

22. **ችሎታ ለሌለው ሰው ጠበቃ ስለመሆን**

1. ደንበኛው ለአካለ መጠን ባለመድረሱ፣ የአእምሮ መታወክ የገጠመው በመሆኑ ወይም በሌላ በማናቸውም ምክንያት ከውክልናው ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ተገቢውን

ውሳኔ ለመስጠት ባልቻለ ጊዜ ጠበቃው የጠበቃና የደንበኛን መደበኛ ግንኙነት በመጠበቅ መሥራት አለበት፡፡

2. ጠበቃው ደንበኛው የራሱን ጥቅም በአግባቡ ለማስጠበቅ የማይችል መሆኑን በተረዳ ጊዜ ሞግዚት እንዲመደብለት ማድረግ ወይም ጥቅሙን ለማስጠበቅ የሚረዱ ሌሎች እርምጃዎችን መውሰድ ይኖርበታል።

23.<u>የሕግ ሙያ ያልሆኑ ተደራቢ ሥራዎች</u>

1. ማንኛውም ጠበቃ በሕግ ሙያ አገልግሎት በተሰማራበት ወቅት ተደራቢ የንግድ ወይም ሌላ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ሥራ የሚያከናውን በሆነ ጊዜ በተደራቢነት የሚሠራው ሥራ የሙያውን ታማኝነት፣ ነፃነት፣ ብቃትና ክብር እንዳይቀንሰው ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
2. ማንኛውም ጠበቃ ከሙያው ውጭ የሚያከናውነውን ተደራቢ ሥራውንና የተሳትፎውን መጠን ለደንበኛው የማስታወቅ ኃላፊነት አለበት፡፡
3. ማንኛውም ጠበቃ ከሙያው ውጭ የሆነ ተደራቢ ሥራ በሚሠራበት ወቅት ከደንበኞቹ ጋር የሚያደርገው ግንኙነት ከጥብቅና ሙያው ውጭ መሆኑን በግልጽ እንዲረዱለት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
4. ማንኛውም ጠበቃ ከጥብቅና ሙያው ውጭ በሆነ ሥራ ተሰማርቶ የሚያገኘውን ገቢ በጥብቅና ሙያው ካገኘው ገቢ ለይቶ የሚያሳይ የሂሣብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡

24.<u>የደንበኛን ንብረት ስለመጠበቅ</u>

1. ማንኛውም ጠበቃ ከውክልናው ጋር በተያያዘ የደንበኛን ንብረት በአደራ በሚጠብቅበት ወይም በሚያስተዳድርበት ጊዜ በኢትዮጵያ ሕግ የታዘዙትን የጥንቃቄ እርምጃዎች በሙሉ የማክበር፣ አግባብነት ያለው ሕግ በሌለ ጊዜ ደግሞ ጠንቃቃ ባለንብረት የሚወስዳቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎች የመውሰድ ግዴታ አለበት፡፡
2. ማንኛውም ጠበቃ ደንበኛው በስሙ ንብረት የሚረከብ መሆኑን በግልፅ የሚያውቅ ካልሆነ በስተቀር የደንበኛውን ንብረት እንደተረከበ መረከቡን የማስታወቅ ግዴታ አለበት፡፡
3. ማንኛውም ጠበቃ የደንበኛውን ንብረት በአደራ በሚጠብቅበት ወይም በሚያስተዳድርበት ወቅት ንብረቱን ለመተሳሰብና ለባለመብቱ ለማሰረከብ

በሚያመች ሁኔታ መዝግቦ የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡ በባንክ መቀመጥ ያለበት ገንዘብ ካለም ለብቻው የተለየ የባንክ ሂሳብ መክፈት አለበት፡፡

4. ጠበቃው የያዛቸውን ንብረትና መረጃዎች ለማየት ሥልጣን የሌላቸው ሰዎች እንዳይመረምሩት ተገቢውን ጥንቃቄ የማድረግ ኃላፊነት አለበት።
5. ማንኛውም ጠበቃ ደንበኛው ንብረቱን ለመረከብ በጠየቀ ጊዜ ወይም ንብረቱን ለባለመብቱ ማስረከብ ተገቢ በሆነ ጊዜ የማስረከብ ኃላፊነት አለበት።
6. ጠበቃው የደንበኛው ንብረት ባለአደራና አስተዳዳሪ በሆነበት ጊዜ በሦስተኛ ወገኖች የተያዘን ንብረት የማስመለስ፣ የደንበኛውን የባለንብረትነት ማረጋገጫ መዛግብትና ሌሎች መረጃዎች የማየት መብት አለው፡፡

25.<u>የደንበኛን ልዩ ፈቃድ ስለማግኘት</u>

ጠበቃ ለደንበኛው በሕግ የተፈቀደለትን የይርጋና ሌሎች ተመሣሣይ መብቶችን በተቃውሞነት በከርክር ወቅት ላያቀርብ የሚችለው ሁኔታውን ለደንበኛው ካስረዳ በኋላ ደንበኛው በጽሑፍ ከፈቀደለት ብቻ ነው።

26.<u>ጉዳዩ በስምምነት እንዲያልቅ ስለመገፋፋት</u>

ጠበቃው የደንበኛው ጉዳይ በፍርድ ቤት ቀርቦ ከሚወሰን ይልቅ በእርቅ ቢያልቅ ተገቢውን ውጤት የሚያስገኝ ሆኖ ባገኘው ጊዜ ጉዳዩ በእርቅ እንዲያልቅ ሊገፋፋ ይችላል፡፡

27.<u>የተከላካይ ጠበቃ ኃላፊነት</u>

1. ማንኛውም ተከላካይ ጠበቃ በደንበኛው ላይ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት የጥፋተኛነት ውሳኔ ሊያሰጥ የሚያበቃ በቂ ማስረጃ መቅረቡን ካላረጋገጠ በስተቀር ደንበኛው በጥፋተኛነት እንዳይቀጣ የመከራከር ግዴታ አለበት፡፡
2. ማንኛውም ጠበቃ ደንበኛው በተከሰሰበት ወንጀል ሙሉ ለሙሉ ጥፋተኛ መሆኑን ማወቁ ወይም በማስረጃነት የሚያቀርባቸው ነገሮች የማያዋጡ መሆናቸውን ማወቁ ለደንበኛው ተገቢውን የክርክር አገልግሎት እንዳይሰጥ ተጽእኖ ሊያሳድር እንደሚችል በመግለጽ ደንበኛውን አስቀድሞ ማስጠንቀቅ ይጠበቅበታል፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ የወንጀል ተከሳሽ በቀረበበት ክስ ጥፋተኛ ከመባሉ በፊት እያንዳንዱን የጉዳዩን ነጥብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ጠበቃው የሚያደርገውን ማጣራትና ክርክር አይመለከትም።

**28.አከራካሪ ጉዳይ በሌለበት ክስና ክርክር ስለአለማቅረብ**

ማንኛውም ጠበቃ ተከራካሪን ለማጉላላት ክስ ማቅረብና መከራከር በተለይም አከራካሪ የሆነ ጭብጥ በሌለበትና የክርከሩ ውጤት በተከራካሪ ወገኖች መብት ላይ ለውጥ የማያመጣ መሆኑ በግልጽ በሚታይበት ጉዳይ ክስ ማቅረብና መከራከር አይችልም፡፡

**29.ለተቃራኒ ወገን ቅን ስለመሆን**

ማንኛውም ጠበቃ የሚከተሉትን ድርጊቶች መፈጸም የለበትም፤

1. ተቃራኒ ወገን ማስረጃ እንዳያገኝ ማናቸውም እንቅፋት መፍጠር ወይም ሌሎች ሰዎች ይህን መሰል አድራጎት እንዲፈጽሙ መምከር ወይም መርዳት፤
2. ማስረጃን ማሳሳት ወይም ሌሎች ሰዎች ይህን መሰል አድራጎት እንዲፈጽሙ መምከር ወይም መርዳት፤
3. ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት የሌለው ወይም በማስረጃ ሊደገፍ የማይችል ነገር ማቅረብ፣ በምስክርነት ካልቀረበ በስተቀር በግሉ የማያውቀውን የጭብጥ ፍሬ ነገሮች መሰንዘር፣ ወይም የጉዳዩን ፍትሃዊነት፣ የአንድን ምስክር ተአማኒነት፣ የተከሳሽን ጥፋተኛ ወይም ተጠያቂ መሆንና አለመሆን አስመልክቶ የግል አስተያየቱን መስጠት፤
4. ደንበኛው ወይም ምስክርነታቸውን እንዲሰጡ የማይገደዱ ሰዎችን በተመለከት ካልሆነ በስተቀር ሌላ ማንኛውንም ሰው ለተቃራኒ ወገን የምስክርነት ቃሉን ወይም ሌላ አግባብነት ያለው መረጃ እንዳይሰጥ መገፋፋት፡፡

**30.በጠበቃ ያልወከለ[42] ተከራካሪ ሲያጋጥም**

ማንኛውም ጠበቃ ጠበቃ ያልወከለ ተከራካሪ ባጋጠመው ጊዜ ጠበቃው ሆን ብሎ ይህንኑ ተከራካሪ ወገን ሊያሳስቱ የሚችሉ ድርጊቶች ከመፈጸም መቆጠብ አለበት። ከተቻለም ጠበቃ ላልያዘው ተከራካሪ ጉዳዩን በተመለከተ የጠበቃ ሚና ምን እንደሆነ ማስረዳት አለበት፡፡

**31.የሦስተኛ ወገኖችን መብት ስለማክበር**

ማንኛውም ጠበቃ ለደንበኛው በሚሰጠው የጥብቅና አገልግሎት ሦስተኛ ወገኖችን ማጉላላት፤ ማዋረድ ወይም በእነዚሁ ወገኖች ላይ ተገቢ ያልሆነ ጫና መፍጠር፤ ሌላ

[42] “ያልወከለ” የሚለው ቃል በእንግሊዘኛው “unrepresented ” ብሎ የተገለፀ ሲሆን ትክክለኛ ትርጓሜው “ያልተወከለ” ሆኖ መፃፍ ነበረበት፡፡

መሠረታዊ ግብ በሌለው ወይም የሦስተኛ ወገኖችን ሕጋዊ መብት በሚጋፋ መንገድ ማስረጃ የማግኘት ዘዴ መጠቀም የለበትም፡፡

32.<u>ጉዳዩን በመገናኛ ብዙሃን ስለመግለጽ</u>

1. ማንኛውም ጠበቃ በሕግ ሙያ አገልግሎቱ ምክንያት ያወቀውን መረጃ ለመገናኛ ብዙሃን ሊገልጽ የሚችለው በሚዛናዊ የህሊና ግምት የመረጃው መገለጽ የፍርድ ሂደትን የማያደናቅፍና የደንበኛውን ጥቅም የማይጎዳ ከሆነ ብቻ ነው።
2. በንዑስ ቁጥር (1) የተመለከተው ክልከላ ቢኖርም ዝርዝር ጉዳይ ውስጥ ሳይገባ ጠበቃው በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ለመገናኛ ብዙሃን መረጃ ለመስጠት ይችላል፤
   ሀ/ የክሱን ወይም የመከላከያውን ጠቅላላ ሁኔታ ወይም ዓይነት፤ እንዲሁም የወንጀል ጉዳይ ከሆነ የክሱን ዓይነት፤ በሕግ ካልተከለከለ በስተቀር የወንጀል ክሱን ወይም የመከላከያውን ዓይነት፤ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ሰዎች ማንነት፤
   ለ/ በሕዝብ መዝገብ ውስጥ የሰፈረን መረጃ፤
   ሐ/ በጉዳዩ ላይ የተሰጠውን ቀነ ቀጠሮ ወይም ጉዳዩ የደረሰበትን ደረጃ፤
   መ/ መረጃ ለመሰብሰብ የቀረበን የዕርዳታ ጥያቄና የተፈላጊውን መረጃ ዓይነት፤
   ሠ/ ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው በግለሰቦች ወይም በሕዝብ ላይ ከፍተኛ አደጋ ሊያስከትል ይችላል የሚል ግምት ካለ ስለዚሁ ሰው ባህርይ አደገኛነት ማስጠንቀቂያ፡፡
3. ጠበቃ በደንበኛው ላይ የተሰራጩትን አሉታዊ ዜናዎችና መግለጫዎች በማስተባበል የደንበኛውን ጥቅምና መልካም ስም ለማስጠበቅ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሚዛናዊ የሆነ የማስተባበያ ወይም የማለዘቢያ መግለጫ ለመገናኛ ብዙሃን ለመስጠት ይችላል፡፡

33.<u>የጥብቅና አገልግሎት ስለማቋረጥ</u>

1. ማንኛውም ጠበቃ ለደንበኛው ሊሰጥ የገባውን የጥብቅና አገልግሎት ውል ለማቋረጥ የሚያስችል በቂና አሳማኝ ምክንያት ከሌለው በስተቀር በገባው የውል ግዴታ መሠረት የደንበኛውን ጉዳይ እስከ መጨረሻው የመከታተል ግዴታ አለበት፡፡
2. ጠበቃው ለደንበኛው በገባው የውል ግዴታ መሠረት የደንበኛውን ጉዳይ እስከ መጨረሻው ለመከታተል ባልቻለ ጊዜ ሁኔታውን ለደንበኛው የመግለጽና አገልግሎቱን በማቋረጡ ምክንያት በደንበኛው ላይ ሊደርስ የሚችለውን ወጭና መጉላላት ለመቀነስ እንዲሁም ጉዳዩ በተቃና ሁኔታ በሌላ ጠበቃ ሊሸፈን የሚችልበትን ሁኔታ የማመቻቸት ግዴታ አለበት፡፡

## 34.<u>አገልግሎት ለማቋረጥ በቂ ምክንያቶች</u>

ጠበቃ ለደንበኛው የሚሰጠውን አገልግሎት ለማቋረጥ የሚያስገድዱ በቂ ምክንያቶች የሚከተሉትን ይጨምራል፤

1. ይህን የሥነ ምግባር ደንብ ወይም ሌላ ሕግ የማጥስ ከሆነ፤
2. ጠበቃው የተወከለበት ጉዳይ በመታየት ላይ ባለበት ወቅት ደንበኛው በጉዳዩ አካሄድ ላይ አስነዋሪ እርምጃ የወሰደ ከሆነና ከጠበቃው የሚያገኘውን አገልግሎት ለወንጀል ወይም ለማታለል ድርጊት ከተጠቀመበት፣ ወይም ክርክሩን በሌላ ሰው ላይ መጉላላትን ለማስከተል ወይም ጉዳት ለማድረስ የተጠቀመበት ከሆነ፤
3. ጠበቃው ጉዳዩን በአግባቡ ለመምራት ችሎታና ብቃት ያነሰው እንደሆነ ወይም ከጥብቅና ሥራው ከተወገደ፤
4. ደንበኛው ውክልናውን በተመለከተ ከጠበቃው የሚፈለግበትን ግዴታ ሳይወጣ ሲቀር እና ግዴታውን ካልፈጸመ አገልግሎት የሚያቋርጥ መሆኑን ጠበቃው ካስጠነቀቀው፤
5. በጠበቃውና በደንበኛው መካከል ሊኖር የሚገባው መተማመን አንዱ ወገን የማታለል ወይም የማጭበርበር ድርጊት በመፈጸሙ የተነሳ በከፍተኛ ሁኔታ የተናጋ ከሆነ፤
6. የጉዳዩን ሂደት በሚመለከት ጠበቃው ወሣኝ በሆኑ ነገሮች ላይ የሚሰጠውን የሕግ ምክር ደንበኛው ውድቅ በማድረጉ የተነሣ በሁለቱ ወገኖች መካከል ሊኖር የሚገባው መተማመን ከጠፋ፤
7. ደንበኛው ለጠበቃው መክፈል ያለበትን የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፍልና ሌሎችንም ወጭዎች እንዲተካ ተገቢውን ማሳሰቢያ ተሰጥቶት ኃላፊነቱን ለመወጣት ፈቃደኛ አለመሆኑን በግልጽ ካሳየ፡፡

## 35.<u>አገልግሎት የሚያቋርጥ ጠበቃ ግዴታዎች</u>

ማንኛውም ጠበቃ ውል ሲያቋርጥ የሚከተሉትን ግዴታዎች መወጣት አለበት፤

1. ለደንበኛው በቂ ማስታውቂያ መስጠት እና ደንበኛው ሌላ ጠበቃ እንዲወክል በቂ ጊዜ መስጠት፤
2. የደንበኛውን ንብረትና ሠነዶች ሥርዓት ባለው መንገድ ወዲያውኑ ማስረከብ፤
3. ስለጉዳዩ ደንበኛው የሚጠይቀውን ማንኛውንም መረጃ መስጠት፤

4. በደንበኛው እጅ የሚገኝ ማንኛውንም ሂሣብ መተሳሰብ ወደፊት ለሚሠራ ሥራ የተቀበለውን ገንዘብ ከወጪ ቀሪውን ተመላሽ ማድረግ፤
5. ለሥራ ማስኬጃ የተረከባቸውን ሂሣቦች መተሳሰብና ቀሪ መመለስ፤
6. ከተተኪው ጠበቃ ጋር በመተባበር በጉዳዩ መጓተት፣ መቋረጥ ወይም አላስፈላጊ ወጭ እንዳያጋጥመው መከላከል፡፡

## 36.<u>የተተኪ ጠበቃ ግዴታዎች</u>

1. ተተኪው ጠበቃ ደንበኛው ከቀድሞ ጠበቃው ጋር ያለውን ማንኛውንም ሂሣብ እንዲያወራርድ ማስገንዘብ ይጠበቅበታል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ደንበኛው ለቀድሞ ጠበቃው መክፈል ያለበትን የአገልግሎት ክፍያ አለማጠናቀቁ አዲሱ ጠበቃ በቀጠሮ ቀን በፍርድ ቤት ተገኝቶ ተገቢውን አገልግሎት እንዳይሰጥ ሊያግደው አይችልም፡፡

## 37.<u>በሽሪክ ወይም በተቆጣጣሪ ጠበቃ ስለሚሰጥ የጥብቅና አገልግሎት</u>

1. የጥብቅና ድርጅት ሽሪክ የሆነ ጠበቃ በድርጅቱ ውስጥ የሚሠራ ማንኛውም የሕግ ባለሙያ ይህን የሥነ-ምግባር ደንብ ማክበሩን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡
2. ማንኛውም ሌላውን ጠበቃ በቀጥታ የመቆጣጠር ሥልጣን ያለው ጠበቃ በእርሱ ሥር የሚያገለግል ጠበቃ የሙያውን የሥነ ምግባር ደንብ ማክበሩን የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት፤
3. ማንኛውም ጠበቃ ለሌላ ጠበቃ የሥነ ምግባር ጉድለት ተጠያቂ የሚሆነው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው፤
   ሀ/ ጥፋት የፈጸመው ሰው ድርጊቱን የፈጸመው በጠበቃው ታዝዞ ሲሆን ወይም ጉድለት እየተፈጸመ መሆኑን እያወቀ ድርጊቱን ያጸደቀው ሲሆን፤
   ለ/ ጥፋት የፈጸመው ሰው ጠበቃው በሚሠራበት የጥብቅና አገልግሎት ድርጅት ሽሪክ ከሆነ ወይም በጠበቃው ቀጥተኛ ቁጥጥር ሥር የሚሠራ ከሆነና ግለሰቡ በሥነ ምግባር ደንብ የሚያስቀጣ ድርጊት እየፈጸመ መሆኑን እያወቀ ድርጊቱ የሚያስከትለውን የማስተካከያ እርምጃ ያልወሰደ ሲሆን፡፡

## 38.<u>ክልከላ</u>

1. በማንኛውም የጥብቅና አገልግሎት ድርጅት ውስጥ የሚሠራ ጠበቃ በድርጅቱ ውስጥ ከሚሠሩት ሌሎች ጠበቃዎች አንዱ በዚህ ደንብ መሠረት አንድን ጉዳይ በጥብቅና

ለብቻው ከመያዝ የሚያግደው ምክንያት መኖሩን እያወቀ የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት አይችልም፡፡

2. የሚከተሉት ሁኔታዎች ካላጋጠሙ በስተቀር የጥብቅና አገልግሎት ድርጅትን የለቀቀ ጠበቃ በድርጅቱ ውስጥ በነበረበት ጊዜ ወክሎት ከነበረ ደንበኛ ጥቅም ጋር የሚጋጭ ጥቅም ያለው ደንበኛን ድርጅቱ ከመወከል አያግደውም፡፡
   ሀ/ ጉዳዩ ከዚህ ቀደም ለድርጅቱ የቀረበ ወይም ከቀድሞው ጉዳይ ጋር መሠረታዊ በሆነ መንገድ የተያያዘ ከሆነ፤
   ለ/ በጥብቅና አገልግሎት ሰጭ ድርጅቱ ውስጥ ያለ ጠበቃ በቀረበው ጉዳይ ላይ በማስረጃነት ሊያገለግል የሚችል መረጃ በእጁ የሚገኝ ከሆነ፤
3. በዚህ አንቀጽ የተጣለው ክልከላ ጉዳዩ የሚመለከተው ደንበኛ ክልከላው ተፈጻሚ እንዳይሆን በጽሑፍ በተስማማ ጊዜ ቀሪ ይሆናል፡፡

39.<u>የበታች ጠበቃ ግዴታ</u>

1. በሌላ ጠበቃ አመራር ሥር የሚሠራ ማንኛውም ጠበቃ ይህን የሥነ ምግባር ደንብ ማክበር አለበት፡፡
2. የበታች ጠበቃ አከራካሪ በሆነ የሥነ ምግባር ጥያቄ ላይ የበዩን ትዕዛዝ በመቀበል የሠራ መሆኑን ለማስረዳት በቻለ ጊዜ ከተጠያቂነት ነጻ ይሆናል፡፡

40.<u>የሕግ ሙያተኛ ያልሆኑ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን ስለመቆጣጠር</u>

የሕግ ባለሙያ ያልሆነን ሰው በተቀጣሪነት ወይም ለሚሰጠው አገልግሎት የተወሰነ ክፍያ በመስጠት ወይም በተባባሪነት የሚያሠራ ጠበቃ ወይም ጥብቅና አገልግሎት ድርጅት፤

1. ተገቢውን የጥንቃቄ እርምጃና ተፈላጊውን ቁጥጥር በማድረግ የግለሰቡ ምግባር ይህን የሥነ ምግባር ደንብ እንዳይጥስ ይቆጣጠራል፣
2. የሕግ ሙያተኛ ያልሆነው ባልደረባ ስለፈጸመው የሥነ ምግባር ጉድለት ጠበቃው ተጠያቂ የሚሆነው፤
   ሀ/ ድርጊቱን እንዲፈጽም ያዘዘው ከሆነ ወይም የተፈጸመውን ድርጊት የሚያውቅ ከሆነና አፈጻጸሙንም የፈቀደ ወይም ያጸደቀ ከሆነ፤
   ለ/ ሙያተኛ ባልሆነው ሰው ላይ የቁጥጥር ሥልጣን ኖሮት የሥነ ምግባር ጉድለት የሆነውን ድርጊት መፈጸሙን እያወቀና ድርጊቱ የሚያስከትለውን ውጤት

ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ እየቻለ ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ያልወሰደ፤ ከሆነ ነው፡፡

41. <u>ሙያዊ ነጻነት</u>

1. ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት በሚከተሉት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር የጥብቅና አገልግሎት ክፍያን ጠበቃ ካልሆነ ሰው ጋር መካፈል አይችልም፤

ሀ/ ጠበቃው ከጥብቅና ድርጅቱ፣ ከሸሪኩ ወይም ከተባባሪው ጋር በሚያደርገው ስምምነት መሠረት በሚሞትበት ጊዜ ወደ ሟቹ ጠበቃ ሀብት ወይም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለይቶ ላስታወቃቸው ሰዎች የሚደረግ ክፍያ፤

ለ/ ከሟች፣ ችሎታ ካጣ ወይም ከጠፋ ጠበቃ ላይ የጥብቅና አገልግሎት ድርጅት የገዛ ሰው ለሟች ጠበቃ ሀብት ወይም ለተወካዩ የሚፈጽመው የግዥ ክፍያ፤

ሐ/ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የሕግ ባለሙያ ላልሆኑ ሠራተኞች የአገልግሎት ወይም የጡረታ ዋስትና ተጠቃሚ ከሚያደርገው ስምምነት ውስጥ በመግባቱ የሚደረግ ክፍያ።

2. ማንኛውም ጠበቃ የሕግ ሙያተኛ ካልሆነ ሰው ጋር የጥብቅና አገልግሎትን የሚያካትት የሽርክና ግንኙነት መመሥረት ወይም ሙያዊ ግዴታውን በመወጣት ረገድ የሕግ ሙያተኛ ላልሆነ ሰው የመምራትና የመቆጣጠር ሥልጣን በሚሰጥ ሁኔታ መሥራት አይችልም።

42. <u>የአገልግሎት ክፍያ አተማመን</u>

ማንኛውም ጠበቃ ከደንበኛው የሚጠይቀው የአገልግሎት ክፍያ ተገቢና ሚዛናዊ መሆን አለበት፡፡ የክፍያውን መጠን ለመወሰን የሚከተሉትን መመዘኛዎች ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፤

1. ለደንበኛው የሚሰጠው አገልግሎት የሚወስደው ጊዜና የሚጠይቀው ድካም፤
2. ጉዳዩን በሚገባ ለማከናወን የሚያስፈልገው ችሎታ፤ የጉዳዩ አዲስነት እና አስቸጋሪነት፤
3. ከደንበኛው ጋር የሚደረገው የጥብቅና ሥራ ስምምነት የሌሎች ደንበኞችን ጉዳይ ተቀብሎ ለመሥራት የሚያስችል መሆን አለመሆኑን፤
4. ተመሣሣይ ጉዳዮች በተለምዶ የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ መጠን፤
5. ለክርክሩ መነሻ የሆነው የሀብት ግምት እና የሚገኘው ውጤት፤

6. በጠበቃው እና በደንበኛው መካከል ያለው የሙያ ግንኙነት ርዝመት፤ እና
7. የጠበቃው የሥራ ልምድ፣ ጥሩ ዝናና የሙያ ችሎታ፤ እና
8. ሌሎች መሰል መመዘኛዎች፡፡

43.<u>የአገልግሎት ክፍያ ስምምነት</u>

1. የአገልግሎት ክፍያ ስምምነት በጽሑፍ የሚደረግና በተዋዋይ ወገኖች ወይም በወኪሎቻቸው የሚፈረም ሕጋዊ ሰነድ ነው፡፡
2. በጠበቃና በደንበኛ መካከል የሚፈፀም የአገልግሎት ክፍያ ስምምነት የሚከተሉትን መሠረታዊ ጉዳዮች ይወስናል፤

ሀ/ ደንበኛው ለጠበቃው የሚከፍለውን አጠቃላይ ገንዘብ፣ ደመወዝ፣ የማካካሻ ክፍያ፣ የመጠባበቂያ ክፍያ ወይም ሌላ የክፍያ ሥርዓት በመግለጽ የአከፋፈሉን ስልትና ጊዜ፤

ለ/ ጠበቃው በጉዳዩ ላይ የሚያስገኘውን የውጤት ዓይነት ወይም ዓይነቶች።

44.<u>መጠኑ ያልተወሰነ የአገልግሎት ክፍያ ስምምነት</u>

የአገልግሎት ክፍያው ክርክሩ በሚያስገኘው የገንዘብ መጠን ላይ የተመሰረተ በሆነ ጊዜ ስምምነቱ የሚከተሉትን መሠረታዊ ጉዳዮች የያዘ ይሆናል፡፡

1. ጉዳዩ በስምምነት፣ በይግባኝ ወይም በሌላ መንገድ ቢያልቅ ከእነዚህ ሁኔታዎች ባንዱ ደንበኛው ከሚያገኘው ገንዘብ ላይ ለጠበቃው በመቶኛ ስሌት ሊከፈለው የሚገባውን የገንዘብ መጠን፤
2. ለጠበቃው የሚደርሰው ሂሳብ የዳኝነት ክፍያ እና ሌሎች ወጭዎች ከተቀናነሱ በኋላ የሚታሰብ ወይም ከአጠቃላዩ ገንዘብ የሚታሰብ መሆኑን፡፡

45.<u>መጠኑ ያልተወሰነ የአገልግሎት ክፍያ የማይጠየቅባቸው ጉዳዮች</u>

ጠበቃ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ያልተወሰነ የአገልግሎት ክፍያ ስምምነት ሊያደርግ አይችልም፤

1. በመደበኛ ፍርድ ቤት በባልና ሚስት ክርክር ፍቺን በማስገኘት ላይ ተመስርቶ ወይም በሚያስወስነው የቀለብ ወይም የልጆች ማሳደጊያ ገንዘብ ወይም በሚያስገኘው የንብረት መጠን፤
2. በወንጀል በተከሰሰ ሰው ላይ ፍርድ ቤት በሚሰጠው ውሳኔና ቅጣት ላይ ተመርኩዞ።

46.<u>በደንበኞች መካከል የጥብቅና አገልግሎት ክፍያን በድርሻቸው ስለማከፋፈል</u>

በአንድ ጉዳይ ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎችን ወክሎ የሚከራከር ጠበቃ በተቃራኒው ግልጽ የሆነ ስምምነት ከሌለ በስተቀር የአገልግሎት ክፍያውን ፍትሐዊ በሆነ መንገድ እያንዳንዱ ደንበኛ ድርሻውን እንዲከፍል ያደርጋል፡፡

47.<u>የአገልግሎት ክፍያን ከሌላ ጠበቃ ጋር ስለመካፈል</u>

ማንኛውም ጠበቃ የአገልግሎት ክፍያን የሙያ ሸሪኩ ካልሆነ ሌላ ጠበቃ ጋር ለመካፈል የሚችለው፤

1. ሌላው ጠበቃ በጉዳዩ ላይ አገልግሎት እንዲሰጥ ደንበኛው ቀጥተኛ በሆነ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የፈቀደ ሲሆን፣ እና
2. የገንዘብ አከፋፈሉ እያንዳንዱ ጠበቃ ከሠራው ሥራና ከተቀበለው ኃላፊነት ጋር ተመጣጣኝ ሲሆን፤

   ብቻ ነው፡፡

48.<u>የሕግ አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች አባል ስለመሆን</u>

ማንኛውም ጠበቃ የጥብቅና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች አባል ለመሆን ይችላል፡፡ ጠበቃው አባል የሆነበት ድርጅት በሚሰጣቸው ውሳኔዎች ወይም በሚወስዳቸው እርምጃዎች ላይ መካፈል የማይችለው፤

1. በውሳኔው ተካፋይ መሆኑ ከደንበኛው ጥቅም ጋር የሚጋጭ ሲሆን፣
2. አገልግሎት የሚሰጠው ሰው ወይም ማህበረሰብ ከጠበቃው ወይም ከጠበቃው ደንበኛ ጋር የማይጣጣም ጥቅምና ፍላጎት ያላቸው ሲሆን፣

49.<u>ነፃ የሕግ አገልግሎት ስለመስጠት</u>

ማንኛውም ጠበቃ በነፃ ወይም በአነስተኛ ክፍያ በዓመት ቢያንስ የ50 ሰዓት የሕግ አገልግሎት መስጠት አለበት፡፡ አገልግሎት የሚሰጠውም፤

1. የመክፈል አቅም ለሌላቸው ሰዎች፤
2. ለበጎ አደራጎት ድርጅቶች፣ ለሲቪክ ድርጅቶች፣ ለማህበረሰብ ተቋማት፤
3. ፍርድ ቤት የጥብቅና አገልግሎት እንዲያገኙ ለሚጠይቃቸው ሰዎች፤
4. ሕግን የሕግ ሙያንና የፍትሕ ሥርዓቱን ለማሻሻል ለሚሠሩ ኮሚቴዎችና ድርጅቶች፤

ነው።

50.<u>አገልግሎትን አስመልክቶ ስለሚሰጥ መግለጫ</u>

ማንኛውም ጠበቃ ስለ እራሱ ወይም ስለሚሰጠው አገልግሎት ሀሰተኛ ወይም የሚያሳስት መግለጫ መስጠት የለበትም። ከጠበቃ የሚሰጥ መግለጫ ሀሰተኛ ወይም የሚያሳስት ነው ሊባል የሚችለው፤

1. ፍሬ ነገር ወይም ሕግ ያልሆነውን እንደሆነ አድርጎ ላቀረበ ወይም አንድን ፍሬ ነገር በመደበቅ አንድን አባባል እውነት አስመስሎ ካቀረበ፤
2. ጠበቃ በክርክር ሊያስገኘው የሚችለውን ውጤት አጋኖ በማቅረብ ተገቢ ያልሆነ ተስፋ እንዲፈጠር ከገፋፋ ወይም ይህን የሥነ ምግባር ደንብ የሚጥስ ዘዴን በመጠቀም ለጉዳዩ ውጤት ለማስገኘት ቃል የገባ ሲሆን፤
3. በተጨባጭ ማረጋገጥ የሚቻል ካልሆነ በስተቀር አንድ ጠበቃ የራሱን የጥብቅና አገልግሎት ከሌሎች ጠበቆች አገልግሎት ጋር በማነፃፀር የራሱን አጉልቶ የሚያሳይ መግለጫ ከሰጠ፤

ነው፡፡

## 51.ደንበኛን አስመልክቶ ስለሚሰጥ መግለጫ

ማንኛውም ጠበቃ የደንበኛውን ጉዳይ አስመልክቶ ለሦስተኛ ወገኖች በፍሬ ጉዳዩም ሆነ በሕግ ረገድ ሃሰተኛ የሆነ መረጃ መስጠት አይችልም።

## 52.ማስታወቂያ ስለማስወጣት

1. ማንኛውም ጠበቃ የሚሰጠውን የሕግ አገልግሎት በሚለጠፍ ማስታወቂያና በሌሎች መገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች ማስተዋወቅ ይችላል፡፡ ማስታወቂያው አጭር፣ ግልጽና ትክክለኛ ሆኖ የጠበቃውን ስም፣ አድራሻ፣ የሚሰጠውን አገልግሎትና የሥራ ልምድ መግለጽ ይኖርበታል፡፡
2. ማንኛውም ጠበቃ ማስታወቂያውን ለመገናኛ ብዙሃን ከመላኩ ከሠላሳ ቀናት በፊት ለጥብቅና ፈቃድ ሰጭው አካል አንድ ኮፒ እንዲደርሰው ማድረግ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ መሠረት ለሚዘጋጅ ማስታወቂያ ይዘት ተጠያቂ የሚሆን ቢያንስ የአንድ ጠበቃ ስም መጨመር አለበት፡፡

## 53.የሙያ ዘርፍን ስለማስተዋወቅ

1. ማንኛውም ጠበቃ በተወሰነ የሕግ ዘርፍ አገልግሎት የሚሰጥ ወይም የማይሰጥ መሆኑን ማስታወቅ ይችላል።
2. ጠበቃ በተወሰነ የሕግ ዘርፍ ልዩ ዕውቀት ወይም ጠበብትነት አለኝ ብሎ ለማስታወቅ የሚችለው የልዩ ዕውቀት ወይም የጠበብትነት ማዕረግ ለመስጠት በሕግ ሥልጣን

የተሰጠው አካል የምስክር ወረቀት ሲሰጠውና ምስክርነቱ በጥብቅና ፈቃድ ሰጪው አካል ሲታጠቅ ነው፡፡

54.**በድርጅት ስም ስለመጠቀም**

1. ማንኛውም ጠበቃ የሚጠቀምበት የጥብቅና አገልግሎት ድርጅት ስያሜ ከመንግሥት፣ ከሕዝብ ወይም ከበጎ አድራጎት ድርጅት ስም ጋር የሚመሳሰል እስካልሆነ ድረስ የጥብቅና አገልግሎቱን በተወሰነ ስም፣ ፊደላት ወይም ሌላ የሙያ ስያሜ ማስተዋወቅ ይችላል፡፡
2. ከአንድ ክልል በላይ ወይም በተለያየ የሥልጣን እርከን ደረጃዎች አገልግሎት የሚሰጥ የጥብቅና ድርጅት በሚሠራባቸው ሥፍራዎች እራሱን በአንድ ስም ማስተዋወቅ ይችላል፤ በሚያወጣው ማስታወቂያ ግን የሚሠራበትን ክልልና በእያንዳንዱ ክልል እንዲሠራ የተፈቀደለትን የሥልጣን እርከን መግለጽ አለበት፡፡
3. የጥብቅና ድርጅት አባል የነበረ ጠበቃ በመንግሥት ኃላፊነት ላይ ሲሆን የዚህን ሰው ስም በድርጅቱ መጠሪያነት መገልገል ወይም ከድርጅቱ አባላት አንዱ የነበረ መሆኑን መግለጽ የተከለከለ ነው፡፡

55.**የሙያ ባልደረባን ስለማክበር**

1. ማንኛውም ጠበቃ ከሌሎች የሙያ ባልደረቦቹ ጋር የሚኖረው ግንኙነት በቅን ልቦና፤ በመከባበርና በመግባባት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ማድረግ አለበት፤
2. በፍትህ መድረክ የሙያ ባልደረባን መዝለፍ፣ ማንቋሸሽ ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ ክብሩን ለመቀነስ መሞከር የተከለከለ ነው፤
3. ማንኛውም ጠበቃ ከደንበኛው ወይም ከሌላ ጠበቃ ጋር የሚያደርገውን ንግግር ለመቅረጽ የሚፈልግ መሆኑን አስቀድሞ ሳያሳውቅ መቅረጽ የለበትም፤
4. ማንኛውም ጠበቃ ከሙያ ባልደረባው ለሚደርሱት የሥራ ግንኙነት ደብዳቤዎች ተገቢውን ምላሽ የመስጠትና ይህን ግንኙነት አስመልክቶ የተደረገውን ስምምነት የማክበር ግዴታ አለበት፡፡
5. የተለየ ስምምነት ካልተደረገ በስተቀር አንድ ጠበቃ የተከራካሪው ወገን ጠበቃ ሳያውቀው ወይም እርሱ በሌለበት ከተከራካሪው ጋር መደራደር የለበትም፡፡

56.**በክርክር ወቅት የጠበቃ ግዴታዎች**

ማንኛውም ጠበቃ በክርክር ወቅት የሚከተሉትን ድርጊቶች ከመፈጸም መቆጠብ አለበት፣

1. በምቀኝነት ወይም በክፉ ልቦና ተነሳስቶ ሌላውን ወገን የሚጎዳ ክስ ወይም ክርክር ማቅረብ፣
2. ደንበኛው የወራዳነት ወይም የማጭበርበር ድርጊት እንዲፈጽም ማበረታት ወይም መፍቀድ፣
3. ዳኛን ወይም ሌላ የፍርድ ቤት ሠራተኛን በሕግ መሠረት ከማሳመን ውጭ ሌላ ተገቢ ያልሆነ ማንኛውም ዓይነት ዘዴ በመጠቀም ተጽዕኖ ለማሳደር መሞከር ወይም በሌላ ሰው እንዲሞከር ማድረግ፣
4. ሆን ብሎ ፍርድ ቤትን የሚያሳስት ወይም የተጋነነ ጽሑፎችና ንግግር ማድረግ፣
5. በምስክርነት ቃል ወይም የሠነድ ይዘት ላይ የሐሰት ድርጊት በመፈጸም ፍርድ ቤትን ለማሳሳት መሞከር፣
6. በግልጽ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ማስረጃ አግባብነት ያለው አስመስሎ ለፍርድ ቤት ማቅረብ፣
7. ለጉዳዩ በምስክርነት መቅረብ የሚገባው ሰው ፍርድ ቤት እንዳይቀርብ ማባበል ወይም መምከር፣
8. አንድን ምስክር ተገቢ ባልሆነ መንገድ ማመናጨቅ፣ ማስጨነቅ ወይም ማስፈራራት፣

## 57.<u>አስነዋሪ ከሆኑ ሥነ ምግባሮች ስለመራቅ</u>

ማንኛውም ጠበቃ በሕይወቱ ውስጥ የሙያውን ክብር ሊያጎድፍ ከሚችል ማንኛውም ዓይነት አስነዋሪ ባህሪ የራቀ መሆን አለበት።

## 58.<u>የሥነ ምግባር ጉድለት መፈጸሙን ስለማሳወቅ</u>

ማንኛውም ጠበቃ ከዚህ በታች የተመለከቱት መፈጸማቸውን እንዳወቀ ድርጊቱን የፈጸመውን ሰው ስምና የጥፋቱን ዓይነት በመግለጽ ለፈቃድ ሰጪው አካል ወይም በአካባቢው ለሚገኘው የፍትሕ አስተዳደር ባለሥልጣን የማስታወቅ ግዴታ አለበት፣

1. አንድ ጠበቃ ይህን ደንብ ጥሶ ከተገኘ፣
2. አንድ ሰው የጥብቅና ፈቃድ ሳይኖረው የጥብቅና አገልግሎት ሲሰጥ ከተገኘ፣ ወይም
3. አንድ ጠበቃ በጥብቅና ፈቃዱ ከተፈቀደለት ውጭ ሲሠራ ከተገኘ፡፡

## 59.<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መስከረም 13 ቀን 1992 ዓ.ም**
**መለስ ዜናዊ**
**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## አዋጅ ቁጥር 199/1992

## የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች ፈቃድ አሰጣጥና ምዝገባ አዋጅ

የጥብቅና አገልግሎት በሕግ ሙያ የሠለጠነና ሰፊ ልምድ ያለው፤ የፍርድ ቤት አሠራርን ጠንቅቆ የሚያውቅ፤ የታማኝነት፤ የቅንነትና የእውነተኝነት መንፈስን የተላበሰ ሰው ለሕግ የበላይነትና ለፍትሕ መስፈን ከፍትሕ አካላት ጐን በአጋዥነት የሚሰለፍበት ሙያ በመሆኑ፤

በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ለመሥራት የሚችሉ ጠበቆችን ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ ሁኔታ በተሟላ መልኩ በሕግ መደንገግ በማስፈለጉ፤

የጥብቅና ሥራ የሚሠሩ ሰዎችን የሙያ ብቃት ደረጃ ከሚሰጡት አገልግሎት ጋር የተመጣጠነ ለማድረግ በሥራው ለመሠማራት የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን ከፍ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች ፈቃድ አሰጣጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 199/1992" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

   1. "ፍርድ ቤት" ማለት የፌዴራል ፍርድ ቤቶችንና መሰል የዳኝነት አካላትን ያጠቃልላል፤
   2. "የጥብቅና አገልግሎት" ማለት የገንዘብ ክፍያ በመቀበል፤ ወይም ወደፊት የሚገኝ ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ሲባል ወይም ያለክፍያ ፍ/ቤት

ፊት ሊቀርብ የሚችል ማናቸውንም ዓይነት የውል ስምምነት፤ የድርጅት ማቋቋሚያ፤ ማሻሻያ ወይም ማፍረሻ ሰነድ ወይም ለፍ/ቤት የሚቀርብ ሰነድ ማዘጋጀትን፤ ሦስተኛ ወገኖችን በመወከል በፍ/ቤት ፊት ቀርቦ መከራከርን እና ማናቸውንም ዓይነት የሕግ ምክር አገልግሎት መስጠትን ያጠቃልላል፤

3. "ጠበቃ" ማለት የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ለመስጠት ስሙ በመዝገብ የተመዘገበ የሕግ ባለሙያ ነው፤
4. "የሕግ ጉዳይ ጸሐፊ" ማለት የሕግ ምክርና አስተያየትን በመስጠትና ሕግ ነክ ሰነዶችን በማዘጋጀት ጠበቃውን የሚያግዝ ሰው ነው፤
5. "የጠበቃ ረዳት" ማለት በጠበቃው ሥር በመሆን በጠበቃው የተዘጋጁ የክስ ማመልከቻዎችን ለፍርድ ቤት በማቅረብ ፋይል የሚያስከፍት፣ ከፍርድ ቤት የሚወጡ መጥሪያዎችን ትእዛዞችን እና የፍርድ ግልባጮችን በማውጣት ለሚመለከታቸው ሰዎች የሚያደርስ ሰው ነው፤
6. "ደንበኛ" ማለት ስለራሱ ወይም ስለሌላ ሰው ጉዳይ ማንኛውንም የጥብቅና አገልግሎት ለማግኘት ከጠበቃ ጋር የተዋዋለ ወይም የጉዳዩን ፍሬ ነገር ለጠበቃ ያስረዳ ሰው ነው፡
7. "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የፍትሕ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤[43]
8. "መዝገብ" ማለት ጠበቆች የሚመዘገቡበትና በሚኒስቴሩ የሚጠበቅ ሪኮርድ ነው፤
9. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለፈቃድ አሰጣጥ ሁኔታ እና ስለጠበቆች ምዝገባ

### 3. ፈቃድ ስለማስፈለጉ

1. የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልግ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የጥብቅና ፈቃድ ሊኖረው ይገባል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ቢኖርም የሚከተሉት ሰዎች ያለጥብቅና ፈቃድ አገልግሎት መስጠት ይችላሉ፡

ሀ/ ስለራሱ ጉዳይ የሚከራከር ሰው፤

[43] በአዋጅ ቁጥር 943/2008 መሰረተ የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ሆኗል፡፡

ለ/ ያለክፍያ ለትዳር ጓደኛው፣ ለወላጆቹ፣ ለልጆቹ፣ ለአያቶቹ፣ ለእህቱ፣ ለወንድሙ እንዲሁም ሞግዚት ወይም አሳዳሪ ለሆነለት ሰው የሚከራከር ሰው፤

ሐ/ ከሥራው ጋር በተያያዘ ጉዳይ የሚከራከር የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ፤

መ/ የግል ድርጅትን ወይም ኩባንያን በፍርድ ቤት ለመወከል ሥልጣን ተሰጥቶት የድርጅቱን ወይም የኩባንያውን ጉዳዮች በሚመለከት የሚከራከር ማንኛውም የድርጅት ኃላፊ ወይም ሽሪክ፣

ሠ/ የመንግሥት መሥሪያ ቤትን ወይም የልማት ድርጅትን በሚመለከት የሚከራከር ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የልማት ድርጅት ባለሥልጣን ወይም ኃላፊ ወይም በእርሱ የተወከለ ሰው፤

ረ/ ማንኛውም የሠራተኛ ማኅበር መሪ ወይም ማኅበሩ የሚወክለው ሰው።

4. <u>ፈቃድ ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>

1. የጥብቅና ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ ለዚሁ ተግባር በሚኒስቴሩ በተዘጋጀ ቅጽ ተሞልቶ ይቀርባል፡፡

2. አመልካቹ ከማመልከቻው ጋር የሚከተሉትን ሰነዶች ማቅረብ ይኖርበታል፡

ሀ/ የትምህርት ማስረጃውን፤

ለ/ ከቀድሞ አሠሪው ስለ ሥነምግባሩ ወይም ስለ ሥራ አፈጻጸሙ የሚገልጽ ደብዳቤ፤

ሐ/ እንደአስፈላጊነቱ ፈቃድ ለማግኘት የሚሰጠውን የሙያ መግቢያ ፈተና ማለፉን የሚያሳይ ማስረጃ፣

መ/ የፈቃድ ክፍያ መፈጸሙን የሚያሳይ ማስረጃ፣

ሠ/ የሙያ ኃላፊነት መድን ዋስትና መግባቱን የሚያሳይ ማስረጃ፣

ረ/ ሌሎች በሚኒስቴሩ የሚጠየቁ ማስረጃዎች፤

ማቅረብ አለበት፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሐ) የሚቀርብ ሠርተፊኬት ዋጋ የሚኖረው ፈተና ማለፉ በታወቀ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከቀረበ ብቻ ነው፡፡

5. <u>ፈቃድ ስለመስጠት</u>

1. ሚኒስቴሩ የጥብቅና ፈቃድ ማመልከቻ በአንቀጽ 4 መሠረት ተሟልቶ ሲቀርብለት ከ30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ተገቢውን ውሣኔ መስጠት አለበት፡፡

2. በፈቃዱ ላይ የሚጠቀሱት የሚከተሉትን ይጨምራል፤

ሀ/ የጠበቃውን ሙሉ ስምና ዜግነት፣

ለ/ መደበኛ የመኖሪያና የሥራ አድራሻ፣

ሐ/ የፈቃዱን ዓይነት፣

መ/ የፈቃድ ሰጭውን ስምና ፊርማ።

3. ቋሚ ሥራ ላለው ሰው የጥብቅና ፈቃድ አይሰጥም።

6. **የፈቃድ እድሣት**

1. የጥብቅና ፈቃድ በየአመቱ መታደስ አለበት ፡፡
2. ፈቃድ ለማሳደስ የሚቀርብ ማመልከቻ ፈቃዱ የሚያገለግልበት የአንድ ዓመት ጊዜ ከማለቁ ከአንድ ወር በፊት መቅረብ አለበት ፡፡
3. አመልካች በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው ደንብ የሚወሰነውን የማሳደሻ ክፍያ ይከፍላል፡፡

7. **የፈቃድ ዓይነቶች**

በሚኒስቴሩ የሚሰጡ የሚከተሉት ሦስት ዓይነት የጥብቅና ፈቃዶች ይኖራሉ፤

ሀ/ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ፣

ለ/ የፌዴራል ማናቸውም ፍርድ ቤት ጥብቅና ፈቃድ፣ እና

ሐ/ የፌዴራል ልዩ የጥብቅና ፈቃድ፡፡

8. **የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጥብቅና ፈቃድ**

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ያሟላ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ ይሰጠዋል፡

1. በሕግ ዕውቅና ካገኘ የትምህርት ተቋም በሕግ በዲፕሎማ የተመረቀ፣ የኢትዮጵያን መሠረታዊ ሕጎች የሚያውቅና በሙያው ቢያንስ የአምስት ዓመት ልምድ ያለው ወይም በሕግ በዲግሪ የተመረቀ፣ የኢትዮጵያን መሠረታዊ ሕጎች የሚያውቅና በሙያው ቢያንስ የሁለት ዓመት ልምድ ያለው፣
2. ለፍትሕ ሥራ አካሄድ መልካም ሥነ ምግባር ያለው፣
3. ለደረጃው የሚሰጠውን የጥብቅና መግቢያ ፈተና ያለፈ
4. ምግባረ ብልሹነትን በሚያመለክት ወንጀል ተከሶ ያልተቀጣ፤
5. የሙያ የኃላፊነት መድኅን ዋስትና መግባቱን የሚያሳይ ማስረጃ ያቀረበ፡፡

9. **የፌዴራል ማናቸውም ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ**

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ያሟላ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የፌዴራል ማናቸውም ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ ይሰጠዋል ፡

1. በሕግ ዕውቅና ካገኘ የትምህርት ተቋም በሕግ ዲግሪ የተመረቀ፣ የኢትዮጵያን መሠረታዊ ሕጎች የሚያውቅና በሙያው ቢያንስ የአምስት ዓመት ልምድ ያለው፣
2. ለፍትሕ ሥራ አካሄድ መልካም ሥነ ምግባር ያለው፣
3. ለደረጃው የሚሰጠውን የጥብቅና መግቢያ ፈተና ያለፈ፣
4. ምግባረ ብልሹነትን በሚያመለክት ወንጀል ተከሶ ያልተቀጣ፣
5. የሙያ የኃላፊነት መድኅን ዋስትና መግባቱን የሚያሳይ ማስረጃ ያቀረበ፡፡

10. <u>የፌዴራል ልዩ የጥብቅና ፈቃድ</u>

1. የኅብረተሰቡን አጠቃላይ መብትና ጥቅም ለማስከበር የሚሚገትና ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ያሟላ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የፌዴራል ልዩ የጥብቅና ፈቃድ ይሰጠዋል፤

   ሀ/ በሕግ ዕውቅና ካገኘ የትምህርት ተቋም በሕግ በዲግሪ የተመረቀ፣ የኢትዮጵያን መሠረታዊ ሕጎች የሚያውቅና በሙያው ቢያንስ የአምስት ዓመት ልምድ ያለው፤

   ለ/ ከሚወክለው የህብረተሰብ ክፍል ወይም ደንበኛ ምንም ዓይነት ክፍያ የማይቀበል፣

   ሐ/ ፀባዩ ይህን ኃላፊነት ለመቀበል ተስማሚ የሆነ፤

   መ/ ምግባረ ብልሹነትን በሚያመለክት ወንጀል ተከሶ ያልተቀጣ፡፡

2. የጥብቅና ፈቃድ ያለው ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጹትን የሚያሟላ ከሆነ ልዩ የጥብቅና ፈቃድ ሳያስፈልገው አገልግሎት መስጠት ይችላል፡፡ ነገር ግን ይህን ግልጋሎት ከመስጠቱ በፊት ሚኒስቴሩን ማስታጠቅ አለበት፡፡
3. ሚኒስቴሩ ስለ ልዩ የጥብቅና ፈቃድ አሰጣጥ፣ በፈቃዱ ስለሚሰጠው አገልግሎት ዓይነት የአገልግሎት ጥራት እና ስለ ባለፈቃዶች ሥነ ምግባር ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

11. <u>ለጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና ስለመቀመጥ</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 እና 9 መሠረት የጥብቅና ፈቃድ የሚጠይቀውን መስፈርት የሚያሟላ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የፈተና መመዝገቢያ ክፍያ ፈጽሞ የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና መውሰድ ይኖርበታል፡፡

2. የትምህርት ተቋም ውስጥ በሕግ ቢያንስ በረዳት ፕሮፌሰርነት ወይም የመጀመሪያ ዲግሪ ኖሮት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና ከዚያ በላይ በዳኝነት ወይም ዓቃቤ ሕግነት ወይም በታወቁ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች በሕግ አማካሪነት እና ነገረ ፈጅነት ቢያንስ ለአምስት ዓመት ያገለገለ ማንኛውም ሰው ሥራውን በለቀቀ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የጥብቅና ፈቃድ ማመልከቻ ካቀረበ የጥብቅና መግቢያ ፈተና እንዲወስድ አይገደድም፡፡

12.<u>የመድን ዋስትና ስለመግባት</u>

1. የፌዴራል ፍርድ ቤት ጠበቃ ወይም የጥብቅና አገልግሎት ድርጅት የሙያ ኃላፊነት መድን ዋስትና መግባት ይኖርበታል። አፈጻጸሙ ሚኒስትሩ የፌዴራል ፍ/ቤት ጠበቆች የመድን ዋስትና መግባትን በተመለከተ በቂ ጥናት በማድረግ ለሚነስትሮች ም/ቤት አቅርቦ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚያወጣው ዝርዝር የአፈጻጸም ደንብ በሥራ ላይ እስከሚውልበት ጊዜ ድረስ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (5) እና አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ (5) ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

13.<u>ቃለ መሐላ ስለመፈፀም</u>

ማንኛውም ፈቃድ የሚሰጠው ጠበቃ የሚከተለውን ቃለ መሐላ በጽሑፍ ያረጋግጣል፡ እኔ........... ዛሬ......ቀን........19..... ዓ/ም ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የጥብቅና ፈቃድ ስቀበል በሙያዬ በቅንነትና በታማኝነት በመሥራት የምወክላቸውን የደንበኞቼን ጥቅም ሕግ በሚፈቅደው መጠን ላስከብር፤ ከተከራካሪዎቼና ከሙያ ባልደረቦቹ ጋር በመግባባት ልሠራ እና ለፍርድ ቤቶች ተገቢውን ክብር በመስጠት ለሕግ መከበር አጋዥ ለመሆን ቃል እገባለሁ፡፡

14.<u>ፈቃድን ስለመመለስ</u>

1. ማንኛውም ጠበቃ ከሙያው ውጭ በሆነ ሥራ በዋናነት የተሰማራ እንደሆነ ወይም በሌላ በማናቸውም ምክንያት ሙያዊ አገልግሎት ለመስጠት ያልቻለ እንደሆነ ፈቃዱን እንደሁኔታው ለተወሰነ ጊዜ ወይም በቋሚነት ለሚኒስቴሩ ይመልሳል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ፈቃዱን የመለሰ ጠበቃ ፈቃዱን እንዲመልስ ያስገደደው ምክንያት እንዳበቃ ወይም እንደተወገደ ከሥራው ተለይቶ

በቆየበት ጊዜ በሥነ ምግባር ጉድለት ሊያስጠይቀው የሚችል ጥፋት ካልፈጸመ ፈቃዱን ሊወሰድ ይችላል፡፡

## 15.ፈቃድን ስለማገድ ወይም ስለመሠረዝ

1. ይህን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን ወይም የጠበቆች የሥነ ምግባር ደንብን የጣሰ ጠበቃ እንደሁኔታው ፍቃዱ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ሚኒስቴሩ ከሚከተሉት ሁኔታዎች በአንዱ ፈቃድን ሊሰርዝ ይችላል፤

   ሀ/ ፈቃዱ የተገኘው በማታለል ወይም የሀሰት ማስረጃ ወይም መግለጫ በማቅረብ እንደሆነ፤

   ለ/ ለጥብቅና ሙያ ብቃት የሌለው መሆኑን በሚያሳይ የወንጀል ድርጊት ተከሶ ጥፋተኝነቱ የተረጋገጠ እንደሆነ፤

   ሐ/ ከተሰጠው የጥብቅና ፈቃድ ደረጃ በላይ ሲሠራ የተገኘ እንደሆነ፤

   መ/ በማንኛውም ዓይነት የማጭበርበር ድርጊት ወይም የሙያ ሥነ ምግባሩን በከባድ ሁኔታ በመተላለፍ የጥብቅና ሥራ ማካሄዱ የተረጋገጠ እንደሆነ፤

   ሠ/ ከጥብቅና ሙያ በታገደበት ወቅት የጥብቅና ሙያ አገልግሎት መስጠቱ የተረጋገጠ እንደሆነ፤

   ረ/ ለራሱ ወይም ለሌላ ጠበቃ በአገናኝ አማካይነት ሥራ ለማስገኘት ገንዘብ የሰጠ ወይም ለመስጠት የሞከረ እንደሆነ፤

   ሰ/ ከጥብቅና ሙያ ጋር በግልጽ የሚጋጭ ወይም የማይጣጣም ተጨማሪ ሥራ ሲያከናውን የተገኘ እንደሆነ።
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ሚኒስቴሩ ከሚከተሉት ሁኔታዎች በአንዱ ፈቃድን ሊያግድ ይችላል፡፡

   ሀ/ ያለበቂ ምክንያት ፈቃዱን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 መሠረት ያላሳደሰ እንደሆነ፤

   ለ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተውን በመተላለፍ የሕግ ጉዳይ ጸሐፊ ወይም የጠበቃ ረዳት አድርጎ ያሠራ እንደሆነ።

## 16.ስለመመዝገብ

1. ፈቃድ የተሰጠውን ጠበቃ ስምና ዜግነት፣ የፈቃድ ዓይነት፣ መደበኛ የመኖሪያና የሥራ አድራሻውን እና ሌሎች በሚኒስቴሩ የሚጠየቁ አስፈላጊ መረጃዎች የሚይዝ መዝገብ ይኖረዋል፡፡
2. ስሙ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ሥር በተመለከተው መዝገብ ውስጥ ያልገባ ሰው የጥብቅና አገልግሎት መስጠት አይችልም፡፡
3. መዝገቡ ለሕዝብ ግልጽ ይሆናል።

17.<u>ከጠበቃው ጋር የሚሠሩ ሰዎችን ስለመመዝገብ</u>

1. ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና አገልግሎት ድርጅት በሥራው የሚያግዙትን የሕግ ጉዳይ ጸሐፊዎች፣ የጠበቃ ረዳቶች፣ ፀሐፊዎች፣ የሌሎች ሠራተኞች ስም እና የሥራ ኃላፊነት ሚኒስቴሩ ለዚህ ጉዳይ ለመደበው ባለሥልጣን በጽሑፍ በማሳወቅ ያስመዝግባል።
2. ማንኛውም ጠበቃ ከሚኒስትሩ ወይም በእርሱ ከተወከለ ባለሥልጣን ፈቃድ ሳያገኝ፤

   ሀ/ ከመዝገብ ስሙ የተፋቀን፤

   ለ/ ከጥብቅና ሙያ አገልግሎት የታገደን፤

   ሐ/ በዲሲፕለን ጥፋት ከመሥሪያ ቤቱ የተባረረን ሰው፤

   መ/ ምግባረ ብልሹነትን በሚያመለክት ወንጀል ተከስሶ የተፈረደበትን ወይም፤

   ሠ/ በመንግሥት ሥራ ተቀጥሮ የሚሠራን ሰው፤

   በጠበቃ ረዳትነት ወይም በሕግ ጉዳይ ፀሐፊነት መቅጠር አይችልም፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የሕግ ትምህርት ወይም ሥልጠና ወይም ልምድ የሌለው ሰው በሕግ ጉዳይ ፀሐፊነት ሊቀጠር አይችልም፡፡

18.<u>የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ድርጅትን ስለመመዝገብና ፈቃድ ስለመስጠት</u>

1. የጥብቅና ሙያ ድርጅት ለማቋቋም የሚፈልጉ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ጠበቆች ለሚኒስቴሩ በጽሑፍ ማመልከት ይችላሉ።
2. በዚህ አዋጅ መሠረት የሚቋቋመው ድርጅት የንግድ ማኅበር ያልሆነ ኃላፊነቱ ያልተወሰነ ማኅበር ይሆናል፡፡
3. ሚኒስቴሩ ወይም እርሱ የወከለው ባለሥልጣን የድርጅት ማቋቋሚያ ሠነዱን ከመረመረ በኋላ የድርጅቱ መቋቋም፤

   ሀ/ ጠበቆችን የሥነ ምግባር ደንብ የማይጥስ፤

ለ/ የደንበኞችን ወይም የሦስተኛ ወገኖችን ጥቅም የማይጐዳ፣

መሆኑን ሲያምን ስሙን በመዝገብ አስገብቶ ፈቃድ ይሰጠዋል።

4. ስለጥብቅና ሙያ ድርጅት ፈቃድ አሰጣጥ እና ከዚሁ ጋር ስለተያያዙ ጉዳዮች በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ መመሪያ በዝርዝር ይወሰናል።

## ክፍል ሦስት

## አስፈጻሚ አካላት

### 19.የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር

ሚኒስቴሩ፤

1. የጥብቅና ፈቃድ ይሰጣል፤ ጠበቆችን ይመዘግባል፤ የጥብቅና ፈቃድን ያድሳል፤ ያግዳል፤ ይሠርዛል።
2. በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ በሚወሰነው መሠረት ለሚሰጠው አገልግሎት ክፍያ ያስከፍላል፡፡

### 20.የጥብቅና ፈቃድ ገምጋሚ ኮሚቴ

1. የሚከተሉት አባላት የሚኖሩት የጥብቅና ፈቃድ ገምጋሚ ኮሚቴ (ከዚህ በኋላ “ኮሚቴው”እየተባለ የሚጠራ) ይኖራል፤

   ሀ/ የሚኒስቴሩ ሁለት ተወካዮች፣

   ለ/ የጠበቆች ማኅበር ሁለት ተወካዮች፣

   ሐ/ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ተወካይ።
2. የአንድ አባል የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ሲሆን የኮሚቴው ሰብሳቢ ከአባላቱ ውስጥ በሚኒስትሩ ይሰየማል።

### 21.የኮሚቴው ሥልጣንና ተግባር

ኮሚቴው፤

1. የአመልካቹን ማስረጃዎች መርምሮ አመልካቹ ፈቃድ እንዲሰጠው ወይም እንዳይሰጠው ለሚኒስትሩ የውሣኔ ሀሳብ ያቀርባል፤
2. አመልካቹ ለፍትሕ ሥራ አካሄድ የሚስማማ የሥነ-ምግባር ብቃት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ ማንኛውንም ሰው መጠየቅ ወይም ማስረጃ አስቀርቦ መመርመር ይችላል፤

### 22.የኮሚቴው ስብሰባ

1. ኮሚቴው እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል።

2. ከኮሚቴው አባላት አብዛኛዎቹ ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል
3. የኮሚቴው ውሣኔዎች በስብሰባው በተገኙ አባላት በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ ፡ ሆኖም ድምጽ እኩል በኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሣኝ ድምጽ ይኖረዋል፣
4. በዚህ አንቀጽ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ኮሚቴው የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

23.<u>የጠበቆች የዲሲፕሊን ጉባዔ</u>

1. የሚከተሉት አባላት የሚኖሩት የጠበቆች የዲሲፕሊን ጉባዔ (ከዚህ በኋላ "ጉባዔው" እየተባለ የሚጠራ) ይኖራል፤

   ሀ/ የሚኒስቴሩ ሁለት ተወካዮች፤

   ለ/ የጠበቆች ማኅበር ሁለት ተወካዮች፤

   ሐ/ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ተወካይ፡፡
2. የአንድ አባል የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ሲሆን፤ የጉባዔው ሰብሳቢ ከአባላቱ ውስጥ በሚኒስትሩ ይሰየማል።

24.<u>የጉባኤው ሥልጣንና ተግባር</u>

ጉባኤው፤

1. ይህን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጣውን የሥነ ምግባር ደንብ ወይም መመሪያ በመተላለፍ በጠበቃ ላይ የሚቀርብ ክስን ተቀብሎ ያጣራል፤ ይመረምራል፤
2. በጠበቃው ላይ የቀረበውን ክስ ለማየት የሚያበቃ ማስረጃ መኖሩን ሲያረጋግጥ ጠበቃው መልሱን በ30 ቀን ውስጥ እንዲያቀርብ በመጥሪያው ላይ በመግለጽ ክሱን ለጠበቃው ይልካል፤
3. በጠበቃው ላይ የቀረበውን ክስና ማስረጃ እንዲሁም በጠበቃው በኩል የተሰጠውን መልስና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ፤

   ሀ/ ክሱ ተገቢ ካልሆነ ወይም በበቂ ማስረጃ ካልተደገፈ ክሱን በመሠረዝ ጠበቃው እንዲሰናበት፤

   ለ/ ክሱ ተገቢና በማስረጃ የተደገፈ ከሆነ እንደ ጥፋቱ ክብደት፤

      1) ጠበቃው የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠው፤
      2) ጠበቃው ከአምስት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ከሥራው እንዲታገድ፤
      3) ከብር 10,000 (አስር ሺ ብር) ያልበለጠ ቅጣት እንዲጣልበት፤

4) ፈቃዱ ተሠርዞ ስሙ ከመዝገብ እንዲፋቅ፣ ወይም፣
5) ተገቢነው ያላቸውን ሌሎች ውሣኔዎች እንዲሰጥ፣
የውሣኔ ሃሣብ ለሚኒስትሩ ያቀርባል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ተገቢውን ውሣኔ እስኪወስድ ድረስ የጥብቅና ፈቃዱን ሊያግድ ይችላል፡፡
5. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በጠበቃው ላይ የሚጣለውን የቅጣት መጠን ለመወሰን የወንጀል ሪኮርድ፣ የጠበቃውን የግል ማኅደር ወይም ሌላ ተመሣሣይ ማስረጃ መስማትና መመርመር ይችላል።
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3(ለ) መሠረት የተሰጠው ማንኛውም ውሳኔ በጠበቃው የግል ማኅደር ውስጥ እንዲመዘገብ ያደርጋል፡፡
7. የጠበቆች የሥነ ምግባር ብቃት የሚጎለብትበትን የጥብቅና ሙያ ክብር የሚጠበቅበትን ሁኔታ እየጠና ለሚኒስቴሩ ሀሳብ ያቀርባል።
8. የቀረበውን ማንኛውም ክስ ክሱ በቀረበ ከስድስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የመጨረሻ የወሳኔ ሀሣብ ሚኒስትሩ ያቀርባል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ጉዳዩን ለማጠናቀቅ የማይቻልበት በቂ ምክንያት ሲያጋጥም ምክንያቱን በጽሑፍ በመግለጽ ከሦስት ወር የማይበልጥ ተጨማሪ ጊዜ እንዲፈቀድለት ሚኒስትሩን በጽሑፍ መጠየቅ ይችላል፡፡

## 25.<u>የጉባዔው ስብሰባ</u>

1. ጉባኤው እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ጊዜ መሰብሰብ ይችላል፡፡
2. ከጉባዔው አባላት አብዛኛዎቹ ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፡፡
3. የጉባዔው ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፡፡ ሆኖም እኩል በኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሣኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጉባኤው የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

## 26.<u>የሚኒስትሩ ስልጣን</u>

1. ሚኒስትሩ በአንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም በአንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ከኮሚቴው ወይም ከጉባዔው የቀረበውን የውሣኔ ሃሣብ ከመረመረ በኋላ ተገቢውን ውሣኔ ይሰጣል።

2. ኮሚቴው ወይም ጉባዔው በአግባቡ ያላጣራው ወይም ያላጤነው ፍሬ ነገር ወይም ማስረጃ ካለ ይኸው ተጣርቶ ወይም ተገንዝቦ እንዲቀርብለት ለኮሚቴው ወይም ለጉባዔው ለአንድ ጊዜ መመለስ ይችላል፡፡

27.**<u>የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና አዘጋጅና የችሎታ ብቃት መለኪያ ቦርድ</u>**

1. የሚከተሉት አባላት የሚኖሩት የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና አዘጋጅና የችሎታ ብቃት መለኪያ ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርዱ" እየተባለ የሚጠራ) ይኖራል፤

ሀ/ የሚኒስቴሩ ሁለት ተወካዮች፤

ለ/ የጠበቆች ማኅበር ተወካይ፤

ሐ/ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ተወካይ፤

መ/ የሕግ ፋክልቲዎች ተወካይ፤

ሠ/ በሚኒስትሩ የሚመረጡ ሌሎች ሁለት አባላት፡፡

2. የአንድ አባል የሥራ ዘመን ለአራት ዓመት ሲሆን የቦርዱ ሰብሳቢ በሚኒስትሩ ይመረጣል፡፡

28.**<u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>**

ቦርዱ፤

1. ከሚኒስትሩ ወይም በእርሱ ከሚወከል ባለሥልጣን ጋር በመመካከር በየዓመቱ የጥብቅና ችሎታ መመዘኛ ፈተና እያዘጋጀ በተወሰነ ጊዜና ቦታ ለአመልካቾች ይሰጣል፤
2. የፈተና ወረቀቶችን ያርማል፤ ለማለፊያ የሚያበቃውን ነጥብ ይወስናል፤ የፈተናውን ውጤት ለሚኒስትሩ ወይም በእርሱ ለሚወከል ባለሥልጣን አቅርቦ ሲጸድቅ ውጤቱን በይፋ ያስታውቃል፡፡
3. የሥነ ሥርዓት ደንቡን አዘጋጅቶ ለሚኒስትሩ ያቀርባል፤ ሲጸድቅም በሥራ ላይ ያውላል፡፡

29.**<u>በሚኒስትሩ ላይ ስለሚቀርብ ይግባኝ</u>**

1. ሚኒስትሩ የሰጠው ውሣኔ ስሕተት ያለበት ሆኖ ከተገኘ በውሣኔው ቅር የተሰኘው ወገን ውሣኔው በደረሰው በሠላሣ ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ ወደ ፍሬ ነገር ሳይገባ በሕግ ጉዳይ ላይ ውሣኔ በመስጠት ጉዳዩን ወደ ሚኒስትሩ ይመልሰዋል።

3. የሚኒስትሩ ውሣኔ የሕግ ስሕተት ያለበት ሆኖ ከተገኘ ሚኒስትሩ የፍርድ ቤቱን ውሳኔ መሠረት በማድረግ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ያደርጋል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 30.የጠበቃው ግዴታዎች

ማንኛውም ጠበቃ፤

1. ይህን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጣውን ደንብና መመሪያ እና የሚሰጡትን ትዕዛዞችና ውሣኔዎች የማክበር፤
2. ከደንበኛው ለሚቀበለው ማንኛውም ዓይነት ክፍያ ደረሰኝ የመስጠት፤
3. በደንበኞቹ ላይ በሙያው ለሚያደርሰው የፍትሐ ብሔር ጥፋት ጉዳት ካሣ እንዲሆን በአንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሠረት መድን የመግባት፤
4. ፈቃድ ሲያወጣ፣ ሲያድስና ሲተካ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው ደንብ የሚፈለግበትን የፈቃድ ክፍያ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

### 31.ቅጣት

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የበለጠ ቅጣት የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ሰው፤ በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ ሳያወጣ ወይም የጥብቅና ፈቃዱን ሳያሳድስ የጥብቅና አገልግሎት የሰጠ ወይም ለመስጠት የሞከረ እንደሆነ፤ ከብር ሁለት ሺ ባላነሰ እና ከብር አስር ሺ ብር ባልበለጠ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከስድስት ወር ባላነሰ እና ከሁለት ዓመት ባልበለጠ እሥራት ያቀጣል።

### 32.ደንብ የማውጣት ሥልጣን

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የሚረዱ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

### 33.መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ሚኒስትሩ ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የሚረዱ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

### 34.የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1. የዚህ አዋጅ አንቀጽ (11) እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ አዋጅ በወጣበት ቀን፡-

   ሀ/ የሕግ ዲግሪ ያለው፤ ወይም

   ለ/ የሕግ ዲፕሎማ ያለውና በማናቸውም ፍርድ ቤት ከአሥር ዓመት ላላነሰ የጥብቅና አገልግሎት የሰጠ ወይም በማናቸውም ፍርድ ቤት በዳኝነት ወይም

በዐቃቤ ሕግነት ወይም በነገረ ፈጅነት ያገለገለበት ጊዜ ተዳምሮ ከአሥር ዓመት ያላነሰ አገልግሎት ያለው፤

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቃ፣ በዚህ አዋጅ መሠረት የፌዴራል ማናቸውም ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ እንደተሰጠው ይቆጠራል፡፡

2. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ይህ አዋጅ በወጣበት ቀን፤

ሀ/ የሕግ ዲፕሎማ ያለው፤ ወይም

ለ/ የሕግ ሰርተፊኬት ኖሮት ከአምስት ዓመት ያላነሰ የጥብቅና አገልግሎት የሰጠ ወይም በማናቸውም ፍርድ ቤት በዳኝነት፤ በዓቃቤ ሕግነት ወይም በነገረ ፈጅነት ያገለገለበት ጊዜ ተዳምሮ ከአምስት አመት ያላነሰ አገልግሎት ያለው፤

ሐ/ ሰርተፊኬት ሳይኖረው ከአስር ዓመት ላላነሰ የጥብቅና አገልግሎት የሰጠ ወይም በማናቸውም ፍርድ ቤት በዳኝነት ወይም ዓቃቤ ሕግነት ወይም በነገረ ፈጅነት ያገለገለበት ጊዜ ተዳምሮ ከአስር ዓመት ያላነሰ አገልግሎት ያለውና በሚኒስቴሩ የተሰጠውን ፈተና ያለፈ፤

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጠበቃ፤

በዚህ አዋጅ መሠረት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ እንደተሰጠው ይቆጠራል፡፡

## 35.ስለተሻሩና ተፈጻሚነት ስለሌላቸው ሕጐች

1. ስለጠበቆች በመዝገብ መግባት የወጣው ደንብ /የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 166/1944 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡
2. ይህን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሕግ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## 36.አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከየካቲት 30 ቀን 1992 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት 30 ቀን 1992 ዓ/ም**

**ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**ደንብ ቁጥር 65/1992**

**የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የጥብቅና ፈቃድ፣ የፈተና መመዝገቢያ እና የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ድርጅት መመዝገቢያ ክፍያ መወሰኛ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 4/1987 አንቀጽ (5) እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች ፈቃድ አሠጣጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀጽ 32 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የጥብቅና ፈቃድ፣ የፈተና መመዝገቢያ እና የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ድርጅት መመዝገቢያ ክፍያ መወሰኛ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 65/1992" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **የፈቃድ እና የፈተና መመዝገቢያ ክፍያ**

   በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ አዋጅ ቁጥር 199/1992 መሠረት ለጥብቅና ፈቃድና ለፈተና ለመመዝገቢያ የሚከፈሉ ክፍያዎች የሚከተሉት ናቸው፤

   1. ለፈቃድ ማውጫ ...........................ብር 400.00
   2. ለፈቃድ ማደሻ ..............................ብር 300.00
   3. ለፈቃድ መተኪያ ...........................ብር 100.00
   4. ለፈተና መመዝገቢያ........................ብር 200.00
   5. የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ድርጅት መመዝገቢያ ...............ብር 100.00

3. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ መጋቢት 1 ቀን 1992 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

ሠ/ ሙስናን መከላከል

## ደንብ ቁጥር 144/2000

## የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች አሠራርን ለመወሰን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/1998 አንቀጽ 5 እና በተሻሻለው የፌዴራል የሥነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 433/1997 አንቀጽ 30 (1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የሥነ ምግባር መከተታያ ክፍሎች አሠራር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 144/2000" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፤

1. "ኮሚሽን" ማለት የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ነው፤
2. "አዋጅ" ማለት የተሻሻለው የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 433/1997 ነው፡፡
3. "የመንግሥት መሥሪያ ቤት"፣ "የመንግሥት የልማት ድርጅት"፣ "የመንግሥት ባለሥልጣን" እና "የመንግሥት ሠራተኞች" በአዋጁ አንቀጽ 2 ሥር የተሰጣቸው ትርጓሜ ይኖራቸዋል።

## ክፍል ሁለት

## የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች

3. **መቋቋም**

በመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች ውስጥ የሥነ-ምግባር ጉዳዮችን የሚያስተባብሩና ለየመሥሪያ ቤቶቹና የልማት ድርጅቶቹ የበላይ ሃላፊዎች የሚያማክሩ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች በአዋጁ አንቀጽ 24(1) መሠረት ይቋቋማሉ፡፡

4. **ዓላማዎች**

የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍሎች የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሯቸዋል።

1. ሠራተኛውን በፀረ ሙስና ትምህርቶች፣ በሥራ ዲሲፒሊን፣ በሙያ ሥነ-ምግባር፣ በህዝብ አገልጋይነትና በሃላፊነት ስሜት በማነጽ የነቃና ሙስናን ሊሸከም የማይችል ሠራተኛ እንዲፈጠር ጥረት የማድረግ፤
2. በየመሥሪያ ቤቶቹና የልማት ድርጅቶቹ የሙስና ወንጀልንና ብልሹ አሠራርን የመከላከል፤
3. የሙስና ወንጀልና ብልሹ አሰራር እንዲጋለጥ፣ እንዲመረመርና በአጥፊዎች ላይ ተገቢው እርምጃ እንዲወስድ ጥረት የማድረግ፡፡

5. **<u>አቋም</u>**

1. የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍል በሥነ-ምግባር መኮንን የሚመራ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ሠራተኞች ይኖሩታል።
2. መሥሪያ ቤቱ ወይም ድርጅቱ ቅርንጫፎች ካሉት እንደአስፈላጊነቱ የቅርንጫፍ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች ይቋቋማሉ፡፡

6. **<u>ተጠሪነት</u>**

1. የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍል ተጠሪነት ለሚመለከተው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅት የበላይ ኃላፊ ይሆናል፡፡
2. የቅርንጫፍ የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍል ተጠሪነት ለመስሪያ ቤቱ ወይም ለልማት ድርጅቱ ቅርንጫፍ ሃላፊ ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም የቅርንጫፍ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ከዋናው መስሪያ ቤት የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ጋር የሥራ ግንኙነት ይኖረዋል።

7. **<u>ተግባራት</u>**

የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍል፣

1. የመሥሪያ ቤቱ ወይም የልማት ድርጅቱ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች የፀረሙስና ፖሊሲዎች፣ የፀረ ሙስና ህጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች፣ የመልካም ሥነ-ምግባር፣ የሙስና አስከፊ ገጽታዎችና ጎጂነት ግንዛቤ እንዲዳብር ያደርጋል፡፡
2. የፀረ-ሙስና ፖሊሲዎች፣ የፀረ-ሙስና ህጎች፣ የመሥሪያ ቤቱ ወይም የድርጅቱ ደንቦችና መመሪያዎች መከበራቸውን ይከታተላል፤ ስለአፈጻጸማቸውም የመሥሪያ ቤቱን ወይም የልማት ድርጅቱን የበላይ ኃላፊ ያማክራል፤

3. የመሥሪያ ቤቱን ወይም የልማት ድርጅቱን የሥራ ሃላፊዎችና ሠራተኞች የሥነ-ምግባር መመሪያ አግባብነት ካላቸው የሥራ ክፍሎች ጋር በመሆን ያዘጋጃል፣ ያስፀድቃል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤
4. በመሥሪያ ቤቱ ወይም በልማት ድርጅቱ ለሙስናና ለብልሹ አሠራር ቀዳዳ የሚከፍቱ አሠራሮች እንዲስተካከሉ ለጥናት የሚሆኑ መነሻ ሃሳቦችን በማመንጨት ለኮሚሽኑ ያሳውቃል፤ ይሽንኑ የመሥሪያ ቤቱ ወይም የልማት ድርጅቱ የበላይ ሃላፊ እንዲያውቀው ያደርጋል፤ በራሱ ወይም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ጥናት በማድረግ አማራጭ ሃሳቦችን ለመሥሪያ ቤቱ ወይም ለልማት ድርጅቱ የበላይ ሃላፊን ያቀርባል፤ ሲወሰንም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
5. ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ጋር በመሆን የአስተዳደርና የአገልግሎት አሰጣጥ ለሕዝብ ጥያቄ ተገቢ ምላሽ ለመስጠት በሚያስችል መልክ እንዲሻሻል የመሥሪያ ቤቱን ወይም የድርጅቱን የበላይ ሃላፊ ያማክራል፤ በመሥሪያ ቤቱ ወይም በድርጅቱ አገልግሎት አሰጣጥ መድልዎ እንዳይፈፀም ይከታተላል፣ መድልዎ ተፈጽሞ ሲገኝ ለመሥሪያ ቤቱ ወይም ለድርጅቱ የበላይ ሃላፊ ሪፖርት ያደርጋል፤
6. የሙስና ወንጀል ስለመፈጸሙ ራሱ ጥርጣሬ ሲኖረው ወይም ከሌሎች ወገኖች የሚቀርቡ ጥቆማዎች ካሉ ተቀብሎ ይመዘግባል፣ ለኮሚሽኑ ሪፖርት ያደርጋል፣ ይህንኑ ለመስሪያ ቤቱ ወይም ለልማት ድርጅቱ የበላይ ሃላፊ ያሳውቃል፣ ጉዳዩ የደረሰበትን ሁኔታ ይከታተላል፤
7. በመሥሪያ ቤቱ ወይም በልማት ድርጅቱ ውስጥ ሥነ-ምግባር እንዲዳብር፣ የኃላፊነት ስሜት እንዲጎለብት እና ሙስናን ለማጋለጥ የሚደረገውን እንቅስቃሴ ለማበረታታት ሠራተኛውን ከቂም በቀል እርምጃ ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት በሚዘረጋበት ሁኔታ ላይ የመሥሪያ ቤቱን ወይም የልማት ድርጅቱን የበላይ ሃላፊን ያማክራል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤
8. የሥነ-ምግባር ጥሰቶችን የሚመለከቱ ጥቆማዎችን ተቀብሎ በመሥሪያ ቤቱ ወይም በልማት ድርጅቱ ደንብና መመሪያ መሠረት በማጣራት በቀጣይነት መደረግ ስለሚገባው ምርመራና መወሰድ ስለሚገባው እርምጃ የውሳኔ ሀሳብ ለመሥሪያ ቤቱ ወይም ለድርጅቱ የበላይ ሃላፊ ያቀርባል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ ስለአፈጻፀሙ ለመሥሪያ ቤቱ ወይም ለድርጅቱ የበላይ ሃላፊ ሪፖርት ያቀርባል፤

9. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (8) የተጠቀሰው ጥፋት ከባድ የሥነ-ምግባር መጣስ ነው ብሎ ካመነ ወይም ከባድ የሥነ ምግባር መጣስ መሆኑ የታወቀው ምርመራ ከተደረገ በኋላ ከሆነ እንደታወቀ ወዲያውኑ ጉዳዩን ኮሚሽኑ እንዲያውቀው ሲያደርግ፣ ይኸንኑ ለመስሪያ ቤቱ ወይም ለልማት ድርጅቱ የበላይ ሃላፊ ያሳውቃል፤
10. የሠራተኛን ቅጥር፣ እድገት፣ ዝውውር ወይም ሥልጠና፣ የዕቃ ወይም የአገልግሎት ግዥን ወይም የማንኛውንም ሌላ ውል በሚመለከት ደንብና መመሪያ ተጥሶአል ብሎ ሲያምን ለመሥሪያ ቤቱ ወይም ለድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ማስተካከያ እንዲደረግ ከአስተያየት ጋር ሪፖርት ያደርጋል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤
11. ሰራተኛው የሙስና ወንጀልና ከመልካም ስነ-ምግባር ተቃራኒ የሆኑ ድርጊቶችን በማጋለጡ ማንኛውም ተጽዕኖ እንዳይደርስበት ክትትል ያደርጋል፤ ተጽዕኖ ያደረገ ወይም የቀጣ ወይም ተጽዕኖ ለማድረግ ወይም ለመቅጣት የሞከረ ካለ እያጣራ ከተጨባጭ ማስረጃ ጋር ድርጊቱን ለመሥሪያ ቤቱ ወይም ለድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ሪፖርት ያደርጋል፤ ስለሚወሰድበት እርምጃ ይከታተላል፤ ተፅዕኖ አድራጊው የመሥሪያ ቤቱ ወይም የድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ሲሆን ጉዳዩን ለኮሚሽኑ ወይም ለሚመለከተው የምርመራ አካል ያሳውቃል፤
12. በመሥሪያ ቤቱ ወይም በድርጅቱ የሥነ-ምግባር ጉዳዮች ወይም ችግሮች ላይ ሠራተኛው ወቅታዊ ውይይት እንዲያደርግ የመሥሪያ ቤቱን ወይም የድርጅቱን የበላይ ሃላፊን ያሳስባል፤
13. በራሱ ወይም በውጭ ወይም በውስጥ ኦዲተሮች እርምጃ እንዲወሰድባቸው ወይም እንዲስተካከሉ ሪፖርት በቀረበባቸው ጉዳዮች ላይ ስለተወሰደው እርምጃ እንዲሁም የዲሲፕሊንና የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች የሚያስተላልፏቸው ሪፖርቶችና ውሳኔ የተሰጠባቸው ጉዳዮች ላይ ክትትል በማድረግ ለድርጅቱ ወይም ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ እንዲሁም በግልባጭ ለድርጅቱ ወይም ለመሥሪያ ቤቱ ተቆጣጣሪ አካልና ለኮሚሽኑ ያሳውቃል፤
14. በሕግ ወይም በመመሪያ በሚወጣ መስፈርት መሠረት ሙስናን ወይም ብልሹ አሠራርን በመዋጋት ግንባር ቀደም የሆኑ አርአያነት ያላቸውን የሥራ ሃላፊዎችና ሠራተኞች ዝርዝር መረጃ መዝግቦ ይይዛል፣ ሲጠየቅም ሃላፊውን አሳውቆ መረጃውን ለኮሚሽኑ ይሰጣል፤

15. ሥነ ምግባርን በማስፈንና ሙስናንና ብልሹ አሠራርን በመዋጋት ረገድ በመሥሪያ ቤቱ ወይም በድርጅቱ ውስጥ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን ያቀናጃል፤
16. በየበጀት ዓመቱ ስለሚያከናውናቸው ተግባሮች ዕቅድ፣ መርሃ ግብርና በጀት አዘጋጅቶ ለመሥሪያ ቤቱ ወይም ለድርጅቱ የበላይ ሃላፊና ለኮሚሽኑ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
17. በክፍሉ ስለተከናወነ ተግባራት፣ ስላጋጠሙ ችግሮችና ስለተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች የሩብ ዓመትና ዓመታዊ ሪፖርት በማዘጋጀት ለመሥሪያ ቤቱ ወይም ለድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ሪፖርት ያቀርባል፣ በግልባጭ ለኮሚሽኑ ያሳውቃል፣
18. አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ተለይተው የሚሰጡትን ሥነ-ምግባርን የሚመለከቱ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል።

8. <u>የሥነምግባር መኮንን ኃላፊነት</u>

የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የልማት ድርጅት የሥነ-ምግባር መኮንን በዚህ ደንብ ለሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል የተሰጡትን ተግባራት ያስፈጽማል፡፡

9. <u>የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም ድርጅት የበላይ ኃላፊ ኃላፊነት</u>

የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የልማት ድርጅት የበላይ ኃላፊ የሚከተሉት ኃላፊነቶች አሉበት፤

1. በመሥሪያ ቤቱ ወይም በልማት ድርጅቱ መልካም ሥነ-ምግባር ያለው የሥራ መሪና ሠራተኛ እና የሰመረ የሥራ ግንኙነት እንዲኖርና መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን ክትትል የማድረግ፤
2. የመሥሪያ ቤቱ ወይም የልማት ድርጅቱ የአሠራር ሥርዓት ለሙስናና ለብልሹ አሠራር የማይመች፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለበት እንዲሆን የማድረግ፤
3. የመሥሪያ ቤቱን ወይም የልማት ድርጅቱን የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ሃላፊነቱን ለመወጣት በሚያስችለው አኳኋን በተፈላጊው የሰው ኃይልና አገልግሎቶች በማሟላትና ለኃላፊውና ለሠራተኞቹ ተመጣጣኝ ደመወዝና ጥቅማጥቅሞች በመስጠት ለክፍሉ ምቹ የሥራ ሁኔታን የመፍጠር፤
4. በመሥሪያ ቤቱ ወይም በልማት ድርጅቱ ውስጥ የሥነምግባር ጉድለቶች፣ የሙስናና የብልሹ አሠራር ዝንባሌዎች ሲታዩ በፍጥነት ከሠራተኞችና ከሥራ መሪዎች ጋር የመመካከርና መፍትሔ የመሻት፤

5. የሚወሰዱ አስተዳደራዊና የዲሲፐሊን እርምጃዎች በበቂ ማስረጃ የተደገፉ፣ ክቂም ከበቀል የፀዱ፣ በመሥሪያ ቤቱ ወይም በልማት ድርጅቱ መልካም አስተዳደር ለማስፈን አስተዋጽኦ የሚያደርጉ መሆናቸውን፣ እርምጃዎቹ ሕግንና መመሪያን መሠረት ያደረጉና ፍትሃዊ መሆነቸውን የማረጋገጥ፤
6. የመከታተያ ክፍሉ ለሠራተኛው በቂ የሥነ-ምግባር ትምህርት በየጊዜው መስጠቱን፣ ብልሹ አሠራሮችን ለሙስና የሚያጋልጡ ሁኔታዎችን በበቂ ሁኔታ ተከታትሎ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ ማድረጉን የመከታተልና የመቆጣጠር፤
7. የጠቋሚዎችን የጥበቃ ሥርዓት የመዘርጋትና የጠቋሚዎችን መብቶችና ግዴታዎችን በተለይም የሚከተሉትን የሚመለከት ማስታወቂያ በግልጽ በሚታይ ቦታ ላይ በጉልህ እንዲለጠፍ የማድረግ፤
   ሀ/ ማንኛውም የሥራ ሃላፊ ወይም ሠራተኛ ሙስናና ብልሹ አሠራሮችን የማጋለጥ ግዴታ ያለበት መሆኑንና አለማጋለጥ የሚያስጠይቅ መሆኑን፤
   ለ/ ጥቆማዎች በአካል ቀርቦ በቃል ወይም በጽሁፍ፣ ስምን ገልጾ ወይም ሳይገልጽ በስልክ፣ በፖስታ፣ በኢ-ሜል፣ በፋክስ ወይም በመሳሰሉት የኤሌክትሮኒክስ ዘዴዎች ሊቀርቡ የሚችሉ መሆኑን፣
   ሐ/ በሥነ-ምግባር ደንብ ጥሰት ወይም በሙስና ወንጀል ጠቋሚዎች ላይ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለና ተፈጽሞ ከተገኘ በአስተዳደርና በወንጀል የሚያስጠይቅ መሆኑን፣
   መ/ ሆን ብሎ ሰውን ለማጥቃት በሀሰት የተዘጋጀ ወይም የተቀነባበረ ጥቆማ በአስተዳደርና በወንጀል የሚያስጠይቅ መሆኑን፣
   ሠ/ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሉ የቂም በቀል እርምጃዎችን የሚመረምርና የውሳኔ ሀሳብ የሚያቀርብ መሆኑን፣ ይህንን ሲያደርግ በግልባጭ ለኮሚሽኑ ማሳወቅ የሚገባው መሆኑን፣
   ረ/ በቂም በቀል እርምጃው ላይ መሥሪያ ቤቱ ወይም የልማት ድርጅቱ በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ሠራተኛ ለኮሚሽኑ አቤቱታ ማቅረብ የሚችል መሆኑን፣
8. ለክትትል እንዲያመች በውጭና በውስጥ ኦዲተሮች እርምጃ እንዲወሰድባቸው ወይም እንዲስተካከሉ ሪፖርት የቀረበባቸው ጉዳዮችን የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሉ በግልባጭ እንዲያውቃቸው የማድረግ፤

9. የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሉ ለሥራው ጠቃሚ የሆነ ትምህርትና ሥልጠና እንዲያገኙ ተገቢውን የማድረግ፣
10. የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሉ የሚፈለገውን ትብብር በተሟላ ሁኔታ እንዲያገኝ ሁኔታዎችን የማመቻቸት፡፡

10.<u>የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም ድርጅት ሠራተኞች ኃላፊነት</u>

1. ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የልማት ድርጅት ሠራተኛ የመሥሪያ ቤቱ ወይም የድርጅቱ የሥነ-ምግባር መኮንን ለሥራው የሚፈልጋቸውንና የሚጠይቃቸውን መረጃዎችና ሌሎች ድጋፎች በመስጠት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡
2. ትብብር ስለመከልከል በሌሎች ሕጎች የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ለሥነ ምግባር መኮንኑ ትብብር መከልከል አስተዳደራዊ ተጠያቂነትን ያስከትላል።

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>የቅጥርና የሥራ ሁኔታ</u>

11.<u>የኃላፊና ሠራተኞች አመዳደብ</u>

1. የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊና ሠራተኞችን የመሥሪያ ቤቱ ወይም የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ በቅጥር፣ በዕድገት ወይም በዝውውር ይመድባል፡፡
2. የዚህ ደንብ አንቀጽ 12 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ለሥራ መደቡ የሚያስፈልገው የትምህርትና የሥራ ልምድ እንዲሁም የሥነ-ምግባር ሁኔታ ለልማት ድርጅት ሲሆን በድርጅቱ ደንብና መመሪያ፣ ለመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲሆን በሲቪል ሰርቪስ ሕግ ወይም መሥሪያ ቤቱን በሚመለከተው ልዩ ሕግ መሠረት እና ከኮሚሽኑ ጋር በመመካከር ይወሰናል፡፡
3. የቅጥር፣ የዕድገት ወይም የዝውውር ዝርዝር አፈጻጸም እንደሁኔታው በሲቪል ሰርቪስ ህግ ወይም በመንግስት መስርያ ቤቱ ወይም በልማት ድርጅቱ ሠራተኛ አስተዳደር ደንብ ወይም ህብረት ስምምነት መሠረት ይሆናል፡፡

12.<u>በሥነ-ምግባር መኮንንነት ለመመደብ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች</u>

1. የሥነ-ምግባር መኮንን ሆኖ የሚመደብ ሰው፣

ሀ/ በሥነ-ምግባሩ በአካባቢው የተመሰገነ፣

ለ/ ሙስናና ብልሹ አሠራርን የሚጸየፍና በዚህ አቋሙ የታወቀ፣ እና

ሐ/ ከአደንዛዥ ዕጽና መጠጥ ሱሰኝነት የራቀ እና በዚህ ጽኑ አቋሙ በህብረተሰቡ የታወቀ፣

መሆን አለበት፡፡

2. በሥነ-ምግባር መኮንንነት የሚመደብ ሰው በተቻለ መጠን በሥነምግባር፣ በሕግ፣ በፍልስፍና፣ በፖለቲካል ሳይንስ፣ በሥነ-ማህበረሰብ፣ በሥራ አመራር፣ በሂሳብ አያያዝ ወይም በመንግስት መስርያ ቤቱ ወይም የልማት ድርጅቱ ስራዎች ጋር ተያኘነት ባለው ሌላ ተዛማጅ ትምህርት የሰለጠነ ሲሆን ይገባል፡፡

13. <u>ስለ ደረጃ እድገትና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች</u>

1. የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ወይም በመንግሥት ልማት ድርጅት ውስጥ የስነ-ምግባር መኮንን ሆኖ የተቀጠረ ወይም የተመደበ ማንኛውም ሰው በመስርያ ቤት ወይም በድርጅቱ ደንብና መመርያ መሰረት ለደረጃ እድገት የመወዳደር መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

2. ለሌሎች የመንግስት መስርያ ቤቱ ወይም የልማት ድርጅቱ ሰራተኞች ተፈጻሚ የሚሆኑ ጥቅማ ጥቅሞች ለስነ-ምግባር መኮንኑም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

3. ልዩ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊነት ወይም የስነ-ምግባር መኮንነት የስራ ልምድ በማንኛውም መስርያ ቤቱ ወይም የልማት ድርጅቱ የስራ ክፍል ውስጥ እንደተሰራ አግባብነት ያለው የስራ ልምድ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

14. <u>ስለመደበኛና ስለተደራቢ ሥራ</u>

1. የሥነ-ምግባር መኮንኑ ሥራውን የሚያከናውነው በሙሉ የሥራ ጊዜው ይሆናል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው ቢኖርም ስራው ሙሉ ጊዜ የማይወስድ በሚሆንበት ጊዜ የስነ-ምግባር መኮንኑ መደበኛ ስራውን በማይጎዳ ሁኔታ ከሙያው ጋር ተዛማጅነት ያለው ሌላ ስራ ሊሰራ ይችላል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የዲስፕሊን እርምጃ አወሳሰድ</u>

15. <u>የዲስፕሊን እርምጃ አወሳሰድ</u>

በዚህ ደንብ አንቀጽ 16 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሥነ-ምግባር መኮንን ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ አግባብ ባለው ሕግና የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ወይም የልማት ድርጅቱ ደንብ መሠረት ይጠየቃል፡፡

**16.ክስራ ስለማስነሳት**

1. ከባድ የሥነ-ምግባር ጥሰት የፈጸመ ወይም ሥራውን በአጥጋቢ ሁኔታ ያላከናወነ የሥነ-ምግባር መኮንን አግባብነት ባለው ሕግና የመሥሪያ ቤቱ ወይም የልማት ድርጅቱ ደንብ መሠረት ከኃላፊነቱ ሊነሳ ይችላል፡፡
2. የመሥሪያ ቤቱ ወይም የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ በሥነ-ምግባር መኮንኑ ላይ ያሳለፈውን ውሳኔ ለመሥሪያ ቤቱ ወይም ለልማት ድርጅቱ ሠራተኞች በተገኘው ማናቸውም ዘዴ ማሳወቅ አለበት፡፡

**17.ስለቅሬታ አቀራረብና ስለይግባኝ**

1. የሥነ-ምግባር መኮንኑ ከሥራው የታገደበት ወይም የተነሳበት ምክንያት አለአግባብ ነው ብሎ ካመነ አግባብ ባለው ሕግና በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ወይም የልማት ድርጅቱ ደንብ ወይም የህብረት ስምምነት መሠረት ሥነሥርዓቱን ተከትሎ ቅሬታ ወይም ይግባኝ ለማቅረብ ይችላል፡፡
2. በቀረበው ቅሬታ ወይም ይግባኝ መሠረት የተወሰደው እርምጃ ተገቢ አለመሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ የመሠሪያ ቤቱ ወይም የድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ይህንኑ ለሠራተኛው በተገኘው ማናቸውም ዘዴ ማሳወቅ አለበት፡፡

**ክፍል አምስት**

**የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎችና የኮሚሽኑ የስራ ግንኙነት**

**18.ትብብር**

በዚህ ደንብ ሌሎች አንቀጾች የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆኖ ኮሚሽኑ፣

1. የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች በመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሥነ-ምግባር ትምህርትን ለማስፋፋትና ሙስናን ለመከላከል በሚያደርጉት ጥረት የቴክኒክና የሙያ ዕገዛ ያደርጋል፣ ስልጠናዎችን ያዘጋጃል፣ እንዲሰጥ ያደርጋል፤
2. ከመሥሪያ ቤቶችና ከልማት ድርጅቶች የበላይ ኃላፊዎችና የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች ጋራ የሚወያይበት የጋራ መድረክ በማዘጋጀት የተከናወኑ ተግባራትና ባጋጠሙ ችግሮች ላይ ይወያያል፡፡
3. በስነ-ምግባር መከታታያ ክፍሎች በሚቀርቡ ሌሎች የትብብርና የድጋፍ ጥያቄዎች መሰረት አስፈላጊውን ትብብርና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

19.**ስለስነምግባር መከታታያ ክፍሎች ጉዳይ ክፍል**

ኮሚሽኑ በየመሥሪያ ቤቱ ወይም በየልማት ድርጅቱ የሚገኙ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎችን ጉዳይ የሚከታተልና ኮሚሽኑን የሚያማክር የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች ጉዳይ ክፍል አመቺ መስሎ በታየው መልኩ ያደራጃል፡፡

20.**ሪፖርት ስለማቅረብ**

የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል፣

1. በመንግሥት መ/ቤቱ ወይም በልማት ድርጅቱ የሥነ-ምግባር ትምህርቶችን በመስጠት ረገድ ስለተሰሩ ሥራዎችና ስላጋጠሙ ችግሮች፣
2. በመስሪያ ቤቱ ወይም በልማት ድርጅቱ ለሙስናና ለብልሹ አሰራር የተጋለጡ አሰራሮችን ለማስተካከል ስለተወሰዱ እርምጃዎችና ስላጋጠሙ ችግሮች፣
3. በመሥሪያ ቤቱ ወይም በልማት ድርጅቱ ስለተከሰቱ የሙስና ወይም የብልሹ አሠራር ችግሮች፣ ስለተወሰዱ እርምጃዎች ወይም ሁኔታው ስላለበት ደረጃ፣ እና
4. በኮሚሽኑ በኩል ሊደረጉ ስለሚገባቸው ድጋፎችና ትብብሮች፣ በየሩብ አመቱና በየአመቱ ለኮሚሽኑ ሪፖርት ያቀርባል።

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

21.**የቂም በቀል እርምጃ ስለመከልከሉ**

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 7 ለሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል የተሰጡትን ተግባራት በማከናወኑ ምክንያት በሥነ-ምግባር መኮንን ላይ የቂም በቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው፡፡
2. የቂም በቀል እርምጃ የተወሰደበት የሥነ-ምግባር መኮንን የበቀል እርምጃው እንዲታገድለት ለኮሚሽኑ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡
3. ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ የቂም በቀል እርምጃ መወሰዱን ካረጋገጠ የበቀል እረምጃው እንዲቆም የእግድ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

22.**ቅነሳ**

ሠራተኛን መቀነስ ግዴታ በሚሆንበት ወቅት የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ሃላፊን ሠራተኞች በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 29(3) ሠ ለሠራተኞች ተጠሪዎች የተሰጠው ጥበቃ ይደረግላቸዎል፡፡

**23.** **<u>ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>**

ይህንን ደንብ የሚቃረኑ ደንቦችና የአሠራር ልማዶች በዚህ ደንብ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም ፡፡

**24.** **<u>መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን</u>**

ኮሚሽኑ ለዚህ ደንብ አፈጻጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**25.** **<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር 23 ቀን 2000 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

# አዋጅ ቁጥር 668/2002

## የሀብት ማሳወቂያና ማስመዝገቢያ አዋጅ

ሀብትን ማሳወቅና ማስመዝገብ የመንግሥት አሠራርን በግልጽነትና በተጠያቂነት ላይ ለመመስረት አስፈላጊ በመሆኑ፤

ሀብት ማሳወቅና ማስመዝገብ ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከልና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ፤

የመንግሥት የሥራ ሃላፊነትና የግል ጥቅም ሳይቀላቀሱ በየራሳቸው መንገድ የሚመሩበትን ግልጽ ሥርዓት መዘርጋት ሊፈጠር የሚችለውን የጥቅም ግጭት ለማስወገድ እንደሚረዳ በመታመኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55 (1) መሠረት ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የሀብት ማሳወቂያና ማስመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር 668/2002" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

   1. "ሀብት" ማለት ማንኛውም የማይንቀሳቀስ ወይም የሚንቀሳቀስ ወይም ግዙፍነት ያለው ወይም የሌለው ንብረት ሲሆን የመሬት ይዞታን እና ዕዳን ይጨምራል፤
   2. "ኮሚሽን" ማለት የፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ነው፤
   3. "የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል" ማለት በመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም በመንግስት የልማት ድርጅት የስነ-ምግባር ሁኔታን የሚያስተባብርና የሚያማክር አካል ነው፤
   4. "ተሿሚ" ማለት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

      ሀ/ የሪፐብሊኩን ፕሬዚዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩን፣ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩን፣ ሚኒስትሮችን፣ ሚኒስትር ዴኤታዎችን፣ ምክትል ሚኒስትሮችን፣ ኮሚሽነሮችን፣ ምክትል ኮሚሽነሮችን፣ ዋና ዳይሬክተሮችንና ምክትል ዋና ዳይሬክተሮችን፤

ለ/ የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮች ከንቲባዎችንና ሌሎች ተሿሚዎችን፣

ሐ/ የመደበኛና የከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ፕሬዝዳንቶችን፣ ምክትል ፕሬዝዳንቶችንና ዳኞችን፣

መ/ የመከላከያ ሠራዊትና ፖሊስ ተሿሚዎችን፣

ሠ/ አምባሳደሮችን፣ የቆንስላዎችና የሌሎች የዲፕሎማቲክ ሚሲዮን ኃላፊዎችን፣

ረ/ ዋና ኦዲተርንና ምክትል ዋና ኦዲተርን፣

ሰ/ የብሔራዊ ባንክ ገዥና ምክትል ገዢን፣

ሸ/ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሥራ አመራር ቦርድ አባላትን፣ ሥራ አስኪያጆችንና ምክትል ሥራ አስኪያጆችን፣

ቀ/ የመንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች ፕሬዝዳንቶችንና ምክትል ፕሬዝዳንቶችን።

5. "ተመራጭ" ማለት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

ሀ/ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባሎችን፣

ለ/ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባሎችን፣ እና

ሐ/ የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደር ምክር ቤቶች አባሎችን።

6. "የመንግሥት ሠራተኛ" ማለት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

ሀ/ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች የመምሪያ ኃላፊነት፣ የዳይሬክተርነት፣ የአገልግሎት ኃላፊነትና ከነዚህ ተመጣጣኝና በላይ ደረጃ ያላቸው ሠራተኞችን፣

ለ/ የተሿሚዎች አማካሪዎችን፣

ሐ/ ፈቃድ የመስጠት፣ የመቆጣጠር ወይም ግብር የመሰብሰብ ሥራ የሚያከናውኑ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሠራተኞችን፣ ዐቃቤ ሕጎችን፣ መርማሪዎችን፣ የትራፊክ ፖሊሶችን፣ እና

መ/ ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ ተለይተው የሚወሰኑ ሌሎች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሠራተኞችን።

7. "ቤተሰብ" ማለት የተሿሚ፣ የተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ የትዳር ጓደኛ ወይም በሥሩ የሚተዳደር ዕድሜው 18 ዓመት ያልሞላ ልጅ ሲሆን ጋብቻ

ሳይፈጽም እንደ ባልና ሚስት አብሮ የሚኖር ሰውን እና የጉዲፈቻ ልጅን ይጨምራል፤

8. "የቅርብ ዘመድ" ማለት የተሿሚ፣ የተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ ወላጆችን፣ ተወላጆችን፣ እህቶችን፣ ወንድሞችን እና ሌሎች እስከ ሦስተኛ ደረጃ የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያላቸው ሰዎችን ያጠቃልላል፤
9. "የመንግስት መስርያ ቤት" ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግስት በጀት የሚተዳደርና የህግ አውጪነት፣ የዳኝነት እና ወይም አስፈጻሚነት የመንግስት ስራዎች የሚከናወኑበት ማናቸውም መስርያ ቤት ነው፤
10. "የመንግስት ልማት ድርጅት" ማለት የባለቤትነት ድርሻ በሙሉ ወይም በከፊል ያለበት ማንኛውም የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም የአክሲዮን ኩባንያ ነው፤
11. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
12. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸ አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

3. **የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ አዋጅ በፌዴራል መንግሥት እና በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮች ተሿሚዎች፣ ተመራጮችና የመንግስት ሠራተኞች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ሀብትን ስለማሳወቅና ስለማስመዝገብ

4. **የማስመዝገብ ግዴታ**

1. ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ፡-

   ሀ/ በራሱና በቤተሰቡ ባለቤትነት ወይም ይዞታ ሥር የሚገኝ ሀብትን፣ እና

   ለ/ የራሱንና የቤተሰቡን የገቢ ምንጮች፣ የማሳወቅና የማስመዝገብ ግዴታ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ሀብቱን የሚያስመዘግብ ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ የራሱንና የቤተሰቡን ሀብትና የገቢ ምንጮች ለየብቻ ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀ ቅጽ ላይ በመሙላት ትክክለኛነቱን በፊርማው ያረጋግጣል።

5. **<u>በምዝገባ ስለማይካተት ሀብት</u>**
   1. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ድንጋጌ ቢኖርም የሚከተሉት ሀብቶች አይመዘገቡም፡-
      ሀ/ በውርስ ተገኝቶ በጋራ የተያዘና ለወራሾቹ የግል አገልግሎት የሚውል ንብረት፤
      ለ/ የቤት እቃዎችና የግል መገልገያዎች፤
      ሐ/ ከጡረታ የሚገኝ ገቢ፡፡
   2. ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1//ሀ/ መሠረት በጋራ የተያዘ ንብረት በወራሾች መካከል እንደተከፋፈለ ድርሻውን አሳውቆ ማስመዝገብ አለበት፡፡
6. **<u>ስለመዝጋቢው አካል</u>**
   1. የተሿሚዎችን፣ የተመራጮችንና የመንግሥት ሠራተኞችን ሃብት የሚመዘግበው ኮሚሽኑ ይሆናል፡፡
   2. ኮሚሽኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የተሿሚዎችን፣ የተመራጮችን ወይም የመንግሥት ሠራተኞችን ሃብት እንዲመዘግብ እንደሁኔታው በሙሉ ወይም በከፊል የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍልን ሊወክል ይችላል፡፡
   3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት ውክልና የተሰጠው እያንዳንዱ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት የቀረበለትን የሃብት ማስመዝገቢያ ስነድ ምዝገባው በተደረገ በ30 ቀናት ውስጥ ለኮሚሽኑ ያስተላልፋል።
   4. ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ መሠረት የተከናወኑ የሀብት ምዝገባ ሰነዶች ጠባቂ ሆኖ ያገለግላል። ሃብታቸውን ላስመዘገቡ ተሿሚዎች፣ ተመራጮችና የመንግሥት ሠራተኞች የምዝገባ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡
7. **<u>ምዝገባ ስለሚካሄድበት ጊዜ</u>**
   1. ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግስት ሠራተኛ ይህ አዋጅ ስራ ላይ ከዋለበት ከስድስት ወር በኋላ ባለው ስድስት ወር ውስጥ ሀብቱን ማሳወቅና ማስመዝገብ አለበት፡፡
   2. ማንኛውም አዲስ ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግስት ሠራተኛ ሀብቱን የሚያሳውቀውና የሚያስመዘግበው ከተሾመበት፣ ከተመረጠበት ወይም ከተቀጠረበት ቀን ጀምሮ በ45 ውስጥ ነው፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ወይም /2/ መሠረት ሀብቱን ያስመዘገበ ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ ከዚያ በኋላ ሀብቱን የሚያሳውቀውና የሚያስመዘግበው በየሁለት ዓመቱ ሆኖ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በ30 ቀናት ውስጥ ይሆናል፡፡

8. <u>የምዝገባ ጊዜን ስለማራዘም</u>

1. የምዝገባ ጊዜ እንዲራዘምለት የሚጠይቅ ሰው ምዝገባውን ማራዘም ያስፈለገበትን ምክንያት በጽሑፍ በመግለጽ የምዝገባ ጊዜው በተጠናቀቀ በአምስት ቀናት ውስጥ ለኮሚሽኑ ወይም ለሚመለከተው የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ማመልከት ይችላል።
2. ኮሚሽኑ ወይም ጉዳዩ የሚመለከተው የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የቀረበለት ጥያቄ በበቂ ምክንያት የተደገፈ ሆኖ ሲያገኘው የምዝገባውን ጊዜ ለአንድ ጊዜ እስከ 30 ቀናት ሊያራዝም ይችላል።
3. የምዝገባ ጊዜ እንዲራዘምለት ለሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ያቀረበው አቤቱታ ውድቅ የተደረገበት አመልካች ውሳኔው በደረሰው አምስት ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለኮሚሽኑ ሊያቀርብ ይችላል። ኮሚሽኑ የሚሰጠው ውሳኔም የመጨረሻ ይሆናል፡፡

9. <u>ዘግይቶ ስለማስመዝገብ</u>

በመደበኛው ወይም በተራዘመለት የማስመዝገቢያ ጊዜ ውስጥ ሀብቱን ያላስመዘገበ ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ ብር አንድ ሺ መቀጫ ከፍሎ በ30 ቀናት ውስጥ ሊያስመዘግብ ይችላል፡፡

10. <u>ከስንብት በኋላ ስለሚከተሉ ግዴታዎች</u>

ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ በጡረታ ሲገለል ወይም በማንኛውም ምክንያት አገልግሎቱን ሲያቋርጥ ሁብቱን በ30 ቀናት ውስጥ ለኮሚሽኑ ወይም ለሚመለከተው የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል እንዲሁም ከሁለት ዓመት በኋላ ለመጨረሻ ጊዜ ለኮሚሽኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

11. <u>የምዝገባን ትክክለኛነት ስለማረጋገጥ</u>

1. ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት በተሿሚ፣ በተመራጭ ወይም በመንግሥት ሠራተኛ በተሞላ መረጃ ያልተሟላ፣ ትክክል ያልሆነ ወይም የሀሰት መረጃ የያዘ መሆኑን ለመጠርጠር በቂ ምክንያት ሲኖረው ወይም ሀብቱ

በትክክል አልተመዘገበም የሚል ጥቆማ ሲቀርብ ወይም በተፈጸመ ወንጀል ምክንያት ምርመራ ሲጀመር የምዝገባውን ትክክለኛነት የማጣራት ተግባር ያከናውናል።

2. ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የማጣራት ተግባር ሲያከናውን፡-

ሀ/ ጉዳዩ የሚመለከተው ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ ተጨማሪ መረጃ ወይም ማብራሪያ እንዲያቀርብ ሊጠይቀው፣

ለ/ የተሿሚውን፣ የተመራጩን ወይም የመንግሥት ሠራተኛውን ሀብት የሚመለከት መረጃ ያለው ባንክ፣ የፋይናንስ ተቋም ወይም ማንኛውም ሌላ ሰው መረጃውን እንዲሰጥ ሊያዘው፣ እና

ሐ/ የዋና ኦዲተርን ወይም የሌላ አግባብነት ያለውን አካል ሙያዊ ድጋፍ ሊጠቀም፣ ይችላል።

3. ኮሚሽኑ ያልተሟላ፣ ትክክል ያልሆነ ወይም የሀሰት መረጃ መቅረቡን በማስረጃ ሲያረጋግጥ ጥፋት በፈጸመው ሰው ላይ በህጉ መሠረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድበት ያደርጋል፡፡

12.<u>የምዝገባ መረጃ ተደራሽነት</u>

1. በኮሚሽኑ እጅ የሚገኝ ማንኛውም የተሿሚ፣ የተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ የሀብት ምዝገባ መረጃ ለህዝብ ክፍት ይሆናል፡፡
2. ስለሀብት ምዝገባ መረጃ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ጥያቄውን በጽሁፍ ለኮሚሽኑ ወይም ጉዳዩ ለሚመለከተው የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ሊያቀርብ ይችላል።
3. ኮሚሽኑ ወይም የሚመለከተው የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል የቀረበውን ጥያቄ በመቀበል የምዝገባውን መረጃ ለጠየቀው ሰው መስጠት አለበት፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ቢኖሩም የቤተሰብ ሀብትን የሚመለከት የምዝገባ መረጃ ለፍትህ ሥራ ወይም ኮሚሽኑ አስፈላጊ ነው ብሎ ለሚወስነው ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር በሚስጥር የሚያዝ ይሆናል፡፡
5. ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ መሠረት በየሁለት ዓመቱ ስላከናወነው የሀብት ምዝገባ አጠቃላይ መረጃ በሪፖርት መልክ ያወጣል።

## 13.የሃብት አለመመዝገብ የሚያስከትለው ውጤት

በዚህ አዋጅ መሠረት ያልተመዘገበ ማናቸውም የተሿሚ፣ የተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ ሀብት ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በስተቀር ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 419/2/[44] ድንጋጌ አፈጻጸም ሲባል ምንጩ እንዳልታወቀ ንብረት ይቆጠራል።

## ክፍል ሶስት

## የጥቅም ግጭትን ስለማሳወቅና ስለማስወገድ

## 14.መርህ

ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ የያዘውን መንግሥታዊ የሃላፊነት ቦታ የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ብቻ ማዋል አለበት፡፡ በማንኛውም ምክንያት ቢሆን በሥራው አጋጣሚ ያገኘውንና ሕዝብ እንዲያውቀው ያልተደረገን መረጃ ለግል ጥቅሙ ማዋል የለበትም፡፡

## 15.ስጦታ፣ መስተንግዶና የጉዞ ግብዣ

1. ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ የመወሰን ሥልጣኑን የሚፈታተን ወይም የጥቅም ግጭት የሚፈጥር ስጦታ፣ መስተንግዶ ወይም የጉዞ ግብዣ መቀበል የለበትም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገው ቢኖርም የቀረበለትን ስጦታ፣ መስተንግዶ ወይም የጉዞ ግብዣ ያለመቀበል በስራ ግንኙነት ላይ ጉዳት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ስጦታውን፣ መስተንግዶውን ወይም የጉዞ ግብዣውን ለመቀበል ይችላል፡፡ ሆኖም የተቀበለውን ስጦታ አግባብ ላለው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የልማት ድርጅት ገቢ ማድረግ ወይም መስተንግዶውን ወይም የጉዞ ግብዣውን ለኮሚሽኑ ወይም አግባብ ላለው የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ማሳወቅ አለበት፡፡

## 16.የጥቅም ግጭትን ለማስወገድ መወሰድ ስላለበት እርምጃ

1. ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ በመንግሥት የሥራ ሃላፊነቱና በራሱ ወይም በቅርብ ዘመዱ የግል ጥቅም መካከል ግጭት ሊያስከትልበት የሚችል ጉዳይ ሲያጋጥመው፡-

---

[44] ይህ ድንጋጌ በ21/36(2007) አ.881 አንቀፅ 35 ተሽሯል።

ሀ/ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ወይም አስተያየት ከመስጠት እንዲሁም ከኃላፊነቱ ጋር የማይጣጣም ወይም ታማኝነቱን ጥርጣሬ ውስጥ የሚጥል ማንኛውንም ድርጊት ከመፈጸም መቆጠብ፣ እና

ለ/ ሁኔታውን ለሚመለከተው የበላይ ኃላፊ ማሳወቅ

አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የጥቅም ግጭት ሊከሰት መቻሉ የተገለጸለት የበላይ ኃላፊ እንደሁኔታው ተሿሚው፣ ተመራጩ ወይም የመንግሥት ሠራተኛው ጉዳዩን ማየቱን እንዲቀጥል መመሪያ ሊሰጠው ወይም ሌላ ሰው ተተክቶ እንዲያየው ሊያደርግ ይችላል።

17. **<u>የጥቅም ግጭት መከሰቱን ተከትሎ ስለሚወሰድ እርምጃ</u>**

ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ በመንግሥት የሥራ ሃላፊነቱና በራሱ ወይም በቅርብ ዘመዱ የግል ጥቅም መካከል ግጭት መከሰቱን ተከትሎ በራሱ ተነሳሽነት ወይም በበላይ ኃላፊው ሲጠየቅ ጥፋተኛ መሆኑን በይፋ አምኖ ይቅርታ የመጠየቅ ወይም ራሱን ከኃላፊነት የማግለል ግዴታ አለበት፡፡

18. **<u>ከሥራ መልቀቅ በኋላ ስለሚኖር ክልከላ</u>**

ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ ሥራ በለቀቀ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ሲቆጣጠራቸው ከነበረው ሰዎች ጋር ጥቅም የሚያስገኙ ሥራዎች መሥራት የለበትም፡፡ ዝርዝሩ በደንብ እና /ወይም/ በመመሪያ ይገለጻል፡፡

19. **<u>የጥቅም ግጭትን የማሳወቅ ግዴታን ስላለመወጣት</u>**

ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ የጥቅም ግጭት መኖሩን በዚህ አዋጅ መሠረት የማሳወቅ ግዴታውን ካልተወጣ አግባብ ባለው የሥነ-ምግባር ደንብ መሠረት ተገቢው አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስድበታል።

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

20. **<u>ጥቆማ ስለማቅረብ</u>**

1. ማንኛውም ሰው ይህንን አዋጅ ጥሷል በሚለው ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ ላይ ጥቆማ ማቅረብ ይችላል።
2. ጥቆማው እስከተቻለ ድረስ ከደጋፊ ማስረጃ ጋር በፅሁፍ ለኮሚሽኑ ወይም አግባብ ላለው የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ይቀርባል፡፡

3. በቀረበው ጥቆማ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ የምርመራ ሂደቱና መዛግብቱ በሚስጥር ተይዘው ይቆያሉ።
4. በዚህ አንቀጽ መሠረት በቀረበ ጥቆማ የተገኘው መረጃ በወንጀል ህግ አንቀጽ 419(2)[45] የሀብት መወረስ ውሳኔ ለማሰጠት ካስቻለ የተወረሰው ሀብት ከሚያስገኘው ገቢ ውስጥ 25 በመቶ ለጠቋሚው ይከፈላል።

21.<u>የአዋጁን ተፈጻሚነት ስለማረጋገጥ</u>

ማንኛውም የመንግስት መስርያ ቤት ወይም የመንግስት የልማት ድርጅት የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በስራ ላይ መዋላቸውን ለማረጋገጥ፡-

1. ተሿሚዎች፣ ተመራጮችና የመንግስት ሠራተኞች ሀብታቸውን በወቅቱ እንዲያስመዘግቡ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
2. አግባብ ያላቸው የስነ-ምግባር ደንቦችን አውጥቶ ተፈጻሚ ያደርጋል፡፡

22.<u>ቅጣት</u>

1. ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ፡-
   ሀ/ ሀብቱን በዚህ አዋጅ መሠረት ለምዝገባ ሳያሳውቅ ከቀረ ወይም ሆን ብሎ ትክክል ያልሆነ የምዝገባ መረጃ ከሰጠ፣ ወይም
   ለ/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በመተላለፍ ስጦታ፣ መስተንግዶ ወይም የጉዞ ግብዣ ከተቀበለ ወይም የተቀበለውን ስጦታ፣ መስተንግዶ ወይም የጉዞ ግብዣ ሳያሳውቅ ከቀረ፣

   በወንጀል ሕግ አንቀጽ 417[46] መሠረት ይቀጣል።
2. ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 20 መሠረት ለኮሚሽኑ ወይም ለሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ጥቆማ አቅርቧል ወይም ምስክርነት ሰጥቷል ወይም ጥቆማ ለማቅረብ ወይም ምስክርነት ለመስጠት ተዘጋጅቷል በሚል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የበቀል እርምጃ የወሰደ እንደሆነ በወንጀል ህግ አንቀጽ 444 መሠረት ይቀጣል።
3. ማንኛውም ተሿሚ፣ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ የጥቅም ግጭት መኖሩን ሳያሣውቅም ሆነ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት ተፈቅዶለት ሲሠራ የመንግሥት ኃላፊነቱን ተጠቅሞ የራሱን ወይም የቅርብ

[45] ይህ ድንጋጌ በ21/36(2007) አ.881 አንቀፅ 35 ተሽሯል፡፡
[46] ይህ ድንጋጌ በ21/36(2007) አ.881 አንቀፅ 35 ተሽሯል፡፡

ዘመዱን የግል ጥቅም ያራመደ እንደሆነ አግባብ ባለው የወንጀል ህግ ድንጋጌ መሠረት ይቀጣል፡፡

4. ማንኛውም ሰው በክፉ ልቦና በመነሳሳት ምንም ዓይነት መሠረት የሌለው ጥቆማ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 20 መሠረት ካቀረበ እስከ ሦስት ዓመት ሊደርስ በሚችል እሥራት ወይም እስከ ብር 2,000 ( ሁለት ሺ) በሚደርስ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

23.**ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጐች**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ህግ ወይም ማንኛውም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

24.**ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ኮሚሽኑ ይህንን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

25.**አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሚያዝያ 4 ቀን 2002 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትየጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት**

## ክፍል ሰባት

## በተለይ የወጡ የወንጀል ህጎች

## አዋጅ ቁጥር 384/1996 ዓ.ም

## አደገኛ ቦዘኔነትን ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ

በሀገራችን በየጊዜው በቁጥር እየጨመረና እየተስፋፋ በመሄድ ላይ የሚገኘው አደገኛ ቦዘኔነት ሁኔታ በሕዝብ የተረጋጋ ኑሮና ፀጥታ ላይ ከፍተኛ ሥጋትን እያስከተለ መምጣቱን በመገንዘብ፤

ይህን ሥጋት ዘለቄታ ባለው መንገድ ለመቅረፍ ወንጀለኞችን ለፍርድ ማቅረብና ማህበራዊ ተሃድሶ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55/1/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የአደገኛ ቦዘኔነት መቆጣጠርያ አዋጅ ቁጥር 384/1996" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

   1. "ማዕከል" ማለት በፍርድ ቤት አደገኛ ቦዘኔ መሆኑ የተረጋገጠበት ማንኛውም ሰው ተሃድሶ የሚያገኝበት በፌዴራል ወይም በክልል የሚቋቋም ማዕከል ነው።
   2. "ፖሊስ" ማለት የፌዴራል፣ የክልል ወይም የአዲስ አበባ ከተማ ወይም የድሬዳዋ ከተማ ፖሊስ ነው፡፡
   3. "ኮሚሽን" ማለት የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ማለት ነው፡፡[47]

3. **ዓላማ**

   የዚህ አዋጅ ዓላማ የአደገኛ ቦዘኔነት ለመቆጣጠር፣ ለፍርድ ለማቅረብና ለድርጊታቸው ተመጣጣኝ ቅጣት እንዲያገኙ በማድረግ አምራች ዜጎች የሚሆኑበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው።

---

[47] የፌዴራል ማረሚያ ቤት አስተዳደር ሆኗል።

4. **<u>አደገኛ ቦዘኔነት</u>**

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የበለጠ ቅጣት የሚያስቀጣ ካልሆነ በቀር፣ ሥራ ለመስራት አቅም እያለው የታወቀ መተዳደሪያ የሚሆን ገቢ ሳይኖረው እና

1. በአደባባይ ወይም በሕዝብ መጠቀሚያ ሥፍራ ወይም ለሕዝብ በሚታይ ቦታ ወይም ለሕዝብ ክፍት በሆነ ቦታ በገንዘብ ወይም በሌላ ቁሳዊ ጥቅም ውርርድ ወይም ቁማር ወይም መሰል ሕገወጥ ጨዋታ ሲጫወት የተገኘ፤
2. ሕጋዊ ፈቃድ ባይኖረው የጦር መሣሪያ የያዘ ወይም ያለበቂ ምክንያት ለሰው ወይም ለእንስሳት ማጥቂያ የሚሆን ጩቤ ወይም ስለታም መሣሪያ ወይም ሌላ ተመሣሣይ መሣሪያ በአደባባይ፣ በሕዝብ መሰብሰቢያ ወይም መዝናኛ ቦታ ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ ወይም አካባቢ ወይም በሌላ በማናቸውም ተመሣሣይ ቦታ ይዞ የተገኘ፤
3. የባለቤቱን ወይም የባለይዞታውን ወይም በንብረቱ ላይ የማዘዝ መብት ያለውን ሰው ፈቃድ ሳያገኝ በግል ባለቤትነት ወይም ይዞታ ስር የሚገኝ ንብረት ውስጥ ገብቶ የተገኘ፤
4. ወደ ትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ በሃይል ወይም በማስፈራራት ወይም በማጭበርበር ለመግባት የሞከረ ወይም ገብቶ የተገኘ በመንገዶች ላይም ሆነ ወይም በትምህርት ቤት አካባቢ በመዘዋወር የትምህርት ሂደትን ያወከ፣ ወይም ተማሪዎችን በማስገደድ ወይም በማስፈራራት ማናቸውም ጥቅም ለማግኘት የሞከረ፤
5. መጠጥ በመጠጣት ወይም አእምሮ በሚያደነዝዝ ዕፅ በመጠቀም ሆነ ብሎ የሕዝብን ወይም የአንድን አካባቢ ሰላም ያወከ፤
6. ለአንድ ሕግ አክባሪ ዜጋ ባልተለመደ ጊዜ ወይም አኳኋን የአካባቢውን ነዋሪዎች ሕይወት ወይም ንብረት ደህንነት ስጋት ላይ በሚጥል ሁኔታ ቆሞ ወይም ሲዘዋወር የተገኘና ማንነቱን ሲጠየቅ ለመግለጽ ፈቃደኛ ያልሆነ ወይም ለመደበቅ የሞከረ ወይም ሕግ አስከባሪን ሲያይ የሸሸ፤
7. በማናቸውም ቦታ የጾታ ጥቃት ለማድረስ ወይም የፍትወት ሥጋ ስሜትን ለማርካት በማናቸውም መንገድ ሴትን ለማስገደድ የሞከረ፤

8. በአንድ ንብረት ላይ የማዘዝ መብት ያለው ሰው ሳይፈቅድ አገልግሎት በመስጠት ገንዘብ የጠየቀ ወይም ከተስማማበት ያገልግሎት ክፍያ በላይ የጠየቀ ወይም አገልግሎቱ ባለመፈለጉ ከንብረቱ እንዲርቅ ሲጠየቅ ፈቃደኛ ያልሆነ፤
9. በቡድን በመደራጀት እርስ በርስ በመጋጨት የአካባቢውን ነዋሪዎች ሰላም ያወከ፤
10. በተደጋጋሚ በስርቆት ተግባር የተሳተፈና ለተመሳሳይ የስርቆት ተግባር ራሱን ሲያዘጋጅ የተገኘ ወይም የአካባቢውን ሕዝብ ስጋት ውስጥ የጣለ፤
11. በልማደኛ ተደባዳቢነቱ ወይም በጨካኝነቱ በአካባቢው ነዋሪዎች መታወቁን መከታ በማድረግ ወይም በነዋሪዎቹ ላይ ያሳደረውን ስጋት በመጠቀም በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ገንዘብ ወይም ሌላ ጥቅም የተቀበለ ወይም እንዲሰጠው ያደረገ፣ ወይም
12. የራሱ ያልሆኑ ወይም በአደራ ያልተሰጡትን የቤት፣ የመኪና ወይም ሌላ የማናቸውም ነገሮች ቁልፎች ወይም ተመሳሳይ መሳሪያዎች ይዞ የተገኘ፡

ከአንድ ዓመት ተኩል እስከ ሁለት ዓመት ሊደረስ በሚችል እስራት ይቀጣል። የተፈጸመው ድርጊት አደገኛነቱን ወይም የተደጋገመ እንደሆነ የቅጣቱ ጣሪያ እስከ 3 ዓመት ሊደርስ ይችላል፡፡

5. <u>ስለ ቅጣት አፈፃፀም</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 መሠረት በአደገኛ ቦዘኔነት ወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ሰው የተወሰነበትን ቅጣት የሚፈጽመው በማዕከሉ ይሆናል፡፡
2. እያንዳንዱ ክልል የራሱን ማዕከል እስከ ሚያቋቁም እና እስከሚያደራጅ ድረስ በዚህ አዋጅ መሠረት በክልል ፍርድ ቤት የሚሰጥ ውሣኔ የሚፈጸመው በፌዴራል ተሃድሶ ማዕከል ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ተጠርጣሪን ለፍርድ የማቅረብ ሂደት</u>

6. <u>ስለመያዝ</u>

1. ማንኛውም ፖሊስ አደገኛ ቦዘኔ መሆኑን በሚገባ የሚጠረጥረውን ሰው ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ መያዝ ይችላል፡፡

2. ፖሊስ በጥርጣሬ የያዘውን ሰው ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ 48 ሰዓት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ለፍርድ ቤት ማቅረብ አለበት፡፡ ይህም ተጠርጣሪው ከተያዘበት ቦታ ወደ ፍርድ ቤት ለማምጣት አግባብ ባለው ግምት የሚጠይቀውን ጊዜ አይጨምርም።
3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6/1/ መሰረት በአደገኛ ቦዘኔነት በሚገባ ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው በዋስትና አይለቀቅም።

7. **ስለጊዜ ቀጠሮ**

1. አንድን በአደገኛ ቦዘኔነት የተጠረጠረን ሰው የያዘ መርማሪ ምርመራውን በሃያ ስምንት ቀን ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅና የምርመራ መዝገቡን ለዐቃቤ ሕግ መላክ አለበት፡፡
2. መርማሪው ፖሊስ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት መሠረት አስፈላጊውን ምርመራ ያከናውናል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ምርመራው በተለይ የሚከተሉትን ይጨምራል፣

   ሀ/ የተጠርጣሪውን ዕድሜ፣

   ለ/ ሥራ ለመሥራት አቅም ያለው ስለመሆኑ፤

   ሐ/ የተጠርጣሪውን መተዳደሪያ ወይም የገቢ ምንጭ፤

   መ/ ተጠርጣሪው የትና ከማን ጋር እንደሚኖር፤

   ሠ/ ተጠርጣሪው በአካባቢው ሕዝብ የሚታወቅበትን ባህርይ፤
4. መርማሪው ፖሊስ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 38/ሐ/ መሠረት ተጨማሪ ምርመራ እንዲያደርግ ከታዘዘ ትዕዛዙ በደረሰው በአምስት ቀናት ውስጥ ምርመራውን አጠናቆ ለዐቃቤ ሕግ መመለስ አለበት፡፡

8. **ስለ ዐቃቤ ህግ**

1. በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት አንቀጽ 38/ሐ/ የተሰጠው ሥልጣን ቢኖርም አቃቤ ሕግ የምርመራ መዝገብ ሲደርሰው በአስር ቀናት ውስጥ ክስ መመስረት ይኖርበታል።
2. በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት አንቀጽ 42 (1) (ሀ) መሠረት ክስ ላለማቅረብ የወሰነ እንደሆነ ተጠርጣሪውን ወዲያውኑ እንዲለቀቅ በማድረግ ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ያሳውቃል።

9. **ስለ ፍርድ ቤት**

1. ክስ የቀረበለት ፍርድ ቤት የአደገኛ ቦዘኔነት የወንጀል ጉዳይ በቀረበለት ከአራት ወር በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ውሣኔ ይሰጣል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ ተጠርጣሪው በወንጀሉ ጥፋተኛ መሆኑን አረጋግጦ አጥፊው ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 መሠረት ቅጣት የጣለ እንደሆነ የቅጣት ውሣኔው የሚፈፀምበትን ማዕከል ይወስናል።

## ክፍል ሦስት

## ስለ ኮሚሽኑና ማዕከሉ

### 10.የማዕከሉ አደረጃጀት

የፌደራል ማረሚያ ቤቶች ተቋም አካል የሆነ የአደገኛ ቦዘኔዎች ተሃድሶ ማዕከል ይደራጃል።

### 11.የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር

ኮሚሽኑ፡-

1. ወደ ተሃድሶ ማዕከል የሚላኩ አደገኛ ቦዘኔዎች ሕግ አክባሪና አምራች ዜጎች እንዲሆኑ ለማድረግ በማዕከሉ የሚከናወኑት የተሃድሶ እንቅስቃሴዎችን በሚመለከት የዕቅድ ሃሳብ አዘጋጅቶ ለፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትር ያቀርባል[48]፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል።
2. ስለታራሚዎች የኑሮ ሁኔታና የተሃድሶ እርምጃዎች አፈፃፀም ቁጥጥርና ክትትል ያደርጋል።
3. የታራሚዎችን አጠባበቅ ለማሻሻል የሚረዱ የዕቅድ አቅጣጫዎችን ለተሃድሶ ማዕከሉ አስተዳዳሪ ይሰጣል፣ የሥራውን ውጤት ይገመግማል።

### 12.የማዕከሉ ኃላፊነት

ማዕከሉ፡-

1. በፍርድ ቤት ውሣኔ መሰረት በአደገኛ ቦዘኔነት ወንጀል ጥፋተኝነታቸው ተረጋገጠ ወደ ማዕከሉ የሚገቡ ታራሚዎችን ይጠብቃል።
2. ለታራሚዎች መሠረታዊ የቀለም ትምህርት፣ የሙያ ሥልጠና የስነ ዜጋና፣ የማህበራዊ ምክር አገልግሎት ይሰጣል፡፡ እንዲሁም የተሃድሶ ውጤት ሊያስከትል የሚችል የጉልበት ሥራ ታራሚዎች እንዲሰሩ ያደርጋል።

---

[48] በአዋጅ ቁጥር 22/12(2008) አ.916 መሰረት የፌዴራል እና አርብቶ አደር ጉዳዮች ልማት ሚኒስቴር ተተክቷል።

3. የታራሚዎችን ጤንነት ይጠብቃል፣ ነፃ ሕክምና፣ ምግብና መጠለያ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡
4. ታራሚዎች በራሳቸው የሚመሩና ሃላፊነት የሚሰማቸው እንዲሆኑ ያበረታታል።
5. ታራሚዎች የሚኖሩባቸው ወይም የሚያድሩባቸው ክፍሎች ወይም ግቢዎች በጤናቸው ላይ ጉዳት የማያስከትሉ ንፁሕ አየርና በቂ ብርሃን የሚያገኙ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡
6. ታራሚዎች በተሃድሶ ማዕከሉ ውስጥ በሚቆዩባቸው ጊዜያት በማዕከሉ የሚወጡትን የሥነ ሥርዓት ደንቦች ማክበራቸውን ይቆጣጠራል፣ እነዚህን ደንቦች በሚተላለፉት ላይ በኮሚሽኑ የዲስፐሊን ሥርዓት መሠረት እርምጃዎችን ይወስዳል።

**ክፍል አራት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

13. **ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

1. የፌዴራል ተሃድሶ ማዕከልን በተመለከተ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ኮሚሽኑ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

14. **ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸዉ ህጎች**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ሕጎች በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

15. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከጥር 18 ቀን 1996 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር 18 ቀን 1996 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 652/2001 ዓ.ም

## ስለፀረ ሽብርተኝነት የወጣ አዋጅ

ሕዝቦች በሰላም፣ በነጻነትና በተረጋጋ ሁኔታ ለመኖር ያላቸው መብት ከሽብርተኝነት አደጋ ሁልጊዜ መጠበቅ ያለበት በመሆኑ፤

ሽብርተኝነት ለሀገራችን ሰላም፣ ደኅንነትና ዕድገት ፀር እንደሆነ፣ ለአካባቢያችንና ለዓለም ሰላም እና ደህንነትም ከፍተኛ ስጋት እንደሆነ ግንዛቤ የተወሰደ በመሆኑ፤

በስራ ላይ ያሉት የሀገሪቱ ሕጎች በበቂ ሁኔታ ሽብርተኝነትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ባለመሆናቸው ጠንካራ የሕግ አቅም መፍጠር በማስፈለጉ፤

ሽብርተኝነትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና ለማምከን በቂ መረጃዎችንና ማስረጃዎችን ለማስባሰብና ለማጠናቀር፣ በሽብርተኝነት የተጠረጠሩ ሰዎችን ወይም ድርጅቶችን ለሕግ ለማቅረብ የሚያስችሉ የተጠናከሩ የምርመራና ክስ የማቅረብ አዳዲስ ስልቶችንና ስርዓቶችን በሕግ ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ፤

ሽብርተኝነትን በሚገባ ለመዋጋት የፀረ-ሽብርተኝነት ዓላማ ካላቸው የአካባቢያችን፣ የአሕጉራችንና የሌላዉ የዓለም ክፍሎች መንግስታትና ሕዝቦች ጋር መተባበር እና በተለይ ከተባበሩት መንግስታትና ከአፍሪካ ሕብረት አባል ሀገራት ጋር የተደረጉትን ስምምነቶች ስራ ላይ ማዋል አስፈላጊነቱ የታመነበት በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 55/1/ መሠረት የሚከተለው ታዉጇል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. “ንብረት” ማለት ማናቸውም ግዙፍነት ያለው ወይም የሌለው ወይም ተንቀሳቃሽ ወይም የማይንቀሳቀስ ሀብት ሲሆን፣ የባንክ ሂሳብን የመሰሉ የዚሁ ንብረት ወይም ሀብት ባለሃብትነትን ወይም ጥቅምን የሚያስረዱ ሰነዶችና ደብተሮችን ያካትታል፤
2. “ከሽብርተኝነት ድርጊት የተገኘ ንብረት” ማለት ገንዘብን ጨምሮ በማንም ስም፣ ይዞታ ወይም ቁጥጥር ስር ቢገኝም ከሽብርተኝነት ድርጊት በመነጨ ንብረት አማካኝነት የተገኘ ወይም የተፈራ ማናቸውም ንብረት ነው፤
3. “የሽብርተኛ ንብረት” ማለት ከሽብርተኝነት ድርጊት የተገኘ ንብረት፣ የሽብርተኛ ድርጅት ንብረት ወይም የሽብርተኝነት ድርጊት ለመፈፀም የዋለ፣ እየዋለ ያለ ወይም የሚውል ንብረት ነው፤
4. “ሽብርተኛ ድርጅት” ማለት፡-

   ሀ/ የሽብርተኝነት ድርጊትን የመፈፀም ዓላማ ያለው ወይም የሽብርተኝነት ድርጊት ለመፈፀም ያቀደ፣ የተዘጋጀ፣ የፈፀመ፣ ያስፈጸመ ወይም እንዲፈፀም በማናቸውም ሁኔታ የረዳ ወይም ያነሳሳ ከሁለት ያላነሱ አባላትን የያዘ ቡድን፣ ማህበር ወይም ድርጅት፣ ወይም

   ለ/ በዚህ አዋጅ መሰረት በሽብርተኝነት የተሰየመ ድርጅት፣

   ነው፤
5. “እገታ ወይም ጠለፋ” ማለት ሰውን በመያዝ ወይም በቁጥጥር ስር በማድረግ የያዘውን ሰው ለመልቀቅ መንግስት አንድ ነገር ካላደረገ የያዘውን ሰው እንደሚገድል፣ ከባድ ጉዳት እንደሚያደርስበት ወይም እንደማይለቀው መዛት ነው፤
6. “ማነሳሳት” ማለት ድርጊቱ ባይሞከርም ሌላውን ሰው በመጎትጎት፣ ተስፋ በመስጠት፣ በገንዘብ፣ በስጦታ፣ በማስፈራራት ወይም በማናቸውም ሌላ ዘዴ የሽብርተኝነት ድርጊት እንዲፈጸም ማግባባት ነው፤
7. “የህዝብ አገልግሎት” ማለት ለህዝብ አገልግሎት ለመስጠት የተደራጁ የኢሊክትሮኒክ፣ የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን፣ የትራንስፖርት፣ የፋይናንስ፣ የህዝብ ግልጋሎት መስጫ፣ የመሰረተ ልማት ወይም እነዚህን የመሰሉ ተቋማት ወይም ስርዓቶች ነው፤
8. “ዲጅታል ማስረጃ” ማለት በዲጂታል ቅርፅ የተቀመጠ ወይም የተላለፈ የማስረጃነት ዋጋ ያለዉ ሆኖ በማናቸውም ማስተላለፊያ ላይ በኮምፒዉተር፣ በኮምፒዉተር ዉስጥ ወይም በሌላ ተመሳሳይ መሳሪያ የተቀረፀ ወይም የተቀመጠ በሰው፣

በኮምፒውተር ወይም በተመሳሳይ መሳሪያ መነበብ ወይም መረዳት የሚችል መረጃ ሲሆን በመግለጫ፣ በህትመት ወይም በሌላ መንገድ የሚወጣ የዚህኑ መረጃ ዉጤት ይጨምራል፤

9. "መንግስት" ማለት የፌዴራል መንግስት ወይም የክልል መንግስት ወይም የመንግስት አካል ወይም የዉጭ ሀገር መንግስት የዓለም አቀፍ ድርጅት ነው፤
10. "ፍርድ ቤት" ማለት እንደ አግባብነቱ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው፤
11. "ፖሊስ" ማለት የፌዴራል ፖሊስ ወይም የፌዴራል ፖሊስ ሥልጣን በውክልና የተሰጠው የክልል ፖሊስ ማለት ነው፤
12. "ሰዉ" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
13. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለሽብርተኝነት እና ተያያዥ ወንጀሎች

### 3. የሽብርተኝነት ድርጊቶች

ማንኛውም ሰው ወይም ቡድን የፖለቲካ፣ የሃይማኖታዊ ወይም የአይዲዮሎጂ ዓላማን ለማራመድ በማሰብ በመንግሥት ላይ ተፅዕኖ ለማሳደር፣ ህብረተሰቡን ወይም የህብረተሰቡን ክፍል ለማስፈራራት ወይም የሃገሪቱን መሠረታዊ ፖለቲካዊ፣ ህገመንግሥታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም ማህበራዊ ተቋማትን ለማናጋት ወይም ለማፍረስ፡-

1. ሰውን የገደለ ወይም በአካሉ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፤
2. የህብረተሰቡን ወይም የህብረተሰቡን ክፍል ደህንነት ወይም ጤና ለከፍተኛ አደጋ ያጋለጠ፤
3. እገታ ወይም ጠለፋ የፈፀመ እንደሆነ፤
4. በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፤
5. በተፈጥሮ ሀብት፣ በአካባቢ፣ በታሪካዊ ወይም የባህል ቅርስ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፤
6. ማናቸውንም የህዝብ አገልግሎት ለከፍተኛ አደጋ ያጋለጠ፣ የያዘ፣ በቁጥጥር ስር ያደረገ፣ ያቋረጠ ወይም ያበላሸ እንደሆነ፤ ወይም

7. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (6) ከተመለከቱት ድርጊቶች መካከል ማናቸውንም ለመፈጸም የዛተ እንደሆነ፣
   ከ15 አመት እስከ እድሜ ልክ በሚደርስ ጽኑ እስራት ወይም በሞት ይቀጣል፡፡

4. **<u>የሽብርተኝነት ድርጊት ለመፈፀም ማቀድ፣ መዘጋጀት፣ ማሴር፣ ማነሳሳትና ሙከራ</u>**

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (6) የተመለከተውን ማናቸውንም የሽብርተኝነት ድርጊት ለመፈፀም ያቀደ፣ የተዘጋጀ፣ ያሴረ፣ ያነሳሳ ወይም የሞከረ እንደሆነ በዚሁ አንቀጽ በተቀመጠው መሠረት ይቀጣል፡፡

5. **<u>ለሽብርተኝነት ድጋፍ መስጠት</u>**

1. ማንኛውም ሰው የሽብርተኝነት ድርጊት አፈፃፀምን ወይም የሽብርተኛ ድርጅትን የሚረዳ መሆኑን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባዉ፡-
   ሀ/ ሀሰተኛ ሰነድ ያዘጋጀ፣ ያቀረበ ወይም የሰጠ እንደሆነ፣
   ለ/ የሙያ፣ የልምድ፣ የሞራል ምክር ወይም ድጋፍ የሰጠ እንደሆነ፣
   ሐ/ ማናቸውንም ዓይነት ንብረት በማናቸውም ሁኔታ ያቀረበ፣ ያሰባሰበ ወይም እንዲቀርብ ያደረገ እንደሆነ፣
   መ/ የገንዘብ ወይም የፋይናንስ ወይም ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው አገልግሎቶችን ያቀረበ ወይም የሰጠ እንደሆነ፣[49]
   ሠ/ ማናቸውንም ፈንጂ፣ ዳይናሚት፣ ሊቀጣጠል የሚችል ነገር፣ የጦር መሳሪያ ወይም ሌላ ገዳይነት ያለው መሳሪያ ወይም መርዛማ ነገር ያቀረበ ወይም የሰጠ እንደሆነ፣ ወይም
   ረ/ ማናቸውም አይነት ሥልጠና ወይም ትምህርት ወይም መመሪያ የሰጠ እንደሆነ፣
   ከ10 እስከ 15 አመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል
2. ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ የተመለከተ የሽብርተኝነት ድርጊት የፈፀመ መሆኑን እያወቀ ለማንኛውም ሰው ከለላ የሰጠ ወይም እንዲያመልጥ የረዳ ወይም የደበቀ እንደሆነ ከ10 ዓመት እስከ እድሜ ልክ በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

6. **<u>ሽብርተኝነትን ስለማበረታታት</u>**

[49] ይህ ንዑስ አንቀፅ በአዋጅ ቁጥር 19/25(2005) አ.780 አንቀፅ 57(2) መሰረት ሽበርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን በተመለከተ ተፈፃነት እንደማይኖረው ተደንግጓል፡፡

ማንኛውም ሰው መልእክቱ እንዲታተምላቸው የተደረገው የህብረተሰቡ አባላት በከፊል ወይም በሙሉ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 3 የተመለከተ ማናቸውንም የሽብርተኝነት ድርጊት እንዲፈጽሙ ወይም ለመፈጸም እንዲዘጋጁ ወይም እንዲነሳሱ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያበረታታቸው ወይም በማናቸውም ሌላ ሁኔታ የሚገፋፋቸው እንደሆነ አድርገው ይረዱታል ተብሎ ሊገመት የሚችል መልዕክት ሆነ ብሎ ወይም በግዴለሽነት ያተመ ወይም ያሳተመ እንደሆነ ከ10 እስከ 20 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

7. **<u>በሽብርተኛ ድርጅት ውስጥ ስለመሳተፍ</u>**

1. ማንኛውም ሰው ለሽብርተኛ ድርጅት ወይም የሽብርተኝነት ድርጊቶችን ለመፈፀም ሰው የመለመለ ወይም አባል የሆነ ወይም ስልጠና የወሰደ ወይም በድርጅቱ በማናቸውም መልክ የተሳተፈ እንደሆነ እንደየተሳትፎ ደረጃው ከ5 እስከ 10 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡
2. ማንኛውም ሰው በሽብርተኛ ድርጅት ውስጥ በአመራርነት ወይም በውሳኔ ሰጪነት የሰራ እንደሆነ ከ20 ዓመት እስከ እድሜ ልክ በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

8. **<u>ለሽብርተኝነት ድርጊት መፈፀሚያነት እንዲውል ንብረት መያዝ ወይም መጠቀም</u>**

ማንኛውም ሰው የሽብርተኝነት ድርጊት ለመፈፀም ወይም እንዲፈጸም ለማመቻቸት እንደሚውል እያወቀ ወይም እንዲውል በማሰብ ማናቸውንም ንብረት የያዘ ወይም የተጠቀመ እንደሆነ፣ የንብረቱ መወረስ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከ5 እስከ 20 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

9. **<u>በሽብርተኝነት ድርጊት የተገኘን ንብረት ስለመያዝና መገልገል</u>**

ማንኛውም ሰው ከሽብርተኝነት ድርጊት የተገኘ ንብረት መሆኑን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው አንድን ንብረት በባለቤትነት የያዘ ወይም በይዞታው ስር ያደረገ ወይም የተጠቀመ ወይም የለወጠ ወይም የደበቀ ወይም ያመሳሰለ እንደሆነ፣ የንብረቱ መወረስ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከ5 እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

10. **<u>ምስክር ማባበል ወይም ማስፈራራትና ማስረጃ ማጥፋት</u>**

ማንኛውም ሰው፣

1. በሽብርተኝነት ድርጊት ላይ ምስክር የሆነን ወይም ለመሆን የሚችል ሰውን እንዳይመሰክር የደለለ ወይም ያስፈራራ ወይም በምስክሩ ወይም ከምስክሩ ጋር የቅርብ ግንኙነት ባለው ሰው ላይ የሀይል ድርጊት የፈፀመ እንደሆነ፣ ወይም

2. ማስረጃ ያጠፋ ወይም የደበቀ እንደሆነ፣

ከ5 እስከ 20 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

11. <u>በሀሰት የሽብርተኝነት ድርጊት ስለማስፈራራት</u>

ማንኛውም ሰው ሀሰተኛ መሆኑን እያወቀ ወይም እያመነ የሽብርተኝነት ድርጊት እንደተፈፀመ ወይም እየተፈፀመ እንደሆነ ወይም እንደሚፈፀም በማናቸውም መንገድ ለሌላ ሰው ሆን ብሎ የገለፀ እንደሆነ ከ3 እስከ 10 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

12. <u>የሽብርተኝነት ድርጊቶችን አለማሳወቅ</u>

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ የተመለከተ የሽብርተኝነት ድርጊት ሳይፈፀም ለመከላከል የሚረዳ መረጃ እያለው ወይም የሽብርተኝነት ድርጊትን የፈፀመን ወይም ሊፈፅም የተዘጋጀን ሰው ለመያዝ ወይም ለመክሰስ ወይም ለማስቀጣት የሚያስችል መረጃ ወይም ማስረጃ እያለው ያለበቂ ምክንያት መረጃውን ወይም ማስረጃውን ለፖሊስ ወዲያውኑ ያልገለፀ ወይም ሀሰተኛ መረጃ የሰጠ እንደሆነ ከ3 እስከ 10 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>የመከላከልና የምርመራ እርምጃዎች</u>

13. <u>ለሽብርተኝነት ጥቃት የተጋለጡ ሰዎችን ስለማዳን</u>

1. ፖሊስ በአንድ የተወሰነ ቦታ ላይ የሽብርተኝነት ድርጊት የተፈፀመ ወይም እየተፈፀመ ለመሆኑ ወይም ሊፈፀም እንደሚችል ወይም በዚሁ አካባቢ ያሉ ሰዎች ለሽብርተኝነት ጥቃት የተጋለጡ ወይም ሊጋለጡ እንደሚችሉ በቂ ምክንያት ሲኖረዉ፡-

   ሀ/ በአካባቢው ያሉ ሰዎች ወደ አንድ ሥፍራ እንዲገቡ ወይም እንዳይገቡ ወይም ሥፍራውን እንዲለቁ ወይም በተገለለ ቦታ እንዲቆዩ፤

   ለ/ ለአደጋው ምንጭ የሆነው ወይም ሊሆን የሚችለው ዕቃ እንዲወድም፣ እንዲወሰድ ወይም ከነበረበት ቦታ እንዲነሳ፤

   ሐ/ ሰዎችን ከመመረዝ ለማዳን ተገቢ የሆኑ ትእዛዞን እንዲፈፅሙ፤

   መ/ የተመረዘዉ ቤት ወይም ቦታ በቁጥጥር ስር እንዲዉል፤ ወይም

   ሠ/ አደጋዉን ወይም መመረዙን ለመከላከል ወይም ለመቀነስ የሚያስችል ማንኛውም እርምጃ እንዲወሰድ፤

የፅሁፍ ወይም የቃል ትእዛዝ ለመስጠትና ይህንንም ለማስፈፀም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ የማስገደድ እርምጃ ሊወሰድ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) የተሰጠ ትእዛዝ በፖሊስ በሚነገር ማስታወቂያ ሊነሳ ወይም ሊራዘም ይችላል፡፡
3. ለሽብርተኝነት አደጋ የተጋለጠ ማንኛውም ሰው ፖሊስ የሰጠውን ትእዛዝ የመፈፀምና የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡ እንዲሁም የህንፃ፣ የምድረ ግቢ ወይም ሥፍራ ባለቤት ወይም አስተዳዳሪ የሆነ ሰው በዚህ አንቀጽ መሠረት የተሰጠውን ትእዛዝ የማስፈፀም ኃላፊነት አለበት፡፡
4. መንግስት እንደአስፈላጊነቱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ማናቸውም አምራች ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም ከድንገተኛ አደጋ ሰዉን ለማዳን እቅድ እንዲኖረዉ ሊያደርግ ይችላል፡፡

14. <u>መረጃ ስለማሰባሰብ</u>

1. የሽብርተኝነት ድርጊት ለመከላከልና ለመቆጣጠር የብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት ከፍርድ ቤት ፈቃድ በመዉሰድ፡-

   ሀ/ በሽብርተኝነት ወንጀል የተጠረጠረን ሰው የስልክ፣ የፋክስ፣ የሬድዮ፣ የኢንተርኔት፣ የኤሌክትሮኒክስ የፖስታና የመሳሰሉ ግንኙነቶችን ለመጥለፍ ወይም ለመከታተል፤

   ለ/ ጠለፋውን ለማስፈፀም ወደ ማናቸውም ቤት ውስጥ በሚስጥር ለመግባት፤ ወይም

   ሐ/ ይህንኑ ለመፈፀም የሚያስችሉ ማሰሪያዎችን ለማስቀመጥ ወይም ለማንሳት፤

   ይችላል፡፡
2. በጠለፋ የሚገኝ መረጃ በምስጢር መጠበቅ አለበት፡፡
3. ማናቸውም የመገናኛ አገልግሎት አቅራቢ በብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት ጠለፋዉን ለማካሄድ ሲጠየቅ አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ አለበት፡፡
4. የሽብርተኝነት ድርጊትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት ወይም ፖሊስ ክትትል በማድረግ መረጃዎች ሊያሰባስብ ይችላል፡፡

15. <u>ተከራይን ስለሚመለከቱ መረጃዎች</u>

1. ማንኛዉም ቤት፣ ቦታ፣ ክፍል ወይም ተሽከርካሪ ወይም ተመሳሳይ መገልገያ አከራይ የሆነ ሰው የተከራዩን ማንነት በዝርዝርና በፅሁፍ የመያዝ እና በአቅራቢያዉ ላለ ፖሊስ ጣቢያ በሃያ አራት ሰአት ውስጥ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

2. ማንኛውም ሰው በቤቱ ውስጥ የውጭ ሀገር ዜጋን ሲያኖር በአቅራቢያው ላለ ፖሊስ ጣቢያ ስለሚያኖረዉ ሰው ማንነት ዝርዝር መግለፅና የፓስፖርቱን ኮፒ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

16. **ድንገተኛ ፍተሻ**

ፖሊስ የሽብርኝነት ድርጊት ሊፈፀም እንደሚችል በቂ ጥርጣሬ ሲኖረውና ድርጊቱን ለመከላከል ድንገተኛ ፍተሻ ማድረግ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን በፌዴራል ፖሊስ ዋና ዳይሬክተር ወይም እርሱ በሚወክለው ሀላፊ ፈቃድ በአካባቢው ያለን ተሽከርካሪ እና እግረኞችን በማስቆም በማንኛውም ጊዜ በድንገት ለመፈተሽና አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመያዝ ይችላል፡፡

17. **በድብቅ የሚደረግ ብርበራ**

ፖሊስ፣

1. የሽብር ድርጊት የተፈፀመ እንደሆነ ወይም ሊፈፀም እንደሚችል፣ ወይም
2. በሚበረብረዉ ቤት ውስጥ ነዋሪ ወይም ባለ ይዞታ የሆነው ሰዉ የሽብርተኝነት ድርጊት ለመፈፀም ዝግጅት ስለማድረጉ ወይም ዕቅድ ስለመንደፉ፣ እና
3. የሚደረገው ብርበራ የሽብርተኝነት ድርጊት ወይም በሽብርተኝነት ድርጊት የሚጠረጠር እንቅስቃሴን አስቀድሞ ለመከላከል ወይም እርምጃ ለመውሰድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው፣

   በበቂ ምክንያት ያመነ ከሆነ በድብቅ የሚደረግ የብርበራ ማዘዣ ከፍርድ ቤት እንዲሰጠው በፅሁፍ ወይም አስቸኳይ ሁኔታ ሲኖር በስልክ ፈቃድ ሲጠይቅ ይችላል፡፡

18. **በድብቅ የሚደረግ ብርበራ ለማካሄድ ስለሚሰጥ ትእዛዝ**

1. ፍርድ ቤቱ በአመልካች በሚቀርብለት መረጃ መሰረት፣

   ሀ/ የተፈጸመውን ወይም የተጠረጠረዉን የሽብር ድርጊት ባህሪ ወይም አደገኛነት፣ እና

   ለ/ በማዘዣው መሰረት የሚወሰደው እርምጃ የሽብር ድርጊቱን ለመከላከል ወይም ተጠርጣሪውን በቁጥጥር ስር ለማዋል የሚኖረውን አስተዋፅኦ፣

   ከግምት ውስጥ በማስገባት በድብቅ የሚደረግ ብርበራ ማዘዣ ይሰጣል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚሰጥ ማዘዣ፡-

   ሀ/ ማዘዣው የሚመለከተውን ቤት አድራሻና የሚታወቅ ከሆነ የቤቱን ነዋሪዎች ስም፣

   ለ/ ከፍተኛው ሠላሳ ቀናት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ማዘዣው ተፈፃሚ የሚሆንበትን ጊዜና ማዘዣው የተሰጠበትን ቀን፣ እና

ሐ/ እንደ አስፈላጊነቱ የሚበረበሩትንና የሚያዙትን ማስረጃዎች አይነት ወይም ዝርዝር፣

መያዝ አለበት፡፡

19. **የመያዝ ሥልጣን**

1. በዚህ አዋጅ የተመለከተ የሽብርተኝነት ድርጊት ለመፈፀሙ ወይም እየተፈፀመ ያለ ስለመሆኑ በሚገባ የሚጠረጥረውን ማንኛውንም ሰው ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ፖሊስ ለመያዝ ይችላል፡፡
2. የተያዘው ሰው በ48 ሰዓታት ውስጥ ፍርድ ቤት የመቅረብ መብት አለው፡፡ ይህም ጊዜ ከተያዘበት ቦታ ወደ ፍርድ ቤት ለመድረስ አግባብ ባለው ግምት የሚጠይቀውን ጊዜ አይጨምርም።

20. **በእስር የማቆያ ትእዛዝ**

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19 በተመለከተው መሠረት የተያዘ ሰው የቀረበለት ፍርድ ቤት ለምርመራ ወይም ክሱን በፍርድ ቤት ለመስማት የተያዘው ሰው በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ሲወስን ይችላል፡፡
2. ምርመራው ያልተጠናቀቀ እንደሆነ መርማሪው ፖሊስ ምርመራውን የሚፈጽምበት በቂ ጊዜ እንዲሰጠው ፍርድ ቤቱን መጠየቅ ይችላል፡፡
3. በማረፊያ ቤት ለምርመራ ለማቆየት የሚሰጠው እያንዳንዱ ጊዜ ቢያንስ ለ28 ቀናት ይሆናል፤ ሆኖም በአጠቃላይ የሚሰጠው ጊዜ ከአራት ወራት መብለጥ አይኖርበትም፡፡
4. በዋስትና ጉዳዮች ላይ ዐቃቤ ህግ ይግባኝ ለማቅረብ ይችላል፡፡
5. በዚህ አዋጅ መሰረት በሽብርተኝነት ወንጀል ክስ የቀረበ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ክሱን ሰምቶ ዉሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ተከሳሹ በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ያዛል።

21. **ናሙናዎችን የመስጠት ግዴታ**

ፖሊስ በሽብርተኝነት ወንጀል ጉዳይ የተጠረጠረ ሰው የእጅ ጽሑፉን፣ የጣት አሻራውን፣ ፎቶግራፉን፣ የፀጉሩን፣ የድምፁን፣ የደሙን፣ የምራቁንና ሌሎች በሰውነቱ የሚገኙ ፈሳሽ ነገሮችን ናሙናዎች ለምርመራ እንዲሰጥ ሲያዝ ይችላል፡፡ በተጨማሪም የህክምና ምርምራ እንዲያደርግ ሲያዝ ይችላል፡፡ ተጠርጣሪው ለምርመራው ፈቃደኛ ካልሆነ ፖሊስ አስፈላጊ የሆነ ተመጣጣኝ ሀይል ተጠቅሞ ከተጠርጣሪው ናሙና ሲወስድ ይችላል፡፡

22. **መረጃ የመስጠት ግዴታ**

የሽብርተኝነት ወንጀል ለመከላከል ወይም ምርመራ ለማከናወን ፖሊስ ለምርመራው የሚረዳው መሆኑን በሚገባ የሚያምንበትን መረጃ ወይም ማስረጃ ከማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት፣ ባለሥልጣን፣ ባንክ፣ የግል ድርጅት ወይም ግለሰብ እንዲሰጠው ሊጠይቅ ይችላል፡፡ መረጃ ወይም ማስረጃ የተጠየቀው ወገን መረጃውን ወይም ማስረጃውን የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል አራት

## የማስረጃና የሥነሥርዓት ደንቦች

### 23. ተቀባይነት ስለሚኖራቸው ማስረጃዎች

በወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ህግና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች የሚቀርቡ ማስረጃዎች ተቀባይነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ማስረጃዎች በሽብርተኝነት ጉዳዮች በፍርድ ቤት በማስረጃነት ተቀባይነት ይኖራቸዋል፡-

1. የመረጃውን ምንጭ ወይም መረጃው እንዴት እንደተገኘ ባይገልጽም በሽብርተኝነት ወንጀል የተዘጋጀ የመረጃ ሪፖርት፤
2. የሰሚ ሰሚ ወይም በተዘዋዋሪ የተገኙ ማስረጃዎች፤
3. ዲጂታል ወይም ኤሌክትሮኒክ ማስረጃዎች፤
4. በጠለፋ ወይም በክትትል የተገኙ ማስረጃዎች ወይም በውጭ ሀገር የህግ አስከባሪ አካላት በተደረገ ጠለፋ የተገኙ መረጃዎች፤ እና
5. በሽብርተኝነት ድርጊት ከሚጠረጠር ሰው በፅሑፍ፣ በድምፅ መቅረጫ፣ በቪድዮ ካሴት፣ ወይም በማናቸውም ሌላ ሜካኒካል ወይም ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ የተቀረፀ የእምነት ቃል፡፡

### 24. የሽብርተኝነት ወንጀል በይርጋ የማይታገድ ስለመሆኑ

በዚህ አዋጅ የተመለከተ ማናቸውንም የሽብርተኝነት ወንጀል በፈፀመ ሰው ላይ የሚቀርብ ክስ በይርጋ አይታገድም፡፡

## ክፍል አምስት

## የሽብርተኛ ድርጅቶችንና ከሽብርተኝነት ድርጊት የተገኙ ንብረቶችን

## የመቆጣጠር እርምጃዎች

### 25.ድርጅት በሽብርተኝነት ስለሚሰየምበት ሥርዓት

1. ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በመንግስት አቅራቢነት አንድን ድርጅት በሽብርተኝነት የመሰየም እና የሽብርተኝነቱን ስያሜን የመሻር ሥልጣን ይኖረዋል፡፡
2. ማንኛውም ድርጅት በሽብርተኛ ድርጅትነት የሚሰየመው በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ፡-
   ሀ/ የሽብርተኝነት ወንጀል ከፈጸመ፤
   ለ/ የሽብርተኝነት ወንጀል ለመፈፀም ከተዘጋጀ፤
   ሐ/ ሽብርተኝነትን ከደገፈ ወይም ካበረታታ፤ ወይም
   መ/ በሌላ መንገድ ከሽብርተኝነት ጋር ተያያዥነት ያለው ሆኖ ከተገኘ፤
   ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሰረት በሽብርተኝነት የተሰየመ ድርጅት ህጋዊ ሰውነቱን ያጣል፡፡
4. በዚህ አዋጅ መሰረት የሚቋቋመውን የሽብርተኝነት ተጎጂዎች ፈንድ የሚያስተዳድረው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ህጋዊ ህልውናውን ላጣ ድርጅት ንብረት አጣሪ ይመድባል፤ የማፍረስ ሂደቱን ያስፈፅማል፡፡

### 26.የሽብርተኛ ንብረት ስለማገድና ሰለመያዝ

1. ፖሊስ በሚያካሂደው ምርመራ የባንክ ሂሳብን ጨምሮ ማናቸውም ንብረት በዚህ አዋጅ የተመለከተ የሽብርተኝነት ወንጀል የተፈፀመበት ወይም ሊፈፀምበት እንደሚችል በሚገባ የጠረጠረ እንደሆነ ከፍርድ ቤት በሚያገኘው ፈቃድ መሰረት ንብረቱን በቁጥጥሩ ስር ለማድረግ ይችላል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በሚሰጠው ትዕዛዝ የተጠቀሰው ንብረት ለሌላ ሦስተኛ ወገን እንዳይተላለፍና ማናቸውም ሌላ ሕጋዊ ግንኙነት እንዳይፈጸምበት ጊዜያዊ የእግድ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡
3. የእግዱ ትዕዛዝ ግልባጭ ለሚመለከተው የአስተዳደር መሥሪያ ቤትና ለንብረቱ ባለቤት ወይም ባለይዞታ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡
4. የተያዘው ወይም የእግድ ትዕዛዝ የተጣለበት ንብረት ባለቤት ወይም ባለይዞታ ቅር የተሰኘ እንደሆነ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

5. ፍርድ ቤቱ ንብረቱ የተያዘው ወይም የታገደው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሰረት አለመሆኑን ሲያረጋግጥ ንብረቱ እንዲለቀቅ ወይም ዕግዱ እንዲነሳ ማድረግ ይችላል፡፡

27.**<u>የሽብርተኛ ንብረት ስለመውረስ</u>**

1. በሽብርተኝነት ድርጊት የተገኘ ንብረት ወይም የሽብርተኛ ድርጅት ወይም የሽብርተኛ ንብረት በመንግሥት ይወረሳል፡፡
2. የሽብርተኛ ንብረት እንዲወረስ ለማድረግ በጉዳዩ ላይ የወንጀል ክስ ቀርቦ እንደሆነ በዚሁ የክስ መዝገብ ዐቃቤ ህግ መጠየቅ ይችላል፡፡ የወንጀል ክስ ባልተመሰረተበት ሁኔታ ማመልከቻው ለብቻው መዝገብ ተከፍቶለት ለፍርድ ቤቱ ይቀርባል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የመውረስ ትእዛዝ ከመሰጠቱ በፊት ፍርድ ቤቱ በተጠቀሰው ንብረት ላይ መብት ወይም ጥቅም አለኝ ለሚል ማንኛውም ሰው የመሰማት እድል መስጠት ይኖርበታል።
4. የተወረሰው ንብረት በዚህ አዋጅ መሠረት ወደ ተቋቋመው የሽብርተኝነት ተጎጂዎች ፈንድ ገቢ ይደረጋል፡፡

**<u>ክፍል ስድስት</u>**

**<u>የሽብርተኝነት ጉዳይ የሚከታተሉ ተቋማት</u>**

28.**<u>የሽብርተኛትን ድርጊትን ስለሚከታተል ዐቃቤ ህግና ፖሊስ</u>**

1. በሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሽብርተኝነት የወንጀል ጉዳይን የሚከታተል ዐቃቤ ሕግ ወይም ፖሲስ፡-
   ሀ/ አግባብነት ባለው ሙያ ቢያንስ ከአምስት ዓመት በላይ የሥራ ልምድ ያለው፣ ሥልጠና የወሰደና በሥራው ታታሪ የሆነ ፣ እና
   ለ/ እንደአግባብነቱ ከፍትህ ሚኒስቴር[50] ወይም ከፌዴራል ፖሊስ የበላይ ኃላፊዎች የሙያ ብቃትና የሥነ ምግባር ማረጋገጫ ምስክርነት ያገኘ፣ መሆን አለበት፡፡
2. የፍትህ ሚኒስቴር የሽብርተኝነት ጉዳዮችን የሚከታተል የተለየ የሥራ ክፍል ያደራጃል፡፡

[50] በ22/68(2008) አ.943 መሰረት የፌዴረል ጠቅላይ አቃቤ ህግ ሆኗል። ውስጥ "የፍትህ ሚኒስቴር" እና "የፍትህ ሚኒስትር" ተብሎ የተገለፀው እንደቅደም ተከተላቸው "የፌዴራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ" እና "ጠቅለይ አቃቤ ህጉ" ተብሎ የነበብ።

3. የፌዴራል ፖሊስ የሽብርተኝነት ጉዳዮችን የሚከታተል የተለየ የሥራ ክፍል ያደራጃል፡፡

**29.የሽብርተኝነት ጉዳይ ስለሚከታተሉ የደህንነት ሠራተኞች**

በብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት የሽብርተኝነት ጉዳዮችን የሚከታተሉ የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞችን መርጦ ይመድባል፡፡ የሽብርተኝነት ጉዳይን የሚከታተል የተለየ የሥራ ክፍል ያደራጃል፡፡

**30.ስለብሔራዊ የፀረ ሽብርተኝነት አስተባባሪ ኮሚቴ**

1. የሽብርተኝነት ድርጊትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የፍትሕ ሚኒስቴር፣ የብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት እና የፌዴራል ፖሊስ መሥሪያ ቤት ኃላፊዎችን ያቀፈ ብሔራዊ የፀረ ሽብርተኝነት አስተባባሪ ኮሚቴ ይዋቀራል።
2. የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ኮሚቴውን ይመራል፡፡
3. ኮሚቴው የጋራ የፀረ ሽብርተኝነት እቅድ ያወጣል፣ የጋራ የፀረ ሽብርተኝነት ግብረ ሀይል በማደራጀት ተቋሞቹ ሽብርተኝነትን ለመዋጋት የሚያደርጉትን ጥረት በማቀናጀት በጋራና በተደጋጋፊነት እንዲሠሩ ያደርጋል፡፡

**31. በሽብርተኝነት ወንጀል የዳኝነት ሥልጣን**

1. የፌዴራል ከፍተኛና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች፡-

   ሀ/ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚቀርቡ ጉዳዮችን፣

   ለ/ በዚህ አዋጅ ከተመለከቱ ወንጀሎች ጋር ተያይዘው የሚፈፀሙ ሌሎች ወንጀሎችን፣ ወይም

   ሐ/ በዚህ አዋጅ መሠረት የቀረበን ክስ ፍርድ ቤቱ የክሱን አንቀጽ የሚቀይራቸዉን ጉዳዮች፣

   የመዳኘት ሥልጣን ይኖራቸዋል፡፡
2. የሀገር መከላከያ ሠራዊት የሀገሪቱን ሉዓላዊነት ለማስከበር በሚያደርገው ውጊያ የተማረከ ሰው የጦር ምርከኛ መሆን ወይም ያለመሆኑን የመወሰን ሥልጣን በዚህ አዋጅ ለቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤት ተሰጥቷል፡፡
3. የዳኝነት ሥልጣንን የተመለከቱ የ1996 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ አንቀጽ 13 እና 17(1)(ለ) ድንጋጌዎች የሽብርተኝነት ወንጀሎችንም ያካትታሉ።

**ክፍል ሰባት**

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 32.ለምስክሮች ጥበቃ ስለማድረግ

1. ፍርድ ቤት ማንኛውንም የሽብርተኝነት ጉዳይ በሚያይበት ጊዜ በራሱ ተነሳሽነት ወይም በዐቃቤ ወይም በምስክሩ ጠያቂነት የምስክሩ ህይወት አደጋ ላይ መሆኑን የተረዳ እንደሆነ የምስክሩን ማንነትና አድራሻ በሚስጥር ለመጠበቅ አስፈላጊ እርምጃዎችን ሊወስድ ይችላል፡፡ የሚወስዳቸው እርምጃዎችም በተለይ የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡-

   ሀ/ ክሱ የሚሰማበትን ቦታ መወሰን፤

   ለ/ የምስክሮች ስሞችና አድራሻዎች በፍርድ ቤቱ ትእዛዞች፣ ውሳኔዎችና መዝገቦች ላይ እንዳይገለፁ ማድረግ፤

   ሐ/ የምስክሮች ማንነትና አድራሻ እንዳይገለጽ ትእዛዞችን መስጠት፤ እና

   መ/ በፍርድ ቤቱ እየተካሄዱ ያሉ የክስ መስማት ሂደቶች በከፊልም ሆነ በሙሉ እንዳይታተሙ ወይም በማናቸውም መንገድ እንዳይገለፁ መወሰን፡፡

2. ማንኛውም ሰሙ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) መሠረት የተሰጠን ውሳኔ የተላለፈ እንደሆነ ከአምስት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራትና ከብር 10,000 እስከ 30,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

### 33. የፍርድ ሂደትን ሰለመርዳት

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ የተመለከተ ወንጀል በመፈፀሙ በአድራጎቱ የተፀፀተ እንደሆነና ስለወንጀሉ አፈፃፀም በዝርዝር ለማስረዳት የተባበረ እንደሆነ ወይም ወንጀሉን በመፈፀሙ ከርሱ ጋር የተሳተፉ ሰዎችን ያጋለጠ እንደሆነ በዐቃቤ ህግ ጥያቄ መነሻነት ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን ሊያቀልለት ይችላል፡፡

### 34. ፈንድ ስለማቋቋም

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረተ የሽብርተኝነት ተጎጂዎች ፈንድ ይቋቋማል፡፡

### 35. የመተባበር ግዴታን መጣስ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13፣ 14፣ 15፣ 21 ወይም 22 መሠረት የተጠየቀውን ትብብር ያላደረገ፣ ለመተባበር ፈቃደኛ ያልሆነ ወይም በፖሊስ የወንጀል መከላከል ወይም ምርመራ ሥራ ላይ ሆን ብሎ ማናቸውንም እንቅፋት የፈጠረ ማንኛውም ሰው ከሦስት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

## 36. ተፈጻሚ የማይሆኑ ሕጎች

1. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ የወንጀል ሕግና የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## 37. ደንብ የማውጣት ስልጣን

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 38. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ 22 ቀን 2001 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

# አዋጅ ቁጥር 761/2004

## የቴሌኮም ማጭበርበር ወንጀል አዋጅ

በየጊዜው እየተስፋፋ በመሄድ ላይ ያለው የቴሌኮም ማጭበርበር ተግባር የቴሌኮም ኢንዱስትሪው ለሀገሪቱ ሰላም፣ ልማትና የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ መጫወት የሚገባውን ቁልፍ ሚና እንዳይጫወት ፈተና እየሆነ መምጣቱን በመገንዘብ፤

የቴሌኮም ማጭበርበር ከሚያስከትለው ኢኮኖሚያዊ ኪሳራ ባሻገር የሀገሪቱን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ስጋት መሆኑን በመረዳት፤

በስራ ላይ ያሉት የሀገሪቱ ህጎች በበቂ ሁኔታ በቴሌኮም ኢንዱስትሪው ላይ እየደረሱ ያሉትን ጥቃቶች ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ባለመሆናቸው የተሟላ ሕግ ማውጣት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የቴሌኮም ማጭበርበር ወንጀል አዋጅ ቁጥር 761/2004" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

1. “የቴሌኮም አገልግሎት” ማለት የቴሌኮም ማዞሪያዎች አገልግሎት፣ ሴሉላር ሞባይል አገልግሎት፣ የኢንተርኔት አገልግሎት፣ የሳተላይት ቴሌፎን አገልግሎት፣ የዳታ ኮምኒኬሽን አገልግሎት፣ የቴሌ ሴንተር አገልግሎት ወይም ሪሴል አገልግሎት፣ የተንቀሳቃሽ ወይም የቋሚ የሬድዮ አገልግሎት፣ የቪሳት አገልግሎት፣ የኬብል ዝርጋታና ጥገና ስራ፣ የቴሌኮም ማዞሪያዎች ተከላና ጥገና ስራ፣ በኤሌክትሪክ ወይም በኢሌክትሮ ማግኔቲክ ኃይል አማካኝነት በስልክ ሽቦ፣ በሬድዮ፣ በሳተላይት፣ በኦፕቲካል ፋይበር ወይም በሌላ ኤሌክትሮ ማግኔቲክ ወይም ማናቸውም ሌላ ስልት ድምፅ፣ ምልክት፣ ፅሁፍ ወይም ምስል ማሰራጨት ወይም መቀበል እንዲሁም ሚኒስቴሩ የቴሌኮም አገልግሎት ብሎ የሚወስናቸውን የሚጨምር ሲሆን የብሮድካስቲንግና የኢንተርኮም ግንኙነትን አይጨምርም፤
2. “የቴሌኮም መሳሪያ” ማለት ለቴሌኮም አገልግሎት የዋለ ወይም ሲውል የታቀደ ማንኛውም መሳሪያ ሲሆን የመሳሪያውን ተገጣሚ አካልንና ሶፍትዌርን ይጨምራል፤
3. “የኮል ባክ አገልግሎት” ማለት የሀገር ውስጥ የቴሌኮም ድርጅት ሳያውቀው የሌላ ሀገር የቴሌኮም ድርጅት ጥሪ ቶንን ለዓለም አቀፍ ግንኙነት መጠቀም ወይም ዓለም ዓቀፍ የስልክ ጥሪዎችን የሀገር ውስጥ ማስመሰል ሲሆን በዓለም ዓቀፍ የቴሌኮመዩኒኬሽን ህብረት ኮልባክ ተብለው የሚታወቁ አገልግሎቶችንም ይጨምራል፤
4. “ሚኒስቴር” ማለት የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ነው፤
5. “የቴሌኮም አገልግሎት ድርጅት” ማለት ኢትዮ-ቴሌኮም ወይም የቴሌኮም አገልግሎት እንዲሰጥ ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሌላ ሰው ነው፤
6. “ፖሊስ” ማለት የፌዴራል ፖሊስ ወይም እንደሁኔታው የክልል ፖሊስ ነው፤
7. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 47(1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤
8. “ሰዉ” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
9. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል።

## ክፍል ሁለት

## ስለቴሌኮም ማጭበርበር ወንጀሎች

### 3. ከቴሌኮም መሳሪያዎች ጋር የተያያዙ ወንጀሎች

1. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ውጪ ማንኛውም አይነት የቴሌኮም መሳሪያ የሚያመርት፣ የሚገጣጥም፣ ከውጭ ሃገር የሚያስመጣ ወይም የሚሸጥ ማንኛውም ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከ10 እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር 100,000 እስከ ብር 150,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ማንኛውም አይነት የቴሌኮም መሳሪያ የሚጠቀም ወይም ይዞ የሚገኝ ማንኛውም ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከ1 እስከ 4 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር 10,000 እስከ ብር 40,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡
3. ሚኒስቴሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ያለፈቃድ ሊመረቱ፣ ሊገጣጠሙ፣ ከውጭ ሀገር ሊገቡ፣ ሊሸጡ ወይም ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ የቴሌኮም መሳሪያዎችን ዝርዝር እና ቴክኒካዊ ስታንዳርድ ያወጣል።

4. <u>**የቴሌኮም አገልግሎት ከመስጠት ጋር የተያያዙ ወንጀሎች**</u>

አግባብ ባላቸው ህጎች መሰረት የተሰጠ የፀና ፈቃድ ሳይኖረው የቴሌኮም አገልግሎት በመስጠት ሥራ ላይ የተሠማራ ማንኛውም ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከ7 እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ያለፈቃድ በሚሠራበት ጊዜ ሊያገኝ ይችላል ተብሎ የሚገመተውን ገቢ ሦስት እጥፍ የሚሆን መቀጮ ይቀጣል፡፡

5. [51]

6. <u>**የቴሌኮም አገልግሎትን ለህገ ወጥ ዓላማ ስለማዋል**</u>

ማንኛዉም ሰዉ፡-

1. በፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 ከሚያስቀጣ ወንጀል ጋር የተያያዘ ሽብር የሚያስከትል መልዕክት ለማሰራጨት ወይም በወንጀል ህግ የሚያስቀጣ አስነዋሪ የሆነ መልዕክት ለማሰራጨት ማንኛዉንም የቴሌኮም ኔትዎርክ ወይም መሳሪያ የተጠቀመ ወይም በጥቅም ላይ እንዲዉል ያስደረገ እንደሆነ፤ ወይም
2. የቴሌኮም አገልግሎት ሰጪ ድርጅቱ የሚሰጠዉን አገልግሎት ወይም የቴሌኮም መሰረት ልማትን ለሕገ ወጥ ዓላማ ያዋለ ወይም እንዲዉል ያስደረገ እንደሆነ፤ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከ3 እስከ 8 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር 30,000 እስከ ብር 80,000 በሚደረስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

[51] ይህ አንቀፅ በ22/83(2008) አ.958 ተሽሯል፡፡

7. **<u>የአገልግሎት ዋጋ የማጭበርበር ወንጀል</u>**

ማንኛውም ሰው፡-

1. ላገኘው የቴሌኮም አገልግሎት መክፈል የሚገባውን ትክክለኛ ዋጋ በተጭበረበረ መንገድ ሳይከፍል የቀረ እንደሆነ፣ ወይም
2. ለቴሌኮም አገልግሎት ድርጅቱ መክፈል የሚገባውን የአገልግሎት ዋጋ በተጭበረበረ መንገድ በሌላ ሰው እንዲፈፀምለት በማድረግ የቴሌኮም አገልግሎት ያገኘ እንደሆነ፣ ወይም

   በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከ5 እስከ 10 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ተጭበርብሯል ተብሎ የሚገመተውን የቴሌኮም አገልግሎት ዋጋ ሦስት እጥፍ የሆነ መቀጮ ይቀጣል፡፡

8. **<u>የኮልባክ አገልግሎትን ስለሚመለከቱ ወንጀሎች</u>**

1. ማንኛውም ሰው የኮልባክ አገልግሎት የሰጠ እንደሆነ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከ5 እስከ 10 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና የኮልባክ አገልግሎቱን በሰጠበት ጊዜ ውስጥ ሊያገኝ ይችላል ተብሎ የሚገመተውን ገቢ አምስት እጥፍ የሚሆን መቀጮ ይቀጣል፡፡
2. ማንኛውም ሰው አስቦ ወይም በቸልተኝነት የኮልባክ አገልግሎት ያገኘ እንደሆነ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከ3 ወር እስከ 2 ዓመት በሚደርስ እስራት እና ከብር 2,500 እስከ ብር 20,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

9. **<u>ህገወጥ የቴሌኮም ኦፕሬተርን ስለሚመለከቱ ወንጀሎች</u>**

1. ማንኛውም ሰው፡-

   ሀ/ የቴሌኮም አገልግሎት ሰጪ ድርጅቱ ከዘረጋው የቴሌኮም መሰረተ ልማት ውጪ ማንኛውንም የቴሌኮም መሰረተ ልማት የዘረጋ እንደሆነ፣ ወይም

   ለ/ የቴሌኮም አገልግሎት ሰጪ ድርጅቱ የዘረጋውን የቴሌኮም መሰረተ ልማት ወደ ጎን ትቶ የሀገር ውስጥም ሆነ ዓለም አቀፍ የቴሌኮም አገልግሎት የሰጠ እንደሆነ፣

   በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከ10 እስከ 20 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራትና አገልግሎቱን በሰጠበት ጊዜ ውስጥ ሲያገኝ ይችላል ተብሎ የሚገመተውን ገቢ አስር እጥፍ የሚሆን መቀጮ ይቀጣል፡፡

2. ማንኛውም ሰው አስቦ ወይም በቸልተኝነት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ከተመለከተው ህገ ወጥ የቴሌኮም ኦፐሬተር የቴሌኮም አገልገሎት ያገኘ እንደሆነ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከ3 ወር እስከ 2 ዓመት በሚደርስ እስራት እና ከብር 2,500 አስከ ብር 20,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

10. <u>ሌሎች ወንጀሎች</u>

1. በሕገ ወጥ መንገድ ሲም ካርድ፣ ክሬዲት ካርድ፣ የደንበኞችን መለያ ቁጥር ወይም ዳታ የሚሰራ ወይም የሚያባዛ ወይም በሕገ ወጥ መንገድ የተባዙትን ሲም ካርዶች፣ የደንበኞች መለያ ቁጥሮች ወይም ዳታዎች የሚሸጥ ወይም በማናቸውም መንገድ የሚያሰራጭ ማንኛውም ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከ10 እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ፅኑ አስራት እና ከብር 100,000 አስከ ብር 150,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡
2. ማንኛውም ሰው፡-
   ሀ/ ማንኛውንም አይነት መሳሪያ ከህዝብ ቴሌፎን ጋር በማገናኘት ወይም ማንኛውንም ሌላ መንገድ በመጠቀም በህዝብ ቴሌፎን አማካኝነት በመደበኛ ሁኔታ ሊገኝ የማይችልን አገልግሎት ያገኘ እንደሆነ፤ ወይም
   ለ/ የተሳሳተ ወይም የተጭበረበረ የደንበኝነት ስምምነት በማቅረብ፣ የሌላ ሰው የማንነት መለያ ኮድን በመጠቀም ወይም በሌላ ማንኛውም የተጭበረበረ መንገድ የቴሌኮም አገልግሎት ተጠቃሚ የሆነ ወይም ሌሎች እንዲጠቀሙ ያደረገ እንደሆነ፣

   በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከ3 እስከ 8 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር 30,000 እስከ ብር 80,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡
3. ኢንተርኔትን በመጠቀም የስልክ ጥሪ ወይም የፋክስ አገልግሎት የሚሰጥ ማንኛውም ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከ3 እስከ 8 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራትና ሊያገኝ ይችላል ተብሎ የሚገመተውን ገቢ አምስት እጥፍ የሚሆን መቀጮ ይቀጣል፡፡
4. ማንኛውም ሰው አስቦ ወይም በቸልተኝነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከተውን አገልግሎት ያገኘ እንደሆነ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከ3 ወር እስከ 2 ዓመት እስራት እና ከብር 2,500 እስከ ብር 20,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

11. <u>በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው አካል የሚፈፀም ወንጀል</u>

በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ የሚፈፀም ማንኛውም ወንጀል በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው አካል የተፈፀመ እንደሆነ ለወንጀሉ የተደነገገው መቀጮ በአስር ተባዝቶ ተፈፃሚ ይሆናል።

12. <u>ንብረትን ስለመዉረስ</u>

ፍርድ ቤት በዚህ አዋጅ መሰረት በጥፋተኛ ላይ ቅጣት ሲወስን ወንጀሉን ለመፈጸም በጥቅም ላይ የዋለ ማንኛውም የቴሌኮም መሣሪያ በመንግሥት እንዲወረስ በተጨማሪነት ያዛል።

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

13. <u>ቴክኒካል ግብረ ስለማቋቋም</u>

የቴሌኮም ማጭበርበር ወንጀልን ለመከላከል፣ ለመመርመርና ለመቆጣጠር ከሚመለከታቸው አካላት የተውጣጣ ብሔራዊ ቴክኒካል ግብረ ሃይል ይቋቋማል፡፡

14. <u>በድብቅ የሚደረግ ብርብራ</u>

ፖሊስ የቴሌኮም ማጭበርበር ወንጀል የተፈፀመ እንደሆነ ወይም ሊፈፀም እንደሚችል በበቂ ምክንያት ያመነ ከሆነ በድብቅ የሚደረግ የብርበራ ማዘዣ ከፍርድ ቤት እንዲሰጠው በፅሁፍ ፈቃድ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

15. <u>ተቀባይነት ስለሚኖራቸዉ ማስረጃዎች</u>

በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ስርዓት ህግና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች መሠረት የሚቀርቡ ሌሎች ማስረጃዎች ተቀባይነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ማስረጃዎች በቴሌኮም ማጭበርበር ጉዳዮች በፍርድ ቤት በማስረጃነት ተቀባይነት ይኖራቸዋል፡-

1. ዲጂታል ወይም የኤሌክትሮኒክስ ማስረጃዎች፣
2. በጠለፋ ወይም በክትትል የተገኙ ማስረጃዎች፣ እና
3. ውጭ ሀገር የህግ አስከባሪ አካላት በተደረገ ጠለፋ የተገኙ ማስረጃዎች።

16. <u>የዳኝነት ሥልጣን</u>

በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን የቴሌኮም ማጭበርበር ወንጀሎች በመጀመሪያ ደረጃ የመዳኘት ሥልጣን የሚኖረው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይሆናል፡፡

17. <u>የተሸሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>

1. የቴሌኮሙኒኬሽን አዋጅ ቁጥር 49/1989 (በአዋጅ ቁጥር 281/1994 እንደተሻሻለ) አንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ (1)፣ (2) እና (3) በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡፡
2. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማናቸውም ህግ ወይም የአሰራር ልማድ በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

18. <u>ደንብ የማውጣት ስልጣን</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚረዳ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

19. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ 29 ቀን 2004 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**አዋጅ ቁጥር 780/2005 ዓ.ም**

**በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ**

በወንጀል ድርጊት ተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት የደህንነት ስጋት ብቻም ሳይሆን የፋይናንስ ሥርዓቱ የተረጋጋ፣ ግልጽነት ያለው፣ ጤናማና ቀልጣፋ እንዳይሆን የሚያደርግ በመሆኑ፤

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብንና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመዋጋት በዓለም አቀፍ ደረጃ ጥረት እየተደረገ በመሆኑ እና ኢትዮጵያም የዚህ ዓለም አቀፍ ጥረት አካል በመሆኗ፤

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተሟላ የሕግ ማዕቀፍ እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 780/2005" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ዉስጥ፡-

1. “በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 29 የተመለከተው ወንጀል ነው፤
2. “ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 31 የተመለከተው ወንጀል ነዉ፤
3. “የወንጀል ፍሬ” ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከአመንጪ ወንጀል የተገኘ ማንኛውም ገንዘብ ወይም ንብረት ነው፤
4. “አመንጪ ወንጀል” ማለት ማንኛውም ለወንጀል ፍሬ ምንጭ የሆነና ቢያንስ አንድ ዓመት ቀላል እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል ነው፤
5. “ገንዘብ ወይም ንብረት” ማለት ማንኛውም ተንቀሳቃሽ ወይም የማይንቀሳቀስ ወይም ግዙፍነት ያለው ወይም የሌለው ሀብት ሲሆን በሀብቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም መኖሩን የሚያረጋግጥ እንደ ባንክ ክሬዲት፣ ትራቭለር ቼክ፣ የባንክ ቼክ፣ የክፍያ ትዕዛዝ፣ አክስዮን ወይም ቦንድ የመሰለ ማንኛውንም ዓይነት ሰነድ እና ከሀብቱ የተገኘን ወለድ፣ የትርፍ ድርሻ ወይም ሌላ ገቢን ወይም ኢኮኖሚያዊ ጥቅምን ይጨምራል፤
6. “የሽብርተኝነት ድርጊት” ማለት
   ሀ/ በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በሌላ ቦታ የተፈጸመ እ.አ.አ በ1999 ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከል በወጣው ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን አባሪ ከሆኑት ስምምነቶች በአንዱ የተፈጻሚነት ወሰንና ትርጓሜዎች የሚሸፈን የወንጀል ድርጊት፤
   ለ/ በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በሌላ ቦታ የተፈጸመ ከድርጊቱ ባህሪ ወይም ይዘት ሲታይ ህብረተሰቡን ለማስፈራራት ወይም መንግሥት ወይም ዓለም አቀፍ ድርጅት አንድን ድርጊት እንዲፈጽም ወይም እንዳይፈጽም የማስገደድ ዓላማ ኖሮት ሲቪል በሆነ የህብረተሰቡ አባል ላይ ወይም በውጊያ ሁኔታ ውስጥ ተሳታፊ ባልሆነ ማንኛውም ሌላ ሰው ላይ ሞትን ወይም ከባድ የአካል ጉዳት ለማድረስ ታስቦ የተፈጸመ ማንኛውም ሌላ ድርጊት፤
   ሐ/ በአዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀፅ 3 እና አንቀፅ 4 ላይ የተደነገገው የሽብርተኝነት ድርጊት ትርጉምን ይጨምራል፤
7. “ሽብርተኛ” ማለት

ሀ/ በማንኛውም መንገድ፣ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ፣ ሕግን በመጣስና በራሱ ፈቃድ የሽብርተኝነት ድርጊት የሚፈጽም ወይም ለመፈጸም የሚሞክር፤

ለ/ በሽብርተኝነት ድርጊት በአባሪነት የሚሳተፍ፤

ሐ/ ሌሎች ሰዎች በሽብርተኝነት ድርጊት እንዲሳተፉ የሚያደራጅ ወይም አመራር የሚሰጥ፤ ወይም

መ/ የሚያደርገው አስተዋፆ ሽብርተኝነትን እንዲያስፋፋ በመፈለግ ወይም ቡድኑ የሽብርተኝነት ድርጊት ለመፈጸም ማሰቡን እያወቀ ለጋራ ዓላማ በቡድን የተሰባሰቡ ሰዎች ለሚፈጽሙት የሽብርተኝነት ድርጊት አስተዋፆ የሚያደርግ፤

በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በሌላ ቦታ የሚገኝ ማንኛውም ግለሰብ ነው፤

8. "የሽብርተኛ ድርጅት" ማለት፡-

ሀ/ በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በሌላ ቦታ የሚገኝ ወይም የሚንቀሳቀስ ሆኖ፡-

1) በማንኛውም መንገድ፣ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ፣ ሕግን በመጣስና በራሱ ፈቃድ የሽብርተኝነት ድርጊት የሚፈጽም ወይም ለመፈጸም የሚሞክር፤
2) በሽብርተኝነት ድርጊት በአባሪነት የሚሳተፍ፤
3) ሌሎች ሰዎች በሽብርተኝነት ድርጊት እንዲሳተፉ የሚያደራጅ ወይም አመራር የሚሰጥ፤ ወይም
4) የሚያደርገው አስተዋፆ ሽብርተኝነትን እንዲያስፋፋ በመፈለግ ወይም ቡድኑ የሽብርተኝነት ድርጊት ለመፈጸም ማሰቡን እያወቀ ለጋራ ዓላማ በቡድን የተሰባሰቡ ሰዎች ለሚፈጽሙት የሽብርተኝነት ድርጊት አስተዋፆ የሚያደርግ፤

ማንኛውም ቡድን፤ ወይም

ለ/ በፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 ድንጋጌዎች መሠረት በሽብርተኝነት የተሰየመ ድርጅት ነው፤

9. "የፋይናንስ ተቋም" ማለት ባንክ፣ መድን ሰጪ ኩባንያ፣ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም፣ የፖስታ ቁጠባ ድርጅት፣ የሐዋላ ድርጅት ወይም ብሔራዊ ባንክ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የፋይናንስ ተቋም ብሎ የሚሰይመው ማናቸውም ሌላ ተቋም ነው፤

10. "ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች" ማለት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

ሀ/ የሪል ስቴት ወኪሎችንና ደላሎችን፤

ለ/ የከበሩ ድንጋዮች ወይም የከበሩ ብረቶች ነጋዴዎችን፤

ሐ/ የሚከተሉትን ለደንበኞቻቸው የሚያዘጋጁ፣ የሚፈጽሙ ወይም የሚያከናውኑ ጠበቆች፣ ኖታሪዎችን እና ራሳቸውን ችለው የሚሠሩ ሌሎች የሕግ ባለሙያዎችን፡-

1) ሪል ስቴት መግዛትና መሸጥ፤
2) የደንበኛውን ገንዘብ፣ የገንዘብ ሰነዶችና ሀብት ማስተዳደር፤
3) የባንክ፣ የቁጠባ ወይም የገንዘብ ሰነድ ሂሳቦችን ማስተዳደር፤
4) ኩባንያ ለማቋቋምና ለማካሄድ ወይም ለመምራት የሚደረጉ መዋጮዎችን ማደራጀት፤ ወይም
5) በሕግ የሰዉነት መብት የሚኖራቸዉን አካላት መመሥረት፣ ማካሄድ ወይም መምራትና የንግድ ተቋማትን መግዛትና መሸጥ፤

መ/ ራሳቸዉን ችለዉ የሚሠሩ የሂሳብ ባለሞያዎችን፤

ሠ/ በማዕከሉ የሚሰየሙ ሌሎች የንግድና የሙያ ሥራዎችን፤

11.“ለፖለቲካ ተጽኖ የተጋለጠ ሰው” ማለት በማናቸውም አገር ወይም ዓለም አቀፍ ድርጅት ውስጥ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ሃላፊነት የተሰጠው ወይም ተሰጥቶት የነበረ ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ሲሆን የዚህን ሰው ቤተሰብ አባል ወይም ከዚሁ ሰው ጋር የቅርብ ግንኙነት ያለውን ማንኛውንም ሰው ይጨምራል፤

12.“በቁጥጥር ሥር የሚደረግ ማስተላለፍ” ማለት የወንጀል ድርጊትን ለመመርመርና የድርጊቱ ተሳታፊዎችን ለመለየት ዓላማ፣ የወንጀል ፍሬን ወይም ሕገ ወጥ የሆነን ወይም የሚጠረጠር ሌላ ጭነትን ወይም ጥሬ ገንዘብን አግባብ ባላቸው ባለሥልጣናት እውቅናና ቁጥጥር ሥር ሆኖ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲዘዋወር፣ ከኢትዮጵያ እንዲወጣ፣ የኢትዮጵያን ግዛት አቋርጦ እንዲያልፍ ወይም ወደ እንዲገባ የመፍቀድ ስልት ነው፤

13.“ማገድ” ማለት የዚህ አዋጅ አንቀጽ 37 እንደተጠበቀ ሆኖ ገንዘብን ወይም ሌላ ንብረትን በፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረትና ውሳኔው ጸንቶ ለሚቆይበት ጊዜ እንዳይተላለፍ፣ ወደ ሌላ እንዳይለወጥ፣ እንዳይወገድ ወይም እንዳይንቀሳቀስ መከልከል ነው፤

14.“መያዝ” ማለት ገንዘብን ወይም ሌላ ንብረትን በፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረትና ውሳኔው ጸንቶ ለሚቆይበት ጊዜ እንዳይተላለፍ፣ ወደ ሌላ እንዳይለወጥ፣

እንዳይወገድ ወይም እንዳይንቀሳቀስ መከልከል እና በፍርድ ቤቱ በተሾመና ቁጥጥር በሚደረግበት ንብረት ጠባቂ ሥር እንዲተዳደር ማድረግ ነው፤

15. “መውረስ” ማለት በፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረት የገንዘብ ወይም የንብረት ባለቤትነትን በቋሚነት ማሳጣት ነው፤

16. “የወንጀል መፈጸሚያ” ማለት በማንኛዉም መንገድና በሙሉ ወይም በከፊል በዚህ አዋጅ የተደነገገ ወንጀል ወይም አመንጪ ወንጀል ለመፈጸሚያ የዋለ ወይም እንዲውል የታቀደ ማንኛውም ንብረት ነው፤

17. “የወንጀለኞች ቡድን” ማለት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የገንዘብ ወይም የሌላ ቁሳዊ ጥቅም በማግኘት ዓላማ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ከባድ ወንጀሎችን ለመፈጸም የተሰባሰቡና ተቀናጅተው የሚንቀሳቀሱ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎችን የያዘና ለተወሰነ ጊዜ የሚቆይ የተደራጀ ቡድን ነው፡፤

18. “ተጠቃሚ የሚሆነው ባለቤት” ማለት ደንበኛን ወይም አንድን ሂሳብ በፍጹም ባለቤትነት የሚይዝ ወይም የሚቆጣጠር ግለሰብ፣ ግብይት በስሙ የሚካሄድለት ሰው ወይም አንድን በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠውን አካል ወይም ከሕግ የመነጨ አደረጃጀትን ለመቆጣጠር ፍጹም ሥልጣን ያለው ሰው ነው፤

19. “ኤሌክትሮኒክ ማስተላለፍ” ማለት ላኪ በሆነው ሰዉ በፋይናንስ ተቋም አማካይነት በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚፈጸም በሌላ የፋይናንስ ተቋም ዘንድ ቀርቦ ክፍያውን ለሚቀበል ሰው ገንዘብ ማስተላለፍ ነው፤

20. “መዝገብ ወይም ሰነድ” ማለት ማንኛውም ዓይነት መረጃ ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

ሀ/ ጽሑፍ የሰፈረበትን ማንኛውም ነገር፤

ለ/ ሊተረጉመው ለሚችል ሰው መልዕክት የሚያስተላልፍ በማንኛውም ነገር ላይ ያለን ጭረት፣ ቁጥር ፣ ምልክት ወይም ብስ፤

ሐ/ በሌላ ነገር እገዛ ወይም ያለ እገዛ ድምፅ፣ ምስል ወይም ጽሑፍ ሊያወጣ ወይም ሊያሳይ የሚችልን ማናቸውም ነገር፤

መ/ ካርታን፣ ፕላንን፣ ስዕልን፣ ፎቶን ወይም ሌላ ተመሳሳይ ነገርን፤

ሠ/ የኤሌክትሮኒክ ሰነዶችን፤

ረ/ በሰዉ፣ በኮምፒውተር ወይም በሌላ መሣሪያ መነበብና መረዳት የሚቻል መረጃ የተመዘገበበትን ወይም ምልክት የተደረገበትን ማናቸዉም ማቴሪያል፤

ሰ/ ማንኛውም መረጃ በኮምፒውተር ውስጥ፣ በዲስክ ወይም በካሴት ወይም በማይክሮ ፊልም የተያዘ ወይም በማናቸውም መካኒካል ወይም ኤሌክትሮኒክ መሣሪያ የተያዘ ማናቸውም መረጃ፤

21.“ማዕከል” ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 171/2002 የተቋቋመዉ የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል ነው፤

22.“አግባብ ያለው ባለሥልጣን” ማለት ማዕከሉ፣ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት፣ ፖሊስ፣ ዐቃቤ ሕግ ወይም የምርመራ ሥራን በሃላፊነት የሚያከናውን አካል፣ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ወይም የሚመለከተው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ነው፤

23.“ጥርጣሬ ያለበት ግብይት” ማለት በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 17(1) የተመለከተው ግብይት ነው፤

24.“ከሕግ የመነጨ አደረጃጀት” ማለት በግልጽ የተሰጠ የባለአደራነት ወይም ሌላ ተመሳሳይ አደረጃጀት ነው፤

25.“ገንዘብ” ማለት የኢትዮጵያ ወይም የማንኛውም አገር የወረቀት ወይም የሳንቲም መገበያያ ነው፤

26.“ለአምጪው የሚከፈል ተላላፊ የገንዘብ ሰነድ” ማለት እንደ ቼክ፣ የመንገደኞች ቼክ፣ የተስፋ ሰነድ እና የገንዘብ ክፍያ ትዕዛዝ የመሰለ ለአምጪው የሚከፈል ወይም ያለገደብ በጀርባው ላይ ተፈርሞ የሚተላለፍ፣ ማንነቱ ለማይታወቅ ሰው እንዲከፈል የታዘዘ ወይም ሰነዱን በመስጠት ብቻ ሊተላለፍ በሚያስችል ማናቸውም ፎርም የታዘዘ የገንዘብ ሰነድ ሲሆን የክፍያ ትዕዛዙ ተፈርሞበት ሳለ የሚከፈለው ሰው ስም ግን ባለመጻፉ ጉድለት ያለበትን የገንዘብ ሰነድ ይጨምራል፤

27.“ድንበር ተሻጋሪ የባንክ አገልግሎት እና ተመሳሳይ ግንኙነት” ማለት በአንድ አገር ውስጥ ባለ ባንክ ሌላ አገር ውስጥ ላለ ባንክ አገልግሎት መስጠት ወይም በገንዘብ ተቋማት መካከል ለገንዘብ ሰነዶች ግብይት ወይም ለገንዘብ ዝውውር የሚደረግ ተመሳሳይ ግንኙነት ነው፤

28.“ደንበኛ” ማለት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

ሀ/ የፋይናንስ ግብይት ወይም ሂሳብ የተዘጋጀለት፣ የተከፈተለት ወይም የተፈጸመለትን ሰው፤

ለ/ የፋይናንስ ግብይት ወይም የሂሳብ ፈራሚ የሆነን ሰው፤

ሐ/ ሂሳብ የተከፈተለትን ወይም በፋይናንስ ግብይት መብት ወይም ግዴታ የተሰጠውን ወይም የተላለፈለትን ሰው፤

መ/ የፋይናንስ ግብይት እንዲፈጽም ወይም ሂሳብን እንዲቆጣጠር ሥልጣን የተሰጠውን ሰው፤

ሠ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (መ) ከተገለጹት ድርጊቶች መካከል አንዱን ለመፈጸም የሚሞክርን ሰው፤

ረ/ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ማንኛውንም ሰው፤

29.“ተጠቃሚ” ማለት ጥቅምን ወይም ትርፍን የሚያገኝ ወይም ገንዘብ ወይም ሌላ ንብረትን እንዲቀበል የተሰየመ ሰው ነው፤

30.“ተቆጣጣሪ ባለስልጣን” ማለት የፋይናንስ ተቋማትን በሚመለከት ብሔራዊ ባንክ ሲሆን፣ እያንዳንዱን ፋይናንስ ነክ ያልሆነ የተሰየመ የንግድ ወይም የሙያ ሥራ በሚመለከት ይህንኑ የንግድ ወይም የሙያ ሥራ እንዲቆጣጠር ከሕግ ሥልጣን የተሰጠው የመንግሥት አካል ነው፤

31.“ሰዉ” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

32.ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል።

## ክፍል ሁለት

## በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስ መስሎ ማቅረብንና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት ስለመከላከል

### 3. ጥሬ ገንዘብና ለአምጪው የሚከፈሉ የክፍያ ሰነዶችን ድንበር አቋርጦ ስለማጓጓዝ

1. ማንኛውም ሰው ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ወይም ከኢትዮጵያ ሲወጣ የያዛቸውን ገንዘብ፣ ለአምጪው የሚከፈሉ የክፍያ ሰነዶች፣ የከበሩ ድንጋዮች ወይም የከበሩ ንብረቶችን በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሲጠየቅ ማሳወቅ አለበት፡
2. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ገንዘብን፣ ለአምጪው የሚከፈሉ የክፍያ ሰነዶችን፣ የከበሩ ድንጋዮችን ወይም የከበሩ ብረቶችን አስመልክቶ ሀሰተኛ መግለጫ የተሰጠ እንደሆነ ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት መግለጫ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ወይም ገንዘቡ፣ የክፍያ ሰነዶቹ፣ የከበሩ ድንጋዮቹ ወይም የከበሩ ብረቶቹ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወንጀል፣ የአመንጪ ወንጀል ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት

ወንጀል ውጤት ስለመሆናቸው ወይም ወንጀሉን ለመፈጸሚያ እንደሚውሉ ጥርጣሬ ሲኖር እነዚህኑ በሙሉ ወይም በከፊል የመያዝ ሥልጣን ይኖረዋል።

3. በጉምሩክ አዋጅ የዕቃ ውርስን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የተያዘ ገንዘብን፣ የክፍያ ሰነድን፣ የከበረ ብረትንና የከበረ ድንጋይን በሚመለከት ተፈጻሚ ይሆናሉ።
4. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ከተመለከተው ጥርጣሬ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ለማዕከሉ ማቅረብ አለበት፡፡

## 4. በፋይናንስ ግብይቶች ሊኖር ስለሚገባዉ ግልጽነት

የፋይናንስ ተቋማት፡-

1. በተመዘገበበት ወይም ፈቃድ ባወጣበት የውጭ አገር በአካል ከማይገኝና የተጠናከረ የጋራ አመራርና ቁጥጥር ከሚደረግበት የፋይናንስ ተቋማት ስብስብ ውስጥ ከማይካተት ባንክ፤ ወይም
2. በተመዘገበበት ወይም ፈቃድ ባወጣበት የውጭ አገር በአካል የማይገኝና የተጠናከረ የጋራ አመራርና ቁጥጥር ከሚደረግበት የፋይናንስ ተቋማት ስብስብ ውስጥ የማይካተት ባንክ ሂሳቦቹን እንዲጠቀምባቸው ከሚፈቅድ የፋይናንስ ተቋም፤ ጋር ድንበር ተሻጋሪ የባንክ አገልግሎት ወይም ተመሳሳይ የሥራ ግንኙነት ሊመሠርቱ ወይም የነበራቸውን ግንኙነት ሊቀጥሉ አይገባም፡፡

## 5. በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው አካላትን የሚመለክት ግልጽነት

1. በኢትዮጵያ ዉስጥ የተቋቋሙና በሕግ የሰዉነት መብት የተሰጣቸው አካላት ተጠቃሚ ስለሚሆኑት ባለቤቶቻቸዉና ስለአመራር መዋቅራቸው የተሟሉ፣ ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃዎች መያዝ አለባቸዉ፡፡
2. አግባብ ያለዉ ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱትን መረጃዎች ሲጠይቅ በተፋጠነ መንገድ የማግኘት መብት ይኖረዋል።

## 6. የደንበኞችን ማንነት ስለማጣራት

1. የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብንና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀልን በመከላከልና በመቆጣጠር ዙሪያ ያሉትን ስጋቶች ለመለየት እና ለመመዘን አግባብ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ

አለባቸው። እነዚህን ስጋቶች ለመመዘን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13(1) መሠረት በማዕከሉ የሚሰጡ መረጃዎች ሙሉ በሙሉ ከግምት ውስጥ መግባት አለባቸው።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተካሄደው የስጋት ምዘና እና ከዚሁ ጋር የተያያዘ ማንኛዉም ጠቃሚ ማስረጃና መረጃ በፅሁፍ ተመዝግቦና ወቅታዊነቱ ተጠብቆ መያዝና በተፈለገ ጊዜ ለማዕከሉ፣ ለፖሊስ፣ ለዐቃቤ ሕግና የምርመራ ሥራን በሃላፊነት ለሚመራ አካል ተደራሽ መሆን አለበት፡፡
3. የፋይናንስ ተቋም ወይም ፋይናንስ ነክ ያልሆነ የተሰየመ የንግድና የሙያ ሥራ፡-

ሀ/ ከደንበኛ ጋር የንግድ ግንኙነት ከመመሥረቱ ወይም ሂሳብ ከመክፈቱ በፊት፤

ለ/ በፋይናንስ ተቋሙ ዘንድ የባንክ ሂሳብ ከሌለዉ ወይም ፋይናንስ ነክ ካልሆነዉ የተሰየመ የንግድ ወይም የሙያ ሥራ ጋር የሥራ ግንኙነት ከሌለዉ እና፡-

1) በአንድ ጊዜ ወይም የተያያዙ ሆነው በተለያየ ጊዜ ቢፈጸሙም ሲዳመሩ በማዕከሉ ከተወሰነው የገንዘብ መጠን በላይ የሆኑ ግብይቶችን ለመፈፀም፤ ወይም

2) በአገር ውስጥ ወይም ወደ ውጭ በኤሌክትሮኒክ ገንዘብ ለማስተላለፍ፤ ከሚፈልግ ደንበኛ ጋር ግብይት ከመጀመሩ በፊት፤

ሐ/ ቀደም ሲል የተወሰደ የደንበኛ መረጃ ትክክለኛ ወይም የተሟላ ስለመሆኑ ጥርጣሬ ሲፈጠር፤ ወይም

መ/ በወንጀል የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀልን የሚመለከት ጥርጣሬ ሲኖር፤

የደንበኛን ማንነት ለማወቅ የሚያስችሉ የጥንቃቄ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)(ለ)(1) የተጠቀሰው የገንዘብ መጠን በወቅቱ የማይታወቅ ከሆነ የደንበኛውን ማንነት የማጣራቱ እርምጃ የገንዘቡ መጠን እንደታወቀ ወይም ዝቅተኛው መጠን ላይ እንደደረሰ ወዲያውኑ መከናወን አለበት፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የደንበኞችን ማንነት ለማወቅ የሚወሰዱ የጥንቃቄ እርምጃዎች የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው፡-

ሀ/ የንግድ ግንኙነቱን ዓላማና ባሕሪ መረዳትንና መረጃ ማሰባሰብን፤

ለ/ ገለልተኛ የሆኑ አስተማማኝ ምንጮችን፣ ሰነዶችን፣ ዳታዎችንና መረጃዎችን መሰረት በማድረግ ደንበኛውን መለየትንና ማንነቱን ማረጋገጥን፤

ሐ/ ተጠቃሚ የሚሆኑትን ባለቤቶች ማንነት መለየትን እና ይህንኑ ለማረጋገጥ ተገቢ የሆኑ እርምጃዎችን መዉሰድ፤

መ/ ደንበኛን ወክሎ የሚሰራ ማንኛውም ሰው ከደንበኛው ውክልና የተሰጠው መሆኑን ማረጋገጥን እንዲሁም ማንነቱን መለየትንና ማረጋገጥን፤ እና

ሠ/ በማዕከሉ የሚወስኑ ሌሎች እርምጃዎች መውሰድን፡፡

6. የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች ከደንበኞቻቸው ጋር የሚኖሯቸውን እያንዳንዱን የሥራ ግንኙነት ያለማቋረጥ በጥንቃቄ መከታተልና የሚፈጽሟቸው ግብይቶች ስለደንበኞቻቸው ካላቸው እውቀት፣ ከንግድ ሥራዎቻቸውና ከስጋት ደረጃዎቻቸው እና አስፈላጊ ሲሆን ከገንዘብ ምንጮቻቸው ጋር መጣጣሙን በትኩረት መመርመር አለባቸው።

7. የፋይናንስ ተቋማት እና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች፡-

ሀ/ አዳዲስ አገልግሎቶች፣ የአገልግሎት መስጫ ዘዴዎችንና አሠራሮችን በሥራ ላይ ለማዋል ወይም ለአዲስም ሆነ ነባር አገልግሎቶች አዳዲስ ወይም የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን ከመጠቀም ጋር ተያይዞ የሚመጡ በወንጀል የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ የማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀል ስጋቶችን መለየትና መመዘን፣ እና

ለ/ እነዚህን ስጋቶች ለመቆጣጠርና ለመቀነስ ተገቢ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ፤ አለባቸው።

8. የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች አንድ ደንበኛ ሊሆን የሚችል ወይም ደንበኛ የሆነ ወይም ተጠቃሚ የሚሆነው ባለቤት ለፖለቲካ ተጽኖ የተጋለጠ ሰው መሆን አለመሆኑን ለመለየት የሚያስችል አግባብ ያለው የስጋት መቀነሻ ዘዴ በሥራ ላይ ማዋልና እንደዚህ ዓይነት ደንበኛ ሲያጋጥምም፡-

ሀ/ ከደንበኛው ጋር የሥራ ግንኙነት ከመመሥረቱ በፊት የከፍተኛ አመራር አባላት ፈቃድ እንዲገኝ ማድረግ፤

ለ/ የደንበኛዉን የሀብትና የገንዘብ ምንጭ ለማወቅ ተገቢ የሆነዉን እርምጃ መዉሰድ፤ እና

ሐ/ ከደንበኛዉ ጋር በሚኖራቸው የሥራ ግንኙነት የተጠናከረና የማያቋርጥ ክትትል ማድረግ አለባቸው።

9. የፋይናንስ ተቋማት ድንበር ተሻጋሪ የባንክ አገልግሎትን እና ተመሳሳይ ግንኙነትን በተመለከተ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (3) እስከ (6) ከተደነገጉት እርምጃዎች በተጨማሪ፡-

ሀ/ የእያንዳንዱን ተቋም ሃላፊነት በግልጽ መረዳትና መመዝገብ፤

ለ/ ግንኙነት የፈጠሩበትን የፋይናንስ ተቋም የሚመለከቱ መረጃዎችን መሰብሰብ እና የሥራ ባህሪያቸውን በተሟላ ሁኔታ መረዳት፤

ሐ/ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀል ምርመራ የተካሄደበት መሆን አለመሆኑን ጨምሮ ለሕዝብ ይፋ በተደረጉ መረጃዎች ላይ ተመሥርቶ የፋይናንስ ተቋሙን መልካም ስም እና የሚደረግበትን የቁጥጥር ዓይነት መገምገም፤

መ/ አዲስ ድንበር ተሻጋሪ የባንክ ግንኙነት ወይም ተመሳሳይ ግንኙነት ከመመሥረቱ በፊት የከፍተኛ አመራር አባላት ፈቃድ እንዲገኝ ማድረግ፤

ሠ/ ግንኙነት የፈጠሩበት የፋይናንስ ተቋም በወንጀል የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀልን ለመከላከል በሥራ ላይ ያዋለውን የቁጥጥር ሥርዓት መገምገም፣ እና

ረ/ በባንክ ሂሳብ አማካይነት ክፍያ የሚፈጸም ሲሆን ግንኙነት የፈጠሩበት የፋይናንስ ተቋም የባንክ ሂሳቡ ቀጥተኛ ተጠቃሚ ደንበኞችን ማንነት ለማጣራት በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (3) እስከ (6) እና በንዑስ አንቀጽ (8) መሠረት የተደነገጉ እርምጃዎችን መውሰዱን እና በአስተላላፊ ተቋሙ ሲጠየቅም ሁሉንም የደንበኞች ማንነት መረጃዎች ማቅረብ የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸዉ፡፡

10. ፋይናንስ ተቋማትና ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (3) እስከ (9) የተመለከቱትን ጥንቃቄ የማድረግ ግዴታዎቻቸውን ሊወጡ የማይችሉ ሲሆን የሥራ ግንኙነቱን መመሥረት፣ የባንክ ሂሣብ መክፈት ወይም ግብይት መፈፀም የለባቸውም፤ የንግድ ግንኙነት መስርተውም ከሆነ ማቋረጥ

አለባቸው። አግባብ ሆኖ ሲገኝም በዚህ አዋጅ መሠረት ለማዕከሉ ሪፖርት ማድረግ አለባቸዉ፡፡

11. ይህ አዋጅ ሥራ ላይ በሚውልበት ወቅት ነባር የሆኑ ደንበኞችን በሚመለከት በዚህ አንቀጽ የተመለከቱት የደንበኛ ማንነትን የማጣራት እርምጃዎች አግባብ ባለው ጊዜና ያለውን ተጨባጭ ሁኔታና ስጋት መሠረት በማድረግ የሚፈጸሙ ይሆናል፡፡

12. የፋይናንስ ተቋማት እና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድ እና የሙያ ሥራዎች ባልታወቀ ወይም የፈጠራ መሆኑ በግልጽ በሚታወቅ ስም የባንክ ሂሣብ መክፈት የለባቸውም፡፡

7. ማንነትን የመለየት ልዩ ግዴታ

1. የከበሩ ድንጋዮችና የከበሩ ብረቶች ነጋዴዎች በማዕከሉ ከተወሰነዉ መጠን በላይ የሆኑ ክፍያዎችን በጥሬ ገንዘብ ሲቀበሉ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 መሠረት የደንበኞቻቸውን ማንነት መለየት አለባቸው።
2. የሪል ስቴት ወኪሎችና ደላሎች በሪል ስቴት ግዥና ሽያጭ ሲሳተፉ የተዋዋዮቹን ማንነት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 መሠረት መለየት አለባቸው።

8. የኤሌክትሮኒክ ማስተላለፍን የሚመለከቱ ግዴታዎች

1. ሥራቸው የኤሌክትሮኒክ ማስተላለፍን የሚጨምር የፋይናንስ ተቋማት የላኪውን ሙሉ ስም፣ የባንክ ሂሳብ ቁጥር እና አድራሻ ወይም አድራሻ ከሌለ የዜግነት መታወቂያ ቁጥርን ወይም የትውልድ ዘመንና ቦታን እንዲሁም የተጠቃሚውን ስምና አድራሻ ወይም አድራሻ ከሌለ የዜግነት መታወቂያ ቁጥርን ወይም የትውልድ ዘመንና ቦታን እና ለማስተላለፉ ጥቅም ላይ የዋለውን የተጠቃሚውን የባንክ ሂሣብ ቁጥር መውሰድና ማጣራት አለባቸው። መረጃው በኤሌክትሮኒክ የማስተላለፍ መልዕክቱ ወይም የክፍያ ፎርሙ ውስጥ መካተት አለበት፡፡ የባንክ ሂሳብ ቁጥር በማይኖርበት ጊዜ የኤሌክትሮኒክ ማስተላለፊያው ልዩ ማጣቀሻ ቁጥር እንዲይዝ ይደረጋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሱት የፋይናንስ ተቋማት በኤሌክትሮኒክ ማስተላለፉ ሂደት በአቀባባይነት የሚሳተፉ ሲሆን እነዚህኑ መረጃዎች መያዝና አብረው ማስተላለፍ አለባቸው።
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ድንጋጌዎች፡-

ሀ/ የክሬዲት ካርድ ወይም የዴቢት ካርድ ቁጥሩ አብሮ እስከተገለጸ ድረስ በክሬዲት ካርድ ወይም በዴቢት ካርድ አማካይነት የተፈጸመ ግብይትን ተከትሎ የተደረገ ማስተላለፍን፤ ወይም

ለ/ ላኪውና ተቀባዩ ሁለቱም የፋይናንስ ተቋማት ሆነው በመካከላቸው የሚፈጽሙትን የገንዘብ ማስተላለፍ፤

በሚመለከት ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡

4. የፋይናንስ ተቋም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱ መረጃዎችን አሟልቶ ያልያዘ የኤሌክትሮኒክ ማስተላለፍ ትዕዛዝ ሲያጋጥመው የማስተላለፍ ትዕዛዙን ተግባራዊ ማድረግ የለበትም፡፡
5. ድንበር ተሻጋሪ የኤሌክትሮኒክ ማስተላለፍ የሚሰጥ ወይም የሚቀበል ማንኛውም የፋይንናስ ተቋም ላኪውን ወይም ተቀባዩን በሚመለከት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚፈለጉ መረጃዎች የሚጎድሏቸውን የኤሌክትሮኒክ ማስተላለፎች ለመለየት ተገቢ እርምጃዎችን መውሰድና እንደ ስጋቱ መጠን የኤሌክትሮኒክ ማስተላለፉን ለመፈጸም ወይም ለመቀበል፣ ውድቅ ለማድረግ ወይም ለማገድ እና መወሰድ ያለባቸውን የክትትል እርምጃዎች ለመወሰን የሚያስችል ሥርዓት እንዲኖረው ማድረግ አለበት፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ያልተሟላ የላኪዉን መረጃ የያዘ የድንበር ተሻጋሪ የኤሌክትሮኒክ ማስተላለፍን የስጋት መጠኑ ዝቅተኛ መሆኑን ወስኖ የተቀበለ የፋይናንስ ተቋም የተጠቃሚውን ማንነት ማጣራት አለበት፡፡
7. በአሰራር የሚፈጠሩ የቴክኒክ ጉድለቶች የአገር ውስጥ የኤሌክትሮኒክ ማስተላለፍን አስመልክቶ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱ የላኪው ወይም የተቀባዩ መረጃዎች እንዳይተላለፉ ያደረጉ እንደሆነ ማስተላለፉን ያስፈጸመው ተቋም ከላኪው ወይም የማስተላለፉን ትዕዛዝ ከሰጠው ተቋም ያገኛቸውን መረጃዎች በሙሉ መዝግቦ መያዝ አለበት፡፡

9. <u>**የተጠናከሩ ወይም ቀለል ያሉ የጥንቃቄ እርምጃዎች አወሳሰድ**</u>

1. የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች፡

ሀ/ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀል ሊፈጸም ይችላል የሚል

ከፍተኛ ስጋት መኖሩ ሲታወቅ የተጠናከረ የደንበኞችን ማንነት የመለየት እርምጃዎች መውሰድ ይኖርባቸዋል፣ ወይም

ለ/ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀል ሊፈጸም የመቻሉ ስጋት ዝቅተኛ መሆኑ ሲታወቅ ቀለል ያለ የደንበኞችን ማንነት የመለየት እርምጃዎች መውሰድ ይችላሉ፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች፡-

ሀ/ ውስብስብ የሆኑ ግብይቶች፣ ባልተለመደ ሁኔታ ከፍተኛ መጠን ያላቸው ግብይቶችን፣ ያልተለመዱ ሥርዓቶችን በመከተል የሚፈጸሙ ግብይቶችን እና በግልጽ ሊታይ የሚችል ኢኮኖሚያዊ ወይም ሌላ ሕጋዊ ዓላማ የሌላቸውን ግብይቶች፣ እና

ለ/ በዓለም አቀፍ ደረጃ ክትትል እንዲደረግባቸው ጥሪ በቀረበባቸው አገሮች ውስጥ ከሚገኙ ወይም ከነዚሁ አገሮች ከመጡ ሰዎች ጋር የሚያደርጉትን የንግድ ግንኙነቶችና ግብይቶችን፣

በሚመለከት የተጠናከረ የደንበኞችን ማንነት የመለየትና የክትትል እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)(ሀ) የተመለከቱት ግብይቶች፣ መነሻ ምክንያቶችና ዓላማዎች በተቻለ መጠን ምርመራ ተካሂዶባቸው የተገኙት መረጃዎች በጽሁፍ ተመዝግበው መያዝ አለባቸው።

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)(ለ) መሠረት የሚወሰዱ እርምጃዎች ውጤታማና ከስጋቱ ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለባቸው፣ ማዕከሉም እነዚህኑ በተመለከተ የበኩሉን ተጓዳኝ እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል፡፡

10. **<u>የመዝገብ አያያዝ</u>**

1. የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች፡

ሀ/ በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ 6 እስከ አንቀጽ 9 በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት የደንበኞችን ማንነት ከማጣራት እርምጃዎች የተገኙ የትንታኔ ውጤቶችን ጨምሮ የሂሳብ መዝገቦችን እና የንግድ መጻጻፎችን የንግድ ግንኙነቱ ካበቃበት ቀን አንስቶ ወይም ግብይቱ የተካሄደው ወይም የግብይት

ሙከራ የተደረገዉ የንግድ ግንኙነት ካልመሠረተ ደንበኛ ጋር ከሆነ ግብይቱ ከተካሄደበት ወይም ከተሞከረበት ቀን አንስቶ፤ እና

ለ/ የኤሌክትሮኒክ ማስተላለፍን ጨምሮ የአገር ውስጥም ሆነ ድንበር ተሻጋሪ፣ የተሞከሩም ሆነ የተፈፀሙ ሁሉንም ግብይቶች የሚመለከቱ የተሟሉና የእያንዳንዱን ግብይት መረጃዎች መልሶ ለማየት የሚያስችሉ ዝርዝሮችን የያዙ መዝገቦችን ግብይቱ ከተፈጸመበት ወይም የግብይት ሙከራው ከተደረገበት ቀን አንስቶ፤

ቢያንስ ለአስር አምስት ዓመታት ይዘጡ ማቆየት አለባቸዉ፡፡

2. የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተያዙ መዝገቦች ማዕከሉና ሌሎች አግባብ ያላቸዉ ባለሥልጣናት ሊያዩዋቸው እንዲችሉ ዝግጁ ሆነው መቀመጣቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌዎች መዝገቦችን ለበለጠ ጊዜ ጠብቆ ስለመያዝ በሌሎች ሕጎች የተመለከቱ ድንጋጌዎችን ተፈጻሚነት አያስቀሩም፡፡

11. <u>የውስጥ የመከላከል ፕሮግራሞች</u>

1. የፋይናንስ ተቋማት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6(1) የተጠቀሱትን ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13(1) መሠረት በማዕከሉ ተለይተው የተገለፁትን ስጋቶች ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመቆጣጠርና ለመቀነስ የሚያስችሉ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብንና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን የመከላከል የውስጥ ፖሊሲዎችና ቁጥጥሮች መዘርጋትና በሥራ ላይ ማዋል እንዲሁም የእነዚህን ፖሊሲዎችና ቁጥጥሮች አተገባበር መከታተልና አስፈላጊ ሲሆንም ማጠናከር አለባቸው።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በሥራ ላይ እንዲውሉ የሚደረጉ ፖሊሲዎችና ቁጥጥሮች የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው፡

ሀ/ በዚህ አዋጅ መሠረት የተጠቃሚ ባለቤቶችን ማንነት መለየትና ማረጋገጥን ጨምሮ የደንበኞችን ማንነት የመለየትና የማረጋገጥ እርምጃዎችን፣ ግብይት መከታተልን እና የማያቋርጥ የጥንቃቄ እርምጃ አወሳሰድ ሥርዓትን፤

ለ/ የሕግ መከበርን ተገቢ በሆነ ቡድን ደረጃ የማረጋገጥ አመራር ሥርዓትን፤

ሐ/ ከፍተኛ የብቃት ደረጃን ለማስጠበቅ የሚያስችል የተሟላ የሠራተኞች ምልመላ ሥርዓትን፤

መ/ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ከማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ጋር ግንኙነት ሊኖራቸው የሚችሉ

አጠራጣሪ ግብይቶችንና እንቅስቃሴዎችን ለመለየት የሚያግዙ ሥልጠናዎችን ጨምሮ ተከታታይ የሆኑ ሥልጠናዎችን ለሃላፊዎችና ለሠራተኞች መስጠትን፣

ሠ/ የደንበኞችን ማንነት ለማጣራትና በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ከማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ጋር የተያያዙ ስጋቶችን ለመቆጣጠር የመረጃ ልውውጥ ደህንነትና አጠቃቀምን ጨምሮ መረጃዎችን በፋይናንስ ተቋማት መካከል ለመለዋወጥ የሚያስችል ስርዓትን፤ እና

ረ/ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚወሰዱ እርምጃዎች መከበራቸውንና ውጤታማ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የውስጥ ኦዲት ሥርዓትን፡፡

3. የፋይናንስ ተቋም ይህ አዋጅ በተቋሙ መከበሩን የማረጋገጥ ሃላፊነት ያለው ኦፊሰር በከፍተኛ አመራር ደረጃ መመደብ አለበት፡፡
4. የፋይናንስ ተቋማት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ያወጧቸው ፖሊሲዎችና የቁጥጥር ሥርዓቶች በውጭ ያሉ ቅርንጫፎቻቸውንና በአብላጫ ባለቤትነት የያዟቸውን ተቋምቻቸውን ጨምሮ በቡድን ደረጃ ተግባራዊ መደረጋቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።
5. ማዕከሉ ፋይናንስ ነክ ያልሆነ የተሰየመ የንግድ ወይም የሙያ ሥራ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ከማቅረብና ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ጋር በተያያዘ የሚኖረውን የስጋት ተጋላጭነትና የሥራውን ስፋት በማገናዘብ በዚህ አንቀጽ ለተመለከተው ለእያንዳንዱ ግዴታ ምን ዓይነት እርምጃዎች መወሰድ እንደሚገባቸው መወሰን አለበት፡፡

12. <u>ለትረፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች እና የሃይማኖት ድርጅቶች</u>

ማንኛውም የሃይማኖት ድርጅት ወይም ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት የስራው አካል አድርጎ ገንዘብ የሚሰበስብ፣ የሚቀበል፣ የሚሰጥ ወይም የሚያስተላልፍ ከሆነ ገንዘቡ ሽብርተኝነትን በገንዘብ ለመርዳት አለመዋሉን ወይም በወንጀል የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ከማቅረብ ጋር ያልተያያዘ መሆኑን ለማረጋገጥ ከሚመለከተው ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ጋር በመተባበር አግባብነትያለው አጠቃላይ ቁጥጥር በማዕከሉ ይደረግበታል፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብንና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ስለመከታተል</u>

13.<u>የማዕከሉ ሥልጣንና ተግባር</u>

ማዕከሉ በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆኖ፡-

1. በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ከማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ስጋቶች ጋር የተያያዙ መረጃዎችን በዚህ አዋጅ መሠረት ይሰበሰባል፤ ይቀበላል፣ ያከማቻል፣ ይመረምራል፣ ይተነትናል፣ ያሰራጫል፤
2. በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ከማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ጋር በተያያዘ የሕዝቡን ግንዛቤ እንዲዳብር ያደርጋል፤
3. በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ከማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ጋር የተያያዙ ወንጀሎችን መነሻ፣ የአፈጻጸም ስልት፣ ዓይነት፣ ባህሪ እና አደጋ ያጠናል፤ ለሚመለከታቸው አካላትም የመፍትሔ አቅጣጫ ይጠቁማል፤
4. የፋይናንስ ተቋማትን በመቆጣጠር ረገድ ለብሔራዊ ባንክ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ከማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ጋር የተያያዙ በዚህ አዋጅ የተመለከቱ ግዴታዎቻቸውን ለመወጣት የሚረዷቸው የአሠራር መመሪያዎችን ያወጣል፤
5. በዚህ አዋጅ መሠረት ያገኛቸውን በቀላሉ ለጉዳት የሚጋለጡና ሚስጥራዊ መረጃዎችን ለመጠበቅ የሚያስችል ተገቢ የመረጃ አስተዳደር ሥርዓት ያቋቁማል፤
6. በአዋጁ መሠረት የተቀበላቸውን ሪፖርቶች፣ ለሕግ አስፈጻሚ አካላት የተመሩ ጉዳዮችን፣ ከተመሩት ውስጥ ምርመራ የተካሄደባቸውንና ክስ የተመሠረተባቸው የወንጀል ጉዳዮችን እና ዓለም ዓቀፍ ድጋፍ የተጠየቀባቸው ጉዳዮችን ጨምሮ ሥራውን በተመለከተ የተሟላ ስታትስቲክስ ይይዛል፤
7. የደረሰው ሪፖርት ወይም መረጃ በማዕከሉ ግምገማ በዚህ አዋጅ ከተመለከቱት ወንጀሎች ውጭ ከሆነ ሌላ ወንጀል ጋር በተያያዘ ምርመራ ለማካሄድ ወይም ክስ

ለመመሥረት የሚያስችል መሆኑን በበቂ ምክንያት ከጠረጠረ ጉዳዩን ወዲያውኑ አግባብ ላለው ሕግ አስፈጻሚ አካል ይመራል፤

8. የዚህን አዋጅ ተፈጻሚነት ለማረጋገጥ በራሱ ወይም ከሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣናት ጋር በመተባበር በፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ባልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች ላይ ቁጥጥር፣ ፍተሻና ክትትል ያደርጋል፤
9. በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብንና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ከመከላከል ጋር በተያያዘ ሌሎች ተቋማት የሚያከናዉናቸዉን ሥራዎች ያስተባብራል፣ ያቀናጃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
10. ከስራው ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሌሎች ስራዎች ያከናውናል።

## 14. ከውጭ አገር መሰል ተቋማት ጋር ስለሚኖር ግንኙነት

1. ማዕከሉ ተመሳሳይ ተልዕኮ ካለውና ተመሳሳይ የሚስጥር አጠባበቅ ደረጃ ከሚከተል የሌላ አገር መሰል ተቋም ጋር በእንካ ለእንካ መርህ ላይ ተመሥርቶ የመረጃ ልውውጥ ሊያደርግ ወይም በሌላ መንገድ ሊተባበር ይችላል፡፡
2. ማዕከሉ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አፈጻጸም ዓላማ ከሌላው አገር መሰል ተቋም ጋር ስምምነት ሊፈራረም ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ መሠረት የተገኘ መረጃ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን፣ አመንጪ ወንጀሎችን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ዓላማ ብቻ ይውላል፡፡

## 15. መረጃ ስለማግኘት

1. መረጃ ማዕከሉ ሥራውን ለማከናወን የሚያስፈልገውን ተጨማሪ መረጃ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 መሠረት ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ ካለበት ማንኛውም ሰው የማግኘት ሥልጣን ይኖረዋል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ተፈጻሚ የሚደረገው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2(10)(ሐ) እና አንቀጽ 17(2) የተደነገጉት ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነዉ ነዉ፡፡
3. ማዕከሉ ከደረሰው ሪፖርት ጋር ተያይዞ ለሥራው ያስፈልገኛል ብሎ የሚገምተውን ተጨማሪ መረጃ ከሚከተሉት አካላት ጠይቆ ማግኘት ይችላል፡-

   ሀ/ ከፖሊስ ክፍሎች፤

   ለ/ ይህ አዋጅ የሚፈጸምባቸውን ሰዎች የመቆጣጠር ሃላፊነት ካለባቸው አካላት፤

   ሐ/ ከሌሎች የመንግሥት አካላት፡፡

4. ማዕከሉ የሌላ አገር መሰል ተቋምን ጥያቄ መሠረት አድርጎ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (3) የተመለከቱትን መረጃዎች ማግኘት ይችላል፡፡

16.<u>ለተቆጣጣሪ አካላት ስለማሳወቅ</u>

ማዕከሉ የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን ግዴታዎቻቸውን እየተወጡ እንዳልሆነ ወይም ያልተወጡ መሆናቸውን ሲደርስበት ይህንኑ ለሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ አካላት ያሳውቃል።

17.<u>ጥርጣሬዎችን ሪፖርት ስለማድረግ</u>

1. የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች ገንዘብ ወይም ንብረት የወንጀል ፍሬ ስለመሆኑ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ጋር የተያያዘ ወይም የተገናኘ ወይም ለዚሁ ተግባር ሊውል የሚችል ስለመሆኑ ሲጠረጥሩ ወይም ለመጠርጠር በቂ ምክንያት ሲኖራቸው ወዲያውኑ ጥርጣሬያቸውን ለማዕከሉ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው። ይህም ግዴታ ግብይት ለማድረግ የተፈጸመ ሙከራንም ይመለከታል።
2. ጠበቆች፣ ኖታሪዎችና ራሳቸውን ችለው የሚሠሩ ሌሎች የሕግ ባለሞያዎች ደንበኞቻቸው ከሕግ አንፃር ሊይዙት የሚገባውን አቋም በመወሰን ሂደት ወይም በፍርድ ቤት ጉዳይ ወይም ከፍርድ ቤት ጉዳይ ጋር በተያያዘ ደንበኞቻቸውን ደግፈው ከመከራከር ወይም ከመወከል እንዲሁም ወደ ክርክር እንዲገባ ወይም እንዳይገባ ምክር ከመስጠት ሃላፊነታቸው ጋር ተያይዞ የሚያገኟቸውን የደንበኞቻቸውን መረጃዎች ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አይኖርባቸውም፡፡
3. ማዕከሉ ሪፖርቶች የሚቀርቡበትን ሥርዓትና ፎርም በመመሪያ ይወሰናል፡፡

18.<u>የጥሬ ገንዘብ ግብይትን ሪፖርት ስለማድረግ</u>

የፋይናንስ ተቋማት እና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች በአንድ ጊዜ ወይም የተያያዙ ሆነዉ በተለያየ ጊዜ ቢፈጸሙም ተዳምረው በማዕከሉ ከተወሰነው መጠን በላይ የሆኑ የጥሬ ገንዘብ ግብይቶችን ለማዕከሉ ሪፖርት ማድረግ አለባቸዉ፡፡

19.<u>ግብይትን ስለማዘግየት</u>

1. የፋይናንስ ተቋማት እና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ከማቅረብ ወይም

ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ጋር የተያያዘ ነው ብለው የሚጠረጥሩትን ግብይት ጥርጣሬያቸውን ለማዕከሉ ሪፖርት እስከሚያደርጉ ድረስ ከመፈጸም መቆጠብ አለባቸው።

2. ግብይትን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ከመፈጸም መቆጠብ የማይቻል ሲሆን ወይም ጥርጣሬውን ለማጣራት በሚደረግ ምርመራ ላይ እንቅፋት የሚፈጥር ሲሆን የፋይናንስ ተቋማት እና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች ግብይቱን ፈጽመው ጥርጣሬያቸውን ወዲያውኑ ለማዕከሉ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው።
3. ማዕከሉ ከጉዳዩ ክብደት የተነሳ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አጠራጣሪ የሆነን ግብይት ከሦስት የሥራ ቀናት ላልበለጠ ጊዜ እንዲታገድ ሊያዝ ይችላል፡፡

20.<u>መረጃን አሳልፎ መስጠትን ስለመከልከል</u>

1. የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች፣ ዳይሬክተሮቻቸዉ፣ ሃላፊዎቻቸዉና ሠራተኞቻቸው፡-

   ሀ/ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ጥርጣሬን የሚመለከት መረጃ ለማዕከሉ ሊሰጥ መሆኑን ወይም በመሰጠት ላይ ወይም የተሰጠ መሆኑን፤ ወይም

   ለ/ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ምርመራ ሊካሄድ መሆኑን ወይም በመካሄድ ላይ ወይም የተካሄደ መሆኑን፤

   የሚመለከት መረጃ ለደንበኞች ወይም ለሦስተኛ ወገኖች በምንም ሁኔታ መስጠት የለባቸውም፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌዎች በፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች ዳይሬክተሮች፣ ሃላፊዎች፣ ሠራተኞችና የሕግ አማካሪዎች እና አግባብ ባላቸው ባለሥልጣናት መካከል በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ጥርጣሬን የሚመለከት መረጃ መግለጽን ወይም መለዋወጥን የሚከለክሉ አይሆኑም፡፡

21.<u>በጥርጣሬ ሪፖርት ላይ ስለሚወሰድ እርምጃ</u>

ማዕከሉ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመጠርጠር በቂ ምክንያት ሲኖረው የሚመለከተው ወንጀል መርማሪ አካል በቀጣይ ስለሚወሰደው እርምጃ እንዲወስን አግባብ ያለውን መረጃ ያስተላልፍለታል፡፡

22.<u>የተቆጣጠሪ ባለሥልጣኖች ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኖች የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን ግዴታዎች አክብረው መሥራታቸውን መቆጣጠር አለባቸዉ፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኖች፡-

   ሀ/ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን፣ አመንጪ ወንጀሎችን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን በመመርመርና በመክሰስ ረገድ ከሌሎች አግባብ ካላቸው ባለሥልጣኖች ጋር ይተባበራሉ፣ መረጃ ይለዋወጣሉ፤

   ለ/ በውጭ አገር የሚገኙ የፋይናንስ ተቋማት ቅርንጫፎችና የአብዛኛው አክስዮን ባለድርሻ የሆኑባቸው ተቋማት የአገሩ ሕጎች እስከፈቀዱ ድረስ ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር የሚጣጣሙ እርምጃዎችን መቀየሳቸውንና መተግበራቸውን ያረጋግጣሉ፤

   ሐ/ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ከማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ሊገናኙ የሚችሉ ግብይቶችን ወይም ድርጊቶችን የሚመለከቱ መረጃዎችን በፍጥነት ለማዕከሉ ሪፖርት ያደርጋሉ፤

   መ/ የዚህን አንቀጽ ድንጋጌዎች በማስፈጸም ረገድ የተወሰዱ እርምጃዎችንና የተጣሉ ቅጣቶችን በሚመለከት የስታትስቲክስ መረጃዎችን ይይዛሉ።
3. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኖች የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ባልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች መጣሳቸውን ሲያረጋግጡ ከሚከተሉት መካከል አንዱን ወይም ከዚያ በላይ የሆኑትን እርምጃዎችና ቅጣቶች መወሰን ይችላሉ፡-

   ሀ/ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፤

   ለ/ የተወሰነ መመሪያ እንዲከበር ማዘዝ፤

ሐ/ የፋይናንስ ተቋማቱና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑት የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች እየወሰዱ ቸው ስላሉ እርምጃዎች በየጊዜው ሪፖርት እንዲያደርጉ ማዘዝ፤

መ/ ከብር 10,000 ባላነሰና ከብር 100,000 ባልበለጠ የገንዘብ መቀጮ መቅጣት፤

ሠ/ ግለሰቦችን በንግዱ ወይም በሙያው ዘርፍ ተቀጥረው እንዳይሠሩ መከልከል፤

ረ/ ጊዚያዊ አስተዳዳሪ መመደብን ጨምሮ የሥራ አስኪያጆችን፣ የዳይሬክተሮችን እና በወሳኝነት የመቆጣጠር ሥልጣን የሚኖራቸውን ባለቤቶች ሥልጣን መገደብ፣

ሰ/ ፈቃድ ማገድ ወይም መሠረዝና በሥራዉ ወይም በሙያዉ መሥራት መቀጠልን መከልከል፤ ወይም

ሸ/ አግባብነት ያላቸው ሌሎች እርምጃዎች መዉሰድ፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የተቋም ሥራ አስኪያጅ በከፊል ወይም በሙሉ ሥራውን እንዳያከናውን የተደረገ ክልከላ ወይም ክልከላዉን ለማንሳት የተወሰደ እርምጃ በንግድ መዝገብ እንዲመዘገብ የሚመለከተው ተቆጣጣሪ ባለስልጣን አግባብ ላለው አካል ማስተላለፍ አለበት፡፡

5. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኖች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ሚወስዷቸውን እርምጃዎችና ቅጣቶች ለማዕከሉ ማሳወቅ አሰባቸዉ፡፡

## 23.<u>ሚስጥር ስለመጠበቅ</u>

በማዕከሉ ዘንድ የሚገኝ መረጃ በተገቢዉና በሕጋዊ መንገድ በእጃቸዉ የገባ የማዕከሉ ሃላፊዎች፣ ሠራተኞች፣ በትዉስት ከሌላ ቦታ ተመድበዉ በማዕከሉ የሚሠሩ ሠራተኞች ወይም ሌሎች ሰዎች በዚህ አዋጅ በተደነገገዉ መሠረት ካልሆነ በቀር መረጃውን ለሌሎች ሰዎች መግለጽ አይችሉም።

## 24.<u>ከተጠያቂነት ነፃ ስለመሆን</u>

1. በዚህ አዋጅ መሠረት በቅን ልቦና መረጃ በሚሰጡ ወይም ሪፖርት በሚያደርጉ የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች ላይ ወይም በዳይሬክተሮቻቸዉ፣ በሃላፊዎቻቸው ወይም በሠራተኞቻቸው ላይ የባንክ ሥራ ወይም የሙያ ሚስጥር ወይም የውል ግዴታ ተጥሷል በሚል የወንጀል፣ የፍትሐ ብሔር ወይም አስተዳደራዊ ክስ ሊቀርብባቸዉ አይችልም።

2. በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ 17 እስከ አንቀጽ 19 በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት በቅን ልቦና ሪፖርት እስከተደረገ ድረስ ጥርጣሬ ያስከተለን ግብይት በፈጸሙ የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች ላይ ወይም በዳይሬክተሮቻቸዉ፣ በሃላፊዎቻቸው ወይም በሠራተኞቻቸው ላይ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀል ክስ ሊቀርብባቸው አይችልም።
3. የማዕከሉ ወይም የተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ሃላፊዎች፣ ሠራተኞችና በትውስት ከሌላ ቦታ ተመድበው የሚሠሩ ሠራተኞች ይህን አዋጅ ወይም በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን ለማስፈጸም ሲባል በቅን ልቦና ለሚፈጽሙት ማናቸውም ድርጊት በፍትሐብሔር፣ በወንጀል ወይም በአስተዳደር ተጠያቂ አይሆኑም፡፡

## ክፍል አራት
## ስለምርመራ

### 25.የምርመራ ዘዴ

1. በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን የሚመለከት ማስረጃ ለማግኘት ወይም የወንጀል ፍሬን ተከታትሎ ለመለየት የዳኝነት አካላት ለተወሰነ ጊዜ፦

   ሀ/ በባንክ ሂሳቦችና በሌሎች ተመሳሳይ ሂሳቦች ላይ ክትትል ለማድረግ፤

   ለ/ የኮምፒውተር ሥርዓቶችን፣ መረቦችንና ሰርቨሮችን ለማየት፤

   ሐ/ መገናኛዎችን በክትትል ሥር ለማዋል ወይም ለመጥለፍ፤

   መ/ ድርጊቶችን፣ ባህሪዎችንና ንግግሮችን በድምጽና በምስል ለመቅረጽና ፎቶግራፍ ለማንሳት፤ እና

   ሠ/ የደብዳቤ ልውውጦችን ለመጥለፍና ለመያዝ፤

   የሚያስችል ትዕዛዝ ለወንጀል መርማሪ አካላት መስጠት ይችላሉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱት የምርመራ ዘዴዎች በጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚደረገው የተባሉት ሂሳቦች፣ የኮምፒውተር ሥርዓቶች፣ መረቦችና ሰርቨሮች፣ የስልክ መስመሮች ወይም ሰነዶች በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ በማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ

በመርዳት ድርጊት የሚሳተፉ ሰዎች እየተጠቀሙባቸው ስለመሆኑ ወይም ሊጠቀሙባቸው እንደሚችሉ የሚጠቁም አስተማማኝ ምክንያት ሲኖር ብቻ ነው፡፡

26.<u>በሽፋን ሥር ምርመራና በቁጥጥር ሥር የሚደረግ ማስተላለፍ</u>

1. በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን የመመርመር ሃላፊነት የተሰጠው ሰው እነዚህን ወንጀሎች የሚመለከት ማስረጃ ለማግኘት ወይም የወንጀል ፍሬን ተከታትሎ ለመለየት ሲባል በሽፋን ሥር ከሚደረግ ምርመራና በቁጥጥር ሥር ከሚደረግ ማስተላለፍ ጋር ተያይዞ የሚፈጽመው ድርጊት በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህዊ አስመስሎ በማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ በመርዳት ወንጀልነት ሊፈረጅ የሚችል ቢሆንም ቅጣት አይጣልበትም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን አሠራር ለመከተል በቅድሚያ የፍርድ ቤት ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ መሠረት በሽፋን ሥር የሚደረግ ምርመራ ወይም በቁጥጥር ሥር የሚደረግ ማስተላለፍን እንዲያስፈጽም የተመደበ ሰው ተጠርጣሪው ማንኛውንም ወንጀል እንዲፈጽም መገፋፋት የለበትም፡፡

27.<u>የምስክሮች ጥበቃና እንዳይታወቅ የተደረገ ምስክር ቃል</u>

1. ፍርድ ቤት በራሱ ተነሳሽነት ወይም በምስክሩ ወይም በዐቃቤ ሕግ ጥያቄ ላይ ተመሥርቶ ምስክሩ ወይም የቤተሰቡ አባል በምስክርነቱ ምክንያት ለአደጋ የሚጋለጥ መሆኑን ሲረዳ የምስክሩ ማንነት በሚስጥር እንዲያዝ ሊወስን ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የምስክር ማንነት በሚስጥር ተይዞ የፍርድ ሂደቱ እንዲቀጥል የሚደረገው ሌሎች የምርመራ ዘዴዎችን መጠቀም እውነቱ ላይ ለመድረስ በቂ ሆኖ ሳይገኝ ሲቀር ብቻ ነው፡፡

28.<u>ሚስጥር የመጠበቅ ሙያዊ ግዴታን ወይም ልዩ መብትን በምክንያትነት መጠቀም ስለመከልከሉ</u>

በዚህ አዋጅ መሠረት መረጃ የመስጠት ወይም ተያያዥነት ያለው ሰነድ የማቅረብ ግዴታን ላለመወጣት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17(2) በተደነገገው መሠረት ካልሆነ በስተቀር ሚስጥር የመጠበቅ ሙያዊ ግዴታን ወይም ልዩ መብትን በምክንያትነት መጠቀም አይቻልም።

## ክፍል አምስት

## የወንጀል ጥፋቶችና ቅጣቶች

### 29.በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ

1. ማንኛውም ሰው ንብረቱ የወንጀል ፍሬ መሆኑን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባዉ፡-

   ሀ/ የንብረቱን ሕገ ወጥ ምንጭ ለመደበቅ ወይም ለመሸፈን ወይም አመንጪውን ወንጀል የፈጸመው ሰው ከሕግ ተጠያቂነት እንዲያመልጥ ለማድረግ ንብረቱን የለወጠ ወይም ያስተላለፈ እንደሆነ፣

   ለ/ ንብረቱን፣ የንብረቱን ትክክለኛነት፣ ምንጩን፣ ቦታውን፣ ዝውውሩን ወይም የባለቤትነት መብቱን የደበቀ ወይም እንዳይታወቅ ያደረገ እንደሆነ፣

   ሐ/ ንብረቱን የተረከበ፣ በይዞታው ያደረገ ወይም የተጠቀመ እንደሆነ፣ ወይም

   መ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ሐ) የተጠቀሱትን ወንጀሉን የሚያቋቁሙ ተግባራትን በመፈፀም የተሳተፈ፣ ለመፈጸም ያደመ፣ የሞከረ፣ የረዳ፣ ያመቻቸ ወይም እንዲፈፀም ያማከረ እንደሆነ፣

   በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የንብረቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 35 መሠረት መወረስ እንደተጠበቀ ሆኖ ከ10 ዓመት እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ አስራት እና ከብር 100,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚጣል ቅጣት በሚከተሉት ምክንያቶች በመክበድ ከ15 ዓመት እስከ 25 ዓመት ጽኑ እስራት እና እስከ ብር 150,000 መቀጮ ሊደርስ ይችላል፦

   ሀ/ የተፈፀመው አመንጪ ወንጀል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተመለከተው በላይ የእሥራት ቅጣት የሚያስከትል ከሆነ፣

   ለ/ ወንጀሉ የተፈፀመው በንግድ ወይም በሥራ ተግባርነት ተይዞ ከሆነ፣

   ሐ/ የተደራጀ የወንጀል ቡድን ከዓላማዎቹ አንዱ አድርጎት የፈጸመው ከሆነ፣

   መ/ ሕጋዊ እንዲመስል ተደርጎ የቀረበው በወንጀል ድርጊት የተገኘው ገንዘብ ወይም ንብረት ግምት ከብር 10 ሚሊዮን የሚበልጥ ከሆነ፣

   ሠ/ ወንጀሉ የተፈፀመው ትርፍን ለማግኘት ታስቦ ከሆነ፣ ወይም

   ረ/ ወንጀሉ የተፈፀመው ሌላ ወንጀል እንዲሠራ ለማመቻቸት ከሆነ፡፡

3. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ አፈፃፀም ሲባል፡-

   ሀ/ የተከሳሽ የሀሳብ ክፍል ወይም ወንጀሉን ለመፈጸም የተነሳበት ዓላማ ከተጨባጭ

የሁኔታዎች ክስተት በመነሳት ግምት የሚወሰድበት ይሆናል፤

ለ/ የንብረቱ ምንጭ ሕገወጥ መሆኑን ለማስረዳት በተከሳሽ ላይ በአመንጪው ወንጀል የጥፋተኛነት ፍርድ መሰጠቱ የግድ የሚያስፈልግ አይሆንም፤

ሐ/ የአመንጪው ወንጀል ድርጊት ከኢትዮጵያ ግዛት ውጭ የተፈጸመ ቢሆንም ድርጊቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ቢፈፀም ኖሮ ወንጀል ሆኖ ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ የመነሻው ወንጀል ይህንኑ ድርጊት ጭምር የሚያካትት ይሆናል፤

መ/ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወንጀል ተጠያቂነት አመንጪውን ወንጀል የፈፀመውን ሰውም የሚመለከት ይሆናል፤

ሠ/ በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወንጀል ለመፈጸም መሞከር፣ መደገፍ፣ ማመቻቸት ወይም ማማከር ወንጀሉ እንደተፈጸመ ተቆጥሮ የሚያስቀጣ ይሆናል፡፡

30.<u>በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ተቀፅላ ወንጀሎች</u>

1. ማንኛዉም ሰው ሆን ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት፡-

ሀ/ ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ወይም ከኢትዮጵያ ሲወጣ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ተጠይቆ የያዘውን ጥሬ ገንዘብ ወይም ለአምጪው የሚከፈሉ የገንዘብ ሰነዶች ያልገለጸ እንደሆነ፤

ለ/ የዚህን አዋጅ አንቀጽ 4 ድንጋጌ በመተላለፍ፡-

1) በተመዘገበበት የውጭ አገር በአካል ከማይገኝና የተጠናከረ የጋራ አመራርና ቁጥጥር ከሚደረግበት የፋይናንስ ተቋማት ስብስብ ውስጥ ከማይካተት ባንክ ጋር፤ ወይም

2) ሂሳቦቹን በተመዘገበበት የውጭ አገር በአካል የማይገኙና የተጠናከረ የጋራ አመራርና ቁጥጥር ከሚደረግበት የፋይናንስ ተቋማት ስብስብ ውስጥ የማይካተት ባንክ እንዲጠቀምባቸው ከሚፈቅድ የፋይናንስ ተቋም ጋር፤

የንግድ ግንኙነት ከመሠረተ የነበረውን የንግድ ግንኙነት ካስቀጠለ፤

ሐ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 በተደነገገው መሠረት በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸውን አካላት ተጠቃሚ የሚሆኑ ባለቤቶቻቸውንና የአመራር

መዋቅራቸውን የሚመለከት የተሟሉ፣ ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃዎች ያልያዘ እንደሆነ፤

መ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6፣ አንቀፅ 7 እና አንቀጽ 8 መሠረት የደንበኞችን ማንነት የማጣራትና የስጋት መቀነሻ እርምጃዎችን ያልወሰደ እንደሆነ፤

ሠ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 መሠረት የክትትል እርምጃዎችን ያልወሰደ እንደሆነ፤

ረ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 መሠረት መዝገብ ያልያዘ ወይም መዝገቡ እንዲወድም ወይም እንዲወገድ ያደረገ እንደሆነ፤

ሰ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 መሠረት የውስጥ ቁጥጥር ፕሮግራም ተግባራዊ ያላደረገ እንደሆነ፤

ሸ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5፣ አንቀጽ 10 ወይም አንቀጽ 15 መሠረት አግባብ ባላቸው ባለሥልጣኖች ሲጠየቅ በወቅቱ መረጃ ያልሰጠ ወይም መዝገብ ያላሳየ እንደሆነ፤

ቀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 መሠረት ጥርጣሬዎችን በሚመለከት ለማዕከሉ ሪፖርት ያላቀረበ እንደሆነ፤

በ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 18 መሠረት የጥሬ ገንዘብ ግብይቶችን በሚመለከት ለማዕከሉ ሪፖርት ያላቀረበ እንደሆነ፤

ተ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19 መሠረት ሲጠየቅ ግብይት ከመፈፀም ለመቆጠብ ፍቃደኛ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ፤ ወይም

ቸ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 23 የተደነገገውን በመተላለፍ መረጃ ለደንበኛ ወይም ለሌላ ሦስተኛ ሰው አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፤

በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከሦስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራትና ከብር 5,000 እስከ ብር 10,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተጠቀሰው ማንኛውም ተቀጽላ ወንጀል ጥፋተኛ የሆነ ሰው ከእሥራቱና የገንዘብ ቅጣቱ በተጨማሪ ወንጀሉን ለመፈጸም እድል የፈጠረለትን የንግድ ወይም የሙያ ሥራ ለዘለቄታው ወይም ከአምስት ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ እንዳይሠራ ሊታገድ ይችላል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚጣሉ ቅጣቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኖች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 22 መሠረት ሊወስዱ የሚችሏቸውን አስተዳደራዊ እርምጃዎች አያስቀሩም፡፡

**31. ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት**

1. ማንኛውም ሰው፡-

ሀ/ ገንዘቡ በሙሉ ወይም በከፊል፡-

1) የሽብርተኝነት ድርጊት ለመፈጸም፣

2) ለአሸባሪ መጠቀሚያ፣ ወይም

3) ለሽብርተኛ ድርጅት መጠቀሚያ፣

እንዲውል በማሰብ ወይም እንደሚውል እያወቀ በማንኛውም መንገድ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በገዛ ፈቃዱ ገንዘብ የሰጠ ወይም የሰበሰበ ወይም ገንዘብ ለመስጠትም ሆነ ለመሰብሰብ የሞከረ እንደሆነ፣

ለ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ (ሀ) የተመለከተውን ወንጀል በመፈጸም በአባሪነት የተሳተፈ እንደሆነ፣

ሐ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ (ሀ) የተመለከተውን ወንጀል ለማስፈጸም ሌሎችን ያደራጀ ወይም አመራር የሰጠ እንደሆነ፣ ወይም

መ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ሐ) የተመለከቱትን ወንጀሎች የሚያቋቁሙ ተግባራትን በመፈፀም የተሳተፈ፣ ለመፈፀም ያደመ፣ የምከረ፣ የደገፈ፣ ያመቻቸ ወይም እንዲፈፀም ያማከረ እንደሆ፣

በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 35 መሠረት የንብረቱ መወረስ እንደተጠበቀ ሆኖ ከ10 ዓመት እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር 100,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚጣል ቅጣት በሚከተሉት ምክንያቶች በመክበድ ከ15 ዓመት እስከ 25 ዓመት ጽኑ እስራት እና እስከ ብር 150,000 መቀጮ ሊደርስ ይችላል፡-

ሀ/ ወንጀሉ የተፈፀመው በንግድ ወይም በሥራ ተግባርነት ተይዞ ከሆነ፣ ወይም

ለ/ የተደራጀ የወንጀል ቡድን ከዓላማዎቹ አንዱ አድርጎት የፈጸመው ከሆነ፡፡

3. ሽብርተኝነትን በገንዘብ በመርዳት ወንጀል መሳተፍ፣ ወንጀሉን ለመፈጸም ማደም፣ መሞከር፣ መደገፍ፣ ማመቻቸት ወይም ማማከር ወንጀሉ እንደተፈጸመ ተቆጥሮ የሚያስቀጣ ይሆናል፡፡

## 32.ሌሎች ወንጀሎች

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠን ገንዘብ ወይም ንብረት የማገድ፣ የመያዝ ወይም የመውረስ ትዕዛዝ ያላከበረ ማንኛውም ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከሦስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር 5,000 እስከ ብር 10,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡
2. ለዚህ አዋጅ ዓላማ፡-

ሀ/ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ከማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ወይም በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ከተሰጠ ትዕዛዝ ጋር በተያያዘ ለሚደረግ ምርመራ ጠቃሚ የሆነ ሰነድ ወይም ማቴሪያል ወደ ሐሰት የለወጠ፣ ያጠፋ ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ የስወገደ ወይም ወደ ሐሰት ሰነድነት እንዲለወጥ፣ እንዲጠፋ ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ እንዲወገድ የፈቀደ አንደሆነ፤

ለ/ በማዕከሉ ዘንድ የተቀመጠውን መረጃ ሆነ ብሎ ያጠፋ ወይም በሌላ በማናቸዉም መንገድ ለሚፈለገዉ ዓላማ እንዳይውል ያደረገ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ በማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ በመርዳት ድርጊት ላይ ምስክር የሆነን ወይም ለመሆን የሚችል ሰውን እንዳይመሰክር የደለለ ወይም ያስፈራራ ወይም በምስክሩ ወይም ከምስክሩ ጋር የቅርብ ግንኙነት ባለው ሰው ላይ የሀይል ድርጊት የፈፀመ እንደሆነ፤

ከአምስት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር 10,000 እስከ ብር 50,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

## 33.በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው አካል ላይ የሚጣል ቅጣት

1. የመንግሥት አካል ያልሆነ ማንኛውም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል፡-

ሀ/ ወክሎት በሚሠራ ወይም በዚሁ አካል ውስጥ የመቆጣጠር ሥልጣን ያለው ግለሰብ በተናጠልም ሆነ ከሚመራው ቡድን ጋር በመሆን ሲሠራ አካሉን በመወከል ወይም ለአካሉ ጥቅም ሲባል በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀል የተፈጸመ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ በአካሉ ሃላፊነት ሥር የሚሠራን ግለሰብ በሚመለከት ሊደረግ በሚገባው ክትትልና ቁጥጥር መጓደል ምክንያት አካሉን በመወከል ወይም ለአካሉ ጥቅም ሲባል በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀል የተፈጸመ እንደሆነ፤

ግለሰቦቹ በወንጀል ፈጻሚነት ወይም አባሪነት የጥፋተኝነት ፍርድ ቢሰጥባቸዉም ባይሰጥባቸውም በሕግ የሰዉነት መብት የተሰጠዉ አካል በዚህ አዋጅ አንቀጽ 29 ወይም አንቀጽ 31 የተመለከተው የገንዘብ ቅጣት በአሥር ተባዝቶ ይፈጸምበታል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በወንጀል ተጠያቂ የተደረገ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል፣ በፍርድ ቤቱ ተጨማሪ ዉሳኔ፡-

   ሀ/ የተወሰኑ የንግድ ሥራዎችን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለዘለቄታዉ ወይም ከአምስት ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ እንዳያካሂድ ሊታገድ፤

   ለ/ ወንጀሉን ለመፈጸም በጥቅም ላይ የዋለውን የሥራ ቦታውን ለዘለቄታዉ ወይም ከአምስት ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ እንዲዘጋ፤ ወይም

   ሐ/ እንዲፈርስና ሂሳቡ እንዲጣራ ሊደረግ፤

   ይችላል፡፡

3. በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል በዚህ አንቀጽ መሠረት በወንጀል መጠየቁ ወንጀሉን በመፈጸም የተሳተፉ ግለሰቦችን ከተጠያቂነት አያድናቸዉም፡፡

## 34.<u>የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች</u>

የወንጀሉ ፈጻሚ ለፍትሕ አካላት፡-

1. ወንጀሉ የሚያስከትለውን ጉዳት ለመከላከል ወይም ለመቀነስ፤
2. የወንጀሉን ሌሎች ፈጻሚዎች ለመለየት ወይም ለፍርድ ለማቅረብ፤
3. ከወንጀሉ ጋር የተያያዘ ማስረጃ ለማግኘት፤ ወይም
4. የተደራጁ የወንጀለኛ ቡድኖችን ሀብታቸውን ወይም በወንጀል ፍሬነት ያገኙትን ለማሳጣት፤

   የሚያስችላቸውንና በሌላ መንገድ ሊያገኙ የማይችሉትን መረጃ የሰጣቸው እንደሆነ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 29 ወይም አንቀጽ 31 የተመለከቱት ቅጣቶች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 179 የተመለከቱት ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው ሊቀነሱለት ይችላሉ፡፡

## 35. ስለመዉርስ

1. በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ በማቅረብ ወይም በአመንጪው ወንጀል ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ በመርዳት ወንጀል የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠ እንደሆነ፡-

   ሀ/ የወንጀሉ ፍሬ የሆነው ገንዘብ ወይም ንብረት፣ ተቀላቅሎት ወይም ተለውጦበት የተገኘ ንብረትን ጨምሮ፤

   ለ/ ከወንጀሉ ፍሬ የተገኘን ገቢና ሌሎች ጥቅሞች የሚመለከት ገንዘብ ወይም ንብረት፤

   ሐ/ ለወንጀሉ መፈጸሚያነት የዋለ ንብረት፤

   መ/ ባለቤትነቱ የተላለፈለት ምንጩ ሕገወጥ መሆኑን ሳያውቅና ተገቢ የሆነ ዋጋ ከፍሎበት ወይም ለሰጠው ተመጣጣኝ አገልግሎት ታስቦለት ወይም በሌላ ሕጋዊ ምክንያት መሆኑን ፍርድ ቤቱ ካላመነ በስተቀር በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከተራ ፊደል (ሀ) እስከ (ሐ) ከተመለከቱት መካከል ለማንኛውም ወገን የተላለፈ ገንዘብ ወይም ንብረት፤ ወይም

   ሠ/ ከወንጀሉ ፍሬ ጋር ተመጣጣኝ ግምት ያለው የወንጀል ፈጻሚው ንብረት፤ እንዲወረስ ፍርድ ቤቱ ያዛል።

2. በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ በማቅረብ ወይም በአመንጪዉ ወንጀል ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ በመርዳት ወንጀል የተፈረደበት ሰዉ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የያዘዉና በወንጀሉ ከመከሰሱ አስቀድሞ ባሉት አምስት ዓመታት ዉስጥ የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ጥፋተኛ የተሰኘበት ወንጀል ውጤት ነው ብሎ ለመገመት የሚያስችል በቂ ምክንያት ካለና ግለሰቡ በሕጋዊ መንገድ ያፈራዉ ስለመሆኑ በማስረጃ ማረጋገጥ ካልቻለ በተጨማሪነት እንዲወረስ ፍርድ ቤቱ ሊወስን ይችላል፡፡

3. የወንጀሉ ፈጻሚ ባለመታወቁ፣ በመሰወሩ ወይም በመሞቱ ምክንያት የጥፋተኝነት ውሳኔ መስጠት ባይቻልም፣ ፍርድ ቤቱ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወይም የአመንጪው ወንጀል ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀል መፈጸሙን ካረጋገጠና የተያዘው ንብረት የወንጀል ፍሬ ወይም የወንጀል መፈጸሚያ መሆኑን የሚያሳይ በቂ ማስረጃ ከቀረበለት እንዲወረስ ሊወስን ይችላል፡፡

4. የመውረሻ ትዕዛዝ የሚወረሰውን ንብረት መግለጽና ንብረቱን ለመለየትና የሚገኝበትን ሥፍራ ለማመልከት የሚያስፈልጉ ዝርዝሮችን መያዝ አለበት፡፡
5. ፍርድ ቤቱ ዓላማው የንብረቱን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት መወረስ ለማስቀረት የሆነን ማንኛውንም ህጋዊ ሰነድ ተፈጻሚነት እንዳይኖረው ማድረግ ይችላል፤ ሆኖም ተፈጻሚነት እንዳይኖረው የተደረገው ውል የተፈረመው ዋጋ በተከፈለበት ግንኙነት ላይ ተመሥርቶ ከሆነ በቅን ልቦና ክፍያ የፈጸመው ተዋዋይ ወገን የከፈለው ገንዘብ ብቻ ተመላሽ ይደረግለታል፡፡

36.<u>ማገድና መያዝ</u>

1. ፍርድ ቤቱ በራሱ ተነሳሽነት ወይም በዐቃቤ ህግ አመልካችነት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 35 መሠረት ሊወረስ የሚችል የወንጀል ፍሬ ወይም የወንጀል መፈጸሚያ ተጠብቆ እንዲቆይ ለማድረግ የሚያስችሉ ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ጊዜያዊ እርምጃዎችን ጨምሮ የማገድ ወይም የመያዝ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ተፈጻሚ የሚደረገው በቅን ልቦና የተገኙ የሦስተኛ ወገን መብቶች ሳይነኩ ነው፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተወሰነን ማንኛውም ጊዜያዊ እርምጃ ውሳኔውን የሰጠው ፍርድ ቤት በራሱ ተነሳሽነት ወይም በዐቃቤ ህጉ፣ በወንጀሉ ተጠርጣሪ ወይም በንብረቱ ላይ መብት አለኝ በሚል ሰው አመልካችነት በማናቸውም ጊዜ ሊያነሳው ይችላል፡፡

37.<u>ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ጋር የተያያዘ ገንዘብን ስለማገድ</u>

1. የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት በተባበሩት መንግሥታት ቻርተር ምዕራፍ ሰባት መሠረት የሰየማቸው አሸባሪዎች፣ አሸባሪዎችን በገንዘብ የሚረዱ እና ሽብርተኛ ድርጅቶች ገንዘብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ ይታገዳል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚሰጠው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ እግዱ የሚያስከትላቸውን ግዴታዎችና ሁኔታዎች እና ጸንቶ የሚቆይበትን የጊዜ ገደብ የሚገልጽ ሆኖ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ላይ ታትሞ መዉጣት አለበት፡፡
3. የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚሰጠውን ውሳኔ ተከትሎ የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች፡-

ሀ/ በእጃቸው የሚገኘውንና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተጠቀሱት ግለሰቦችና አካላት ጋር ግንኙነት ያለውን ገንዘብ ወዲያውኑ እንዳይንቀሳቀስ ማድረግ፣ እና

ለ/ የተባለው ገንዘብ በእጃቸው መኖሩን ሳይዘገዩ ለማዕከሉ ሪፖርት ማድረግ፣ አለባቸዉ፡፡

## ክፍል ስድስት

## ዓለም አቀፍ ትብብር

### 38. ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 47(1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ያላቸው ባለሥልጣኖች በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀሎችን በሚመለከት ወንጀለኛን አሳልፎ በመስጠት፣ በመመርመርና ለፍርድ በማቅረብ ረገድ ከሌሎች አገሮች አግባብ ያላቸው ባለሥልጣኖች ጋር በሚቻለው መጠን ሁሉ የጋራ የህግ ድጋፍ ትብብር ማድረግ አለባቸው።
2. በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ዓላማ እንደ ፖለቲካ ወንጀል፣ ከፖለቲካ ወንጀል ጋር ግንኙነት እንዳለው ወንጀል ወይም በፖለቲካ ፍላጎት በመገፋፋት እንደተፈጸመ ወንጀል አይቆጠርም፡፡

### 39. የጋራ ትብብር የሕግ ድጋፍ ጥያቄ

1. በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን በሚመለከት የጋራ ትብብር የሕግ ድጋፍ ጥያቄ በሌላ አገር አመልካችነት ሲቀርብ በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሠረት ይስተናገዳል፡፡
2. የጋራ ትብብር የሕግ ድጋፍ ጥያቄ በተለይ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡-

   ሀ/ ከሰዎች ማስረጃ ወይም ቃል መቀበልን፣

   ለ/ የተያዙ ሰዎችን ወይም ፈቃደኛ የሆኑ ምስክሮችን ማስረጃ እንዲሰጡ ወይም ምርመራውን እንዲረዱ ለጠያቂው አገር የዳኝነት አካላት ማቅረብን፣

   ሐ/ የፍርድ ቤት ሰነዶችን ለሚመለከታቸው እንዲደርሱ ማድረግን፣

መ/ የፍተሻና የመያዝ ትዕዛዞች ማስፈጸምን፣

ሠ/ ቁሳቁሶችንና ሠፍራዎችን መፈተሸን፣

ረ/ መረጃዎችን፣ የማስረጃ ቁሳቁሶችንና የባለሞያ ግምቶችን መስጠትን፣

ሰ/ የመንግሥት፣ የባንክ፣ የፋይናንስ፣ የተቋም ወይም የንግድ ሥራ መዝገቦችን ጨምሮ አግባብነት ያላቸውን ሰነዶችና መዝገቦች ዋና ወይም የተረጋገጡ ቅጅዎችን መስጠት፤

ሸ/ የወንጀል ፍሬን፣ የወንጀል መፈጸሚያዎችን ወይም ሌሎች ነገሮችን ለማስረጃነት ወይም ለመዉረስ ዓላማ ተከታትሎ መለየትን ወይም ማግኘትን፤

ቀ/ ገንዘብን ወይም ንብረትን መዉረስን፤

በ/ የማገድ ወይም የመያዝ እና ሌሎች ጊዜያዊ እርምጃዎችን ማስፈጸምን፤

ተ/ ሌሎች ከኢትዮጵያ ሕጎች ጋር የማይቃረኑ የጋራ ትብብር ድጋፍ ጥያቄዎችን፡፡

## 40. ድጋፍ ስለመከልከል

1. የጋራ ትብብር የህግ ድጋፍ ጥያቄ ተቀባይነት ሊነፈገው የሚችለው በሚከተሉት ምክንያቶች ብቻ ይሆናል፡-

   ሀ/ በጠያቂው አገር ሕግ መሠረት አግባብ ባለው አካል የቀረበ ጥያቄ ካልሆነ ወይም ይዘቱ በመሠረታዊ ደረጃ ከዚህ አዋጅ አንቀጽ 48 ድንጋጌዎች ጋር የሚጣጣም ካልሆነ፤

   ለ/ አፈጻጸሙ የኢትዮጵያን ሕግና ሥርዓት፣ ሉዓላዊነት፣ ደህንነት፣ የሕዝብ ጥቅም ወይም ሌሎች መሠረታዊ ጥቅሞችን የሚነካ ከሆነ፤

   ሐ/ ጥያቄው የሚመለከተው የወንጀል ድርጊት በኢትዮጵያ ውስጥ በመዳኘት ላይ ከሆነ ወይም የመጨረሻ የፍርድ ውሳኔ የተሰጠበት ከሆነ፤

   መ/ እርምጃው ወይም ትዕዛዙ በተፈላጊዉ ግለሰብ ላይ ያነጣጠረው በግለሰቡ ዘር፣ ሃይማኖት፣ ዜግነት፣ የዘር ሐረግ፣ የፖለቲካ አመለካከት፣ ጾታ ወይም አቋም ላይ ብቻ ተመሥርቶ መሆኑን ለማመን የሚያስችል ተጨባጭ ምክንያት ሲኖር፤

   ሠ/ በድጋፍ ጥያቄው ውስጥ የተጠቀሰው ወንጀል በኢትዮጵያ ሕግ በወንጀልነት የተፈረጀ ካልሆነ ወይም በኢትዮጵያ ሕግ ከተደነገገው ወንጀል ጋር የሚያመሳሰለው ባህሪ የሌለው ከሆነ፤

ረ/ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተጠቀሰውን ወንጀል በሚመለከት የተጠየቀውን እርምጃ ወይም ተመሳሳይ ውጤት የሚኖረውን ሌላ እርምጃ መውሰድ የማይፈቀድ ከሆነ፤

ሰ/ በኢትዮጵያ ወይም በጠያቂዉ አገር ሕግ በተደነገገ የይርጋ ጊዜ ምክንያት የተጠየቀውን እርምጃ ማዘዝ ወይም ማስፈጸም የማይፈቀድ ከሆነ፤

ሸ/ እንዲፈጸም የተጠየቀውን ውሳኔ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ተፈጻሚ ማድረግ የማይቻል ሲሆን፤ ወይም

ቀ/ በውጭ አገር የተሰጠዉ ውሳኔ የተከሳሹን የመከላከል መብት በበቂ ደረጃ ባላስተናገደ ሁኔታ የተሰጠ ከሆነ፡፡

2. አግባብ ያለው ባለሥልጣን የጋራ ትብብር የህግ ድጋፍ ጥያቄው ተቀባይነት ሳያገኝ የቀረበትን ምክንያት አግባብ ላለው የጠያቂው አገር ባለሥልጣን ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

41.<u>የምርመራ ሥራን የሚመለከት የድጋፍ ጥያቄ</u>

1. አግባብ ያለዉ የጠያቂዉ አገር ባለሥልጣን በኢትዮጵያ ሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ጋር የማይቃረን ለየት ያለ ሥርዓትን ተከትሎ እንዲፈጸም ካልጠየቀ በስተቀር ምርመራ የሚካሄደዉ በኢትዮጵያ ሕግ የተደነገገውን የምርመራ ሥርዓት ተከትሎ ነዉ፡፡
2. የጠያቂው አገር አግባብ ያለዉ ባለሥልጣን የመደበዉ የመንግሥት ሃላፊ የምርመራ ሥራዉን አፈጻጸም እንዲታዘብ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

42.<u>ጊዜያዊ እርምጃዎች መውሰድን የሚመለከት የድጋፍ ጥደቄ</u>

1. በጠያቂዉ አገር እንዲወሰዱ የተጠየቁ ጊዜያዊ እርምጃዎች አግባብ ባለዉ የኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ይፈጸማሉ፡፡ እንዲወሰዱ የተጠየቁት እርምጃዎች በጥቅል አነጋገር የተገለጹ ከሆነ በሕጉ የተደነገጉትና ይበልጥ አግባብነት ያላቸው እርምጃዎች ይወሰዳሉ።
2. የተጠየቁት እርምጃዎች በኢትዮጵያ ሕግ የተደነገጉ ካልሆኑ አግባብ ያለው ባለሥልጣን በኢትዮጵያ ሕግ የተደነገጉትና በውጤት ይበልጥ ቅርበት ያላቸው እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል፡፡

3. ጊዜያዊ እርምጃዎችን ስለማንሳት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 36(3) የተመለከተው ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል፤ ሆኖም እርምጃዎቹ እንዲነሱ ከመደረጋቸው በፊት አግባብ ያለው የጠያቂው አገር ባለሥልጣን እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡

43.<u>የመውረስ እርምጃን የሚመለከት የድጋፍ ጥያቄ</u>

1. የመውረሻ ትዕዛዝ እንዲፈጸም የድጋፍ ጥያቄ ሲቀርብ አግባብ ያለው ባለሥልጣን በጠያቂው አገር ፍርድ ቤት ለተሰጠው ውሳኔ እውቅና ሰጥቶ ማስፈጸም ወይም በኢትዮጵያ ፍርድ ቤት የመውረሻ ትዕዛዝ ለማሰጠት ጉዳዩን ለዐቃቤ ሕግ መምራትና ትዕዛዙ ከተሰጠም ማስፈጸም አለበት፡፡
2. አግባብ ያለዉ ባለሥልጣን በጠያቂው አገር ፍርድ ቤት ለተሰጠው የመውረሻ ትዕዛዝ እዉቅና ሰጥቶ የሚያስፈጽመው ከሆነ ትዕዛዙ የተመሠረተባቸውን የመረጃ ግኝቶች እንዳሉ ወስዶ ማስፈጸም ይኖርበታል።
3. የመውረሻ ትዕዛዙ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 35 ድንጋጌዎች የሚሸፈንና በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የሚገኝ ገንዘብን ወይም ንብረትን የሚመለከት መሆን አለበት፡፡
4. ከጠያቂው አገር ጋር የተደረገ የተለየ ስምምነት ካልኖረ በስተቀር የሚመለከተው የመንግሥት አካል የተወረሰውን ንብረት የማስወገድ ሥልጣን ይኖረዋል።

44.<u>አሳልፎ የመስጠት ጥያቄ</u>

1. በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን በሚመለከት ወንጀለኛን ወይም ተጠርጣሪን አሳልፎ የመስጠት ጥያቄ ኢትዮጵያ ተዋዋይ ወገን በሆነችበት አግባብ ያለው ዓለም አቀፍ ስምምነት በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሠረት ይስተናገዳል፡፡
2. በዚህ አዋጅ መሠረት ወንጀለኛን ወይም ተጠርጣሪን አሳልፎ መስጠት የሚቻለዉ ለጥያቄው መነሻ የሆነው ወንጀል ወይም ተመሳሳዩ በጠያቂው አገርና በኢትዮጵያ ሕግ በወንጀልነት የተፈረጀ ሲሆን ነዉ፡፡
3. የጠያቂው አገር ሕግ ወንጀሉን ከኢትዮጵያ ሕግ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ወይም ባልሆነ የወንጀል ምድብ ወይም ስያሜ ቢገልጸውም ድርጊቱ በሁለቱም አገር ሕጎች በወንጀልነት የተፈረጀ እስከሆነ ድረስ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተሟላ ይቆጠራል።

## 45.አሳልፎ የመስጠት ጥያቄ ስለአለመቀበል

1. ወንጀለኛን ወይም ተጠርጣሪን አሳልፎ የመስጠት ጥያቄ የሚከተሉት ምክንያቶች ሲኖሩ ተቀባይነት አይሰጠውም፡-
   ሀ/ ተላልፎ እንዲሰጥ የተጠየቀው ሰዉ የኢትዮጵያ ዜግነት ያለው ሲሆን፤
   ለ/ ጥያቄው የቀረበው ተላልፎ እንዲሰጥ የተጠየቀውን ሰው በጾታው፣ በዘሩ፣ በሃይማኖቱ፣ በዜግነቱ፣ በዘር ሃረጉ ወይም በፖለቲካ አመለካከቱ ሳቢያ ለመክሰስና ለመቅጣት ተፈልጎ መሆኑን ለማመን የሚያስችል በቂ ምክንያት ሲኖር፤
   ሐ/ አሳልፎ የመስጠት ጥያቄ የቀረበበትን ወንጀል በሚመለከት በኢትዮጵያ ውስጥ የመጨረሻ የፍርድ ውሳኔ የተሰጠ ሲሆን፤
   መ/ ከሁለቱ አገሮች በአንዳቸው ሕግ መሠረት ምህረትና የይርጋ ጊዜ ገደብን ጨምሮ ተላልፎ እንዲሰጥ የተጠየቀውን ሰው ከመከሰስ ወይም ከመቅጣት ነፃ የሚያደርግ ማንኛውም ምክንያት ሲኖር፤ ወይም
   ሠ/ ተላልፎ እንዲሰጥ የተጠየቀው ሰው የማሰቃየት ወይም የጭካኔ ድርጊት ወይም ኢሰብዓዊ ወይም የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የተፈጸመበት ወይም ሊፈጸምበት የሚችል ስለመሆኑ፣ ወይም በሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን አንቀጽ 14 እንደተደነገገው በወንጀል ፍርድ ሂደት መሠረታዊ መብቶቹን ተነፍጎ እንደነበር ወይም ሊነፈግ እንደሚችል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችል በቂ ምክንያት ሲኖር።
2. ወንጀለኛን ወይም ተጠርጣሪን አሳልፎ የመስጠት ጥያቄ የሚከተሉት ምክንያቶች ሲኖሩ ተቀባይነት ሊያጣ ይችላል፡-
   ሀ/ አሳልፎ የመስጠት ጥያቄ የቀረበበትን ወንጀል የሚመለከት ክስ በኢትዮጵያ ውስጥ በመታየት ላይ ሲሆን፤
   ለ/ አሳልፎ የመስጠት ጥያቄ የቀረበበት ወንጀል የተፈጸመው ከሁለቱም አገሮች የግዛት ክልል ውጪ ሲሆን፤
   ሐ/ ተላልፎ እንዲሰጥ የተጠየቀው ሰው በፈጸመውና ለጥያቄው መነሻ በሆነው ድርጊት ምክንያት በጠያቂው አገር ውስጥ ባለ መደበኛ ባልሆነ ወይም ፍትሃዊነት በሌለው ልዩ ወይም ጊዜያዊ ፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት አካል ተፈርዶበት የነበረ ወይም ተከሶ ሊፈረድበት የሚችል ሲሆን፤

መ/ የወንጀሉ ሁኔታና የጠያቂው አገር ጥቅሞች ጭምር ተገናዝበው ቢታዩም ተላልፎ እንዲሰጥ ከተጠየቀው ሰው የእድሜ፣ የጤና ወይም ሌሎች የግል ሁኔታዎች አንፃር ሲታይ አሳልፎ መስጠቱ ከሰብዓዊነት መመዘኛዎች ጋር የማይጣጣም ሆኖ ሲገኝ፤ ወይም

ሠ/ ጥያቄው ተከሳሹ ከአቅሙ በላይ በሆነ ምክንያት ስለክሱ በቂ መረጃ ሳይኖረዉ ወይም ራሱን ለመከላከል በቂ የመዘጋጃ ዕድል ሳይኖረው በሌለበት በተሰጠ የመጨረሻ ፍርድ ላይ ተመሥርቶ የቀረበ ከሆነና ክሱ እንደገና ባለበት እንዲታይ እድል ያላገኘ ወይም ሊያገኝ የማይችል ሲሆን።

3. አሳልፎ የመስጠት ጥያቄው ውድቅ የተደረገው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ተራ ፊደል (ሀ) ወይም (ሠ) ወይም ንዑስ አንቀጽ (2) ተራ ፊደል (ሐ) ወይም (ሠ) መሠረት ከሆነ ግለሰቡ ለጥያቄው መነሻ በሆነው ወንጀል እንዲከሰስ ለማድረግ ጉዳዩ አግባብ ላለው ባለሥልጣን እንዲተላለፍ ይደረጋል፡፡

## 46.አሳልፎ የመስጠት ቀላል ሥርዓት

ተላልፎ እንዲሰጥ ጥያቄ የቀረበበት ሰዉ አግባብ ያሰው ባለሥልጣን ፊት ቀርቦ ተላልፎ እንዲሰጥ በመደረጉ መስማማቱን በግልጽ ካሳወቀ አሳልፎ መሰጠቱ ተጨማሪ ሥነ ሥርዓት መከተል ሳያስፈልግ ይፈቀዳል።

## 47.የጋራ ትብብር የሕግ ድጋፍና ወንጀለኛን አሳልፎ የመስጠት ጥያቄዎችን ስለማስተላለፍ

1. ማዕከሉ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን በተመለከተ አግባብ ባላቸው የሌሎች አገሮች ባለሥልጣኖች የሚቀርቡ የጋራ ትብብር የሕግ ድጋፍና ወንጀለኛን አሳልፎ የመስጠት ጥያቄዎችን የመቀበልና ለአፈጸጸማቸው አግባብ ላላቸው ባለሥልጣኖች የማስተላለፍ ሃላፊነትና ሥልጣን ይኖረዋል።
2. ጥያቄዎችና መልሶች ለማዕከሉ የሚላኩት በፖስታ ወይም ማዕከሉ ትክክለኛነታቸውን ሊያረጋግጥ የሚችልባቸውን የጽሑፍ ወይም ተመጣጣኝነት ያላቸውን ማቴሪያላዊ ማስረጃዎች በሚያስገኙ የተሻለ ፍጥነት ባላቸዉ ሌሎች መንገዶች ይሆናል፡፡
3. ጥያቄዎችና አባሪዎቻቸው በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ መቅረብ ወይም ከአማርኛ ወይም የእንግሊዝኛ ትርጉማቸው ጋር ተያይዘው መቅረብ አለባቸዉ፡፡

## 48.የጥያቄዎች ይዘት

1. የሚቀርቡ ጥያቄዎች ይዘት የሚከተሉትን መግለጽ አለበት፡-

ሀ/ ጥያቄውን ያቀረበውን ባለሥልጣን ማንነት፤

ለ/ የምርመራዉን፣ የክሱን ወይም የፍርድ ሂደቱን የሚያካሂደዉን ባለሥልጣን ስም፤

ሐ/ ጥያቄው የቀረበለትን ባለሥልጣን፤

መ/ የጥያቄዉን ዓላማና ማንኛዉንም አግባብነት ያለው ተያያዥ መግለጫ፤

ሠ/ የጥያቄው ደጋፊ የሆኑ መረጃዎችን፤

ረ/ የሚመለከተውን ሰዉ ማንነት ለመለየት የሚረዳ ማንኛውንም የሚታወቅ ዝርዝር መግለጫ፣ በተለይም የግለሰቡን ስም፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ዜግነት፣ አድራሻና የሚገኝበትን ሥፍራ እና ሥራ፤

ሰ/ የሚመለከተዉን ሰዉ፣ የወንጀል መፈጸሚያ፣ ገንዘብ ወይም ንብረት ለመለየትና ለመከታተል የሚያስፈልግ ማንኛውንም መረጃ፤

ሸ/ ወንጀሉን የሚያቋቁመውን የሕግ ድንጋጌ ይዘት፣ ወይም አግባብነት ያለው ከሆነ በወንጀሉ ተፈፃሚነት የሚኖረውን ሕግና ወንጀሉ ሊያስከትል የሚችለውን ቅጣት የሚመለከት መግለጫ፤ እና

ቀ/ የተጠየቀውን ድጋፍ ዓይነት የሚያመለክት መግለጫ።

2. የተወሰኑ የድጋፍ ዓይነቶችን የሚመለከቱ ጥያቄዎች በተጨማሪ የሚከተሉትን ዝርዝሮች መያዝ አለባቸው፡-

ሀ/ ጊዜያዊ እርምጃዎች እንዲወሰዱ የሚጠየቅ ሲሆን የሚፈለጉትን እርምጃዎች የሚያመለክት መግለጫ፤

ለ/ የመውረሻ ትዕዛዝ ለማሰጠት የሚቀርብ ጥያቄ ሲሆን የዳኝነት አካላት በአገሪቱ ሕግ መሠረት ትዕዛዝን ለመስጠት የሚያስችሏቸውን መረጃዎችንና የመከራከሪያ ነጥቦችን የያዘ መግለጫ፤

ሐ/ ጊዜያዊ እርምጃዎችን የሚመለከት ትዕዛዝ ወይም የመውረሻ ትዕዛዝ እንዲፈጸም የሚጠየቅ ሲሆን፡-

1) የትዕዛዙን የተረጋገጠ ቅጅ እና በትዕዛዙ ውስጥ ያልተካተቱ ከሆነ ትዕዛዙን ለመስጠት ያስቻሉትን ምክንያቶች የሚያሳይ መግለጫ፤

2) ትዕዛዙ ተፈጻሚነት ያለውና መደበኛ ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችል ያለመሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ፤ እና

3) አስፈላጊና የሚቻል ሲሆን በገንዘቡ ወይም ንብረቱ ላይ ሊቀርቡ የሚችሉ የሦስተኛ ወገን የመብት ጥያቄዎችን፤

መ/ ወንጀለኛን አሳልፎ የመስጠት ጥያቄዉ በወንጀሉ የተፈረደበትን ሰው የሚመለከት ሲሆን የፍርድ ውሳኔውን ዋና ወይም የተረጋገጠ ቅጅ ወይም የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔዉን፣ ቅጣቱ የሚኖረውን ተፈጻሚነት እና ያልተፈጸመውን ቀሪ የቅጣት መጠን የሚያሳይ ማንኛውንም ሰነድ፡፡

49.<u>ተጨማሪ መረጃዎች</u>

ማዕከሉ ወይም ጉዳዩን በማየት ላይ ያለዉ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ትዕዛዙን ለመፈጸም የሚያስፈልግ ወይም የሚረዳ ሆኖ ሲያገኘዉ አግባብ ያለው የጠያቂው አገር ባለሥልጣን ተጨማሪ መረጃዎች እንዲሰጠዉ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

50.<u>ሚስጥር ስለመጠበቅ</u>

ጥያቄው መቅረቡ ወይም ይዘቱ በሚስጥር እንዲያዝ በጥያቄው ውስጥ የተገለጸ ከሆነ ይኸው መከበር ይኖርበታል። ጉዳዩን በሚስጥር መያዙ የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ ወዲያውኑ ጠያቂው አገር እንዲያዉቀዉ መደረግ አለበት፡፡

51.<u>ጥያቄ ማስተናገድን ስለማዘግየት</u>

እንዲፈጸም የተጠየቀው እርምጃ ወይም ትዕዛዝ በኢትዮጵያ ውስጥ በመካሄድ ላይ ባለ ምርምራ ወይም የክስ ሂደት ላይ በመሠረታዊ ደረጃ ጣልቃ የሚያስገባ ሲሆን ማዕከሉ ጉዳዩን የማየት ሃላፊነት ላለው ባለሥልጣን መምራቱን ሊያዘገየው ይችላል፡፡ ይህንኑም ለጠያቂው አገር አግባብ ያለው ባለሥልጣን ወዲያውኑ ያሳውቀዋል።

## <u>ክፍል ሰባት</u>
## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

52.<u>የማስረጃዎች ተቀባይነት</u>

በዚህ አዋጅ መሠረት የተያዘን መረጃ የሚመለከት ሰነድ ወይም የሰነዱ የተረጋገጠ ግልባጭ ወይም የተረጋገጠ የኤሌክትሮኒክ ሕትመት በፍርድ ቤት በመታየት ላይ ላለ ጉዳይ በማስረጃነት ተቀባይነት ይኖረዋል።

53.**ስለይርጋ ጊዜ**

በወንጀል የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀል በፈፀመ ሰው ላይ የሚቀርብ ክስና የሚጣል ቅጣት በይርጋ አይታገድም፡፡

54.**ደንብና መመሪያ የማዉጣት ስልጣን**

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ለማዉጣት ይችላል፡፡
2. ማዕከሉ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

55.**የሌሎች ሕጎች ተፈፃሚነት**

1. አግባብ ያላቸዉ የተሻሻለው የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/1997 ድንጋጌዎች ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር የማይጣጣሙ እስካልሆኑ ድረስ በዚህ አዋጅ መሠረት ገንዘብ ወይም ንብረት ስለማገድ፤ ለመያዝና ስለመዉረስ የሚሰጡ ትዕዛዞችን አፈጻጸም በሚመለከት ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።
2. የአዋጅ ቁጥር 652/2001 ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

56.**የዳኝነት ስልጣን**

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ አዋጅ በተደነገጉ ወንጀሎች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል።

57.**የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸዉ ህጎች**

1. የሚከተሉት በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡-
   ሀ/ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 657/2002፤ እና
   ለ/ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 684፡፡
2. የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/ 2001 አንቀጽ 5(1)(መ) ድንጋጌ ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀልን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

58.**አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር 27 ቀን 2005 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 881/2007

## የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ

በ1996 ዓ/ም የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች ውስጥ በአፈፃፀም ወቅት የተስተዋሉ ግልጽነት የሚጎድላቸውን ድንጋጌዎች ግልጽ ማድረግና ማሻሻል በማስፈለጉ፤

የሙስና ወንጀሎቹ ማካተት የነበረባቸውን ተመሳሳይ ተግባራት በተለይም ከህዝብ የተሰባሰበ ወይም ለህዝብ ተብሎ የተሰባሰበ ሀብት በሚያስተዳድሩ የግል ዘርፍ አካላት የሚፈፀሙ ተመሳሳይ ተግባራትን በአግባቡ ያላካተቱ በመሆናቸው እነዚህኑ ማካተት በማስፈለጉ፤

ሀገራችን ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው የተባበሩት መንግስታት የፀረ ሙስና ኮንቬንሽን እና የአፍሪካ ህብረት የሙስና መከላከያና መዋጊያ ኮንቬንሽን በግል ዘርፍ ተቋማት ውስጥ የሚፈፀሙ ጉቦኝነት፣ የምዝበራ እና ተመሳሳይ ተግባራት በሙስና ወንጀልነት መፈረጅ እንዳለባቸው በፈራሚ አገሮች ላይ ግዴታ የሚጥል በመሆኑ ሕጉን ከዚህ አኳያ ማሻሻል በማስፈለጉ፤

በተግባር የታዩ ችግሮችን በመፍታት የተሟላ የህግ ማዕቀፍ እንዲኖር ማድረግ የፀረ ሙስና ትግሉን ለማጠናከር እና ሀገራችን ያለባትን አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ግዴታ በአግባቡ እንድትወጣ ለማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የሙስና ወንጀሎች በፈጣን ሁኔታ የመቀያየር ባህሪ ስላላቸው አጠቃላይ ወንጀሎችን በሚደነግገው የወንጀል ህግ (ኮድ) ውስጥ እንዲካተቱ ከማድረግ ይልቅ ራሱን በቻለ አዋጅ እንዲደነገጉ ማድረግ ተመራጭ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 55(1) እና (5) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

1. “የመንግስት መሥሪያ ቤት” ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግስት በጀት የሚተዳደር እና የፌደራል ወይም የክልል መንግስት ሥራዎች የሚከናወኑበት ማናቸውም መሥሪያ ቤት ነው፤
2. “የመንግስት ሠራተኛ” ማለት በመንግስት መሥሪያ ቤት ወይም በመንግስት የልማት ድርጅት ውስጥ ተቀጥሮ፣ ተሹሞ፣ ተመድቦ፣ ወይም በህዝብ ተመርጦ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ሥራን የሚያከናውን ማንኛውም ሰው ሲሆን የሥራ አመራር ቦርድ አባልን ይጨምራል፤
3. “የመንግስት የልማት ድርጅት” ማለት የመንግስት የባለቤትነት ድርሻ በሙሉ ወይም በከፊል ያለበት የፌደራል ወይም የክልል መንግስት የልማት ድርጅት ወይም የአክሲዮን ማህበር ነው፤
4. “ህዝባዊ ድርጅት” ማለት በማንኛውም አግባብ ከአባላት ወይም ከህዝብ የተሰበሰበ ወይም ለህዝባዊ አገልግሎት ታስቦ የተሰበሰበ ገንዘብ፣ ንብረት ወይም ሌላ ሀብትን የሚያስተዳድር አካልንና አግባብነት ያለው ኩባንያን የሚያካትት የግል ዘርፍ ሲሆን፣ የሚከተሉትን አያካትትም፡

   ሀ/ የሃይማኖት ድርጅትን፤

   ለ/ የፖለቲካ ድርጅትን (ፓርቲን)

   ሐ/ የዓለም አቀፍ ድርጅት፤ እና

   መ/ ዕድርንና ተመሳሳይ ባህላዊ ወይም ሃይማኖታዊ ይዘት ያለው ማህበርን፡፡
5. “የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ” ማለት በህዝባዊ ድርጅት ውስጥ ተቀጥሮ፣ ተመድቦ፣ ወይም በአባላት ተመርጦ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት የሚሠራ ሰራተኛ ሲሆን የድርጅቱን መሪ፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባልን፣ የአክሲዮን ማህበር ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅት የሚያደራጅ ሰውን ወይም ኮሚቴን ያካትታል፤
6. “አግባብነት ያለው ኩባንያ” ማለት በሕዝባዊ ድርጅት የተቋቋመ ኃላፊነቱ የተወሰነ ኩባንያ ሲሆን እንደዚህ ዓይነት ኩባንያ ከሌሎች ጋር የሚያቋቁመውን የሽርክና ማኅበርን ያጠቃልላል፤
7. “ለህዝባዊ አገልግሎት የተሰበሰበ ሀብት” ማለት የተወሰነ የህብረተሰብ ክፍልን ወይም ህብረተሰቡን በአጠቃላይ ለመርዳት ወይም ለመደገፍ ወይም ለማበረታታት ወይም ለማልማት ታስቦ የተሰበሰበ ወይም ለዚሁ ዓላማ እንዲውል በማንኛውም መንገድ

የተገኘ እና በበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የሚተዳደር ወይም የሚንቀሳቀስ ገንዘብ፣ ንብረት ወይም ሀብት ነው፤

8. "የበጎ አድራጎት ድርጅት" ማለት አግባብ ባለው ህግ መሰረት የተመዘገበ ሆኖ ለበጎ አድራጎት ዓላማ ብቻ የተቋቋመና ለህዝብ ጥቅም የሚሰጥ ተቋም ነው፤
9. "የሃይማኖት ድርጅት" ማለት የአንድ ሃይማኖት ተከታዮች ሃይማኖታቸውን ለማደራጀት እና ለማስፋፋት የሚያቋቀሙት ተቋም ወይም ቤተእምነት ሲሆን የበጎ አድራጎት ዓላማዎችን ለማሳካት በሃይማኖት ድርጅቱ የተቋቋሙ ድርጅቶችን አያጠቃልልም፤
10. "የፖለቲካ ፓርቲ" ማለት አግባብ ባለው ህግ መሰረት የተዘመገበ እና የፖሊቲካ አጀንዳ የሚያራምድ ድርጅት ነው፤
11. "ዓለም አቀፍ ድርጅት" ማለት የኢትዮጵያ መንግስት ከሌላ አገር መንግስት ወይም ከዓለምአቀፍ ወይም አህጉራዊ ተቋም ጋር በሚያደርገው ስምምነት መሠረት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚንቀሳቀስ ዓለም አቀፍ ተቋም ወይም የውጭ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ነው፤
12. "በጊዜያዊነት ሥራን የሚያከናውን ሰው" ማለት በቋሚነት ሳይቀጠር በክፍያ ወይም ያለ ክፍያ በሙሉ ጊዜ ወይም በትርፍ ጊዜ የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግስት ልማት ድርጅት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራን የሚያከናውን ሰው ሲሆን ተለማማጅ ሰራተኛን ያካትታል፤
13. "ጥቅም" ማለት የሚከተሉትን ያካትታል፡-
    ሀ/ በገንዘብ ወይም በማናቸውም ዋጋ ባለው መያዣ ወይም በሌላ ንብረት ወይም በንብረት ላይ ያለን ጥቅም (መብት)፤
    ለ/ ማንኛውንም ሹመት፣ ቅጥር ወይም ውል፤
    ሐ/ ብድርን፣ ግዴታን ወይም ማናቸውንም ዕዳ በሙሉም ሆነ በከፊል መክፈልን፣ ማስቀረትን፣ ማወራረድን ወይም ከእነዚህ ነገሮች ነፃ ማድረግን፤
    መ/ ከተመሰረተ ወይም ካልተመሰረተ የአስተዳደር የፍትሐብሔር ወይም የወንጀል ክስ ወይም ካስከተለው ወይም ከሚያስከትለው ማናቸውም ቅጣትነወይም የችሎታ ማጣት በማዳን ወይም ይህን በመሰለ ዘዴ የሚደረግን አገልግሎት ወይም ውለታ፤
    ሠ/ ማናቸውንም መብት ወይም ግዴታ መፈጸምን ወይም ከመፈጸም መታቀብን

ረ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ሠ) ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች ውጭ በገንዘብ የማይተመን ማናቸውንም ሌላ ጥቅም ወይም አገልግሎት፤ እና

ሰ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ረ) ከተጠቀሱት ጥቅሞች አንዱን ማቅረብን፣ ጥቅሙ የሚገኝበትን መንገድ ማመቻቸትን ወይም ይህንኑ በሚመለከት የተስፋ ቃል መግባትን ወይም መቀበልን፡፡

14.“የማይገባ ጥቅም” ማለት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ወይም አግባብ ባልሆነ መንገድ የተገኘ ጥቅም ነው፤

15.“ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

16.ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል።

3. **ጥቅም የማግኘት ወይም የመጉዳት የሓሳብ ግምት**

ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በስተቀር የሙስና ወንጀሎቹ የተፈፀሙት የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም ሌላውን ሰው ለመጉዳት መሆኑ በተደነገገ ጊዜ በድንጋጌው የተመለከተው ግዙፋዊ ፍሬ ነገር መፈጸሙ ከተረጋገጠ ድርጊቱ የተፈፀመው ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራስ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም የሦስተኛ ወገንን መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት እንደሆነ ይገመታል።

4. **መርህ**

1. ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተውን የሙስና ባህርይ የሚያሟላ ወንጀል በፈጸመ ጊዜ ለወንጀሉ የተደነገጉት የቅጣት ድንጋጌዎች ይፈፀሙበታል፡፡
2. ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የማይገባ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ በተሰጠው ኃላፊነት ወይም ተግባር ማድረግ የሚገባውን እንዳያደርግ ወይም ማድረግ የማይገባውን እንዲያደርግ ከሌላ ሰው ላይ ጥቅም የተቀበለ ወይም የጠየቀ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ለማስገኘት የተሰጠውን ስልጣን ወይም የህዝብ አደራ ያላግባብ የተገለገለበት እንዲሆን ወይም ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ ለመንግስት ወይም ለህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለመስጠት ቃል የገባ፤ ያቀረበ፣ የሰጠ ወይም ለማቅረብ የተስማማ

እንደሆነ፣ ወይም በአግባቡ ለተፈፀመ ወይም በአግባቡ ለወደፊቱ ለሚፈፀም የመንግስት መሥሪያ ቤት ወይም የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራ የማይገባ ጥቅም ለማንኛውም ሰው የሰጠ ወይም ከማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የተቀበለ እንደሆነ፣ በሙስና ወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

3. ማንኛውም የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ፡-

ሀ/ በተጣሰው የሙስና ወንጀል ድንጋጌ ከሚወሰንበት ቅጣት በተጨማሪ በሕገ ወጥ መንገድ ያገኘው ጥቅም፣ ገንዘብ ወይም ንብረት እንዲሁም ጥቅሙን፣ ገንዘቡን ወይም ንብረቱን በማሰማራት የተገኘው ትርፍ ወይም ወለድ እንዲወረስ ወይም ጥቅሙ፣ ገንዘቡም ሆነ ንብረቱ ካልተገኘ የወንጀል ውጤት ካልሆነ ሀብቱ ተመጣጣኝ ዋጋው ተወርሶ እንዲመለስ ይደረጋል፤

ለ/ በሙስና ወንጀሉ ምክንያት ያገኘው ጥቅም ባይኖርም በመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግስት ልማት ድርጅት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ሀብት ላይ ጉዳት ማድረሱ ከተረጋገጠ ካደረሰው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ዋጋ ተወርሶ በማካካሻነት እንዲከፍል ይደረጋል።

4. ማንኛውም ሰው ከመንግስት ሠራተኛ ወይም ከህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ጋር ባለው ግንኙነት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ያገኘ ወይም በመንግስት መሥሪያ ቤት፣ በመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ሀብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ያደረገ እንደሆነ እንደአግባቡ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆኑበታል።

5. <u>**በህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በሙስና ወንጀል ተጠያቂነት**</u>

በወንጀል ህጉ አንቀፅ 90 (3) የተደነገገው ቢኖርም የመንግስት የአስተዳደር አካላትን ሳይጨምር የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በሙስና ወንጀል ተካፋይ ሆኖ ሲገኝ የድርጅቱ ኃላፊዎች ወይም ሠራተኞች በየግላቸው መጠየቃቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1. በቀላል እስራት ለሚያስቀጣ ለእያንዳንዱ የቅጣት ዓመት ሃያ ሺህ ብር፤
2. ከ 5 ዓመት በታች ፅኑ እስራት ለሚያስቀጣ ለእያንዳንዱ የቅጣት ዓመት ሰላሣ ሺህ ብር፤
3. ከአምስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት ፅኑ አስራት ለሚያስቀጣ ለእያንዳንዱ የቅጣት ዓመት ሃምሳ ሺህ ብር፤

4. ከአስር ዓመት በላይ ፅኑ እስራት ለሚያስቀጣ ለእያንዳንዱ የቅጣት ዓመት ሰማንያ ሺህ ብር መቀጮ እንዲከፍል ይወሰንበታል፡፡

6. **ከፍትህ ስለማምለጥ**

1. ማንኛውም ሰው፡-

ሀ/ የሙስና ወንጀል በመፈጸሙ በፍትህ አካል እየተፈለገ መሆኑን እያወቀ ወይምተፈላጊ መሆኑን የሚገልፅ ማስታወቂያ መውጣቱን እያወቀ ወይም በዋስ ከተለቀቀ በኋላ ከፍትህ ያመለጠ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ ለፖሊስ ወይም መርማሪ ሊይዘው ወይም ሊጠራው መምጣቱን አውቆ ወይም ከተያዘ ወይም በቁጥጥር ሥር ከዋለ በኋላ ያመለጠ እንደሆነ፤

በተገኘበት ወቅት በሕግ መሰረት ለፍትህ መቅረቡ ወይም በሌለበት የተፈረደበት የእስር ቅጣት ተፈፃሚ መሆኑ እና በሙስና ወንጀል ምክንያት መወረስ የሚገባው ሀብት መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ ከፍትህ በማምለጡ ብቻ በተከሰሰበት ወንጀል ለተፈረደበት ለእያንዳንዱ ዓመት ከሃያ ሺህ ብር በማያንስ ከሰባ ሺህ ብር በማይበልጥ በተጨማሪነት እንዲከፍል ይወሰንበታል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚወሰነው መቀጮ ጥፋተኛው ባይገኝም ሊገኝ ከሚችል ሀብቱ እንዲከፈል ይደረጋል።

7. **የአስተዳደር ቅጣትና የፍትሐብሄር ኃላፊነት በተደራራቢነት ተፈጻሚ ስለመሆን**

በሙስና ወንጀል ተከሶ መቀጣት ወይም በነፃ መለቀቅ በአስተዳደርም ሆነ ወይም በፍትሐብሔር ተጠያቂ መሆንን አያስቀርም፡፡

8. **ከክስ ነጻ ማድረግ**

1. ማንኛውም ሰው ከሙስና ወንጀሎች በአንዱ ተካፋይ ከሆነ በኋላ ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት ስለተፈፀመው ድርጊትና ስለተካፋዮቹ ሚና ጠቃሚ መረጃ ከሰጠ በሕግ ስልጣን በተሰጠው አካል በሙስና ወንጀል እንዳይከሰስ ሊደረግ ይችላል።
2. ስለመረጃው ጠቃሚነት አወሳሰንና ድርጊቱን ያጋለጠው ሰው እንዳይከሰስ ስለሚደረግበት ሁኔታ የሚደነግጉ ልዩ ሥነ-ሥርዓቶች አግባብ ባለው የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ ይወስናሉ።

3. ህጋዊ በሆነ መልኩ ላገኘው ወይም ሊያገኘው ለሚገባ አገልግሎት የሰጠውን ማናቸውንም ጥቅም እንደሰጠ ላጋለጠ ሰው የሰጠው ጉቦ ወይም ስጦታ ወይም ዋጋ ያለው ነገር በወንጀሉ ምክንያት ከተወረሰው ንብረት ላይ ይመለስለታል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የሙስና ወንጀል ድንጋጌዎች

9. **በስልጣን አላግባብ መገልገል**

1. ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ፡-

   ሀ/ የተሰጠውን ሹመት፣ ኃላፊነት በግልፅ ተግባር ወይም በግድፈት ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነ፤

   ለ/ በግልፅ ከተሰጠው ሥልጣን ወይም ኃላፊነት አሳልፎ የሠራ እንደሆነ፤ ወይም

   ሐ/ ሥልጣኑ ወይም ኃላፊነቱ የማይፈቅድለትን ጉዳይ፣ በተለይም ሥልጣን ወይም ኃላፊነት ሳይኖረው ወይም ከሥራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ ወይም ሥልጣኑን ወይም ኃላፊነቱን ከተወ በኋላ የሠራበት እንደሆነ፤

   እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት እና ከሦስት ሽህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከአሥር ሽህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

2. ኃላፊነቱ ወይም ግዴታው እንዲጣስ የተፈለገበት ዓላማ፤ የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት፣ የጥፋተኛው የኃላፊነት ወይም የሥልጣን ደረጃ ወይም በግለሰብ፣ በመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ጥቅም ወይም በህዝብ ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተፈጸመውን ወንጀል ከባድ አድርጎት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከሰባት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ፅኑ አስራት እና ከአስር ሺ.ህ ብር እስከ አንድ መቶ ሺ.ህ ብር የሚደርስ መቀጮ ይሆናል።

3. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (2) ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ሁለቱ ወይም ከዚያ በላይ ተደራርበው ሲገኙ ቅጣቱ ከአስር ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከሃያ ሺ.ህ ብር እስከ ሁለት መቶ ሺ.ህ ብር የሚደርስ መቀጮ ይሆናል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተገለፀው ቢኖርም በህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የሚፈፀም ከሰው ሃይል አስተዳደር ጋር የተያያዘ ጥፋት ጉቦ የመስጠትና የመቀበል ሁኔታ መኖሩ ካልተረጋገጠ በስተቀር በሙስና ወንጀል አያስከስስም።

10. **ጉቦ መቀበል**

1. ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራ ግዴታው ማድረግ የማይገባውን ለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባውን ላለማድረግ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም እንዲሰጥ የጠየቀ፣ የተቀበለ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ፣ እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት እና ከሦስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ፣ ወይም ከአስር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከአርባ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።
2. ኃላፊነት ወይም ግዴታው እንዲጣስ የተፈለገበት ዓላማ፣ የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት፣ የጥፋተኛው የኃላፊነት ወይም የሥልጣን ደረጃ ወይም በግለሰብ በመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ጥቅም ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተፈጸመውን ወንጀል ከባድ አድርጎት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከሰባት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ፅኑ እስራት እና ከአስር ሺህ ብር የማያንስ ከአንድ መቶ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል፡፡
3. ወንጀሉን የፈጸመው በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (2) ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ሁለቱ ወይም ከዚያ በላይ ተደራርበው ሲገኙ ቅጣቱ ከአስር ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከሃያ ሺህ ብር እስከ ሁለት መቶ ሺህ ብር የሚደርስ መቀጮ ይሆናል።
4. ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) በተገለፀው መሠረት ወንጀሉን የፈጸመው ከዓለም አቀፍ ግብይት ወይም ግንኙነት ጋር በተያያዘ የሥራ ግዴታ ድንበር ዘለል ኮርፖሬሽንን ጨምሮ ከማንኛውም የሌላ አገር መንግስት፣ ድርጅት፣ ሰው ወይም ዓለም አቀፍ ድርጅት ጥቅም ወይም ስጦታ የጠየቀ፣ የተቀበለ ወይም ለመቀበል የተስማማ እንደሆነ፣ እንደነገሩ ሁኔታ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)፣ (2) ወይም (3) ከተመለከቱት ቅጣቶች በአንዱ ይቀጣል፡፡

11. **<u>የማይገባ ጥቅም መቀበል</u>**

1. ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት ማድረግ የሚገባውን ተግባር ለማከናወን ሲል ይህንኑ ተግባር ከመፈፀሙ በፊት ወይም ከፈፀመ በኋላ ጥቅም እንዲሰጠው የጠየቀ፣ ያገኘ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ፣ እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት እና ከሦስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከሃያ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በተፈጸመው ወንጀል የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት፣ የጥፋተኛው የኃላፊነት ወይም የሥልጣን ደረጃ የወንጀሉን አፈጻፀም ከባድ አድርጎት እንደሆነ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ፅኑ እስራት እና ከአምስት ሺህ ብር በማያንስ ከስልሳ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይሆናል፡
3. ወንጀሉ የተፈፀመው ከዓለም አቀፍ ግብይት ወይም ግንኙነት ጋር በተያያዘ የሥራ ኃላፊነት ወይም ግዴታ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሠረት ያስቀጣል።

12. **<u>አስታራቂ ሽማግሌ፣ የግልግል ዳኛና ሌሎች ሰዎች የሚፈፅሙት ጉቦ የመቀበል ወንጀል</u>**

1. ማንኛውም አስታራቂ ሽማግሌ፣ የግልግል ዳኛ፣ የፍርድ ቤት ነባሪ፣ ንብረት ጠባቂ፣ ወይም አጣሪ፣ ሥራውን ለማካሄድ በባለስልጣን የተሾመ ተርጓሚ ወይም አስተርጓሚ ወይም በዳኝነት ወይም በዳኝነት ነክ በሚታይ ጉዳይ ላይ በሙያው ረገድ አስተያየቱን ወይም የምስክርነት ቃሉን የሚስጥ ማንኛውም ልዩ አዋቂ /ኤክስፐርት/ ወይም ገቢና ወጪን ኦዲት የሚያደርግ ኦዲተር፣ ወይም ግንባታ በተገባው ውል መሰረት መከናወኑን የሚያረጋግጥ መሃንዲስ ማድረግ የሚገባውን ለማድረግ ጉዳዩ ከሚመለከተው ሰው ላይ ጥቅም እንዲሰጠው የጠየቀ ወይም የተቀበለ እንደሆነ፣ እንደነገሩ ሁኔታ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ (1)፣ (2) ወይም (3) ከተመለከቱት ቅጣቶች በአንዱ ይቀጣል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀጽ (1) ከተመለከቱት ሰዎች አንዱ በተሰጠው ኃላፊነት ወይም ተግባር መሠረት ማድረግ የሚገባውን ተግባር ለማከናወን ሲል ይህንኑ ተግባር ከመፈፀሙ በፊት ወይም ከፈፀመ በኋላ ጥቅም እንዲሰጠው የጠየቀ ወይም

የተቀበለ እንደሆነ፣ እንደነገሩ ሁኔታ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 11 (1) ወይም (2) ከተመለከቱት ቅጣቶች በአንዱ ይቀጣል።

13. ***የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ስራን በማያመች አኳኋን መምራት***

1. ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት፣ ወይም ለማስገኘት በማሰብ ሥልጣኑን ወይም ሃላፊነቱ ተጠቅሞ፡-

   ሀ/ በንግድ ወይም በሌላ ሥራ፣ በግዢ ወይም በሽያጭ ወይም ከሚያከናውነው ሥራ ጋር በተያያዘ በማናቸውም የሥራ ግንኙነት ማናቸውም ዓይነት ጥቅም የወሰደ ወይም ይህን ጥቅም የሚያገኝበትን ውል የተዋዋለ ወይም ሌላ ዘዴ የፈጠረ እንደሆነ፤

   ለ/ አግባብ ባለው ባለሥልጣን ወይም ኃላፊ ከተወሰነው በላይ በሆነ ዋጋ የዕቃ ማቅረብ ውል፣ የሥራ መቋረጥ ውል ወይም ማናቸውም የሥራ ውል የተዋዋለ ወይም በውል ከተመለከተው ዕቃ ወይም አገልግሎት ውጭ የተቀበለ እንደሆነ፤

   ሐ/ በጠቅላላው በሥራው ሥልጣን ወይም ኃላፊነት መሠረት በአደራ የተሰጠውን ወይም ሊጠብቀውና ሊከላከለው የሚገባውን የመንግስት መሥሪያ ቤት፣ የመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ጥቅም የሚጎዳ ተግባር በማናቸውም ዘዴ የፈፀመ እንደሆነ፤

   እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት እና ከሦስት ሺህ ብር በማይበልጥ ወይም ከአስር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከአንድ መቶ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

2. ኃላፊነቱ ወይም ግዴታው እንዲጣስ የተፈለገበት ዓላማ፣ የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት፣ የጥፋተኛው የኃላፊነት ወይም የሥልጣን ደረጃ ወይም በግለሰብ፣ በህዝባዊ ድርጅት፣ በመንግስት ወይም በህዝብ ጥቅም ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተፈጸመውን ወንጀል ከባድ አድርጎት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከሰባት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ፅኑ እስራት እና ከአስር ሺህ ብር የማያንስ ከሁለት መቶ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ሁለቱ ወይም ከዚያ በላይ ተደራርበው ሲገኙ ቅጣቱ ከአስር ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሚደርስ ፅኑ

እስራት እና ከሃያ ሺህ ብር እስከ አራት መቶ ሺህ ብር የሚደርስ መቀጮ ይሆናል፡፡

4. የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ጥቅም የማግኘት ወይም የማስገኘት ሐሳብ ሳይኖረው፡-

   ሀ/ እራሱ ወይም የቅርብ ዘመዱ ባለጥቅም ወይም ባለአክሲዮን በሆነበት ድርጅት ወይም መስራች ወይም አባል በሆነበት የበጎ አድራጎት ድርጅት እና እርሱ በሚሠራበት መሥሪያ ቤት ወይም ድርጅት መካከል በንግድ ወይም በሌላ ሥራ፣ በግዢ ወይም በሽያጭ ወይም ከሚያከናውነው ሥራ ጋር በተያያዘ በማናቸውም የሥራ ግንኙነት ውል እንዲፈፀም ያደረገ እንደሆነ፣ ወይም

   ለ/ የተወሰኑ ንብረቶችን እንዳይገዛ ወይም እንዳይጫረት በህግ፣ በደንብ ወይም በመመሪያ ተከልክሎ እያለ በስሙ ወይም በሌላ ሰው ስም ወይም ከሌላ ሰው ጋር ንብረት የገዛ ወይም የተጫረተ እንደሆነ፣

   በቀላል እስራት እና በመቀጮ ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

5. ለዚህ አንቀጽ ንዕስ አንቀጽ (4) አፈፃፀም "ዘመድ" ማለት አግባብ ባለው ህግ መሠረት ከተጠርጣሪው ጋር የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው ሰው ነው።

6. በማንኛውም ደረጃ የሚገኝ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት የሥራ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ሆነ ብሎ የሚስጥር ኮድ በሚጠቀሙ አሠራሮች የሚስጥር ኮዱን ማወቅ የማይገባው ሰው እንዲያውቀው፣ ወይም አንድ ሰው ብቻ ሊይዘው የሚገባውን ቁልፍ መያዝ የማይገባው ሰው እንዲይዘው በማድረግ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሀብት ወይም ንብረት እንዲመዘበር፣ እንዲወሰድ፣ ወይም እንዲጠፋ ያደረገ እንደሆነ፣ ከአሥር ዓመት እስከ ሃያ ዓመት በሚደርስ ፅኑ አስራት እና ከሃምሳ ሺህ ብር እስከ ሦስት መቶ ሺህ ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) የተመለከተው ወንጀል የተፈፀመው በቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ ከሦስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከአሥር ሺህ ብር እስከ ሃምሳ ሺህ ብር በሚደርስ መቀጮ ያስቀጣል፡፡

8. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) አፈፃፀም ተጠርጣሪው የሚስጥር ኮዱ ወይም ቁልፉ ከእርሱ ፈቃድ ወይም ዕውቅና ውጪ የተወሰደ መሆኑን ካላስረዳ በስተቀር የሚስጥር ኮዱን ወይም ቁልፉን ሆነ ብሎ እንደሰጠ ይገመታል።

9. ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ አግባብ ባለው ኃላፊ እንዲጠቀምበት ወይም እንዲይዘው ያልተፈቀደለትን ወይም ያልተሰጠውን የሚስጥር ኮድ ወይም ቁልፍ ወስዶ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሀብት ወይም ንብረት የመዘበረ፣ የወሰደ ወይም ያጠፋ ወይም እንዲመዘበር፣ እንዲወሰድ ወይም እንዲጠፋ ያደረገ እንደሆነ፣ እንደነገሩ ሁኔታ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) ወይም (7) መሠረት ይቀጣል፡፡

14. <u>**አደራ በተሰጠው ዕቃ ያለ አግባብ ማዘዝ**</u>

1. ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ በህግ አግባብ ሳይፈቀድለትና የግል ንብረት ለማድረግ በማሰብ ሳይሆን ታሽጎ የተረከበውን ጥቅል፣ ኢንቨሎፕ፣ ሰነድ፣ ባለዋጋ ነገር ወይም አደራ ወይም እንደታሸገ የተረከበውን ማናቸውንም ዕቃ፡-

   ሀ/ የከፈተ፣ ያስከፈተ፣ የወሰደ፣ ወይም ያስወሰደ ወይም የእሽጉን ይዘት የገለጠ ወይም ዕቃውን አሳልፎ የሰጠ፤ ወይም

   ለ/ የተገለገለበት ወይም ሌላ ሰው እንዲገለገልበት የፈቀደ እንደሆነ፤

   ከሰባት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአምስት አመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ይቀጣል፡፡

2. ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ለራሱ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን ወንጀል የፈፀመ እንደሆነ፣ እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት እና ከሦስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ፣ ወይም ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከሃያ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

3. የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት የጥፋተኛው የኃላፊነት ወይም የሥልጣን ደረጃ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የተፈጸመውን ወንጀል ከባድ አድርጎት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ፅኑ እስራት እና ከአምስት ሺህ ብር በማያንስ ከስልሳ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይሆናል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ወንጀል የተፈፀመው በቸልተኝነት እንደሆነ፣ ቅጣቱ እስከ ሁለት ሺህ ብር የሚደርስ መቀጮ ይሆናል።

15.**በስራ ተግባር የሚፈጸም የመውሰድ እና የመሰወር ወንጀል**

1. የማይገባ ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ ማንኛውም፡-

   ሀ/ የመንግስት ሠራተኛ በብርበራ፣ በመያዝ፣ በመውረስ ሥርዓት፣ በሐራጅ ሽያጭ፣ በሕግ ውርስ ወይም ፍርዱ በንብረቱ ላይ እንዲፈፀም በመወሰኑ ወይም ይህን የመሰለ ማናቸውም ሥራ በሚያከናውንበት ወይም በሚያስፈፅምበት ጊዜ፤ ወይም

   ለ/ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በማንኛውም የሥራ አጋጣሚ በእጁ ሊገቡ የቻሉትን ወይም በአደራ የተረከባቸውን ወይም የሚጠብቃቸውን፣ ዕቃዎችን፣ ሰነዶችን፣ ባለዋጋ ነገሮችን፣ ጥሬ ገንዘቦችን፣ ተንቀሳቃሽ ወይም አላቂ ዕቃዎችን የወሰደ ወይም የሰወረ እንደሆነ፤

   እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት እና ከሦስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከአሥር ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

2. የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት፣ የጥፋተኛው የኃላፊነት ወይም የሥልጣን ደረጃ ወይም በግለሰብ በህዝብፓ በመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ጥቅም ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተፈአመጠን ወንጀል ከባድ አድርጎት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከሰባት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ፅኑ እስራት እና ከሰባት ሺህ ብር በማያንስ ከስልሳ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።

3. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (2) ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ሁለቱ ወይም ከዚያ በላይ ተደራርበው ሲገኙ ቅጣቱ ከአስር ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከአሥር ሺህ ብር የማያንስ እና ከአንድ መቶ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል፡፡

16. **በስልጣን ወይም  በኃላፊነት መነገድ**

1. ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በሥራው ምክንያት ባለው ወይም አስመስሎ ባቀረበው ተሰሚነት፡-

   ሀ/ አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም ኃላፊ ተወስኖ የሚሰጥ የሥራ ደረጃ፣ ሹመት፣ ሥራ፣ ሽልማት፣ የአገልግሎት ዋጋ፣ ልዩ ችሮታ፤

   ለ/ በቁጥጥሩ ወይም በአመራሩ ሥር በሚገኙ ባለስልጣኖች ኃላፊዎች ወይም የአስተዳደር ክፍሎች የሚደረግ ውል፣ የንግድ ስምምነት፣ የሥራ ጨረታ፣

የዕቃ ማቅረብ ውል፣ ወይም ሌላ ጥቅም፤ ወይም

ሐ/ በአጠቃላይ ከአንድ ባለስልጣን፣ ኃላፊ ወይም የአስተዳደር ክፍል የሚሰጠውን ጥቅም ወይም የሚረዳ ውሳኔ፤

ለሌላ ሰው ለማስገኘት ስጦታ ወይም ሌላ ጥቅም የጠየቀ ወይም የተቀበለ እንደሆነ፤ እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከሦስት ሺህ ብር በማያንስ ከስልሳ ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

2. ኃላፊነቱ ወይም ግዴታው እንዲጣስ የተፈለገበት ዓላማ፣ የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት፣ የጥፋተኛው የኃላፊነት ወይም የሥልጣን ደረጃ ወይም በግለሰብ፣ በመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ጥቅም ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተፈጸመውን ወንጀል ከባድ አድርጎት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከሰባት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ፅኑ እስራት እና ከሰባት ሺህ ብር የማያንስ ከአንድ መቶ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።

3. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (2) ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ሁለቱ ወይም ከዚያ በላይ ተደራርበው ሲገኙ ቅጣቱ ከአስር ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከአሥር ሺህ ብር የማያንስ እና ከሁለት መቶ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።

17. **<u>በህገወጥ መንገድ መሰብሰብ ወይም ማስረከብ</u>**

1. ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት በማሰብ፡-

ሀ/ ሊከፈል የማይገባ መሆኑን ወይም በህግ ከተወሰነው ታሪፍ በላይ መሆኑን እያወቀ ቀረጥ፣ ግብር፣ ልዩ ልዩ ገቢ ወይም ልዩ ልዩ የገቢ ጥቅም፣ ምንዳ፣ ደመወዝ፣ ካሣ ወይም ሌላ ወጪ የሰበሰበ ወይም እንዲሰበሰብ ያዘዘ እንደሆነ፤

ለ/ ማናቸውም ዕቃ ወይም ክፍያ በሚያስረክብበት ወይም በሚሰጥበት ጊዜ ማስረከብ ወይም መክፈል ከሚገባው አሳንሶ ያስረከበ ወይም የከፈለ እንደሆነ፤

እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት እና ከሦስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከአሥር ሺህ ብር በማያንስ ከሠላሳ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

2. ኃላፊነቱ ወይም ግዴታው እንዲጣስ የተፈለገበት ዓላማ፣ የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት፣ የጥፋተኛው የኃላፊነት ወይም የሥልጣን ደረጃ ወይም በግለሰብ፣ በመንግስት፣ ወይም በህዝባዊ ድርጅት ጥቅም ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተፈጸመውን ወንጀል ከባድ አድርጎት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከሰባት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ፅኑ አስራት እና ከሰባት ሺ.ህ ብር በማያንስ እና ከስልሳ ሺ.ህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።
3. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (2) ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ሁለቱ ወይም ከዚያ በላይ ተደራርበው ሲገኙ ቅጣቱ ከአስር ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከአሥር ሺ.ህ ብር የማያንስ እና ከአንድ መቶ ሺ.ህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ወንጀል የተፈፀመው በቸልተኝነት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ቀላል እስራት እና መቀጮ ይሆናል፡፡

18. <u>**ያላግባብ ጉዳይን ማጓተት**</u>

ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራው ምክንያት በቀረበለት ጉዳይ ላይ ጥቅም ካለው ማንኛውም ሰው በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ጥቅም ለማግኘት በጉዳዩ ላይ ጥቅም ያለውን ማንኛንውም ወገን ወይም ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ሲል ከህግ፣ ከስራ ደንብ፣ ከመመርያ ወይም ከተለመደው አሰራር ውጪ ያለበቂ ምክንያት ያልወሰነ፣ ያዘገየ ወይም ባለጉዳይን ያጉላላ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ በመቀጮ ወይም በቀላል እስራት ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ አስራት እና ከአምስት ሺ.ህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

19. <u>**ዋጋ ያለውን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማግኘት**</u>

1. ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ምክንያት ሳይኖረው ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማናቸውም ዋጋ ያለውን ነገር የተቀበለ እንደሆነ፤ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከአምስት ሺ.ህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡
2. ንብረትን፣ የፋይናንስ አቋምን ወይም ስጦታ መቀበልን ማስመዝገብ ወይም ማሳወቅ እንደሚገባ በህግ ወይም በደንብ በተደነገገ ጊዜ አለማሳወቅ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው መሰረት ያስቀጣል፡፡

3. በአገሩ ወይም በአካባቢው ባህል ወይም ልማድ መሰረት እንደተራ የወዳጅነት ምልክት የሚሰጥ ዋጋ ያለው ስጦታ መቀበል ወይም ከስጋ ወይም ከጋብቻ የቅርብ ዘመድ ወይም የቅርብ ወዳጅ ስጦታ ማግኘት በዚህ አንቀጽ ለተመለከተው ወንጀል ማቋቋሚያ አይሆንም።

20. <u>ያለአግባብ ፈቃድ መስጠት ወይም ማጽደቅ</u>

1. ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ ሆነ ብሎ ብቁ ላልሆነ ወይም በህግ ሊሰጠው ለማይገባ ሰው ማናቸውንም የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ የሰጠ ወይም ያጸደቀ እንደሆነ፣ ወይም አንድ ነገር የሚከናወንበትን ቦታ ያለ አግባብ የፈቀደ ወይም የሰጠ እንደሆነ፣ እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እስራትና መቀጮ ወይም ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከሦስት ሺህ ብር በማያንስ ከሠላሳ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።
2. ማንኛውም ፈቃድ ወይም ማረጋገጫ የመስጠት ኃላፊነት ያለው ሰው ሆነ ብሎ ብቁ ላልሆነ ወይም በህግ ሊሰጠው ለማይገባ ሰው የመንጃ ፈቃድ፣ የተሽከርካሪ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ፣ የሰው የጤንነት ማረጋገጫ ወይም የትምህርት ደረጃ ማረጋገጫ የሰጠ ወይም ያፀደቀ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ይቀጣል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) የተመለከተው ወንጀል የተፈጸመው በቸልተኝነት እንደሆነ ቅጣቱ ቀላል እስራትና መቀጮ ይሆናል፡፡

21. <u>ምንጩ ያልታወቀ ንብረት እና ገንዘብ</u>

1. ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የሆነ ወይም የነበረ ሰው፡-
   ሀ/ የኑሮ ደረጃው አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚያገኘው ወይም ሲያገኘው ከነበረው ህጋዊ ገቢ የበለጠ እንደሆነ፤
   ለ/ ያለው ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚያገኘው ወይም ሊያገኘው ከነበረው ህጋዊ ገቢ ጋር የማይመጣጠን እንደሆነ፤ የዚህ ዓይነቱ የኑሮ ደረጃ እንዴት ሊኖረው እንደቻለ ወይም ያለው ንብረት ወይም ገንዘብ በእጁ እንዴት ሊገባ እንደቻለ ለፍርድ ቤት ካላስረዳ በስተቀር የንብረቱ ወይም የገንዘብ ምንጩ መወረስ ወይም ለባለቤቱ መመለስ እንደተጠበቀ ሆኖ በቀላል እስራት እና በመቀጮ፣ ወይም ነገሩ ከባድ ሲሆን

ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ለ) የተጠቀሰው ወንጀል በፍርድ ቤት እየታየ ባለበት ጊዜ ማንኛውም ሰው ከተከሳሽ ጋር ካለው ቅርበት ወይም ሌሎች ሁኔታዎች የተነሳ ለተከሳሹ ባለአደራ በመሆን አንድን ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ እንደያዘ ወይም ከተከሳሹ በስጦታ እንዳገኘ ፍርድ ቤት ካመነበት ጉዳዩን በሌላ ማስረጃ ካላፈረስ በስተቀር ንብረቱ ወይም የገንዘብ ምንጩ በተከሳሹ ይዞታ ሥር እንደሆነ ይቆጠራል።

22. <u>**የስራ ሚስጥር መግለጽ**</u>

1. አግባብነት ባለው ህግ አያስጠይቅም ተብሎ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት፣ ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ በሥራው ምክንያት ያወቀው ሆኖ በጠባዩ ሚስጥር የሆነውን ወይም በሚስጥር እንዲጠበቅ የታዘዘውን ወይም ለህዝብ እንዳይገለፅ የተከለከለውን መረጃ፣ ሰነድ ወይም ፍሬ ነገር ሥራውን ወይም ሹመቱን ከለቀቀ በኋላ ቢሆንም እንኳ የገለፀ ወይም ያስተላለፈ እንደሆነ ከሁለት ዓመት በማያንስ ከአስራ ሁለት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከአምስት ሺህ ብር እስከ ከሠላሳ አምስት ሺህ ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ለተፈጸመው ወንጀል ጥፋተኛው የተለየ ሚስጥር የመጠበቅ ግዴታ ወይም እምነት የተጣለበት ወይም ወንጀሉ በተለይ ከፍ ያለ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ ሀያ ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከአስር ሺህ ብር እስከ ሀምሳ ሺ ብር የሚደርስ መቀጮ ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ወንጀል የተፈጸመው በቸልተኝነት ሲሆን ከአንድ ዓመት ያልበለጠ ቀላል እስራት እና በመቀጮ ይቀጣል፤ ሆኖም የወንጀሉ አፈጻጸም በንዑስ አንቀጽ (2) እንደተመለከተው ከባድ ሲሆን ከሦስት ዓመት ያልበለጠ ቀላል እስራት እና ከአምስት ሺህ ብር ያልበለጠ መቀጮ ይሆናል፡፡

23. <u>**መንግስታዊ ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰነዶች አስመስሎ ማዘጋጀት፤ ወደ ሀሰት መለወጥ ወይም በሐሰተኛ ሰነድ መገልገል**</u>

1. ማንኛውም ሰው የሌላውን ሰው መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ማናቸውም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ፡-

   ሀ/ አንድ ፅሑፍ፣ መዝገብ ወይም ማንኛውንም ሰነድ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት በማስመሰል ያዘጋጀ ወይም የፈጠረ እንደሆነ፤

   ለ/ በመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት መዝገብ፣ ጽሑፍ ወይም ሰነድ የሰፈረን እውነተኛውን ጽሑፍ በመለወጥ ወይም በመደለዝ፣ በሐሰተኛ ፊርማ፣ በእጅ በተደረገ ምልክት ወይም በጣት ፊርማ በማህተም ወይም የሌለውን ስልጣን ወይም ችሎታ እንዳለው አስመስሎ በመፈረም ሐሰተኛ ስነድ የፈጠረ እንደሆነ፤ ወይም

   ሐ/ አንድን የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰነድ በተለይም የፈራሚውን ስም ወይም ፊርማ ወይም የሰነዱን ይዘት፣ አሃዝ፣ ፍሬ ነገር ወይም ዝርዝር መገለጫ በሙሉ ወይም በከፊል በመለወጥ፣ በማሻሻል፣ በመቀነስ ወይም በመጨመር ወይም በማጥፋት ወደ ሐሰተኛነት የለወጠ ወይም ማናቸውንም ሐሰተኛ ፍሬ ነገር ያስገባ ወይም እንዲገባ ያደረገ እንደሆነ፤

   ከሦስት ዓመት  እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ፅኑ አስራት እና ከሦስት ሺህ ብር እስከ ሰላሳ ሺህ ብር በሚደርስ ይቀጣል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ወንጀል የተፈጸመው እነዚህን የመሳሰሉትን መዝገቦች፣ ጽሑፎች፣ የታወቀ ሰነዶች ወይም ሌሎች ሰነዶችን እንዲያዘጋጅ፣ እንዲመዘገብ፣ እንዲጠብቅ ወይም ከነዚሁ ውስጥ ቅጅዎችን እንዲሰጥ ኃላፊነት በተሰጠው የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ እንደሆነ ወይም ሰነዱን በመገልገል የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት ወይም በግለሰብ፣ በመንግስት፣ ወይም በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝብ ጥቅም ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛነት፡-

   ሀ/ የወንጀሉን አፈፃፀም ከባድ አድርጎት እንደሆነ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሚደርስ ፅኑ አስራት እና ከአምስት ሺህ ብር እስከ ሃያ አምስት ሺህ ብር የሚደርስ መቀጮ ይሆናል፤

   ለ/ የወንጀሉ አፈፃፀም በጣም ከባድ አድርጎት እንደሆነ ቅጣቱ እስከ ዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት ድረስ ይሆናል፡፡

3. ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው መሰረት ወደ ሐሰት በተለወጠ ወይም በሐሰት በተዘጋጀ ሰነድ እያወቀ የተገለገለበት እንደሆነ በዚሁ ንዑስ አንቀጽ በተመለከተው ቅጣት ይቀጣል።
4. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በስሙ ወይም ለራሱ ጥቅም እንዲውል ተመሳስሎ የተሠራ ወይም ወደ ሐሰት የተለወጠ ሰነድ በቤቱ፣ በተሽከርካሪው፣ በኪሱ ወይም በማንኛውም አግባብ በቀጥጥሩ ሥር የተገኘ እንደሆነ ተቃራኒ ማስረጃ ካላቀረበ በስተቀር ሰነዱን እራሱ እንዳዘጋጀው ወይም እንዲዘጋጅ እንዳደረገው ይገመታል።

24. <u>**መንግስታዊ ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰነዶች ማጥፋት ወይም ጉዳት ማድረስ**</u>

1. ማንኛውም ሰው የሌላውን ሰው መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ማናቸውንም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ በመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝብ ሰነድ ላይ ጉዳት እንዲደርስበት ያደረገ የቀደደ፣ ያጠፋ፣ ጥቅም ላይ እንዳይውል ያደረገ ወይም የወሰደ እንደሆነ ከሦስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከአሥር ሺህ ብር እስከ ሰባ ሺህ ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ወንጀል የተፈፀመው እንደዚህ ያለውን ሰነድ እንዲያዘጋጅ፣ እንዲመዘግብ፣ እንዲጠብቅ ወይም እንዲሰጥ ኃላፊነት በተሰጠው የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከሰባት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከሃያ አምስት ሺህ ብር እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር የሚደርስ መቀጮ ይሆናል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው ወንጀል አፈፃፀም በጣም ከባድ በሆነ ጊዜ ቅጣቱ ዕድሜ ልክ እስራት ይሆናል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) የተመለከተው ወንጀል የተፈፀመው በቸልተኝነት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት ያልበለጠ ቀላል እስራት እና ከሰባት ሺህ ብር ያልበለጠ መቀጮ ይሆናል፡፡

25. <u>**ጉቦ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም መስጠት**</u>

1. ማንኛውም ሰው አንድ የመንግስት ሠራተኛ ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራ ግዴታው ማድረግ የማይገባውን እንዲያደርግ ወይም ማድረግ የሚገባውን እንዳያደርግ ጥቅም ወይም ስጦታ የሰጠ ወይም ያቀረበ

እንደሆነ፣ እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እስራት እና በመቀጮ፣ ወይም ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከሰባት ሺህ ብር በማያንስ ከሠላሳ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

2. ማንኛውም ሰው ከዓለም አቀፍ ግብይት ወይም ግንኙነት ጋር በተያያዘ ለማንኛውም የሌላ አገር መንግስት፣ ድርጅት ወይም የዓለም አቀፍ ድርጅት ባለስልጣን ወይም ሠራተኛ በሥራ ግዴታው ማድረግ የማይገባውን እንዲያደርግ ወይም ማድረግ የሚገባውን እንዳያደርግ ጥቅም ወይም ስጦታ የሰጠ ወይም ያቀረበ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው መሠረት ይቀጣል፡፡
3. ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 12 ለተመለከቱት ሰዎች ጉቦ የሰጠ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው መሠረት ይቀጣል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)፣ (2) ወይም (3) ለተመለከተው ወንጀል ወንጀል አድራጊው ያቀረበው ገንዘብ ከፍተኛነት፣ ወይም ድርጊቱ በግለሰብ፣ በህዝብ፣ በመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ጥቅም ላይ ከፍተኛ ጉዳትን በማስከተሉ የወንጀሉን አፈጻጸም ከባድ አድርጎት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራት እና ከአምስት ሺህ ብር የማያንስ ከአንድ መቶ ሺ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል፡፡
5. የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት ማድረግ የሚገባውን ተግባር እንዲያከናውን ሲል ይህንኑ ተግባር ከመፈፀሙ በፊት ወይም ከፈፀመ በኋላ ለዚሁ ሠራተኛ ጥቅም ወይም ስጦታ የሰጠ ወይም ያቀረበ ማንኛውም ሰው፤ እንደ ነገሩ ሁኔታ በመቀጮ፣ በቀላል እስራት እና በመቀጮ፣ ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (5) የተመለከተው ወንጀል የተፈፀመው የሕግ ሰውነት በተሰጠው ሰው የሆነ እንደሆነ፣ በጥፋቱ ከሚሰጠው ቅጣት በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛው ከመንግስት መሥሪያ ቤት፣ ከመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም ከህዝባዊ ድርጅት ጋር ማናቸውንም ዓይነት ውል ወይም ግብይት እንዳይፈፅም በዘላቂነት ወይም ለተወሰነ ጊዜ የሚከለክል ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

26.***<u>ዋጋ ያለውን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ መስጠት</u>***

1.ማንኛውም ሰው ተገቢ ምክንያት ሳይኖረው ለማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ወይም ከእርሱ ጋር ግንኙነት ላለው ማንኛውም ሌላ ሰው ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማናቸውንም ዋጋ ያለው ነገር ያቀረበ የሰጠ ወይም ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ፣ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

2.በአገሩ ወይም በአካባቢው ባህል ወይም ልማድ መሰረት እንደተራ የወዳጅነት ምልክት የሚሰጥ ዋጋ ያለው ስጦታ መስጠት ወይም ለስጋ ወይም ለጋብቻ የቅርብ ዘመድ ወይም ለቅርብ ወዳጅ ስጦታ መስጠት በዚህ አንቀጽ ለተመለከተው ወንጀል ማቋቋሚያ አይሆንም።

27. **ማቀባበል**

ማንኛውም ሰው ለራሱ ማናቸውንም ዓይነት ጥቅም ባያገኝም እንኳ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራን ለሚያከናውን ሰው ጉቦ ለመስጠት ገንዘብ፣ ዋጋ ያለው ነገር፣ አገልግሎት ወይም ሌላ ዓይነት ጥቅም ከሌላ ሰው የተቀበለ እንደሆ፤ ወይም የራሱን የባንክ ሂሳብ እንደዚህ ዓይነት ጉቦ ለማቀባበል ያዋለ እንደሆነ፤ ወይም ጉቦ እንዲሰጣጡ ሁኔታዎችን ያመቻቸ፣ ያገናኘ፣ ያስማማ ወይም የደለለ እንደሆነ፤ እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እስራት እና በመቀጮ፣ ወይም ከሦስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከሦስት ሺህ ብር እስከ አሥር ሺህ ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

28. **በሌለው ስልጣን መጠቀም**

ማንኛውም ሰው፡-

1.ከመንግስት ወይም ከህዝባዊ ድርጅት ሥራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ፣ ከተወገደ ወይም ሥልጣኑን ወይም ኃላፊነቱን ከተወ በኋላ በሥራው ላይ ያለ በማስመሰል፤

2.ለወደፊቱ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ እሆናለሁ ብሎ በማሳመን፤ ወይም

3.የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ሳይሆን መስሎ በመቅረብ፤

ይህንን አደርጋለሁ በማለት የተስፋ ቃል በመግባት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ወይም ስጦታ ከሌላ ሰው ላይ የጠየቀ ወይም የተቀበለ እንደሆነ፣ እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እስራት እና በመቀጮ ወይም ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከአሥር ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

29. **<u>በግል ተሰሚነት መነገድ</u>**

1. ማንኛውም ሰው የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ባለመሆኑ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 16 ለመንግስት ወይም ለህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የተደነገገው የማይመለከተው ቢሆንም፣ ያለውን ወይም እንዳለው ያስመስለውን ተሰሚነት በመጠቀም በአንድ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ብቻ ሊሰጥ የሚችለውን ልዩ መብት ወይም ጥቅም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ሲል ከሌላው ሰው ገንዘብ፣ ስጦታ፣ እጅ መንሻ ወይም ሌላ ጥቅም የጠየቀ፣ የተቀበለ ወይም እነዚህን በተመለከተ የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ፣ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት እና ከሦስት ሺህ ብር በማያንስ መቀጮ ይቀጣል፡፡
2. ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው መሰረት በአንድ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ብቻ ሊሰጥ የሚችለውን ልዩ መብት ወይም ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ገንዘብ፣ ስጦታ እጅ መንሻ ወይም ሌላ ጥቅም የሰጠ ወይም ለመስጠት የተስማማ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሰረት ይቀጣል፡፡
3. ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 16(1) ፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ) ወይም (ሐ) የተመለከተውን ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ለማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ስጦታ ወይም ሌላ ጥቅም የሰጠ ወይም ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሰረት ይቀጣል፡፡

30. **<u>በምርጫ ላይ የሚሰጥ መደለያ</u>**

1. ማንኛውም ሰው የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት ያለው ሌላ ሰው በመብቱ በተወሰነ መንገድ እንዲጠቀም ወይም መብቱን እንዲተው ለማድረግ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ገንዘብ ወይም ማናቸውም ሌላ ዓይነት ጥቅም የሰጠ፣ ወይም ለመስጠት ቃል የገባ እንደሆነ፣ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡
2. የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት ያለው ማንኛውም ሰው በዚሁ መብቱ እንዲጠቀምበት ወይም በአንድ በተወሰነ መንገድ እንዲጠቀምበት ወይም ሳይጠቀምበት እንዲቀር ገንዘብ ወይም ማናቸውም ሌላ ዓይነት ጥቅም የተቀበለ ወይም ለመቀበል የተስማማ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው ቅጣት ይቀጣል፡፡

31. **<u>ከባድ የእምነት ማጉደል</u>**

1. ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዋጋ ያለውን ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ያደረገ፣ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ፤ የወሰደ፣ ያስወሰደ፣ የሰወረ፣ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ ወይም ይህን የመሳሰለውን ማናቸውንም አድራጎት የፈጸመ እንደሆነ ከሦስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከአሥር ሺህ ብር እስከ ሃምሳ ሺህ ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።
2. የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት፣ የጥፋተኛው የሥልጣን ወይም የኃላፊነት ደረጃ ወይም በመንግስት፣ በህዝባዊ ድርጅት፣ በህዝብ ወይም በግለሰብ ጥቅም ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተፈጸመውን ወንጀል ከባድ አድርጎት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከሰባት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከሃምሳ ሺህ ብር እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር በሚደርስ መቀጮ ይሆናል፡፡
3. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) አፈጻጸም፡-
   ሀ/ ተከሳሹ በእምነት እንዲሸጥ ወይም እንዲገዛ ወይም እንዲለውጥ ወይም ለተወሰነ አገልግሎት እንዲያውል የተሰጠውን ገንዘብ ወይም ዕቃ ወይም ዋጋ ያለውን ነገር በተባለው መሠረት ፈፅሞ በምትኩ ያገኘው ገንዘብ፣ ወይም ዕቃ ወይም ዋጋ ያለው ነገር የሌላ ሰው እንደሆነ ይቆጠራል፡፡
   ለ/ ተከሳሹ ሲጠየቅ በእምነት ወይም በአደራ የተሰጠውን ገንዘብ ወይም ዕቃ ወይም ዋጋ ያለውን ነገር ለመመለስ ወይም ለመክፈል ወይም ዕቃው ያለበትን ሁኔታ ለማሳየት ወይም ለተገቢው አገልግሎት ያዋለው መሆኑን ለማስረዳት ካልቻለ ንብረቱን ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም የማዋል አሳብ እንዳለው ይቆጠራል።
4. ለዚህ አንቀፅ አፈፃፀም ሲባል "እምነት ማጉደል" ማለት ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ የሌላ ሰው የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ገንዘብ ወይም ዕቃ ወይም ዋጋ ያለውን ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው

የማድረግ የመውሰድ፣ የማስወሰድ፣ የመሰወር፣ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት የማዋል፣ ወይም ይህን የመሳሰለውን ማናቸውም እምነት የማጉደል ወንጀልን ያካትታል።

32. <u>**ከባድ አታላይነት**</u>

1. ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ አሳሳች የሆኑ ነገሮችን በመናገር፣ የራሱን ማንነት ወይም ሁኔታ በመሰወር ወይም መግለፅ የሚገባውን ነገር በመደበቅ ወይም የሌላውን ሰው የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት በመጠቀም፣ በማድረግም ሆነ ባለማድረግ ሌላውን ሰው በማታለል የተታለለው ሰው የራሱን ወይም የሌላውን ሰው የንብረት ጥቅም የሚጎዳ ድርጊት እንዲፈጽም ያደረገው እንደሆነ ከሦስት ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከሦስት ሺህ ብር እስከ ሰላሳ ሺህ ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ወንጀል የተፈጸመው የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት ወይም በመንግስት፣ ወይም በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝብ ጥቅም ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛነት፣ በወንጀል አድራጊው የስልጣን ደረጃ የወንጀሉን አፈጻፀም ከባድ አድርጎት እንደሆነ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት የሚደርስ እስራት እና ከአሥር ሺህ ብር እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡
3. ወንጀሉ የተፈፀመው በሕዝብ አስተዳደር ወይም በሕዝብ አገልግሎት ላይ የሆነ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ ከላይ ከተመለከቱት ንዑስ አንቀዖች በአንዱ መሰረት ያስቀጣል፡፡

33. <u>**በሙስና ወንጀል የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና በወንጀሉ ስለመርዳት**</u>

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወንጀል የተፈፀመው በሙስና ወንጀል አመንጪነት ከሆነ አግባብነት ያለው በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ህግ ተፈፃሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ እንደነገሩ ሁኔታ በዚህ አዋጅ መሰረት የሙስና ወንጀል ክስ ይቀርባል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

34. **ተፈጻሚነት ስላላቸው ሕጎች**

በወንጀል ህጉ የመጀመሪያ ታላቅ ክፍል ከአንቀጽ (1) እስከ አንቀጽ 237 ያሉት ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ ለተመለከቱት የሙስና ወንጀሎችም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

35. **የተሻሩ ድንጋጌዎች**

የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 379፣ አንቀጽ 381፣ ከአንቀጽ 402 እስከ አንቀጽ 419፣ ከአንቀጽ 427 እስከ አንቀጽ 431፣ አንቀጽ 468 እና የአንቀጽ 676(1) በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡፡

36. **ተፈጻሚነት የሌላቸው ህጎች**

የሚከተሉት በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

1. የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 696 ድንጋጌዎች፤
2. ኃላፊነትን አላግባብ መገልገልን፣ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ማግኘትን ወይም ማስገኘትን እና በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት ማድረስን ለመቅጣት የተደነገጉ የወንጀል ሕጉ ድንጋጌዎች፤
3. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች እና የአሠራር ልማዶች፡፡

37. **የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

የዚህ አዋጅ አንቀጽ 35 እና 36 ድንጋጌዎች ቢኖሩም ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተፈጸሙ የሙስና ወንጀሎች የሚታዩት በወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች መሠረት ይሆናል፡፡

38. **አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት 25 ቀን 2007 ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ 909/2007

## ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ

ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር በተለይም የሴቶችና ሕጻናት ዝውውር እና ስደቶኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀል ከጊዜ ወደ ጊዜ ሥር እየሰደደ እና እየተባባሰ ዜጎችን ለአስከፊ የሰብዓዊ መብት ጥሰት እና እንግልት እየዳረገ በመሆኑ፣ ችግሩን ለመፍታት በኢኮኖሚና ማህበራዊ ዘርፍ ከሚደረገው ጥረት በተጨማሪ የሕግ ማዕቀፉ በመከላከል ላይ የተመሠረተ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የወንጀሉ ተጎጂ ለሆኑ ሰዎች ጥበቃ፣ እንክብካቤ እና መልሶ ማቋቋም ሊደረግላቸው እንደሚገባ በመገንዘብ እና ለችግሩ ይበልጥ ተጋላጭ ለሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች ዕድሜያቸውን፣ ጾታቸውንና ልዩ ፍላጎታቸውን ያገናዘበ የተለየ ጥበቃ፣ እንክብካቤ እና ድጋፍ ሊደረግላቸው እንደሚገባ በማመን፤

በወንጀል ሕጉም ሆነ በሌሎች ሕጎች የተቀመጡ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ከችግሩ ስፋት አንፃር በቂ ምላሽ የማይሰጡ በመሆናቸው እና በወንጀለኞች ላይ ለጥፋታቸው ተመጣጣኝ የሆነ ቅጣት ለመጣል የሚያስችል ሕግ ማውጣት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 18 (2) በተደነገገው መሠረት በሰዎች መነገድ የተከለከለ በመሆኑ፣ ኢትዮጵያ የተደራጁ ድንበር ዘለል ወንጀሎችን ለመከላከል የተደረሰውን ዓለም አቀፍ ስምምነት ፈራሚ አገር በመሆኗ፣ ስምምነቱን ተከትለው በወጡት ሕገ-ወጥ የሰዎች በተለይም የሴቶችና ሕጻናት ዝውውር ለመከላከል ለመቆጣጠርና ወንጀል ፈጻሚዎችን ለመቅጣት በወጣው ፕሮቶኮል እና ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ በየብስ፣ በባህርና በአየር ማስወጣትና ማስገባት ለመከላከል የወጣ ፕሮቶኮልን ያጸደቀች በመሆኗ፣ እንዲሁም ከሕገ መንግስቱ እና ከእነዚህ ዓለም አቀፍ ሰነዶች ጋር የተጣጣመና የተሟላ ሕግ ማውጣት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 55 (1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 909/2007" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "ሕገ-ወጥ ሰው አዘዋዋሪ" ወይም "ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር አሻጋሪ" ማለት፦
   - ሀ/ በማንኛውም መንገድ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ፣ ሕግን በመጣስ ወይም በራሱ ፈቃድ ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል የፈፀመ ወይም ለመፈፀም የሞከረ፤
   - ለ/ በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር የወንጀል ድርጊት ላይ በአባሪነት የተሳተፈ፤
   - ሐ/ ሌሎች ሰዎች በወንጀል ድርጊቱ እንዲሳተፉ ያደራጀ ወይም በተደራጀ የወንጀል ቡድን ውስጥ አመራር የሰጠ፤
   - መ/ ሰዎችን ከመኖሪያ አካባቢያቸው ጀምሮ የተስፋ ቃል በመስጠት ለወንጀል ድርጊቱ ወይም ለስደተኝነት የዳረገ፤
   - ሠ/ በማንኛውም መልኩ የወንጀል ድርጊቱን ያበረታታ፣ የወንጀል ድርጊቱ እንዲስፋፋ ያደረገ ወይም የተደራጀው የወንጀል ቡድን በዚህ አዋጅ የተደነገጉ ወንጀሎችን ለመፈፀም ማሰቡን እያወቀ ለጋራ ዓላማ በቡድን ለተሰባሰቡ ሰዎች አስተዋፅዖ ያደረገ፤

   በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በሌላ አገር የሚገኝ ማንኛውም ሰው ነው።
2. "የተደራጀ የወንጀል ቡድን" ማለት በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በሌላ አገር የሚገኝወይም የሚንቀሳቀስ ሆኖ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የገንዘብ ወይም ሌላ ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት ዓላማ አንድ ወይም ከዚያ በላይ በዚህ አዋጅ የተደነገጉ ወንጀሎችን ለመፈፀም የተሰባሰቡና የሚንቀሳቀሱ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎችን የያዘና ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ የሚቆይ የተደራጀ ቡድን ሲሆን

በማናቸውም መልኩ በሰዎች ለመነገድ የተቋቋመ ቡድንን ወይም ማህበርን ይጨምራል፤

3. “ድንበር ተሻጋሪ የወንጀል ድርጊት” ማለት በዚህ አዋጅ የተደነገገው ወንጀል፦

ሀ/ ከአንድ በላይ በሆኑ አገራት የተፈጸመ፤

ለ/ በኢትዮጵያ የግዛት ክልል ውስጥ የተፈጸመ ሆኖ የድርጊቱ ዝግጅት፣ እቅድ፣ አመራር ወይም የገንዘብ ምንጭ በሌላ አገር የሆነ፤

ሐ/ የተፈጸመው በሌላ አገር ሆኖ የድርጊቱ ዝግጅት፣ እቅድ፣ አመራር ወይም የገንዘብ ምንጭ በኢትዮጵያ ከሆነ ወይም በሌላኛው አገር የግዛት ክልል አማካይነት የሆነ፤

መ/ የተፈፀመው ከአንድ በላይ በሆኑ አገራት በሚንቀሳቀስ የተደራጀ የወንጀል ቡድን የሆነ፤ ወይም

ሠ/ በኢትዮጵያ የግዛት ክልል ውስጥ ወይም በሌላ አገር የተፈፀመ ቢሆንም የወንጀሉ ውጤት በሌላ አገር ወይም በኢትዮጵያ ላይ የሆነ፤

ድርጊት ነው።

4. “ብዝበዛ” ማለት የሚከተሉትን ያካትታል፦

ሀ/ በሌሎች ሰዎች ዝሙት አዳሪነት መጠቀም ወይም ሌላ ማንኛውም አይነት ወሲባዊ ብዝበዛን፤

ለ/ የጉልበት ብዝበዛ፣ የግዳጅ ሥራ ወይም አገልጋይነት፤

ሐ/ ባርነት ወይም ባርነት መሰል ተግባር፤

መ/ የወሲብ አገልጋይነትን ጨምሮ ሰውን የማይገባ አገልጋይ ማድረግ፤

ሠ/ በመያዣነት መያዝ ወይም አሳልፎ ለሌላ መስጠት፤

ረ/ የሰው ልጅን አካል ማውጣት ወይም መውሰድ፤

ሰ/ አስገድዶ በልመና ተግባር ማሰማራት፤ ወይም

ሸ/ ህፃናትን ለወታደራዊ አገልግሎት ማሰማራት።

5. “ባርነት” ማለት የሌላ ሰው የባለቤትነት መብት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል እየተፈጸመበት ያለ ሰው የሚገኝበት ሁኔታ ወይም አቋም ነው፤

6. “ሰውን በማይገባ አገልጋይ ማድረግ” ማለት አንድ ሰው ሊያስቀረው፣ ሊከላከለው ወይም ሊቀይረው በማይችልበት ሁኔታ አገልግሎት እንዲሰጥ ወይም ሥራ እንዲሰራ ማድረግ ወይም ማስገደድ ነው፤

7. “የዕዳ መያዣ ማድረግ” ማለት በሌላ ሦስተኛ ወገን አስቀድሞ በማናቸውም ሁኔታ ግዴታ ለተገባ ወይም ለተጠየቀ ዕዳ የራስን ወይም ኃላፊ የሆነውን ሰው አገልግሎት በመያዣ ከማቅረብ የሚመነጭ ሆኖ የሚሰጠው አገልግሎት ዓይነትና የጊዜ መጠን ባልተወሰነበት ሁኔታ የሚከሰት ማንኛውንም ዓይነት በሰው ልጅ የመነገድ ተግባርን ታሳቢ የሚያደርግ የመያዣነት ተግባር ነው፤
8. “በሕገ ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር” ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የገንዘብ ወይም ሌላ ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ሰዎችን ዜግነት ወደሌላቸው ወይም የመኖሪያ ፈቃድ ወዳላገኙበት አገር በሕገ-ወጥ መንገድ በየብስ፣ በባህር ወይም በአየር ማስገባት ወይም እንዲወጡ ማድረግ ነው፤
9. “ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን” ማለት እንደ አግባብነቱ የኢትዮጵያ መንግስት በውጭ ሃገራት ያቋቋማቸው ኤምባሲዎች፣ ቋሚ መልዕክተኛ ጽሕፈት ቤት፣ ቆንሲላ ጽሕፈት ቤቶች እና የክብር ቆንሲላዎች ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የውጭ አገር ኤምባሲዎች እና ቆንሲላ ጽሕፈት ቤቶች ማለት ነው፤
10. “ስደተኛ” ማለት በስደተኞች ጉዳይ አዋጅ የተመለከቱ መስፈርቶችን የሚያሟላ ሰው ነው፤
11. “ተጎጂ” ማለት በዚህ አዋጅ የተደነገጉ የወንጀል ድርጊቶች የተፈፀሙበት ሰው ወይም የወንጀል ድርጊቱ በመፈፀሙ ጉዳት የደረሰበት ሰው ሲሆን ማንኛውንም የሥነ-ልቦና፣ ሞራላዊ፣ አካላዊ ወይም የኢኮኖሚ ጉዳት ወይም ሌላ መሠረታዊ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት የደረሰበት ሰው ነው፤
12. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ 47 (1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል የአዲስ አበባንና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደርን ይጨምራል፤
13. “ሕጻን” ማለት ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ማንኛውም ሰው ነው፤
14. “ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር” ማለት እንደቅደም ተከተሉ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፍትህ ሚኒስቴር ወይም የፍትህ ሚኒስትር ነው[52]፤

[52] በ22/63(2008)አ.943 መሰረት የፌዴራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ የሆነ ሲሆን በዚህም መሰረት በአዋጁ ውስጥ “የፍትህ ሚኒስቴር” እና “የፍትህ ሚኒስትር” የሚሉት “የፌዴራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ” እና “ጠቅላይ አቃቤ ህግ” በሚል ይነበባሉ።

15.“ፖሊስ” ማለት የፌዴራል ፖሊስ ወይም በዚህ አዋጅ ለተመለከቱ ጉዳዮች የፌዴራል ፖሊስ ሥልጣን በውክልና የተሰጠው የክልል ፖሊስ ነው፤

16.“ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

17.ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀሎች

### 3. ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር

1. ማንኛውም ሰው በኢትዮጵያ የግዛት ክልል ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ የግዛት ክልል ውጪ ለብዝበዛ ዓላማ ሲባል፦

   ሀ/ በአገር ውስጥ ሥራና ሠራተኛን ለማገናኘት ወይም ለሥራ ወይም ለሥራ ልምምድ ወደ ውጭ አገር መላክ በሚል ሽፋን፤

   ለ/ የጉዲፈቻ ስምምነት በማድረግ ወይም በጉዲፈቻ ሽፋን፤ ወይም

   ሐ/ ለሌላ ማንኛውም አይነት ዓላማ፤

   ዛቻን፣ ሀይልን ወይም ሌላ የማስገደጃ ዘዴ በመጠቀም፣ በማገት፣ በመጥለፍ፣ በተንኮል፣ በማታለል ወይም የተስፋ ቃል በመስጠት፣ ሥልጣንን አላግባብ በመጠቀም፣ የሰዎችን ለጥቃት ተጋላጭነት በመጠቀም ወይም ስለሌላው ኃላፊነት ያለበትን ሰው ፈቃድ ለማግኘት መደለያ ወይም ጥቅም በመስጠት ወይም በመቀበል ሰዎችን የመለመለ፣ ያጓጓዘ፣ ያዘዋወረ፣ ያስጠለለ ወይም የተቀበለ እንደሆነ ከ15 ዓመት እስከ 25 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራትና ከብር 150,000 እስከ ብር 300,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የወንጀል ድርጊት የተፈፀመው፦

   ሀ/ በሕጻናት፣ በሴቶች ወይም በአዕምሮ ወይም በአካል ጉዳተኞች ላይ ከሆነ፤

   ለ/ ተጎጂው ለአካላዊ ወይም አዕምሯዊ ጉዳት ከተዳረገ፤

   ሐ/ አደንዛዥ ዕፅ፣ መድሃኒት ወይም የጦር መሣሪያ በመጠቀም እንደሆነ፤

   መ/ በመንግስት ባለሥልጣን ወይም ሠራተኛ ከሆነና ወንጀሉን የፈጸመው የተሰጠውን ኃላፊነት መከታ በማድረግ ከሆነ፤ ወይም

   ሠ/ በተጎጂው ወላጅ፣ ወንድም፣ እህት፣ አሳዳጊ ወይም በተጎጂው ላይ ሥልጣን ባለው ሰው የሆነ እንደሆነ፤

ከብር 200,000 እስከ ብር 500,000 በሚደርስ መቀጮ እና ከ25 ዓመት በማያንስ ፅኑ እስራት ወይም እድሜ ልክ እስራት ይሆናል፡፡

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ላይ የተጠቀሱት ልዩ ልዩ መንገዶች በጥቅም ላይ ባይውሉም፣ ህጻናትን ለብዝበዛ አላማ መመልመል፣ ማጓጓዝ፣ ማዘዋወር፣ ማስጠለል ወይም መቀበል ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ነው፡፡

4. <u>ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውርን መደገፍና ማመቻቸት</u>

ማንኛውም ሰው ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውርን፡-

1. እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው የራሱንም ሆነ በይዞታው ሥር ያለን ቤት፣ ሕንጻ ወይም ግቢ ለሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ዓላማ ያከራየ፣ እንዲጠቀሙበት የፈቀደ፤
2. ለማስፋፋት የተለያዩ የህትመት ውጤቶችን ያባዛ፣ ያጠራቀመ፣ ያሰራጨ፣ ወደ አገር ውስጥ ያስገባ ወይም ወደ ውጪ ያስወጣ፤
3. ለማበረታታት በማሰብ የሥራ ቅጥር ተቋም በማደራጀት ያስተዳደረ፣ የመራ ወይም በገንዘብ የደገፈ፤
4. እያወቀ የትራንስፖርት አገልግሎት ያመቻቸ ወይም ተጎጂዎችን በአየር፣ በምድር ወይም በባህር ያጓጓዘ ወይም አገልግሎቱን ያመቻቸ፤
5. ለማመቻቸት ሌላውን ሰው የተጭበረበረ፣ ሀሰተኛ ወይም በሕገ-ወጥ መንገድ መታወቂያ ወይም የጉዞ ሰነድ እንዲያገኝ የረዳ፣ እንዲዘጋጅ ያደረገ፣ ያቀረበ፣ ይዞ የተገኘ ወይም እነዚህን ሰነዶች ወደ ሀሰት የለወጠ፤ ወይም
6. ለማመቻቸት የሌላውን ሰው የመንቀሳቀስ ነፃነቱን እንዳይጠቀም ወይም ሕዝባዊ አገልግሎቶች እንዳያገኝ ለማድረግ የተጎጂዎችን መታወቂያ ወይም የጉዞ ሰነድ መያዣ ያደረገ፣ በኃይል የነጠቀ፣ የሰወረ፣ ያጠፋ ወይም እንዲጠፋ ያደረገ፤
7. እንደሆነ ከ15 ዓመት እስከ 25 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር 150,000 እስከ ብር 300,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

5. <u>ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀል</u>

1. ማንኛውም ሰው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የገንዘብ፣ ቁሳዊ ወይም ሌላ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ለማስገባትም ሆነ ከኢትዮጵያ ግዛት ለማስወጣት ሲል ድንበር ካሻገረ፣ ድንበር ለማሻገር ከሞከረ ወይም ድንበር ለማሻገር በዝግጅት ላይ ከሆነ ከ15 እስከ 20

ዓመት የሚደርስ ፅኑ እስራትና ከብር 150,000 እስከ ብር 300,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው የወንጀል ድርጊት የተፈጸመው፦
   ሀ/ በሕጻናት፣ በሴቶች ወይም በአዕምሮ ወይም በአካል ጉዳተኞች ላይ ከሆነ፤
   ለ/ ተጎጂውን ለአካላዊ ወይም አዕምሯዊ ጉዳት ከተዳረገ፤
   ሐ/ አደንዛዥ ዕፅ፣ መድሃኒት ወይም የጦር መሣሪያ በመጠቀም ከሆነ፤
   መ/ ከዚህ ቀደም ተመሳሳይ የወንጀል ጥፋተኛነት ሪከርድ ባለበት ሰው እንደሆነ፤ ወይም
   ሠ/ በመንግስት ባለሥልጣን ወይም ሠራተኛ ከሆነ እና ወንጀሉን የፈጸመው የተሰጠውን ኃላፊነት መከታ በማድረግ ከሆነ፤

   በቅጣቱ ከ20 ዓመት ያላነሰ ፅኑ እስራት እና ከብር 300,000 እስከ ብር 500,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

6. <u>ከባድ ሁኔታ</u>

   በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 3 ወይም 5 የተመለከተው የወንጀል ድርጊት በተጎጂው ላይ ከፍተኛ የአካል ጉዳት ወይም ሞት ያስከተለ እንደሆነ ወይም ወንጀል አድራጊው ድርጊቱን የፈፀመው የተደራጀ የወንጀል ቡድን አባል በመሆን ወይም ቡድኑን በመምራት ወይም በማስተባበር እንደሆነ ወይም ወንጀሉ የተፈጸመው በስፋትና በብዛት እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ ቅጣቱ የእድሜ ልክ ፅኑ እስራት ወይም ሞት ይሆናል፡፡

7. <u>መታወቂያ ወረቀትና የጉዞ ሰነዶችን የሚመለከት ወንጀል</u>

   ማንኛውም ሰው ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር በማሻገር ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ለማስገባት ወይም ከኢትዮጵያ ግዛት ለማስወጣት የተጭበረበረ ወይም ሐሰተኛ መታወቂያ ካርድና የጉዞ ሰነዶችን ካዘጋጀ፣ ይዞ ከተገኘ፣ ካቀረበ ወይም ካስተላለፈ ከ10 ዓመት በማያንስ እና ከ20 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራትና ከብር 100,000 እስከ ብር 200,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

8. <u>ሕገ-ወጥ ስደተኛ ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ ወይም በአገር ውስጥ እንዲቆይ ድጋፍ ስለመስጠት</u>

   በሌላ ሕግ የተደነገገው ቢኖርም የውጭ አገር ዜጋ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ እንዲቆይ ወይም እንዲኖር ለማድረግ የመኖሪያ ፈቃድ፣ መታወቂያ ካርድና ሌሎች የጉዞ ሰነዶች የሚያስፈልግ መሆኑን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው ሕገ-ወጥ ስደተኛ ወደ ኢትዮጵያ

ግዛት እንዲሻገር ድጋፍ የሰጠ ወይም በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የተሻገረ ስደተኛ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ እንዲኖር ወይም እንዲቆይ የረዳ ማንኛውም ሰው ከ3 ዓመት እስከ 5 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

9. **በሕገ-ወጥ መንገድ በአንድ አገር ውስጥ እንዲቆይ መተባበር**

ማንኛውም ሰው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የገንዘብ ወይም ሌላ ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ፦

1. ሕግን በመጣስ ዜግነት ወይም የመኖሪያ ፈቃድ የሌለውን የውጭ አገር ሰው በሕጋዊ መንገድ ለመኖር የሚያስፈልጉትን መስፈርቶች ሳያሟላ በኢትዮጵያ ውስጥ ወይም ኢትዮጵያዊ የሆነን ሰው በሌላ አገር እንዲቆይ የተባበረ፤
2. ሕግን በመጣስ ሌላን ሰው ወደ ኢትዮጵያ ወይም ወደ ሌላ አገር እንዲገባ ወይም ድንበር አቋርጦ እንዲሻገር ያመቻቸ፤ ወይም
3. አድራጎቱ ሰዎችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ለማሻገር መጠቀሚያ ሊሆን እንደሚችል እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው ወይም ሊያውቅ የሚችልበት መንገድ እያለ ሐሰተኛ መታወቂያ ካርድ ወይም የጉዞ ሰነድ ለመስጠት የተስማማ፣ የሰጠ፣ ያስተላለፈ፤
4. እንደሆነ ከ10 ዓመት እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር 100,000 እስከ ብር 500,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

10. **ማስረጃን ስለማጥፋት ወይም ምስክርነት እንዳይሰጥ ስለማድረግ**

ማንኛውም ሰው በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል የምርመራ፣ የክስ ወይም በፍርድ ሂደት ወቅት ጥቆማ ያቀረበን፣ መረጃ የሰጠን፣ ምስክር የሆነን ወይም ምስክር ሊሆን የሚችል ሰውን እንዳይመሰክር፣ የሀሰት ምስክርነት እንዲሰጥ ወይም ማስረጃ እንዲደብቅ በማናቸውም መልኩ ያስፈራራ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ መደለያ የሰጠ ወይም ራሱ ማስረጃን ያጠፋ ወይም የደበቀ እንደሆነ ከ10 ዓመት እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

11. **ወንጀልን እና በወንጀል ተጠርጣሪን ስለመደበቅ**

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ የተደነገጉ ወንጀሎችን የፈፀመን ሰው የደበቀ፣ ወንጀል የተፈፀመበትን ወይም ሊሰራ የታቀደበትን ማንኛውንም ዓይነት ንብረት የሸሸገ ወይም ለወንጀሉ ማስፈፀሚያ የሆነውን ገንዘብ ምንጭ ወይም ከወንጀል ድርጊቱ የተገኘ

ማንኛውንም ገንዘብ እንዳይታወቅ ሆነ ብሎ የደበቀ ወይም ምንጩንም ሆነ ገንዘቡ ከወንጀል ድርጊት የተገኘ መሆኑን ማወቅ ሲገባው በማናቸውም መልኩ እንዳይታወቅ ያደረገ ወይም ሳያሳውቅ የቀረ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ ከ5 ዓመት እስከ 10 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

12.<u>የወንጀል ድርጊቶችን አለማስታወቅ</u>

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ የተመለከተ ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር የወንጀል ድርጊት፦

1. ሊፈፀም የመሰናዳት ተግባር መከናወኑን እያወቀ እና ጉዳት ከመድረሱ በፊት ለመከላከል የሚረዳ ማንኛውም ማስረጃ እያለው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ወይም አሳማኝ በሆነ ምክንያት ለማስታወቅ አለመቻሉን ካላስረዳ በስተቀር ያለበቂ ምክንያት መረጃውን ወይም ማስረጃውን ለፖሊስ ወይም ለሌላ አግባብነት ያለው አካል ወዲያውኑ ያልገለፀ ወይም ሐሰተኛ ማስረጃ የሰጠ እንደሆነ በቀላል እስራት ይቀጣል፣ ወይም ይህ የወንጀል ድርጊት ሊያስከትል ይችል የነበረው አደጋ ከፍ ያለ እንደሆነ እስከ 5 አመት የሚደርስ ፅኑ እስራት ያስቀጣል፤
2. በወንጀል ድርጊቱ የተጠረጠረን ወይም ሊፈጽም የተዘጋጀን ሰው ለመያዝ፣ ለመክሰስ ወይም ለማስቀጣት የሚያስችል መረጃ ወይም ማስረጃ እያለው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ወይም አሳማኝ በሆነ ምክንያት ለማስታወቅ አለመቻሉን ካላስረዳ በስተቀር ያለበቂ ምክንያት መረጃውን ወይም ማስረጃውን ለፖሊስ ወይም ለሌላ አግባብነት ያለው አካል ወዲያውኑ ያልገለፀ ወይም ሐሰተኛ ማስረጃ የሰጠ እንደሆነ ከ5 ዓመት የማያንስና ከ10 ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከብር 10,000 እስከ ብር 50,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

13.<u>የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የወንጀል ተጠያቂነት</u>

1. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 90(1)፣ (3) እና (4) ላይ የተደነገገው ቢኖርም በዚህ ክፍል የተደነገገ ወንጀል የተፈፀመው የሕግ ሰውነት በተሰጠው ድርጅት ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ተሳትፎ ከሆነ፣ ድርጊቱ የተፈፀመው ከተደራጀ የወንጀል ቡድን ጋር በመተባበር ከሆነ ወይም በሰዎች ለመነገድ ወይም በሕገ-ወጥ መንገድ ለማዘዋወር በተቋቋመ ድርጅት ወይም ማህበር ከሆነ፦

ሀ/ ለወንጀሉ የተጣለው ቅጣት መቀጮ ከሆነ መቀጮው ከብር 1 ሚሊዮን እስከ ብር 5 ሚሊዮን ይሆናል፣

ለ/ ለወንጀሉ የተጣለው ቅጣት የእስራት ቅጣት ከሆነ የቅጣቱ መጠን፦

1) እስከ 5 ዓመት ፅኑ እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል እስከ ብር 500,000፣
2) እስከ 10 ዓመት ፅኑ እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል ከብር 500,000 እስከ ብር 1 ሚሊዮን፣
3) እስከ 15 ዓመት ለሚያስቀጣ ወንጀል ከብር 1 ሚሊዮን እስከ ብር 1 ሚሊዮን 500,000፣

እስከ 25 ዓመት ፅኑ እስራት እና ከዚያ በላይ ለሚያስቀጣ ወንጀል ከብር 2 ሚሊዮን 500,000 ያላነሰ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እስከተመለከተው ከፍተኛው ወሰን ለመድረስ በሚችል፣

መቀጮ ይቀጣል፡፡

ሐ/ በዚህ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) ከተደነገገው ቅጣት በተጨማሪ ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ፈርሶ የድርጅቱ ወይም የማህበሩ ማንኛውም ንብረት ወይም ሐብት ይወረሳል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቅጣት የድርጅቱን ወይም የማህበሩን ባለቤት፣ ሥራ አስኪያጅ ወይም በድርጅቱ ስም ወይም ለድርጅቱ ጥቅም ለማስገኘት በማሰብ በድርጊቱ የተሳተፈውን የድርጅቱን ወይም የማህበሩን ሠራተኛ የወንጀል ተጠያቂነት አያስቀረውም፡፡

3. የግል ሥራና ሠራተኛ አገኛኝ ኤጀንሲ በሥራና ሠራተኛ ማገናኘት አገልግሎት ሥራ ላይ ተሰማርቶ እያለ ፈቃዱ በታገደበት ወይም በተሰረዘበት ወቅት ማንኛውንም ኢትዮጵያዊ ለሥራ ወደ ውጭ አገር የላከ እንደሆነ ወይም ሕጋዊ ፈቃድ እያለው በሌላ ማናቸውም ሁኔታ በዚህ አዋጅ የተደነገጉ የወንጀል ድርጊቶችን የፈፀመ ወይም ለወንጀሉ መፈፀም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ማንኛውንም ዓይነት ድጋፍ ያደረገ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገጉትን ቅጣቶች ይቀጣል፡፡

14.<u>የተጎጂ ፈቃድ</u>

1. ማንኛውም ተጎጂ ብዝበዛ የሚፈፀምበት መሆኑን እያወቀ ፈቃደኝነቱን ቢገልጽም ፈቃደኝነቱ የተገኘው በዛቻ፣ በኃይል፣ በሌላ የማስገደጃ ዘዴ በመጠቀም፣ በመጥለፍ፣ በተንኮል፣ በማታለል፣ ሥልጣንን አላግባብ በመጠቀም፣ የሰዎችን ለጥቃት ተጋላጭነት በመጠቀም ወይም ስለሌላው ኃላፊነት ያለበትን ሰው ፈቃድ ለማግኘት መደለያ ወይም ጥቅም በመስጠት ወይም በመቀበል ከሆነ ሕገ-ወጥ ሰው አዘዋዋሪን ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር አሻጋሪን የወንጀል ተጠያቂነት አያስቀረውም፡፡
2. ለሕፃናት ሕገ-ወጥ ዝውውር ወይም ሕፃናት ስደተኞን ከኢትዮጵያ ግዛት ለማስወጣትም ሆነ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ለማስገባት ማንኛውም ሕፃን ወይም የሕፃኑ አሳዳሪ ሕፃኑን በተመለከተ በማንኛውም ሁኔታ ፈቃደኝነቱን የገለፀ ቢሆንም ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>
## <u>የመከላከል፣ የምርመራና ክስ፣ የማስረጃና የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች</u>

15.<u>ጠቅላላ</u>

1. ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል የመከላከል፣ የምርመራ፣ ክስ፣ የፍርድ ሂደትና የማስረጃ አሰባሰብ በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሠረት ይከናወናል።
2. የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ አዋጅ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ የወንጀል ሕግ ጠቅላላ ክፍሎች፣ የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎች ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ በተደነገጉ ወንጀሎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

16.<u>ሪፖርት የማድረግ ግዴታ</u>

1. በዚህ አዋጅ ሥር የተመለከቱት ወንጀሎች መፈፀማቸውን ወይም ሊፈፀሙ መሆኑን የሚያውቅ ማንኛውም ሰው፣ የወንጀል ድርጊቱን ለፖሊስ፣ ሌላ አግባብነት ላለው ባለሥልጣን ወይም በአካባቢው ለሚገኝ የአስተዳደር አካል የማሳወቅ እና ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ተገቢውን እርምጃ የመውሰድ ግዴታ ይኖርበታል፡፡
2. ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ በተመለከተ የወንጀል ድርጊት ምክንያት ወይም በሌላ ማንኛውም ሽፋን በዚህ አዋጅ ለተመለከተ የወንጀል ድርጊት ዓላማ የቤተሰብ አባሉ

የሆነ ሰው ከመደበኛው የመኖሪያ አካባቢው የጠፋ መሆኑን ያወቀ ከሆነ ይህንኑ ወዲያዉኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 17.ለአደጋ የተጋለጡ ሰዎችን ስለመጠበቅ

1. ፖሊስ በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀል የተፈጸመ፣ እየተፈፀመ ወይም ሊፈፀም የተቃረበ ለመሆኑ በቂ ጥርጣሬ ሲኖረው ተጎጂዎችን ለማዳን፦
   - ሀ/ ማንኛውንም ቤት፣ ተሽከርካሪ፣ መርከብ ወይም የመጓጓዣ አውሮፕላን በመፈተሽ ተገቢውን እርምጃ ሊወሰድ፤
   - ለ/ በማንኛውም የአገሪቱ ክፍሎች ወይም ድንበር አካባቢዎች ተገቢውን ፍተሻ በማድረግ ተጎጅዎች እየተዘዋወሩ ወይም ድንበር እያቋረጡ ከሆነ በማዳን ተገቢው እንክብካቤና ድጋፍ ወደሚያገኙበት ቦታ ሊያጓጉዝ፤
   - ሐ/ በከፍተኛ የህመም ስቃይ ውስጥ የሚገኙ ተጎጂዎች ባጋጠሙ ጊዜ በማናቸውም መንግስታዊም ሆነ መንግሥታዊ ያልሆነ የህክምና ተቋም ውስጥ እርዳታ እንዲደረግላቸው ተገቢውን ትዕዛዝ ሊሰጥ፤

   ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ፖሊስ የሚወስደውን እርምጃ ወይም የሚሰጠውን ትዕዛዝ ማንኛውም ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው ማክበርና ማስፈፀም አለበት፡፡

## 18.ልዩ የምርመራ ዘዴዎችን ስለመጠቀም

1. ፖሊስ በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል የተፈጸመ፣ እየተፈፀመ ወይም ሊፈፀም የተቃረበ ስለመሆኑ ለማመን የሚያስችል በቂ ጥርጣሬ ካለው፦
   - ሀ/ በወንጀሉ የተጠረጠሩ ሰዎች፣ ቡድኖች ወይም ድርጅቶች ውስጥ ሰርጎ በመግባት፤
   - ለ/ በተጠርጣሪዎች ላይ በድብቅ ክትትል ሊያደርግ፤
   - ሐ/ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሠረት የተጠርጣሪዎችን የግል የመገናኛ ዘዴዎችን ሊጠልፍ፤
   - መ/ የህጋዊ ይምሰል ግንኙነት ሊፈጥር፤ ወይም

ሠ/ ሰብአዊ መብትን ባከበረ ሁኔታ ሌላ ተገቢነት ያለው የልዩ የምርመራ ዘዴ በመጠቀም፣

ስለወንጀሉ አፈፃፀም የሚያሳዩ ማስረጃዎችን ለማሰባሰብ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ሐ) የተደነገገው ቢኖርም አስቸኳይ ሁኔታ ካጋጠመ እና ወንጀሉን በተመለከተ በሌላ መንገድ ማስረጃ ማግኘት የማይቻል መሆኑ ከታመነ ሚኒስትሩ በሚሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ፖሊስ የተጠርጣሪን የግል የመገናኛ ዘዴዎች ሊጠልፍ ይችላል፣ ሆኖም ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ የግል የመገናኛ ዘዴዎችን የመጥለፍ ተግባር እንዲፈፀም መነሻ የሆኑ ማስረጃዎችና ምክንያቶች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት በ72 ሰዓት ውስጥ በፅሁፍ መቅረብና መጽደቅ አለባቸው፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ሀ) መሠረት በሰርጎ መግባት ተግባር ላይ የተሰማራ መርማሪ ወይም በፖሊስ የተመደበ ሰርጎ ገብ በተጎጂዎች ላይ የሰው መግደል ወንጀል ወይም የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ካልፈፀመ በስተቀር ከሰርጎ መግባት ተግባሩ ጋር በተያያዘ ለሚፈፅማቸው የወንጀል ድርጊቶች ከወንጀል ተጠያቂነት ነፃ ይሆናል፣ መርማሪ ወይም በፖሊስ የተመደበ ሰርጎ ገብ የሰርጎ መግባት ተግባሩን ከመፈፀሙ በፊት ከክስ ነፃ ስለሚሆንባቸው የወንጀል ጉዳዮች ያለመከሰስ ስምምነት ከሚኒስቴሩ ጋር መፈራረም አለበት፡፡

4. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) አፈፃጸም ሲባል ሚኒስቴሩ መመሪያ ያወጣል፡፡

19. <u>ልዩ መብትን በምክንያትነት መጠቀም ስለመከልከሉ</u>

1. ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ጥቆማ፣ መረጃ ወይም ማስረጃ የማቅረብ ግዴታን ላለመወጣት ሲል ልዩ መብትን በምክንያትነት መጠቀም አይቻልም፣ ግዴታውን ባለመወጣቱ ምክንያት እንደነገሩ ሁኔታ በዚህ አዋጅ ወይም በሌላ አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ቢኖርም ልዩ መብት ያላቸው ሰዎች ሊከሰሱ የሚችሉት ያለመከሰስ መብታቸው በህግ አግባብ ከተነሳ በኋላ ነው::

20. <u>ስለመያዝና በእስር ስለማቆየት</u>

በሌሎች ሕጎች የተደነገጉት ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው፡-

1. በዚህ አዋጅ የተመለከቱት በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል የተፈጸመ፣ እየተፈፀመ ወይም ሊፈፀም የተቃረበ

ስለመሆኑ ለማመን የሚያስችል በቂ ጥርጣሬ ሲኖር በወንጀል ሕግ ሥነ-ሥርዓት በተደነገገው መሠረት ፖሊስ ተጠርጣሪዎችን ሊይዝ ይችላል፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተያዘ ሰው ምርመራ ያልተጠናቀቀ እንደሆነ በወንጀል ሕግ ሥነ-ሥርዓት በተደነገገው መሠረት ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ በፍርድ ቤት ሊሰጥ ይችላል፣ ሆኖም በጠቅላላ የሚሰጠው ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ከአራት ወራት መብለጥ የለበትም፡፡

21.<u>የማስረዳት ሸክም</u>

1. በዚህ አዋጅ የተደነገጉ የወንጀል ድንጋጌዎች ተጥሰው ፍርድ ቤት የቀረበ የወንጀል ክስን ማስረጃ አቅርቦ የማስረዳት ኃላፊነት የዐቃቤ ሕግ ነው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3፣ 4፣ 5፣ 6፣ 10 እና 11 የተደነገጉ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ለሚቀርብ ክስ ዐቃቤ ሕግ መሠረታዊ ፍሬ ነገሮችን ካስረዳ ፍርድ ቤቱ እንደነገሩ ሁኔታ በጉዳዩ ላይ የማስረዳት ሸክም ወደ ተከሳሹ እንዲዞር ሊያደርግ ይችላል፡፡

22.<u>በቅን ልቦና ስለሚደረግ ግንኙነት</u>

1. በቅን ልቦና በተመሠረተ የውል ወይም በሌላ በማንኛውም መልኩ በተመሠረተ ሕጋዊ ግንኙነት ለሌላ ሦስተኛ ወገን በተላለፈ ማንኛውም ዓይነት ንብረት፣ ገንዘብ ወይም ቁስ በዚህ አዋጅ የተደነገጉ ወንጀሎችን ለመፈፀም ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነ ሊወረስ አይችልም፡፡
2. ማንኛውም ንብረቱን በሚመለከት በቅን ልቦና ያከራየ ወይም የውል ግንኙነት የፈፀመ ሰው በውሉ ግንኙነት ምክንያት ስለሚመጡ ማናቸውም ኃላፊነቶች ለማወቅ ይችል ዘንድ ተገቢውን መፈፀም አለበት፡፡

23.<u>አባሪ ተጠርጣሪን ከክስ ነፃ ስለማድረግ ወይም ቅጣትን ስለመቀነስ</u>

1. በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀል ተካፋይ የነበረ ተጠርጣሪ የወንጀል ጉዳዩ ፍርድ ቤት መቅረቡ በፊት ስለተፈፀመው ድርጊት እና ወንጀሉን ስለፈፀሙ ተጠርጣሪዎች ጠቃሚ ማስረጃዎችን ለመስጠት ፈቃደኛ ከሆነ በሚኒስትሩ ውሳኔ መሠረት ከክሱ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ነፃ ሊደረግ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገው ቢኖርም በወንጀል ድርጊቱ ምክንያት ተጎጂው የሞተ፣ የአካል ክፍሉ የተወሰደ ወይም በማይድን በሽታ የተያዘ እንደሆነ

ተጠርጣሪው ከክሱ ነፃ ሊደረግ አይችልም፣ ሆኖም በወንጀል ድርጊቱ የነበረው ተሳትፎን እና በሌሎች ላይ የሰጠውን ማስረጃ ጠቀሜታ ግምት ውስጥ በማስገባት ቅጣቱ መቀነስ አለበት፡፡

3. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም ሲባል “ጠቃሚ ማስረጃ” ማለት፦

ሀ/ የቀረበው ማስረጃ ብቻውን በቀረበው የወንጀል ክስ የጥፋተኝነት ውሳኔ ለመስጠት በቂ ከሆነ፤

ለ/ ማስረጃው በመገኘቱ ሌሎች ማስረጃዎችን ወይም ተጠርጣሪዎችን ለማግኘት መሠረታዊ ምንጭ ሆኖ የሚያገለግል ከሆነ፤ ወይም

ሐ/ የተገኘው ማስረጃ ከሌሎች ማስረጃዎች ጋር በመቀናጀት የጥፋተኝነት ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ከሆነ እና ይኸው ማስረጃ ባለመካተቱ ወንጀሉን ለማረጋገጥ በሌላ መልኩ የተሰባሰበው ማስረጃ በቂ የማይሆን ነው ተብሎ ሲታመን ነው፡፡

24.**<u>የዳኝነት ሥልጣን</u>**

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በዚህ አዋጅ በተደነገጉ ወንጀሎች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡
2. የዳኝነት ሥልጣንን የተመለከቱ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 13 እና አንቀጽ 17 (1) (ለ) ድንጋጌዎች ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልንም ያካትታሉ፡፡

25.**<u>ወንጀሉ በይርጋ የማይታገድ ስለመሆኑ</u>**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 እና 5 የተመለከቱ ወንጀሎችን በፈፀመ ሰው ላይ የሚቀርብ ክስ ወይም ቅጣት በይርጋ አይታገድም፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ስለተጎጂዎች ጥበቃ፣ መልሶ ማቋቋምና ካሳ</u>

26. **<u>ተጎጂዎችን ስለመለየትና ስለመታደግ</u>**

1. መንግስት አግባብነት ካላቸው የሌሎች አገራት ሚሲዮኖች፣ መንግሥታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት እና ሌሎች ድጋፍ የሚያደርጉ አካላት ጋር በመተባበር ተጎጂዎችን ለመለየት፣ ለመታደግ፣ ወደ

አገራቸው ለመመለስ እና መልሶ ለማቋቋም የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

2. በሌሎች ሕጎች የተደነገጉ መብቶች እንደተጠበቁ ሆኖ፦

ሀ/ ተጎጂዎች የሚደረግላቸውን ጥበቃ፣ እገዛ፣ ድጋፍ እና በፍርድ ሂደት ወቅት ስለጉዳዩ ደረጃ መረጃ እንዲያገኙ፤

ለ/ ተጎጂዎች ግላዊ ሚስጥራቸው እና ሰብዓዊ ክብራቸውን በጠበቀ መልኩ በርህራሄና በክብር እንዲያዙ፣ ተገቢው የጤና፣ የማሕበራዊ አገልግሎት፣ ጊዜያዊ መጠለያ፣ የማህበራዊና ሥነ ልቦናዊ ምክር ድጋፍ እንዲያገኙ፤

ይደረጋል፡፡

3. በዚህ አዋጅ ሥር የተመለከቱ የወንጀል ጉዳዮችን ለመመርመር፣ ክስ ለማቅረብ ወይም ዳኝነት ለመስጠት ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት የተጎጂዎችን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት የተሻለ ድጋፍ እና እንክብካቤ ወደሚያደርጉ ተቋማት መላክ አለባቸው፡፡

4. ተጎጂዎች በጊዜያዊ መጠለያ እንዲጠለሉ በሚደረግበት ጊዜ በማንኛውም ሁኔታ በፖሊስ ጣቢያ፣ በማረፊያ ቤቶች፣ ወይም በማረሚያ ቤቶች እንዲቆዩ መደረግ የለባቸውም፣ በወንጀል ክሱ የፍርድ ሂደት በምስክርነት ካላስፈለጉ በስተቀር በጊዜያዊ መጠለያ ውስጥ ከሶስት ወራት በላይ መቆየት የለባቸውም፡፡

5. ማንኛውም የሌላ አገር ዜግነት ያለው ተጎጂ ጉዳዩ በሌላ አግባብነት ባለው ሕግ የሚታይ ወይም በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት በፍርድ ሂደት ለምስክርነት የሚያስፈልግ ካልሆነ በስተቀር በጊዜያዊ መጠለያም ሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ ከአንድ ወር በላይ መቆየት የለበትም፡፡

27.<u>ተጎጂዎችን ወደአገራቸው መመለስ</u>

በሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር በማሻገር ወንጀል ተጎጂ ሆኖ ከአገር ውጭ የሚገኝ ኢትዮጵያዊን፦

1. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሚመለከተው የኢትዮጵያ ኤምባሲ፣ ከሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከዓለምአቀፍ ድርጅቶች እና አስፈላጊም ሲሆን ከሌሎች የአገር ውስጥ ተቋማት ጋር በመተባበር ወደ ኢትዮጵያ የሚመለስበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

2. ተጎጂው ባለበት አገር የሚገኝ ወይም በቅርበት የሚሠራ የኢትዮጵያ ሚሲዮን ተጎጂው የታሰረ ወይም የተያዘ መሆኑን ካወቀ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር

በመተባበር ተጎጂውን ለመታደግ፣ ተጎጂ በሆነበት የወንጀል ጉዳይ ጋር በተያያዘ በእስር ላይ የሚገኝ ከሆነ ከእስር ለማስለቀቅ ወይም ወደ አገሩ እንዲመለስ ለማድረግ አስፈላጊውን ይፈጽማል፤

3. ተጎጂው በማናቸውም ጉዳይ ባለበት አገር መቆየት ካለበት የሕግ ምክርን ጨምሮ ሌሎች አስፈላጊ ድጋፎች ከተሟሉ እንዲቆይ ሊያደርግ ይችላል፣ ተጎጂው በሚቆይበት አገር የሚገኘው ወይም በቅርበት የሚሰራው የኢትዮጵያ ሚሲዮን የተጎጂውን አያያዝና የጉዳዩን ደረጃ በመከታተል ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በየወቅቱ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 28.<u>የውጭ አገር ዜግነት ያላቸውን ተጎጂዎች ወደ አገራቸው ስለመመለስ</u>

1. ማንኛውም የውጭ አገር ዜጋ የሆነ ወደ ኢትዮጵያ የገባ ተጎጂ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 26 (2)፣ (3) እና (4) የተመለከቱ ድጋፎች በሙሉ ይደረግለታል፣ እንደነገሩ ሁኔታ ጊዜያዊ የመኖሪያ ፈቃድ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡
2. ማንኛውም በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር በማሻገር ወንጀል ተጎጂ የሆነ የውጭ አገር ዜጋ በኢትዮጵያ የሚገኝ ከሆነ ወደ ኢትዮጵያ የግዛት ክልል ውስጥ በሕገ-ወጥ መንገድ በመግባቱ ምክንያት በወንጀል ሊጠየቅ አይችልም፡፡
3. ለወንጀል ምርመራ፣ ክስና የፍርድ ሂደት ውጤታማነት የውጭ አገር ዜጋ የሆነ በኢትዮጵያ የሚገኝ ተጎጂ ለምስክርነት አስፈላጊ መሆኑ ከታመነ እና ተጎጂው ምስክርነቱን ለመስጠት ፈቃደኛ ከሆነ የፍርድ ሂደቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ አግባብነት ባለው ህግ መሰረት ጊዜያዊ የመኖሪያ ፈቃድ እንዲያገኝ ይደረጋል፣ ሰብዓዊ መብቶቹም በተሟላ መልኩ እንዲከበሩ ይደረጋል፡፡
4. ስለቪዛ፣ ስለጉዞ ሰነድ እና ሌሎች ሁኔታዎች በሌሎች ሕጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የውጭ አገር ዜጋ የሆነ ተጎጂ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ መሆኑ ከተለየ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እና ከሚመለከተው አገር ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን ጋር በመተባበር ተጎጂው ወደ አገሩ የሚመለስበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

## 29.<u>የተጎጂዎችና ምስክሮች ጥበቃ</u>

በሌሎች ሕጎች ለተጎጂዎች የተሰጡ ልዩ ልዩ መብቶች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር

ወንጀል ተጎጂ የሆነ ምስክር እንደነገሩ ሁኔታ በምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 699/2003 የተደነገጉ ጥበቃዎችን እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

**30.ከወንጀል ተጠያቂነት ነፃ ስለመሆን**

ማንኛውም ተጎጂ ለሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል ከመፃረጉ ጋር በተያያዘ በወንጀል አይጠየቅም፡፡

**31.ስለካሣ**

1. ፍርድ ቤት በጥፋተኛው ላይ ከሚወስነው ቅጣትና መቀጮ በተጨማሪ ለተጎጂው ወይም በተጎጂው ስም ወጭ ላወጡ ሌሎች ሰዎች ወይም ድርጅቶች ካሣ እንዲከፈል ሊወስን ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚከፈል ካሣ የሕክምና፣ የትራንስፖርት፣ የሞራል ካሳ፣ ከወንጀሉ ጋር በቀጥታ ተያያዥነት ባላቸው ምክንያቶች የደረሱ ጉዳቶች ካሳ እና ሌሎች ተገቢነት ያላቸው ወጭዎችን ለማካካስ የሚችል መሆን አለበት፣ በማናቸውም ሁኔታ ለተጎጂው የሚከፈል ካሣ እንደነገሩ ሁኔታ ለሕገ-ወጥ ሰው አዘዋዋሪው ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር አሻጋሪው ከከፈለው ገንዘብ፣ ሊከፍል ከሚችለው ወይም በወንጀል ድርጊቱ ምክንያት ተጎጂው ካጣው ወይም ለሕገ-ወጥ ሰው አዘዋዋሪው ወይም ስደተኞችን ሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር አሻጋሪው ካገኘው ጥቅም መጠን ያነሰ መሆን የለበትም፡፡
3. ተጎጂው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት ካሣ ማግኘት ያልቻለ እንደሆነ የማካካሻ ክፍያ ከፈንዱ እንዲከፈል ይደረጋል፣ የማካካሻ ክፍያ ተጠቃሚ መሆን የሚችለው ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው ተጎጂ ነው፡፡

## ክፍል አምስት
## ስለፈንድ መቋቋም

**32.መቋቋም**

ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ ድንበር ማሻገር ወንጀልን የመከላከል፣ የመቆጣጠር እና ተጎጂዎችን መልሶ ማቋቋሚያ ፈንድ (ከዚህ በኋላ “ፈንድ” እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

**33.የገቢ ምንጭ**

የፈንዱ የገቢ ምንጭ ከመንግስት ከሚመደብ በጀት፣ በዚህ አዋጅ መሠረት ከሚወረሱ ንብረቶችና መቀጮዎች፣ ከግለሰቦች፣ ከልዩ ልዩ መንግስታዊ፣ ከበጎ አድራጎት

ድርጅቶችና ማህበራት ከሚገኝ ልገሳ፣ ከልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችና የእርዳታ ተቋማት ከሚገኝ ድጋፍ እና ከሌሎች የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ከሚያፀድቃቸው የገንዘብ ምንጮች ከሚገኝ ገቢ ይሆናል፡፡

34.**ዓላማ**

1. ፈንዱ የተቋቋመበት ዋና ዓላማ የሚከተሉትን ያካትታል፦
2. ለተጎጂዎች የሚሰጥ ቁሳዊ እርዳታ ለመደገፍ፤
3. ለተጎጂዎች የሚሰጥ የሙያ ሥልጠናን ለመደገፍ፤
4. ተጎጂዎችን ለመታደግ፣ መልሶ ለማቋቋም እና ከቤተሰቦቻቸውና ከማሕበረሰቡ ጋር እንዲቀላቀሉ ለማድረግ እንዲሁም ቤተሰቦችን ለማፈላለግ የሚወጡ ወጭዎችን ለመሸፈን፤ እና
5. የተጎጂዎች ጊዜያዊ መጠለያ ግንባታን እና ሌሎች ድጋፎች ለማድረግ፡፡

35.**የፈንዱ አስተዳደር**

የፈንዱ አስተዳደር፣ አሰራርና ፈንዱን የሚያስተዳድረው አካል ተጠሪነት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሰረት ይወሰናል፡፡

36.**የፈንዱ ተጠቃሚዎች**

በዚህ አዋጅ መሠረት ከተቋቋመው ፈንድ ተጠቃሚ መሆን የሚችለው ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው ተጎጂ ይሆናል፣ ሆኖም የሌላ አገር ዜግነት ያላቸው ተጎጂዎች ከፈንዱ ተጠቃሚ ስለሚሆኑበት ሁኔታ መንግስት ሊወስን ይችላል፡፡

37.**የፈንዱ የሂሳብ መዝገብና ኦዲት**

1. የፈንዱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየዓመቱ በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር ይመረመራሉ፡፡
2. ፈንዱን የሚያስተዳድረው አካል የኦዲት ሪፖርቱን የበጀት አመቱ በተጠናቀቀ በአራት ወራት ጊዜ ውስጥ ተጠሪ ለሆነለት አካል ማቅረብ አለበት፡፡

38.**የበጀት ዓመት**

የፈንዱ የበጀት ዓመት የመንግስት የበጀት ዓመት ይሆናል፡፡

## **ክፍል ስድስት**
## **የባለድርሻ አካላት ትብብር**

39.**ስለብሔራዊ ኮሚቴ መቋቋም**

1. የሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር፣ ተጎጂዎችን ለመጠበቅ፣ ድጋፍና የመልሶ ማቋቋም ተግባራትን ለማከናወን እና አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ለማድረግ፣ በአገሪቱ የሚወጡ ፖሊሲዎች፣ እቅዶች እና መርሃ ግብሮች የተጎጂዎችን ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባ እንዲሆን ለማድረግ፣ ወንጀሉ የሚያስከትለው ማህበራዊ ቀውስ፣ በአገር ገፅታ ላይ የሚኖረውን አሉታዊ ተጽዕኖ እና ሌሎች ጉዳዮችን አስመልክቶ በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ እንዲካተት ለማድረግ፣ ይህንኑ ሥራ በልዩ ልዩ አካላት ዘንድ ለማስተባበር፣ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን እና አደረጃጀቶችን ፍላጎትና ጥቅም ለማስከበር የሚያስችል ብሔራዊ ኮሚቴ ይቋቋማል፡፡
2. ብሔራዊ ኮሚቴው በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራ ሆኖ የፍትህ ሚኒስቴር፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር፣ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የትምህርት ሚኒስቴር እና ሌሎች ልዩ ልዩ የመንግስት ተቋማትን፣ የሃይማኖት ተቋማትን፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን፣ ልዩ ልዩ አደረጃጀቶችን፣ ክልሎችን እና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት ያቀፈ ይሆናል፡፡[53]
3. የብሔራዊ ኮሚቴው ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ሆኖ ወንጀሉን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና ተጎጂዎችን እንደገና መልሶ ለማቋቋም የሚደረገውን ጥረት በአገር አቀፍ ደረጃ ይመራል፣ ያስተባብራል፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የብሔራዊ ኮሚቴው አደረጃጀት፣ አባላት አሰያየም፣ ሥልጣንና ተግባር እና የሌሎች ተቋማት ኃላፊነት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

**40.** **<u>ግብረ ሀይል ስለማቋቋም</u>**

1. ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ስደተኞችን በሕገ- ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና ተጎጂዎችን መልሶ ለማቋቋም የሚደረገውን ጥረት የሚደግፍና ተጠሪነቱ ለብሔራዊ ኮሚቴ የሆነ የፀረ ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር

---

[53] በዚህ ንዑስ አንቀፅ ውስጥ የተጠቀሱት "የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር" እና "የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር" በ22/12(2008) አ.916 መሰረት እንደቅደምተከተላቸው "የፈዴራልና አርብቶ አደር ጉዳዮች ልማት ሚኒስቴር" እና "ሴቶችና ህፃናት ሚኒስቴር ሆነዋል፡፡

እና ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል የጋራ ግብረ ሀይል (ከዚህ በኋላ "ግብረ ሀይል" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

2. ግብረ ሀይሉ በፍትህ ሚኒስትሩ የሚመራ ሆኖ፡-

ሀ/ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አግልግሎት፣ የትምህርት ሚኒስቴር፤

ለ/ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ የበጎ አድራጎትና ማህበራት ኤጀንሲ፤

ሐ/ በሚኒስትሩ የሚወከል አንድ ኃላፊ፤ እና

መ/ በብሔራዊ ኮሚቴው ሰብሳቢ የሚሰየሙ ሌሎች ሰዎችን፤

ያካተተ ይሆናል፡፡

3. ግብረ ሀይሉ፡-

ሀ/ ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት፣ ከአጋር ድርጅቶች እና እንዳስፈላጊነቱ ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ተጎጂዎችን ለመጠበቅና ለመርዳት እንዲሁም ወንጀሉን ለመከላከል የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ መርሐ ግብሮችንና እርምጃዎችን በመቅረጽ በብሔራዊ ኮሚቴው ሲፀድቅ ተፈፃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

ለ/ ወንጀሉን በመከላከልና በመቆጣጠር ረገድ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ያዘጋጃል፣ ለብሔራዊ ኮሚቴው አቅርቦ ያስፀድቃል፣ የድርጊት መርሃ ግብሩን አፈፃፀም ይከታተላል፣ በየወቅቱ ለብሔራዊ ኮሚቴው ሪፖርት ያቀርባል፤

ሐ/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ተጎጂዎችን መልሶ ለማቋቋም፣ ድጋፍ ለማድረግና ከህብረተሰቡ ጋር ተቀላቅለው እንዲኖሩ ለማስቻል ተገቢውን ይፈጽማል፤

መ/ ሌሎች በብሔራዊ ኮሚቴው የሚሰጡ ልዩ ልዩ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

41. <u>የፍትሕ ሚኒስቴር ኃላፊነት</u>

የፍትህ ሚኒስቴር፡-

1. ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ልዩ ልዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በመተባበር፡-

ሀ/ ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀሎችን የሚመለከቱ በተለይም ሕገ-ወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎች እና

ሕገ-ወጥ ስደተኞችን ድንበር አሻጋሪዎች የሚጠቀሚቸውን የተለመዱ ተጎጂዎችን የመመልመያ ዘዴዎች፣ የብዝበዛና የማቆያ ሥልቶች፣ ተጎጂዎች ተጋላጭ ሊሆኑባቸው ስለሚችሉ የብዝበዛ ዓይነቶች፣ ተጎጂዎች መረጃ እና ድጋፍ ሊያገኙባቸው ስለሚችሉ ተቋማትና የሕግ አስከባሪ አካላት ሚና፤

ለ/ ተጎጂዎች ስላላቸው መብት፣ የተጎጂዎችን ደህንነት ለመጠበቅ፣ ለመታደግና ወደ አገራቸው ለመመለስ ስለሚያስችሉ በሥራ ላይ ስላሉ የሕግ ወይም ሌላ መንገዶች፣ ተጎጂዎች መረጃ እና ድጋፍ ሊያገኙ ስለሚችሉባቸው ድርጅቶች፣ ተቋማትና የሕግ አስከባሪ አካላት መረጃ እና ትምህርት የሚሰጡ፤ እና

ሐ/ ተጎጂዎች በተለይም ሴቶችና ሕጻናት ለእነዚህ ወንጀሎች እንዲዳረጉ የሚገፋፉ ምክንያቶችን ለማዳከም የሚያስችሉ የግንዛቤ መፍጠሪያ፤

መ/ ወንጀሉን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ጥቅም ላይ የዋሉ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመለየት የማስተዋወቂያ፤

መርሃ ግብሮች፣ አጫጭር ጽሑፎች፣ የማስተማሪያ ሞጁሎች፣ ድራማዎች፣ ሌሎች መሰል የማስተማሪያ ዘዴዎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ አስፈላጊ ወጭዎችም ከፈንዱ እንዲሸፈኑ በማድረግ በመገናኛ ብዙሃን እና ሌሎች የግንኙነት አውታሮችን በመጠቀም ለሕዝብ እንዲተላለፉ ያደርጋል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገጉት መርሐ ግብሮች እና የመከላከል እርምጃዎች የገጠሩን ማሕበረሰብ ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችሉ ስልቶችን በአግባቡ ማካተታቸውንና ውጤታማነታቸውንም ለማረጋገጥ በየወቅቱ ግብረ ሀይሉ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

42.<u>የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ኃላፊነት</u>

በሌሎች ሕጎች ለልዩ ልዩ አካላት የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፦

1. ከብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት እና ሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል ጋር በተያያዘ ተጎጂ የሆኑ ሰዎችን ዝርዝር፣ የሚገኙበትን አገር፣ ያሉበትን ሁኔታ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን መረጃ ያጠናቅራል፣ ለሚመለከታቸው ያደርሳል፤

2. በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል ምክንያት በተለያዩ አገራት ለሚገኙ ተጎጂዎች እና ስደተኞች የየአገራቱን የሥጋት ደረጃ በመለየት በየወቅቱ በተለያዩ የግንኙነት ዘዴዎች እንዲያውቁት ያደርጋል፣
3. በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል መዳረሻ በሆኑ አገራት የሚገኙ ዜጎች የየራሳቸውን ኮሚዩኒቲ እንዲያቋቁሙ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፣ በኮሚዩኒቲው አደረጃጀት መሠረት በየአገራቱ መብትና ጥቅማቸው እንዲከበር ያደርጋል፡፡

43.<u>የፖሊስ ኃላፊነት</u>

1. ፖሊስ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፍትሕ ሚኒስቴር፣ የብሔራዊ መረጃ ደህንነት አገልግሎት፣ ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በዚህ አዋጅ የተደነገጉ ወንጀሎችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር እንደነገሩ ሁኔታ በምርመራ፣ መረጃ በመለዋወጥ፣ በአቅም ግንባታ እና በመሳሰሉ ጉዳዮች ዙሪያ በጋራ ይሰራል፡፡
2. ፖሊስ ተጎጂዎችን በመለየት፣ ተጎጂዎችን ድንበር ለማሻገር ጥቅም ላይ የዋሉ ንብረቶችን፣ ሰነዶችና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን ለመለየት፣ የተደራጁ የወንጀል ቡድኖች የዘረጓቸውን የወንጀል መረቦችና ስልቶች ለመለየት ከአገር ውስጥና ከሌሎች የውጭ አገራት መሰል ተቋማት ጋር ግንኙነት ሊፈጥር ይችላል፡፡

## <u>ክፍል ሰባት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

44.<u>ዓለም አቀፍ ትብብር</u>

1. ፍትሕ ሚኒስቴር እንደጉዳዩ አግባብነት ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር መረጃ መለዋወጥን፣ በጋራ የምርመራ ሥራ ማከናወንን፣ ወንጀለኛ አሳልፎ መስጠትን እና ሌሎች የጋራ የሕግ ትብብርን ጨምሮ ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ከሌላ ሀገር አግባብ ያለው ባለሥልጣን ጋር በዚህ አዋጅ እና ኢትዮጵያ ተዋዋይ ወገን በሆነችበት ስምምነት እና የኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት በሚፈቅደው መሠረት በትብብር ይሰራል፣ ማዕከላዊ ባለስልጣን ሆኖ ያገለግላል፡፡

2. ፍትሕ ሚኒስቴር እንደአስፈጊነቱ በዚህ አዋጅ የተደነገጉ የወንጀል ጉዳዮችን ለመከላከል እና ተጠርጣሪዎችን ለፍርድ ለማቅረብ የሚያስችሉ ስምምነቶችን ከሌሎች አገራት ጋር ልዩ ልዩ የትብብር ማዕቀፎችን ሊፈራረም ይችላል፡፡
3. ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል ፖሊስ ተመሳሳይ ተልዕኮ ካለው መሰል የሌላ ሀገር ተቋም ጋር እንካ በእንካ መርህ ላይ ተመስርቶ የመረጃ ልውውጥ፣ በሌላ መልኩ የጋራ ትብብር ሊያደርግ ወይም እንደአስፈላጊነቱ ከሌላው አገር መሰል ተቋም ጋር የመግባቢያ ስምምነት ሊፈራረም ይችላል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ መሠረት ሊኖሩ የሚገባቸው የስምምነት ማዕቀፎች አለመፈረማቸው መንግስት የጋራ የሕግ ትብብርና ድጋፍ ለማድረግ ወይም ለመቀበል የሚያስችል አስተዳደራዊ እርምጃ ከመውሰድ አያግደውም፡፡
5. በዚህ አዋጅ ከተደነገገው በላይ ከፍተኛ ቅጣት ሊያስቀጣ ለሚችል ወንጀል ማስረጃ ወይም መረጃ ካልሆነ በስተቀር በዚህ አንቀጽ መሠረት የተገኘ ማንኛውም መረጃ ወይም ማስረጃ ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከል ወይም ለመመርመር ዓላማ ይውላል፡፡

**45.<u>ንብረት ስለመውረስ</u>**

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13 እና 22 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፍርድ ቤቱ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የጥፋተኝነት ውሳኔ ከሰጠ በጥፋተኛው ላይ ከሚወሰኑ ቅጣቶች በተጨማሪ የወንጀል ፍሬ የሆነ ማንኛውም ንብረት እንዲወረስ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል አመንጪ ወንጀል ሆኖ በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 780/2005 አንቀፅ 35 ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**46.<u>ስለሌሎች ወንጀሎች</u>**

ማንኛውም የመንግስት የሥራ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ በዚህ አዋጅ ከተደነገጉት ወንጀሎች ውጭ በሌላ ሕግ የተደነገገን ወንጀል ፈጽሞ የተገኘ እንደሆነ ወይም በዚህ አዋጅ መሰረት ተጠያቂ የሆነ ሰው ሌሎች ተደራራቢ ወንጀሎችን የፈፀመ እንደሆነ

አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በተደራራቢነት የሚኖርበት የወንጀል ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ይሆናል፡፡

**47.ስለውክልና**

ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል በህገ መንግስቱ ለክልል ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የውክልና ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ እንደቅደም ተከተሉ ሚኒስቴሩ ወይም የፌደራል ፖሊስ በወንጀል ጉዳዩ ላይ ያላቸውን ስልጣን እንደአስፈላጊነቱ ለክልል ፍትህ ቢሮ ወይም ለክልል ፖሊስ ኮሚሽን በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

**48.ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች**

1. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 243፣ 596፣ 597፣ 598፣ 599 እና 635 ለዚህ አዋጅ ተፈፃሚነት የላቸውም፡፡
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**49.ደንብ የማውጣት ስልጣን**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚረዳ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**50.አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ 11 ቀን 2007 ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 958/2008

## የኮምፒዩተር ወንጀልን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ

የኢንፎርሜሽንና የኮምኒዩኬሽን ቴክኖሎጂ ለሃገሪቱ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እድገት ቁልፍ ሚና የሚጫወት በመሆኑ፤

የኢንፎርሜሽንና የኮምኒዩኬሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ተገቢ ጥንቃቄና ጥበቃ ካልተደረገለት የሃገሪቱን ሁለንተናዊ እድገት ሊያደናቅፍ እንዲሁም የዜጎችን የግል ነፃነት አደጋ ላይ ሊጥሉ ለሚችሉ የተለያዩ የኮምፒዩተር ወንጀሎች እና ሌሎች የደህንነት ስጋቶች የተጋለጠ በመሆኑ፤

በሥራ ላይ ያሉ የሀገሪቱ ሕጎች ከአዳዲስ የቴክኖሎጂ ለውጦች ጋር በበቂ ሁኔታ ተጣጥመው የማይሄዱ እና የኮምፒዩተር ወንጀልን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር፣ ለመመርመርና ተጠርጣሪዎችን ወደ ፍትህ ለማቅረብ የሚያስችሉ ባለመሆናቸው፤

የኮምፒዩተር ወንጀልን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር፣ ለመመርመርና ኤሌክትሮኒክ ማስረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚያስችሉ አዳዲስ ስልቶችንና ሥርዓቶችን በሕግ መደንገግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 55(1) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡-

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የኮምፒዩተር ወንጀል አዋጅ ቁጥር 958/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

   1. "የኮምፒዩተር ወንጀል" ማለት፡-

      ሀ/ በኮምፒዩተር፣ በኮምፒዩተር ስርዓት፣ በኮምፒዩተር ዳታ ወይም ኔትዎርክ ላይ የሚፈፀም ወንጀል፤

      ለ/ ኮምፒዩተርን፣ የኮምፒዩተር ስርዓትን፣ የኮምፒዩተር ዳታን ወይም ኔትዎርክን በመጠቀም የሚፈፀም መደበኛ ወንጀል፤ ወይም

ሐ/ በኮምፒዩተር፣ በኮምፒዩተር ስርዓት ወይም ኔትዎርክ አማካኝነት የሚሰራጭ ህገወጥ የኮምፒዩተር ዳታ ይዘት ነው፤

2. “የዳታ ፕሮሰሲንግ አገልግሎት” ማለት በኮምፒዩተር ሥርዓት አማካኝነት ዳታን የመቀበል፣ የማከማቸት፣ የመተንተን፣ የማሰራጨት፣ የማጓጓዝ ወይም የማስተላለፍ አገልግሎት ሲሆን የኔትዎርክ አገልግሎትንም ይጨምራል፤
3. “ኮምፒዩተር ወይም የኮምፒዩተር ሥርዓት” ማለት በሶፍትዌር እና ማይክሮቺፕ ቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ የዳታ ፕሮሰሲንግ፣ ክምችት፣ ትንተና፣ ስርጭት፣ ግንኙነት ወይም ሌሎች ሂሳባዊ ወይም አመክንዮአዊ ተግባራትን የሚያከናውን ማንኛውም መሳሪያ ሲሆን የመሳሪያው ተገጣሚ አካልንም ይጨምራል፤
4. “የኮምፒዩተር ዳታ” ማለት በኮምፒዩተር ሥርዓት አማካኝነት ሊተነተን የሚችል ማንኛውም የይዘት ዳታ፣ የትራፊክ ዳታ፣ የኮምፒዩተር ፕሮግራም ወይም ደንበኞችን የሚመለከት ማንኛውም ኢንፎርሜሽን ነው፤
5. “የኮምፒዩተር ፕሮግራም” ማለት አንድ የኮምፒዩተር ሥርዓት ተግባሩን እንዲያከናውን ወይም የታሰበውን ውጤት እንዲያስገኝ የሚያስችል በቃላት፣ በኮድ ወይም በዘዴ የሚገለጽ የመመሪያ ወይም የትዕዛዝ ስብስብ ነው፤
6. “የትራፊክ ዳታ” ማለት በኮምፒዩተር ሥርዓት አማካኝነት የሚደረግን ኮምዩኒኬሽን መነሻ፣ መድረሻ፣ ዑደት፣ ጊዜ፣ ቀን፣ የግንኙነት ቆይታ፣ የዳታው መጠን፣ የአገልግሎት ዓይነት ወይም መሰል የኮምዩኒኬሽን ሰንሰለት የሚያሳይ በኮምፒዩተር ስርዓቱ የሚመነጭ ዳታ ነው፤
7. “የይዘት ዳታ” ማለት በድምፅ፣ በተንቀሳቃሽ ምስል፣ በስዕል፣ በሂሳባዊ ቀመር ወይም በሌላ ማንኛውም ቅርፅ የሚገኝን የተከማቸ ወይም በስርጭት ሂደት ላይ ያለ ዳታ ወይም የኮምፒዩተር ኮምዩኒኬሽን ምንነት፣ ፍሬ ነገር፣ ትርጉም ወይም መልዕክት የሚያሳይ የኮምፒዩተር ዳታ ነው፤
8. “ኔትዎርክ” ማለት ሁለትና ከዚያ በላይ የኮምፒዩተር ሥርዓቶች እርስ በርስ በማስተሳሰር የዳታ ፕሮሰሲንግ አገልግሎት ለመስጠት ወይም ለማግኘት የሚያስችል ሥርዓት ነው፤
9. “የኮምፒዩተር ዳታ ደህንነት” ማለት የኮምፒዩተር ዳታ እንዳይጠፋ፣ እንዳይቀየር፣ ላልተፈቀደለት አካል ተደራሽ እንዳይሆን፣ ምስጢራዊነቱ እንዳይጋለጥ ወይም ሌላ ማንኛውም ጉዳት እንዳይደርስበት መጠበቅ ነው፤

10. “ደራሽነት” ማለት ከኮምፒዩተር ስርዓት ጋር ግንኙነት የመፍጠር፣ ወደ ኮምፒዩተር ስርዓቱ የመግባት፣ ዳታ የማከማቸት፣ የተከማቸን ዳታ የማግኘት፣ የማየት፣ የመውሰድ፣ የማንቀሳቀስ፣ ወደ ሌላ ማከማቻ መሳሪያ የመገልበጥ ወይም ሌላ ማንኛውም የዳታ ፕሮሰሲንግ አገልግሎትን የማግኘት ተግባር ነው፤
11. “ቁልፍ መሰረተ ልማት” ማለት በዚህ አዋጅ ከአንቀፅ 3 እስከ 6 የተመለከተው ማናቸውም የወንጀል ድርጊት ቢፈጸምበት በሕዝብ ደኅንነት እና በብሔራዊ ጥቅሞች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል የኮምፒዩተር ሥርዓት፣ ኔትወርክ ወይም ዳታ ነው፤
12. “ጠለፋ” ማለት በኮምዩኒኬሽን ሂደት ላይ ያለን የኮምፒዩተር ዳታ ወይም የዳታ ፕሮሰሲንግ አገልግሎት መከታተል፣ መቅዳት፣ ማዳመጥ፣ መውሰድ፣ ማየት፣ መቆጣጠር ወይም ሌላ ተመሳሳይ ድርጊት ነው፤
13. “አገልግሎት ሰጪ” ማለት በኮምፒዩተር ስርዓት አማካኝነት ቴክኒካዊ የዳታ ፕሮሰሲንግ ወይም የግንኙነት ስርዓት አገልግሎት ወይም ምትክ መሰረተ ልማት ለተጠቃሚዎች የሚያቀርብ ሰው ነው፤
14. “ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ” ማለት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሾመ የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ኃላፊ ነው፤
15. “ዓቃቤ ሕግ” ማለት በጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ ተሹሞ በዓቃቤያነ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የሚተዳደር የሕግ ባለሙያ፤ ሲሆን ጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉንና ምክትል ጠቅላይ ዓቃቤያነ ሕግን ይጨምራል፤
16. “መርማሪ አካል” ማለት በሕግ የመመርመር ሥልጣን የተሰጠው አካል ነው፤
17. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47(1) የተመለከተዉ ማንኛውም ክልል ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የአዲስ አበባ ከተማ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤
18. “ፖሊስ” ማለት የፌደራል ፖሊስ ወይም የፌደራል ፖሊስ ሥልጣን በውክልና የተሰጠው የክልል ፖሊስ ነው፤
19. “ኤጀንሲ” ማለት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ነው፤
20. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
21. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል፡፡

# ክፍል ሁለት

## የኮምፒዩተር ወንጀሎች

## ንኡስ ክፍል አንድ

## በኮምፒዩተር ሥርዓትና በኮምፒዩተር ዳታ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

### 3. ሕገ ወጥ ደራሽነት

1. ማንኛውም ሰው ሆነ ብሎ ያለፈቃድ ወይም ከተሰጠው ፈቃድ ውጪ የኮምፒዩተር ስርዓት፣ የኮምፒዩተር ዳታ ወይም ኔትዎርክ ደራሽነት በከፊልም ሆነ በሙሉ ያገኘ እንደሆነ ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከብር 30,000 እስከ ብር 50,000 በሚደርስ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) ላይ የተመለከተው የወንጀል ድርጊት የተፈጸመው፣
   ሀ/ በሕግ የሰውነት መብት ለተሰጠው ተቋም አገልግሎት ብቻ በሚውል የኮምፒዩተር ሥርዓት፣ የኮምፒዩተር ዳታ ወይም ኔትዎርክ ላይ ከሆነ ከሶስት ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር 30,000 እስከ ብር 50,000 በሚደርስ መቀጮ ያስቀጣል፣
   ለ/ በቁልፍ መሠረተ ልማት ላይ ከሆነ ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር 50,000 እስከ ብር 100,000 በሚደርስ መቀጮ ያስቀጣል፡፡

### 4. ሕገ ወጥ ጠለፋ

1. ማንኛውም ሰው ሆነ ብሎ ያለፈቃድ ወይም ከተሰጠው ፈቃድ ውጪ ይፋዊ ያልሆነን የኮምፒዩተር ዳታ ወይም የዳታ ፕሮሰሲንግ አገልግሎት የጠለፈ እንደሆነ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከብር 10,000 እስከ 50,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ላይ የተመለከተው የወንጀል ድርጊት የተፈጸመው:-
   ሀ/ በሕግ የሰውነት መብት ለተሰጠው ተቋም አገልግሎት ብቻ በሚውል የኮምፒዩተር ዳታ ወይም የዳታ ፕሮሰሲንግ አገልግሎት ላይ ከሆነ ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር 50,000 እስከ ብር 100,000 በሚደርስ መቀጮ ያስቀጣል፤

ለ/ በቁልፍ መሠረተ ልማት ላይ ከሆነ ከአስር ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር 100,000 እስከ ብር 200,000 በሚደርስ መቀጮ ያስቀጣል፡፡

5. <u>በኮምፒዩተር ሥርዓት ላይ ጣልቃ መግባት</u>

1. ማንኛውም ሰው ሆነ ብሎ ያለፈቃድ ወይም ከተሰጠው ፈቃድ ውጪ የኮምፒዩተር ዳታን በማስገባት፣ በማሰራጨት፣ በማጥፋት ወይም በመለወጥ የኮምፒዩተር ሥርዓትን ወይም ኔትወርክን መደበኛ ተግባር በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ ያደናቀፈ፣ ያወከ፣ ያወደመ ወይም እንዲቋረጥ ያደረገ እንደሆነ ከሶስት ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር 50,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ላይ የተመለከተው የወንጀል ድርጊት የተፈጸመው፣

ሀ/ በሕግ የሰውነት መብት ለተሰጠው ተቋም አገልግሎት ብቻ በሚውል የኮምፒዩተር ሥርዓት ላይ ከሆነ ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር 50,000 እስከ ብር 100,000 በሚደርስ መቀጮ ያስቀጣል፤

ለ/ በቁልፍ መሠረተ ልማት ላይ ከሆነ ከአስር ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር 100,000 እስከ ብር 200,000 በሚደርስ መቀጮ ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ ከአስራ አምስት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር 200,000 እስከ ብር 500,000 በሚደርስ መቀጮ ያስቀጣል፡፡

6. <u>በኮምፒዩተር ዳታ ላይ ጉዳት ማድረስ</u>

1. ማንኛውም ሰው ሆነ ብሎ ያለፈቃድ ወይም ከተሰጠው ፈቃድ ውጪ የኮምፒዩተር ዳታን የለወጠ፣ ያጠፋ፣ ያፈነ፣ ትርጉም እንዳይኖረው ወይም ጥቅም እንዳይሰጥ ወይም ለሕጋዊ ተጠቃሚዎች ተደራሽ እንዳይሆን ያደረገ እንደሆነ ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከብር 30,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀፅ (1) ላይ የተመለከተው የወንጀል ድርጊት የተፈጸመው፣

ሀ/ በሕግ የሰውነት መብት ለተሰጠው ተቋም አገልግሎት ብቻ በሚውል የኮምፒዩተር ዳታ ላይ ከሆነ ከሦስት ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር 30,000 እስከ ብር 50,000 በሚደርስ መቀጮ ያስቀጣል፤

ለ/ በቁልፍ መሠረተ ልማት ላይ ከሆነ ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር 50,000 እስከ ብር 100,000 በሚደርስ መቀጮ ያስቀጣል፡፡

7. <u>ከኮምፒዩተር መሣሪያና ዳታ አጠቃቀም ጋር የተያያዙ ወንጀሎች</u>

1. ማንኛውም ሰው በኮምፒዩተር ሥርዓት፣ በኮምፒዩተር ዳታ ወይም በኔትዎርክ ላይ ጉዳት ሊያደርሱ እንደሚችሉ እያወቀ ለዚህ ዓላማ ተብለው የተመረቱ ወይም የተሻሻሉ የኮምፒዩተር ፕሮግራሞችን ሆን ብሎ በኮምፒዩተር ሥርዓት አማካኝነት ያሰራጨ እንደሆነ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከብር 30,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።
2. ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ 3 እስከ 6 የተዘረዘሩትን የወንጀል ድርጊቶች ለማስፈጸሚያ እንደሚውሉ እያወቀ ለዚህ ዓላማ የሚውሉ የኮምፒዩተር መሣሪያዎችን ወይም የኮምፒዩተር ዳታዎችን ሆን ብሎ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባ፣ ያመረተ፣ ለሽያጭ ያቀረበ፣ ያከፋፈለ ወይም ሌሎች እንዲያገኙት ያመቻቸ እንደሆነ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራትና ከብር 10,000 እስከ ብር 50,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።
3. ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ 3 እስከ 6 የተዘረዘሩትን የወንጀል ድርጊቶች ለመፈፀም በማሰብ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) የተመለከቱትን የኮምፒዩተር መሳሪያዎች ወይም ዳታዎች ይዞ የተገኘ እንደሆነ ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከብር 5,000 እስከ ብር 30,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።
4. ማንኛውም ሰው ሆን ብሎ ያለፈቃድ ወይም ከተሰጠው ፈቃድ ውጭ የኮምፒዩተር ሥርዓት፣ የኮምፒዩተር ዳታ ወይም ኔትዎርክ ደራሽነት ማግኘት የሚያስችል የኮምፒዩተር ፕሮግራም፣ የምስጢር ኮድ፣ ቁልፍ፣ የይለፍ ቃል ወይም ሌላ መሰል ዳታ ይፋ ያደረገ ወይም ለሌላ ሰው አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር 10,000 እስከ ብር 50,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።

5. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀፅ (4) ላይ የተመለከተውን የወንጀል ድርጊት በቸልተኝነት የተፈፀመ እንደሆነ ቅጣቱ ከአንድ ዓመት የማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር 10,000 የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።

8. <u>ከባድ ሁኔታዎች</u>

በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ 3 እስከ 6 የተመለከተው ማንኛውም የወንጀል ድርጊት የተፈፀመው:-

ሀ/ ለወታደራዊ ጥቅም ወይም ለዓለም አቀፍ ግንኙነት ሲባል በሚመለከተው አካል ጥብቅ ምስጢር ተብሎ በተሰየመ የኮምፒዩተር ዳታ ወይም ዳታው በሚገኝበት የኮምፒዩተር ሥርዓት ወይም ኔትዎርክ ላይ ከሆነ፣ ወይም

ለ/ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በታወጀበት ወይም ሀገሪቱ በአስጊ ሁኔታ ላይ በምትገኝበት ወቅት ከሆነ፣

ቅጣቱ ከአስራ አምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይሆናል፡፡

## <u>ንኡስ ክፍል ሁለት</u>
## <u>በኮምፒዩተር አማካኝነት የሚፈፀሙ የማጭበርበር፣</u>
## <u>የማታለል እና የስርቆት ወንጀሎች</u>

9. <u>የኮምፒዩተር ዳታን ወደ ሐሰት መለወጥ</u>

ማንኛውም ሰው የሌላውን ሰው መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ማናቸውንም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ ሕጋዊ ውጤት ያለውን ወይም ሊኖረው የሚችለውን የኮምፒዩተር ዳታ ወደ ሐሰት የለወጠ ወይም ሐሰተኛ የኮምፒዩተር ዳታ ያዘጋጀ ወይም በዚሁ የተገለገለ እንደሆነ ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት እና ከ30,000 ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ወንጀሉ ከባድ በሆነ ጊዜ ከአስር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከብር 10,000 እስከ ብር 100,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

10. <u>በኮምፒዩተር አማካኝነት የሚፈፀም የማታለል ወንጀል</u>

1. ማንኛውም ሰው አሳሳች የኮምፒዩተር ዳታዎችን በማሰራጨት፣ የራሱን ማንነት ወይም ሁኔታ በመሰወር ወይም መግለጽ የሚገባውን ነገር በመደበቅ ወይም የሌላውን ሰው የተሳሳተ እምነት በመጠቀም፣ ሌላውን ሰው አታልሎ የራሱን ወይም

የሶስተኛ ወገንን ማንኛውም ጥቅም የሚጎዳ ድርጊት እንዲፈጽም ያደረገው እንደሆነ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከብር 50,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

2. ማንኛውም ሰው በተጭበረበረ መንገድ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት የኮምፒዩተር ዳታን በመለወጥ፣ በማጥፋት ወይም ሌላ ማንኛውም ጉዳት በማድረስ በሌላ ሰው ላይ ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከብር 10,000 እስከ ብር 50,000 በሚደርስ መቀጮ ወይም ወንጀሉ ከባድ በሆነ ጊዜ እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር 10,000 እስከ ብር 100,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።

**11.<u>የኤሌክትሮኒክ ማንነት ስርቆት</u>**

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 ላይ የተመለከተውን የወንጀል ድርጊት ለመፈፀም በማሰብ ወይም ለሌላ ማንኛውም ዓላማ የሌላን ሰው የኤሌክትሮኒክ ማንነት የሚያረጋግጥ ዳታ ያለባለቤቱ ፈቃድ በኮምፒዩተር ሥርዓት አማካኝነት ያመረተ፣ ያገኘ፣ የሸጠ፣ ይዞ የተገኘ ወይም ለሌላ ሰው ያስተላለፈ እንደሆነ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከብር 50,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

**<u>ንኡስ ክፍል ሦስት</u>**

**<u>ስለሕገወጥ የይዘት ዳታ</u>**

**12.<u>ለአካለ መጠን ባልደረሱ ልጆች ላይ የሚፈፀሙ ፀያፍ ወይም ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሆኑ ወንጀሎች</u>**

1. ማንኛውም ሰው፣

ሀ/ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ወሲባዊ ድርጊት በግልጽ ሲፈጽም የሚያሳይ፣ ወይም

ለ/ አዋቂ ሰው ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ መስሎ ወሲባዊ ድርጊት በግልጽ ሲፈፅም የሚያሳይ፣ ስዕላዊ መግለጫ፣ ፖስተር፣ ቪዲዮ ወይም ምስል የኮምፒዩተር ሥርዓትን በመጠቀም ሆነ ብሎ ያዘጋጀ፣ ያሰራጨ፣ ለሽያጭ ያቀረበ፣ ያከፋፈለ፣ ሌሎች እንዲያገኙት ያመቻቸ ወይም ያለ ፈቃድ ይዞ የተገኘ እንደሆነ ከሦስት ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

2. ማንኛውም ሰው ወሲባዊ ይዘት ያላቸውን ንግግሮችን፣ ስዕሎችን፣ የጽሁፍ መልእክቶችን ወይም ቪዲዮችን በኮምፒዩተር ሥርዓት አማካኝነት በማሰራጨት ወይም በመላክ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅን ለወሲባዊ ድርጊት ያነሳሳ ወይም የመለመለ እንደሆነ ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

13.<u>በሰዎች ነፃነትና ክብር ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች</u>

ማንኛውም ሰው ሆነ ብሎ፣

1. የኮምፒዩተር ሥርዓትን በመጠቀም በሚያሰራጨው ጽሁፍ፣ ንግግር፣ ቪዲዮ ወይም ስዕል አማካኝነት በሌላ ሰው ወይም በተጎጂው ቤተሰቦች ላይ ከባድ ጉዳት ወይም አደጋ ለማድረስ በማሰብ ያስፈራራ ወይም የዛተ እንደሆነ ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም እንደወንጀሉ ከባድነት ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል፤
2. ተጎጂውን ወይም ቤተሰቦቹን የሚመለከት መረጃ ወይም መልእክት በኮምፒዩተር ሥርዓት አማካኝነት በተደጋጋሚ በመላክ፣ በማሰራጨት ወይም የተበዳዩን የኮምፒዩተር ኮምዩኒኬሽን በመከታተል ፍርሃትን፣ ስጋትን ወይም የሥነ-ልቦና ጫናን የፈጠረ እንደሆነ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም እንደወንጀሉ ከባድነት ከአስር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል፤
3. የሌላን ሰው ክብር ወይም መልካም ስም የሚያጎድፍ ጽሁፍ፣ ንግግር፣ ስዕል ወይም ተንቀሳቃሽ ምስል በኮምፒዩተር ሥርዓት አማካኝነት ያሰራጨ እንደሆነ፣ የግል አቤቱታ ሲቀርብበት ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከብር 30,000 በማይበልጥ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

14.<u>በሕዝብ ደህንነት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች</u>

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ አንቀፅ 257 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም ሰው ሆነ ብሎ በህብረተሰቡ መካከል አመጽ፣ ሁከት ወይም ግጭት እንዲፈጠር የሚያነሳሳ ጽሁፍ፣ ተንቀሳቃሽ ምስል፣ ድምጽ ወይም ማንኛውንም ሌላ ምስል በኮምፒዩተር ሥርዓት አማካኝነት ያሰራጨ እንደሆነ ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

15.**<u>በኮምፒዩተር ስርዓት አማካኝነት ስለሚሰራጭ ማስታወቂያ</u>**

1. ማንኛውም ሰው ምርትን ወይም አገልግሎትን ለማስተዋወቅ ወይም ለሽያጭ ለማቅረብ ሆነ ብሎ የማስታወቂያ መልዕክቶችን ያለተቀባዩ ፈቃድ በኢሜይል ወይም መሰል የኮምፒዩተር አድራሻ አማካኝነት ያሰራጨ እንደሆነ ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር 30,000 በማይበልጥ መቀጮ ወይም ወንጀሉ ከባድ በሆነ ጊዜ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከብር 50,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም፡-

   ሀ/ ማስታወቂያው በዋናነት ደንበኞችን ከአዳዲስ ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ጋር ለማስተዋወቅ ያለመ ከሆነና ደንበኞቹ ፈቃደኛ ከሆኑ፣ ወይም

   ለ/ የላኪውን ትክክለኛ ማንነት፣ አድራሻ እና የመልእክቱ ተቀባይ ተመሳሳይነት ያላቸው መልእክቶችን በቀጣይነት ላለመቀበል የሚያስችል ቀላልና ትክክለኛ አማራጭ የያዘ ከሆነ በወንጀል አያስጠይቅም።

16.**<u>ስለአገልግሎት ሰጪዎች የወንጀል ተጠያቂነት</u>**

ማንኛውም አገልግሎት ሰጪ በሚያስተዳድረው የኮምፒዩተር ሥርዓት አማካኝነት ለተሰራጨ ማንኛውም የሦስተኛ ወገን ሕገወጥ የይዘት ዳታ በሚከተሉት ሁኔታዎች በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ 12 እስከ 14 በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፤

1. ሕገ-ወጥ የይዘት ዳታውን በማሰራጨት ወይም አርትኦት በማድረግ በቀጥታ የተሳተፈ ከሆነ፤
2. ሕገ-ወጥ የይዘት ዳታ መሆኑን እንዳወቀ ዳታውን ለማስወገድ ወይም ተደራሽ እንዳይሆን ለማድረግ ወዲያውኑ እርምጃ ያልወሰደ ከሆነ፤ ወይም
3. ሕገ-ወጥ የይዘት ዳታውን እንዲያስወግድ ወይም ተደራሽ እንዳይሆን እንዲያደርግ በሚመለከተው አካል ተነግሮት ተገቢ እርምጃ ሳይወስድ የቀረ እንደሆነ፡፡

**<u>ንኡስ ክፍል አራት</u>**

**<u>ስለሌሎች ወንጀሎች</u>**

17.**<u>የመተባበር ግዴታን ስለመጣስና የምርመራ ሂደትን ስለማደናቀፍ</u>**

ማንኛውም ሰው፡-

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 24(2)፣ አንቀፅ 25(6)፣ አንቀፅ 30(2)፣አንቀፅ 31(2) ወይም አንቀፅ 32(4) መሰረት የተጣለበትን የመተባበር ግዴታ ያልተወጣ እንደሆነ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከብር 10,000 በማይበልጥ በመቀጮ ይቀጣል፤
2. በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከናወን የኮምፒዩተር ወንጀል ምርመራ ሂደትን ሆነ ብሎ ያደናቀፈ እንደሆነ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከብር 50,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

**18.<u>በሌላ ሕግ ስለተደነገገ የወንጀል ድርጊት</u>**

በዚህ ክፍል ከተደነገጉት ወንጀሎች ውጭ ሌላ ወንጀል በኮምፒዩተር ሥርዓት አማካይነት የተፈጸመ እንደሆነ አግባብነት ያለው ሕግ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**19.<u>ተደራራቢ ወንጀሎች</u>**

በኮምፒዩተር ሥርዓት አማካይነት የሚፈፀም ማናቸውም ዓይነት ወንጀል በልዩ ሕጎች ወይም በወንጀል ሕግ የሚያስቀጣ ሌላ ወንጀል አስከትሎ እንደሆነ፤ ለዚሁ ወንጀል ተገቢነት ያለው ድንጋጌ በተደራቢነት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**20. <u>በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ላይ የሚጣል ቅጣት</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 90(1)፣ (3) እና (4) ላይ የተደነገገው ቢኖርም በዚህ ክፍል የተመለከተውን ወንጀል የፈፀመው በሕግ ሰውነት መብት በተሰጠው አካል ሲሆን፣

1. ለወንጀሉ የተጣለው ቅጣት መቀጮ ከሆነ መቀጮው ከብር 50,000 እስከ ብር 500,000 ይሆናል፡፡
2. ለወንጀሉ የተጣለው ቅጣት የእስራት ቅጣት ከሆነ የቅጣቱ መጠን፡-

   ሀ/ እስከ ሦስት ዓመት ቀላል እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል እስከ ብር 50,000፣

   ለ/ እስከ አምስት ዓመት ቀላል እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል እስከ ብር 100,000፣

   ሐ/ እስከ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል እስከ ብር 150,000፣

   መ/ እስከ አስር ዓመት ጽኑ እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል እስከ ብር 200,000፣

   ሠ/ ከአስር ዓመት በላይ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል ሲሆን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እስከተመለከተው ከፍተኛ መቀጮ መጠን ለመድረስ በሚችል፣ መቀጮ ይቀጣል፡፡

3. ለወንጀሉ የተጣለው ቅጣት መቀጮ ሆኖ መጠኑ በግልጽ ከተመላከተ መቀጮው አምስት እጥፍ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የመከላከልና የምርመራ ሂደቶች

**21.መርህ**

በዚህ ክፍል እና በክፍል አራት ስር የተደነገጉት ስነ ስርዓቶች፣ የምርመራ ሂደቶች እና የማስረጃ ድንጋጌዎች በህገ መንግስቱ እና አገሪቷ ተቀብላ ባፀደቀቻቸው ዓለምአቀፍ ስምምነቶች ጥበቃ ያገኙ ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ባረጋገጠ መልኩ ተፈፃሚ መሆን አለባቸው፡፡

**22.ጠቅላላ**

1. የኮምፒዩተር ወንጀልን የመከላከልና የምርመራ ሂደት በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሰረት ይከናወናል።
2. የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ ህግ በግልፅ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ የወንጀል ሕግ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የሕግ ድንጋጌዎች በኮምፒዩተር ወንጀሎች ላይም ተፈፃሚ ይሆናሉ።

**23.. የመመርመር ሥልጣን**

1. በዚህ አዋጅ የተደነገጉ ወንጀሎችን አቃቤ ሕግ እና ፖሊስ በጋራ የመመርመር ስልጣን አላቸው፤ አቃቤ ሕግም የምርመራ ሂደቱን ይመራል፡፡
2. ኤጀንሲው በኮምፒዩተር ወንጀል ምርመራ ሂደት ድጋፍ እንዲያደርግ ሲጠየቅ አስፈላጊውን ቴክኒካዊ ድጋፍ ይሰጣል፣ በምርመራ ሂደት የተገኙ መረጃዎችን ይተነትናል፤ እንዳስፈላጊነቱ ማስረጃዎችን ያቀርባል፡፡

**24.. የኮምፒዩተር ዳታን ይዞ ስለማቆየት**

1. በሌሎች ሕጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም አገልግሎት ሰጭ አካል በኮምዩኒኬሽን ሂደት ላይ ያለን የኮምፒዩተር ትራፊክ ዳታ ወይም ከዳታ ፕሮሰሲንግ አገልግሎት ጋር በተያያዘ የሚያገኛቸውን የትራፊክ ዳታዎች ቢያንስ ለአንድ ዓመት ይዞ ማቆየት ይኖርበታል፡፡
2. በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሰረት እንዲገለጥ ካልተወሰነ በስተቀር ዳታው በምስጢር መያዝ አለበት፡፡

## 25. <u>የኮምፒዩተር ዳታን ስለማሰባሰብ</u>

በሌሎች ሕጎች የተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣

1. የኮምፒዩተር ወንጀልን ለመከላከል እና ለምርመራ መነሻ የሚሆኑ መረጃዎችን ማሰባሰብ ተገቢ ሆኖ ሲገኝ የተጠርጣሪዎችን በኮምኒዩኬሽን ሂደት ላይ ያለን የኮምፒዩተር ዳታ፣ የዳታ ፕሮሰሲንግ አገልግሎት ወይም የኢንተርኔት እና ሌሎች መሰል ግንኙነቶችን እንዲጠለፍ ወይም ክትትል እንዲደረግበት መርማሪ አካል ለፍርድ ቤት ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱም ተገቢውን በመወሰን እንዳስፈላጊነቱ ጠለፋው ወይም ክትትል የሚደረግበት ሁኔታ እና ትዕዛዙን የሚያስፈፅመውን አካል ይወስናል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው በሌላ አኳኋን ዳታውን ማሰባሰብ የማይቻል ሲሆን እና ይኸው በጠቅላይ ዓቃቤ ህጉ ተቀባይነት አግኝቶ ሲወሰን ብቻ ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገገው ቢኖርም በቁልፍ መሰረተ ልማት ላይ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል የኮምፒዩተር ወንጀል ስለመፈፀሙ ወይም ሊፈፀም ስለመሆኑ በቂ ጥርጣሬ ሲኖር እና አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም ጠለፋው ወይም ክትትሉ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንዲከናወን ጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ ለመርማሪ አካል ሊፈቅድ ይችላል፡፡
4. ጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ለመጥለፍ ወይም ለመከታተል መነሻ የሆኑትን ምክንያቶች በ48 ሰዓት ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ማቅረብ አለበት፤ ፕሬዚዳንቱም ተገቢውን ትዕዛዝ ወዲያውኑ መስጠት ይኖርበታል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (4) መሠረት የሚገኝ ማንኛውም መረጃ ለጉዳዩ አግባብነት ከሌለው በጠቅላይ ዓቃቤ ህጉ ውሳኔ ወዲያውኑ መወገድ አለበት፡፡
6. ማንኛውም አገልግሎት ሰጭ አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገውን ለማካሄድ ሲጠየቅ አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ አለበት፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚሰበሰብ ማንኛውም መረጃ በምስጢር መያዝ አለበት፡፡

**26. <u>ኮምፒዩተርን፣ የኮምፒዩተር ሥርዓትን ወይም መሠረተ ልማቶችን ከአደጋ ስለመጠበቅ</u>**

1. የኮምፒዩተር ወንጀል ሊፈፀም እንደሚችል በቂ ጥርጣሬ ሲኖር እና ጥቃቱን ለመከላከልና ለመቆጣጠር፣ ዜጎችን አስቀድሞ ለማስጠንቀቅ፣ የምርመራ ሂደቱን ውጤታማ ለማድረግ ወይም የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ ኤጀንሲው ከመርማሪ አካላት ጋር በመተባበር እና ከፍርድ ቤት ፈቃድ በማውጣት የጥቃት ሰለባ ወይም መነሻ ሊሆኑ እንደሚችሉ በተጠረጠሩ ኮምፒውተሮች፣ የኮምፒዩተር ሥርዓቶች ወይም መሠረተ ልማቶች ላይ ድንገተኛ ፍተሻ ወይም የዲጂታል ፎረንሲክ ምርመራ ሊያካሂድ፣ ተስማሚ የሆነ የደህንነት መሳሪያ ወይም አገልግሎት ሊያቀርብ ወይም ሌላ መሰል ማንኛውንም እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡
2. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ተፈፃሚነት አስፈላጊ ከሆነ እና ጥያቄ ከቀረበ የሚመለከታቸው አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

**27. <u>ሪፖርት የማድረግ ግዴታ</u>**

1. ማንኛውም አገልግሎት ሰጪ አካል ወይም የመንግስት ተቋም በዚህ አዋጅ የተደነገጉት ወንጀሎች እየተፈጸሙ መሆኑን ያወቀ እንደሆነ ወይም በሚያስተዳድረው የኮምፒዩተር ሥርዓት አማካኝነት ማንኛውም የሦስተኛ ወገን ሕገ ወጥ የይዘት ዳታ እየተሰራጨ መሆኑን ከተረዳ ወዲያውኑ ለኤጀንሲው እና ወንጀሉን በተመለከተ ለፖሊስ ማሳወቅ እና አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡
2. ኤጀንሲው ሪፖርት የሚቀርብበትን ፎርም እና ሥርዓት በተመለከተ በመመሪያ ይወስናል፡፡

**28. <u>ስለመያዝና በእስር ስለማቆየት</u>**

በሌሎች ልዩ ሕጎች የተደነገጉት ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣

1. በዚህ አዋጅ የተመለከተ የኮምፒዩተር ወንጀል ለመፈጸሙ ወይም እየተፈፀመ ስለመሆኑ በቂ ጥርጣሬ ሲኖር በወንጀል ሕግ ሥነ-ሥርዓት በተደነገገው መሰረት ፖሊስ ተጠርጣሪዎችን ሊይዝ ይችላል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የተያዘ ሰው ምርመራ ያልተጠናቀቀ እንደሆነ በወንጀል ሕግ ሥነ-ሥርዓት በተደነገገው መሰረት ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል፤ ሆኖም በጠቅላላ የሚሰጠው ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ከአራት ወራት መብለጥ የለበትም፡፡

## ክፍል አራት
## የማስረጃና የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች

**29. ጠቅላላ**

1. የኮምፒዩተር ወንጀል የፍርድ ሂደትና የማስረጃ አሰባሰብ በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሰረት ይከናወናል።
2. የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የወንጀል ሕግ ጠቅላላ ክፍልና የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች በኮምፒዩተር ወንጀሎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

**30. የኮምፒዩተር ዳታ ደህንነት ለማስጠበቅ ስለሚሰጥ ትዕዛዝ**

1. መርማሪው አካል ለኮምፒዩተር ወንጀል ምርመራ ዓላማ አስፈላጊ የሆነን የተወሰነ የኮምፒዩተር ዳታ ሊጠፋ ወይም ሊቀየር እንደሚችል በበቂ ምክንያት ሲያምን ዳታውን የያዘ ወይም በቁጥጥር ሥር ያደረገ ሰው አስፈላጊውን የደህንነት ጥበቃ እንዲያደርግ በጽሁፍ ሊያዝ ይችላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት ትዕዛዝ የተሰጠው ሰው በጽሁፍ የተገለፀውን የኮምፒዩተር ዳታ ደህንነት ለመጠበቅ ወዲያውኑ አስፈላጊውን እርምጃ የመውሰድና ከሦስት ወራት ላልበለጠ ጊዜ ጠብቆ የማቆየት እንዲሁም የተሰጠውን ትዕዛዝ በምስጢር የመያዝ ግዴታ አለበት።
3. መርማሪው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው የጊዜ ገደብ ሲያበቃ ለተጨማሪ ሦስት ወራት ለአንድ ጊዜ ብቻ እንዲራዘም ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

**31. የኮምፒዩተር ዳታ ለማግኘት ስለሚሰጥ ትእዛዝ**

1. በማንኛውም ሰው ይዞታ ወይም ቁጥጥር ሥር ያለ የኮምፒዩተር ዳታ ለኮምፒዩተር ወንጀል ምርመራ አስፈላጊ መሆኑ በበቂ ምክንያት ሲታመን መርማሪው አካል የኮምፒዩተር ዳታውን ለማግኘት ወይም ለማየት ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል።
2. ፍርድ ቤቱ የቀረበውን ጥያቄ ካመነበት እና ጉዳዩ የሚመለከተውን ሰው መጥራት ካላስፈለገው ማንኛውም ሰው በእጁ የሚገኘውን የኮምፒዩተር ዳታ ለመርማሪው አካል እንዲሰጥ ወይም እንዲያሳይ ሊያዝ ይችላል።

32. <u>ስለደራሽነት፣ ብርበራ እና መያዝ</u>

1. ለኮምፒዩተር ወንጀል ምርመራ ዓላማ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መርማሪ አካል ከፍርድ ቤት ፈቃድ በማውጣት ማንኛውም የኮምፒዩተር ሥርዓት፣ ኔትዎርክ ወይም የኮምፒዩተር ዳታ ከርቀት ወይም በቦታው በአካል በመገኘት መበርበር ወይም ደራሽነት ማግኘት ይችላል።
2. መርማሪ አካል በብርበራ እንዲያዝ የተፈለገውን የኮምፒዩተር ዳታ የብርበራ ፈቃድ በወጣበት የኮምፒዩተር ሥርዓት አማካኝነት ሊገኝ በሚችል ሌላ የኮምፒዩተር ሥርዓት ውስጥ የተከማቸ መሆኑን በበቂ ምክንያት ሲያምን ድጋሚ የፍርድ ቤት ፈቃድ ሳይጠይቅ የብርበራ ሥራውን ማከናወን ወይም ደራሽነት ማግኘት ይችላል።
3. መርማሪ አካል በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) እና (2) መሰረት የብርበራ ሥራውን ሲያከናውን ከወንጀሉ ጋር ግንኙነት ያለውን፣

   ሀ/ ማንኛውም የኮምፒዩተር ሥርዓት ወይም ዳታ መያዝ፣

   ለ/ በብርበራ የተገኘውን የኮምፒዩተር ዳታ ኮፒ ወይም ፎቶ ግራፍ ማስቀረት፣

   ሐ/ ማንኛውም ቴክኖሎጂ በመጠቀም የዳታውን ደህንነት ማስጠበቅ፣

   መ/ብርበራ በተከናወነበት የኮምፒዩተር ሥርዓት ውስጥ የቀረውን ዳታ በምንም መልኩ ተደራሽ እንዳይሆን ማድረግ፣ ወይም

   ሠ/የጠፉ ዳታዎችን መልሶ ማግኘት፣ ይችላል።

4. መርማሪው አካል ብርበራ የሚከናወንበትን የኮምፒዩተር ሥርዓት አሰራርን ወይም የኮምፒዩተር ዳታ ደህንነት ለማስጠበቅ የተወሰዱ እርምጃዎችን በሥራው ምክንያት የሚያውቅ ማንኛውም ሰው የብርበራ ሥራውን ሊያግዝ የሚችል አስፈላጊውን መረጃ ወይም የኮምፒዩተር ዳታ እንዲሰጠው ሊያዝ ይችላል።
5. መርማሪ አካል ብርበራውን ሲያካሂድ ያገኛቸው ማናቸውም የኮምፒዩተር ሥርዓት አሰራር ወይም የኮምፒዩተር ዳታ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም ሌሎች ሕጎችን የሚፃረሩ መሆናቸውን ሲያምን የኮምፒዩተር ሥርዓቱ ወይም የኮምፒዩተር ዳታው ጥቅም ላይ እንዳይውል፣ እንዲታገድ ወይም በተወሰነ መልኩ እንዲገደብ ለፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንዲሰጥለት ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል፤ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩ በቀረበለት በ48 ሰዓት ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን ትዕዛዝ መስጠት አለበት፡፡
6. የሕግ ሰውነት ባላቸው አካላት ላይ በሚደረግ ብርበራ የተቋሙ ኃላፊ ወይም ተወካይ መገኘት አስፈላጊ ከሆነ መርማሪው ተገቢውን መፈፀም አለበት፡፡

## 33. ተቀባይነት ስለሚኖራቸው ማስረጃዎች

1. በዚህ አዋጅ መሰረት የተያዘን የኮምፒዩተር ዳታ የሚመለከት ሰነድ፣ የሰነዱ የተረጋገጠ ግልባጭ ወይም የተረጋገጠ የኤሌክትሮኒክስ መዝገብ ወይም ህትመት በፍርድ ቤት ለቀረበው የክስ ጉዳይ በማስረጃነት ሊቀርብ ይችላል፤ ተቀባይነትም ይኖረዋል፡፡
2. በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሰረት የሚቀርቡ ማስረጃዎች ተቀባይነት እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

   ሀ/ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት መንገዶች የተሰበሰቡ ማስረጃዎች፣ ወይም

   ለ/ ከውጭ ሀገር አግባብ ባላቸው የሕግ አስከባሪ አካላት የኢትዮጵያ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት የተገኙ ዲጂታል ወይም ኤሌክትሮኒክ ማስረጃዎች የኮምፒዩተር ወንጀሎችን ጉዳይ ለማስረዳት በፍርድ ቤት ተቀባይነት ይኖራቸዋል።

## 34. ትክክለኛነትን ስለማረጋገጥ

በሌሎች ሕጎች የሰነድ ማስረጃ ስለሚረጋገጥበት ሁኔታ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 33 የተመለከቱ ማስረጃዎችን ለፍርድ ቤት በማስረጃነት የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው የማስረጃዎቹን ተአማኒነት እና ትክክለኛነት የማስረዳት ኃላፊነት አለበት፡፡

## 35. ስለዋና የኤሌክትሮኒክ ሰነድ

1. አስተማማኝነቱ በተረጋገጠ የኤሌክትሮኒክ ዳታ የተመዘገበበት ወይም የተከማቸበት ሥርዓትን ተከትሎ የተገኘ የኤሌክትሮኒክ መዝገብ የኤሌክትሮኒክ ዋና ሰነድ ይሆናል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በተከታታይ ሲሠራበት በቆየ አስተማማኝነት ባለው ዳታን ሲያከማች ወይም ሲመዘግብ በቆየ ሥርዓት በመጠቀም ወደ ወረቀት ጽሑፍ የተቀየረ ወረቀት የኤሌክትሮኒክ ዋና ማስረጃ ይሆናል፡፡
3. የኤሌክትሮኒክ መዝገብ ሥርዓትን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ባልተቻለ ጊዜ፣

   ሀ/ ኮምፒውተሩ ወይም መሣሪያው በተግባር ሲሠራ መቆየቱን፣ ብልሽት ያጋጠመው ቢሆንም የኮምፒውተሩን አስተማማኝነት የማያጓድለው መሆኑን፤

ለ/ የኤሌክትሮኒክ መዝገቡ እንዲመዘገብ የተደረገው ማስረጃውን ለማቅረብ ከሚፈልገው ወገን በተቃራኒ ባለው ሌላኛው ተከራካሪ ወገን መሆኑን፣ ወይም

ሐ/ የኤሌክትሮኒክ መዝገቡ እንዲመዘገብ ወይም እንዲከማች ያደረገው ሰው ማስረጃውን ለማቅረብ በሚፈልገው ሰው ቁጥጥር ሥር ያለመሆኑና ምዝገባው ወይም ክምችቱ የተለመደውን ሥራ ተከትሎ የተፈፀመ መሆኑን፣ የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል፡፡

36. **<u>ስለፍርድ ቤት ግምት</u>**

ፍርድ ቤቱ በዚህ አዋጅ መሠረት የኤሌክትሮኒክ ሰነድ ተቀባይነትን ለመወሰን ተመሳሳይ ኮምፒዩተር ሥራውን የሚያከናውንበትን ሥነ-ሥርዓት፣ ደረጃ እና አሠራር ግምት ውስጥ ማስገባት ይችላል፡፡

37. **<u>የማስረዳት ሸክም</u>**

1. ዐቃቤ ሕግ ባቀረበው ክስ ላይ የተመለከተ ፍሬ ነገርን የማስረዳት እና በሕግ በተቀመጠው መመዘኛ መሠረት የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም አቃቤ ህግ መሠረታዊ ፍሬ ነገሮችን ካስረዳ እና ፍርድ ቤት የማስረዳት ኃላፊነቱን ወደ ተከሳሹ ማዞር አስፈላጊ መሆኑን ካመነ የማስረዳት ሸክም ወደ ተከሳሽ ሊዞር ይችላል፡፡

**<u>ክፍል አምስት</u>**

**<u>የኮምፒዩተር ወንጀል ጉዳዮችን የሚከታተሉ ተቋማት</u>**

38. **<u>የኮምፒዩተር ወንጀል የሚከታተል አቃቤ ሕግና ፖሊስ</u>**

1. በሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የኮምፒዩተር ወንጀልን የሚከታተል አቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን የመፈፀምና የማስፈፀም ኃላፊነት አለበት፡፡
2. በዚህ አዋጅ ሥልጣን የተሰጠው የአቃቤ ሕግ እና ፖሊስ የኮምፒዩተር ወንጀልን የሚከታተል ልዩ የስራ ክፍል እንደአስፈላጊነቱ ሊያደራጁ ይችላሉ፡፡

39. **<u>ስለኤጀንሲው ኃላፊነት</u>**

ኤጀንሲው በቀጥታ የኮምፒዩተር ሥርዓት አማካኝነት የኮምፒዩተር ወንጀል ምርመራ የሚካሄድበትን ዘዴዎች እና ሌሎች አስፈላጊ የምርመራ ቴክኖሎጂዎችን የማቅረብ ኃላፊነት አለበት፡፡

**40.** **<u>የኮምፒዩተር ወንጀል የዳኝነት ሥልጣን</u>**

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ አዋጅ በተደነገጉ ወንጀሎች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡
2. የዳኝነት ሥልጣንን የተመለከቱ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 13 እና አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ለ) ድንጋጌዎች የኮምፒዩተር ወንጀልንም ያካትታሉ፡፡

**41.** **<u>አስፈፃሚ ግብረ-ኃይል ስለማቋቋም</u>**

1. በሌላ ሕግ ለኤጀንሲው የተሰጠው ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ኦፐሬሽንን በበላይነት የመምራትና የማስተባበር ሥልጣኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የኮምፒዩተር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ፣ የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን አካላት ኃላፊዎችን ያቀፈ ብሔራዊ አስፈፃሚ ግብረ-ኃይል ይዋቀራል፡፡
2. የጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ አስፈፃሚ ግብረ ኃይሉን ያስተባብራል፤ በግብረ ኃይሉ ሊሳተፉ የሚገባቸውን አግባብነት ያላቸው ሌሎች ተቋማትን ይለያል፤ ውክልና እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡
3. አስፈፃሚ ግብረ ኃይሉ የኮምፒዩተር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የጋራ አገራዊ ምክክሮች እንዲኖሩ ያደርጋል፣ በየጊዜው በሚያጋጥሙ አደጋዎች ላይ ምክረ-ሐሳብ ያቀርባል፣ በየተቋማቱ ሊሰሩ የሚገቡ ጉዳዮችን በመለየት የአጭር እና የረጅም ጊዜ እቅዶችን ይነድፋል፣ እንዲሁም ልዩ ልዩ አካላትን በማስተባበር የተቀናጀ አሰራር እንዲኖር ያደርጋል፡፡

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**42.** **<u>ዓለም አቀፍ ትብብር</u>**

1. ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ መረጃ መለዋወጥን፣ በጋራ የምርመራ ሥራ ማከናወንን፣ ወንጀለኛ አሳልፎ መስጠትን እና ሌሎችን ጨምሮ የኮምፒዩተር ወንጀልን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ከሌላ ሀገር አግባብ ያለው ባለሥልጣን ጋር በዚህ አዋጅ፣ ኢትዮጵያ ተዋዋይ ወገን በሆነችበት ስምምነት እና የኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት በሚፈቅደው መሠረት በትብብር ይሰራል ወይም ስምምነት ሊፈራረም ይችላል።

2. ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል መርማሪ አካል ተመሳሳይ ተልዕኮ ካለው የሌላ ሀገር መሰል ተቋም ጋር የመረጃ ልውውጥን፣ በሌላ መልኩ የጋራ ትብብርን ሊያደርግ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ስምምነት ሊፈራረም ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ መሰረት የተገኘ ማንኛውም መረጃ ወይም ማስረጃ የኮምፒዩተር ወንጀልን ለመከላከል ወይም ለመመርመር ዓላማ ይውላል፡፡

43. <u>የኮምፒዩተር ሥርዓትን ወይም ንብረትን ስለማገድ፣ ስለመውረስ ወይም ስለመዝጋት</u>

1. ፍርድ ቤት በዚህ አዋጅ መሰረት በጥፋተኛ ላይ ቅጣት ሲወስን ወንጀሉን ለመፈፀም ጥቅም ላይ የዋለ ማንኛውም የኮምፒዩተር ሥርዓት፣ ዳታ ወይም መሳሪያ በመንግስት እንዲታገድ፣ እንዲወረስ፣ እንዲወገድ ወይም የዳታ ፕሮሰሲንግ አገልግሎቱ እንዲዘጋ በተጨማሪነት ሊያዝ ይችላል።
2. ተከሳሹ በመጨረሻ ውሳኔ መሰረት ጥፋተኝነቱ ከተረጋገጠ ጥፋተኝነቱ በተረጋገጠበት ወንጀል ሥራ በቀጥታ መንገድ ያገኘው ንብረት ወይም ሐብት ይወረሳል፡፡
3. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም ሲባል አግባብ ያላቸው ሌሎች ህጎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

44.<u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልግ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ኤጀንሲው ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልግ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

45. <u>ስለተሻሩና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>

1. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 706 እስከ አንቀጽ 711 የተመለከቱት ድንጋጌዎች እና የቴሌኮም ማጭበርበር ወንጀል አዋጅ ቁጥር 761/2004 አንቀጽ 5 በዚህ አዋጅ ተሽረዋል።
2. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማናቸውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሰራር ልማድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት የለውም፡፡

46. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ 30 ቀን 2008 ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**